
የፓፒዮ ቀጣይ የህይወት ጉዞ

# ባንኮ ፓፒዮን

እውነተኛ ታሪክ



ትርጉም

ናትናኤል ጌታቸው እና ናርዶስ ዓለማየሁ

# ባንኮ

## ፓፒሎን

የሄነሪ ሻሪዬ ቀጣይ የህይወት ጉዞ

ተርጓሚዎች

ናትናኤል ጌታቸው እና ናርዶስ ዓለማየሁ

# መታሰቢያነቱ

የሄንሪ ሻሪየን የመጀመርያውን ክፍል የያዘውን መፅሀፍ 'ፓፒዮ' በሚል ርዕስ ተርጉመው ለአንባቢያን እንዲደርስ ካደረጉት ለአቶ ጌታቸው ጉብሬ ይሁንልን:: ምንም እንኳን ቀጣዩን የሄንሪን በውጣ ውረድ የተሞላ የህይወት ጉዞ ተርጉመው ሙሉ ታሪኩን ለህዝብ የማድረስ ጉጉት እና እቅድ ቢኖራቸውም ሰው እንዳሰበው ኖሮ አያውቅምና ህልማቸውን ከግብ ሳያደርሱ ሞት ሊነጥቀን ችሏል:: እኛም እሳቸው በከፈቱልን በር ተራምደን ይህንን ትልቅ ስም እና ዝናን ያተረፈውን መፅሀፍ ቀጣይ እና የመጨረሻውን ክፍል ተርጉመን ለአንባቢ እናደርስ መታሰቢያነቱ የሚገባውን ክብር እና ስም ሳያገኙ ካለፈው አቶ ጌታቸው ጉብሬ እንዲሆንልን እናስብ ከተርጓሚው ያለን ክብር እና ፍቅር ከፍ ያለ መሆኑን በመግለፅም ጭምር ነው:: ፈጣሪ ነፍሱን በአፀደ ገነት ያኑርልን!!

# ልዩ ምስጋና

**በማይመረመር ጥበቡ ስንወድቅ እያነሳ ስናነክስ እያቃና የጅማሬያችንን ፍፃሜ እንድናይ ከፈቀደልን ከኃያሉ አምላክ ክብር እና ምስጋና ይግባው ! !**

## ምስጋና

አቅማችሁ የፈቀደውን በማድረግ እንዲሁም በፀሎት ይህ ስራ ተጀምሮ እስኪፈፀም ድረስ ከጎናችን ከነበሩት ከአሀታችን የምስራች ጌታቸው እና ከወንድማችን ከዶ/ር ናታኒም ባለማየሁ፣ ከአቶ ጌታቸው አሰፋ ወጀቡ፣ ከወ/ሮ ብርቄ በቀለ፣ ከመምህር ባለማየሁ አካለ፣ ከወ/ሮ ገነት ኃይለማርያም እና ከሀብታሙ ጌታቸው ላቅ ያለ ምስጋና ይድረስልን።

# ማውጫ

ምዕራፍ አንድ ....................................................................................................9

ለነፃነት የመጀመሪያ እርምጃ ....................................................................................9

ምዕራፍ ሁለት ..................................................................................................32

የማዕድን ማውጫው ..............................................................................................32

ምዕራፍ ሦስት ..................................................................................................54

ጆጆ ላ ፔሴ ......................................................................................................54

ምዕራፍ አራት ..................................................................................................90

ወደ ኢል ሴሎ መመለስ ........................................................................................90

ምዕራፍ አምስት ................................................................................................99

ካራካስ .........................................................................................................99

ምዕራፍ ስድስት ................................................................................................112

ከባንኩ ስር ያለው ዋሻ .........................................................................................112

ምዕራፍ ሰባት ..................................................................................................127

ካሮቴ እና አራጣ አበዳሪው ......................................................................................127

ምዕራፍ ስምንት ................................................................................................145

ቦምቡ ...........................................................................................................145

ምዕራፍ ዘጠኝ ..................................................................................................160

ማራካይቦ በህንዶች መሀከል ....................................................................................160

ምዕራፍ አስር ...................................................................................................181

ሪታ የቬራ ክሩዟ ................................................................................................181

ምዕራፍ አስራ አንድ ....................................................................................20

አባቴ ....................................................................................20

ምዕራፍ አስራ ሁለት ....................................................................................21

ቬንዙዌላዊ መሆን ....................................................................................21

ምዕራፍ አስራ ሶስት ....................................................................................21

ወደ ስፔን ጉዞ ....................................................................................23

ምዕራፍ አስራ አራት ....................................................................................240

ነውጡ ....................................................................................240

ምዕራፍ አስራ አምስት ....................................................................................247

ካማሩንስ ....................................................................................247

ምዕራፍ አስራ ስድስት ....................................................................................254

ጎሬላዎቹ ....................................................................................254

ምዕራፍ አስራ ሰባት ....................................................................................265

ምንትማርትሪ ....................................................................................265

# መግቢያ

ሄነሪ ሻሪየ በህይወት ያሳለፈውን ውጣ ውረድ የመጀመሪያውን ክፍል እንዲወደድ እና ለትውልድ እንዲሸጋገር በማድረግ ደራሲ 'ጌታቸው ገብሬ' በሚደንቅ ሁኔታ ተርጉመው 'ፓፒዮ' በሚል ርዕስ ለህዝብ እንዲደርስ አድርገውታል፡፡ እኛም የሄነሪን ቀጣዩን የህይወት ጉዞ የያዘውን ይህን መፅሀፍ ተርጉመን ለአንባቢ እንድናበቃ የ'ፓፒዮ' ተርጓሚ አቶ ጌታቸው ያበረከቱት አስተዋፅዖ ላቅ ያለ ነው፡፡

'ፓፒዮ' በሚል ርዕስ ወደ አማርኛ የተተረጎመው የሄነሪን ታሪክ የመጀመሪያውን ክፍል የያዘው መፅሀፉ በወህኒ ቤቶች ያሳለፈውን አሰቃቂ ጊዜያቶች እና ለማምለጥ ሲል የሚገባባቸውን ውጥመዶች በአፋት እየዳሰሰ ነፃነቱን እስከተጎናፀፈበት ጊዜ ድረስ ያለውን ታሪኩን አስቀምጧል፤ ይሄኛው መፅሀፉ ደግሞ ከፍርድ ግዞት በኋላ ለአኖረው ህይወት እና ሀሳቡን ለማሳካት ሲል ለአከናወናቸው ነገሮች እያለፈን የታሪኩን መደምደሚያ ይሰጠናል፡፡

የሄነሪ ሻሪየ የህይወት ታሪክ ማንም ሰው በውስጡ ይዞት የሚኖረው ቁልፍ የእድሜ ልክ ህመም እንደሚሆን ትልቅ ማሳያ ነው፤ ከእነዚም በተጨማሪ በአካም ላይ ለንኖር ከሚያጋጥሙን መሰናክሎች ሁሉ መልስ እንዳለው እሱ ያከፈላቸው መንገዶች በቂ ምላሾች እንደሆኑ በመፅሀፉ አሳይቶናል፡፡ ሄነሪ ባከፈላቸው የህይወት መንገዶች ሁሉ እልህ አስጨራሽ ተጋድሎዎችን በድል እየተወጣ የሚያጋጥሙትን ተስፋ አስጨራሽ ፈተናዎች ድባቅ እየመታ የኖረ ሰው ነው፡፡ ይህ ሰው ባልፈፀመው ወንጀል እስራ አራት ዓመታት አሰቃቂ በሚባል ሁኔታ ውስጥ በወህኒ ቤት ህይወቱን እንዲገፋ የተፈረደ ሰው ነው፡፡ ሄነሪ ከብዙ የማምለጥ ሙከራ በኋላ ተሳክቶለት ነፃነቱን ካረጋገጠ በኋላ አእምሮው ሌት ተቀን የሚያስበው ስለ አንድ ነገር ብቻ ነው . . . በቀል ! ! የሄነሪ ሻሪየ አብዛኛውን እድሜውን ያሳለፈው እሱ ለቀመሰው ስቃይ እና እንግልት ምክንያት የሆኑትን የሀሰት ፈራጆችን እንዴት? . . . መቼ? እና የት ቦታ እንደሚቀጣቸው በማሰብ ነው፡፡ ውስጡን እንደለመጥ እሳት የሚያቃጥለው ነገር ቢኖር በሀሰት መስክረው እና አስመስክረው በሰው ልጅ ላይ ሊደርስ የማይገባ በደል እንዲፈፀምበት ምክንያት የሆኑትን ሰዎች ሲያስብ ነው፤ ከእነሱ ደግሞ እራሱ ያስቀመጣቸውን ፍርድ መስጠት ይፈልጋል፡፡ ሄነሪ ይህን የበቀል እቅዱን ለማሳካት ሲል የማይቆፍረው ጉድጓድ ስለሌለ እጅጉን ፀጉርን እንደ ቀንድ በሚያቆሙ እና ልብን ቀጥ በሚያደርጉ ጀብዱዎች የተሞላ ነው፡፡

የእዚህ ሰው ታሪክ በአለም ዙርያ ከመታወቁ እና ከመወደዱ የተነሳ በተለያዩ ሀገራት ቋንቋ ተተርጉሞ ለአንባቢያን ደርሷል። 'ባንኮ' የተሰኘው የሄንሪ ቀጣይ የህይወት ታሪክ ከፈረንሳይኛ ወደ እንግሊዘኛ በ 'ፓትሪክ ኦ ብሬን' አማካኝነት ተተርጉሟል። ከዛ በተጨማሪ በ1973 ዓ.ም አሜሪካን ሀገር የሚገኘው ሆሊውድ የፊልም ድርጅት በእሱ ታሪክ ላይ ተመስርቶ ፓፒሎን በሚል ርዕስ ፊልም ሰርቶበት ለእይታ አብቅቶታል፤ እንደገና ደግሞ ተሻሽሎ በ2018ዓ.ም በድጋሚ ተሰርቶ ለእይታ ቀርቧል።

ይህ በአለም ዙርያ የናኘው የሄንሪ የህይወት ታሪክ ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ እንዲደርስ ከተርጓሚው በተጨማሪ ፋና ብሮድካስት ኮርፖሬሽን የአየር ሰዓት በመስጠት እንዲሁም አርቲስት ሽመልስ አበራ እና አርቲስት ባዩሽ ከበደ በመተረክ ለአድማጮች እንዲደርስ ጉልህ ሚና ተጫውተዋል። እኛም ለእነዚህ አካላት ድርጅቶቹንም ሆነ ግለሰቦቹን ሳናመሰግን አናልፍም።

እኛም ባንኮ ወይም ፓፒሎን በሚል ርዕስ የተፃፈውን የሄንሪን ቀጣይ የህይወት ታሪክ እዳሉን እግንተን፤ ተርጉመን ለአንባብያን ለማድረስ ከ አንድ አመት በላይ ጊዜያችንን ሰውተንበታል። ይህም ከመፅሀፉ ዋና ባለታሪክ ሄንሪ ሻሪየ እና የመጀመሪያውን ታሪኩን ተርጉሞ ለእኛ በር ከከፈተልን ጌታቸው ገብሬ ያለን አክብሮት ከፍተኛ እንደሆነ ማሳያ ነው።

በመጨረሻም አንባብያን እንዲረዱልን የምፈልገው ነገር በመፅሀፉ ውስጥ የተጠቀምናቸው የሰው የአካባቢ እና የምግብ ስሞች ከቀላል እንፃር በጥቂቱ ሊዛነፉ ስለሚችሉ መደናገር ውስጥ እንዳይከቷችሁ በአክብሮት እንገልፃለን። ከእዚህም ሌላ የአንድን ሀገር አኗኗር ዘይቤ፣ ባህል፣ ልማድ እና ወግ ወደ እራስ አምጥቶ ለአንባቢ እንዲሆን አድርጎ አዋዝቶ መፃፍ በጣም ከባድ ነው፤ እኛም ወደ አማርኛ ተርጉመን ለናቀርበው መጨመር ያሉብንን ጨምረን ከሁላችን ቋንቋ ጋር እንዲጣጣም አድርገን ነው። በመፅሐፉ ውስጥ የተጠቀምናቸው ዓመት ምህረቶች በሙሉ በአውሮፓውያን አቆጣጠር መሆኑን ልንጠቁም እንወዳለን።

መፅሀፍ የህይወት ስንቅ ነው እና ይህን መፅሀፍ መርጣችሁ ለምታነቡ አንባብያን መልካም የተመላ ጊዜን ተመኘን!!

ተርጓሚዎቹ

ናትናኤል ጌታቸው እና ናርዶስ ዓለማየሁ

# ምዕራፍ አንድ

## ለነፃነት የመጀመሪያ እርምጃ

"በመንገድህ ሁሉ ቀና ነገር ይግጠምህ አንተ የፈረንሳይ ሰው... .ከዚች ሰዓት ጀምሮ ነፃ ሰው ነህ... ሰላም ሁን" አለ የኢልዶራዶው የፖሊሶች መኮንን በፈገግታ ከታጀብ ሰላምታ ጋር እጁን እየዘረጋልኝ... እኔም ለመልካም ምኞቱ አፀፋውን መልሼ መንገዴን ቀጠልኩ።

ጥቂት እነደተራመድኩ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የኢል ዶራዶን እስር ቤት ለማየት ስዞር የፖሊሶቹ አዛዥ እጁን እያውለበለበ በድጋሚ ሲሰናበተኝ ተመለከትኩ።

እንግዲህ እነዚያ ሲያንገላቱኝ የነበሩት ካቴናዎች ከእጀም ከአዕምሮዬም የተወገዱልኝ ከአስራ አራት አመታት የምጥና የሰቆቃ ጊዜ በኋላ መሆኑ ነው። በእጆቼ ፒኮሊኖን እንደያዝኩ ከእኛ ፊት ለፊት የሚገኘውን ወንዝ ተከትለን ወደ ኢል ዶራዶ መንደር በሚያስኬደው መንገድ እየተጓዝን ነበር።

ዛሬ ላይ ወቅቱ ነሀሴ 18 ቀን1971 ነው። ባረጀው የስፓኒሽ ቤቴ ውስጥ እንደተቀመጥኩ በሀሳብ የኋሊት ተጉዤ ያሳለፍኩትን ውጥንቅጡ የወጣ ህይወት ሳስብ አሁን የተከናወነ ይመስል በአእምሮዬ ጥርት ብሎ ይታየኛል።

እኩለ ለሊት ነው፤ ውጪው ጨልሟል፤ ጨረቃም በቦታዋ የለችም። ለኔ... ለኔ ግን ፀሀይዋ የእውነት ብርሀኑዋን ይዛልኝ እየወጣች ነበር። ጠዋት ሁለት ሰዓት ላይ የፖሊሶቹን አዛዥ ጀርባ እያፈጠጥኩበት ነበር። ከአጠገቤ እየራቀ ቢሄድም ያ ሁሉ መሽሎክለክ፣ በሚስጥር ማውራቱ፣ ረሀቡ፣ ብቸኝነቱ... ለአስራ አራት አመት ቀን ከለሊት ለደቂቃዎች፣ ለሰከንዶች ስፀልይለት የነበረው ነፃነቴ መደምደሚያ ማግኘቱ ታወሰኝ።

ለመጨሻ ግዜም ከሰው ተገልዬ መከራና ስቃይ ያሳለፍኩባቸውን እነዚያን እስር ቤቶች ለመመልከት ፊቴን አዙሬ ደሴቷን አየሁ።

እንደነገሩ የፒኮሊኖን እጅ እንደያዝኩ በኔ መሪነት ጉዞ ጀመርን። "ግን ወዴት? የት መሄድ እንዳለብን እስካሁን አልወሰንኩም። ጥቂት እንደተጓዝንም ቢሄዱት የሚጨረስ የማይመስል ኮረብታማ ቦታ አጋጠመን። ኃይል ለመቆጠብም እርምጃችንን በጣም ከመቀነሳችን የተነሳ ቆመናል በሚያስብል ደረጃ ያንን ኮረብታማ ዳገት መውጣት ጀመርን። ከጎኔ ፒኮሊኖ በረጅሙ ሲተነፍስ ስለሰማሁት ወደሱ ዞሬ ተመለከትኩት። እሱም ድካም በተሞላበት ስሜት ፈገግ አለ። እኔም በረጅሙ አየር ከሳብኩ በኋላ ቀስ ብዬ ለቀቅሁት፤ ሳስበው እነዚያን የመጀመሪያ የነፃነት ደቂቃዎች ያባከንኩዋቸው መስሎ ስለተሰማኝ የሳብኩትን አየር እንኳን ስለቀው ዘና፣ እረጋ ብዬ ነበር።

ከፍታውን እንደጨረስንም ጥቂት እረፍት ካደረግን በኋላ ያለንበትን ቦታ መቃኘት ጀመርኩ፤ ሁሉም ነገር በግልፅ ይታይ ነበር። በስተግራም በስተቀኝም በኩል ለአይን የሚማርኩና ንፁህ ቤቶች ይታያሉ፤ የቤቶቹም ዙሪያ በሚያማምሩ አበቦች ያሸበረቀ ነው። የቀረንን ጉልበት አሟጠን በመጓዝ ወደ መንደሩ መቅረብ ቻልን፤ መንደሩ አካባቢም የተወሰኑ ህፃናት እየተጫወቱ አገኘን። በእርግጥ ከየት እንደመጣን ቢያውቁም የመደንገጥም ሆነ የፍርሀት ምልክት አይታይባቸውም ነበር። እንደውም ጨዋታቸውን ትተው እኛ ወዳለንበት ቦታ በመምጣት አይን አይናችንን ማየት ጀመሩ። ስለ የዋህነታቸው አይናቸውን ብቻ አይቶ መናገር ይቻል ነበር። "ምነው አለማደግ ቢኖር" ብዬ ተመኘው። ያልደማ፣ ያልቆሰለ ልብ ያለው እነሱ ጋር ብቻ ነው። ታዲያ በእነዚህ ህፃናት እንደተከበብን ወደ ቤቶቹ ማዝገማችንን ቀጠልን።

ወደ መንደሩ በሚያስገባው ቅያስ ላይ አንዲት ጥቁርና ወፍራም ሴትዮ ከእንጨት በተሰራ ጠረጴዛ ላይ ቡና እና የበቆሎ ቂጣ በቅቤ እየሸጠች ስለተመለከትን ወደእሷ ሄድን።

"እንዴት አደርሽ እህት"

"Buenas dias hombras"

"ሁለት ቡና እባክሽ"

"Si senores"

ወፍራሟ ፍጥረትም ግሩም የሆነ ቡና ሰጠችን፤ የደከመ ሰውነታችንን ለማሳረፍ ብንፈልግም ምንም አይነት ወንበር በቅርብ ባለመኖሩ የተሰጠንን ቡና ቆመን ለመጠጣት ተገደድን። ቡናውን ጠጥተን እንደጨረስንም ሂሳብ

ለመክፈልም እጄን ወደ ኪሴ ስከት "አይ ምንም አያስፈልግም" አለችኝ ያንን ችምችም ያሉ ጥርሶቹዋን እያሳየችኝ

"እንዴ ለምን?"

"እንደውም ለነፃነታችሁ የመጀመሪያውን ቡና ስለሰጧችሁ ደስታው የኔ ነው"

"ኦ… በጣም እናመሰግናለን… ኧ… እኔ ምልሽ ምነው መኪኖችን አላየሁም?" አልኳት በአካባቢው ምንም አይነት መኪና ባለማየቴ

"ዛሬ እሁድ ስለሆነ ብዙዎቹ መኪኖች እረፍት ያረጋሉ… ወደ አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ ግን አንድ ገልባጭ መኪና ስለሚመጣ በሱ መሄድ ትችላላቹ" አለችኝ፡፡

እኔም ላደረገችልን ነገር ሁሉ ምስጋናዬን በመገለፅ ላይ እንዳለሁ ከፊታችን ያለው ቤት በር ተከፍቶ፤ አንዲት ነጣ ያለ የቆዳ ቀለም እንዲሁም ጥቋቁር አይኖች ያሉዋት ልጅ  ከቤቱ ወጥታ "ኑ ግቡ" አለች በሚያምር ፈገግታ፡፡

እኛም ግብዣዋን ተቀብለን ተከትለናት ወደ ውስጥ ዘለቅን፡፡ ቤቱ ከደርዘን በለይ በሆኑ ሰዎች ተሞልቷል፡፡ ሁሉም በየጎራቸው ሩም እየጠጡ ጨዋታ ይዘዋል፡፡ እኔም በአይኔ እየማተርኩ ባዶ ቦታ መፈለግ ጀመርኩ፤ ወደ ግርግዳው ጠርዝ አካባቢም ክፍት ቦታ ስላገኘሁ ፒኮን ይዤ ወደዚያው ሄድኩ፡፡

"ጓደኛህ ምን ሆኖ ነው ምላሱን ወደ ውጪ የጎለጎለው?" አለችኝ

"አሞታል" አጠር ያለ መልስ መለስኩላት

"የምንረዳው ነገር ይኖር ይሆን?"

"አይ የለም… ግማሽ አካሉ ፓራላይዝ ሆኖ ነው… ወደ ሆስፒታል መሄድ ይኖርበታል"

"ማነው የሚመግበው?"

"እኔ"

"ወንድምህ ነው?"

"አይደለም… ጓደኛዬ ነው"

"ብር ይዘሃል ፈረንሳዊው?"

"በጣም ትንሽ... ግን እንዴት ፈረንሳዊ መሆኔን አወቅሽ?"

"እዚህ አዲስ ነገር ወዲያው ነው የሚሰማው... ትላንት እንደምትለቀቁ እና አንተም ከሰይጣን ደሴት በማምለጥህ ምክንያት እነዚያ የፈረንሳይ ፖሊሶች መልሰው ማሰር እንደሚፈልጉ ሁሉ እናውቃለን... እዚህ ግን ምንም የሚያስጋ ነገር የለም... እኛ ሀገር ላይ ምንም አይነት ትዕዛዝ መስጠት እስካልቻሉ ድረስ የሚያሳስብህ ነገር አይኖርም... ይልቁንስ እኛ ነን እናንተን የመንከባከብ ኃላፊነት ያለብን"

"ለምን?"

"ምክንያቱም..." ብላ አቋረጠች

"እንዴ ምን ማለትሽ ነው?... ጨርሽው እንጂ"

"እንካ ሩም ጠጣ... ለጓደኛህም ስጠው" ብላኝ የጀመረችውን ወሬ ሳትጨርስ እዛው የተቀመጥንበት ቦታ ጥላን ሄደች፡፡ ጥቂት ቆይቶም አንድ እድሜዋ ወደ ሠላሳዎቹ የሚጠጋ ጠቆር የምትል ሌላ ሴት አጠገባችን መጥታ ከተቀመጠች በኋላ ጨዋታ ጀመርን፡፡ ስለአንዳንድ ነገር ካወራን በኋላም ትዳር ያለኝ መሆኑን ጠየቀችኝ

"የለኝም"

"ቤተሰቦችህስ በህይወት አሉ?"

"አባቴ ብቻ"

"ቬንዙዌላ መሆንህን ሲሰማ መቼስ ይደሰታል"

"በሚገባ"

ከእሷ ጋር እንዲህ ያሉ ቃላት እየተለዋወጥን ባለንበት ሰዓት አንድ ረዥም፣ ቀጭን፣ ትላልቅና ማፈጠጥ የሚወዱ አይኖች ያሉት፣ ፈካ ያለ የቆዳ ቀለም የተላበሰ ሰው እኛ ከተቀመጥንበት አጠገብ ካለው ወንበር ላይ ከተቀመጠ በኋላ በቀጥታ ወደኛ ዞሮ

"ይቅርታ ቅድም በወሬያችሁ መሀል ጣልቃ መግባት ስላልፈለኩ ነው… ቅድም ሴትየዋ እናንተን የመንከባከብ ድርሻ የእኛ ነው ስትል ምን ማለቷ መሰለህ… የሰው ልጅ ሆኖ ማንም ካልተናደደ ወይም ከአእምሮ በላይ የሆነ ችግር ካልገጠመው በስተቀር ወንጀል ለመስራት አይገደድም… እናም ደግሞ ሰው ሆነን ላጠፋነው ጥፋት ሰው የሆነ ሁሉ ይቅርታ ሊያደርግልህ ይገባል… ማንም ሰው የሚረዳው ካገኘ ወደ መልካም ባህሪ የማይመለስበት ምክንያት የለም… ታዲያ ቅድም እናንተን የመንከባከብ ኃላፊነት አለብን ያለችው ከእዚህ አስተሳሰብ በመነሳት ነው" አለኝ… ንግግሩ የእሱን ቅንነት ብቻ ሳይሆን በዙሪያው ያሉትን ሰዎችን ጭምር የሚገልፅ ነበር። እኔም ባዋራው የማጣው ነገር እንደሌለ ስለገባኝ ጨዋታዬን በጥያቄ ጀምርኩ።

"በሰይጣን ደሴት ለምን የታሰርኩ ይመስልሃል?"

"እ… በጣም አደገኛ ወንጀል ስለፈፀምክ ይመስለኛል… ወይ ሰው ገድለሃል አልያም ከባድ የዘረፋ ወንጀል ፈፅመሀል… ለመሆኑ ስንት ዓመት ፈረዱብህ?"

"እድሜ ልክ"

"እዚህ ከመጣህስ በኂላ ስንት ዓመት ፈረዱብህ?… ለነገሩ እዚህ ረጅሙ ፍርድ ሠላሣ ዓመት ነው"

"በጠቅላላው አስራ አራት ዓመት ታስሬያለሁ… ነገር ግን አሁን ነፃ ሰው ነኝ"

"ደስ ይላል!!… አሁን እንግዲህ ሁሉንም ነገር መርሳት አለብህ… ዛሬ አንተ አዲስ ሰው ነህ… ስለዚህ በአዲስ ማንነት አንተነትህን መገንባት ይኖርብሀል… በተቻለህ አቅም እዚህም ሆነ ፈረንሳይ በህይወትህ ውስጥ ያጋጠመህን ማንኛውንም መከራን መርሳት አለብህ… ምክንያቱም ስለስቃይህ ብዙ ባሰብክ ቁጥር ከአንተ አልፎ የሌላው ሰው ህመም ሊሰማህ ይቻላል… በዛ ላይ የልብ ቁስል ጥላቻን ይፈጥራል… ስለዚህ ብቸኛው መፍትሄ መርሳት ነው… መርሳትህ ባለፈው ታሪክህ እንዳትታሰር ከማድረጉም በላይ ለምታቅደው አዲስ ህይወት እንደ መጀመሪያ እርምጃ በመሆን ያግዝሀል… ከእሱ በተጨማሪ ደግሞ ቶሎ ለማግባት ሞክር… የእዚህ ሀገር ሴቶች ደግሞ የፍቅር ሰዎች ናቸው" ካለ በኂላ ፈገግ አለ… እኔም ለፈገግታው አፀፋ ፈገግታዬን ቸርኩት… ቀጠለናም" ስለዚህ በቶሎ ደስታህን ይመልሱልሀል፤ ልጅም ይወልዱልሀል… ይህ ማለት ደግሞ በስቃይና በመከራ ያጣኸውን ደስታ በልጆችህ ታገኘዋለህ ማለት ነው… እመነኝ ከነገርኩህ ነገር ውስጥ ስህተት የምታወጣለት አይመስለኝም" አለኝ ሩም የያዘውን ብርጭቆ ወደ አፉ እየላከ

እኔም በአዎንታ ራሴን ነቅንቄ በሀሳቡ መስማማቴን ከገለፅኩ በኋላ ለለገሰኝ ምክር የሚገባውን ምስጋና ቸርኩት፡፡ ብዙም ሳይቆይ የተባለው ገልባጭ መኪና ስለመጣ እነዛን ደግ እና ሩህሩህ ሰዎች ላደረጉልን ነገር ከልብ አመስግኜ የፒኮሊኖን እጅ እንደያዝኩ ወደ መኪናው ሄድን፡፡ መኪናው ገልባጭ እንደ መሆኑ መጠን ከኋላው ለመቀመጫ የሚሆን ከእንጨት የተሰራ ረዥም መቀመጫ ተዘጋጅቶለት ነበር፡፡ በውስጡም ወደ አስር የሚጠጉ ሰዎች አግዳሚው ወንበር ላይ ተቀምጠዋል፡፡ እኔና ፒኮም መኪናው ጋር ከደረስን በኋላ ከሹፌሩ አጠገብ ያለውን ምርጥ ቦታ ስለለቀቁልን ተዝናንትን ጉዞችንን ጀመርን፡፡

እየተንዝን ባለበት ሰዓት አእምሮዬ የሚያሰላስለው ከኋላ ስለተቀምጡት ቬንዙዌላውያን ነበር፡፡ ከመካከላቸው የተወሰኑት የፓሪያ ባህረ ሰላጤ አሳ አጥማጆች ሲሆኑ የቀሩት ደግሞ የኢል ዶራዶ ወታደሮች እና የቀን ሰራተኞች ነበሩ፡፡ ለእኔ ግርምትን የፈጠረብኝ ነገር ቢኖር በዚህ መኪና ውስጥ ያሉት ብቻ ሳይሆን በመንደሯ ውስጥ የሚኖሩትም ሰዎች ሁሉም በሚያስብል ደረጃ የተማረ የሚገኝበት አይመስለኝም፤ ታዲያ ያ ሁሉ ለጋስነትና ትህትና ከየት መጣ?... መቼም ይሔን የጨዋነት ባህሪ ከአውሮፓውያን እንደማይወርሱት እርግጠኛ ነኝ፡፡ ምን አልባት ከህንዶች ሲሆን ይችላል፡፡ ለነገሩ ሁሉም ሰው እንደተፈጠረበት ማህበረሰብ ይዞት የሚያድገው የእራሱ መልካም ጎን አለው፡፡ የእነዚህ ቬንዙዌላውያን ባህሪ ግን የተለየ መሰሎ ታየኝ፡፡

ከጥቂት የጉዞ ሰአታት በኋላም ኢል ሴሎ ስለደረስን ለሹፌሩ ያለብንን የጉዞ ሂሳብ ለመክፈል ኪሶቼን ስደባብስ አንዲት መልከ መልካም ሴት ወደኛ መጥታ “ሂሳብ እንዳትከፍሉ” አለችን ሹፌሩም ለሀገሩ አዲስ መሆናችንን ስላወቀ ምንም ሳይል ሰላምታ ሰጥቶን ጉዞውን ቀጠለ፡፡

ወቅቱ ሐምሌ 5 ነበር፡፡ ብሔራዊ ባህላቸውን የሚያከብሩበት ቀን ስለነበር አካባቢው በሙዚቃ ቀውጢ ሆኗል፡፡ በጎዳናው ላይ በተለያየ ህብረ ቀለማት ያሸበረቀ ልብስ የለበሱ ሰዎች ደምቀው ይታያሉ፡፡ በአንድ እጄ ትንሿን ጥቅል ሻንጣዬን በሌላኛው እጄ ደግሞ ሦስት ጣት ብቻ የቀሩትን የፒኮሊኖን እጅ እንደያዝኩ ወዴት መሄድ እንዳለብኝ ቆሜ እያሰብኩ ነበር፤ በእርግጥ እጄ ላይ ጥቂት ቦሊቫርስ ነበረኝ (ቦሊቫርስ -የቬንዙዌላውያን የመገበያያ ገንዘብ ሲሆን የቬንዙዌላ አንድ ቦሊቫር የአሜሪካን አንድ አራተኛ ዶላር ነበር)... ከዛ በተጨማሪ ደግሞ እስር ቤት በነበርኩበት ሰዓት ከቲማቲም እርሻው ያገኘኋቸው ጥቂት አልማዞች ነበሩኝ፡፡

በዚህ ሃሳብ ውስጥ እንዳለሁ ከመኪናው ስንወርድ ብር እንዳትከፍሉ ያለችን ልጅ ስደናበር ስላየችኝ ነው መሰለኝ ወዴት መሄድ እንደፈለግን ጠየቀችን፡፡

የውስጤን ፍላጎቴን ስላወቀችልኝ እየተደሰትኩ ፈጠን ብዬ አነስ ያለች ማረፊያ ቤት እንደምንፈልግ ነገርኳት፡፡

"መጀመሪያ እኔ ወደምኖርበት ቦታ እንሂድ… ከዛ ለማረፊያ የሚሆን ቦታ እንፈልጋለን" አለችኝ… በሀሳቧም ተስማምቼ በእሷ መሪነት ወደ መኖሪያ ቤቷ ጉዞ ጀመርን፡፡ ሁለት መቶ ሜትር ያክል በዋናው መንገድ ከሄድን በኋላ ወደቀኝ ታጥፈን ወደ ሰፈራቸው የሚወስደውን ንጣፍ መንገድ ይዘን መራመዱን ተያያዝነው፡፡ አካባቢው ላይ ያሉ ቤቶች እምብዛም ለአይን የሚማርኩ አይደሉም፤ ሁሉም ቤቶች በሚያስብል ሁኔታ የተሰሩት ከሸክላ ጡብ ሲሆን ጣሪያቸው ደግሞ ከቆርቆሮ የተሰራ ነበር፡፡

ትንሽ ከተራመድን በኋላ አንዱ ቤት ጋር ስንደርስ ቆምን፡፡ ታዲያ እቺ በቅጡ አስራ ስምንት አመት ያልሞላት ልጅም በሩን እየከፈተች "ግቡ" በማለት እኛን አስቀድማ እሷ ተከተለች፡፡ በክፍሉ ውስጥ አንድ ክብ ጠረጴዛ እና የተወሰኑ ወንበሮች ነበሩ፡፡ በአንደኛው ወንበር ላይ በግምት እድሜው ወደ አርባዎቹ የሚጠጋ መካከለኛ ቁመት ያለው፣ የአይኖቹ አቀማመጥ እና የፀጉሩ አለሳለስ የህንዶቹን የሚመስል፣ የቀይ ዳማ የቆዳ ቀለም ያለው ሰው ተቀምጧል፡፡ አጠገቡ ደግሞ የ አስራ አራት፣ የአስራ አምስት እና የአስራ ስድስት አመት ሴት ልጆች በዙሪያው ከበውት ተቀምጠዋል፡፡

ይዛን የመጣችው ልጅ ወደእነሱ ዞራ" አባቴና እህቶቼ እነዚህ ሰዎች ከኢል ዶራዶ እስር ቤት የመጡ ናቸው… ወጼት መሔድ እንዳለባቸው ስለማያወቁ ነው ወደእዚህ ይዣቸው የመጣሁት… ስለዚህ በደንብ ተንከባከቧቸው እሺ" አለች

"እንኳን ደህና መጣችሁ" አለ አባትየው ጎርነን ባለ ድምፅ… "ይሔ ቤት የእናንተም ነው… ስለዚህ ውስጣችሁን ነፃ አድርጉት… እባካቹ ቁጭ በሉ… ምን ይምጣላቹ?… ቡና?… ወይስ… ሩም?"

እምቢ ማለት ስለከበደኝ ብቻ "ቡና" አልኩ… ቤቱ ውስጥ ያሉት እቃዎች ለድህነታቸው ምስክርነት የተቀመጡ ነው የሚመስሉት

"ማሪያ የሁሉም ታላቅ ነች" አለ አባትየው መጀመሪያ ወደ ቤቱ ይዛን ወደመጣችው ልጅ እየተመለከቱ፡፡ በረጅሙ ከተነፈሱ በኋላም" እናታቸው ከአንድ መዓድን ቆፋሪ ሰውዬ ጋር ኮብልላ ከጠፋች ይኸው አምስተኛ አመቷ ሊደፍን ነው… ይሔን የነገርኩህ ከሌላ ሰው ከመስማትህ በፊት እኔው ላሳውቅህ ብዬ ነው" አለኝ

ማሪያ ቡና ከቀዳችልን በኋላ ከእኔ ፊትለፊት ስለተቀመጠች በደንብ ለማየት ችያለሁ። እህቶቿም ከእሷ አጠገብ ተቀምጠው ልክ ማርያ አተኩሬ እንደምታየኝ ሁሉ እነሱም አፍጥጠው እየተመለከቱኝ ነበር። ማሪያ የለውዝ ፍሬ ቅርፅ ያላቸው ትላልቅና ጥቋቁር አይኖች ያላት ልጅ ስትሆን ጥቅልል ብሎ ትከሻዋ ላይ የተዘረጋው ፀጉሯ ደግሞ ሌላ ውበት ጨምሮላታል። የዳሌዎቿ ስፋት እንኳን አፍላ ጎረምሳ ይቅርና በከዘራ የሚራመድ ሽማግሌን እንኳ የማሳሳት አቅም ነበራቸው፤ በአጠቃላይ መልከ መልካምና የምትመስጥ ልጅ ነች። የቆዳዋ ቀለም እንደሚያሳየው የህንዶችን ደም እንደወረሰች ይመስክራል። ስሜት የሚያነቃቁ ውብ ከንፈሮቿ እና ስክትክት ብለው የተሰሩት ጥርሶቿ ደግሞ ሌላ የውበቷ ድምቀቶች ናቸው። ነጭ በአበባ ያቀጠቀጠ ሸሚዝ ለብሳለች፤ የሸሚዟ ሁለት ቁልፎች በመከፈታቸው የጡት መያዣዋ እና የተወሰነው የጡቷ ክፍል ይታያል። ከታች ደግሞ ወይን ጠጅማ ጉርድ ቀሚስ እና አጭር ተረከዝ ያለው ጫማ አድርጋለች። ማሪያም ልክ እንደ በዓሉ ደምቃለች ቢባል ማጋነን አይሆንም።

"እቺ ኢዝመራልድ ትባላለች" አለች ማሪያ ታናሽ እህቷን እያስተዋወቀችኝ "በእነዚህ አረንጓዴ አይኖቿ ምክንያት ነው ኢዝመራልድ የተባለችው... እቺ ደገሞ ኮነቺታ... ኧ... እሷ ድግሞ የመጨረሻዋ ሮዚታ ትባላለች... ሮዚታ የተባለችው የቆዳ ከለሯ ልክ እንደሮዝ አበባ ፈካ ስላለ ነው... አሁን እንግዲህ ቤተሰቦቼን ተዋወቀሃል... የአባቴ ስም ደግሞ ጆዜ ይባላል... ያንተስ ስም ማን ይባላል?"

"ኤኒሪክ... ሄነሪ በስፓኒሽኛ ኤኒሪክ ይባላል" አልኳት

"የጓደኛህስ?" አለች... ይመስለኛል እኔን የጠየቀችኝ ማውራት እንደማይችል ስላስተዋለች ነበር

"ፔኮሊኖ"

"ምን ሆኖ ነው እንዲህ የሆነው?"

"ግማሽ አካሉ ፓራላይዝ ሆኗል"

"ውይ ሲያሳዝን. . . ግን አታስብ እሺ እኛ እንንከባከበዋለን... በእስር ስንት አመት ቆየህ?"

"አስራ አራት አመት"

"ምስኪን ተሰቃይተኃላ" ፊቷ ላይ ከልብ የመነጨ ሀዘን ይነበብ ነበር

"አዎ ብዙ ዋጋ አስከፍሎኛል" አልኳት ያሳለፍኩት መከራ ትውስ ብሎኝ

ወዲያው ፊቷ ወደ አባቷ አዙራ" አባ... ኢኒሪክ እዚህ ምን ቢሰራ ይሻላል ትላለህ?"

"እኔ እንጃ... ንግድ ትችላለህ?"

"አልችልም"

"ጥሩ እንግዲያውስ ወርቅ ወደሚያወጡ ድርጅቶች መሄድ ይኖርብሃል... እነሱ ጋር ስራ አይጠፋም" አለኝ

"አንተስ ጆዜ ምንድነው ምትሰራው?"

"እኔ ምንም አልሰራም" አለኝ... ወዲያው ወሬ ለመቀየር ይመስል" የወርቅ አውጪዎቹ ትንሽ ነው ግን የሚከፍሉት" በማለት መጀመሪያ ወደተነሳው ርዕስ ለወጠው... ደሃ መሆናቸው ግልፅ ቢሆንም የለበሱት ልብስ ግን ንፁህና ያማረ መሆኑን ተመልክቼአለሁ። አባታቸው ገንዘብ ከየት እንደሚያመጣ ለመጠየቅ እምበዛም ፍላጎቱ የለኝም። ምናልባት ገንዘብ ለማግኘት ከመስራት ይልቅ መስረቅን አማራጭ ያደረገ ሰው ሊሆን ይችላል። "ምን አጣደፈህ በቅርቡ ሁሉንም ትመለከት የለ" አልኩት ለራሴ።

"ኢኒሪክ" አለችኝ ማሪያ

"አቤት"

"እንግዲህ ለዛሬ እዚህ ታድራላችሁ... የአባቴ ውንድም ሲመጣ የሚያድርበት ክፍል አለ... አሁን እሱ ስለሌለ ክፍሉ ውስጥ እናንተ ማደር ትችላላቹ"

ከደግነታቸው ብዛት ምን ማለት እንዳለብኝ ሁላ አላወቁም፤ ማሪያ ትንሿን ቦርሳዬን እንደያዘች እህቶቿን አስከትላ ለእኛ ወደተዘጋጀልን ክፍል ከገቡ በኋላ የተለያዩ የሴት አልባሳትን ከክፍሉ ይዘው ሲወጡ ስለተመለከትኩ፤ ከዚህ በፊት ክፍሉን ይጠቀሙበት እንደነበር መገመት አላዳገተኝም። ነገር ግን ቤተሰቡ የእኛን መሳቀቅ ማየት ስላልፈለጉ ክፍሉ የአባታቸው ወንድም ማረፍያ እንደነበር ነግረው ሸነገሉን። ክፍሉን አፅድተው ከጨረሱ በኋላም ማረፍ እንደምንችል ስለነገሩን ከፒኮ ጋር ተያይዘን ወደ ክፍሉ ገባን። ክፍሉ ውስጥ አልጋ ባይኖርም ከአልጋ የተሻለ ከሱፍ ጨርቅ የተሰራ ተንጠልጣይ አልጋ

በጥግ በኩል ተሰቅሎ ይታያል። ከአልጋው ፊት ለፊት ያለው አንድ ትልቅ መስታወት አልባ ተንሸራታች መስኮት ደግሞ ከቤቱ ጎሮ የበቀሉትን ለአይን የሚማርኩ የሙዝ ከባዎችን እና አትክልቶችን ያሳያል።

በተንጠልጣይ አልጋዬ ላይ ጋደም ብዬ ስለ ነፃነት የህይወት ጉዞዬ ማሰብ ጀመርኩ። በእርግጥ ጅማሮው በጣም ቀላል ይመስላል፤ በዛ ላይ የፒኮሊኖም ጉዳይ አሁን ላይ ብዙም አያሳስበኝም፤ምክንያቱም እነዚያ አራቱ ቆነጃጅት እንደሚንከባከቡልኝ ቃላቸውን ሰተውኛል። ግራ የገባኝ ነገር ቢኖር ነፃ ሰው እስከሆንኩ ድረስ የፈለኩት ቦታ መሄድ ስችል ለምን በእዚህ ቤተሰብ ቁጥጥር ስር ለመዋል እንደፈለኩ ነው። በእርግጥ አይፈረድብኝም አንዲት ለረጅም ጊዜ በጎጆ ውስጥ የታሰረችን ወፍ ድንገት በሩን ከፍተን ብረሪ ብንላት ላትበር ትችላለች።የኔም ከእዚህ የተለየ አይደለም አዲስ ህይወት ለመምራት ሁሉንም ነገር መለማመድ ይኖርብኛል። ብዙ በማሰብ ሰውነቴ ስለዛለ ሁሉንም ትቼ እንቅልፍ እንዲወስደኝ በጀርባዬ ተንጋለልኩ።ጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ ለመግባት የፈጀብኝ አስር ደቂቃ ነው፤ የነፃነቴ የመጀመርያዋ ለሊት ከማርም በላይ ጣፋጭ ነበረች

ጠዋት ከእንቅልፌ እንደነቃሁ እጅና ፊቴን እንደነገሩ በውሃ አባብሼ ለቁርስ ተቀመጥኩ። ሁለት የተጠበሱ እንቁላሎች፣ ዳቦ እና ቅቤ ከተለያዩ ፍራፍሬዎች ጋር ወሰድኩ። ማሪያ የሚቀጥለው ክፍል ውስጥ ፒኮሊኖን እያጣጠበችው ነው። በእዚህ መሃል የቤቱ በር ስለተንኳኳ የሪታ እህት ወደበሩ ሄዳ ከፈተች።ውጪ የቆመው ሰውዬ ከጎኑ ገጀራ የታጠቀ ሲሆን ድምፁን ከፍ አድርጎም

“Gente de paz” አለ... “ሰላም ለሁሉም”... በሰላም መምጣታቸውን የሚገልፁበት ቃል ነው

“ምንድን ነው የፈለከው?” አለ ጆዜ

“ዋና አስተዳደሩ ከእስር የተፈቱትን ሰዎች ማየት ይፈልጋል”

“ስም አላቸው እኮ ታዲያ... በስማቸው ጥራቸው እንጂ”

“እሺ ጆዜ... ማነው ስማቸው?”

“አሱኛው ኢንሪክ... ሌላኛው ደግሞ ፒኮሊኖ”

"እሺ... ልጅ ኢንሪክ ከእኔ ጋር እንሂድ እኔ ፖሊስ ነኝ... ከዋናው መስተዳድር ነው የተላኩት"

"ምንድን ነው ከእሱ ምትፈልጉት?" አለች ማሪያ ድንገት ከመኝታ ቤት እየወጣች

"ዋና አስተዳደሩ ፈልገዋቸው ነው" አለ ጆዜ የተፈጠረውን ለማስረዳት

"ቆይ እሺ አንዴ ጠብቁኝ ልብሴን ለባብሼ አብሬያችሁ እሔዳለሁ"

ማሪያ በትንሽ ደቂቃ ውስጥ ተዘገጃጅታ ጨረሰች፤ ልክ ከቤት እንደወጣን ማሪያ እጆቼን ያዘቻቸው:: በስስት አይን ትኩር ብዬ አየኋት:: ስትስቅ ጉንጮቿ ስርጉድ ይላሉ፤ የአይኗ አከፋፈት ልብን ከውስጥ ሰርቀው የሚያወጡ ይመስላሉ:: ወደ ዋና አስተዳደሩ ስንደርስ ስፈራው ላይ ብዙ ፖሊሶች እንዳሉ ተመለከትን:: ሁሉም ልክ ይዞን እንደመጣው ተራ ፖሊስ የደምብ ልብስ ለብሰው ነው የሚታዩት:: አንድ ጥይት ያነገበ ፖሊስ ወደኛ መጥቶ "አንተ ፈረንሳዊው ነህ አይደል?" አለኝ

"አዎ" አልኩት ቆፍጠን ብዬ

"የት አለ ሌላኛው?"

"አሞታል" ማሪያ ነበረች

ፖሊሱ እጁን ለሰላምታ እየዘረጋልኝ... "እኔ የፖሎሶች አዛዥ ነኝ... አልፎንሶ እባላለሁ ማንኛውም እርዳታ ካስፈለጋችሁ መጠየቅ ትችላላችሁ"

"ኢኒሪክ እባላለሁ" አልኩት የዘረጋልኝን እጅ እየጨበጥኩ

"ዋና አስተዳደሩ ሊያይዋችሁ ይፈልጋሉ... ኧ... አንቺ መምጣት አትችይም" አለ ማሪያ አብራኝ ለመሄድ እግሮቿን ስታነሳ ስላየ... ማሪያን እዛው ጥለናት ከፖሊስ አዛዡ ጋር ወደ ሚቀጥለው ክፍል አመራን... .ወደ ክፍሉ ስንገባ አንድ ረዘም ያለ ሰውዬ

"እንዴት አደርክ ፈረንሳዊው" አለኝ የሚያምሩ ጥርሶቹን እያሳየኝ... "ኧ... እኔ የአስተዳደሩ ዋና አዛዥ ነኝ... እንግዲህ ኢል ሴሎ እስከኖርክ ድረስ እኔ ያንተ ሙሉ ሀላፊነት አለብኝ... ለዛም ነው ያስጠራሁህ" አለኝ

ከዛም ብዙ ነገር አወራን፤ ምን መስራት እንደምፈልግ፣ የት መስራት እንደምፈልግ ሁላ ጠየቀኝ:: በመጨረሻም ማንኛውም የምፈልገው እና መጠየቅ ያለብኝ ነገር ካለ ምን ግዜም ቢሆን በሩ ክፍት መሆኑን ነገረኝ፤ እኔም ለመልካም ትብብሩ ከልብ አመስግኜ ልወጣ ስል "አንድ ነገር ይቀረኛል" አለኝ.. እኔም የሚለውን ለመስማት ዝም ብዬ ቆሜ ማዳመጥ ጀመርኩ... "አሁን እየኖርክ ያለኸው ከአስተዋይና ከሀቀኛ ሴቶች ጋር ነው... አባታቸው ጆዜ ግን የባህር ላይ ወንበዴ መሆኑን ስነግርህ እንድትጠነቀቅም ጭምር እያሳሰብኩህ ነው" አለኝ... ከዛም መሄድ እነደምችል ነግሮኝ አሰናበተኝ፤ እኔም እንደገና አመስግኜ ውጪ ወደምትጠብቀኝ ማሪያ ሄድኩ፤ ከማሪያ ጋር እጅ ለእጅ እነደተያያዝን ወደቤት በመሄድ ላይ እንዳለን

"አስተዳደሩ ካንተ ምንድነው የሚፈልጉት?" አለችኝ ፍቅር በሞላበት ቃና

"ምንም... ነገር ግን የሚያስፈልገኝ ነገር ካለ ልጠይቀው እንደምችል ነው የገለፀልኝ"

"ኢኒሪክ ከእዚህ በኋላ የማንንም እርዳታ አያስፈልግህም... ጓደኛህንም ቢሆን ለመንከባከቡ እኛ አለን" ንግግሯ እኔ ላንተ አላንስም አይነት ነው

"አመሰግናለሁ ማሪያ" ብዬ እጆቹዋን ጭምቅ አድርጌ ጨበጥኳቸው

በአጠገባችን ሱቅ በደረቴ የያዙ ልጆች እያለፉ ነበር፤ ሁሉም የሴቶች የጆሮ ጌጥ፣ የእጅ አምባር እና የአንገት ሀብል የያዙ ናቸው:: ወደ አንደኛው ሻጭ ጋር ይዣት ከሄድኩ በኋላ አንድ የአንገት ሀብል እና ከእሱ ጋር የሚሄድ የሚያምር የጆሮ ጌጥ ገዛሁላት:: ለሦስቱ እህቶቿ ደግሞ እንደየእድሜአቸው የሚያማምሩ ጌጣ ጌጦችን ገዛንላቸው:: ለሁሉም ጌጣጌጦች ወደ ሠላሳ ቦሊቫርስ ከፈልኩ:: ማሪያ የገዛሁላትን ሀብልና የጆሮ ጌጥ ወድያው ነበር ያደረገችው፤ ከደስታዋ ብዛት ልክ የሆነ ነገር እነደተሰጠው ህፃን ልጅ ስትፈነድቅ ማየቱ በራሱ ያዝናናል:: እኔንም ካደረኩት እና ከሚገባኝ በላይ አመሰገነችኝ:: ቤትም በእህቶቿ ላይ ያየሁት ደስታ ማሪያ ላይ ካየሁት ደስታ የሚበልጥ እንጂ የሚያንስ አልነበርም:: እኔ ግን ከእራሴ ጋር መሆን ስለፈለኩ እነርሱን እዛው ትቻቸው ወደ ክፍሌ ገባሁ:: ተንጠልጣይ አልጋዬ ላይ ጋደም ብዬ ስለእዚህ ምርጥ ቤተሰብ ማሰብ ጀመርኩ:: በእርግጥ እንግዳ ተቀባይ መሆናቸውን አሳይተውናል:: "እኔም ተቀብዬው ዝም ብዬ ልኑር?" የሚል ጥያቄ ውስጤ ፈጠረብኝ:: ለነገሩ ከአልማዞቹ ውጪ ትንሽ የተረፈ ገንዘብ አለኝ፤ ይህም ማለት አራት ወር እና ከዚያ በላይ ያለ ሀሳብ ያኖረኛል:: ከእዛ በላይ ደግሞ እነዚያ ምስኪን ሴቶች ስለ ፒኮሊኖን እንዳልጨነቅ ይረዱኛል::

እውነት ለመናገር ሁሉም ሴቶች ተወዳጅ ናቸው:: ልክ እንደ ሀሩር አበባ ሙቀት አመንጪዎች፣ አስጎምጂዎች ናቸው:: ደግሞ ለመቅረብ የሚከብድ ባህሪ የላቸውም:: ማሪያ አራሱ የዛሬ አስተያየቷ ልክ በፍቅር ክንፍ እንዳለች አይነት ሴት ነበር:: "እውነት ይህንን የወሲብ ስሜቴን መቆጣጠር አለብኝ" እራሴን ሞገትኩ... "አዎ እሱ ነው የሚሻለኝ አለበለዚያ ሌላ ችግር ይገኙ መምጣቴ ነው" ለእራሴ መለስኩለት::

በእዚህን ግዜ እድሜዬ ሠላሳ ዘጠኝ ነበር፤ ነገር ግን ገና የሠላሳዎቹ ጀማሪ ነበር የምመስለው:: በሌላ በኩል ማሪያ ገና አስራ ስምንት እንኳን የሞላት አይመስለኝም:: እህቶቿ ደግሞ ከእሷ በታች ናቸው:: ስለዚህ ነገር ከመበላሸቱ በፊት አንድ መላ መፍጠር እንዳለብኝ ተረድቻለሁ:: አሪፍ አማራጭ የሚሆነው ፒኮሊኖን እነርሱ ጋር እንዲቆይ ካደረጉ በኋላ እኔ በውጪ ሆኜ እየሰራሁ ፒኮሊኖን መርዳት ነው::

እንግዲህ ለብቻዬ እየተብሰለሰልኩ ጥቂት ደቂቃዎች አሳለፍኩና ከጆዜ ጋር የማውራት ሀሳብ ስለመጣልኝ ከተኛሁበት ተንጠልጣይ አልጋዬ ላይ ወርጄ ጆዜ ወዳለበት ክፍል አመራሁ::

"ጌታዬ ጆዜ... እምትችል ከሆነ ወደውጪ ወጣ ብለን ሩም እየጠጣን ለብቻችን ብናወራ ምን ይመስልሃል?" አልኩት... "እሺ" ብሎ ሳያቅማማ ከመቀመጫው በመነሳት እጆቹን ትከሻዬ ላይ ጭኖ "ከእዚህ በኋላ ደግመህ ጌታዬ ብለህ እንዳትጠራኝ... ጆዜ በቂ ነው" ካለ በኋላ ወደ ማሪያ ዞሮ "ማሪያ ወደ ካፌ ወጥተን ትንሽ ዘና ብለን እንመለሳለን" አላት... እሷም ቀበል አድርጋ "ኢኒሪክ ቲሸርትህን ቀይረው ቆሽሿል" ስላለችኝ ቲሸርት ለመቀየር ወደ ክፍሌ ስገባ ማሪያም ተከትላኝ ገባች... "አታምሹ እሺ.. .ከዛ በላይ ደግሞ ብዙ እንዳጠጡ" ብላኝ ከክፍሉ ከመውጣቴ በፊት ጉንጬ ላይ ሳም አድርጋኝ ወጣች... ሁኔታዋን ሲከታተል የነበረው ጆዜም ከት ብሎ እየሳቀ "አይ ማሪያ ካንተ ፍቅር ሳይዛት አልቀረም" ብሎኝ ሳቁን ሳያቋርጥ ተያይዘን ወደ ውጪ ወጣን:: ወደ ካፌው በመውረድ ላይ ሳለን በቀጥታ ለምን ወደ ጉዳዩ አልገባም ብዬ ወሬ ጀመርኩ::

"እንግዲህ ጆዜ አንተ ወንድ ነህ... ስለዚህ ከአንተ ቤተሰቦች መካከል ስኖር ከልጆችህ መሀል ከአንዷ ልጅህ ፍቅር ሊይዘኝ እንደሚችል አይገባህም ብዬ አላስብም... በዛ ላይ የእኔ እድሜ የትልቋን ልጅህን እድሜ እጥፍ ይሆናል... ከሱ በተጨማሪ ፈረንሳይ እያለሁ ትዳር ነበረኝ... ስለዚህ ጆዜ የእኔ በእናንተ ቤት መቆየት ችግር ይዞ ሊመጣ ስለሚችል አንተ የምታውቀውን እርካሽ የምትለውን ማደሪያ አሳየኝና ልከፈል... እዛ ማደር ነው ፍላጎቴ" ወሬዬን እንደጨረስኩ ካረጋገጠ በኋላ ትንሽ ፋታ ወስደና ጉሮሮውን ጠራርጎ እንዲህ አለኝ

"ፈረንሳዊው እውነት አንተ ትልቅ ሰው ነህ" ቀጥታ አይኔን እያየ ንግግሩን ቀጠለ... "ለእንደኔ አይነት ድሃ አሁን የተናገርካቸው ቃላቶች እጅግ ድንቅ እና ትልቅ ትርጉም ያለው ንግግር ነው... ታውቃለህ?... እዚህ ሀገር ላይ ጋብቻ የሚባል ነገር በአጠቃላይ የለም ማለት ይቻላል... አንዱ ከአንዱ ጋር ከተዋደደ በቃ አንሶላ መጋፈፍ ነው... .ምን አልባት ልጅ ከተፈጠረ ቤት ሰርቶ አብሮ መኖር ሊመጣ ይችላል... የእዚህ ሀገር ሙቀት ደግሞ እንደምታየው ከፍተኛ ነው... ስለዚህ ሴቶች ቶሎ ነው የሚጎለምሱት... ሲመስለኝ የእናንተ ሀገር ሰዎች ከእኛዎቹ በተሻለ ሁኔታ ለሰዎች መብት የሚጨነቁ ይመስላል... ምክንያቱም እዚህ ሀገር ላይ ብዙ ሴቶች ያለ ባል ልጆች አሉዋቸው... ይህ ደግሞ በጣም ከባድ ችግር ነው... ግን ምን ማድረግ ይቻላል?... ፈጣሪስ ቢሆን ብዙ ተባዙ አይደል የሚለው... ስለዚህ ፈረንሳዊው ምንም እንኳን በሴቶች ብትከበብም የእኔ ሀሳብ እዚሁ ከእኛ ጋር ቆይ የሚል ነው... በዛ ላይ እንዳንተ አይነት ቀና እና አስተዋይ ሰው ስላገኘሁ ደስተኛ ነኝ" አለኝ... እኔም ምንም ማለት ስላልፈለኩ ለጊዜው ሀሳቡን ገታ አደረኩት

ወደ ካፌው ስንገባም በዛ ያሉ ሰዎች ተቀምጠዋል፤ እኔም በጆዜ አስተዋዋቂነት ከሁሉም ጋር ሰላምታ ተለዋወጥን፡፡ በእያንዳንዷ ትውውቅ ጆዜ ጓደኛው እንደሆንኩና እሱ ቤት እንደምኖር እየተናገረ ነበር የሚያስተዋውቀኝ፡፡ እኛም የሚጠጣ አዘን ባዶ ቦታ ፈልገን ተቀመጥን፤ ያዘዝነውን መጠጥ እየተጎነጨን ስለተለያዩ ነገሮች ማውራት ጀመርን፡፡ ጆዜ አንዴ ከኔ ጋር ሲለው ከሌሎች ጋር ያወራል፡፡ በእዚህ መሃል ትከሻዬን አንድ እጅ ነካኝ፤ ዞሬ ስመለከት ማሪያ ነበረች፡፡

"ተነስ ወደ ቤት እንሂድ... ምሳ ደርሷል... ደግሞ ብዙ እነደማትጠጣ ቃል ገብተህልኝ ነበር" አለች ለማኩረፍ እየዳዳት

"አባትሽስ?" አልኳት ሞቅ ያለ ጨዋታ የያዘውን ጆዜን እያመለከትኳት

"በራሱ ሰዓት ይመለሳል... ሲጣጣ ምንም ነገር ማለት አልፈልግም" የሚል ምላሽ ስለሰጠችኝ ተያይዘን ከካፌው ወጣን... ወደቤት በመሄድ ላይ እያለን "እኔ እምልሽ አባትሽም አብሮኝ ሳለ እኔን ብቻ ለምን ጎትተሽ ከካፌው አሰወጣሽኝ?"

"አንተ ትለያለህ ኢኒሪክ... ጥሩ ሰው ለመሆን ሞክር እሺ" አለችኝ አይን አይኔን እየተመለከተች... አይኖቿ በጣም ያምራሉ፤ የሆነ ድንዝዝ የሚያረግ ስሜት ውስጥ ይከታሉ፡፡ እንደተቃቀፍን የቤቱ በር ላይ ስንደርስ "መሳም ይገባሃል" ብላ ወደ ከንፈሬ በጣም ተጠግታ ጉንጬ ላይ ሳመችኝ፡፡ ወደ ውስጥ ከገባን በኋላም ለማዕድ ወደተዘጋጀው ቦታ ሄደን ለምሳ ተቀመጥን፡፡ እኔ፣ ማሪያ እና

ሁለቱ እህቶቿ አንድ ላይ እንዲሁም ፒኮሊኖ እና ታናሽ እህታቸው ደግሞ አንድ ላይ ሆነን የሚጣፍጥ ምሳ ተመገብን። ከምሳ በኋላም በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠን ስለተለያዩ ነገሮች ማውራት ጀመርን። በእንደዚህ አይነት የቤተሰብ ወሬ ጥቂት ሰዓታት እንዳለፉ ነበር የመኖሪያ ቤቱ በር በኃይል ተበርግዶ ጆዜ እየተንገዳገደ ወደውስጥ የገባው። በጣም ስለጠጣ የሚያወራውን እንኳን በቅጡ ሳያውቀው እንደምንም ብሎ ወንበር ስቦ ከተቀመጠ በኋላ እየተንተባተበ ማውራቱን ቀጠለ።

"ል.. ልጆቼ... ኢኒሪክ እኮ እናንተን ይፈራችኋል... እንደውም ከመፍራቱ የተነሳ ይሔን ቤት ጥሎ ለመሄድ ሁሉ አስቧል። ...እንደኔ እንደኔ ግን እዚሁ ብትቆይ የተሻለ ነው እያልኩት ነው... ልጆቼ የሚያደርጉትን የሚያውቁበትና በራሳቸው የሚወስኑበት እድሜ ላይ ናቸው ባይ ነኝ... አይደል እንዴ ልጆቼ?" አለ አፉን ያዝ እያረገው... ማሪያ አተኩራ ካየችኝ በኋላ እይታዋን ወደ መሬት አርጋ ለብቻዋ ማሰብ ጀመረች፤ በነገሩ የተደነቀችም የተገረመችም ይመስላል ምን አልባትም ተናዳም ሊሆን ይችላል።

"አባባ መሔድ ከፈለገ ተወው ይሂድ አትከልክለው... ነገር ግን ከእዚህ የተሻለ ቦታ ያገኛል ብዬ አላስብም" ወደእኔ እየዞረችም "ኢኒሪክ አትፍራ... ምን አልባት ከእኛ መካከል አንዷን ከወደድክ ወይም ደግሞ ከወደደችህ... ለምንድን ነው የምትሸሸው?"

"ለማስታወስ ያክል ፈረንሳይ እያለ አግብቶ ነበር" ጆዜ ነበር

"ምን ያህል ግዜ ሆነክ ባለቤትህን ካየኃት?" አለችኝ ማሪያ

"አስራ አራት አመት"

"በእርግጥ ሁሉም ሰው እንደመልኩ ሁሉ አመለካከቱም ይለያያል... ግን ምን መሰለህ ኢኒሪክ አንድን ሰው ካፈቀርከው ማግባት አይጠበቅብህም... ራስህን ለእዛ ሰው አሳልፈህ መስጠት በራሱ ማፍቀር ነው... ከእዚህ በላይ ምን አለ?... ነገር ግን ማግባትህን ለአባታችን መንገርህ ጥሩ አድርገሀል... ምክንያቱም ከሁላችንም ጋር ምንም አይነት ቃል ኪዳን አልፈፀምክምና ነው... ምንአልባት ምንም እገዛ ሳላደርግ እንዴት በነፃ እኖራለሁ የሚል ስጋት ይዞህ ከሆነ ራስህን ነፃ ለማድረግ በመጠኑ መክፈል ትችላለህ" አለችኝ... እኔም ሳልወድ በግዴ ሀሳቧን ተቀብዬ ለመቆየት ተስማማሁ በዛ ላይ የፒኮሊኖ ጉዳይ አለ... ለግዜውም ቢሆን ከእነሱ ጋር መቆየቱ ሳይሻለኝ አይቀርም

ትንሽ በዝምታ እንደተቀመጥንም ማሪያ" ወደ ወርቅ ማውጫ ድርጅቶች ፀሀይዋ በረድ ስትል ወደ አስር ሰዓት አካባቢ እንሄዳለን... ከእዚህ ብዙም አይርቅም... እዛ ላንተ የሚሆን ስራ አይጠፋም" አለችኝ

"ጥሩ እንሄዳለን"

ቀና ብዬ ፊት ለፊቴ የተቀመጠውን ፒኮሊኖን ስመለከተው እዚህ የተባረከ ቤተሰብ ውስጥ መቆየት እንደሚፈልግ ከፊቱና ከእጁ እንቅስቃሴ ተረድቻለሁ፡፡ የሴቶቹ ሩህሩህነት ልቡን ሳያሸንፈው አልቀረም፤ ጓደኛዬ ሲደሰት መመልከቴ በሚደረግለት እንክብካቤ እንደረካ ያስታውቃል፡፡

ከእዚህ ቤተሰብ ያገኘሁት ግሩም የሆነ መስተንግዶ እንዳለ ሆኖ ለአስራ አራት አመት በእነዚያ እነደ ሲኦል በሚያስጨንቁ ጨለማ ክፍል ውስጥ ያሳለፍኩትን ጊዜ፤ እንደገና ደግሞ በዛ እንደ ሾክ በሚዋጋ አልጋ ላይ የተኛሁበት ወቅት መርሳት እነደሌለብኝ ገባኝ፡፡ ቅጣት የሚገባቸውን ሳልቀጣ፤ የእኔን ህይወት አዘቅት ውስጥ የከተቱትን ሰዎች ሳላጠፋ፤ በእነዚህ እንደ እንቡጥ አበባ በሚያስጎምጁ ልጅ አገረዶች ሀሳቤን መቀየር እንደሌለብኝ ተረድቻለሁ፡፡ በእርግጥ ከፊቴ ረጅም መንገድ ይጠብቀኛል፤ ያንን እረጅም መንገድ በሆነ ምክንይት ማሳጠር አለብኝ፡፡ ለአስራ አራት አመታት ለነፃነቴ የታገልኩት ከዛም አሸናፊ እዚህ የደረስኩት በምክንያት ነው... ምክንያቱ ደግሞ ብቀላ ነው!!... ሐሰተኛው ዓቃቤ ህግ፣ የሀሰት ምስክሮቹ፣ ፖሊሶቹ... በፍፁም መርሳት አልችልም... በፍፁም!

በአንዱ ቀን ከተማዋን በመጎብኘት ላይ እንዳለሁ "ፕሮስፔሪ" የሚል ፅሁፍ የተሰቀለበት አንድ ሱቅ ስላየሁ ባለሱቁ ኮርሲካዊ ወይም ጣሊያናዊ ሊሆን እነደሚችል ግምቴን ለራሴ አስቀመጥኩ፤ ግምቴም የተሳሳተ አልነበረም፡፡ እንዳልኩትም የሱቁ ባለቤት የኮርሲካን ዘር ሲወርድ ሲዋረድ ይዞ የመጣ ኮርሲካዊ ነበር፡፡ የሱቁ ባለቤት አቶ ፕሮስፔሪ ጥሩ ፈረንሳይኛ ይናገሩ ነበር፡፡ ከፕሮስፔሪ ጋርም ከትውውቅ አልፈን ስለህይወት ውጣውረድ አወጋን፡፡ በመጨረሻም እንደትብብር ላ ሞኩፒያ ውስጥ ለሚገኘው በፈረንሳውያን ለሚመራ የወርቅ ማወጫ ድርጅት ስራ እነዲፈልጉልኝ የሚጠይቅ ደብዳቤ ለዋና ተቆጣጣሪው ፃፈልኝ፡፡ ይባስ ብሎም ገንዘብ ያስፈልገኝ እንደሆነ ጠየቀኝ፡፡ እኔም ለጊዜው እንደማያስፈልገኝ ነግሬው ስለሁሉም ነገር አመሰግኜ ከመደብሩ ወጣሁ፡፡

"እዚህ ምን ትሰራለህ?" የሚል ድምፅ ከመደብሩ እንደወጣሁ ስለሰማሁ ወደ ኋላ ዞርኩ

"ከየት ነው የመጣኸው?... ከጨረቃ... ወይስ በፓራሹት ወርደህ ነው?... ና እስኪ ልሳምህ" አለ አንድ ፊቱ በፀሀይ የተጠበሰና አናቱ ላይ የወየበ ኮፍያ ያረገ ሰው... ለማውራት እንኳን ግዜ ሳይሰጠኝ "እርግጠኛ ነኝ አላስታወስከኝም አይደል?" አለኝና ሰፊ እና አስቀያሚውን ኮፍያውን አወለቀው፡፡

"እንዴ ትልቁ ቻርሎቴ!!... በእውነት አንተን ባለማስታወሴ የማልረባ ሰው ነኝ "አልኩት ከዚያም ልክ ለብዙ ጊዜያት ተለያይተው ድንገት እንደተገናኙ ወንድማማቾች ተቃቀፍን፤ ለረጅ ደቂቃዎችም አይን ለአይን እየተያየን ተላቀስን፡፡

"ከብላንቼ እና ከክሊንክ በጣም እርቀህል እኮ... እንዴት እዚህ መጣህ?" ደግሞ እንደ እንግሊዞች ጌታ ነው የለበስከው በእዛ ላይ ከእኔ በተሻለ መልኩ እርጅና አይታይህብህም" አለ በእንባ የራሱ አይኖቹን እየጠራረገ

"ወደ ኢል ዶራዶ ሄጄ ነው"

"ስንት ጊዜ ሆነህ እዚህ?"

"ወደ አንድ አመት ገደማ"

"ለምንድነው እዚህ መሆንህን ያልነገርከኝ ታዲያ?... የተቻለኝን ያህል እረዳህ ነበር እኮ... ኢል ዶራዶ ውስጥ ትሆናለህ ብዬ በጭራሽ አስቤ አላውቅም"

"መገናኘታችን በእውነት ተዓምር ነው"

"ሊገርምህ አይገባም" አለ ያወለቀውን ኮፍያ ጭንቅላቱ ላይ እያስተካከለ... አስከትሎም" ያመለጠ ወንጀለኛ የቬንዙዌላን ድንበር አቋርጦ እስከገባ ድረስ እና የፓሪያን ባህረ ሰላጤ ማቋረጡ እስካልቀረ ድረስ ሁሉም ወንጀለኛ እዚህ መገናኘቱ አይቀርም... ሌላ ማቋረጫ የለማ!... ለመሆኑ የት ነበር ያረፍከው?"

"ጆዜ የሚባል ሰው ጋር ነኝ... እንዴት ያለ መልካም ሰው መሰለህ... ሦስት ልጆች አሉት... ታውቀው ይሆን?"

"አዎ አውቀዋለሁ በጣም ጥሩ ሰው ነው... የባህር ላይ ወንበዴ ነው... በቃ አሁን እንሂድ እና ያሉህን እቃዎች ይዘን እንምጣ ከእዚህ በኋላ እኔ ጋር ነው የምትኖረው" አለኝ... እኔን በማግኘቱ በጣም እንደተደሰተው ሁሉ እኔም ተደስቼ ነበር፡፡

"ቻርሎቴ ብቻዬን ብሆን ኖሮ ድንቅ ሀሳብ ነበር... ነገር ግን ከኢል ዶራዶ እስር ቤት አብሮኝ የመጣ ግማሽ አካሉ ብቻ የሚሰራ አንድ ጓደኛ አለኝ... እሱን ድግሞ ጥዬ መሄድ አልችልም"

"ታዲያ ምን ችግር አለው?... ለእሱ አታስብ በአህያ ጭነን እንወስደዋለን... የምንሄደው ወደትልቅ ቤት ነው... እዛ ያለችው ልጅ ደግሞ ጓደኛህን ልክ እንደ እናት ትንከባከብልሀለች"

አህያ ፈልገን እንዳገኘን ወደ ሴቶቹ ቤት ሔድን፤ ልለያቸው መሆኑን ሳስብ ውስጤን የሆነ ያህል ቅር አለው። እውነት ለመናገር እንደእዚህ አይነት ለሰው የሚጨነቁ ከራሳቸው ሳቅ በላይ የሰው ደስታ የሚያስፈነድቃቸውን ቤተሰብ ጥሎ መኮብለል በጣም ያማል። እነርሱም ቢሆኑ በአጋጣሚ ለመሄድ ስነሳ በቀላሉ ሊቀበሉኝ እና ሊለቁኝ አልቻሉም፤ ነገር ግን በማንኛውም ሰዓት መጥተው ሊጠይቁኝ እንደሚችሉ እና እኔም እየመጣሁ እንደምጠይቃቸው ሳስረዳቸው ግን ሳይፈልጉም ቢሆን ለመቀበል ተገደዱ።

ከሁለት ሰዓት ጉዞ በኋላ ቻርሎቴ ቤት ወይም ደግሞ እንደርሱ አጠረር ቻቲው ቤት ደረስን። ቤቱ ቀላልና የማያጨናንቅ ቤት ሲሆን ግዙፍና ብዙ ክፈፍሎች ያሉት ቤት ነው። ቤቱ የተሰራበት ኮረብትማ ቦታ ከካርታል ትንሽ መንደር አንስቶ እስከ ኢል ዶራዶ ድረስ ያለውን ሸለቆ ማየት ያስችል ነበር። በስተቀኝ በኩል ደግሞ ድንግል ጫካ ውስጥ የሚገኘውን ሞኮፒያ የሚባለውን የወርቅ ማውጫ ይገኛል። የቻርሎቴ ቤት ከጠንካራ እንጨት የተሰራ ማራኪ ቤት ሲሆን በውስጡም አንድ የሚያምር የመመገቢያ ክፍል፣ እቃ ቤት እና ሁለት የመታጠቢያ ክፍሎች አሉት። በውጪ በኩል ድግሞ አንድ ተጨማሪ የመታጠቢያ ቤት በሚያምረው አትክልቶች ተከቦ ይገኛል። ሌላው ደግሞ በቤት ውስጥ የሚጠቀሙዋቸው አትክልቶች በሙሉ የተገኙት ከራሳቸው ጓሮ መሆኑን አውቄአለሁ። ከአትክልቶቹ ጎን ደግሞ ለእንስሳት ማርቢያነት የተዘጋጀ ሰፊ መጋዘን የሚመስል ቤት ነበር። በውስጡም አምስት መቶ ያህል ዶሮዎች፣ ጥንቸሎች፣ አሳማዎች፣ ሁለት ፍየሎች እና አንድ የዱር አሳማ ይገኙበታል። ይህ ሁሉ ንብረት እንግዲህ በአንድ ወቅት ጥበብ በሚጠይቁ የተለያዩ ዝርፊያዎች ላይ ይሠራ የነበረው የቻርሎቴ ንብረት ነው።

እንዲህ ለብቻዬ እየተሽከረከርኩ የቻርሎቴን ግቢ በምጎበኝበት ሰዓት ነበር ቻርሎቴ ከየት እንደመጣ ሳላውቅ "እንዴት ነው ፓፒ?... እንዴት አየኸው ግቢዬን?" ብሎኝ ከሀሳቤ ያነቃኝ።

"በጣም የሚያምር ግቢ ውስጥ አይደል እንዴ የምትኖረው"

"ያው እነግዲህ ፓፒ ህይወት ባሰብካት መልኩ ላትሔድ ትችላለች... ይኸው እኔም እዚህ መኖር ከጀመርኩ ሰባት አመት ሊሞላኝ ነው... እንደዚህ ሰላም የሰፈነበት ኑሮ ይኖረኛል ብሎ ማን አስቦ ያውቃል"

"ምን ማለት እንዳለብኝ አላውቅም ቻርሎቴ... ነገር ግን በህይወት ውስጥ ከጨለማ ጀርባ ንጋት ከመከራ ጀርባ ሀሴት አንድ ቀን ልትገኝ እንደምትችል ነው ዛሬ የተረዳሁት... በእውነት በእንደዚህ አይነት የህይወት ደረጃ ላይ ስላገኘሁህ ደስታዬ ላቅ ያለ ነው" አልኩት

እያወራንና እየተሳሳቅን ሁለታችንም ተያይዘን ወደ መመገቢያው ክፍል አመራን፤ ምግብ ለመብላት በጠረጴዛ ዙሪያ እንደተሰባሰብንም ቻርሎቴ ድንገት ወሬ ጀመረ።

"አዎ ፓፒ እንደተገረምክ ይገባኛል... በቀን አስራስምንት ቦሊቫርስ አገኛለሁ... በዛ ላይ ዶሮቹ እንቁላል ሲጥሉልኝ፣ ጥንቸሎቹ እና አሳማዎቹ ሲወልዱ ጥሩ ትርፍ ይኖረኛል... ከአትክልቶቹም ቢሆን ትንሽ የማይባል ብር አገኛለሁ" አለኝና አብራን ወደተቀመጠችው ልጅ ከተመለከተ በኋላ በድጋሚ ወደ እኔ ዞሮ "ሳላስተዋውቅህ ብዙ ቀባጠርኩ አይደል... እቺ የእኔዋ ጥቁሯ ሴት ኮንቺታ ትባላለች" ብሎኝ እንደገና ወደ ኮንቺታ ዞሮ "እነዚህ ጓደኞቼ ናቸው... እንደምታይው ጓደኛው ታሟል... ስለዚህ እሱን እንድትንከባከቢው አደራዬን ሰጥቼሻለሁ... እ... እሱ ደግሞ ኢኒሪክ ይባላል ወይም ደግሞ ፓፒለን ብለሽ መጥራት ትችያለሽ... ፈረንሳይ በነበርንበት ሰዓት ጓደኛሞች ነበርን።

"እንኳን ደህና መጣህ አለች" ጥቁሯ ልጅ አስከትላም "ጓደኛህን እኔ እንከባከበዋለሁ ምንም ሀሳብ እንዳይገባህ" ብላ ለመተማመኛ እንዲሆነኝ ይመስል ደስ የሚል ፈገግታ ቸረችኝ።

እኔና ቻርሎቴ ሞቅ ያለ ጨዋታ ይዘናል፤ ከእስር ቤት እንዴት እነዳመለጠ ይተርክልኝ ጀመር። ፍርድ ከተቀበለ በኋላ በቀጥታ የተወሰደው ወደ ቅዱስ ላውረን ዱ ማሮኒ እስር ቤት ነበር። ከስድስት ወራት ቆይታ በኋላም ሲሞን እና ዲቴኒ ከሚባሉ ሁለት ኮርሲካዊ ወንጀለኞች ጋር ሆኖ አመለጠ።

"ከትንሽ ወራት በኋላም ቬንዙዌላ ደረስን... ከታላቁ አምባገነን ጎሜዝ በኋላ ቬንዙዌላ መድረሳችን በራሱ እድል ነው... ታዲያ እነዚህ ደግና ሩህሩህ ቬንዙዌላውያን አሁን ለመሰረትነው የደስታ ኑሮ በእጅጉ አግዘውናል... ለእኔ እዚህ መድረስ የቬንዙዌላውያን ድጋፍ የላቀ ነው... እዚህ ቬንዙዌላ ከመጣሁ በኋላ ለሁለት አመት ያክል ኢልሴሎ ውስጥ የመኖር ግዴታ ነበረብኝ... ሚስትም አግብቼ ነበር... ነገር ግን ልጅ በምትወልድበት ሰዓት ሚስቴንም

ልጄንም አጣኋቸው... ከእዚያ በኋላ ነው እንግዲህ እቺን ኮንቺታ የተባለች ልጅ አግኝቼ ተረጋግቼ መኖር የጀመርኩት... አንተስ ፓፒ እነዚያ አስራ አራት አመታት የዋዛ ያለፉ አይመስሉኝም እስኪ ንገረኝ"

ከሁለት ሰዓት በላይ ስላሳለፍኩት ከባድ እና አስከፊ ጊዜ ከድሮ ጓደኛዬ ጋር አወጋን፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ሁለታችንም ያሳለፍነውን የህይወት ውጣ ውረድ አያነሳን ማውጋታችን ከመጠን በላይ ደስታን ፈጥሮልናል፡፡ ነገር ግን ይህን ያህል ሰዓት ስንጨዋወት አንዲትም ግዜ ስለሞንትማርትሪ ያነሳነው ነገር አልነበረም፡፡

ወደ አመሻሽ ላይ ጣፋጭ የጣሊያን ነጭ ወይን ከተጠበሰ ዶሮ እና ከፍየል ስጋ ጋር የተለያዩ ፍራፍሬዎች ተደምረውበት በቻርሎቴ ግብዣ ምርጥ እራት ተመገብን፡፡ ከዛም ቻርሎቴ ወደ ከተማው ወጥተን እንድንዝናና ሀሳብ ቢያቀርብም ገና ይሄንን የሚያምር ቤት እንዳልጠገብኩት እና ለጊዜው እዚሁ ቤት ውስጥ ብሆን እንደምመርጥ ነገሬው ሀሳቡን አስቀየርኩት፡፡

እሱም ለአድናቆቴ ካመሰገነኝ በኋላ ወደ ኮንቺታ ዞሮ "ታዲያ ለኢኒሪክ ሚስት አትፈልጊለትም እንዴ?" አላት

"እረ ችግር የለውም... ከእኔ የተሻለች ቆንጆ አስተዋውቅሃለሁ ኢኒሪክ"

"እንዴ አንቺ ከሁሉም ትበልጫለሽ እኮ" አለ ቻርሎቴ

"አዎ... ግን ጥቁር ነኝ" ብላ መለሰች

"ያ እኮ ነው ታዲያ ቆንጆ የሚያረግሽ"

ወዲያው የኮንቺታ አይኖች በደስታ ሲያበሩ አየሁ፤ ገብቼ ባላየውም ልቧ በሀሴት ጮቤ እየረረገጠ እንደሆነ መገመት ግን አዳጋች አይደለም፡፡ ከኮንቺታ አይታ እንደተረዳሁት ቻርሎቴን ከመውደድ አልፋ ሳታመልከው አትቀርም፡፡ ከጥቂት ቆይታ በኋላ ሁላችንም ለመተኛት ስለተስማማን ወደተዘጋጀልኝ ክፍል ሄድኩ፡፡

አልጋዬ ላይ ጋደም እንዳልኩ ከጎኔ ያለውን የቻርሎቴን ራዲዮ ከፍቼ ማድመጥ ጀመርኩ፡፡ ከለንደን የሚተላለፈው ቢ. ቢ. ሲ. እያወራ ነበር፡፡ ከውጪው አለም ርቄ ስለነበር የሚያወራውን ለማድመጥ ፍላጎቱ አልነበረኝም፡፡ ወድያው ሌላ ጣቢያ ለመቀየር ሞከርኩ የካረቢያንውያን ሙዚቃ እየዘፈነ ነው፤ እሱንም ለማድመጥ ወኔውን ስላጣው ራድዮኑን ዘግቼ ማሰብ ጀምረኩ፡፡ ለሁለት

ሰዓታት ያህል በሀሳብ ባህር መቅዘፍን ተያያዝኩት፤ ማሰቡ ሲሰለቸኝ በሆዴ ተገልብጬ ለመተኛት ሞከርኩ፤ ሙቀቱ ግን የማይቻል ነበር፡፡ ብገላበጥም እንቅልፍ ሊወስደኝ ስላልቻለ ከተንጠልጣይ አልጋዬ ላይ ወርጄ ወደ አትክልት ስፍራው አመራሁ፡፡ አንድ ትልቅ ድንጋይ ላይ ቁጭ ብዬ ሽለቆውንና ከወርቅ ማውጫው ጉድጓድ ውስጥ ወርቅ ተሸክምው አልያም ደግሞ ባዶ እጃቸውን ውርውር የሚሉትን የጭነት መኪኖችን መመልከት ጀመርኩ ከዛ ጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ በጣም በብዙ መጠን እንደዚሁም በነጠላ ብዛት ያለው ወርቅ ይወጣል፡፡ የእዚህ ወርቅ ጉዳይ ይመስለኛል ቻርሎቴን ስለነፃነቱ ከማሰብ ይልቅ ወደ ወርቅ ስራው እንዲያዘነብል ያደረገው፡፡ ስለ ወርቁ ጉዳይ ምንም አይነት መረጃ የለኝም፡፡ በውስጡም ብዛት ያለው ወርቅ ይኑር አይኑር የማወቀው ጉዳይ የለም፡፡ በእዚህ ሰዓት ለቻርሎቴ እና ለጥቁሯ ቆንጆ ቤቱ፤ የአትክልት ስፍራው እና እንስሳቶቹ በራሱ ትልቅ የደስታቸው መገለጫዎች ናቸው፡፡

ቻርሎቴ ለፍርድ የቀረበው ትንሹ ሊዊስ እየተባለ የሚጠራው ሰው ለፖሊስ በሰጠው ማስረጃ ምክንያት ነበር፡፡ እስር ቤት በነበርንበት ወቅት ቻርሎቴ ሊዊስ የሚባለውን ሰው እስካላገኘ ድረስ ሰላም እንደማያገኝና እንቅልፍም እንደማይወስደው ጭምርር ነግሮኝ ነበር፡፡ አሁን ባየሁት ነገር ግን በስህተት እንኳን ቻርሎቴ የሊዊስን ስም ሲጠራ አለመስማቴ ግርምትን ፈጥሮብኛል፡፡ ያው የእሱን አልኩ እንጂ እኔም ብሆን በሀሰት ስለወነጀሉኝ ፖሊሶች፣ በሀሰት ስለከሰሰኝ አቃቤ ህግ፣ በሀሰት ስለመሰከሩብኝ እማኞች ምንም ነገር አላልኩም ነበር፡፡ መናገር ግን ነበረብኝ ምክንያቱም ከእስር ያመለጥኩት እዚህ አትክልተኛ ወይም የቀን ሰራተኛ ለሞሆን አይደለም!!... ፍርድ ለሚገባው ፍርድ ለመስጠት እንጂ!!... በእርግጥ ነገሮች እስኪስተካከሉ ድረስ እዚህ ሀገር ለመቆየት ቃል ገብቻለሁ፡፡ ይ ማለት ግን ለዘመናት ውስጤን እንደ እግር እሳት ሲለበልበኝ የነበረውን ህመሜን እረሳለሁ ማለት አይደለም "ፓፒ" አልኩ ለራሴ "ለአስራ አራት አመታት ማቀህ የታገልክለትን ብቀላ መፈፀም ይኖርብሃል" በተቀመጥኩበት ድንጋይ ላይ ሆኜ ሰማዩ ላይ ወደተነጠፉት ከዋክብቶች እያንጋጠጥኩ ለዘመናት ውስጤ ያለውን ቃል አፀናሁ፡፡

ለቻርሎቴ ትንሿ ኮንቺታ በጣም ቆንጆ ናት፡፡ ልቡንም ያሸፈተችው ይመስለኛል፤ ቢሆንም ግን ለቻርሎቴ ከእዚህ የጉድጓድ ኑሮ ይልቅ ወደ ከተማ ሔዶ ቢኖር የሚል ሀሳብ ውስጤ ይመላለሳል፡፡ በአንድ በኩል ደግሞ የእሱ የተስተካከለውንና ሰላም የሰፈነበት ሕይወት ለእኔ አልታይህ ብሎኝ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ሀሳቤን መዋጡ የተሻለ አማራጭ መሆኑን ተገነዘብኩ፡፡ ደግሞም ሲታይ ከፀሀይዋ ንዳድ የተነሳ ፊቱ ጠቁሯል እንጂ ሌላ አካሉ ንቁ እና ጥንካሬን የተላበሰ እንደሆነ ያሳብቃል፡፡ በዛ ላይ የማያውቁት ሀገር ላይ መጥቶ ከተፈጥሮና ከማህበረሰቡ ጋር ተላምዶ እና ተወዳጅቶ መኖር ከቻሉ ሰፋሪዎች

መካከል እርሱን እንደ ምሳሌ መውሰድ ይቻላል፡፡ ስለዚህ በቃ ይህ ቦታ ተገቢው ነው ማለት ይቻላል፡፡

እንግዲህ እዚህ መኖር ከጀመረ ሰባት ዓመት ያህል ተቆጥረዋል፡፡ እርግጠኛ ነኝ ይህንን ቤት ለመስራት እራሱ ከሁለት አመታት በላይ ሳይፈጅበት አይቀርም፡፡ ወደ ጫካ ወርዶ ለቤቱ መስሪያ የሚሆን ዛፍ መምረጥ፣ ከዚያም መቁረጥ፣ ወደ ሚሰራበት ቦታ ይዞ መምጣት፣ እንደገና በተጨማሪ ለቤት መስሪያ የሚያገለግሉ ቁሶችን ማዘጋጀት፣ ሌላም ሌላም ተጨምሮ ብዙ ነገር ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

በቤቱ ውስጥ ያሉ የእንጨት ማገሮች በጠቅላላው ከጠንካራ እንጨት የተሰሩ ናቸው፡፡ እንደውም ከእንጨቶቹ ጥንቃሬ የተነሳ የብረት እንጨቶች ነው የሚባሉት፡፡ ሳስበው በወርቅ ማውጫው ጉድጓድ ውስጥ መስራቱ ሰዎችን እንዲተዋወቅ እና ወዳጅ እንዲሆን ሳይረዳው አልቀረም፤ ምክንያቱም ከሰራተኞቹ መካከል ቤቱን ሲሰራ የረዳው እንደማይጠፋ ያወቅሁት የቤቱ ወለል እና ግድግዳ በሲሚንቶ መሸፈኑን ሳይ ነው፡፡ ምንአልባት ቻርሎቴ ወደ ከተማ ወጥቶ መኖር የማይፈልገው በእራሱ ሙሉ እምነት ስለሌለው ነው ብዬ አሰብኩ፤ በተመሳሳይ ሁኔታ ደግሞ እዚህ ያለምንም ችግር እና ሰቀቀን መኖሩ በራሱ ትልቅ ተዕፅኖ ያሳድራል፡፡ "ሆነም ቀረ ቻርሎቴ አንተ ድንቅ ሰው ነህ!!... አንድ ዘራፊ ወደ ተሻለ የህይወት ደረጃ እንዴት መቀየር እደሚችል ትልቅ ማሳያ ነህ... በእዚህ ደግሞ አድናቂህ ነኝ... አንተን ብቻ ሳይሆን አንተን ወደእዚህ የህይወት እርከን የመሩህንም ሰዎች ሳላደንቅ ማለፍ አልፈልግም"... ቻርሎቴ አብሮኝ ያለ ይመስል ጮክ ብዬ ነበር የማወራው፡፡ እንደዛም ቢሆን ግን ቬንዙዌላውያን በጣም አደገኞች ናቸው፡፡ በእዚህ ገራገር ፀባያቸው እና ጥሩ አሳቢነታቸው እስረኞቸው አርገው ሊያስቀምጡ ይችላሉ፡፡ እኔ ደግሞ ነፃ ሰው ነኝ!!... ስፈጠርም ነፃ ሆኜ እንድኖር ነው የተፈጠርኩት፡፡

ከሁሉም በላይ ግን ልብን በሴት ወጥመድ ውስጥ ገብቶ እዲንታሰር መፍቀድ ተገቢ አይደለም፡፡ ፍቅር የሚያስፈልገው ፍቅርን ለብዙ ጊዜያት ለተጠማ ሰው ነው፡፡ ለእንደኔ አይነቱ ግን ይሄ አይሰራም፡፡ ምክንያቱም እኔም በአንድ ወቅት በፍቅር ባህር ውስጥ ለመዋኘት ችዬ ነበር፡፡ እና ደግሞ እኔ እንደ ቻርሎቴ በፍቅር የተጎዳው ስላልሆንኩ በዚህ ሰዓት ሴት የሚያስፈልገኝ አይመስለኝም፡፡ ምንም እንኳን ይህ ቦታ ምንም አይነት ኮሽታ የማይሰማበት ሰላማዊ ቦታ ቢሆንም የእኔ ቦታ ግን እንዳልሆነ ይሰማኛል፡፡

እዚህ ጋር ግልፅ ለማድረግ ያህል ያለ ፍቅር እኖራለሁ እያልኩ ሳይሆን ያሰብኩትን ሀሳብ ሳላሳካ በፍቅር ምክንያት ከአላማዬ መጨናገፍ ግን ስለማልፈልግ ነው፡፡ ጊዜው ሲደረስ ሁሉም ነገር በሰዓቱ መፈፀሙ ላይቀር

መጣደፍ አስፈላጊ መስሎ አይሰማኝም፡፡ በእዚህ ሰዓት የእኔ አላማ ፍቅር ሳይሆን ወደ ፓሪስ ሄዶ እኔ ላይ ለደረሰብኝ መዓት እና መከራ ተጠያቂ ለሆኑት ሰዎች ቅጣት መስጠት ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ እቅዴን የማሳከበት ገንዘብ ስለሚያስፈልገኝ በቻልኩት አቅም ሰው ሳልጎዳ ገንዘብ የማገኝበትን መንገድ እፈልጋለሁ፡፡ ከዛ በእኔ ላይ የደረሰውን የተዛባ ፍርድ ራሴ ለማተካክል እጥራለሁ፡፡

በእዚህ ሰዓት ከመቼውም በተሻለ ሁኔታ ተረጋግቻለሁ፡፡ አይኖቼ ጨረቃዋን እና ከፊት ለፊቴ ያለውን ድንግል ጫካ መመልከት ሲሰለቻቸው ውስጥ ገብቼ አልጋ ላይ ጋድም አልኩ፡፡ ውሰጤ ከእዚህ ተነስቼ ፓሪስ እስክደርስ ብዙ ፈተና እንደሚያጋጥመኝ ያውቃል፤ ነገር ግን ተመልሼ የፓሪስ መንገዶች ላይ እንደምረማመድ የማያወላውል እምነቴ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## የማዕድን ማውጫው

ለፕሮስፔሪ ደብዳቤ ምስጋና ይግባውና ከሳምንት በኋላ ሞኩፒያ የወርቅ ማውጫ ድርጅት ውስጥ ስራ አገኘሁ፡፡ ስራዬም ከጉድጓዶቹ መግቢያ አካባቢ ያለውን የውሃ ማውጫ መቆጣጠር ነበር፡፡

የማዕድን ማውጫው ሲታይ ልክ የድንጋይ ከሰል ማውጫ ይመስል ነበር፡፡ በውስጡም ከጥቂት ያልተጣራ ወርቅ በስተቀር ምንም አይነት ወርቅ አይታይበትም፡፡ ወርቁ የሚገኘው ጠንካራ ድንጋይ ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህ ያንን ድንጋይ በፈንጂ መበታተን ይጠበቅባቸዋል፡፡ እንደገና ደግሞ ያንን በፈንጂ የተፈረካከሰ ድንጋይ ደግሞ የሰዎችን ኃይል በመጠቀም በትልቅ መዶሻ መፈረካከስ ይኖርባቸዋል፡፡ይህንን የተፈረካከሰውን ድንጋይ ደግሞ በጋሪ ላይ ይጫንና በአሳንሰር ወደ መሬት ይወጣል፡፡ በመቀጠል ወደ መሬት የወጣውን የድንጋይ ፍርክስክስ ወደ ድንጋይ መፍጫ ማሽን ውስጥ ገብቶ እንዲፈጭ ይደረጋል፡፡ ይሄንን ወደ አመድነት የተቀየረውን አፈር ከውሃ ጋር በመደባለቅ በአንድ ትልቅ ማጠራቀሚያ ውስጥ እዲገባ ይደረጋል፡፡ በማጠራቀሚያው ውስጥ ሲያኒድ (የሀይድሮ ሲያሪክ መርዛማ ጨው) የሚባል መርዛማ ውህድ ስለሚገኝ የወርቆቹን ብናኝ ወደ ስር እንዲዘቅጥ ያደርገዋል፡፡ ይህም ወርቁን ከአፈሩ ለመለየት አመቺ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በመቀጠል ይሄንን የሲያኒድ ውህድ ከፍተኛ ሙቀት እንዲያገኘው ሲደረግ የወርቆቹን ብናኝ ይዞ እንዲተን ይሆናል፡፡ በመጨረሻም የተነነውን ውህድ እንዲሰክን በማድረግ እነዚህን የወርቆች ብናኝ በጥንቃቄ እዲሰበሰቡ ይደረጋል፡፡ ከዛ በኋላ በእቃው ላይ ያሉት ወርቆች ተሰብስበው በአንድ ላይ እንዲቀልጡ ተደርጎ የሀያ አራት ካራት ጥራታቸውን መጠበቃቸውን ከተረጋገጠ በኋላ ቅርፃቸውን ጠብቀው እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ ይህ የወጣው ወርቅም ጥብቅ ቁጥጥር እየተደረገለት በመጋዘን ውስጥ ይጠበቃል ማለት ነው፡፡ ግን ማነው የሚጠብቀው?... የሚገርም ነው ይህንን ግዙፍ የወርቅ ማውጫ የሚጠብቀው ሲሞን ነበር፡፡ በአንድ ወቅት ከቻርሎቴ ጋር በመሆን ከእስር ያመለጠ ሰው ነው፡፡

ሁሌም ስራዬን ስጨርስ ወደ ግምጃ ቤት እሔድ እና እነዚያን ብሉኝ ብሉኝ የሚሉ የወርቅ ዳቦዎችን ሲሞን ቆጥሮ በስነ-ስርአት ሲደረድር አያለሁ፡፡ የገረመኝ ነገር ቢኖር ይሄ ሁሉ ንብረት የሚቆጠረው በአንድ ወንጀለኛ መሆኑ ነው፡፡ ከእሱ ይባስ ብሎ ሌላው የሚገርመው ደግሞ ወርቆቹ የሚቀመጡበት ግምጃ ቤት የተሰራው በሲሚንቶ ሆኖ የግድግዳዎቹ ውፍረት ከመደበኛ ቤት ግድግዳ የማይበልጡና በሩ ደግሞ ከመናኛ እንጭት የተሰራ መሆኑ ነው፡፡

አንዴ በመጋዘኑ በኩል ሳልፍ ወደ ሲሞን ሄጄ "ሁሉ ሰላም ነው ሲሞን " አልኩት እንደገባሁ

"አዎ... ክብር ለአምላክ ይሁን!... አንተስ ከቻርሎቴ ጋር በመሆንህ ደስተኛ ነህ?"

"አዎ በጣም"

"ኢልዶራዶ መሆንህን አላወቅሁም እንጂ መጥቼ እወስድህ ነበር"

"ቻርሎቴ ግሩም ሰው ነው... አንተስ እዚህ በምትኖረው ኑሮ ደስተኛ ነህ?"

"አዎ... ያው እንደ ቻርሎቴ ትልቅ ባይሆንም ቤት አለኝ... ከጡብና ከሲሚንቶ እራሴ ነኝ የሰራሁት... በዛ ላይ ቆንጆና ደግ የሆነች ሚስት አለችኝ. . .ከእሷም ሁለት ልጆች ወልጃለሁ... ፓፒ በተመቸህ ሰዓት ቤቴ መጥተህ እኔና ቤተሰቤን ማየት ትችላለህ... ቻርሎቴ ጓደኛህ እንደታመመ ነግሮኛል... ሚስቴ ጥሩ መርፌ ወጊ ስለሆነችም እዚህ ይዘኸው መጥተህ አስፈላጊውን መርፌ እንድትወጋው እናደርጋለን" አለኝ

ከሲሞን ጋር ብዙ አወራን፡፡ አሁን ባለው ህይወቱ ደስተኛ ይመስላል፡፡ በጨዋታችን መኃል አንዴም እንኳን ስለፈረንሳይ ወይም ስለሞንትማርትሪ አላነሳም፤ በቃ... ከቻርሎቴ ጋር ተመሳሳይ ሀሳብ ነው ያለው ማለት ይቻላል፡፡ እነሱ በእዚህ ሰዓት ቤት መስራት፣ልጅ ወልዶ ማቀፍ ላይ ያተኮሩ ይመስላል፡፡ በቀን እስከ ሀያ ቦሊቫር ያገኛል፡፡ በተጨማሪም ልክ እንደ ቻርሎቴ ሁሉ እሱም ጥቂት የሚያረባቸው ዶሮዎች ስላሉት ከእነሱ የሚያገኘው እንቁላል በመሸጥ ሌላ ትርፍ ያገኛል፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ በሀያ ቦሊቫርስ ያን ሁሉ ቤተሰብ ማስተዳደር ባልቻለ ነበር፡፡ አሁንም በእነዚያ በሚያስጎመጁ ወርቆች እይታዬ እንደተወሰደ ነበር፡፡ የበሩ መናኛ መሆን፣ የግድግዳዎቹ ቅጥነት በዛ ላይ ይህ ሁሉ ንብረት በአንድ ሰው መጠበቁ በጣም ገርሞኛል፡፡ ከዚህ ጉድጓድ ተጣርቶ የወጣ አንድ ባለ ሀያ ስምንት ግራም ወርቅ በሠላሳ አምስት የአሜሪካ ዶላር ይሸጣል፡፡ እንግዲህ እዚህ መናኛ መጋዘን ውስጥ በሚሊዮን የሚቆጠር ንብረት

አለ ማለት ነው። እሱ ብቻ ሳይሆን የሚያስገርመው ይሄን ሁሉ የማይታመን ንብረት ለመዝረፍ ልክ የህፃን ጨዋታ ያክል ቀላል መሆኑ ነው።

“በእነዚህ የወርቅ ጥምዞች ሳትገረም አልቀረህም ፓፒ” አለኝ አይታዬ ከእሱ እንደተስወረ ስለገባው...“ በጣም የሚደነቀው ደግሞ የእኛ ሲሆኑ ነው” አልኩት ድንገት ውስጤ የተሰማኝ ምኞቴ ከአፌ አምልጦኝ

“ምን አልባት ልክ ትሆናለህ ነገር ግን እነዚህ ንብረቶች በአደራ ለእኔ ተሰጡ ማለት የእኔ ናቸው ማለት አይደለም”

“አዎ ለአንተ አደራ ሰጥተውኃል... ለእኔ ግን አልሰጡኝም መቼም አንተም ብትሆን እያስመሰልክ ካልሆነ በስተቀር በእዚህ ሁሉ ንብረት ሳትጎመጅ የቀረህ አይመስለኝም”

“ማስመሰል አይደለም ፓፒ...የእውነቴን ነው!”

“እሺ ሊሆን ይችላል... ነገር ግን አንተም ብትሆን ሃያ አራት ሰዓት አትጠብቀውም”

“አይ... እሱማ እኔ የምጠብቀው ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት እስከ ቀኑ ስድስት ሰዓት ነው... ከእዚያ በኋላ ቀኑን በሙሉ በሌላ ዘበኛ ነው የሚጠበቀው... አሌክሳንደር ይባላል ምን አልባት ታውቀው ይሆናል”

“አዎ አውቀዋለሁ... በቃ ወደ ቤት ልግባ ሰዓቱም እየሄደ ነው... ደህና ሁን በቅርቡ እንገናኛለን ቤተሰቦችህንም ሰላም በልልኝ”

“እሺ... መጥተህ ማየቱን እንዳትረሳ”

“ጥሩ... መምጣቴማ አይቀርም... ቻው”

ከእዚህ የማስመሰል ጨዋታ መውጣት ስለነበረብኝ ነበር ያንን ቦታ በፍጥነት ለቅቄ ለመሄድ የወሰንኩት። እስካሁን ድረስ ጭንቅላቴ አምኖ መቀበል ያቃተው ነገር ቢኖር ያንን በብዙ ገንዘብ የሚተመን ወርቅ በአንድ ተወለጋግዶ በተሰራ ግምጃ ቤት ውስጥ ማስቀመጣቸው ሳያንስ ወርቁን የሚጠብቁት ሰዎች ደግሞ ከእዚህ በፊት የወንጀል ስራ ላይ የነበሩ ሰዎች መሆናቸው ይበልጡን አስገርሞኛል። በህይወቴ ሙሉ እንደዚህ አይነት የሚያወዛግብ ነገር ገጥሞኝ አያውቅም!!

* * * * * * * *

ወደ ቻርሎቴ ቤት ለመሄድ የመንደሩን የቀኝ አቅጣጫ መያዝ ነበረብኝ። የዛሬው የስምንት ሰዓታት የጉድጓድ ውስጥ ስራ ከባድ እና አድካሚ ነበር። በዋሻው መግቢያ ላይ ውሃ የሚያወጣው ማሽን ቢያንስ በቀን ውስጥ ሦስት ወይም አራት ጊዜ ሊበላሽ ይችላል። እሱን የማስተካከል የስራ ድርሻው ደግሞ የእኔ ነው። በቀን አስራ ስምንት ቦሊቫርስ ይከፈለኛል። በእርግጥ ለላጤ ሰው አስራ ስምንት ቦሊቫር ለኑሮ በቂ ነው።አንድ ኪሎ ስጋ በሁለት ብር ከሃምሳ ሳንቲም፣ አንድ ኪሎ ስኳር በ ሰባ ሳንቲም፣ ቡና በሁለት ቦሊቫርስ ይሸጣል። እንዲሁም አትክልቶች ለምሳሌ አንድ ኪሎ ሩዝ በሃምሳ ሳንቲም፣ ደረቅ ባቄላ በሃምሳ ሳንቲም መሸመት ይቻላል።ስለዚህ ኑሮ እርካሽ ነው ቢባል አያስገርምም። ነገር ግን አሁን እየኖርኩ ያለሁትን ህይወት ተቀብዬ አርፌ ልኑር የሚለውን ጥያቄ እስካሁን ልመልሰው ያልቻልኩት ጥያቄ ነው።

ከማዕድን ማውጫው የተሰጠኝን ከቆዳ የተሰራ ከስክስ ጫማዬን እንዳጠለኩ ወደ እነቻርሎቴ ቤት መጓዜን ቀጥያለሁ። ስለ እነዚያ የሚያስጎመጁ የወርቅ ክምሮች ማሰብ ባልፈልግም አእምሮዬ ግን በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ስለሚያጎናፅፉ ወርቆች መርሳት ተስኖታል። በማታ ወርቆቹ ወዳሉበት መጋዘን ሄዶ ሲሞንን ሳልገድለው አደንዝዞ ማስቀመጥ በጣም ቀላል ነው። ቀጣዩ ስራ የሚሆነው እነዚያን የሚያስጎመጁ ወርቆች በቦርሳ እያጨቁ ማመላለስ ነው። ሸክሙ እዲቀል በአንዱ መኪና ወይም ጋሪ ተጭኖ እንዲወጣ ማድረግ ይቻላል። በመኪና ከሆነ እስከምፈልግበት ቦታ ድረስ ከሔድኩ በኃላ ወደ ጥልቁ ጫካ ወርጄ ወደ አንዱ ጥግ ከደበቅሁት በኋላ በአመቺ ሰዓት ማውጣት እችላለሁ። ጋሪ?... ጋሪ ለማግኘት አስቸጋሪ ቢሆንም አይገኝም ማለት ግን አይደለም። አዎ አንድ ዝናባማ ምሽት አሁን ላሰብኩት የዝርፊያ እቅድ በቂ ጊዜ ሊሰጠኝ ይችላል። ኧረ እንደውም ያን ያህል እራሱ አልፈጅም፣ ወደ ቤት ተመልሼ መተኛት ሁሉ እችላለሁ።

ወደ መንደራችን ስደርስ ቦታው በመብራቶች ደምቆ እና አሸብርቆ ነበር ያገኘሁት። ሀሳቤ ከዘረፋው ላይ ዝንፍ ሳይል ወደ ቻርሎቴ ቤት አካባቢ ስደርስ የሆኑ ሰብሰብ ብለው የተቀመጡ ሰዎች አንዱ መጠጥ ቤት ቁጭ ብለው እየተሳሳቁ አገኘኃቸው። ታዲያ ልክ እኔን ሲያዩ "*Buenos noches* " ብለው ጮሁ... እኔም ጠጋ ብዬ "እንዴት ናችሁ?... ሰላም አመሻችሁ፤ ብዬ ላልፍ ስል ከመሀከላቸው አንዱ" ና ተቀላቀለን እንጂ" አለኝ። እኔም እምቢ ማለት ስለከበደኝ ከእነዚያ ጥሩ አሳቢ ሰዎች ጋር ቁጭ ለማለት ተገደድኩ። አብሬያቸው ከተቀመጥኩ በኋላ ሁሉም አትኩሮቱን እኔ ላይ በማድረግ

አንዳንድ ጥያቄዎችን መጠየቅ ጀመሩ፡፡ አንዱ "ሚስት የምትሆንህን ቆንጆ ሴት አገኘህ?" ሲል ሌላው "ኮንቺታ ፒኮሊኖን በደንብ እየተንከባከበችው ነው?" ይላል... እሱን መልሼ ስጨርስ ደግሞ አንዱ ምናልባት ገንዘብ ያስፈልገኝ እንደሆን ይጠይቀኛል፡፡ እኔም ለሁሉም ጥያቄዎች እንዳመጣጣቸው እመልስ ነበር፡፡ ለትንሽ ጊዜ ከእነሱ ጋር ከተጫወትኩ በኋላ ወደቤት መግባት ስለፈለኩ ለጠባንበት የእኔንም የእነሱንም ሒሳብ ልከፍል ስል ከመካከላቸው አንዱ "በፍፁም ፈረንሳዊ... አንተማ እንግዳ ነህ... ባይሆን ሌላ ጊዜ ታደርገዋለህ... እግዚአብሔር ካንተ ጋር ይሁን" አለኝ እኔም ለሁሉ ነገር አመስግኜ ወደ ቻርሎቴ ቤት አቀናሁ፡፡ አዎ በእርግጥ ከእንደዚህ አይነት የተረጋጋ ማህበረሰብ የወጣ ፍጡር ትሁት ቢሆን ሊያስገርም አይገባም፡፡ ከየትም መጣህ ከየትም ቀላህ፣ ጠቆርክ፣ ገረጣህ፣ ወዛህ፣ ሀብታም ሆንክ፣ ደሀ ለእዚህ ሀገር ማህበረሰብ እኩል ነው፡፡ ለሁሉም ሰው ተመሳሳይ አክብሮት ይሰጣሉ፡፡ ለእነሱ ክብር ለመስጠት ሰው መሆንህ ብቻ በቂ ነበር፡፡

እቤት እንደደረስኩ ኮንቺታ በፈገግታ ነበር የተቀበለችኝ፡፡ ቻርሎቴ በዚህ ሰዓት በወርቅ ማውጫው ጉድጓድ ውስጥ እየሰራ ነው፡፡ በተቃራኒ ሽፍት ስለምንሰራ እኔ ወደ ስራ ስወጣ እሱ ደግሞ ወደ ቤት ይመለሳል፡፡ ኮንቺታ በመልካምነት የተሞላች እና ደስታ ከፊቷ ፈፅሞ የማይጠፋባት ልጅ ነች፡፡ ከስክስ ጫማዬን ካወለቅሁ በኋላ ኮንቺታ የሰጠችኝን ነጠላ ጫማ አደረኩ፡፡

"ጓደኛህ ተኝቷል... ምግብም በደንብ በልቷል፡፡ ቱማሪዮ ወደሚገኘው ሆስፒታል ፒኮሊኖን እንዲወስዱት የሚያስረዳ ደብዳቤ ልኬአለሁ፡፡ ሆስፒታሉ አሁን ካለንበት ብዙም አይርቅም" አለችኝ፡፡ በወሬ መኃል ብልጭ የሚሉ ጥርሶቿን እያሳየችኝ... ላደረገችው ነገር አመስግኜ እኔን ወደሚጠብቀኝ የምግብ ጠረጴዛ አመራን፡፡

እራታችንን በልተን ከጨረስን በኃላ ግሩም ቡና አፍልታልኝ በመጠጣት ላይ እንዳለን ነበር "እንዴት ዋላችሁ ሰዎች" እያሉ ሁለት ሴቶች እኛ ወዳለንበት ክፍል የገቡት፡፡

"እንዴት ዋላችሁ" አለች ኮንቺታ... ቀጥላም ወደእኔ እየዞረች "ጓደኞቼ ናቸው ተዋወቃቸው" አለችኝ "እሱ ፓፒለን ይባላል"

አንደኛዋ ጠቆር ብላ ረዘም ያለች ስትሆን ግራሴላ ትባላች፡፡ አባቷ ስፓኒሻዊ መሆኑን አውቄአለሁ፡፡ አብራት ያለችው ደግሞ መርሲደስ ትባላለች፡፡ የእሷም ቅድመ አያት ጀርመናዊ ስለነበር ከዘር የወረሰችው ደም የቆዳ ቀለሟን ወደቀይነት ቀይሮታል፣ የፀጉሯም ቀለም ወርቃማ ነበር፡፡ የግራሴላ አይን ጥቁር ሆኖ መኃሉ እንደሚነድ እሳት ቀይ ነው፡፡ የመርሲደስ አይን ደግሞ

አረንጓዴ ነው እንደውም የላሊን አይን አስታውሶኝ ነበር፡፡ ያቺ የጎጂራዋ ህንድ ላሊ… ላሊና ዞራልማ ምን ሆነው ይሆን? እንግዲህ ከተለያየን አስራሁለት አመታት ተቆጥረዋል፡፡ ስለእውነት ሁሌ ስለእነሱ ሳስብ ልቤ ይደማል፡፡ በእርግጠኝነት ግን በእዚህ ሰዓት የእኔ የሚሉትን ወንድ አግኝተው የራሳቸውን ህይወት እየኖሩ መሆን አለበት፡፡ ዳግም ወደእነሱ ህይወት መመለስ ባልችልም ሁሌም ግን ስወዳቸው እኖራለሁ፡፡

"ጓደኞችሽ በጣም አስደሳች ናቸው… ሰላስተዋወቅሽኝ ደስ ብሎኛል" አልኩ ከሀሳቤ ወጥቼ ወደ እነርሱ ለመመለስ ያህል፡፡ ሁለቱም ሴቶች ከባል ነፃ እንደሆኑ እንዲሁም የወንድ ጓደኛ ጭምር እንደሌላቸው ተረዳሁ፡፡ ሁለቱ ሴቶች አብረውን እራት በልተው ትንሽ ከተጫወቱ በኋላ ወደ ቤት ለመሄድ ሲነሱ እኔ እና ኮንቺታም አብረናቸው ወጥተን እስከመንደሩ ጫፍ ድረስ ሸኘናቸው፡፡ ከሸኘት በኋላ ወደቤት በምንመለስበት ሰዓት ኮንቺታ ሁለቱንም ሴቶች እንደወደዱኝ ፊታቸውን አንብባ እንደተረዳች ከገለፀችልኝ በኋላ እኔ የትኛዋን እንደወደድኳት ጠየቀችኝ፡፡

"ሁለቱም ቆንጆዎች ናቸው ኮንቺታ… ነገር ግን ችግር ውስጥ መግባት አልፈልግም"

"ፍቅር መስራትን እንደችግር ነው እንዴ የምታየው?… ፍቅር እኮ ልክ ከመብላትና ከመጠጣት ባልተናነሰ መልኩ ለሰው ልጅ ወሳኝ የሆነ ነገር ነው… ስታስበው ሳንበላ እና ሳንጠጣ መኖር የሚቻል ይመስልሀል እኔ እንደውም ሀያሁለት አመቴ ነው፤ ቢሆንም ግን ፍቅር ሳልሰራ ከቆየሁ ያመኛል፡፡ እነሱ ግን ገና የአስራ ስድስት እና የአስራ ሰባት አመት ልጆች ናቸው፤ ታዲያ በዚህ እድሜያቸው ሰውነታቸው ደስታን ማግኘት ይኖርበታል" በምታዋራኝ ሰዓት ያ ሁሌም የሚማርከው ደማቅ ፈገግታዋ ተሰውሮ ነበር፡፡

"ቤተሰቦቻቸውስ ምን ሊሉ ይችላሉ?"

"እዚህ ማንም እንድትጋባ የሚያስገድድህ የለም… አንዷ ከወደደችህ ልቧን ወዲያው ትሰጥሃለች… ቤተሰቦቿም የሚቀበሉት በደስታ ነው… የሚገርመው ደግሞ እነሱ ካንተ ምንም አለመፈለጋቸው ነው" ብላ ጆዜ ከዚህ በፊት የነገረኝን ተመሳሳይ ንግግር ደገመችልኝ፡፡

"ተረድቼሻለሁ ኮንቺታ… እንግዲህ… ያ የሚጠበቀውን አይነት ወንድ ለመሆን እጥራለሁ" አልኳት

የፈጣሪ ያለህ! ከእንደዚ አይነት ርዕሰ ጉዳይ ለመውጣት በጣም ከባድ ነው። ታዲያ ቻርሎቴ፤አሌክሳንደርና ሲሞን በእነዚህ ደግ አስተሳሰብ ባላቸው ሰዎች የፀባይ ለውጥ በማምጣታቸው ልገረም አይገባም ነበር። በመሰረቱ በእዚህ ኑሮ እጅጉን ተደስተዋል። ለነገሩ ምን ያርጉ እኛ ከምናውቀው ዕርዮተ-አለም ውጪ በሆነ ምድር ላይ እየኖሩ። እቤት እንደደረስንም ድካም ስለተሰማኝ ወደ አልጋዬ ሄጄ ተዘረርኩ።

ጠዋት "ፓፒ… ፓፒ… ተነስ… ፓፒ" የሚለው የኮንቺታ ድምፅ ቀሰቀሰኝ "ሁለት ሰዓት ሆኗል እኮ… ደግሞ ሰው ሊያይህ ይፈልጋል" አለችኝ መንቃቴን ስታረጋግጥ… እኔም መነሳት ባልፈግም ሰው ይፈልግሃል ስለተባልኩ ብቻ እንደምንም እየተጨናበስኩ ከአልጋዬ ላይ ተነስቼ ወደ ሳሎኑ አመራሁ።

"እንዴት አደርክ" አለ አንድ ነጭም ጥቁርም የማይሉት መካከለኛ ቁመት ያለው ዕድሜው ሀምሳዎቹ መጀመሪያ ላይ ያለ ሰውዬ… የአይኖቹ ስልምልም ማለት ሰውዬውን ምስኪን አስመስለውታል። እጁን እየዘረጋልኝ "ዶክተር ቦጋርት እባላለሁ" አለ [በሀያኛው ክፍለዘመን ማርሴል ውስጥ በከፍተኛ ወንጀል የተጠረጠረ ሰው ነበር። በአንድ ወቅት በሚሰራበት ሆስፒታል ውስጥ ባለው የግሉ ክፍሉ ውሰጥ ባለው ቁምሳጥን ውስጥ የሰው ሬሳ ይገኝበታል። ነገሩ ሲጣራም ታካሚው ሊሞት የቻለው ዶክተር ቦጋርት በሰራው ሙያዊ ስህተት ለታካሚው መሰጠት ከሚገባው በላይ የሆነ መድሀኒት በመርፌ በመስጠቱ እንደሆነ ይረጋገጣል። ፍርድ ቤቱ ግን ሆን ተብሎ የተፈፀመ የግድያ ወንጀልነው ብሎ የእድሜ ልክ እስራት ይፈረድበታል። ፍርዱን ተቀብሎ ወደ ሰይጣን ደሴት ከሄደም በኃላም ባገኘው አጋጣሚ አምልጦ ወደ ቬንዙዌላ ካመራ በኃላ ኑሮውን እዚሁ የመሰረተ ወንጀለኛ ነው።]

"የመጣሁት ከእንግዶቹ መሃከል አንዳችሁ መታመማችሁን ተነግሮኝ ነው… እና ማንም ታመመ ማን ወደ ካራካስ ሄዶ አንዱ ሆስፒታል እስካልታከመ ድረስ እዚህ ምንም የሚፈጥረው ነገር እንደሌለ ለመግለፅ ስለፈለግሁ ነው"

"ከእኛ ጋር ለምን ቁርስ አንበላም ዶክተር" አለ ቻርሎቴ በአክብሮት እጅ እየነሳ

"ደስ ይለኛል… አመሰግናለሁ ቻርሎቴ"

ቁርሳችንን እንደነገሩ ቀማመስንና ለጊዜው ምን እንደሆነ ያላወቅሁት ከእንስት ቅጠል የተሰራ ጣፋጭ ጣዕም ያለው ቀለም አልባ መጠጥ በቻርሎቴ ግብዣ ለሁላችንም ከተቀዳልን በኃላጨዋታ ከፍተን በማውራት ላይ ሳለን ነበር ዶክተር ቦጋርት "እሺ ፓፒለን ህይወት እንዴት ይዞሃል ታዲያ" ያለኝ

"ህይወትን እንግዲህ ሀ ብዬ ልጀምር ነው ዶክተር… እንደገና የተወለድኩ ያህል ነው እየተሰማኝ ያለው… ወይም ደግሞ በተቃራኒው ፈጣሪ ለእኔ የሰራልኝን የህይወት መንገድ ወይ እስካሁን ፈልጌ አላገኘሁትም ወይ ደግሞ ከነጭራሹ አልተሰራልኝም ይሆናል" አልኩ እንደመሳቅ እያልኩ።

"መንገዱማ ተሰርቶልሃል ዞር ዞር ማለት ነው ያቃተህ… እኔን ተመልከት ወደ ቬንዙዌላ የመጣሁት በ1928 ዓ.ም ነው። እንግዲህ እኔ እስከማውቀው ድረስ ወደእዚህ አምልጦ የመጣ ማንኛውም ወንጀለኛ እዚህ ከመጣ በኋላ አንዱም ወንጀል ሲፈፅም ሰምቼም አይቼም አላውቅም። ሁሉም አግብተው፣ ልጅ ወልደው ማህበረሰቡ መስለውና ማህበረሰቡን ተቀብለው ነው የሚኖሩት፤ ሁሉም ያለፈውን እረስተው እዚህ የሰላም ኑሮ መስርተዋል። አንዳንዶቹማ እንደውም ምን ሰርተው ወህኒ እንደወረዱ ብትጠይቃቸው አያስታውሱትም። ምክንያቱ ምን መሰለህ ያለፈውን ጭጋጋማ እና ተስፋ አስቆራጭ ጊዜ ረስተው በአዲስ ማንነት አዲስ ህይወት ስለጀመሩ ነው"

እያዳመጥኩት እንደሆነና እንዳልሆነ ለመረዳት ይመስል ጥቂት ፋታ ወስዶ ከተመለከተኝ በኋላ ወሬውን ቀጠለ።

"ስታስበው አንተ ብቻ ይመስልሃል በፊት ያሳለፈውን አስቀያሚ ህይወት ረስቶ ይሄንን አዲስ ሕይወት ለመጀመር የሚጥር?እስኪ ስማኝ ስለአንድ ስለማውቀው አንድ ልጅ ታሪክ ልንገርህ ልብ ብለህ አድምጠኝ… ምን አልባት የምትማርበት ነገር ይኖራል።የልጁ ስም ጆርጅ ዱቦይስ ይባላል። ከአንዲት ምስኪን እናት እና ከአንድ ስለእራሱ ብቻ ከሚያስብ ሰካራም አባት ጋር ላ ቪሌቴ ውስጥ ይኖሩ ነበር. . .ከእሱ ውጪ ሌሎች አምስት ልጆች ስላሉ ለእናታቸው ኑሮ በጣም ከባድ ሆኖባት ነበር" ካለኝ በኃላ ወሬውን ቆም አድርጎ "ይሄንን ታሪክ እዚህ ላይ ያዝልኝና… ሌላ በቅፅል ስሙ 'ጆ' እያሉ የሚጠሩት ከአንድ ከድሃ ቤተሰብ የወጣ ልጅ በዛ አስቸጋሪ ፀባዩ የሰፈሩን ሰው እያመሰ አስቸግሮ ነበር… በፀባዩም ምክንያት ገና በስምንት አመቱ የፀባይ ማረሚያ ሊገባ ችሏል.። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም ከአንዱ ፀባይ ማረሚያ ወደአንዱ ሲዘዋወር ነበር የኖረው። መጀመሪያ ሰፈሩን መረበሽ የጀመረው መንገድ ላይ የተለያዩ ፍራፍሬዎችን የሚሸጡትን ነጋዴዎች በመዝረፍ ነው። ምንም ቢደረግ ፀባዩን ማረም ስላልተቻለ በመጨረሻ በጥብቅነቱ ወደሚነገርለት የህፃናት ፀባይ ማረሚያ እንዲገባ ተደረገ። ይህ ገና በቅጡ እንኳን አስራ አራት አመት ያልሞላው ልጅ ወደ አዲሱ ማረሚያ ከገባ በኋላም አላረፈም። እድሜያቸው ከእሱ ጋር ፈፅሞ ከማይገናኝ አስራስምንትና አስራዘጠኝ ዓመት ከሚሆናቸው ልጆች ጋር ፀብ ይጀምራል. . .ታዲያ ፀባቸው ከሮ በመጨረሻ ጩቤ ለመማዘዝ ይበቃሉ… በጥላቻውም መሀከል ጆ ያንዱን ሆድ እቃ ሊዘረግፈው ቻለ። በእዚህ ስራው እስር የሚገባው ቢሆንም በእድሜው

ምክንያት ወደእስር ቤት ከመውሰድ ይልቅ ወደ አንድ ኢሴ ወደተባለ እጅግ ጥብቅ የሆነ ቁጥጥር ወደሚደረግበት የህፃናት ፀባይ ማረሚያ አስገቡት። በዚያም ድርጅት ውስጥ ሀያአንድ አመት እስኪሞላው ድረስም ማረሚያ ውስጥ አሳለፈ። ገና በሀያ አንድ አመቱ በብዙ ወንጀሎች ላይ ንኪኪ ስለነበረበት የጦር ሰራዊት አባል የመሆን ፍላጎቱን ሊያሳካ አልቻለም። ታዲያ በአንዱ ቀን እዛው በሚኖርበት አካባቢ ካለው የባቡር ጣቢያ አካባቢ እየተራመደ ራሱን በማዝናናት ላይ እንዳለ ወደ ፓሪስ የሚወስደው ባቡር አጠገቡ ይቆማል። በውስጡም ዝም ብለህ ግባ...ግባ የሚል ስሜት ይፈጠርበታል... ስለዚህ ባቡሩ ለመንቀሳቀስ ጥቂት ሰከንዶች ሲቀሩት ወደ ባቡሩ ዘሎ ይገባል... ፓሪስ ሲደርስም ኃይለኛ ደፍ ዝናብ እየጣለ ስለነበር ወደ አንዱ መጠለያ ፈልጎ ይጠለላል።በሀሳቡም እንዴት አድርጎ በፊት ወደሚያውቃት የትውልድ መንደሩ ወደሆነችው ላ ቪሌቱ መሄድ እንደሚችል እያውጠነጠነ ነበር... ታዲያ እሱ ያላስተዋለው ነገር እሱ የተጠለለበት ቦታ ላይ እንደሱ ዝናቡን ፈርታ የተጠለለች ልጅ መኖሯን ነው...ከሀሳቡ ሲነቃም መጠለያ ቦታው ላይ ያለው እሱ ብቻ እንዳልሆነ ይመለከታል. . .ወደ እሷሲ ዞሮም ልጅቷም በተመሳሳይ ሁኔታ እየተመለከተችው መሆኑን ይረዳል. . .ይግረምህ ብላም የሚያምሩ ጥርሶቿን ታሳየው ጀመር... እሱ ሴት የሚያውቀው ኢሴ የህፃናት ፀባይ ማረሚያ ውስጥ በነበረበት ጊዜ የድርጅቱን ዋና አዛዥ ሚስት ብቻ ነበር... እዛ በነበረበት ጊዜ ታላላቆቹ ሁሌም የሚነግሩት ነገር ቢኖር የትኛዋም ሴት በእሱ መልክ የምትማረክ ሴት እንደማትኖር ነበር። ያም ሆነ ይህ ከልጅቷ ጋር ማውራት ጀመሩ

ከየት ነው የመጣሽው?" እሷ ነበር ጨዋታን የጀመረችው በልጁ ተክለሰውነትና መልክ ሳትደመም አልቀረችም

እሱም እንደመቀለድ "ከሀገር" ይላታል

"ሀ.. ሀ.. ሀ ጨዋታ ትችላለህ ባክህ... ለምን ወደ አንዱ ሆቴል ሄደን ይሔን ደፍ ዝናብ ያመጣውን ቅዝቃዜ በሞቀው አልጋ ላይ አናጠፋውም" አለችው ስለማንነቱ እንኳን ሳትጨነቅ

እሱም ምንም እንኳን የማያውቃት ሴት ብትሆንም እንደዚህ አይነት እድል መቼም ሊያገኝ እንደማይችልና በዛ ላይ ልጅቷም ቆንጆ ስለሆነች ባቀረበችው ሃሳብ ወዲያው ነበር የተስማማው... ለልጁ የመጀመሪያው ጣፋጭ እና አስደሳች ምሽት መሆኑ ነው። ልጅቷ ደግሞ የሚያምር ስብዕና ከተሟላ ተክለ ሰውነት ጋር የታደለች ነበረች። ገና ወደ ክፍሉ እንደገቡ ነበር የቀዘቀዘው ሰውነታቸው እንደ ፍም እሳት በሚያቃጥል የውስጥ ንዝረት የተተካው... ለእሱ ደግሞ ሁሉም ነገር አዲስ ነው... ሌሊቱን በሙሉ ያለማቋረጥ በሚያስብል ፡

ደረጃ ዛሬ እንደተገናኙ ሰዎች ሳይሆን ለረጅም ጊዜ እንዳልተገናኙ ፍቅረኛሞች ነበር በወሲብ እሳት ነደው ያደሩት፡፡

በመጨረሻም ማረፍ ስለፈለጉ እዛው አልጋ ላይ እንደሆኑ ሲጋራቸውን ለኩሰው ማውጋት ጀመሩ፡፡

"ከሴት ጋር አልጋ ላይ ስትወጣ ይህ የመጀመሪያህ ነው እንዴ?"

"አዎ" አለ ከእዚህ በፊት አይቷት ባያውቅም ይህንን የመሰለ አለም ያሳየችውን ሴት መዋሸት ስለከበደው

"ለምንድነው ግን ይህን ያህል ጊዜ ያለ ሴት የቆየኸው?"

"አብዛኛውን እድሜዬን ያሳለፍኩት በፀባይ ማረሚያ ተቋም ውስጥ ነበር ... ለዛ ይሆናላ"

"ለረጅም ጊዜ በፀባይ ማረሚያዎች አሳልፈሃላ"

"አዎ ለረጅም ጊዜ"

"በአንድ ወቅት እኔም ገብቼ ነበር... አምልጬ ነው"

"ስንት አመትሽ ነው?"

"አስራስምንት"

"ከየት ነው የመጣሽው?"

"ከ ላ ቪሌቴ"

"ከየትኛው ሰፈር?"

"*Rue de Rouen*"

ጆ የሰፈሩን ስም በሰማ ጊዜ ሰውነቱን የሆነ ሽብር ሲወረው ይታወቀዋል

"ማነው ስምሽ?"

"ጂኔቴ ዱቢየስ"

የእዛች ስድስት ልጆች ያሏት የምስኪን እናት ልጆች መጀመሪያ ባለመተዋወቃቸው ምክንያት አንድ አልጋ ላይ ሲተኙ በቅተዋል፡፡ጆ ይህንን ከሚስማ መሬት ተከፍታ ብትውጠው ይመርጥ ነበር፡፡በአይኖቹ ላይ የቀረሩትን የእንባ ዘለላዎች ዱብ፣ዱብ እያሉ መውረድ ጀመሩ፡፡በማያቋርጥ የእንባ ጎርፍ ታጠቡ… አንሶላ ለመጋፈፍ ያደረጉት መጣደፍ ወንድምና እህትን በአንድ አልጋ ላይ እንዲተኙ አድርጓቸዋል… ሁለቱም ከመደናገጣቸውም እና በስራቸው በማፈራቸው አይን ለአይን እንኳን ለመተያየት ድፍረት አጡ…ዝም ብለው መላቀስ ብቻ!!… ምንም እንኳን ለመረጋጋት አቅም ቢያጡም ከብዙ ለቅሶ በኋላ ወደ እራሳቸው ተመልሰው ምን አይነት የህይወት ጎዞ አሳልፈው እንደመጡ አንዳቸው ለአንዳቸው መተረክ ጀመሩ… ልክ እንደሱ ሁሉ እሷና እህቶቿም አብዛኛውን ጊዜያቸውን በፀባይ ማረሚያ ውስጥ እንዳሳለፉ እና እናታቸው ደግሞ በጠና ስለታመመች ወደ ሆስፒታል መግባቷን ታላቅ እህታቸው ደግሞ እዚሁ ላ ቪሌቴ ውስጥ ሴተኛ አዳሪ ሆና እየሰራች መሆኑን ነገረችው፡፡

በዚህም መሰረት ታላቅ እህታቸውን ማየት ስለፈለጉ በጠዋት ሆቴሉን እንደዛው እንደተዝረከረከ ለቀው ሊወጡ ሲሉ የሆቴሉ ባለቤት ከፊት ለፊታቸው ይመጣል፡፡

"አንቺ ቀጫጫ ሸርሙጣ ድጋሚ እዚህ እንዳላይሽ ብዬ አልነገርኩሽም… ዛሬማ የምለቅሽ እንዳይመስልሽ ስብርብርሽን ነው የማወጣው" ብሎ ወደእነሱ መጠጋት ይጀምራል፡፡

የሆቴሉ ባለቤት የተናገራቸው ነገሮች ለ ጆ ከአቅሙ በላይ የሆኑ ፀያፍ ንግግሮች ነበሩ… ከእዚህ በፊት ወደ ጦር ሰራዊት አገባለው በሚል ተስፋ ሁሌም ከጎኑ የማይለየውን ታጣፊ ጩቤ ከኪሱ ከመቅፅበት አውጥቶ እህቱን ያንቋሸሻትን የዛን ሆቴል ባለቤት ደረት ላይ ይቀረቅረዋል፡፡

የሞት ፍርድ ተፈርዶበት ነበር… ነገር ግን በሀገሪቱ ፕሬዝዳንት ምክንያት የሞት ፍርዱ ወደ የእድሜ ልክ እስራት ተቀይሮለት ወደ ወህኒ ይወርዳል፡፡

አሁን ግን ይገርምሃል ከእስር አምልጦ ምስራቅ ቬንዙዌላ ውስጥ በምትገኘው ኩማና የምትባል ከተማ ውስጥ እየኖረ ይገኛል፡፡ ከዛን ጊዜ ጀምሮም ጫማ በመስራት የሚተዳደር ሲሆን ሚስት አግብቶም ሁለት ልጆች ለመውለድ በቅቷል፡፡

ሁለቱንም ልጆቹ በእንክብካቤ ከማሳደጉም በላይ ትምህርታቸው እንዲከታተሉ አድርጓል፡፡ የመጀመሪያ ልጁም በዚህ ዓመት ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም

ትገባለች፡፡ ኩማና በሄድኩ ቁጥር አንድም ቀን ሳላያቸው ተመልሼ አላውቅም... እና ይሄን ሁሉ ታሪክ ያወራሁት የሰው ልጅ በህይወት ሲኖር ሊያጋጥሙት የሚችሉ ብዙ ችግሮች ይኖራሉ ያ ሳይሆን ቁምነገሩ ተስፋ ባለመቁረጥና በትዕግስት የደረሰብንን ነገር መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ እንግዲህ ጆ ያሳለፈውን ያን አሰቀያሚ ህይወት ረስቶ አሁን ከልጆቹ እና ከባለቤቱ ጋር በደስታ እየኖረ ነው፡፡ እዚህ አብዛኞቻችን በሕይወታችን ለደረሰብን ግፍ ብቀላ የምንፈልግ ሰዎች ነን... ነገር ግን እኔ እስከማውቀው ድረስ የብቀላ ውጥኑን ለመፈፀም ከእዚህ ሀገር የወጣ አንድም ሰው አለመኖሩን ነው... ምክንያቱ ደግሞ እዚህ ሀገር ላይ በነፃነትና በሰላም መኖር ስለቻልን ነው፡፡ በዛ ላይ እዚህ ያለው ማህበረሰብ አስተሳሰቡ ሲበዛ ቀና ነው፡፡ የፈለከውን እየሰራህ ጥሩ ሕይወት መኖር ትችላለህ... በቃ እኔ ልልህ የምችለው ይሄንን ነው" አለኝ

ቦጋርት ይህንን የጆርጅ ዱቢየስን ታሪክ ከነገረን ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሌላ ጊዜ ለመገናኘት ቀጠሮ ይዘን ተለያየን፡፡ ቦጋርት ቢሄድም የሱ ንግግሮች ግን አዕምሮዬ ውስጥ ቀርተው ነበር፡፡ ለሀገር ያስቸገሩ እጆቻቸው በወንጀል የተጨማለቀ ሰዎች ከእነዚህ በአመዛኙ ዘመናዊነትን ካልተላበሱ ማህበረሰብ ጋር ለመኖር መምረጣቸው የራሱ የሆነ ቁልፍ ሚስጥር አለው፡፡ በተለይ ዶክተር ቦጋርት ከአንድ በነፍስ ማጥፋት ከተወነጀለ ሰው እንዲህ ወደመሰለው ጨዋነት የተላበሰ ትሁት ሰውነት መቀየር መቻሉ ለማመን የከበደኝ ነገር ነው፡፡ ታዲያ እኔስ ለአመታት ሳስበውና እስካደርገው የጓጓሁለትን የበቀል እቅዴን እርግፍ አድርጌ ትቼ አርፌ ከእነዚህ ደጋግ ፍጡሮች ጋር ልኑር እንዴ? ልቤ በሁለት ሃሳብ ውስጥ መዋዠቅ ጀምሯል፡፡

* * * * * * * *

በሚቀጥለው ቀን የስራ ቦታዬ ላይ ተገኝቼ አግዳሚ ወንበሬ ላይ ቁጭ ብዬ የውሃ ማውጫ ማሽኑን መቆጣጠሩን ተያይዤዋለሁ፡፡ ዛሬ ማሽኖቹም ያለአንዳች ብልሽት ስራቸውን እያከናወኑ ነው፡፡ ለስሙ ተቀምጬ አይኖቼን ማሽኑ ላይ ላድርግ እንጂ አዕምሮዬ ውስጥ ውስጡን የሚያስበው ግን ሌላ ነው፡፡ 'ፓፒ ሁሉን እረስተህ እዚህ የራስህን አዲስ ሕይወት መስርተህ መኖር ይዋጥልሃል?'... አይሆንም! ከቬንዙዌላውያን ጋር መኖር የሚያስደስት ቢሆንም እኔ ግን ለእንደዚህ አይነት ኑሮ ዝግጁ የሆንኩ ያህል አይሰማኝም ፡፡

ስራዬን እንደጨረስኩ ከዋሻው በሚያስወጣው አሳንሰር ወደ ምድር ወጣሁ፡፡ ያንን ለደቂቃ እንኳን ከአእምሮዬ ሊወጣ ያልቻለውን ያንን የወርቅ ክምር

ላለማየት ለግምጃ ቤቱ ጀርባዬን ሰጥቼ ወደ ቤት የሚወስደኝን መንገድ ተያያዝኩት። ቤት ስደርስ ኮንቺታ እንደተለመደው በደማቅ ፈገግታ ነበር የተቀበለችኝ። "ደህና ዋልክ ፓፒለን... ውሎ እንዴት ነበር?" ለመልስ እንኳን ፋታ ሳትሰጠኝ "ቻርሎቴ ከእዚህ በፊት ችግር ውስጥ እንደነበርክ ነግሮኛል... ምንድነው ችግሩ ፓፒ?... ልትነግረኝ ትችላለህ፤ ግራሴላን ልጥራት ወይስ መርሲደስን... ኧ?... የትኛዋን ትመርጣለህ?... ምን ታስባለህ?" ውስጧ ለእኔ እንደተጨነቀች ያስታውቃል። እሷ ታወራለች እንጂ መልስ አትጠብቅም። በቃ አማራጭ የሚመስለኝን ነገር እንድነግራት ነው ፍላጎቷ።

"ኮንቺታ የኔ ጥቁሯ የኢልሴሎ ቆንጆ... በጣም እኮ ግሩም ልጅ ነሽ... ቻርሎቴ ለምን እንደ ጣኦት እንደሚያመልክሽ አሁን ነው የገባኝ!... ኮንቺታ አንቺ ልክ ሳቶኚ አትቀሪም... ሲመስለኝ ሴት ሳያስፈልገኝ አይቀርም"

"በእርግጠኝነት!... ቻርሎቴ ልክ እስካልሆነ ድረስ"

"ምን ማለትሽ ነው?"

"የእኔ ሀሳብማ በዚህ ሰዓት ላንተ የሚያስፈልግህ ነገር አንዲት ቆንጆ ሴት ነች የሚል ነው... ይመስለኛል ግን ነገሩ ሌላ ነው"

"ነገሩ ሌላ ነው ስትይ... ምን ማለትሽ ነው?"

በነገሩ ትንሽ ካቅማማች በኋላ "ለቻርሎቴ ብትነግረውም ንገረው አይደንቀኝም... ነገር ግን አላማህ እዚህ ቤተሰብ መስርቶ ለመኖር እንዳልሆነ አውቃለሁ"

"ተማመኝብኝ አልነግረውም"

"ጥሩ እሺ... ቻርሎቴ እንዳለው ከሆነ እዚህ መኖርን ምርጫህ ያደረከው እንደሌሎቹ ትዳር መስርቶ ለመኖር ሳይሆን ላሰብከው የበቀል እቅድህ የሚሆን ብር እስክታገኝ ድረስ ብቻ እዚህ ሀገር ላይ እንደምትቆይና አሁን የምትሰራበት የወርቅ ማውጫ ድርጅት ውስጥ ያለውን ያንን የወርቅ ክምር ልክ እንደ አንዱ የገንዘብ ምንጭህ ማድረግ እንደምትፈልግ ነበር የነገረኝ" አለችኝ አንዲትም ነገር ሳትደብቀኝ

"ኮንቺታ... ቻርሎቴ ተሳስቷል አንቺ ነሽ ትክክል... የእኔ ሀሳብ አንቺ እንደገመትሽው ነው አልኩ" ድንጋጤዬን ለመደበቅ እየሞከርኩ።

"እንዲህ በቀላሉ የማምንህ ይመስልሃል?"

"እሺ... አንቺ የመረጥሽልኝን ሴት ይዘሽልኝ ነይ... ከዛ እንዴት ደስተኛ እንደምሆን ታያለሽ" አልኳት ለማሳመን እየሞከርኩ

"በጣም ጥሩ... እሱን እንግዲህ አብረን የምናየው ይሆናል ካለች በኃላ ልብሷን ለመቀየር ወደ መኝታ ክፍሏ ገባች። በዚህ ቅፅበት የቤቱ በር ስለተንኳኳ ወደ በሩ ሄጄ ከፈትኩ። በሩ ላይ የቆመውን ሰው በማየቴም በጣም ተደንቄ ፊቴ በደስታ ወረዛ... ማሪያ ነበረች።

"እንዴ ማሪያ?!!... በጣም የሚገርም ነው... በእዚህ ምሽት እንዴት ተከሰትሽ ባክሽ? ነይ ግቢ" አልኳት እጇን ይዤ ወደ ውስጥ እየጎተትኳት

"ማነው ባክህ በዚህ ሰዓት የመጣው?" አለች ኮንቺታ ከክፍሏ እየወጣች

"ኮንቺታ ማሪያ እሷ ነች እንደውም እኔን እና ፒኮሊኖን እግራችን ኢል ሴሎ ላይ እንደረገጠ ወደ ቤቷ ይዛን የሄደችው ልጅ"

"አዎ አስታወስኩ ነይ እስኪ ልሳምሽ" አለች ኮንቺታ ቀጥላም "እውነትም ፓፒለን እንዳወራልሽ በጣም ውብ ሴት ነሽ"

"ማነው ደግሞ ፓፒለን?" አለች ማሪያ የለመደችው ስም ስለነበር በመደናገር ስሜት

"እኔው ነኝ ማሪያ... ያው ፓፒለንም ኢኒሪክም የእኔ ስም ነው... እስኪ ነይ ቁጭ በይና ስለ ሁሉም ነገር አጫውቺኝ"

ኮንቺታ የማውቀውን ሳቅ እየሳቀች "ይመስለኛል ውጪ መውጣት የሚጠበቅብኝ አይመስለኝም" አለች

ማሪያ ምሽቱን ሙሉ ከእኛ ጋር አሳለፈች። በጣም አይናፋር ብትሆንም በጨዋታችን መኃከል አስተያየት ለሚያስፈልገው ማንኛውም ነገር ግን በድፍረት ትመልስ ነበር።

ሦስታችንም ለሁለት ሰዓት ያህል የሞቀ ጨዋታ ከተጫወትን በኋላ መተኛት ስለነበረብን ኮንቺታም ወደክፍሏ እኔና ማሪያም ወደእኔ ክፍል አመራን። ለማሪያ እንግዲህ የመጀመሪያዋ ወንድ መሆኔ ነው። በአንፖል ፋንታ የለኮስኳቸው ሁለት ሻማዎች ማሪያ የለበሰችው ስስ ልብስን አልፈው ምትሀታዊ ገላዋን አፍክቶ ነበር ያሰየኝ። የፀጉሯ አደፋፍ፣የዳሌዋ ስፋት ብቻ ሁሉ ነገሯ በጣም ያስጎመጅ ነበር፤ ያቺ ሌሊት በጣም ጣፋጭ ስሜት ነበራት።

ያንን በእጅ ቢነኩት የሚቆሸሽ የሚመስለውን የማሪያን ቆዳ እንደፈለኩ የዳሰስኩበት ሌሊት ነበር፡፡ ልክ ከሌሊቱ አስር ሰዓት አካባቢ ከእንቅልፊ ስለነቃሁ ቡና ለማፍላት ወደኩሽናው ሄድኩ፡፡ ቡናውን ለማፍላት ስንጎራደድ ሳላስበው ጠረጴዛ ላይ የነበረውን አንድ ድስት ስለነካሁት መሬት ላይ ወድቆ ድምፅ ስለፈጠረ ኮንቺታን ሊቀሰቅሳት ቻለ፡፡ ወደ ኩሽናውም መጥታም

"ቡና ፈልገህ ነው?"

"አዎ… ይቅርታ ሳላስበው ቀሰቀስኩሽ"

"ኧረ ችግር የለውም… እርግጠኛ ነኝ ቡናው ለአንተ ብቻ መሆን አለበት… መቼም እሷ ለመጀመሪያ ጊዜ ባሳየቻት አዲስ አለም የተነሳ ነገም የምትነሳ አይመስለኝም" አለች እየሳቀች

"ስለሁሉም ነገር ታውቂ ኖሯል?" አልኳት እኔም እንደመሳቅ እያልኩ

"እዚህ ድብቅ የሚባል ነገር የለም… የእኔ ሰዎች በደም ስራቸው ውስጥ እሳት አለ… ያን ደግሞ በዛሬው አዳርህ ሳታስተውል አትቀርም፡፡ ማሪያ የጥቁር፣ የህንድ እና የስፓኒሽ ዘር ያለባት ልጅ ነች፡፡ በዚህ ቅልቅል ደግሞ ደስተኛ ካልሆንክ ሄደህ እራስህን ማንጠልጠል ትችላለህ" ብላኝ በረጅሙ ሳቀች፡፡

ጠዋት ፀሃይ ጨለማውን ገፋ መውጣት እንደጀመረች ማሪያ ከአልጋ ሳትወርድ ቡና ይዤላት ሄድኩ፡፡ ስታየኝ በስስት ፈገግታ ተቀበለችኝ እኔም ቡናውን እየሰጠኋት "ቤተሰቦችሽ ከቤት ሲያጡሽ አይደነግጡም?"

"እህቶቼ ያውቃሉ… ይህ ማለት ደግሞ አባቴም ማወቁ አይቀርም ማለት ነው… ምነው መልሰህ ልትልከኝ ነው እንዴ?"

"አይደለም ውዴ… እስከፈለግሽው ጊዜ መቆየት ትችያለሽ"

ከጠዋቱ አስራሁለት ሰዓት ሊሆን ነው፡፡ ወደ ስራ መሔድ ስለነበረብኝ ማሪያ ከስራ መልስ ተመልሳ እንድትመጣ ከተነጋገረን በኋላ በአንዱ የጭነት መኪና ተሳፍራ ወደቤቷ ሄደች፡፡

ከስራ በኋላም ቤት እንደደረስኩ ማሪያ ቀድማኝ ደርሳ ኖሮ ሮጣ መጥታ አቀፈችኝ፡፡ ቻርሎቴንም የመኝታ ቤቱ በር ላይ ቆሞ ስላገኘሁት ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ በፈረንሳይኛ እንዲህ አለኝ

"ይመስለኛል በህይወትህ የምትፈልጋትን ሴት ሳታገኝ አልቀረህም... በእዚህ ደግሞ እጅጉን ተደስቻለሁ... ስለዚህ ይህንን በማስመልከት ያሁኑ እሁድ መጠነኛ የእራት ፕሮግራም ይዘጋጃል" ካለኝ በኋላ ወደ ማሪያ ዞሮ "ማሪያ ለአባትሽና እና ለእህቶችሽ የሚቀጥለው እሁድ እዚህ ቤት ተሰባስበን እንደምናሳልፍ ንገሪያቸው" ብሎ ወደ መኝታ ቤቱ ተመለሰ

እኔና ማሪያ በቀረችን ጊዜ የከተማዋን መንገዶች ላይ እጅ ለእጅ እንደተያያዝን ቀስ እያልን በመራመድ ንፁህ አየር መቀበል ጀመርን፡፡ ማሪያን ይዣት የወጣሁት አየር ለመቀበል ብቻ ሳይሆን በእዚህ አጋጣሚ በከተማዋ ላይ ያሉ ወይዛዝርት ማሪያ የእኔ እንደሆነች እንዲያወቁልኝ በማሰብም ጭምር ነው፡፡

በቀጣዩ ቀን በስራ ቦታዬ ላይ ቁጭ ብዬ የውሃ ማውጫውን እየተቆጣጠርኩ እንዳለ በአእምሮዬ ላይ አንድ ሃሳብ አቃጨለብኝ 'ለምንድነው ቻርሎቴ ስለወርቁ ያሰብኩትን ነገር ለሌላ ሰው መንገር የፈለገው?' አልገባኝም፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ሲሞንም በእዚያ በወርቅ ግምዣ ቤቱ ውስጥ ስላወራነው ነገር ለቻርሎቴ ሳይነግረው አይቀርም ማለት ነው፡፡ በእርግጠኝነት ደግሞ ጓደኛው ስለሆነ አይነግረውም ብዬ አላስብም፡፡ አሁን እንግዲህ ሁሉም ነገር ፍርጥርጥ ያለ ይመስለኛል፡፡ ሁሉም እዚህ ኑሮ የመሰረቱ ወንጀለኞች ይህንን ቀላልና ምቹ ህይወት ወደውታል ስለዚህ በእሱ መፍረድ አይቻልም፡፡ በእኔም ላይ መፍረድ አይችሉም፡፡ በእነሱ ሀሳብ እቺ እግሬ ኢል ሴሎን ሲረግጥ ያገኘኂት ባለጥቁር ፀጉር ቆንጆ የዘወትር ህልሜ የሆነውን የብቀላ አላማዬን አስረስታ እንደ እነርሱ እዚሁ የሰላም ኑሮ እንድኖር የምታደርግ መሰሏቸዋል፡፡

ስለዚህ አንድ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ ውስጤ ነግሮኛል፡፡ የምፈልገውን ነገር እስካገኝ ድረስ እነዚህ ሰዎች በእኔ ላይ ያላቸውን እምነት እንዲጨምር ማድረግ ይኖርብኛል፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ በህይወቴ ውስጥ ማሪያን ማካተት እንደምፈልግና ቀሪው ህይወቴን ከእሷ ጋር መቀጠል እንደምፈልግ ሁሉንም ማሳመን ስችል ነው፡፡ አለበለዚያ ነገር መበላሸቱ ነው!

በሚቀጥለው ቀን ቻርሎቴን ከግቢው ጓሮ ስላገኘሁት "እንዴት ነው ግብዣው እንደታቀደለት ነው አይደል አልኩት"

"በሚገባ እንጂ ፓፒ"

"ጥሩ... ከተሰባሰብን ላይቀር ሲሞንን እና አሌክሳንደርን ከእነቤተሰቦቻቸው ልጠራቸው አስቢያለሁ" አልኩት

ትክ ብሎ ከተመለከተኝ በኋላ "እንዴት ደስ የሚል ሀሳብ ነው ጓደኛዬ" ብሎኝ ሌላ ምንም ነገር ሳይናገር ወደቤት ተነስቶ ገባ። እኔም ወደ ግምጃ ቤቱ ሄጄ ለሲሞን ስላሰብነው የእራት ዝግጅት በመንገር አሌክሳንደርንም ይዞት እንዲመጣ አሳስቤው ተለያየን።

የእራት ግብዣው ካሰብኩት በላይ ድንቅ ነበር። የተጠሩት ሁሉም እንግዶች ተገኝተዋል። ጆዜ እኔና ማሪያን በምርቃት አንበሸበሸን። የማሪያ እህቶችም ከብ ሰርተው እየተጫወቱና እየተሳሳቁ ያወራሉ። ሲሞንም ከእነሙሉ ቤተሰቦቹ ተገኝቷል። አሌክሳንደርም ያንን ወርቅ የመጠበቅ ተራው የእሱ ቢሆንም በሱ ቦታ ሌላ ሰው ተክቶ ከእነቤተሰቦቹ ተገኝቶ ነበር። ሁሉም ከጎኑ ካለው ሰው ጋር የሞቀ ጨዋታ ከፍቶ እያወጋ ነው። ለእራት ምርጥ ተደርጎ የተጠበሰ የጥንቸል ስጋ ከሚጣፍጥ ወይን ጋር ተመገብን። ከእሱ በተጨማሪ ለዝግጅቱ ማድመቂያ እንዲሆን ተብሎ ተዘጋጅቶ የነበረውን በልብ ቅርፅ የተሰራውን ኬክ በእኔና በሪታ አማካኝነት ከተቆረሰ በኋላ ለሁሉም እንዲዳረስ ተደረገ። ከተበላና ከተጠጣ በኋ ላም ሬዲዮ ከፍተን በአንዱ ሙዚቃ መጨፈር ጀመርን።

ከብዙ መጠጥ እና ጨዋታ በኋላ እነቻርሎቴ ወደ ተቀመጡበት ቦታ ሄጄ ወሬ ጀመርኩ።

"አሁንስ… እንዴት ነው ቻርሎቴ በእኔ ላይ ያለችሁ ጥርጣሬ እንደ ጉም ተኖ አልጠፋም?"

"በሚገባ እንጂ ጓደኛዬ… በእርግጥ ያንን ግምዣ ቤት ውስጥ ያየኸውን ወርቅ ለመውሰድ አስበህ ነበር አይደል ፓፒ?"

"አዎ… ለምን አላስብ… አስበው እስኪ ለአስራ አራት አመት ስለ ብቀላ እቅድ ሳወጣ እና ሳወርድ ነው የኖርኩት። እነዚያን አስራ አራት ዓመታትን እስኪ በሦስት መቶ ስልሳ አምስት ቀን አብዛው ያንን እንደገና በሀያአራት ሰዓታት አብዛው ከዛ ደግሞ በስልሳ ደቂቃ አብዛው… ከዛን ምን ያህል ለብቀላ እቅዴ ቀን ከሌሊት ሳልተኛ በጉጉት እንደጠበቅሁ ትረዳኛለህ… ስለዚህ ያንን የወርቅ ክምር ሳይ ብጓጓ ሊገርማችሁ አይገባም"

"እና አሁንስ?" አለ ሲሞን

"አሁንማ ነገሮችን በተለያየ አቅጣጫ ከተመለከትኩ በኋላ ከእዚህ ደስታንና ፍቅርን ከሰጠኝ ማህበረሰብ ላይ ዘርፌ ሀዘን ማምጣት አሳፋሪ እና አላስፈላጊ ድርጊት እንደሆነ ተረዳሁ… ስለዚህ ከወርቆቹ በፊት እራሴን መግዛት አስፈላጊ

እንደሆነ ተገነዘብኩ… ይህ ሲገባኝ ስለወርቆቹ ከእዚህ በኋላ ላለማሰብ ለራሴ ቃል ገባሁ… ይህ ደሞ ቃሌ ነው ልትተማመኑብኝ ትችላላችሁ"

"በጣም ጥሩ ፓፒ" አለ ቻርሎቴ ፊቱ ላይ የእርካታ ስሜት እየተነበበት አስከትሎም "አሁን እንግዲህ ሁላችንም የሰላም እንቅልፍ መተኛት እንችላለን… እረጅም እድሜ ለፍቅርና ለነፃነት!" ብሎ የያዘውን መጠጥ ከፍ ሲያደርግ ሁላችንም እሱን ተከትለን ብርጭቆአችንን ከፍ ካደረግን በኋላ ተጎነጨን።

እንግዲህ እዚህ ከማጣሁ ስድስት ወር ሆነኝ። ቻርሎቴ ትክክል ነበር። ከዛች ግብዣ ከተከናወነበት ሰዓት አንስቶ ስለወርቅ ማሰቡን ትቸዋለሁ። በመጨረሻም ምስጋና ለውድ ጓደኛዬ ይግባውና ወርቁን የመዝረፍ ፍላጎቴ ቀስ በቀስ ሙሉ ለሙሉ ከአእምሮዬ ተወግዷል። ቢሆንም ግን ውስጤ ሰላም ነው ለማለት አልችልም። ምንም እንኳን ወርቁን የመዝረፍ ፍላጎቴን ብተወውም ሌላ ገንዘብ የማገኝበትን መንገድ ፈልጌ ወደ ፓሪስ መሄድ እንደሚኖርብኝ ግን አምናለሁ። በእዚህም ሊያጋጥመኝ የሚችለውን ማንኛውም ፈተና ራሴን አዘጋጅቻለሁ።

ቡም… ቡም… ቡም የውሃ ማውጫው ማሽን የሚያወጣውን ድምፅ እየሰማሁ ቁጭ ብያለሁ። የዛሬው ሙቀት ደግሞ የተለየ ነበር። ሙቀት ሳይሆን ንዳድ ነው ብል ማጋነን አይሆንብኝም። በእርግጠኝነትም ከሰዓት ዝናብ መዝነቡ እንደማይቀር አሁን በመፋጀት ላይ ያለችውን ፀሀይን ተመልክቶ መገመት ይቻላል። ስራዬን እንደጨረስኩ ትንሽ ግዜ ከእነማሪያ ጋር ማሳለፍ ስለፈለኩ ወደ ኢል ሴሎ አመራሁ። ፒኮሊኖ ለህክምናው ቅርበት ሲባል ከእነቻርሎቴ ወደ ኢል ሴሎ ከሄደ አንድ ወር ሊሆነው ነው። እዛ ያሉት ዶክተሮችም እነ ማሪያ ቤት ድረስ እየመጡ አቅማቸው የፈቀደውን ያክል ፒኮሊኖን ከያዘው በሽታ ለማዳን ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ከጀመሩ ቆየት ብለዋል። በዛ ላይ እድሜ ለእነማሪያ ቤተሰቦች ፒኮሊኖን ልክ እንደ አንዱ ቤተሰባቸው ነበር የሚንከባከቡት ይህም ለኔ ስራዬን ያለሃሳብ እንድሰራ ረድቶኛል። በነገራችን ላይ ወደ ኢል ሴሎ ለመሄድ ያሰብኩት ፒኮሊኖን ለማየት ብቻ ሳይሆን የናፈቀኝን የማሪያን ገላም ለማቀፍ ጭምር ነው። ማሪያን ካገኘኋት አንድ ሳምንት ያለፈኝ በመሆኑ አካሌም አእምሮዬም አግኛት አግኛት እያለኝ ነበር። ስራዬን ጨርሼ ወደ ኢል ሴሎ የሚያደርሰኝን መኪና ይዤ ጉዞዬን ጀመርኩ። እንዳልኩትም በመኪናው ተሳፍሬ ጥቂት መጓዝ እንደጀመርኩ ሃይለኛ ዝናብ መጣል ጀመረ። እነ ማሪያ ቤት ስደርስ ከቀኑ ስምንት ሰዓት ሆኖ ነበር። ከመኪናው ወርጄ ወደ እነማሪያ ቤት እስከደርስም ያ ሀይለኛ ዝናብ የለበስኩትን ልብስ አበስብሶ መላ ሰውነቴን አጥምቆኛል። እንዲከፍቱልኝ ሳልጠብቅ በሩን ከፍቼ ወደ ውስጥ ስገባ ከማሪያ ውጪ ሁሉም በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው

አገኘኋቸው፡፡ ማሪያ ግን በሩ አካባቢ ትንሽ በርጬማ ላይ ቁጭ ብላ በር በሩን እያየች በሀሳብ ተውጣ አገኘኋት፡፡

ገና በሩን ከፈቼ ከመግባቴ ማሪያ ከተቀመጠችበት በርጬማ ላይ ዘላ ተነስታ እላዬ ላይ ከተጠመጠመችብኝ በኋላ "ለምንድ ነው ይህን ያህል ጊዜ የቆየኸው? ሳምንት እኮ ሆነህ... ሳምንት እኮ ብዙ ጊዜ ነው" አለች ያኮረፈ ሰው ለመምሰል እየሞከረች፡፡ "ና እሺ አሁን ልብስህን ቀይር ረጥቧል እኮ" አለችን መጀመሪያ ስትጠመጠምብኝ ያልታወቃት ልጅ ከሳመችኝ በኋላ አይኗ እየተገለጠላት፡፡

እኔም የማሪያን ቤተሰቦች እና ፒኮሊኖን ሞቅ ያለ ሰላምታ ከሰጠኋቸው በኋላ ልብሴን ለመቀየር በማሪያ መሪነት ወደ መኝታ ቤት ሄድን፡፡ ማሪያ ልብሴን እንዳወልቅ ከነገረችኝ በኋላ እዲደርቁ በማሰብ ከዘረጋጋቻው በኋላ "አልጋ ላይ ውጣ" አለችኝ... እኔም እርቃኔን እንደሆንኩ አልጋው ላይ ከመውጣቴ ማሪያም ምን ግዜ ልብሷን እንዳወለቀች እንኳ ሳላውቅ አጠገቤ ተሸጉጣ አገኘኋት... በቀጥታ መጥታም ከንፈሮቼን ከጎረሰቻቸው በኋላ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ከንፈሮቻችን እስኪያብጡ ድረስ በመሳሳም ብቻ አሳለፈን... ያ እንደ እሳት የሚፋጀው ትንፋሿ እኔን ከስሜቴ ከፍታ ላይ አደረሰኝ፡፡ በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ እነጆዜ እኛን እየጠበቁን እንደሆነ ዘንግተን የፍቅር ባህር ውስጥ ሰጠምን፡፡ ሲደክመንም እንደተቃቀፍን እንቅልፍ ይዞን ሔደ፡፡ ከተወሰኑ ሰዓቶች በኋላ ባለ አረንጓዴ አይኗ ኢስመራልድ መጥታ ከእንቅልፋችን ቀስቅሳ እራት እንደደረሰ ነገረችን፡፡

ከእራት በኋላ ጆዜ እኔና እሱ ብቻ እንድናወራ በማሰብ ከቤት ይዞኝ ወጣ፡፡

"እኔ የምልህ ኢኒሪክ... ለዋና አስተዳደሩ በኢል ሴሎ የመኖር ግዴታህ ተነስቶ ወደ ካራካስ ከተማ ሄደህ ለመስራት መፈለግህን የሚገልፅ ደብዳቤ ልከህለታል እንዴ?"

"እዎ ጆዜ... ምነው?"

"አይ... ምንም... ምላሽ እንደተሰጠህ ላሳውቅህ ፈልጌ ነው"

"ጥሩ ዜና ነው ወይስ መጥፎ?"

"ጥሩ ዜና ነው... ግዴታህ ተነስቶልሃል... አሁን በየትኛውም ቦታ መንቀሳቀስ ትችላለህ"

"ስለነገሩ ማሪያ አውቃለች?"

"አዎ"

"ምን አለች?"

"ሁሌም ኢል ሴሎ ውስጥ መቀመጥ እንደማትፈልግ ታውቃለች" ብሎ ከራሱ ጋር ማሰብ ጀመረ። ከትንሽ ዝምታ በኋላም መች ለመሔድ እንዳሰብኩ ጠየቀኝ። እኔም ከተፈቀደልኝማ ዛሬ እዚህ ይዞኝ የመጣው ባለመኪናን ወደ ካራካስ እንዲወስደኝ ማነጋገር እንደምፈልግ ነገርኩት። በነገረኝ ዜና ብደሰትም የጆዜ ፊት ላይ የማየው ግን ሀዘን ነበር፤ ሀዘኑን ምን እንደፈጠረው እያወኩ "ምነው አዝነህብኛል እንዴ ጆዜ?" ብዬ ጠየኩት

"አይ እንዲሁ ነው" ካለኝ በኃላ "ሁሌም ቢሆን እዚህ መቀመጥ እንደማትፈልግ ትናገር ስለነበር ለመሄድ ማሰብህ አላስገረመኝም... ቢሆንም ግን የማልደብቅህ ነገር ያንተ መሄድ ለኔም ለማሪያም ሀዘን ነው"

ምንም ማለት ስለማልችል የሆነ ሰበብ ፈልጌ ርዕሱን ለመቀየር ወሰንኩ።

"በቃ ጆዜ... ከመሄዱ በፊት ይዞኝ ወደመጣው ሹፌር ልሂድና ነገ ወደ ካራካስ ይወስደኝ እንደሆነ ልጠይቀው" አልኩት። ጆዜም እንድፈልገው ስለፈቀደልኝ ጆዜን ወደ ቤት የሚወስደው መንገድ ላይ ጥየው ሹፌሩን መፈለግ ጀመርኩ።

ብዙም ሳልንከራተትም የጭነት መኪና ሹፌሩን ስላገኘሁት የቬንዙዌላ ትልቋ ከተማ ወደሆነችው ካራካስ ከተማ መሄድ እንደምፈልግ ነገርሬው ይዞኝ ይሄድ እንደሆነ ጠየኩት። እንደአጋጣሚ እሱም ወደዛው ሊሄድ እንደሆነና ከእሱም ጋር ሌላ አንድ ተሳፋሪ እንደሚሄድ ከነገረኝ በኂላ ፒኮሊኖን ጋቢና ከሹፌሩና ከአዲሱ ሰውዬ ጋር እኔ ደግሞ ከኂላ ከተጫኑት በርሜሎች በአንደኛው ላይ ቁጭ ብዬ ለመሄድ ተስማማን። በእዚህ ከተስማማን በኂላ ለጉዞው መክፈል የሚገባኝን ገንዘብ ተነጋግረን በነጋታው ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ላይ ለመገናኘት ቀጠሮ ይዘን ተለያየን። ከሹፌሩ ጋር እንደተለያየንም ወዲያውኑ ወደ ዋና አስተዳደሩ ጋር ሄጄ የፈለኩበት ቦታ መሄድ እና መስራት እንደተፈቀደልኝ የሚገልፀውን ሰነድ ተቀበልኩ። ዋና አስተዳደሩም ከዚህ በኂላ ለሚያጋጥመኝ ነገር ሁሉ መልካም ነገር እንዲገጥመኝ ምኞቱን ገልፆልኝ ሰላምታ ሰጥቶ አሰናበተኝ። እኔም ለቀና ትብብሩ በእጅጉ አመስግኜ ቢሮውን ለቅቄ ወጣሁ። ቀጣዩ ስራዬ የሚሆነው የሚያውቁኝ ሰዎችን በሙሉ መሰናበት ነበር። በመጀመሪያ ያቀናሁት ወደ ቻርሎቴ ቤት ነበር። ጥልቅ በሆነ ስሜት ካቀፍኩት በኂላ ለዋለልኝ ውለታ ምስጋናዬ ከልብ የሆነ መሆኑን ገለፅኩለት። ጥቁሯ ኮንቺታንም ለእኔም ሆነ ለፒኮሊኖ ስለሰጠችን ፍቅር የሞላበት መስተንግዶ

ከልቤ አመሰገንኳት፡፡ ለቻርሎቴም የሰጡት ምስጋና ካደረገልኝ አንፃር ትንሽ መስሎ ስለተሰማኝ ደግሜ ደጋግሜ አመሰገንኩት፡፡

"ኧረ ምንም ማለት አይደለም ወዳጄ... አንተም ብትሆን ልታደርገው የምትችለው ነገር ነው ያደረኩልህ ባይሆን ወደ ፓሪስ ከተመለስክ ከሞንትማርትሪ ፃፍልኝ"

"እፅፍልሀለሁ"

ቀጥዬም ሲሞንን እና አሌክሳንደርን ከተሰናበትኩ በኋላ በፍጥነት ወደ ሞኩፒያ የወርቅ ማውጫ ተመልሼ ሁሉንም በስራ ቦታዬ የማውቃቸውን የማዕድን ቁፋሮ ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞችን፣ ዋና ተቆጣጣሪዎቼን እንዲሁም ውጪ ላይ የሚሰሩትን ሰራተኞች በሙሉ ተሰናበትኩ፡፡ ሁሉም ከሞቀ ሰላምታ ጋር በሔድኩበት ሁሉ መልካም እድል እንዲገጥመኝ ተመኝተው ሸኙኝ፡፡ በእውነቱ ከልቤ ነበር ሀዘን የተሰማኝ ያንን የመሰለ ድሎትና ምቾት የሞላበትን ኑሮ ጥሎ መሄድ ሞኝነት ነው፡፡ ነገር ግን ዕድሜዬን ከፈጀሁበት ውጥን ከመሸሽ የበለጠ ሞኝነት አለመኖሩን ሳስብ የሆነ ያህል ተፅናናሁኝ፡፡

ከሁሉም ነገር ግን ከባዱ ነገር ማሪያን መሰናበቱ ነበር፡፡ የመጨረሻው ምሽታችን ፍቅርና ለቅሶ የተቀላቀለበት ሆኖ ነበር ያለፈው፡፡ ሌላው እጅግ ከባዱ እና አስቀያሚው ነገር አንዴ ከሄድኩ በኋላ የማልመለስ መሆኑን ማሳመን ነው፡፡ ያው በመጨረሻም ሳትወድ በግዷ እውነታውን ለመቀበል ተገዳ ነበር፡፡

የጠዋት ፀሀይ ፊቴን ሲነካኝ ነበር ከእንቅልፌ የነቃሁት፡፡ ሰዓቴን ስመለከት ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ይላል፡፡ እዛ ቤት ውስጥ ለአንድ ደቂቃ እንኳ ለመቀመጥ ድፍረቱ አልነበረኝም፡፡ እውነቱን ቢያውቁም የከዳዋቸው ያህል ስለተሰማኝ ውስጤን ከብዶኛል፡፡ ልብሴን ለባብሼ ከመኝታ ቤት እንደወጣሁ ፒኮሊኖ ወንበር ላይ ቁጭ እንዳለ እንባዎቹ ክንብል ክንብል እያሉ ሲወርዱ ተመለከትኩ፡፡ ኢስመራልድ አጣጥፋው ልብሱን እያለበሰችው ነበር፡፡

ማሪያንና የቀሩትን እህቶቿን ግን ላገኛቸው አልቻልኩም፣ ይመስለኛል ስንሄድ ማየት አልፈለጉም፡፡ እኔም የእነሱን ያክል ከእነሱ መለየቴ ስላመመኝ በወሰዱት እርምጃ አልተከፋሁም፡፡ ጆዜ ብቻ ወደ በሩ መውጫ ጋር ቆሞ እየጠበቀን ነበር፡፡ በቬንዙዌላውያን ሰላምታ አሰጣጥ (በአንድ እጁ እየጨበጠ ሌላኛው እጁን ደሞ ትከሻ ላይ በማድረግ) ሰላምታ ከሰጠኝ በኋላ "እንግዲህ እንዳትረሳን ኢኒሪክ... እኛ መችም አንረሳህም... ቻው እግዚአብሄር ከአንተ ጋር ይሁን" ብሎኝ እንዳዘነ ወደቤቱ መመለስ ጀመረ፡፡

ፒኮሊኖም ለተደረገለት ነገር ለማመስገን አንደበቱ ባይፈቅድም የፊቱ ገፅታ ግን ምስጋና እና አክብሮትን እንደሚገልፁ ያስታወቃሉ፡፡ ቦርሳችንን እንደተሸከምኩ ፒኮሊኖን በአንድ እጄ ይዤ ሹፌሩ ጋር ወደተቀጣጠርንበት ቦታ አመራን፡፡ ቦታው ላይ ስንደርስም ሹፌሩ መኪናው መበላሸቱንና የሚቀየረውን እቃ እስኪያገኝ ድረስ መቆየት ሊኖርብ እንደሆነ አስረዳን፡፡ ስለዚህ ፒኮሊኖን ይዤ ወደ እነማሪያ ቤት ተመለስኩ፡፡ እቤት ስንገባ በመመለሳችን ምን ያህል እንደተደሰቱ መገመት ቀላል ነው፡፡ መኪና መበላሸቱንና እስኪሰራ ድረስ መጠበቅ እንደሚኖርብን አስረዳኋቸው፡፡

በመመለሳችን ከሁሉም በላይ የተደሰተችው ማሪያ ነበረች፡፡ ወደ እኔ ጋር ከመጣች በኋላም እጄን ጭምቅ አድርጋ በመያዝ “መኪናው ስለተበላሸ አምላክ የተመሰገነ ይሁን!ምን አልባት እኮ ወደ ካራካስ እንድትሄዱ ፈጣሪ አልፈለገም ይሆናል፤ ምሳ እስክሰራ ድረስ ወጣ በልና ራስህን አዝናና...ፒኮሊኖ እዚህ ከእኛ ጋር ይጫወታል” አለችኝ ውስጤ ትክክል አለመሆኑን ፊቴን አይታ ስለተረዳች፡፡

ይህ አባባሏ ጭንቅላቴን መታው እውነቷን ሊሆን ይችላል ምክንያቱም ካራካስ ትልቅ ከተማ እንደሆነች ሰዎች ሲያወሩ ሰምቻለሁ እንጂ አላውቃትም... እሺ ሄድኩ ይባል... እንዴት እና ምን ስራ እንደምሰራ አላውቅም፡፡ እጆቼን ወደኋላ እንዳደረኩ ስለካራካስ እያሰብኩ ጥዬው ለመኮብለል በተነሳሁበት የኢልሴሎ ጎዳና ላይ መንሸራሸር ጀመርኩ፡፡ የፀሃይዋ ቃጠሎም መቋቋም ስላልቻልኩ ጥላ ፍለጋ በአይኖቼ ከማተርኩ በኋላ ወደ አንድ አልሜንዶ እያሉ ወደሚጠሩት ቅጠል ወደሚበዛበት ዛፍ ስር ሄጄ አረፍ አልኩ፡፡ ዛፉ ስር ትንሽ እንደተቀመጥኩ እዛው ዛፍ ስር አንድ ፀና ያለ ሰውዬ ሁለት በቅሎዎች ላይ የሆነ ጭነት እላያቸው ላይ እየጫነ እንደሆን አስተዋልኩ፡፡ በዚህ ጠራራ ፀሀይ እሱ ብቻ ከበቅሎ ጋር ሲታገል በማየቴ ብገረምም እይታዬን ከእሱ ነቅዬ ከፊት ለፊቴ ያለውን መልከዓ ምድር እያየሁ ስለ ነገ ጉዞዬ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ ምንም ቢሆን ወደእዚያ ከተማ ሄጄ የሚገጥመኝ ጥሩም ሆነ መጥፎ እድል መጋፈጥ መቻል አለብኝ፡፡ በእዚህ ሰዓት ካራካስ ውስጥ ምን እየተካሄደ ይሆን?... እንግዲህ ከአስራ አራት አመታት በኋላ ነገ ትልቅ ከተማ ልመለከት ነው!

# ምዕራፍ ሦስት

## ጆጆ ላ ፔሴ

በፈጣሪ!... ሙዚቃው ፈረንሳይኛ ነው! እዛው ዛፉ ስር ቁጭ እንዳልኩ ያ በቅሎ የሚጭነው ሰውዬ በሚዘፍነው ዘፈን ከነበርኩበት ሀሳብ ወጥቼ ዘፈኑን ማድመጥ ጀመርኩ።

እኔም ዝግ ባለ ድምፅ እየዘፈነ ያለውን ሰውዬ ለማየት ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ሰውየው ወዳለበት ቦታ እንደምራመድ አስመስዬ ተጠጋሁት። ሰውየው እንደበረዶ የነጣ ፀጉር ያለው እንዲሁም ወደ አመዳምነት የሚጠጋ ፂም ያለው ሰው ነው። ሰማያዊ ጅንስ ሱሪ አድርጓል። ሰፊና ትልቅ ቀበቶ ደግሞ በሱሪው ዙሪያ ታጥቋል። ልክ ባጠገቡ እያለፍኩም ፊቱን ለማየት ሞከርኩ። ፊቱ እንደ ማንኛውም ቬንዙዌላዊ ውስጥ እንደሚኖር ሰው ከፀሀይዋ ንዳድ የተነሳ የጠቆረ ነው...ቅንድቦቹ ከብዛታቸው የተነሳ ማበጠሪያ ሳያስፈልጋቸው አይቀርም። አይኖቹ ቡናማ ቀለም አላቸው። አራት እርምጃ እንኳን አልተራመድኩም ነበር ስራውን አቁሞ "ሰላም ነው ወንድም... ከፍታው ላይ ካለው መንደር ነው አይደል የመጣኸው?... ላ ፔሴ እባላለሁ" አለኝ

እኔም "አዎ ከዛ ነው የመጣሁት... ፓፒለን እባላለሁ" አልኩት

"ጆጆ ላ ፔሴ እባላለሁ" አለኝ እጁን ለሰላምታ እየዘረጋልኝ

እኔም ለሰላምታ እጄን ከዘረጋሁ በኋላ "ፀሀይዋ በጣም ጠንክራለች እና ራሴን ለማቀዝቀዝ ወደ መጠጥ ቤት እየሄድኩ ነው ከፈለግህ አብረኸኝ መምጣት ትችላለህ... ግብዣው በኔ ነው" አልኩት አንድም ከፀሀይዋ ሙቀት ለማምለጥ አንድም ደግሞ ወደ ቤት መሄድ ስለነበረብኝ ንግግራችንን ለማሳጠር ያህል ይህን የተናገርኩት

"አይሆንም!... ባይሆን ከልጅነቴ ጀምሮ ያደኩበት ቤት ስላለ ወደ እዛ መሄድ እንችላለን... እዛ ዘና ብለን ማወራት እንችላለን" አለኝ

"አመሰግናለሁ ለሀሳብህ... ነገር ግን ግብዣህን እንዳልተቀበልኩት ስነግርህ እያዘንኩ ነው" አልኩት

"ግድ የለህም አትፀፀትበትም እሺ በለኝ" ብሎ መማፀን በሚመስል ቃና በድጋሚ ጠየቀኝ

እኔም ወደቤት መሄድ ቢኖርብኝም እንኳን ሰውየው እንዲህ አጥብቆ ለምን እንደፈለገኝ ማወቅ ስለፈለግሁ ለምን እሺ አልለውም የሚል ሃሳብ ስለመጣልኝ ወደ ተባለው ቤት ለመሄድ ተስማማሁ። ደስ የሚለው መኖሪያ ቤቱ አሁን ካለንበት ቦታ ብዙም አይርቅም ነበር... ቤቱ እንደደረስንም ባለቤቱ ተቀብላን ወደ ቤት ገባን።የገረመኝ ነገር ቢኖር በሱና በባለቤቱ መሀከል ያለው የእድሜ ልዩነት ነው። እሷ በዛ ከተባለ ሀያአምስት ቢሆናት ነው።እሱ ደግሞ በተቃራኒው ስልሳ እና ከዚያ በላይ ነው። የባለቤቱ ስም 'ሎላ' ሲሆን ጠቆር ያለች ቬንዙዌላዊ ነች።

"እንኳን ደህና መጣቹ" አለች ባለቤቱ ደስ በሚል ፈገግታ

"አመሰግናለሁ"

"እስኪ ቀዝቃዛ አኒሴት አምጭልን" (ከእንስት የሚሰራ ቀለም አልባ ጣፋጭ መጠጥ ነው) አለ ጆጆ ሎላን እያዘዘ ወዲያው ወደ እኔ ዞሮ "አንድ ኮርሲካዊ ሁለት መቶ ጠርሙስ አኒሴት ከፈረንሳይ አስመጥቶልኛል በዛውም እስኪ ትቀምስልኛህ" አለኝ ሎላ ለሁለታችንም አምጥታ ቀዳችልን። ጆጆ የተቀዳለትን አንስቶ ወዲያው ከጨለጠው በኋላ አይን አይኔን እያየ "እሺ" አለ

"እሺ ምን?... ምነው የህይወት ታሪኬን መስማት ትፈልጋለህ እንዴ?" ጠየኩት

"አይ እሱ ሳይሆን... ጆጆ ላ ፔሴ የሚለውን ስም ስትሰማ ምንም ጭንቅላትህ ላይ የተፈጠረ ነገር የለም?"

"የለም"

"እንዴት በአንዴ ረሳህ ባክህ?" አለ ቀጠለናም "የሚገርም ነው በአንድ ወቅት በእነዚያ መንደር ውስጥ በዳይስ ጨዋታ እኔን የሚያክለኝ የለም ነበር ... ማንም ቢሆን ሰባትንና አስራ አንድን ወርውሮ በማግኘት እኔን የሚስተካከል አልነበረም... የሚገርም ነው በእዚች ትንሽ ጊዜ ውስጥ እንዲህ ከረሱኝማ ከትንሽ አመት በኋላማ ጭራሹኑ ይረሱኛል ማለት ነው!" አለ ይህንን ሲናገር ጥልቅ በሆነ የሀዘን ስሜት ውስጥ ገብቶ ነበር ትንሽ ዝም ካለ በኋላም

"እስኪ ንገረኝ እስካሁን ካገኘሀቸው ሰዎች መሀል አንዱም ዲቃላ ጀጀ የሚባለውን ስም የጠራ የለም ነው የምትለኝ?"

"አዎ" አልኩት ስሜቱ እንደሚጎዳ ባውቅም እውነታው ስለሆነ ብቻ

"ለነገሩ እዚህ ብዙ ስላልቆየህ ስለኔ አለመስማትህ አያስደንቀኝም" አለኝ ንዴቱን የሚደብቅለት ይመስል

"ኢል ዶራዶ የኖርኩት ተጨምሮ እዚህ ለአስራ አራት አመት ኖሬአለሁ... እና ይሄ ትንሽ ነው?"

ለማስታውስ ይመስል ከቅድሙ ይልቅ አሁን በአትኩሮት እየተመለከተኝ

"የማይታመን ነገር ነው!... እንዴት ታዲያ ፊትህ አዲስ ሆነብኝ ሁሉንም እዚህ ያሉ ወንጀለኞች ፊታቸውን አይቼ አለያቸዋለሁ... ያንተን ግን ጭራሽ ላስታውስ አልቻልኩም"

"አዎ እስር ቤት ስለነበርኩ ነው"

"የትኛው ወህኒ ቤት ነበርክ?"

"ደሴቶቹ ላይ"

"ደሴቶቹ ላይ?!... ደሴቶቹማ ለበዓል ማድመቂያ የተሰሩ ድንቅ ቤቶች አይደሉ እንዴ!... ቁማር ቤት ብቻ እኮ ነው የሚቀራቸው... እዛማ ታስርኩ ብሎ ለማውራት ይከብዳል... ተባይ የለ!... የወባ ትንኝ የለ!... በዛ ላይ የፈለከውን በልተህ ነው... ስትፈልግ አሳ... ስትፈልግ ዶሮ በዛ ላይ.."

"ቢሆንም በጣም ከባድ ፈተናዎችን አሳልፌአለሁ" ብዬ ስለማያውቀው ታሪክ ከመዘላበዱ በፊት የጀመረውን ወሬ አቋረጥኩት፡፡

"ተው ተው... ልትዋሸኝማ አትሞክር ስለደሴቶቹ ሁሉንም ነገር አውቃለሁ... ደሴቶቹ ላይ ባልኖርም ደሴቱ ላይ ስላሉት እስር ቤቶች የሚያውቅ ሰው ግን ሁሉንም ነገር ነግሮኛል... ካልክስ እውነተኛው ወህኒ ቤት 'ኪሎ ሜትር ሀያ አራት' ተብሎ የሚጠራው እስር ቤት ነው... እዛ አብዛኞቹ እስረኞች በበሽታ የተጠቁ ናቸው... የበረቱት ቆመው ለመራመድ ይችላሉ... አንዳንድ አቅመቢሶች ደግሞ አልጋ ላይ ተኝተው ያላዝናሉ... ለማምለጥ እንዳያስቡ ከፊት ለፊታቸው ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ነው ያለው... ጫካውን አቋርጦ ለማለፍ የማይታሰብ ነው... ለማቋረጥ ብታስብ እንኳን ጫካው እራሱ አንገትህ ቆርጦ

ይጥልልሃል... እዚህ ወህኒ ቤት ውስጥ ረብሻ ለማስነሳት ብትሞክር የእስር ቤቱ ዋና አዛዥ ምላሽ የሚሆነው ወደዚያ ጫቃ መላክ ነው... ስለዚህ ፓፒለን ደሴቶቹ ላይ ባሉት እስር ቤቶች ውስጥ ያሳለፍከውን ህይወት አክብደህ ልትነግረኝ እንዳትሞክር" አለኝ

ይሄ ደደብ ሽማግሌ ከዚህ በፊት በእስር ቤቶች ውስጥ ስላሳለፍኩት ህይወት ምን አባቱ ያውቅና ነው እንዲህ የሚቀባጥረው በዚህ ሃሳብ ውስጥ እያለሁ ከእሱ ጋር የምንለያይበትን ጊዜ እየናፈቅሁ ነበር።

ወዲያው ንዴቴን እንደምንም ከተቆጣጠርኩና ከጠላት ይልቅ ጓደኛ ማድረጉ የተሻለ መስሎ ስለተሰማኝ

"ትክክል ነህ ጆጆ... እንዳንተ አይነት ብዙ ውጣ ውረድ ላሳለፈ ሰው የእኔ ትንሿ ታሪክ ምንም ላይመስለው ይችላል" አልኩት ውስጤ እየበገነ ቢሆንም የሁሉንም ነገር መጨረሻ ማየት ስለፈለኩ

"አሁን ተስማማን!... ከእስር ከተለቀቅህ በኋላ ምን ነበር የምትሰራው?"

"ሞኩፒያ ውሰጥ በሚገኘው የወርቅ ማውጫ ውስጥ ነበር የምሰራው በቀን አስራስምንት ቦሊቫርስ ይከፈለኝ ነበር፤ አሁን ግን በኢል ሴሎ ብቻ የመኖር ግዴታዬ ስለተነሳልኝ ወደ ካራካስ ለመሄድ አስቤአለሁ"

"ወደ ካራካስ ሄደህ እየሰራህ መኖር ነው የምትፈልገው?"

"በትክክል እንደዚያ ነው እቅዴ"

"ግን እኮ ካራካስ ትልቅ ከተማ ነች እዛ አንድ ችግር እፈጥራለሁ ብትል ገሀነም ውስጥ እንደገባህ ቁጠረው... ተመልሶ ለመውጣት በጣም ከባድ ነው"

"ለሱ አታስብ ምንም አይነት ፈተና ቢመጣ ለመጋፈጥ ዝግጁ ነኝ... ወደ ካራካስ የምሄደውም ለእነዚያ በሀሰት ለአስራ አራት አመት በእስር እንድማቅቅ ላደረጉኝ ፖሊሶች፣ የውሸት አቃቤህግ እና የሀሰት መስካሪዎቹ ለመበቀል የሚያስፈልገኝን ብር ለማጠራቀም ነው። አዎ ለእነዚያ የልጅነት ደስታዬን ለነጠቁኝ ሰዎች አፀፋውንማ መመለስ ይኖርብኛል። እንግዲህ አስበው ባልሰራሁት ወንጀል ለእስር ሲሞሽሩኝ ገና የሃያ ሦስት አመት ልጅ ነበርኩ... ስለዚህ ያልኩህ ሰዎች እድሜዬን ቅርጥፍ አድርገው በልተውታል። በእነሱ ምክንያት የመኖር ትርጉሙ ምን ላይ እንደሆነ አሳጥተውኛል... የምልህ እየገባህ ነው?"

"ስለዚህ እኔ ንፁህ ሰው ነኝ እያልክ ነው... የተናገርከው ነገር እውነት ስለመሆኑ ምን ማረጋገጫ አለህ?"

"በሞተችው እናቴ ስም እምልልሃለው"

"አሁን የእውነት ማውራት እንችላለን" አለኝ በእርጋታ መንፈስ "ገንዘብ ለማግኘት ከሆነ አላማህ ካራካስ ድረስ መሄድ አይጠበቅብህም... ከእኔ ጋር ና"

"ወዴት?...ማለቴ ለምን?"

"አልማዞች!... ስለ አልማዞች ነው የማወራው ወዳጄ.... የእዚህ ሀገር መንግስት ብቻ እንደሆነ ታውቃለህ ማንኛውም ሰው ወርቅ ወይም አልማዝ አለ ብሎ የሚያስብበት ቦታ ሄዶ ቆፍሮ ማውጣት እንደሚችል የፈቀደው:: ብቸኛው የማይቻለው ነገር ቢኖር ለመቆፈር ማሽን እንድትጠቀም አለመፍቀዳቸው ነው:: ቢሆንም ግን ዶማ፣ አካፋ እና ሌሎች የእጅ መሳሪያዎችን ግን መጠቀም ይቻላል"

"ብቻ አሁን የምትለኝ ነገር ኢል ዶራዶ ውስጥ እንዳይሆን?"

"አይደለም... ከዚህ የተወሰኑ ቀናቶች የሚፈጅ ጉዞ ማድረግ ይጠበቅብናል... በፈረስ የሚያስፈልገን እቃ ጭነን ለጥቂት ቀናቶች በጫካ ውስጥ መጓዝ ይኖርብናል... ከዛ ደግሞ ጀልባ በመጠቀም የምናቋርጠው ወንዝ ይኖራል... እንግዲህ ይሄንን ካለፍን በኋላ ነው ወደ ትልቁ ሀብት የምንጓዘው... ታዲያ እዚያ ደርሰን በቁፋሮ ሰዓት አንድ አልማዞችን በአንድ ላይ ሰብስቦ የያዘ ድንጋይ ካገኘህ ስራችን እዛ ጋር ተጠናቀቀ ማለት ነው... ሀብት እራሱ አይኑን አፍጥጦ ወደ አንተ ይመጣል ማለት ነው"

ስለእነዚህ በቅፅል ስማቸው 'ፊንጂው' እየተባሉ ስለሚጠሩት የአልማዞች ሰብስብ በአንድ ላይ ስለሚይዘው ድንጋይ ያኔ የወርቅ ጉድጓድ ውስጥ በምሰራበት ወቅት ሰራተኞች ሲያወሩ እሰማ ነበር:: ይህ ድንጋይ ምናልባትም ከ መቶ እስከ አንድ ሺ ካራት የሚመዝን አልማዞችን በአንድ ላይ ሊይዝ ይችላል::

ጆጆ ማውራቱን ቀጥሎ ነበር "አንድ ተቆጣጣሪ አንድ ፊንጂ ካገኘ ወሬው ባንድ ጊዜ ነበር የሚንሰራፋው እሱን በማስመልከት ተጨማሪ ፊንጂ ለማግኘት ከሰሜን፣ ከደቡብ፣ ከምስራቅ እና ከምዕራብ ሰዎች መጉረፍ ይጀምራሉ:: ይህ ብቻ መሰለህ እንዴ ከተለያዩ ሀገራት የሚመጡ ጆብዱ ፈላጊዎች ይህንን የአልማዞች ጥርቅም የግላቸው ለማድረግ የማይቆፍሩት ጉድጓድ የለም!...

ከእንግሊዝ፣ ከፈረንሳይ፣ ከእስፔን፣ ከፖርቹጋል ምን አለፋህ ከሁሉም አቅጣጫ ነበር የሚመጡት... ፈጣሪ ይህንን ቦታ በዘንዶዎች፣ በአስፈሪ እባቦች እና ስጋ በሚበሉ ትንንሽ አሳዎች ቢሞላውም በዛው ልክ ደግሞ በወርቅ፣ በአልማዝና በኢመራልድ የተሞሉ እንዲሆኑ አድርጓል... እንግዲህ እውነተኛ ጀብዱ ለሚፈልግ ሰው ይህ ቦታ አደገኛ ቢሆንም በዛው ልክ ግን ሀብት በአካፋ የሚዛቅበት ቦታ ነው" ካለ በኋላ ጆጆ ዝም አለ ይመስለኛል ዝም ማለት የፈለገው ከንግግሩ ውስጥ የረሳው ነገር ካለ ለማረጋገጥ ነበር።

"እንደተረዳሁት ከሆነ አንተ በእግዚአብሔር የምትተማመነውን ያህል በእነዚያ ፈንጂዎችም ሳትተማመን አትቀርም ስለዚህ በዚያ ጥሩ እድል እንዲገጥምህ እየተመኘሁ እኔም የራሴን እድል ካራካስ ውስጥ እፈልጋለሁ" አልኩት ቁርጥ ባለ ንግግር

"ይገባኛል ሀሳቤን አልወደድከውም... ስላንተ ምን እንደማስብ ታውቃለህ?" አይኖቹን እያቁለጨለጨ ጠየቀኝ

"ቀጥል"

"ጥሩ... መጀመሪያ ከኢልሴሎ ለምን መሄድ እንደፈለግህ ልንገርህ... ምክንያቱም ለምን መሰለህ ሞኩፒያ ውስጥ ያየኸውን ያንን ብዙም ጥበቃ የማይደረግለትን የወርቅ ክምር እያየህ ዝም ማለት ስለማትችል ነው አይደል... እውነት ሀሰት?"

"እውነት ነው"

"እሺ ወርቁንም መዝረፍ ያልፈለከው በአንተ የተነሳ እነዚያን ወርቁን የሚጠብቁትን ጓደኞችህን ላለመረበሽ ነው... እውነት ሀሰት?"

"እውነት ነው"

"ጥሩ... ስለእነዚያ የአልማዝ ፈንጂዎች ሳወራ ከብዙ ሰው እድለኛ የሆነው ብቻ ሊያገኝ እንደሚችል ተረድተሃል... እውነት ሀሰት?"

"እውነት"

"እና አሁንም ሀሳብህን አልቀየርክም?"

"የተረዳህኝ አልምሰለኝም በዚህ ሰዓት አዕምሮዬን ብቀላ የሚሉት ፊሊጥ ወጥሮ ይዞኛል... በእርግጥ እቅዴን ለማሳካት በቂ የሆነ ገንዘብ ያስፈልገኛል ቢሆንም

ግን አንተ የነገርከኝን አልማዞችን ቆፍሮ ለማውጣ ወኔውም ጊዜውም የለኝም አልኩት"

በንግግሬ ከመከፋት ይልቅ እንደውም የእርካታ መንፈስ እየተነበበት "ብቀላም አልከው ጀብዱ ዋናው ነገር ገንዘብ ያስፈልግሃል ስለዚህ ከኔ ጋር መሄድ ይኖርብሃል" አለኝ

"አልማዞችን ቆፍሮ ለማውጣት ወኔው የለኝም አልኩህ እኮ" አልኩት ጤነኛ ለመሆኑ እየተጠራጠርኩ

"ወደእኔ ዞሮ እንደመሳቅ ካለ በኋላ አንድ የረሳኸው ዋና ነገር አለ... ስሜን!... ጆጆ ላ ፔሴ... ጆጆ ቁማርተኛው!... ነው"

"አዎ ልምድ ያለው የዳይስ ተጫዋች መሆንህማ ነገርከኝ... ታድያ አሁን ከምናወራው ወሬ ጋር ያንተ ቁማርተኛ መሆን ምን ያገናኘዋል?" አልኩት ነገሩ ተምታቶብኝ

"ምን ያገናኘዋል?" ብሎ የራሴን ቃል ከደገመልኝ በኋላ ተንከትክቶ ሳቀ

እኔም በሁኔታው የባስ ግራ ተጋብቼ "አልማዞቹን ቆፍሮ ስለማውጣት ያወራኸኝ መስሎኝ... ነው አልማዞቹን የምናገኝበት ሌላ መንገድ አለ እያልከኝ ነው?" አልኩት፡፡ አሁን በወሬው ሙሉ ለሙሉ ተመስጬ ነበር፡፡

"እልህለሁ እንጂ!... እኛ አልማዞቹን የምናገኘው የመዓድን ማውጫ ውስጥ ከሚሰሩት ሰራተኞች ነው"

"እንዴት?" አልኩት በመገረም

"እንዴት ማለት ጥሩ... የዳይስ ጨዋታ በማጫወት... አንዳንዴ በመብላት አንዳንዴ ደግሞ በመበላት" ሌላ ነገር ከማለቴ በፊት ፊት ለፊታችን ያለውን ጠረጴዛ እኛ ወዳለንበት ቦታ ጎትቶ ካመጣው በኋላ ከመሳቢያው ውስጥ ኗሞ ባለ ስድስት ጎን ዳይሶችን አወጣ፡፡ ከዛም አንዱን እየሰጠኝ በደንብ እንዳየው ጠየቀኝ፡፡ እኔም አገላብጬ በድንብ ካየሁት በኋላ ምንም እንከን እንደሌለባቸው ነገርኩት፡፡

"አዎ እርግጠኛ ነበርኩ... ማንም ሰው እነዚህ ዳይሶች የተጭበረበሩ እንደማይመስለው!... ይመስላል እንዴ?"

"ኧረ በጭራሽ!"

አሁንም ደስ የማይል ደረቅ ሳቅ እየሳቀ ሜትር አውጥቶ ከሰጠኝ በኋላ ከዳይሶቹ መሀከል አንዱን ጠጠር አንስቼ እንድለካው ነገረኝ፡፡ ስለካውም በሚገርም ሁኔታ ከመደበኛው የዳይስ ጠጠር በአስር ሚሊ ሜትር እንደሚያንስ አረጋገጥኩ፡፡ በስነ-ስረዓት ተሞርደውና ተወልውለው ከመደበኛው የዳይስ ጠጠር ለመለየት እንዳይቻሉ ተደርገው ተዘጋጅተዋል፡፡ መሞረዳቸው ለምን እደሆነ በማሰብ ላይ እያለሁ ጆጆ

"እስኪ ሰባትን ወይም አስራ አንድን ወርውረህ ለማምጣት ሞክር" አለኝ ሁለት የዳይስ ጠጠሮች እየሰጠኝ፡፡ እኔም ትዕዛዙን ተቀብዬ ወረወርኩ ነገር ግን ሰባትን ሆነ አስራ አንድን ማግኘት አልቻልኩም፡፡ "አሁን ደግሞ የኔ ተራ ነው" አለ ጆጆ ጠጠሮቹን ከእጄ ላይ እየተቀበለ፡፡ ቀጥሎ ዳይሶቹን በተሞረዱበት በኩል በጣቶቹ ጫፍ ገለብጦ ከያዛቸው በኋላ ወረወራቸው ወዲያው ሰባት ወጣ፡፡ "አስራ አንድን ትፈልጋለህ?" አለኝ ወደእኔ ዞሮ "ይኸው!" አለ ጠጠሮቹን እየወረወረ አስራ አንድም ወጣች፡፡ አሁን እንዴት እንደሚያጭበረብር ገባኝ

"እሺ አሁን ደግሞ ስድስትን ላውጣልህ... የትኛው ይሻልሃል ባንደኛው ጠጠር አንድ በአንደኛው ጠጠር ደግሞ አምስት ወይስ አራት በሁለት "... የዳይሶቹን ጠጠሮች እንደፈለገው ነበር የሚጫወትበት፡፡ በጣም የሚደንቅና ለማመን የሚከብድ ነው፡፡ ያሰባቸውን ቁጥሮች ሲያመጣ አንዴም እንኳን አልተሳሳተም ነበር፡፡ በህይወቴ ሙሉ እንደዚህ አይነት ጥበብ የማይ አይመስለኝም፡፡

መደነቄን ከፊቴ ላይ ካስተዋለ በኋላ "የዳይስ ጨዋታን የጀመርኩት ገና የስምንት አመት ልጅ እያለሁ ነው... የጀመርኩትም ፓሪስ ውስጥ በሚገኘው 'ኄሪ ዲ ሴስት' ተብሎ በሚታወቀው የቁማር ማጫወቻ ቤት ውስጥ ነው... አስታውሳለሁ እዚያ ቤት ውስጥ በዳይስ ጨዋታ የተካኑ አደገኛ ተጫዋቾች ይመጡ ነበር... ከእነሱ ውጪ አንዳንድ ፖሊሶች ጭምር በዚያ የዳይስ ጨዋታ ላይ ለመጫወት ወደእዚያ ቤት ይመጣሉ፡፡ ታዲያ እኔም ሁሉንም ከመብላት ወደኋላ አልልም ነበር፡፡ ይህንንምያልኩህ በጨዋታው ላይ ምን ያክል ልምድ እንዳለኝ እንድታውቅልኝ ስለፈለኩና መሸነፍ የሚባል ነገር እንደሌለ ሙሉ ለሙሉ እንድትተማመንብኝ ስለምፈልግ ነው" አለኝ

"ተረድቼሃለሁ!"

"ነገር ግን አንድ ተጨማሪ ማወቅ የሚኖርብህ ነገር አለ... አሁን ወደምንሄድበት ቦታ ያሉት እነዚያ በማዕድን ማውጫው ውስጥ የሚሰሩት ሰራተኞች በዳይስ ጨዋታው ላይ ኄሪ ዲ ሴስቴ ውስጥ ከማውቃቸው ቁማርተኞች ባልተናነስ መልኩ መጫወት ይችላሉ... ልዩነቱ ምኑ ጋር መሰለህ ፓሪስ ውስጥዳይሶቹን ከወረወርክ በኃላ ወዲያው ማንሳት ትችላለህ እዚህ ግን

አንዴ ከወረወርክ በኋላ የዳይስቹን ጠጠር ለትንሽ ጊዜ እዛው መተው ይኖርብሃል፡፡ እዚህ ምንም አይነት ፖሊስ ስሌለለ የራሳቸውን ህግ ነው የሚያወጡት " ካለኝ በኋላ የጀመረውን የአኒስቴት መጠጥ ከጠረጴዛው ላይ አንስቶ ጨለጠው፡፡ ከዚህ በፊት ሄዶ እንደሚያውቅ ምንም አልተጠራጠርኩም ነበር... በመጨረሻም አይኖቼ ላይ እንዳፈጠጠ "እና አሁንስ ከእኔ ጋር ለመሄድ አትፈልግም?"ብሎ ጠየቀኝ

ለተወሰን ጊዜ እራሴን ማዳመጥ ጀመርኩ፤ ሁኔታው በጣም አጓጊ ይመስላል፡፡ ቢሆንም ምንጊዜም ቢሆን ቁማር አደገኛ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም... ያም ሆነ ይህ ብዙ ገንዘብ ሊገኝበት ይችላል!... 'በቃ ፓፒ ገንዘብ እስከሆነ ችግርህ ድፈር!' የሚል ሀሳብ ላይ ስለደረስኩ "እና መቼ ነው የምንሄደው?" አልኩት

"ነገ ከሰዓት ፀሀይዋ በረድ ስትል መሄድ እንችላልን... ለመሆኑ ሽጉጥ አለህ?"

"የለኝም"

"ጥሩ ጩቤስ?"

"የለኝም"

"በቃ ተወው እኔ ራሴ እፈልግልሀለው... በል ተነስ አሁን ልሸኝህ"

"አይ አያስፈልግም እኔ ራሴ እሄዳለሁ... ስለሁሉም ነገር አመሰግናለሁ"

"በል እሺ ቻው የነገ ሰው ይበለን"

ወደ ቤት በመመለስ ላይ እያለሁም ስለማሪያ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ ወደካራካስ ከምሄድ ይልቅ ጆጆ ወደነገረኝ ቦታ መሄዴን በጣም እንደምትወደው እርግጠኛ ነኝ፡፡ ፒኮሊኖን ከእነሱ ጋር ትቸው መሄድ እችላለሁ፡፡ ነገ እንግዲህ ወደ አልማዞቹ ጉዞ ይጀመራል!!... ሰባት... አስራ አንድ... ከእኔ የሚጠበቀው ነገር ቢኖር ቁጥሮች በስፓኒሽና፣ በእንግሊዝኛ፣ በብራዚልኛ እና በጣልያንኛ ምን እንደሚባሉ ማወቅ ነው፡፡

ቤት እንደደረስኩ ጆዜን እቤት ቁጭ ብሎ ስላገኘሁት ወደ ካራካስ ላደርገው የነበረውን ጉዞ ለጊዜው መቀየሬንና ጆጆ ከሚባል ባለነጭ ፀጉር ፈረንሳዊ ጋር ወደ አልማዝ ማውጫዎቹ ልሄድ እንዳሰብኩና እዛም ምን ለማድረግ እንዳቀድን ሁሉንም ነገር ነገርኩት፡፡

"አዎ ጆጆን አውቀዋለሁ... በዳይስ ጨዋታ የሚያክለው የለም... ምኑ በመሆን ነው ከእሱ ጋር የምትሄደው?"

"እንደ ጓደኛው በመሆን ነዋ"

"የምታሸንፋትን ብር እኩል ይሰጥሃል?"

"አዎ... ያ ህጋችን ነው... ከእዚህ በፊት ከእሱ ጋር የሰሩ ሰዎችን ታውቃለህ?"

"ሦስት ሰዎች አውቃለሁ"

"እንዴት ነው እንደተባለው ብዙ ገንዘብ ለማግኘት ችለዋል?"

"አላውቅም... እንደሚያገኙ ግን አልጠራጠርም ምክንያቱም ሶስቱም ሁለትና ሦስት ጊዜ ከጆጆ ጋር በመመላለስ ሰርተዋል"

"ከእነዚያ ከሁለትና ከሦስት ጉዞ በኋላስ?"

"ከእዚያ በኋላማ ማንም የተመለሰ የለም"

"አልተመለሱም ስትል?... እዛው ኑሮ መስርተው መኖር ጀመሩ?"

"አይደለም... ሞተው ነው!"

"እየቀለድክ ነው?"

"የምሬን ነው ፓፒ... በቀጣዩቹ ዙሮች በእዛ በአልማዝ ጉድጓድ ውስጥ በሚሰሩት ሰራተኞች ተገለዋል"

"ታዲያ እድል ከጆጆ ጋር ነች ማለት ነው?... ሁሌም እሱ ብቻ የሚተርፍ ከሆነ"

"እድል ብቻ ሳይሆን ብልጥም ስለሆነ ነው... ብዙ ጊዜ ሌላ ጓደኛ ይዞ የሚሄደው ሆን ብሎ ነው... በዳይስ ጨዋታው ጊዜ በአብዛኛው ገንዘብ እንዲበላ የሚያደርገው ይዞት የሄደውን ጓደኛውን ስለሆነ እሱ ላይ ብዙም ጫና አይበዛበትም"

"እሁን ነገሩ ገባኝ… ስለዚህ አብሮት የሚሄደው ሰው አደጋ ላይ ሲወድቅ ጆጆን ግን የሚነካው የለም ማለት ነው… ይህንን በማወቄ ተጠቃሚው እኔ ነኝ በጣም አመሰግናለሁ ጆዜ"

"መቼም ይህንን ከነገርኩ በኋላ ከጆጆ ጋር ለመሄድ ማሰብህን እንደምትተው እርግጠኛ ነኝ"

"አንድ የመጨረሻ ጥያቄ አለኝ… ስታስበው ሁለትና ሶስት ዙሮች ከጆጆ ጋር ብሰራ ሀብታም ሆኖ የመመለስ እድል አለኝ ብለህ ታስባለህ?"

"በእርግጥ አዎ"

"ስለዚህ ጆጆ ሀብታም ነው ማለት ነው… ታዲያ ለምንድነው ድጋሚ ለመሄድ ያሰበው… በቅሎዎቹን ሲጭናቸው አይቻለሁ እኮ"

"በመጀመሪያ ደረጃ ለመሄድ አላሰበም… በቅሎዎቹም የእሱ ሳይሆኑ የሚስቱ አባት ናቸው… አንተን ሲያይህ ነው ስለቁማሩ ያሰበው እንጂ ቀድሞም ቢሆን የመሄድ ሃሳብ እንዳልነበረው እርግጠኛ ነኝ"

"ግን እኮ የሆነ ነገር በቅሎዎቹ ላይ ሲጭን አይቸዋለሁ"

"ታዲያ ሲጭን አየኸው ማለት ለመሄድ አስቧል ማለት አይደለም… ጭነቱ በራሱ ምን እና ለማን እንደሆነ ምን ታውቃለህ?"

"ሆ… ሆ እሱም አለ ለካ… እሺ ሌላ የምትሰጠኝ ምክር አለ?"

"አትሂድ"

"እሱን ተወው አንዴ ውስጤን አሳምኜዋለሁ… ከእሱ ሌላ"

ጆዜ ለተወሰኑ ሰከንዶች አንገቱን ደፍቶ ካሰበ በኋላ ፊቱ በደስታ ደምቆ ቀና እያለ "እሺ እንግዲህ ምከረኝ ካልክ የአንድ ትልቅ ሰውን ምክር ልብ ብለህ አድምጥ… ሁሌም ቢሆን አሁን ወደምትሄድበት ቦታ ትልልቅ የዳይስ የቁማር ጨዋታዎች ይከናወናሉ… በጣም ትልልቅ ጨዋታዎች! ታድያ በመጨረሻው ሰዓት የምትፈልገውን ያህል ገንዘብ መብላትህን ካረጋገጥክ በኋላ የሆነ ቀን በቀጥታ ማድረግ የሚኖርብህ ነገር ቢኖር ሳያስቡት ተነስተህ ሆድ ቁርጠት እንዳስቸገረህ ተናግረህ የበላኸውን ገንዘብ ይዘህ ወደ ሽንት ቤት መሄድ ይኖርብሃል፡፡ ከዚያም እንደምንም ብለህ ወደ ቁማር ቤቱ ዳግም ላለመመለስ ለመውጣት መሞከር አለብህ፡፡ ያንን ምሽትም የምታድረው መጀመሪያ

የያዛችሁት ቦታ ላይ ሳይሆን ሌላ ማረፊያ ፈልገህ ያንን ምሽት ማሳለፍ ይኖርብሀል"

"በጣም ጠቃሚ ምክር ነው!... ሌላስ?"

"ምን አልባት ከኢልሴሎ ዋጋ አንፃር ሲታይ እዛ ያሉት ገዢዎች የበላሀቸውን የአልማዞቹን ዋጋ ሊያረክሱብህ ይችላሉ... ቢሆንም ግን ሁሌም ቢሆን አልማዞቹን መሸጥ ይኖርብሃልሌ። ሌላው መዘንጋት የለሌብህ ነገር ቢኖር በፍፁም የበላኸውን ጥሬ ገንዘብ አንተ ጋር ማቆየት የለብህም፤ ይልቁንም የበላኸውን ገንዘብ ቶሎ ብለህ ወደ አንዱ የአልማዞች መሸጫ ቦታ ሄደህ በስምህ በደረሰኝ መልኩ እንዲቀይሩልህ አድርግደ። ደረሰኞቹን ሲዩዳድ ወይም ኢልሴሎ ከመጣህ በኋላ ወደ ገንዘብ መተመን ትችላላህ ስለእሱ ምንም የሚያሳስብ ነገር አይኖርም... ለምን በደረሰኝ መልኩ ለመቀበል እንደፈለግህ ቁማርተኞቹም ሆኑ እዛ የምትተዋወቀው ሰው ቢጠይቁህ... በባህሪህ ገንዘብ አጥፊ መሆንህንና የበላኸውን ገንዘብ በአንድ ቀን እንዲጠፋ ስለማትፈልግ በደረሰኝ መልክ መያዙን መምረጥህን አስረዳቸው። ይህንንም የዳይስ ጨዋታ ለመጫወት ለመጣው ሁሉ ማስረዳት ይኖርብሃል። ይህም ድርጊትህ ማንም አንተ ገንዘብ በጥሬ እንደማትይዝ ስለሚያስረዳቸው አንተን ገሎ ለመዝረፍ የሚፈልግ አይኖርም ማለት ነው"

"ስለዚህ ያልከኝን ነገሮች በሙሉ ባደርግ በህይወት ተመልሶ የመምጣት እድሌ ከፍ ያለ ነው ማለት ነው?"

"አዎ በህይወት የመመለስ እድል አለህ ከፈጣሪ ፈቃድ ጋር!"

"በጣም አመሰግናለሁ ጆዜ"

የጆዜን ምክር እና ተግሳፅ በደንብ ከሰማሁ በኋላ የዛለ አእምሮዬን ለማሳረፍ ስለፈለግሁ ወደ መኝታ ክፍሌ ገባሁ። በማሪያ ክንድ ላይ እንደተጋደምኩ ስለነገ ጉዞዬ ማሰብ ጀመርኩ። እነዚያን የሚያማምሩ አልማዞችን እዛ ካሉ ቁማርተኞች ከበላሁ በኋላ ወደ ቦርሳዬ ከትቼ ጆጆን ቦታውን ያዝልኝ ሽንት ቤት ደርሼ እመለሳለሁ ብዬው በዛው እብስ ስል ይታየኛል። ትንሽ እንቅልፍ ለማግኘት በሚል አይኖቼን እንደከደንኳቸው ነበር ጭልጥ ያለ እንቅልፍ የወሰደኝ።

የጠዋት ጊዜው ቶሎ ነበር ያለፈው። ሁሉም ነገር ባለበት ነው። ፒኮሊኖን እዚሁ ከእነማሪያ ጋር ትቼው ስለምሄድ ስለጤንነቱ አላስብም እንደተለመደው ያንን ፍቅር የሞላበት እንክብካቤያቸውን ይሰጡታል። ከጆጆ ጋር

የተቀጣጠርንበት ሰዓት በመድረሱ ለመሄድ እየተነሳሁ ሁሉንም ሳምኳቸው። ማሪያም ከሌላው ጊዜ ይልቅ በአሁኑ ጉዞዬ ብዙም የተከፋች አይመስልም ምክንያቱም ከካራካስ ይልቅ ወደ እነዚያ የማዕድን ማውጫ ብሄድ ወደ እነማሪያ ቤት የመመለስ እድሉ ከፍተኛ ስለሆነ ነው። ኢልሴሎ እስከኖርኩ ድረስ የማሪያ ፍላጎት ከእኔ ጋር መኖር ነው።

* * * * * * * * *

ከጆጆ ጋር ወደተቀጣጠርንበትም ቦታ ስሄድም ማሪያ አብራኝ ቦታው ድረስ በመሄድ ሸኘችኝ። ቦታው ላይ ስንደርስም ጆጆ ከላይ እስከ ታች ዝንጥ ብሎ እንደለበሰ ከአንድ ፈረስና ከአንድ በቅሎ ጋር ቆሞ አገኘነው።

ከማሪያ ጋርም ሰላምታ ከተለዋወጠ በኋላም ወደ እኔ ዞሮ "ሰላም ነው ስውዬው... ለጉዞው ተዘጋጅተሃል አይደል? ፀሀይዋ ከአንድ ሰዓት በኋላ መውረድ ትጀምራለች... ማንም እንዲከተለን ስለማልፈልግ ጉዞአችን በአብዛኛው የሚሆነው ሌሊት ነው" አለኝ

ጉዞ ልንጀምር መሆኑን የተረዳችው ማሪያም ወደእኔ መጥታ ደጋግማ ከሳመችኝ በኋላ ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብላ "በትክክለኛው ሰዓት ወደ ሸንት ቤት መሄድህን እንዳትረሳ እሺ" አለችኝ...እኔም ተንከትክቼ ከሳቅሁ በኋላ "አንቺ ይሁዳ... በሩ ስር ተለጥፈሽ ማታ እኔና ጆዜ ያወራነውን ወሬ እየሰማሽ ነበር ማለት ነው" ብዬ ጣፋጭ ክንፈሮቿን ስሜ ተለየኋት

አሁን እንግዲህ ጆጆ በፈረስ ላይ እኔ ደግሞ በበቅሎ ላይ ሆነን ጉዞአችንን ጀምረናል። የምንሄድበት መንገድ ጥቅጥቅ ያለ ጫቃ ቢሆንም 'ፒከስ' ተብለው የሚጠሩ ማቋረጫ መንገዶች ግን በውስጣቸው ይዘዋል። እነዚህ 'ፒከስ' ተብለው የሚጠሩት መንገዶች ስፋታቸው ከሁለት ሜትር የማይበልጥ ሲሆን ሰዎች ይሔንን ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ለማቋረጥ ሲሉ ዛፎቹን በገጀራ በመመንጠር የተፈጠሩ መንገዶች ናቸው።

አሁን ከምንሄድበት ጫካ ትይዩ ደግሞ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ዛፎች መኖሪያ የሆነው ሲልቫ የሚባለው ጥቅጥቅ ያለጫካ ይገኛል። ታዲያ በእዚህ ጫካ ውስጥ የሚገኙ እፅዋቶችን በሁለት መክፈል እንችላለን። የመጀመሪያዎቹ ቁመታቸው ከአምስት ሜትር የማይበልጡ እፅዋቶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ደግሞ ቁመታቸው ሀያ እና ከዚያ በላይ የሆኑ ዛፎች ይገኙበታል። በጫካው ውስጥ

በምናቋርጥበት ጊዜ አንዳንድ ለመንገዳችን ጋሬጣ የሆኑብንን ዛፎች በያዝነው ገጀራ መቁረጥ ግዴታችን ነበር። ይሄንን ድርጊት እየከወኑ በጫካ ውስጥ ማለፉ በራሱ የሚሰጠው የራሱ የሆነ ደስታ አለ። ከተፈጥሮ ጋር ተወዳጅቶ፤ ተፈጥሮን እያደነቁ፤ የመልከዓ ምድሩን አቀማመጥ እየተመለከቱ እንዲሁም የአእዋፋቱንና የእንስሳቱን ድምፅ እየሰሙ ዘና እንደማለት መንፈስን የሚያድስ ነገር ምን አለ?... በእዚህ ጫካ ውስጥ አንድ ጠላት ብቻ አለ የእርጉሞች ሁሉ እርጉም፣ ስግብግቡ፣ ጨካኙ እና በዛው ልክ ማራኪው የሆነው የሰው ልጅ ነው።

ሌሊቱን በሙሉ እየተጓዝን ነበር ያሳለፍነው። ጠዋት ፀሀይ መውጣጥ ስትጀምር ነበር ትንሽ ለማረፍ የወሰነው። በፔርሙስ ይዘነው የመጣነውን ቡና ለሁታችንም ቀድተን ከደረቀ ቂጣ ጋር አጣጣምነው። ተመግበን እንደጨረስን ለተወሰኑ ደቂቃዎች የፀሀይዋን ሙቀት እየወሰድን አንዱ ዛፍ ስር ቁጭ ብለን ማውራት ጀመርን።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ጉዞ ስንጀምር በቅሎዬ መጎተት ጀመረች። በልምጭ እየገረፍኩ ለማፍጠን ብሞክርም ልግምተኛ ሆነችብኝ። ጆጆ ከእኔ ቢያንስ በመቶ ሜትር እርቋል። በቅሎዬ ትዕግስቴን እያስጨረሰችኝ እንደሆነ ሲከታተል ስለነበር የፈረሱን ልጓም ያዝ አድርጎ እኔ እስክደርስበት ድረስ ከቆመ በኃላ "ስለግልቢያ ምንም እውቀት ያለ አይመስለኝም ፓፒለን" ብሎ ሳቀብኝ አስከትሎም..."አይተህ ተማር!" ብሎ ባደረገው ባለተረከዝ ጫማ ፈረሱን ሲኮረኩረው ፈረሱ ፍጥነቱን ጨምሮ መጋለብ ጀመረ። ጆጆ ፈረሱ ላይ እንደሆነም እየጮኸ "ካፒቴን ኩክ እባላለሁ... አንተ ብላቴና ከዋና አዛዡ ዶን ኪዮቴ ጋር መወዳደር አትፈልግም?" እያለ ተንከትክቶ መሳቅ ቀጠለ

ይሄ ንግግሩ በጣም ስላበሳጨኝ ምን አይነት ዘዴ ተጠቅሜ በቅሎዋን ማንቃት እንዳለብኝ ማሰብ ጀመርኩ። ወዲያው አንድ አሪፍ ሀሳብ መጣልኝ... ለማጨስ የለኮስኩት ሲጋራ!... ጊዜ ሳላጠፋ የበቅሎዋ ጆሮ ላይ ተረኮስኩት።እንዴት እንደፈረጠጠች መገመት ቀላል ነው። ከመደበኛው ፈረስ ባልተናነሰ መልኩ ሽምጥ ጋለበች ጆጆን እንኳን ሳይቀር ቀድሜው ከፊቱ ተገኘው። ጆጆን በመቅደሜ አልማዞቹን ያገኘሁ ያክል ነበር የተሰማኝ። ደስታዬ ግን ብዙም አልቆየም ይቺ መከረኛ በቅሎ ከአንዱ ዛፍ ጋር አላትማ ጣለችኝ። እግሬን ከመሰበር የዳንኩት እራሱ በፈጣሪ ቸርነት ነው። ከመውደቄ በላይ ያመመኝ ደግሞ ጆጆ እንደዛ በጀርባዬ መሬት ላይ ተነጥፌ ሲያይ ከማዘን ይልቅ ልቡ እስኪሰነጠቅ ሲስቅ በማየቴ ነው።

እንግዲህ በቅሎዋን ካቃጠልኳት በኋላ ያለውን ታሪክ መናገር ባያስፈልግም በቅሎዋ እላይዋ ላይ እንድወጣ ስላልፈቀደችልኝ ለሁለት ሰዓታት ያህል

በቅሎዋ ከፊቱ እኔ ደግሞ ከኋላዋ በእግር እየተከተልኳት ለመጓዝ ተገደድኩ። በጣም ከመዳከሜ የተነሳ እግሮቼ እየተንቀጠቀጡ ነበር በዛ ላይ ደግሞ የበቅሎዋ እርግጫና ፊስ ሌላ የሚያማርር ነገር ነው። በመጨረሻም ከበቅሎዋ ጋር እርቅ አውርደን ጀርባዋ ላይ ተቀምጬ ለመሄድ ቻልኩ። እንዲህ እንዲህ እያልን ለተከታታይ አምስት ቀናት ያህል ከተጓዝን በኋላ 'ፖሳዳ'የሚባለውን ቦታ ማለፍ ቻልን። በቀጣቹ ሁለት ቀናቶች ደግሞ በታንኳ በወንዙ ላይ ሄድን ከዛም እንደገና ጥቂት ቀናት የፈጀ የእግር ጉዞ ካደረግን በኋላ ነበር የአልማዝ ማውጫ ጉድጓድ የሚገኝበት ቦታ ልንደርስ የቻልነው።

* * * * * * * * *

ቦታው ላይ እንደደረስንም ጆጆ ከዚህ በፊት ወደሚያውቀው አንድ ምግብ ቤት ይዞኝ ሄደ። ድካም ሰውነቴን ከማዛሉ የተነሳ የተሸከምኩትን እቃ እንኳን ለማስቀመጥ ስላልቻልኩ የምንቀመጥበት ጠረጴዛ ላይ ነበር የወረወርኩት። የጆጆን ገፅታ ስመለከተው ደግሞ ምንም አይነት የድካም ስሜት አይታይበትም ፊቱ ላይ በጣት ከሚቆጠሩ የላብ ዘለላዎች ውጪ የተለየ ነገር አይታይበትም። ጭራሽ ወደ እኔ ዞሮ በአትኩሮት እየተመለከተኝ

"እሺ ጓደኛዬ እንዴት ነበር ጉዞው?... ደህና ነህ አይደል?" አለኝ ሳለከልክ አይቶ

ስሜቴ እነቀው እነቀው ቢለኝም እንደምንም አደብ ገዝቼ "ደህና ነኝ... ደህና ነኝ... ደህና እንዳልሆን የሚያረግ ነገር ምን ይኖራል ብለህ ነው... እኔ ያልገባኝ ግን አልማዞቹን የምናገኛቸው ቆፍረን ሳይሆን በቁማር በልተን እስከሆነ ድረስ ለምንድነው እነዚህን አካፋና ዶማ ያሸከምከኝ አልኩት?"

ጆጆም በረጅሙ ከተነፈሰ በኋላ "ፓፒለን አታሳፍረኝ እንጂ ሁሌም ቢሆን በሚስጥር ማውራት እንዳለብን አትዘንጋ... ሲቀጥል እነዚህን መሳሪያዎች ይዘህ ካልመጣህ ታዲያ ምን ልትሰራ መጣህ? ይህ ነው የጥያቄህ መልስ... ገባህ ፓፒለን እዚህ ሁሉም ሰው ሊጠይቅህ የሚችለው ጥያቄም ይህንን ነው። እዚህ የመጣነው ቁማር ለመጫወት መምሰል የለበትም... ተግባባን?"

"እም"

"እኒም ለቁፋሮ የሚያገለግሉ ቁሶች እስካልያዝኩ ድረስ እዚህ ያሉት ሰዎች እኔን ቁማር ልጫወት እንደመጣው አድርገው ማሰባቸው የማይቀር ነው... ስለሆነ ምን አደርጋለሁ መሰለህ እንደምንም ብዬ የሰራም ቢሆን አንድ የውሃ

መምጠጫ ማሽን እገዛለሁ... ከእዚያ በኋላ የተወሰኑ ሰራተኞች እቀጥርና አልማዞቹ ይኖራሉ ብዬ የማስብበት ቦታ ይዣቸው ሄጄ በገዛሁት የውሃ ማውጫ በመታገዝ አልማዞችን እንዲያወጡ አደርጋለሁ... ከዚያም ከሚገኘውን ትርፍ ምንም እንኳን ከሰራተኞቹ ጋር ሄጄ ባልቆፍርም ያለውህ ማውጫው ግን አልማዞቹን ማውጣት ስለማይቻል ከሚገኘው ትርፍ አንድ አራተኛውን እወስዳለሁ...ከሁሉ በላይ ደግሞ እንደዚህ አይነት ነገር ውስጥ የገባሁት ገንዘብ ለማግኘት ሳይሆን ከዚህ በፊት የሚያውቁኝ የዚህ አካባቢ ነዋሪዎች አሁን ወደዚህ የመጣሁት እንደወትሮዬ ለቁማር ሳይሆን ለሥራ እንደመጣሁ ለማስመሰል ስለሚረዳኝ ነው... አሁን በሁሉ ነገር የተግባባን ይመስለኛል ”

“በትክክል”

ወዲያው “ሁለት ፍረስኮስ አምጭልን” አለ ጆጆ ወደ አንዲት አጠር ብላ ወፈር የምትልና የቆዳ ቀለሟ ፈካ ወዳለ የምግብ ቤቱ አሳላፊ ዞሮ... ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላም ያቺ ተግባቢ የምትመስለዋ አሳላፊ ሁለት ቸኮሌት በመሰለ ፈስሽ የተሞሉና በውስጣቸውም በረዶ እና የሎሚ ቁራጭ ያለባቸውን ሁለት ብርጭቆችን ይዛልን መጣች”

“እንግዲህ ስምንት ቦሊቫርስ መሆኑ ነው ጌቶች” አለች አሳላፊዋ ትህትና በሞላበት መንፈስ

“ከሁለት ዶላር በላይ?! እዚህ ኑሮ ከባድ ነው” አልኩ ለራሴ

ጆጆ ሂሳቡን ለአሳላፊዋ እየሰጠ “ነገሮች እንዴት እየሄዱ ነው” ብሎ ጠየቃት

“ጥሩ ይመስላል”

“እንዴት ነው የሚዘረፍ የለም እንዴ” አላት ቁማር የሚጫወት የለም ወይ ማለቱ ገብቶኛል

“ሰዉ በዛ እንጂ አልማዝ የሚያመጣው ግን ትንሽ ነው... እዚህ ቦታ ላይ አልማዝ ከተገኘ አንስቶ በጣም ብዙ ሰው ወደ እዚህ ቦታ ጎርፏል... ቢያንስ ወደ አራት ሺ የሚጠጋ ሰው መጥቷል ለዛ ነው ሰው በዝቶ አልማዙ ያነሰው... እሱስ ማነው?” አለች ወደእኔ እየጠቆመች አስከትላም “ጀርመናዊ ነው ፈረንሳዊ?”

“ፈረንሳዊ ነው... ከእኔ ጋር ነው”

"ውይ ምስኪን ፍጥረት"

"ለምንድነው ምስኪን ፍጥረት ያልሽው" ጆጆ ወሬ እዳያስቀይራት ስለፈለኩ ካፌ እንደወጣ ነበር ተሽቀዳድሜ የጠየኳት

"ምክንያቱም... አንተ ስትታይ ልጅ እና ጥሩ አቋም ላይ ያለህ ሰው ነህ፤ በእዚህ ሁኔታ ላይ እያለህ መሞትህ አሳዝኖኝ ነው፡፡ ከጆጆ ጋር እዚህ መጥቶ ፍፃሜው ያማረ የለም"

"አፍሽን ዝጊ አንቺ ጅል አሮጊት" ጆጆ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ አምባረቀባት ወደእኔ ዞሮም "ተነስ ፓፒ እንሂድ" ብሎኝ ከምግብ ቤቱ መውጣት እንደጀመርን ያቺ አስተናጋጅ ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብላ "ለማንኛውም ራስህን ጠብቅ" አለችኝ

ሴትየዋ በተናገረችው ንግግር ጆጆ ከአሁን አሁን የሆነ ነገር ይጠይቀኛል የሚል የድንጋጤ የፊቱ ገፅታ ላይ ቢነበብበትም እኔ ግን ስለ ሁኔታውም ሆነ ጆዜ ስለነገረኝ ነገር ቃል አልተነፈስኩም ነበር፡፡

ከብዙ መንከራተት እና ሰዎችን ማነጋገር በኋላ ጆጆ ለማደሪያ የሚሆነንን ቤት አገኘ፡፡ ክፍሉ ሰፋ ያለ ቢሆንም መስኮት የሚባል ነገር ግን አልነበረውም ቢሆንም ግን ንፁህና ቀለል የሚል ክፍል ነበረ፡፡ በክፍሉ ውስጥ በጥግና ጥግ ሁለት ምቹ አልጋዎች ነበሩ ገብተን እቃዎቻችንን ካስቀመጥን በኋላ ጆጆ የቤቱን ኪራይ ለመጨረስ ተመልሶ ከክፍሉ እደወጣ እኔም ሙቀት ስለተሰማኝ ቲሸርቴን አውልቄ ቁጭ አልኩ፡፡ ጆጆ የኪራዩን ጉዳይ ጨርሶ ሲመለስ እራቁቴን ሆኜ በማየቱ በድንጋጤ እየተመለከተኝ

"አንተ አብደሃል እንዴ?... እንደዚህ ሆነህ ሰው ቢመጣስ በመጀመሪያ ደረጃ ፊትህ እራሱ ጨካኝነትህን ይናገራል... ሲቀጥል ደግሞ ሰውነትህ ላይ ያሉትን ውቅሮች ቢያዩ ምን ሊገምቱ እንደሚችሉ አጥተኸው ነው? ስነስረዓት ያዝ እንጂ"

"ስለሞቀኝ እኮ ነው"

"ተው... ተው... ምናልባት ፀባይህ ሊሆን ይችላል... እዚህ ግን እንደዚህ አይነት ነገር አይሰራም... ስነ-ስርዓት ያስፈልጋል፡፡ በፈጣሪ ይዠሃለው ደግመህ እንደዚህ እንዳታደርግ" እኔም ከእዚህ ፈሪ ሽማግሌ በሚወጡት ቃላት ላለመሳቅ እየጣርኩ ያወለቁትን ልብስ መልበስ ጀመርኩ፡፡

ማደሪያችን ከያዝን በኋላ ወደ ውጪ ወጥተን የውሃ መምጠጫውንና ማታ የምንጠጣው አንድ ጠርሙስ ሩም ገዝተን ተመለስን፡፡ እኔን ያጓጓኝ ነገር ቢኖር ግን ጨዋታውን የምንጀምርበት ሰዓት ነው፡፡

በክፍላችን ውስጥ ብዙም ሳንቆይ የዳይስ ጨዋታው ወደሚደረግበት መጠጥ ቤት ሄድን፡፡ እዛ ያሉ ሁሉም ሰዎች ሁሌም ጨዋታው የሚጀመረው ምሽት ሁለት ሰዓት ላይ መሆኑን ያውቃሉ፡፡በቤቱ ውስጥ ለቁማር ማጫወቻ የተዘጋጁ ምንጣፎች እንዲሁም በካርበን ፈሳሽ የሚሰሩ ተንጠልጣይ የአምፖል መብራቶች ዝግጁ ነበሩ፡፡

የመጠጥ ቤቱ ባለቤት አንድ ባለ ቀይ ፀጉር ግዙፍ ሰውዬ ሲሆን ሁሌም እንደሚያደርገው ለተቀመጡት ደንበኞቹ የሚፈልጉትን መጠጥ በመቅዳት ላይ ነበር፡፡ እኛም ሁሉ ነገር ዝግጁ መሆኑን ካረጋገጥን በኋላ ምሽት ላይ ቁማር የሚጀመርበት ሰዓት ላይ ተመልሰን ለመምጣት በማሰብ ወደ ያዝነው የማደሪያ ክፍላችን ለመሄድ ከተቀመጥንበት ተነስተን ወደ በሩ በማምራት ላይ እንዳለን ያ ባለቀይ ፀጉር ሰውዬ ጆጆ አልፎኝ እስኪሄድ ጠብቆ ያዝ ካደረገኝ በኋላ ወደ እኔ መጥቶ "ማን አንደሆንክ አላውቅም... ማወቅም አልፈልግም፤ ነገር ግን አንድ ነገር ልንገር ውስጥህ ሰላም የማይሰጥ ሁኔታ ውስጥ ስትገባ ወደግል መኖሪያ ቤቴ መምጣት ትችላለህ" ብሎ መኖሪያ ቤቱ የሚገኝበት አቅጣጫ ነገረኝ፡፡ የሚናገረው ስብርብር ባለ ፈረንሳይኛ እስከሆነ ድረስና የአነጋገሩ ቅላፄ ወደ ኮርሲካዊ አስካደላ ድረስ ኮርሲካዊ ሊሆን እንደሚችል በመጠርጠር "ኮርሲካዊ ነህ?" ብዬ ጠየኩት

"አዎ ኮርሲዊ ነኝ! ታውቃለህ ደግሞ ኮርሲካዊ ቃሉን ከሰጠ ሰጠ ነው! ክህደት የሚባል ነገር አያውቅም" አለኝ ፈገግ እያለ

"አመሰግናለሁ... ስላወቅሁ ደስ ብሎኛል" ብዬው ማታ እንደምንገናኝ ተነጋግረን ከመጠጥ ቤቱ ወጣሁ፡፡

ልክ ከምሽቱ አንድ ሰዓት አካባቢ እኔና ጆጆ ወደእዚያ መጠጥ ቤት ተመልሰን በመሄድ ጆጆ የዳይስ ጨዋታው የሚከናወንበት ቦታ ላይ አምፖሎቹን እንዲበሩ አስደረገ፡፡ በመቀጠል ሁለት ትልልቅ ለመቀመጫ የሚሆኑ ምንጣፎችን መሬቱ ላይ ዘረጋቸው፡፡ ያ ማለት ቁማር ለመጫወት የሚመጣው ሰው በሙሉ ወይ ቁጢጥ ወይ ደሞ ቆሞ መጫወት ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ በዚህ ምሽት ከመመልከት ውጪ በጨዋታው ላይ እንደማልሳተፍ ከጆጆ ጋር ቀደም ሲል ተስማምተናል፡፡

ከጥቂት ደቂቃዎች በኃላም ቁማርተኞቹ ወደ መጠጥ ቤቱ መጉረፍ ጀመሩ። ከመጡት ውስጥ አንዳንዶቹ አጭር ሆነው ወፍራም ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ግዙፍ ሆነው በፊታቸው ላይ ሪዝ ያሳደጉ ነበሩ። የሁሉም ፊትና እጅ ንፁህ ቢሆንም የለበሱት ልብስ ግን የነተበ መሆኑ አስገርሞኛል።

ከተነጠፈው ምንጣፍ መሃል ጆጆ ሞርዶ ያስተካከላቸውን ስምንት የዳይስ ማጫወቻዎች በስነስርዓት ተቀምጠዋል። ጆጆ የአጫዋች ቦታውን እንደያዘ ሲሆን ሌሎቹ በተነጠፈው ምንጣፍ ዙሪያ ተቀምጠው ነበር። ጨዋታው ከመጀመሩ በፊትም ጆጆ ለተቀመጡት ሰዎች ለሁሉም ኩባያ እንዳድላቸው አዘዘኝ። እኔም ትዕዛዙን ተቀብዬ ሃያ ለሚሆኑ ለነዚያ ቁማርተኞች ኩባያ አድዬ አያይዤም ሩም ቀዳሁላቸው። ሁሉም ቁማርተኞች የቀዳሁላቸውን ሩም ከተጎነጩ በኋላ አጠገባቸው ካስቀመጡት ቱቦ መሳይ እቃ ላይ ያስቀምጣሉ። እነዚያ ቱቦ መሳይ እቃዎች ውስጥ አልማዞቹ እንዳሉ ቀደም ብሎ ጆጆ ነግሮኝ ነበር። ሁሉም ተጫዋቾች የሚቆምሩባቸውን አልማዞች በእነዚያ ቱቦ መሳይ እቃዎች ውስጥ አርገው ነበር ይዘው የሚመጡት። ቤቱ ውስጥ ብዙም የሚያወራ ሰው አይታይም። ይመስለኛል ከስራ ተዳክመውም ስለሚመጡ በዛላይ ከፀሃይዋ ንዳድ ጋር ተደምሮ ሁሉንም ያኮረፉ አስመስሏቸዋል። ከተጫዋቾቹ መሃከል አንድ በእድሜው ጠና ያለ ቻይናዊ ከሁሉም ለየት ብሎ ይታያል።

ነገሮች በፍጥነት መካሄድ ጀመሩ። ከተጫዋቾቹ መሃከል አንዳንዶቹ እነዚያን የተደረደሩትን የዳይስ ጠጠሮች ከተቀመጡበት እያነሱ መመልከት ጀመሩ። አንዱ አይቶ ከጨረሰ በኋላ ለሌላው እንዲያስተላልፍ አድርገን ሁሉም ጠጠሮቹን እንዲመለከቱት ተደረገ። ጆጆም ጠጠሮቹን አይተው እንደጨረሱ ወደ ቦታቸው መለሳቸው። ማንም ጠጠሮቹ የተጭበረበሩ መሆናቸውን ሊያውቅ አልቻለም ይሄም የመጀመሪያውን ፈተናችንን በሚገባ ማለፋችንን የሚገልፅ ነው

በመሀል አንዳንድ ከወገባቸው በላይ እራቁታቸውን ሆነው የሚጫወቱት ተጫዋቾች ቤቱ ውሰጥ ባሉት የወባ ትንኞች ተማረው መነጫነጭ ሲጀምሩ ጆጆ ከደረቀው ሳር አምጥቼ በማቀጣጠል በጭሱ ትንኞቹን እንዳጠፋ ነገረኝ፣

በዚህ ሁኔታ ሁሉም ነገር ከተዘገጃጀ እና ለጨዋታ ዝግጁ በሆንበት ሰዓት ነበር ከተጫዋቾቹ መሃል አንድ ፊቱ መዳብ የመሰለ፤ ጥቁር ፂም ያለውና በቀኝ እጁ ላይ የአባበ ውቅር የተወቀረ ሰው "ማነው የሚጀምረው?" ያለው

"ከተመቸህ አንተ ጀምር" አለ ጆጆ

ይህ ፊቱ ጎሬላ የመሰለ ሰው በወገቡ ዙሪያ ከታጠቀው ቀበቶ ውስጥ የተጠቀለሉ ብዙ ገንዘብ ካወጣ በኋላ ከፊት ለፊቱ አስቀመጠው፡፡

ትንሽ ስለዳይስ ጨዋታ ግልፅ ለማድረግ ያክል ስለጨዋታው ህግ ትንሽ ልበላችሁ፡፡ የዳይስ ጨዋታ ልክ እንደ ካርታ ጨዋታ ሁሉ ህጉ ከሀገር ሀገር ሊለያይ ቢችልም ሁሉንም የሚያስማማ አንድ ነገር ግን አለ፡፡ ከተጫዋቾቹ መሃከል እነዚያን የዳይስ ጠጠሮች ሲወረውር ሰባትን ወይንም አስራአንድን የሚያገኝ ከሆነ ተጋጣሚውን ያሸንፋል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ጠጠሮቹን ሲወረውር የሚወጡት ቁጥሮች ሁለት፣ ሦስት ወይም አስራ ሁለት ከሆነ ደግሞ ተጋጣሚው አሸናፊ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ጆጆ አጫዋች እስከሆነ ድረስ መጋጠም የሚፈልጉትን ቁማርተኞች ያጋጥማል እንዲሁም በተጨማሪ መጋጠም ሲፈልግም ይጋጠማል ማለት ነው፡፡መብላት ያለበት ቦታ ላይ ይበላል... እንዲሁም መበላት ያለበት ቦታ ላይ ይበላል፡፡ ይህ ቁማርተኞቹን ለመብላት ተነጋረን ያወጣነው እቅድ ነው፡፡

"በስንት ነው መሄድ የምትፈልገው?" አለ ጆጆ ያንን መዳብ የመሰለ ፊት ያለውን ሰው እየተመለከተ

"በአምስት መቶ ቦሎስ" (ቦሊቫርስ ሲያጥር ቦሎስ ነበር የሚባለው)

"እሺ በአምስት መቶ ቦሎስ" አለ ጆጆ

ያ ባለመዳብ ፊቱም ሁለት ዳይሶችን ከጆጆ እጅ ላይ ከተቀበለው በኃላ አሽከርክሮ ምንጣፉ መሃል ወረወራቸው... ሰባትንምማግኘት ቻለ፡፡ ጆጆም ሊበላ ቻለ፡፡ ጆጆ የተበላው ሆን ብሎ ሲሆን በሂደት ግን ሁሏንም ቁማርተኛ ኪሳቸው ውስጥ ያለውን አልማዝ ሙልጭ አድርጎ እስካልወሰደ ድረስ ከተቀመጠበት እንደማይነሳ ግን እርግጠኛ ነበርኩ፡፡

ታዲያ በእንዲህ አይነት መልኩ አንዱ ሲገባ ሌላው ሲወጣ ለአምስት ተከታታይ ሰዓቶች ጥሞናና ዝምታ በተሞላበት መንፈስ ጨዋታው ቀጥሎ ነበር፡፡ በዚህ ምሽት ጆጆ ወደ ሰባት ሺህ ቦሎስ ከጎኑ ተቀምጦ የነበረ አንድ ቬንዙዌላዊ ደሞ ወደ አስር ሺህ ቦሎስ ተበሉ፡፡ እኩለ ሌሊት ሲደርስ ጨዋታውን ለማቆም ብንስማማም ለተጨማሪ አንድ ሰዓት ቀጥሎ ነበር፡፡ በመጨረሻም ጆጆና ብዙ ብር የበላው ቻይናዊ ለመጋጠም ዙሩ ስለደረሳቸው ጆጆ የዳይሶቹን ጠጠሮች በመያዝ ለመወርወር ሲዘጋጅ ቻይናዊው ጆጆን ጠጠሮቹን እንዳይወረውር ምልክት እያሳየው "አሸናፊ እስከሆንኩ ድረስ መጀመሪያ መወርወር የሚገባኝ እኔ ነኝ" በማለት ጠጠሮቹን ከጆጆ እጅ ላይ ተቀበለ..." ጨዋታውን እኔ እዘጋዋለሁ... ለዛ ደግሞ እስካሁን የበላሁትን

አልማዞችና ዘጠኝ ሺ ቦሎስ መድቤያለሁ" አለ ጆጆም መስማማቱን በአዎንታ ከገለፀለት በኋላ ቻይናዊው የዳይሶቹን ጠጠሮች ወረወራቸው... በሚገርም ሁኔታም የወረወራቸው ጠጠሮች በአንደኛው ጠጠር አራት ነጥቦች በአንደኛው ደሞ ሦስት ነጥብ በድምሩ ሰባትን በማግኘት አሸናፊ ሊሆን ቻለ።የእዚህ ምሽት ፍርቱና ለዚህ ቻይናዊ አመዝና ነበር። የዛሬው የጆጆ እቅድ መበላት ላይ ያመዘነ ነው፤ ይህም ሁል ጊዜ እንደሚያደርገው ሁሉ እሱ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጫና ለማስወገድ ታስቦ የተደረገ እንደሆነ ገብቶኛል። በዚህ መልኩ ጨዋታው ከተጠናቀቀ በኋላ ጨዋታውን በነጋታው ለመቀጠል ሁላችንም ተስማምተን ተለያየን። ጆጆ ሁሉም ቁማርተኞች መውጣታቸው ከተመለከተ በኋላ አጠገባችን ማንም አለመኖሩን አረጋግጦ "ያንን ሰውዬ አይተኸዋል አይደል" አለኝ

"አዎ አይቼዋለሁ" አልኩት በእርግጠኝነት ያንን ቻይናዊ መሆኑ ገብቶኝ ቀጥዬም "ከሁሉ በላይ ያስገረመኝ ግን ሁሉም ቁማርተኛ ሽጉጥና ጩቤ መታጠቃቸው ነው... ጩቤ ያልያዙት እንኳን በጣም ስለታም ከመሆናቸው የተነሳ ባንድ ስንዘራ አንገትን እንደ ክር ለመበጠስ የሚያስችሉ ትልልቅ ገጀራ ታጥቀዋል... እንደዛሬዋ ቀን በራስ ያለመተማመን ስሜት ተሰምቶኝ አያውቅም" አልኩት ምን ያህል ሁኔታው አስፈሪ እንደሆነ እንዲያውቅ ስለፈለኩ

"ሊገርምህ አይገባም... ለቦታው ጠቃሚ ስለሆነ ነው ሁሉም መሳሪያ የያዙት"

"ሊሆን ይችላል... ነገር ግን ጆጆ... ስለእውነት ስነግርህ እንደዛሬዋ ቀን የአደጋ ሽታ ሸቶኝ አያውቅም"

"ትለምደዋለህ ፓፒ... በነገታው አንተ በጨዋታው ላይ ትገባለህ መብላትም እንጀምራለን... ቦርሳችንም በብር ይሞላል ማለት ነው" ብሎ ከት ብሎ ሳቀ... ትንሽ ስንጫወት አምሽተን መተኛት ስለነበረብን ከመጠጥ ቤቱ ወጥተን ለመኝታ ወደተከራየነው ማደሪያ አመራን። ሌሊቱንም በዚያ ምቹ አልጋዬ ላይ ሆኜ በዛሬው እለት ስላሳለፍኩት ከባድ ጊዜ እያሰብኩ ሳላስበው እንቅልፍ ወሰደኝ

* * * * * * * * *

በሚቀጥለው ቀን ገና በቅጡ ሳይነጋ ነበር ፀሃይዋ ሰዉን በቁሙ ለመጥበስ ቆርጣ የተነሳች እስኪመስል ድረስ ንዳዷን መልቀቅ የጀመረችው፡፡ እኔም ፀሃይዋን ለማሳለፍ እና ራሴንም ዘና ለማድረግ በማሰብ ከመንገዱ ዳርዳር የተተከሉትን ዛፎችን ልክ እንደ ጥላ በመጠቀም ምንም ፀሀይ ሳይነካኝ ማታ ቁማር የተጫወትንበት መጠጥ ቤት ደረስኩ፡፡ እንዳጋጣሚ ሆኖም ያንን ባለቀይ ፀጉር ኮርሲካዊ ስላገኘሁት ከእሱ ጋር ቁጭ ብለን ማውራት ጀመርን፡፡ 'ሚግዌል' ይባላል፡፡ የቬንዙዌላውያንን ቋንቋ በፓራሹት የሚወርዱ ከሚመስሉት ከአንዳንድ እንግሊዝኛና ብራዚልኛ ቋንቋ ጋር ደምሮ አቀላጥፎ ይናገራል፡፡ ብቸኛው ችግሩ የፈረንሳይኛን ቋንቋ ሲናገር ነው፤ የዛኔ የኮርሲካዊ ቅላፄው ይታወቅበታል፡፡ አንዱ ወንበር ላይ ቁጭ ብለን ቡና እየጠጣን ማውራት ጀመርን፡፡

"ከየት ነው የመጣኸው?" ብሎ የመጀመሪያ ጥያቄውን አቀረበልኝ

"ትላንት ከተናገርካቸው ጠንካራ ቃለት የተነሳ ልዋሽህ አልችልም!... ከወህኒ ነው የመጣሁት"

"ኦ!... አምልጠህ ነዋ... ስለነገርከኝ ደስ ብሎኛል"

"አንተስ?"

ጥያቄዬ ማስታወስ የማይፈልገውን ነገር እንዲያስታውስ ያረገው ይመስል መከፋቱን በሚያሳይ ንግግር "እኔም አምልጬ ነው... ነገር ግን ከጊዬና አይደለም፤ ኮርሲካ በነበርኩበት ሰዓት ለእስር ከመቅረቤ በፊት ያመለጥኩ ሰው ነኝ... ለክብር ስል ያመለጥቁ ሽፍታ ነኝ!" ይህንን ካለኝ በኋላ ከመቅፅበት ፊቱ ላይ የሚታይ የነበረው ሀዘን ጠፍቶ ፊቱ በደስታ እያበራ "ታውቃለህ ኮርሲካን ሌሎች አለም ላይ ካሉ ሀገራት ስታነፃፅራት እኮ ገነት ነች ማለት ትችላለህ! ለምን መሰለህ በአለማችን ላይ አንድ ሰው ለክብሩ ሲል የገዛ ህይወቱን የሚሰጥባት ብቸኛዋ ሀገር በመሆኗ ነው?"

ከአነጋገሩ እንደተረዳሁት የሆን ደስ የሚል ስብዕና ያለው ሰው ይመስላል

"ብቸኛዋ ሀገር ነች በሚለው ባልስማማም  አዎ ለክብሩ ሲል ምንም ነገር ከማድረግ ወደኋላ የማይል ህዝብ እንዳላት ግን አውቃለሁ" በማለት እርማት ያለውን አድናቆቱን ቸርኩት

በወሬአችን መሀል እዚህ ያመጣኝን ምክንያት ነግሬው... ሀሳቤ ከተሳካልኝ ቶሎ ጨርሼ ወደ ፓሪስ መመለስ እንደምፈልግ እና እዛ ከደረስኩ በኋላ ላሳካው

ስላስብኩት የብቀላ እቅድ በጥቂቱ አጫወትኩት፡፡ በነገራችን ላይ እኔ ላገኘሁት ሰው ሁላ የበቀል እቅዴን እያወራሁ እምንዘባዘብ ሰው አይደለሁም፡፡ ነገር ግን ካሳለፈው ህይወት ትምህርት ይሰጠኛል ብዬ ለማስበው ሰው እቅዴን በመንገሬ ተጠቃሚ የምሆነው እኔ በመሆኔ ነው፡፡ በእንደኔ አይነት አስቀያሚ የህይወት አረንቋ ውስጥ በማለፋቸው ምክንያት ህይወት ራሷ ያስተማረቻቸው ብዙ ሰዎች አሉ ከእነዚያ ጠቃሚ ነገር መውሰድ ብልህነት ነው ብዬ አስባለሁ፡፡

"ትክክል ነህ... ነገር ግን ብቀላ ጣዕሙ የሚታወቀው በተሳካ እቅድ እና በእልህ አስጨራሽ ትዕግስት የተሞላ ሲሆን ነው ካለበለዚያ ግን ውጥንህን ሳታሳካ መቀደም የሚባል ነገር ስላለ ትርፉ ድካም ይሆናል" ካለኝ በኋላ ለትንሽ ግዜ ዝም ብሎ ተመልክቶኝ "ከሽማግሌው ጆጆ ጋር ነው አይደል የምትሰራው?" አለኝ

"አዎ"

"ኮስታራ ነው... አንዳንድ ሰዎች በዳይስ ጨዋታ የሚስተካከለው የለም ይላሉ፤ እኔ ግን አይመስለኝም፤ ለማኝኛውም ከተዋወቃቹ ብዙ ግዜ ሆናችሁ እንዴ?"

"አይ... እሱን ማወቁ ምን ይሰራልኛል ብለህ ነው"

"ለምን ፓፒ አብረህ እየተጫወትክ እንዴት ስለሱ ማወቁ ምን ይጠቅመኛል ትላለህ? ተው እንጂ ፓፒ! ለምን እንደዚህ እዳልኩህ ታውቃለህ?"

"አላውቅም... ለምንድነው?"

"ከእዚህ በፊት ከጆጆ ጋር የመጡ ሁለት ወይ ሶስት ጓደኞቹ ተገለዋል... ለዛ ነው ትላንት ማን እንደሆንክ እንኳን ሳላውቅ የሚያስጨንቅ ሁኔታ ውስጥ ከገባህ ወደ መኖሪያ ቤቴ መምጣት ትችላለህ ያልኩህ"

ስለነገረኝ ነገር ምንም የማላውቅ በመምሰል ለነገረኝ ነገር ሚግዌልን አመስግኜ ከመጠጥ ቤቱ ወጥቼ ስለዚህ የተባረከ ኮርሲካዊ እያሰብኩ በነበረበት ሰዓት ነበር ከመጠጥ ቤቱ ጎን አንድ ከንፁህ ሉል የተሰሩ የተለያዩ የእጅ አንባሮች እንዲሁም ከቀጫጭን ብረት የተሰሩ የእጅ ሰዓቶች የሚሸጥ ሙስጠፋ ከሚባል ነጋዴ ጋር የተዋወቁት፡፡ እንዳጋጣሚ ሆኖ እኔ የደረስኩት ምሳውን ለመብላት እየተዘገጃጀ በነበረበት ሰዓት ስለነበር "ና እባክህ ምሳ አብረን እየበላን እንጨዋወት" አለኝ እኔም ለግብዣው አመስግኜ ለመብላት አብረን ተቀመጥን ሙስጠፋ ዜግነቱ ሞሮኮአዊ ሲሆን የዋህ እና እርጋታ የተላበሰ ሰው ነው፡፡ ከእርሱ ጋር ደስ የሚል ጊዜ አሳለፍን፡፡ ብዙ መጠየቅ አይወድም... እዚህ

አካባቢ ያሉት ሁሉም ሰዎች ማለት ይቻላል እንደተዋወቅኋቸው የመጀመሪያ ጥያቄአቸው የሚሆነው ከየት እንደመጣሁ ነው ሙስጠፋ ግን ይሄንን እንኳን አልጠየቀኝም ነበር። ጨዋታ ለመፍጠር ያክል ግን ወሬ ይጀምራል። ሲጀመርም አስቀድሞ ከየት እንደመጣሁ ሳያውቅ አይቀርም።

"የሚደንቅ ነው አለኝ" ፊት ፊቴን እያየ

"ምኑ?" አልኩት

"ሀገሬ ላይ እያለሁ ፈረንሳዊ የሆነ ዜግነት ያለውን ማንኛውም ሰው እጠላለሁ፤ እዚህ ግን በተቃራኒው

በጣም ነው የምወዳቸው፤ አንተስ የምታውቃቸው አረቦች አሉ?"

"አዎ ብዙ አረቦችን አውቃለሁ... አንዳንዶቹ ሲበዛ ጥሩዎች ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ የአውሬ ባህሪ ያላቸው ናቸው"

"ይሔማ ሁሉም ሀገር ላይ ያለ ነገር ነው። እኔን በተመለከተ እራስህን በየትኛው ጎራ ትመድባለህ ካልከኝ ግን እራሴን ከጥሩዎቹ ወገን እመድባለሁ። አሁን አንግዲህ ስልሳኛ አመቴን ልይዝ ነው።የዛሬን አያርገውና የሰላሳ ስድስት ዓመት ወንድ ልጅ ነበረኝ። በሽጉጥ ተኩሰው ገደሉብኝ እንጂ ቆንጆና ቅን አሳቢ ነበር" አይኖቹ በእንባ መሞላታቸውን ስላየሁ ከመፍሰሳቸው በፊት እጆቼን ትከሻው ላይ እየጫንኩ ለማፅናናት ሞከርኩ። በእዚች ቅፅበት የታወሰኝ ነገር ቢኖር የራሴ አባት ነው። ያቺ ትንሽዬ ቤታችን ውስጥ ቁጭ ብሎ ስለ እኔ ባሰበ ቁጥር እንባ በአይኖቹ ሲቀሩ ይታየኛል... ማን ይሆን የት እንዳለ የሚነግረኝ?... ምን እየሰራ እንደሆነ ሊነግረኝ የሚችለው?... ምን አልባት በእነዚያ ናዚዎች ምክንያት የሆነ ነገር እስካልተፈጠረ ድረስ ውስጤ እርግጠኛ የሆነበት ነገር ቢኖር ተመልሰን እንደምንገናኝ ነው።

ሰዓቴን ስመለከት ሳይታሰብ ነጉዷል። እንደቀልድ ከእዚህ የአረብ ነጋዴ ጋር ሳወራ ለካ ቀኑ መምሸቱን እንኳን አላስተዋልኩም ነበር። ከተቀመጥኩበት በመነሳት ሙስጠፋን አመስግኜ ለመሄድ ስነሳ እሱም ስላወቀኝ እና አብረን ስላሳለፈነው ጊዜ ደስተኛ እንደነበር እንዲሁም የሚያስፈልገኝ ነገር ሲኖር በተመቸኝ ሰዓት መጥቼ ልጠይቀው እንደምችል ነግሮኝ ተሰነባበትን፤ ወድያውኑ ወደ ማረፊያዬ ከሔድኩና ሰውነቴን ከተጣጠብኩ በኋላ የቁማር ጨዋታው የሚጀመርበት ሰዓት ስለደረሰ ወደዚያ መጠጥ ቤት አመራሁ። በቦታው እንደደረስኩም ጆጆ በቦታው ተቀምጦ የቁማርተኞቹን መምጣት ሲጠባበቅ ተመለከትኩት፤ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላም እና የነበረው መጠጥ

ቤት በአንድ ጊዜ በሰዎች መሞላት ጀመረ፡፡ ይባስ ብሎ የመጠጡ የውስጥ ክፍሎች ስለሞሉ አርፍደው የሚመጡ ቁማርተኞች ውጪ ላይ ለመቀመጥ ተገደዋል፡፡ ምንም እንኳን እዚህ ቤት ውስጥ የቁማሩን መንበር የተቆናጠጡት ጆጆ እና አባሎቹ ቢሆኑም ሌሎች እንደየአቅማቸው ቢጤያቸውን ፈልገው የሚጫወቱ ቡድኖች አሉ፡፡ ቀኑ ቅዳሜ እንደመሆኑ መጠን በጣም ሰው በዝቶ ስለነበር የእኛ ቡድን ደግሞ ሁሉንም ማጫወት ስለማይችል ሃያ አራት ረብጣ ገንዘብ አውጥተው መጫወት የሚችሉ ቁማርተኞችን ብቻ ከመረጥን በኋላ ሁሉም ቦታ ቦታውን ይዞ ተቀመጠ፡፡

ጨዋታውም ሁሉም ነገር ዝግጁ መሆኑን ሁሉም ከተስማማ በኃላ ተጀመረ፡፡በዛሬው ጨዋታ ላይ እኔ እንደምገባ እና ገንዘብ መብላትም እንደምንጀምር ከጆጆ ጋር በትላንትናው እለት ተነጋግረንበታል፡፡ በጨዋታው መሃል አንድ የአስራአንድ አመት ልጅ ሩም የያዘ ጠርሙስ ይዞ የቁማርተኞቹን ብርጭቆ እየተዘዋወረ ይሞላ ነበር፡፡ ብዙም ሳይቆይ ጨዋታው መጋጋል ጀመረ፡፡ አስቀድሜ እንደተናገርኩት ጆጆ መጋጠም የሚፈልጉትን ቁማርተኞች እራሱ የዳይሶቹን ጠጠሮች እየወረወረ ያጫውታል. . .እንዲሁም ከእሱ ጋር መጋጠም ከሚፈልጉት ጋርም እንዲሁ ይጋጠማል ማለት ነው፡፡ እስካሁን ባለው ጨዋታ የተወሰኑ ቦሊቫሮች፣ጥቂት የአሜሪካን እና የምዕራብ ህንድ ዶላሮችን በተጨማሪም ጥቂት የማይባሉ አልማዞችን በጆጆ ምክንያት ልበላ ችያለሁ፡፡ ጆጆ የዳይሶቹን ጠጠሮች እንደያዘ "አሁንም በአምስት መቶ ቦሎስ ነው የምትሄደው?" ብሎ ሲጠይቀኝ "አይ በአንድ ሺህ አድርገው" ብዬ ተኩራራሁ ወዲያው ዳይሶቹን ሲወረውራቸው ሰባትን ለመውጣት ግዜ አልፈጀባትም ነበር... አሁንም ሰባት... ቀጥሎም ሰባት... በለው እንደገና ሰባት... እጄ ላይ ብዙ ገንዘብ መግባት ጀመረ፡፡

"አሁንስ በስንት ነው መሄድ የምትፈልገው?" አለኝ ቻይናዊው በእድሌ በጣም ተገርሞ፡፡ በእርግጥ ቻይናዊው ብቻ ሳይሆን ሁሉም ቁማርተኞች እድል ባንድ ጊዜ ወደ እኔ መምጣቷ አሰገሟቸዋል፡፡

"በአራት ሺው እንዳለ" አልኩት የበላሁትን ሁሉንም ገንዘብ ወደፊት ገፋ እያደረኩት፡፡

"እኔ እሄዳለሁ" አለ አንዱ... ቀና ብዬ ይህን የተናገረውን ሰውዬ ተመለከትኩት... እንደ ጥቁር የጫማ ቀለም የጠቆረ ቆዳ እና ሰፋ ያለ ተክለሰውነት ያለው ብራዚላዊ ሲሆን አይኖቹ ከመጠጡ ብዛት የተነሳ ነው መሰለኝ ቀልተውና ጠበው ይታዩ ነበር፤ በደፈናው ሲታይ ምኑም አያምርም፡፡ እኔም ስመለከተው እሱም ሲያየኝ አይን ለአይን ስለተገጣጠምን "አዎ በአራት ሺህ እኔ እሔዳለሁ" አለ... ከዛ ቱቦ መሳይ እቃ ውስጥ አንድ ትልቅ የአልማዝ

ጉማጅ ካወጣ በኋላ ምንጣፉ ላይ አስቀመጠው። ቻይናዊው ወዲያው አልማዙን ከምንጣፉ ላይ በማንሳት አገላብጦ ማየት ጀመረ። ከዚያም ወደ ራሱ ዞሮ "ይህ አልማዝ ሦስት ሺህ አምስት መቶ ቦሎስ ቢያወጣ ነው" አለው

"እሺ እንዳላችሁ በሦስት ሺህ አምስት መቶ ቦሎስ ሔጃለሁ" አለ ሳያቅማማ… ቻይናዊውም ወደ ጆጆ ዞሮ " ተከስ " አለው… ጆጆም ጠጠሮቹን ለመወርወር እጁን ሲያነሳ ያ ብራዚላዊ የጆጆን እጅ ቀጨም አድርጎ ከያዘው በኋላ ጠጠሮቹን ከጆጆ እጅ ላይ ተቀብሎ ምራቁን በመትፋት መልሶ ለጆጆ እየሰጠ "አሁን መወርወር ትችላለህ" አለው ጆጆም ወደ እኔ እየተመለከተ "ፈቃደኛ ነህ?" ብሎ ጠየቀኝ

"እሱ ፍላጎቱ እስከሆነ ድረስ አድርግለት" አልኩት

ጆጆ የዳይሶቹን ጠጠሮች ረዘም አድርጎ ወረወራቸው ሰባትንም ማግኘት ቻልኩ። በዚህን ግዜ ብራዚላዊው እንደ ፌንጣ ዘሎ ነበር የተነሳው… በጣም ከመበሳጨቱ የተነሳ ሳይታወቀው እጁን ወደ ሽጉጡ ልኮት ነበር። ወዲያው ግን ዛሬ የኔ ቀን አይደለም ማለት ነው ብሎ እየተነጫነጨ መጠጥ ቤቱን ጥሎ ወጣ። በእርግጥ እኔም ሁኔታውን ስከታተል ስለነበር እዚህ ከመምጣታችን በፊት ጆጆ ገዝቶ የሰጠኝ ሽጉጥ ላይ እጄን አሳርፌ ነበር የጠበኩት። ጆጆ ግን ምንም ያላየ በመምሰል ነገሩን ችላ ብሎ ለማለፍ ነው የሞከረው። የሚገርመው ደግሞ ብራዚላዊው በነዚያ በሚያስፈሩ አይኖቹ ሲያይ የነበረው እኔን ሳይሆን ጆጆን መሆኑ ነው። ጨዋታው ሌሊቱን ሙሉ ደምቆ ሲቀጥል ለማቆም እንኳን የተገደድነው ጠዋት ፀሃይዋ መውጣት ስትጀምር ነው። ጠዋት እግሮቼ ብርክ እንደያዘው ሰው እየተንቀጠቀጡ ነበር።ለነገሩ ለተከታታይ ዘጠኝ ሰዓታት እንደ አስተናጋጅ ተገትሬ ነበር ስጫወት የነበረው። ቢሆንም ግን ደስ ያለኝ ነገር ቢኖር አንዴም ቢሆን ለሽንት አለመውጣቴ ነው። ይህም ነርቮቼ በእኔ ቁጥጥር ስር መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው።በዚህ መልኩ ጨዋታውን ካቆምን በኋላ ምንም እንኳን የነጋ ቢሆንም የዛለ ሰውነታችንን ለማሳረፍ ስለፈለግን እኔና ጆጆ እስከ ምሳ ሰዓት ድረስ በያዝነው ማረፊያ ውስጥ ተኛን። ከእንቅልፌ ስነቃ ግን ጆጆ አጠገቤ ከነበረው የራሱ አልጋ ላይ አለመኖሩን አረጋገጥኩ። ሱሪዬን ከተቀመጠበት አንስቼ ከለበስኩ በኋላ ወደ ኪሶቼ ስገባ ባዶ መሆናቸውን ተረዳሁ። በውስጡ ማታ በልቼ ካስቀመጥኩት ገንዘብ ድንቡሎ ሳንቲም እንኳን የለም ነበር። ሁሉንም ጆጆ ወስዶብኛል… ግን ለምን?… እራሴን ጠየኩ ገና እኮ ድርሻችንን አልተከፋፈልንም… ነው ወይስ እኔ ነኝ አለቃ የሚለውን ነገር ለማሳየት እሱ ጋር አስቀምጦት ይሆን… የእውነት ጆጆ ሊያጭበረብረኝ አስቦ ከሆነ ልሰጠው ያሰብኩትን ቅጣት እያሰብኩ ስለሁኔታው ሚግዌል ለማማከር

ወደ መጠጥ ቤቱ አመራሁ። በሚገርም ሁኔታም ጆጆን ከሚግዌል ጋር የመጠጥ ቤቱ በረንዳ ላይ ቁጭ ብሎ መኮረኒ እየበላ አገኘሁት።

ምንም እዳልተፈጠረ በማስመሰል "ሰላም ዋላችሁ" ጓዶች ብዬ አንዱን ወንበር ስቤ ተቀላቀልኳቸው። ስለማታው ጨዋታ እያውሩ ስለሆነ ጣልቃ ላለመግባት ለተወሰኑ ደቂቃዎች ዝም ብዬ ቆየሁ። ከጥቂት ደቂቃዎችም በኋላ ከመጠጥ ቤቱ ውስጥ የሚግዌል ስም ስለተጠራ ሚግዌል ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ውስጥ ገባ። ይሄም ለኔ ጥሩ አጋጣሚ ስለፈጠረልኝ በቀጥታ የጆጆን አይን እያየሁ "አዎ ወይም አይ?" አልኩት ይሄን ጊዜ ጆጆ መብላቱን አቁሞ ብብርጭቆ የተሞላለትን ውሃ ባንድ ጊዜ ከጨለጠው በኋላ መልሶ እያፈጠጠብኝ

"ምንድነው አዎ... ወይም አይ?" አለ ያልገባው በመምሰል

"እኔ ሳላውቅና እና ሳልፈቅድ ከኪሶቼ ውስጥ ገንዘቤን ወስደሃል ወይስ አልወሰድክም?"

"ክፉ ለመናገር አትቸኩል እንጂ ፓፒ... አዎ ወስጃለው! የወሰድኩት ግን ለሁለታችንም ጥቅም ሲባል ነው። ይኸውልህ ፓፒ ትላንት አንተ ብዙ ገንዘብ እና አልማዞች በላህ ከዛ የበላኸውን ወደ ራስህ ኪስ ውስጥ ከተትክ፤ እሺ ከአልማዞቹ እና ከወርቆቹ ብትደብቅ እንዴት አውቃለሁ? እኔም ስበላ በተመሳሳይ እንደዛ ባደርግስ? ስለዚህ ሌላ ያለመተማመን ጣጣ ውስጥ ከምንገባ የምንበላውን ሀብት በጋራ እያወቅነው በተጠራቀመ ቁጥር በየጊዜው ድርሻችንን መካፈሉ የተሻለ ስለመሰለኝ ነው እኔም አንተም የበላነውን ሀብት አንድ ላይ ለማድረግ የወሰንኩት"

ሀሳቡ ትክክል እንደሆነ ስለተሰማኝ ስለነገሩ ሌላ ነገር ከማውራት ተቆጠብኩ። በመሃልም ሚግዌል ስለመጣ ወሬያችንን ቀየርን። ጥቂት ተቀምጠን ስለአንዳንድ ነገር ካወራን በኋላ ጆጆ ከኪሱ ገንዘብ አውጥቶ ለሚግዌል ማታ ሩም ለተጠጣበት እና ለተጨሱት ሲጋራዎች ብሎ ሲከፍለው ተመለከትኩ ሚግዌልም ገንዘቡን ከተቀበለ በኋላ ከተቀመጠበት ተነስቶ ወደ ውስጥ ገባ። ሁኔታው ግራ ስለገባኝ "እኔ የምልህ ጆጆ እነሱ ለጠጡበትና ላጨሱበት ስትከፍል ግን ምንም አይነት ጥርጣሬ ውስጥ አትወድቅም?" አልኩት

እሱም እርጋታው ሳይለየው "ሁል ጊዜ ከቁማር ጨዋታው በኋላ ያሸነፈው ሰው ለእዚያ ቡድን ምሽቱን በሙሉ ለተጠጣበትና ለተጨሰበት ገንዘብ አስቀምጦ መሄድ ግድ ነው። ገንዘቡን ሰብስቤ ለባለቤቱ መስጠት የእኔ ድርሻ

ነው:: ይሄንን ደግሞ ሁሉም ስለሚያውቁ የሚያሳስብ ነገር የለም" ብሎኝ ፈገግ አለ::

ምሽት በመጣ ቁጥር የቁማር ጨዋታውም ሁል ጊዜ ይካሄዳል:: እኛ እራሱ እዚህ ከመጣን ሁለት ሳምንት አስቆጥረናል:: እለት ከእለት ከባድ እና አስጨናቂ የቁማር ጨዋታዎች ይካሄዱ ነበር:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተረዳሁት ደግሞ አሁን በመጫወት ላይ ያለነው ቁማር እጅግ አደገኛ ከመሆኑ የተነሳ በህይወት መውጣቴንም ራሱ መጠራጠር ጀምሬአለሁ:: ነገር ግን አንዴ ገብቼበታለሁ እና ፈራ ተባ ማለት አማራጭ ስለማይሆን ብቻ ነው በነገሩ ለመቀጠል እራሴን ያሳመንኩት::

እንዲሁ አንድ ምሽት ሃይለኛ ዝናብ እየጣለ ባለበት ሰዓት ያንን አደገኛ ጨዋታ ከተጫወትን በኂላ ከመሀከላችን አንዱ የተሳካለት እድለኛ የበላውን ገንዘብ እንደያዘ በእዚያ በዝናብ ወደ ውጪ በወጣበት ቅፅበት አንድ ብር ባለመያዙ ምክንያት እኛ የምንጫወተው የቁማር ጨዋታ ላይ ለመግባት ያልቻለ አጭርና ወፍራም ሰው ተከትሎት ይወጣል:: ከሀያ ደቂቃዎች በኂላ ግን የተመለሰው አጭሩ ሰውዬ ብቻ ነበር፤ የተመለሰውም በእጁ ብዙ ገንዘብ ይዞ ስለሆነ ምን አልባት የቅድሙ አሸናፊ አበድሮት ይሆናል ብዬ አሰብኩ፤ አጭሩ ሰውዬም ጨዋታው ላይ ገብቶም በሞራል መጫወት ጀመረ::

ጠዋት ላይ ማታ ዝናብ እየዘነበ ወደ ውጪ የወጣው ሰው ተገሎ ተገኘ! የሚደንቀው ሬሳው የተገኘው እኛ ከምንጫወትበት መጠጥ ቤት ሠላሳ ሜትር ያህል እንኳን አልራቀም ነበር:: ስለሁኔታው ቀድሜ የሰማሁት እኔ ስለነበርኩ ጆጆ ወሬውን የሰማው ከእኔ ነው:: ሁኔታውን የነገርኩት በተደናገጠ ስሜት ቢሆንም ጆጆ ግን ምንም አልመሰለውም ነበር

"ከእኛ ጋር ታዲያ ምን ያገናኘዋል?" እንዲህ ሲለኝ ምንም አይነት የመደንገጥም ሆነ የመደነቅ ስሜት አይታይበትም ነበር

"ሞቷል እኮ ነው የምልህ!"አልኩት በንዴት ጮኼ

"በቃ በሚቀጥሉት ጊዜያቶች ይጠነቀቃላ!" ብሎ ደረቅ ሳቅ ሳቀ

"ሳታብድ አልቀረህም መሰለኝ... ሞቷል እያልኩህ በሚቀጥለው ይጠነቀቃል ትለኛለህ እንዴ?" ብግን ብዬ ነበር

"እሺ ሞተ እኛ ምን ማድረግ እንችላለን ታዲያ?" እኔም መልሱ ስላናደደኝ እዛው በተቀመጠበት ትቼው ወደ ማረፊያዬ ሄድኩ::

* * * * * * * * *

ከጆጆ ጋር ባደረግነው ስምምነት መሰረት አሁን የበላናቸው ገንዘብ ጠርቀም ማለት ስለጀመረ እኩል መካፈል ከጀመርን ቆይተናል። ለቁማሩ ማስኬጃ ከሚሆን የተወሰነ ብር ውጪም እያንዳንዷን ንብረት እኩል ነበር የምንካፈለው፤ ጆዜ የመከረኝንም ገንዘቦቼን በደረሰኝ የማድረጉንም ነገርም በፍፁም አልረሳሁም ነበር። በየጊዜው ከጆጆ ጋር የምካፈለውን ገንዘብ፣ አልማዝ እና ወርቅ ወደ አንድ ሲውዳድ ውስጥ ለሚሰራ ሊባኖሳዊ ጌጣጌጥ ሻጭ እየወሰድኩ እሸጣለሁ። በምትኩም ደረሰኝ እንዲሰጠኝ አደርጋለሁ። ከሱቁ በላይ 'እዚህ ሱቅ ወርቅና አልማዝ በትልቅ ዋጋ እንገዛለን' ይላል ከእሱ በታች ደግሞ 'ታማኝነት ትልቁ ሀብታችን ነው' የሚል ሌላ ፅሁፍ ተለጥፏል። ከሊባኖሳዊው የተቀበልኩትንም ደረሰኝ በስነ-ስረዓት አጥፌ ኪሴ ውስጥ ማስቀመጥ ሁሌም ቢሆን የማረሳው ስራዬ ነው። ጆዜ እንደነገረኝም ገንዘብ አጥፊ መሆኔንና ለዚህም ሲባል ሁሉንም ገንዘቤን በደረሰኝ መልኩ ማስቀመጥ እንደጀመርኩ ሁሉም ሰው እንዲያውቅ አድርጌአለሁ። ስለዚህ በእጄ ላይ ምንም አይነት ገንዘብ እንደማልይዝ ማወቃቸው በተወሰነ መልኩ እኔ ላይ ያለውን ጫና ሊቀንስልኝ ችሏል። ከዚህ ውጪ ብቸኛው ለአደጋ የምጋለጠው በጨዋታው መሃል ወይም ጨዋታው የተጠናቀቀ ሰዓት ነው። ሌላው ግልፅ የሆነልኝ ነገር ቢኖር ቀን ባለፈ ቁጥር የጨዋታው ሚዛን ወደ አስቀያሚ ሁኔታ እየተቀየረ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ። ይሄ ጨዋታ አጨራረሱ እንደማያምር ልቦናዬ እርግጠኝ ከሆነ ውሎ አድሯል።

ይህ ጥርጣሬዬ ደግሞ እንዲሁ ከመሬት ተነስቶ የተከሰተ አይደለም። ለምሳሌ አንድ ቀን እንዲሁ ቁማር በምንጫወትበት መጠጥ ቤት ውስጥ አራት ብራዚላውያን እኛ ከተቀመጥንበት በጥግ በኩል ጨለም ያለ ቦታ ላይ ተቀምጠው የሁላችንንም እንቅስቃሴ እያስተዋሉ እንደሆነ ተመልክቼያለሁ። ዳይስ ለመጫወትም ሆነ ለመደገፍ እንዳልመጡ ገብቶኛል። ሌላው ከአራቱም አንዱም ሽጉጥ ወይንም ገጀራ የያዘ አልነበረም. . .ይህ ደግሞ ሆን ብለው ምንም መሳሪያ አለመያዛቸውን ሰው እንዲያውቅላቸው ለማድረግ የሸረቡት ሴራ ነው። ነገር ግን እንደዚህ አይነት የጨካኝ ፊት ካላቸው ሰዎች ያለምንም መሳሪያ መንቀሳቀስ ጭራሽ የሚያስጠረጥር ነገር ነው!

በቀጣዩ ቀንም እንደዚሁ እነዛ አራት ሰዎች በትላንቱ ቦታቸው እንደተቀመጡ እኛ ላይ እንዳፈጠጡ ነው። ከትላንቱ የሚለየው አሁን አራቱም የለበሱትን ሸሚዝ ከሱሪዎቻቸው ውጪ ማውጣታቸው ነበር። ይህም ሽጉጥ

መያዛቸውንና እንዳይታይባቸው በሸሚዞቻቸው መደበቃቸው መሆኑ ነው። አይኖቻቸው በፍፁም እኛ ቡድን ውስጥ ከሚጫወቱት ቁማርተኞቹ ላይ አይነቀለም ነበር። እኔም እነሱ ሳያዩኝ በተላያየ ዘዴ የእነሱን እንቅስቃሴ እከታተላለሁ። ለምሳሌ ያልመጣብኝን ሳል በመሳል፣ እንደደከመው ሰው በመንጠራራት፣ የቆሪጥ የሚሰሩትን ነገር እያየሁ ሁሏንም እንቅስቃሴያቸውን እከታተል ነበር።

አንድ ሌላ ያስጨነቀኝ ነገር ደሞ የጆጆ በነገሩ ላይ ምንም አለመምሰል ነው። አላያቸው ይሆን? ወይስ ምንም አያመጡም ብሎ ይሆን? ጨዋታው ደግሞ በጣም ከመክረሩ የተነሳ በእልህ የሚጫወተው ይበዛ ነበር። የገንዘቡም መጠን እስከ ዛሬ ከተጫወትንበት እርከን በጣም ከፍ ብሏል።ችግሩ ያን ሁሉ ገንዘብ እየሰበሰብኩት ያለሁት እኔ መሆኔ ነው። ጆጆ ፈጣሪ በቸረው ጥበብ እየተጠቀመ ቁማርተኞቹን እየበላቸው ነው። ገንዘቡ ደሞ ወደ እኔ ኪስ ይገባል!! ይህ ሁኔታ እነዚያን ብራዚላውያን አትኩሮታቸውን ወደ እኔ እንዲያደርጉ ስለሚገፋፋ ጆጆን ማንም ሳያየኝ በተደጋጋሚ እንድበላ ማድረጉን እንዳልወደድኩት ደጋግሜ ብነግረውም ሊሰማኝ አልቻለም።

ጨዋታው ቀጥሏል እነዚያ ብራዚላውያንም እኛ ላይ እንዳፈጠጡ መጠጡን በላይ በላዩ ይቸልሳሉ። እኔም የእነዚያ የብራዚላውያን ፊት ምንም ሊጥመኝ አልቻለም። የሆነ ያቀዱት ነገር ያለ ይመስለኛል። ትንሽ በቦታቸው እንደተቀመጡ ሁለቱ ከተቀመጡበት ተነስተው እኛ ወደምንጫወትበት አካባቢ ጠጋ ብለው ተቀመጡ። ይህም በቅርበት ሁሉንም ለመከታተልና ማን ብዙ እንደበላ ለማውቅ ስለፈጉ እንደሆነ ሙሉ ለሙሉ እርግጠኛ ነበርኩ።

ከሁሉም ደግሞ ብዙ ገንዘብ የበላሁት እኔ ስለነበርኩ ውስጤን ጭንቀት ወረረው። እራሴን ለማረጋጋት ስለፈለኩ የበላሁትን ሁሉንም ሀብቴን እዛው ምንጣፍ ላይ ትቼ ንፋስ ለመውሰድ ወደ ውጪ ወጣሁ። ውጪው ምንም አዲስ የተፈጠረ ነገር የለም፤ ሁሉ ነገር ዝም ብሏል ውስጤ ግን ዝምታውን አልወደደውም ነበር። ተመልሼ ስገባም ሁለት አይኖች እየተከተሉኝ እንደሆነ ለማወቅ መጠበብ አያስፈልገኝም ነበር። ከእነዚያ ብራዚላውያን ውጪ ደሞ የጨዋታው መንፈስ በራሱ እራስን ለመሰብሰብ የማይቻልበት ደረጃ ደርሷል። በመሀከላችን ያለው የእኔ ልብላ እኔ ልብላ ስሜት ጠፍሮ ይዞናል። ይህ በራሱ ወደሌላ አቅጣጫ መቀየሩ እንደማይቀር ግልፅ ነው። ሁሉም ነገር ሰላላማረኝ ለጆጆ አስቀድሜ መንገር ስላለብኝ በፈረንሳይኛ "ሁኔታው ምንም አላማረኝም ጆጆ... መጥፎ አደጋ እየሸተተኝ ነው ስለዚህ ሸጉጣችንን መፈተሽ ካለብን ጊዜው አሁን ነው" አልኩት ሽጉጤ ያለበትን ቦታ እየነካው እያሳየሁት... ጆጆ ግን የምስራች የነገርኩት ይመስል ፈገግ እያለ እሱም በፈረንሳይኛ መልሶ እንዲህ አለኝ

"ጓደኛዬ እንዲህ ያለ የመንበቅበቅ ባህሪ ከየት አመጣህ ችግር አለ እንዴ?"
አለኝ

'ችግር?' በእርግጥ ለጊዜው ችግር የለም... መፈጠሩ ግን አይቀርም ጥግ ላይ ያሉትን ብራዚላውያን ያንን የሩም መጠጥ ልክ እንደ ቡና አይቀዝቅዝባችሁ ቶሎ ጠጡእንደ ተባሉ ሁሉ ብርጭቆዋቸውን ጠረጴዛው ላይ ከሚያስቀምጡበት ጊዜ ይልቅ ወደአፋቸው የሚልኩበት ጊዜ ይበልጥ ነበር። ነገር ግን ምንም እስካልተፈጠረ ድረስ በጆጆ አይን ምንም የሚያስፈራ ነገር የለም! የእሱ እንደዛ መሆን ደሞ እኔን የበለጠ ሰላም ነስቶኛል። በእዚህ ጨለማ ይህን ቤት ለቆ መውጣት አደገኛ ነው ምክንያቱም ውጪ የሚጠብቀኝን ስለማላውቅ ነው ይህ ማለት በአጭሩ ከየት እንደተተኮሰ እንኳን ሳላይ የጥይት እርሳስ ጭንቅላቴ ውስጥ ለማስገባት አይከብዳቸውም ማለቴ ነው። ወደ አንዱ ክፍል ዝም ብዬ ገብቼ ልደበቅ እንዴ? ግን ደግሞ እዛም እኔን ለመግደል የሚፈልግ ነፍሰ ገዳይ አለመኖሩን በምን አውቃለሁ? ምን እንደማደርግ ግራ ገባኝ! በመጨረሻም ምንም የማያሻማ ውሳኔ ላይ ደረስኩ። ሁሉም እንዲያየው በማድረግ የበላሁትን ሁሉንም ገንዘብ በቦርሳዬ ከትቼ እዛው የተቀመጥኩበት ቦታ ላይ ጥሎ ወደ ሽንት ቤት መሄድ... መቼም አምስት ሺህ ቦሊቫርስ ከህይወቴ ሊበልጥ አይችልም!

ወዲያው ቦርሳዬን አንስቼ ሁሉም እያየኝ የበላኋቸውን የብር ኖቶች፣አልማዞቹንና ወርቆቹን በአንድ ላይ ወደ ቦርሳው መክተት ጀመርኩ። ሁሉም መግባቱን ካረጋገጥኩ በኋላ እዛው ቦታዬ ላይ አስቀመጥኩት። ከዛም ሁሉም እንዲሰሙኝ ድምፄን ከፍ አድርጌ "ጆጆ ውስጤን ጥሩ ስሜት እየተሰማኝ ስላልሆነ ሽንት ቤት ደርሼ እስከምመጣ ድረስ ቦርሳዬን እያየኸው" ብዬው ልሄድ ስል "ና ፓፒ ቦርሳህን እኔ ጋር አምጣው እኔ ጋር ቢሆን ይሻላል" አለኝ እኔም ምን አይነት አደጋ ውስጥ እራሱን እየከተተ እንደሆነ ብረዳም ምንም አማራጭ ስለሌለኝ አንስቼ ሰጠሁት... ምን ማድረግ እችላለሁ ታዲያ? እምቢ ማለት? ይሄ ደሞ የማይታሰብ ነገር ነው።

እጆቼን ሽጉጤ ላይ እንዳደረኩ ቤቱን ለቅቄ ወጣሁ። ውጪ ማንም አልነበረም፤ ቢሆንም ግን የተወሰኑ ሜትሮች ከመጠጥ ቤቱ እስከርቀ ድረስ ከአሁን አሁን በጥይት ደፉኝ እያልኩ እየተጨነቅሁ ነበር። ከኋላዬ ማንም እንዳልተከተለኝ ካረጋገጥኩ በኋላ ሩጫ በሚመስል አካሄድ ወደ ሚግዌል መኖሪያ ቤት አመራሁ። ምን አልባት የመጠጥ ቤቱ ባለቤት እሱ ስለሆነ ነገሩን ያበርደዋል በሚል እሳቤ ነው። የሚግዌል ቤት ከመጠጥ ቤቱ የመቶ ሃምሳ ሜትር ያህል እርቀት ነበረው፤ ስለዚህ ቶሎ ለመድረስ ስል መሮጥን መረጥኩ። ቤቱ እንደደረስኩም ጮክ ብዬ "ሚግዌል... ሚግዌል" ብዬ ተጣራሁ

"ማነው እሱ?" ብሎ የመኖሪያ ቤቱን በር ከከፈተ በኋላ እኔን በዚያ ምሽት በማየቱ እየደነገጠ "ምንድነው ችግሩ?" አለኝ ድንጋጤው ሳይለቀው

"ተነስ ቶሎ!... ሽጉጥህን... እና መብራትህን ያዝ ወደ መጠጥ ቤቱ መሄድ አለብን ችግር ተፈጥሯል! አልኩት በሩጫው ምክንያት ትንፋሼ እየተቆራረጠ... ወዲያው ቡም!... ቡም!... ሁለት ጊዜ የተተኮሰ የሽጉጥ ተኩስ ሰማን... ወዲያው የሚግዌልን መልስ ሳልጠብቅ ነበር ወደ መጠጥ ቤቱ መሮጥ የጀመርኩ። ወደ መጠጥ ቤቱ ስገባም ቤቱ ጨልሞ በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ብቻ የእጅ መብራት ይዘው ውር ውር ሲሉ ተመለከትኩ... እኛ ወደተቀመጥንበት ቦታ ስሄድ ግን ማንነቱን ለጊዜው ባላውቅም አንድ ሰው መሬት ላይ በጀርባው መንጋለሉን አስተዋልኩ... ጆጆ ላፔስ ነበር! ከአንገቱ በስተኋላው በኩል ደሙ እንደጉድ ሲጎርፍ ተመለከትኩ። ነፍሱ ባትወጣም ህሊናውን ግን እንደሳተ ነው፤ እኔ ከወጣሁ በኋላ ምን እንደተፈጠረ ስረዳ በመጀመሪያ በካርቦን የሚሰራውን የቤቱን አምፖል በጥይት ከመቱት በኃላ በተመሳሳይ ሰዓት ሌላ ሽጉጥ በጆጆ ማጅራት በኩል ይተኮሳል፤ ከዛ የእጅ ባትሪ በመጠቀም ጆጆ ጋር የነበረውን እኔ የበላሁትንና ጆጆ ራሱ የበላውን ገንዘብ ብቻ ይዘው ይሰወራሉ። ጆጆ ያደረገው ቲሸርት ተቦጫጭቋል፤ እንዲሁም ሁሌም የሚታጠቀው ብርማ ቀበቶው በጩቤ ወይም በገጀራ እንደተቆረጠ ያስታውቃል። በቤቱ ይጫወቱ የነበሩ ቁማርተኞች አሁን አንዱም የለም፤ በእርግጥ እኔ ወደ ሚግዌል ለመሄድ በወጣሁበት ሰዓት በመጠጥ ቤቱ የነበርነው አስራ ሁለት ተጫዋቾች በተጨማሪም እየተዘዋወረ መጠጥ ለደንበኞች ይቀዳ የነበረው የአስራአንድ አመቱ ልጅ እና እነዚያ አራቱ ብራዚላውያን ብቻ ነበርን። በፍጥነት ጆጆን አፋፍሰን ካነሳነው በኋላ ወደ ሙግዌል መኖሪያ ቤት ወስደን አልጋ ላይ አስተኛነው። እስከ ጠዋት ድረስም ከገባበት ሰመመን አልወጣም ነበር፤ ደግነቱ ደሙ መፍሰሱን አቁሟል።አንድ ሞኩፒያ የወርቅ ማውጫ ውስጥ በምሰራበት ወቅት የማውቀው ሰው ደም መፍሰሱ ማቆሙ ጥሩ ቢሆንም ምንአልባት የጥይቷ እርሳስ የጭንቅላቱን ቅል በስታው ከሆነ ደሙ ወደ ውስጥ ሊፈስም እንደሚችል ስጋቱን ከነገረን በኋላ ለማንኛውም እንዳንነካካው ነገረን።

ምሽት ላይ የተከናወኑትን ሁነቶች ከመጀመሪያው እስከ ፍፃሜው ድረስ ለሚግዌል እና ለሙስጠፋ ነገርኳቸው። እነርሱም በጥሞና ካዳመጡኝ በኋላ ሁኔታው ከመፈጠሩ በፊት ጆጆን አስቀድሜ እስካስጠነቀቅሁት ድረስ እኔ ላይ ምንም ፀፀት ሊኖርብኝ እንደማይገባ ነገሩኝ። ሚግዌል በገዛ መጠጥ ቤቱ ውስጥ ገና ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እንኳን ሳይሞላ ለምን ቶሎ ወደ ቤቱ እንደሚሄድ አሁን ነው የገባኝ።

ከስዓት ወደ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ጆጆ ከገባበት ሰመመን ለመውጣት ችሎ አይኖቹን ለመግለጥ ቻለ። እኛም ጉልበት እንዲያገኝ ትንሽ የሩም ጠብጣዎች ወደ አፉ ስለላክንለት ስብርብር ያለ ቢሆንም ለመናገር ግን ችሎ ነበር።አይን አይኑን እያየኝም "ሁሉም የኔ ጥፋት ነው. . .ጓደኛዬ እራስህን እንዳትኮንን አንተ የገባህን እውነት አስቀድመህ ነግረኸኛል... ሁሉም ነገር ያበላሸሁት እኔው ነኝ" ካለኝ በኋላ ለትንሽ ጊዜ ዝም አለ። ከዚያም አይኖቹን ወደ ሚግዌል አዙሮ "ሚግዌል... ከአንተ መጠጥ ቤት ጓሮ ስር በቆርቆሮ ውስጥ አድርጌ የቀበርኩት ገንዘብ አለ... እሱን ለዛ ለባለ አንድ አይናው ሰውዬ ስጠውና ለባለቤቴ ለሎላ ይዞላት እንዲሄድ አድርግ" ብሎት ወደዚያ ወደነበረበት ሰመመን ውስጥ ገባ። ልክ ጀንበር ደህና እደሩ ብላ ከመግባቷ ጆጆም እቺን አለም ለዘለአለም ተሰናብቷት ሄደ።

`ዶና ካርሜንሲታ' ያቺ ወፍራሟ ሴትዮ ገና ወደእዚህ ስመጣ መጠጥ ቤት ውስጥ ከጆጆ ጋር መስራቱ ፍፃሜው ሞት እንደሆነ የነገረችኝ ሴት በእጇ ጥቂት አልማዞች እና ገንዘብ እንደያዘች ጆጆን ለመጠየቅ መጥታ ነበር። የጆጆን ማረፍም በሰማች ጊዜ ድንጋጤዋ ፊቷ ላይ እየተነበበባት ይዛ የመጣችው አልማዞችና ጥቂት ገንዘቦች ማታ ከረብሻው በኋላ መሬት ላይ አግኝታ የሠበሰበቻቸው መሆኑን ገልፃ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠችው።

ለጆጆ የቀብር ስነ-ስረዓት በዛች ትንሽ መንደር ውስጥ የሚኖር ሰው በሙሉ መጥቷል ማለት ይቻላል። እነዚያ የጭራቅ ፊት ያላቸው ብራዚላውያን እንኳን ሳይቀር መጥተዋል። አሁንም ሸሚዞቻቸው ከሱሪዎቻቸው የወጡ ሲሆን ይባስ ብሎ ከእነሱ መሃከል አንዱ ወደ እኔ ሲመጣ አየሁት። እኔም ያላየሁት በመምሰል ልክ አጠገቤ ሲደርስ እንደመዞር ብዬ ያንን እንደ ፊኛ የተወጠረውን ቦርጩን በሆዴ ለመንካት ሞከርኩ አልተሳሳትኩም ነበር! አስቀድሜ እንደጠረጠርኩት ሽጉጡ ሱሪው መሃል ወትፎ በሸሚዙ ሸፍኖታል አሁን አራቱም ሽጉጥ ለመያዛቸው ምንም አይነት ጥርጣሬ የለኝም! ምን ማድረግ እንዳለብኝ ግራ ተጋባሁ... አሁኑኑ ልበቀላቸው ወይስ በኃላ? ውስጤ መልስ የሌለው ጥያቄ ይጠይቀኛል ... ለሁሉም ግን ምንም ለማድረግ ጊዜው ሳያልፍ አይቀርም!

ከቀብሩ በኋላ ብቻዬን መሆን ብፈልግም ሰው ከተቀበረ በኋላ አንዱ መጠጥ ቤት ተገብቶ የሆነ ነገር መቀማመስ ደንብ ስለሆነ ሳልወድ በግዴ ለመቀመጥ ተገደድኩ። ዶና ካርሜንሲታ በአይኗ እኔ ያለሁበትን ቦታ አማትራ አጠገቤ መጥታ ቁጭ ብላ "ጆጆ በመሞቱ ባዘንም ካንተ ይልቅ እሱ በመመረጡ ግን አልተከፋሁም " ካለችኝ በኋላ "አሁን እግዲህ ወደፈለግከው ቦታ በሰላም መሄድ ትችላለህ ማለት ነው"

"በሰላም ስትይ... ምን ማለትሽ ነው?"

"ሁሉም ሰው የበላሽውን አልማዝ ይሁን ጥሬ ገንዘብ እዛ ሊባኖሳዊው ጋር ሄደህ በደረሰኝ መልኩ እንደምታሰቀይር ሁሉም ስለሚያውቁ ምንም የሚያሰጋ ነገር የለም ማለቴ ነው"

"እሱስ ልክ ነሽ... ግን እኮ ትንሽ ከተጠራጠሩ ሊባኖሳዊውን ሊገድሉት ይችላሉ አይደል?" አልኳት

"በትክክል!" አለች ከዚህ በፊት ስታስበው የነበረ ነገር መሆኑን በሚያሳብቅ ሁኔታ

ከዶና ጋር ትንሽ ከተጨዋወትን በኋላ የእኔን እና የሷን ሂሳብ ከፍዬ ከመጠጥ ቤቱ ወጣሁ ለምን እንደሄድኩ ባላውቅም እግሮቼ ጆጆ ወደ ተቀበረበት መቃብር ቦታ ይዞኝ ሄደ። እዛም እደደረስኩ ሙስጠፋ የጆጆ መቃብር ላይ አቀርቅሮ አየሁት

"ምን እያደረክ ነው ሙስጠፋ?" አልኩት

"ለጓደኛዬ ፀሎት እያደረኩለት ነው... በዛውም መስቀል መቃብሩ ላይ ልሰራለት ነው አመጣጤ... ይህንን ማድረግ እኮ ረስተሃል ፓፒ"

"አዎ ማድረግ ነበረብኝ... ጭንቅላቴ በብዙ ነገሮች ተወጥሮ ስለነበር ነው የረሳሁት" ካልኩት በኋላ ምንም እንኳን ከእሱ ሃይማኖት ጋር የማይገናኝ ነገር ቢሆንም ለጓደኛው ሲል ያደረገው ቅን ተግባር ልቤን ስለነካኝ የዚህን አረብ እጅ እየጨበጥኩ ከልብ አመሰገንኩት።

"እኔ የምልህ ክርስቲያን አይደለህም እንዴ? ቅድም ቀብሩ ላይ አፈር ወደ ጉድጓዱ ሲመለስ ስትፀልይ አላየሁህም" አለኝ

"በፈጣሪ አምናለሁ! ከእሱ በተጨማሪም ፈጣሪ ከጆጆ ጋር አብሬ እንዳልሄድ ስላደረገኝ አመሰግነዋለሁ! ለጆጆም ቢሆን ይቅርታ ከማድረግም በላይ እየፀለይኩለት ነው። ይህ ምስኪን ሰው በህይወቱ ይህን ያህል ዓመት ሲኖር የተማረው ነገር ቢኖር ዳይሶችን መወርወር ብቻ ነው"

"ምንድነው የምታውራው ጓደኛዬ ምንም ሊገባኝ አልቻለም" አለኝ ሙስጠፋ ፊቱ ግራ መጋባቱን በሚገልፅ አይታ

"ተወው በቃ! ዋናው ነገር በጆጆ ሞት በጣም አዝኛለሁ... ህይወቱን ለማትረፍ የተቻለኝን ሁሉ አድርጌአለሁ... አሁን እንግዲህ ጆጆ በሰላም ተኝቷል። ከሚወደው ተፈጥሮ እና ጅብዱ ጋር ላይነሳ ለዘላለም ተኝቷል። የእግዚአብሔር ይቅርታም ከእሱ ጋር እንዲሆን ምኞቴ ነው!"

"እም ፈጣሪ ይቅር እንደሚለው እማ አልጠራጠርም እንዴት ያለ ጥሩ ሰው ነበር" አለ ሙስጠፋ መቃብሩ ላይ እያፈጠጠ

"እውነት ነው"

ከሙስጠፋ ጋር ከተለየሁ በኋላ ወደ ማደሪያዬ በመመለስ ላይ እያለሁ ስለጆጆ እያሰብኩ ነበርኩ፤ ምንም እንኳን ለእኔ መሞት በቀጥታ ተጠያቂው እሱ ቢሆንም ምንም አይነት ቅሬታ በእሱ ላይ አላደረብኝም ነበር። በስልሳ አመት እድሜው የአዕምሮ አስተሳሰቡ እና ቅልጥፍናው የሚወስዳቸው እርምጃዎች በእርግጥ ሁሌም እንዳስደመሙኝ ነው። በዛ ላይ ስለ ስነ-ስርዓት ያለው አመለካከት ደስ ይል ነበር። መጀመሪያ የያዝነው ማደሪያ ውስጥ እራቁቴን ሲያየኝ 'ስለፈጣሪ ብለህ ፀባይህን አርም' ያለኝ ትዝ አለኝ። ታዲያ ለእኔ መትረፍም ዋና ምክንያት የጆዜን ምክር መስማቴ እንደሆነ ጥርጥር የለውም! ያለእሱ ምክር እዚህ ልገኝ አልችልም ነበር።

ወደ ክፍሌ እንደገባሁ ተንጠልጣይ አልጋ ላይ ጋደም ብዬ ሲጋራዬን ለኩሼ ጭሱን እነዚያን ንክሻቸው እንደ መርፌ የሚያመውን ቢንቢዎች ላይ መንፋት ጀመርኩ። ከጭስ ውጪ ሌላ አማረጭ ስለሌለኝ ሳንባዬን ለሲጋራው ኒኮቲን መስዋት አድርጌ በላይ በላዩ ነበር የማጨሰው። ተንጠልጣይ አልጋዬ ላይ እንዳለሁም አሁን ስለቀረኝ ገንዘብ ማሰብ ጀመርኩ። በእርግጥ ጆጆ የተገደለበት ቀን ካጣሁት ገንዘብ ውጪ ከዛ በፊት በነበሩት ጨዋታዎች ያጠራቀምኩት አስር ሺህ ዶላር አለኝ። ስለዚህ አሁን ከኔ የሚጠበቀው ነገር ወደ ኢልሴሎ በመመለስ ሊባኖሳዊ የሰጠኝን ደረሰኝ መመንዘር ነው።

አሁን እንግዲህ ሠላሳ ዘጠነኛ አመቴን ይዣለሁ፤ ከእነዚያ አስራ አራት የስቃይና ተስፋ አስቆራጭ የእስር ጉዞዬ በኋላ ራሴን ለመቀየር እንዲሁም የበቀል እቅዴን ለማሳካት የሚጠቅመኝን ገንዘብ ለማግኘት ብዙ ጥረት አድርጌአለሁ። እንደማገኘውም ሰራተኛ አካፋና ዶማ ይዞ ቆፍሮ የእለት ጉርሱን ለመሸፈን እደሚጥሩት ሰዎች መሆን በጭራሽ አልፈልግም። በእርግጥ ልጅ እያለሁ የመሰናዶ ትምህርቴን ብጨርስም ሙያ የሚጠይቁ ስራዎችን ለመስራት ግን በቂ አልነበሩም ነበር። እንደዛም ቢሆን ግን በትምህርት ያጣሁትን እውቀት ህይወት ራሷ አስተምራኛለች፤ ለዚህም ፈጣሪዬን አመሰግነዋለሁ!

ያም ሆነ ይህ አሁን እኔን የሚያስጨንቀኝ ነገር ቢኖር ስለብቀላ ውጥኔ ነው፡፡ ለአስራ አራት አመት የተፋለምኩለት ነፃነቴ ለምን ሆነና... ነፃነቴን ነፍገውና ቤተሰቦቼን ችግር ውስጥ እንዲገቡ ላደረጉት ሰዎችማ ቅጣት መስጠት አለብኝ! 'ተረጋጋ እንጂ ፓፒ... እቅድህን ለመተግበር እኮ በቂ ግዜ አለህ' አልኩ ለራሴ

ሁሉንም ነገር ትቼ ዘና ብዬ ለመተኛት በማሰብ በጀርባዬ ከተመቻቸው በኋላ አይኖቼን ከደንኳቸው አዕምሮዬ ግን ማሰቡን አልተወም ነበር... አሁንም አሁንም ነፃ... ነፃ... ነፃ ሰው ነህ!! እያለኝ ነበር!

# ምዕራፍ አራት

## ወደ ኢል ሴሎ መመለስ

ጠዋት ወደ አራት ሰዓት አካባቢ ሊባኖሳዊውን ለማግኘት ወደ ሱቁ አመራሁ። እንዳጋጣሚ ሆኖ ሱቁ ውስጥ ጌጣጌጦችን እያፀዳና እያስተካከለ አገኘሁት። ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላም በቀጥታ ወደ እሱ ያመጣኝን ጉዳይ ማውራት ጀመርኩ

"እኔ የምልህ... ከእኔ የሚጠበቀው የሰጠኸኝን ደረሰኞች... ኢል ሴሎ ውስጥ ወይም ሲዩዳድ ወደሚገኘው ያንተ ተወካይ ጋር ሄጄ ደረሰኞቹን አንተ እንደሰጠኸኝ ተናግሬ ገንዘቤን መመንዘር ብቻ ነው አይደል?"

"በሚገባ... አሰራሩም እንደዛ ነው"

"ነገር ግን እኔ እዛ ከመድረሴ በፊት አንተን ቢገድሉህስ?"

"አያሳስብም! እኔ ላይ ምንም ነገር ቢፈጠር ይከፍሉሃል... ወደ ኢል ሴሎ ልትመለስ ነው እንዴ?"

"አዎ"

"ከየትኛው የፈረንሳይ አካባቢ ነው የመጣኸው?"

"ከአቪግኖን አካባቢ... ከማርሴል ብዙም አትርቅም"

"ይገርማል! እኔም ከማርሴል የመጣ አሌክሳንደር ጉጁ የሚባል ጓደኛ አለኝ... አሁን ግን ከዚህ በጣም እርቆ የሚገኝ ቦታ ላይ የራሱን ኑሮ መስርቶ እየኖረ ነው።

"አጋጣሚው ለእኔም አስገራሚ ነው አሌክሳንደርን ጉጁን እኔም አውቀዋለሁ። እንደውም የቅርብ ጓደኛዬም ጭምር ነበር"

"ኸረ?... ስላወቅኸው ደስ ብሎኛል"

ፈረንሳይ ውስጥ የማውቀውን የድሮ ጓደኛዬን ለማግኘት በጣም ስለጓጓሁ በዛ ላይ በጆጆ ሞት ምክንያት የተጨናነቀውን አዕምሮዬን ለምን አላፍታታም የሚል ሀሳብ ስለመጣልኝ

"አሁን ታዲያ የት ነው የሚኖረው አልከኝ?እንዴትስ ነው መሄድ የምችለው?" አልኩት

"ቦዋ ቪስታ የሚባል ቦታ ነው የሚኖው... ከዚህ ተነስተህ ለመሄድ በጣም ውስብስብና ረጅም መንገድ ይጠብቅሀል"

"እዛ ምንድነው የሚሰራው?"

"ፀጉር ቆራጭ ነው... በቀላሉ ፈረንሳዊውን ፀጉር ቆራጭ አሳዬኝ ብትላቸው ማንም ያሰይሃል" አለኝ

'ታዲያ ፓፒ ምን ታስባለህ' አልኩ ለራሴ ብሄድ ምን ችግር አለው... እዛ የሚያጋጥመኝን እድል ደግሞ መሞከር አለብኝ ብዬ ለመሄድ ወሰንኩ... ሊባኖሳዊው እንደነገረኝ ከሆነ ከቁማሩ የበላሁትን ገንዘብ በፈለኩት ሰዓት ወደ ኢል ሴሎ ተመልሼ መመንዘር እስከቻልኩ ድረስ አሌክሳንደር ጋር ለተወሰኑ ወራቶች ቆይቼ ብመጣ አንድም ለመንፈሴ እርካታ አንድም ደግሞ እዛ ህይወት የምትሰጠኝን አዲስ ነገር ካለ ለመቅሰም ይጠቅመኛል፡፡ ከሊባኖሳዊው እንደተለየሁ በዚህ እና በመሳሰሉትን ሀሳብ ተወጥሬ ነበር የማደሪያ ክፍሌ የደረስኩት፡፡ ያስፈልጉኛል ብዬ የማስባቸውን እቃዎች በቦርሳዬ ከታትቼ ካዘገጃጀሁ በኋላ ከክፍሌ ወጥቼ ወደ ቦታው ሊመራኝ የሚችል ሰው ማፈላለግ ጀመርኩ፡፡

ብዙም ሳልንከራተትም ሁለት ሰዎችን አነጋግሬ ወደብራዚል የሚያስኬደውን መንገድ አጥርተው እንደሚያውቁና የምፈልገው ቦታ ድረስ እንደሚያደርሱኝ ስምምነት ላይ ደረስን፡፡ በጉዞው ወቅት የሚያስፈልገኝን ምግብና ለመኝታ የሚሆኑ ቁሶችን ሊይዙልኝ ተስማምተን ጉዞ ጀመርን፡፡ ነገር ግን ለአስር ቀናት ያህል ብንጓዝም ብራዚል ከመድረሳችን በፊት የሚገኘውን የቅዱስ ሄሊናን የወርቅ ማውጫ እንኳን ልናገኘው አልቻልንም ነበር፡፡ በመጨረሻም ራሳችንን አሚኖስ ተብሎ ከሚጠራ የብሪቴን ድንበር ለመድረስ ምንም ያህል ከማይቀረው የወርቅ ማውጫ መንደር ውስጥ ራሳችንን አገኘነው፡፡ እዛም የሆኑ ህንዶችን አግኝተን በተሳሳተ መንገድ መምጣታችንን ነግረውን እንደትብብር የኪዩኒንን ወንዝ እንድናገኝ ከረዱን በኋላ እሱን ተከትለን 'ትንሿ ቬንዙዌላ' ወይም

'ካስቴሎ' ተብሎ የሚጠራው ቦታ ድረስ በህንዶቹ ሽኝት ደረስን፡፡ እዛም እንደደረስን ህንዶቹ ላደረጉልን ቀና ትብብር ለሁሉም ገጀራ በስጦታ መልክ ሰጥቼ አሰናበትኳቸው፡፡ ቀጥዬም እነዚያን ሳያውቁ እናውቃለን ብለው ያንከራተቱኝን ሁለት ሰዎች በተፈጠረብኝ ንዴት ምክንያት አንድ ነገር ከማድረጌ በፊት አይናቸውን ላለማየት ትቻቸው ብቻዬን ጉዞ ጀመርኩ፡፡ ከዚህ በኋላም በድካሙ ምክንያት ወደ ቦዋ ቪስታ የመሄድ ፍላጎቴ ሙሉ ለሙሉ ስለጠፋ ወደ ኢል ሴሎ የሚመልሰውን መንገድ ከሚያውቅ አንድ መንገደኛ ጋር በመሆን ተጉገዤ ከአምስት ቀናት በኋላ ኢልሴሎ ልደርስ ቻልኩ፡፡

ወደ እነ ማሪያ ቤትም ስደርስም መሽቶ ነበር፤ ወደበሩም ሄጄ ከፍቼ ስገባ ኢስመራልድ በሩ አካባቢ ስለነበረች ልክ እንዳየችኝ "እሱ ነው! እሱ ነው!" ብላ ላንቃዋ እስኪሰነጠቅ ድረስ መጮህ ጀመረች፡፡ ካሳለፍኳቸው አሰቃቂ ጊዜአቶች በኋላ በፍቅር አይን የሚመለከተኝ ሰው በማግኘቴ ሀሴት እየተሰማኝ ኢስመራልድን ትከሻዋን ያዝ አድርጌ በእጆቼ ዝም እንድትል ምልክት ሰጠኋት፡፡

"ይሄ ሁሉ ጩኸት ለማን ነው?" እያለች ማሪያ ከጓዳ ስትወጣ እኔን በማየቷ ያልጠበቀችው ነገር በመሆኑ በደስታ ከአይኖቿ የእንባ ዘለላዎች እየተንጠባጠቡ ሮጣ መጥታ ተጠመጠመችብኝ፡፡ እሷን ሰላም ካልኩ በኋላ ፒኮሊኖ ወደ ተቀመጠበት ቦታ ሄጄ አቅፌ ሰላም አልኩት፤ ቀጥሎም ጆዜንና የቀሩትን የማሪያን እህቶች ሰላም ብዬ አንዱ ወንበር ላይ ተቀመጥኩ፡፡ ማሪያ አጠገቤ ተቀምጣ ጡት እንዳየ ህፃን ትፍለቀለቃለች... ማንም ጋር ሳልሄድ እነሱ ጋር መሄዴ በጣም አስደስቷታል፡፡ ምንም እንኳን በመምጣቴ ብትደሰትም ኢል ሴሎ የመቆየት አላማ እንደሌለኝ ጠንቅቃ ስለምታውቅ አይን አይኔን እያየች "ኢልሴሎ ለትንሽ ጊዜ አትቆይም?" አለችኝ

"ነገሮች እስኪስተካከሉ ድረስ ለትንሽ ጊዜ እቆያለሁ"

"ይሁን ደስ እስካለህ ድረስ ቆይ... ደግሞ እራስህን መገንባት መቻል አለብህ በጣም ከስተሃል እኮ... ለነገሩ ካሁኗ ሰዓት ጀምሮ ስለምንከባከብህ ሙሉ ሀይልህ በቅርቡ ይመለስልሃል ውዴ... ተመልሰህ መሄድህን ባልወደውም ባንተ ግን አልፈርድም ምክንያቱም አስቀድመህ እዚህ መኖር እንደማትፈልግ ነግረኸኛል እና ነው፡፡ ስለዚህ ጠንካራ ሴት መሆን መቻል ይኖርብኛል፡፡ አንተም ሁሌም ጠንካራ እንድትሆንልኝ እፈልጋለሁ... ወደ ምትመኛት ካራካስ ስትሄድ የሚገጥምህን አታውቅምና በርታልኝ" ብላ ጉንጬ ላይ ሳም አድርጋኝ እራት ለመስራት ወደ ኩሽና ገባች፡፡

ከአራት በኋላም በማሪያ ክንድ ላይ ተንተርሼ በክፍላችን ውስጥ እንደተኛን ስለዚህ ቤተሰብ ዝም ብዬ እያሰብኩ ነበር። በዚህ ተፈጥሮ ባደለቻት መንደር ውስጥ ከወርቅና እና ከብር በላይ ፍቅር እንደልብ መሸመት ይቻላል። ለሰው ልጅ ያላቸው ክብር በጣም ጥልቅ ነው። አንድ የማያውቁት ሰው ወደ መንደሩ ከመጣ ከእሱ ማለት የሚጠበቀው ነገር ቢኖር "እንግዳ ነኝ" ማለት ብቻ ነው... እነሱም "ቤት የፈጣሪ ነው ቤታችን ቤትህ ነው" ከማለት ውጪ ሌላ ምላሽ አይሰጡም... ሌላው የሚያስጨንቀኝ ነገር ስለማሪያ ሳስብ ነው። ሲፈጥራት ገና የፍቅር ሰው እንድትሆን አድርጎ የሰራት ሴት ነች!! ሁል ጊዜ ስለእሷ ሳስብ የውስጤን ሰላም አጣለሁ፤ እስክሞት ድረስ አብሬያት ብኖር ደስተኛ ነበርኩ። ግን ምን ዋጋ አለው ይህን እንዳላደርግ ደግሞ ከእሷ በፊት ልቤ ላይ ያተምኩት ሌላ እውነት አለ።

እኔ ማለት እኮ በተንደለ ፍረድ ዘመኔን በመማቀቅ ያሰለፍኩ ሰው ነኝ!! ይሄ ደግሞ እውነት ነው!! በእርግጥ የማልዋሸው ነገር ቢኖር ምንም እንኳን ዘመኔን በስቃይ ባሳልፍም በህይወቴ ውስጥ ግን አስደሳች የሚባሉ ጀብዱዎችን ፈፅሜአለሁ። አደገኛ የሚባሉ ወጥመዶችንም በጣጥሼ ለማለፍ ችዬአለሁ። ያ ደግሞ ማንም እንደፈለገ ሊያገኘው የማይችል የውስጥ እርካታን አግኝቼበታለሁ።

አሁን እንግዲህ ከባድ ውሳኔ የሚያስፈልገው ቦታ ላይ እደሆንኩ ይሰማኛል። ሁለት ምርጫ አለኝ አንዱ ከእነዚህ እንደማር ከሚጣፍጡ ሰዎች ጋር ተወዳጅቶ መኖር አለበለዚያ ደግሞ ለዘመናት እንቅልፍ ሲነሳኝ የነበረውን ያለ ምክያት ለመታሰሬ ምክንያት ለሆኑት ሰዎች ትምህርት መስጠት የሚሉት ናቸው። ለሁሉም ነገር ለመወሰን በቂ ግዜ ስላለኝ እራሴን በእዚች ሌሊት ውሳኔ ላይ ካልደረስክ ብዬ ማጨናነቁ ትርጉሙ ስላልታየኝ ከጎኔ የተኛችውን ቆንጆ አቅፌ ለመተኛት አይኖቼን ከደንኳቸው።

በቀጣዩ ቀን ከእንቅልፌ እንደነቃሁ ሊባኖሳዊው ሰው በሰጠኝ አድራሻ መሰረት የተቀበልኩትን ደረሰኝ ለመመንዘር ተወካዩ ወዳለበት ቦታ ሄድኩ። በእርግጥ ተወካዩን ለማግኘት ችዬ ነበር ነገር ግን ሊባኖሳዊው ላይ ብዙ ብር እዳለበትና ያንን በቅድሚያ እዲከፍል ስላስገደደው ደረሰኞቹን ሊመነዝርልኝ እንደማይችል ነገረኝ። ስለዚህ እኔም ሲዩዳድ ውስጥ ወደሚገኘው የሊባኖሳዊው ሁለተኛ ተወካይ ጋር መሄድ እዳለብኝ የወሰንኩት ወዲያው ነበር "እኔ የምልህ ሊባኖሳዊው ከአንተ ውጪ ሲዩዳድ ውስጥ ለሚገኘው ሌላ ተወካዩ ጋር ሄጄ ደረሰኞቼን መመንዘር እንደምችል ነግሮኝ ነበር... ታውቀው ይሆን?"

"በደንብ ነዋ! እልም ያለ ሌባ ነው... አሁን ደህይቷል። አሁንማ ጭራሽ በአደራ የሚሰጠውን እቃ ሁሉ መውሰድ ጀምሯል። እኔ ራሱ የሆነ እቃ ሰጥቼው

ይኸው የውሃ ሽታ ሆኖብኝ ከቀረ ስንት ግዜው መሰለህ" አለኝ በሚያንቋሽሽ ንግግር

"እና መሄድህ ዋጋ የለውም በለኛ?"

"እንደዛ ነው የሚሰማኝ"

ይሄ ጅል የሚመስለው ሰውዬ የነገረኝ ነገር እውነት ከሆነ ነፍሴን ሽጬ ያጠራቀምኩትን ወደ አስር ሺህ ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ ህልም እንደሚሆን አልጠራጠርም። ይህንንም ተከትሎ ከፍተኛ የገንዘብ ቀውስ ውስጥ እንደምገባ እርግጥ ነው። በዚህ ሰዓት እየተሰማኝ ያለው ነገር ቢኖር እንደዚህ አይነት ችግር እኔ ላይ ብቻ እየደረሰ እንዳለ ነው። እንደዚህ አይነት ችግር ውስጥ ለመግባቴም ዋና ተጠያቂው ያ ወሸካታ ሊባኖሳዊ መሆኑ ግልፅ ነው። እነዚያን በተራ ደረሰኝ ወረቀት የቀየርኳቸውን አስር ሺህ ዶላሮች ለማግኘት ቢያንስ ከሀያ ላላነሱ ጊዜአቶች እራሴን አደጋ ላይ ጥያለው። በዛ ላይ ደግሞ አብሬው የተንዝኩትን ጓደኛዬን አሳጥቶኛል። ታዲያ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ያገኘሁትን ገንዘብ ያ መሽቁቅ ሊባኖሳዊ እንደኛ ህይወቱን አደጋ ላይ ሳይጥልና ምንም አይነት አስዋፅኦ ሳያደርግ አስር ሺህ ዶላር ወደ እሱ ካዝና አስገብቷል! በዚህ ይሁዳ ሊባኖሳዊ ብናደድም በጥበቡ አታሎ ስለወሰደብኝ ብልህ መሆኑን ማመን ግን ግዴታዬ ነው!

* * * * * * * * *

ወደ ቤት በምመለስበት ሰዓት አዕምሮዬ ከማሰብ አልቦዘነም ነበር፤ ተሳካልኝ ስል በድጋሚ በሰዎች ቁጥጥር ስር ልወድቅ ነው ስለዚህ ቶሎ ተመልሼ ያንን ሊባኖሳዊ ማግኘት አለበኝ! ያለበለዚያ ግን ሊያመልጠኝ ይችላል። ስለዚህ ጊዜ ሳላጠፋ ወዲያውኑ ስጉዞዬ የምትሆን በቅሎ አፈላልጌ ለመሄድ ወሰንኩ።

አሁንም በእጄ ላይ ጆጆ የገዛልኝ ሽጉጥ እና ጩቤዬ ስላለ የሚያስፈራ ነገር አይኖርም። ብቸኛው ችግር የሆነብኝ ወደ አልማዝ ማውጫዎቹ የሚወስደውን አቅጣጫ አለማወቄ ነው። ቤት እንደደረስኩም ለማሪያ ስለ ሁኔታው ሳስረዳት ለመንገዱ ከበቅሎ ይልቅ ፈረስ የተሻለ አማራጭ መሆኑን ስለነገረችኝ በሃሰቧ ተስማምቼ ፈረስ ተከራየሁ

"እኔ ምልሽ ማሪያ የመንገዱን አቅጣጫ ግን በደንብ አላስታውሰውም... ምን ባደርግ ይሻላል?" አልኳት

"እኔ እኮ አውቀዋለሁ ለምን አብሬህ አልሄድም?" አለች ፊቷ ላይ የደስታ ስሜት እየታየባት "ከእኔ ጋር እስከወንዙ ድረስ አብረን እንሄድና እኔ የተጓዝንባቸውን ፈረሶች ይዤ እመለሳለሁ" አለችኝ አሁንም ፊቷ እንደበራ

"ላንቺ በጣም አደገኛ ነው ማሪያ በተለይ ስትመለሺ ብቻሽን ነው"

"ለእሱ አትጨነቅ ወደ ኢልሴሎ የሚመለስ ሰው ጠብቂ አብሬ እመለሳለሁ... እባክህ እሺ በል" አለችኝ እንደፃን ልጅ እየጠቀለሰለሰች

"እሺ ግን በመጀመሪያ ከጆዜ ጋር ላውራበት" ብያት ጆዜ ወደተቀመጠበት ቦታ ሄጄ ስለሁሉም ነገር ነገርኩት፤ እሱም ነገሩን እኔ እንዳሰብኩት ሳያከብደው አብራኝ መሄድ እንደምትችልና ለማንኛውም ነገር ደግሞ የገዛ ሽጉጡን እንደሚሰጣት እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ስለምታውቅበት ምንም የሚያሳስብ ጉዳይ እደሌለ ስለነገረኝ ውስጤ ሰላም አገኘ።

ከጥቂት ቀናት በኋላም ሌላ ሁለተኛ ፈረስ ለማርያ ተከራይተን ለጉዞ ተሰናዳን። ማሪያ 'ሊና' ከምትባል ቬንዙዌላዊ ጓደኛዋ በስጦታ መልክ የተሰጣትን የሰውነቷን ቅርጽ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ጥብቅ ያለ ሱሪ አድርጋለች፤ ሊና የማትመስጥና ግዙፍ ሴት ነች! እሷ በተወለደችበት ቀዬ ያሉ ሴቶች ነገረ ስራቸው ሁሉ እንደ ወንድ ነው። ሽጉጥ አነጣጥረው ሲተኩሱ ወንድ ተኳሽን ያሳፍሩ ነበር። ገጀራ አጠቃቀማቸው በጣም የሚያስደንቅ ነው። በዛ ላይ ትዕግስት የሚባል ነገር ፈፅሞ አልፈጠረባቸውም። እንደዛም ቢሆን ግን ለፍቅር ራሳቸውን ይሰዉ ነበር። ማሪያ ታዲያ የእነሱ አይነት ባህሪ ያላት ልጅ አይደለችም ይልቁንም ትዕግስተኛ እና ሳቂታ ነች ሁሉ ነገሯ ከተፈጥሮ ጋር የተዛመዱ ናቸው። በቃ ተፈጥሮን ታደንቃለች! ተፈጥሮን ትወዳለች።

ከማሪያ ጋር ያሳለፍኳቸውን እነዚያን የጉዞ ቀናት ምን ያህል ጣፋጭ እንደነበሩ ለመግለፅ ቃላት ያጥረኛል። ከእስር ከወጣሁበት እለት አንስቶ እስከ አሁኗ ሰዓት ድረስ ያለ ሀሳብና ጭንቀት ያሳለፍኩት ቀን ቢኖር ከማሪያ ጋር በጉዞ ያሰለፍኩት ጊዜ ነው ብል ውሸት አይሆንብኝም!! ሲለን ከብርጭቆ ውሃ በላይ በጠራው የምንጭ ውሃ ውስጥ ሰውነታችንን እያለቀለቅን ሲለን ደግሞ አረንጓዴ ሳሩ ላይ እርቃናችንን ተኝተን በሚያማምሩ ቢራቢሮዎች እና ወፎች ተከበን ፍቅር የሰራንባቸው ጊዜያቶች በፍፁም አይረሱኝም! ቀናቶቹ ምነው በረዘሙ ብዬ የተመኘሁበት ቀን ቢኖር አሁን ከማሪያ ጋር የሄድኩት ጉዞ ብቻ ነው።

ከስድስት ቀናት በኋላም ወንዙን ጋር ለመድረስ ቻልን፡፡ ወንዙን ሳየው ነው እኔም የመጣሁበት አላማ ትዝ ያለኝ፡፡ ይህም ሌሊቱን ወንዙ ዳር ካደርን በኋላ በጠዋት ማሪያ ፈረሶቹን ይዛ ወደ ኢልሴሎ እንድትሄድ አደርጋለሁ ማለት ነው፡፡ በእነዚህ ስድስት የጉዞ ቀናት ውስጥ ከማሪያ ጋር ያሰለፍኩት ጊዜ አሁን ላመጣው ካሰብኩት አስር ሺህ ብር ጋር ሳነፃፅረው የአስር ሺህ እጥፍ ያህል ደስታ ስለሰጠኝ ለአፍታ ያህል ሁሉን ትተህ 'ማሪያን ይዘህ ወደ ኢልሴሎ ተመለስ...ተመለስ' የሚል ሃሳብ ውስጤን በእጅጉ እያጨናነቀው ነበር፡፡ ቢሆንም ግን ሌላኛው ስሜቴ "አትሞኝ እንጂ ፓፒ! ይሄ አስር ሺህ ዶላር እኮ ደም የተከፈለበት ገንዘብ ነው. . .ላሰብከውም እቅድ ወሳኝ ነገር መሆኑን አትርሳ እንጂ" ይለኛል ይህን በማሰብ ላይ እንዳለሁ እያለ ነበር ማሪያ "ይኸው ወንዙ ጋር ደረስን" ያለችኝ

እኔም ከገባሁበት ሀሳብ ወጥቼ "አዎ ደረስን... የእኔና አንቺ ጉዞም እዚህ ላይ ያበቃል፡፡ ለዛሬ እዚህ ጋር እናድርና ነገ ፈረሶቹን ይዘሽ ወደኢልሴሎ ከሚሄዱ ሰዎች ጋር ትሄጃለሽ ማለት ነው" አልኳት ምንም እንኳን መናገር የፈለኩት ነገ እሷን ይዤ ወደ ኢልሴሎ መመለስ እንደምፈልግና ከእሷ ጋር ለዘላለም መኖር እንደሆነ ቢሆንም የተናገርኩት ግን የሱን ተቃራኒ ነበር፡፡

እንደ እድል ሆኖም ጠዋት ወደ ኢልሴሎ በመሄድ ላይ ያሉ አራት ቤተሰቦች ስላገኘን ማሪያን ለእነሱ አደራ ሰጥቼ እኔም በአንዱ ጀልባ ላይ ተሳፍሬ ወንዙን ለማቋረጥ የብቸኝነት ጉዞዬን ጀመርኩ፡፡ ጀልባው ላይ ሆኜ ማሪያ በሀዘን ስሜት ውስጥ ሆና በሩቁ ቆማ ስትመለከተኝ እያየኋት ነበር፡፡ እኔም አንድ ጊዜ ዞሬ ካየኋት በኋላ ራሴን በድጋሚ ዞሮ እንዳያያት አስገደድኩት፡፡ ይህን ያደረኩት ምናልባት ባለ ጀልባውን በቃ ወደ ማሪያ መልሰኝ እንዳልለው ከሚል ፍራቻ የመጣ ነው፡፡ ቶሎ ብዬ ያንን ሊባኖሳዊ እንደምንም ካገኘሁ በኋላ ገንዘቤን ተቀብዬ ወደ ፓሪስ ሄጄ ያሰብኩትን ብቀላ ፈፅሜ ቶሎ ወደ ማሪያ መመለስ አለብኝ ከተሳካልኝ!

ሊባኖሳዊውን ገንዘቤን እስከሰጠኝ ድረስ ላለመግደል ለራሴ ቃል ገብቻለሁ፡፡ ከዛ ውጪ ግን እንዲረዳልኝ የምፈልገው ነገር ቢኖር በእሱ የተነሳ ከማሪያ ጋር ያሳለፍኳቸው እነዚያ ስድስት ቀናቶች በእሱ ላይ የነበረኝን ቂም እንዳጠፉልኝ ነው፡፡

የአልማዝ ማውጫዎቹ ጋር እንደደረስኩ በቀጥታ የሄድኩት ወደ ሚግዌል መጠጥ ቤት ነበር፡፡ ገና እንዳየኝ ነበር የተጠመጠመብኝ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ በቀጥታ ሊባኖሳዊውን የት ላገኘው እንደምችል ጠየኩት

"ሊባኖሳዊው... እርግጠኛ ነኝ ከሄደ ቆይቷል" አለኝ

ጊዜ ሳናቃጥል ወደ ሊባኖሳዊው የጌጣጌጥ መሸጫ ሱቅ ሄድን፡፡ ሱቁ በዚጋም ከላይ የሰቀለው ጣፋጭ ጥቅስ ግን እንዲለ ነበር 'ታማኝነታችን ታላቅ ሀብታችን ነው!'

"ይሄ ዲቃላ... ከዚህ ሀገር የወጣ ይመስልሃል ግን ሚግዌል?"

"ተረጋጋ ፓፒ... ሁሉንም ነገር የምናየው ይሆናል"

ዝም ብዬ እንደለፋሁ ገብቶኛል አስቀድሞ ስሜቴ ገንዘቡን እንደማላገኘው ነግሮኝ ነበር፤ ውስጤን ማመን ነበረብኝ፡፡ ከጥቂት ማጣራት በኋላ ሙስጠፋ ሊባኖሳዊው ሀገሩን ለቆ እነደወጣ ነገረኝ፡፡ ግን የት ሊሄድ ይችላል? ከሁለት ቀናት በኋላ ነበር የሆኑ አራት ሰራተኞች ሊባኖሳዊው ሶስት አጃቢዎቹን አስከትሎ ወደ ብራዚል መሔዱን የነገሩኝ፡፡ የገረመኝ ነገር ቢኖር ሁሉም እዛ አካባቢ የሚኖሩ ሊባኖሳዊውን የሚያውቁት ሰዎች ሊባኖሳዊው ሀቀኛ መሆኑን በሙሉ ልብ ነበር የሚናገሩት፡፡ ታዲያ እኔ ላይ እንደዚህ አይነት ሸፍጥ ለምን አሰበ? የማልመልሰው ጥያቄ ሆነብኝ... ፍንጭ ካገኘሁ ብዬ እነዚያን ሰራተኞች ስለደረሰኞቹ እና ኢል ሴሎ ስላለው የሊባኖሳዊው ተወካይ ጋር ሄጄ ስላጋጠመኝ ነገር ነገርኳቸው፡፡ ሰራተኞቹም ያልኩት ነገር ትክክል ከሆነ እነሱም እንደኔው ኪሳራ ውስጥ እንደሚገቡ ነገሩኝ፡፡ የትኛው አጭበርባሪ እንደሆነ የትኛው ደግሞ ሀቀኛ እንደሆነ እየተከራከሩ ባለበት ሰዓት እኔ ግን ውስጤን ገንዘቡን እንዳጣሁት እና በፍፁም ላገኘውም እንደማልችል ራሴን እያሳመንኩት ነበር፤ ሁሉም ነገር የሆነው ለበጎ እንደሚሆን አልጠራጠርም፡፡ እንደዛም ሆኖ ግን ከዚህ በኋላ ወዴት መሄድ እንዳለብኝ ግን እስካሁን አልወሰንኩም ነበር፡፡ ወደ አሌክሳንደር ጋር ተመልሼ ልሂድ ይሆን? ያ ደግሞ በጣም አሰልቺና አደገኛ ጉዞ ይሆንብኛል፡፡ ባደረኩት ሙከራም ከእነዚያ የማይረቡ ሁለት ሰዎች ጋር ጫቃ ውስጥ ጠፍቼ ነበር፤ ስለዚህ ይሄን ሃሳቤን ትቼ ወደ ኢል ሴሎ መመለሱ አማራጭ እንደሌለው ተረድቻለሁ፡፡

ወደ ኢልሴሎ ከመሄዴ በፊትም እዚህ ካሉት ሰራተኞች ጋር ሊባኖሳዊው ተመልሶ በመጣ ሰዓት ለእኔ መልዕክት እንዲልኩልኝ ተነጋገርን፡፡ ኢልሴሎ በምቆይባቸው ትንሽ ጊዜአት ምናልባት ተመልሶ ከመጣ እኔም የሚገባውን ሽልማት ከመሸለም ወደኋላ አልልም! እስከዛ ድረስ ካልመጣ ግን እድሉ የሰጠችው ሀብት ነውና ነገሩን መተውን እንዳለብኝ ራሴን ሙሉ ለሙሉ አሳምኛለሁ፡፡

ከሳምት በኋላ ወደ ኢልሴሎ ተመልሼ ከእነ ጆዜ ጋር በጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠን እያወራን ነበር፤ ምን እዳጋጠመኝ ሁሉንም ዘክዝኬ ነገርኳቸው፡፡ ማሪያ የታመመን የሚፈውስ በሚመስለው ጣፋጭ አንደበቷ ልታፅናናኝ ሞከረች፡፡

ጆዜም ሁሉንም ነገር ትቶ ከእነሱ ጋር እንድኖር ሀሳብ አቀረበልኝ፡፡ ቢሆን ያለ ባለኝ ነበር ነገር ግን የማይሆን ነገር ነው እሳካሁንም ማነቆ ሆኖ እንዳልሄድ ያደረገኝ ነገር በኖር የማሪያ ገደብ የለሽ ፍቅር መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ነገርግን ምንም ያህል የማሪያ ፍቅር ጠንካራ ቢሆንም ውስጤ የተቀረፀውን የብቀላ ግንብ ማፈራረስ ግን አልቻለም፡፡

በቀጣዩ ቀን ወደ እነ ቻርሎቱ ቤት ሄጄ ቀኑን በሙሉ ከእነሱ ጋር ስጫወት ከዋልኩ በኋላ ወደ ካራካስ ከትንሽ ቀናት በኃላ ፒኮሲኖን ይገፍ ለመሄድ እንዳሰብኩ ነገርኩት፡፡ እሱም እንደእኔ አይነት ጓደኛ ስለኖረው እንደሚኮራ እና በሄድኩበት ሁሉ ጥሩ ነገር እንዲገጥመኝ እየተመኘልኝ ምናልባት ከጠቀመኝ በሚል አንድ ካራካስ ውስጥ የሚኖር ከዚህ በፊት በውንብድና አለም ውስጥ የነበረ ጓደኛውን አድራሻ ሰጠኝ፡፡

ለጥቂት ቀናት ኢልሴሎ ውስጥ ከቆየሁ እና ከእነዚያም የአልማዝ ጉድጓድ ውስጥ ከሚሰሩት ሰራተኞች ስለሲባኖሳዊው ምንም መልዕክት እንዳልተላከ ካረጋገጥኩ በኃላ ወደ ካራካስ የመሄጃው ጊዜ የደረሰ ስለመሰለኝ ሊወስደን የሚችል መኪና ማፈላለግ ጀመርኩ፡፡ አንድ የጭነት መኪና ወደ ካራካስ እንደሚሄድም ስለሰማሁ ሹፌሩን አግኝቼው ወደ ካራካስ መሄድ እንደምንፈልግ ነገርኩት፡፡ እሱም ይዞን ለመሄድ ፈቃደኝ ከሆነ በኃላ በነጋታው ሁለት ሰዓት አካባቢ ለመገናኘት ቀጠሮ ይዘን ተለያየን፡፡

የዛን ቀን ያደርኩት ብቻዬን ሲሆን ይህንም ያደረኩት ሆን ብዬ ነበር፤ ከእዚሁ ማሪያን ለማዘጋጀት አስቤ ነው፡፡ አዳሬም በጣም ያስጠላ ነበር፤ ከማሪያ የመለየት ሀሳቡ ውስጤ ስላለ ትንሽ እንቅልፍ ይወስደኝና እባንናለሁ፡፡ እንዲህ የሰመመን እንቅልፍ የሞላበት ሌሊት ካሳለፍኩ በኂላ ነበር የነጋልኝ፡፡ ከአልጋዬ እንደወረድኩ መያዝ ያለብኝ እቃዎች ወደ ቦርሳዬ ከከተትኩ በኂላ ምስቅልቅል ያለውን ፒሜን ሙልጭ አድርጌ ተላጨሁት፡፡ በተመሳሳይ ጊዜም ኢስመራልድ ፒኮሲኖን አጣጥባና ቁርሱን አብልታ ለጉዞ ዝግጁ አድርጋው ነበር፤ በመጨረሻም ከቤት ከመውጣቴ በፊት ማሪያን ለመሰናበት ወደ ክፍሏ ልገባ ስል ኢስመራልድ በእጇ ይዛ አስቁማኝ "አይሆንም ኢኒሪክ" አለችኝ እኔም ነገሩ ስለገባኝ ሳልሰናበታት መሔዱን መረጥኩ፡፡ ጆዜ እኔንና ፒኮሲኖን ከሹፌሩ ጋር እስከ ተቀጣጠርንበት ቦታ ድረስ ሸኘን፡፡ እዛ እስክንደርስ ድረስ ልክ ፀበኛ እንደሆንን ሰዎች አንዳችም ቃል ከጆዜ ጋር አልተለዋወጥንም ነበር፤ ይገባኛል እኮ! ሰው ለምዶ ከመለየት መጀመሪያውኑ አለመተዋወቅ ይሻላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ካራካስ

ወደ ካራካስ ያደረግነው ጉዞ እጅጉን ፈታኝ ነበር፤ በተለይ ለፒኮሊና ወደ አንድ ሺህ ኪሎ ሜትር የሚጠጋ መንገድ ለሀያ ሰአታት ለእረፍት የቆምንባቸውን ሳንቆጥር መጓዝ በጣም አሰልቺ ነው። የተወሰነ ጊዜ በሲዳድ ቦሊቫር አርፈን የኦሪኖኮን ወንዝ መኪናም ሰውም በሚያሻግር ጀልባ ላይ ሆነን ከእነመኪናችን ከተሻገርን በኋላ እንደገና ጉዞ ጀመርን። ሹፌራችን እነዳዱ ውድድር ያለበት ነበር የሚመስለው፤ በእርግጠኝነት መኪናው ክንፍ የለውም እንጂ ቢኖረው ኖሮ ፍጥነቱ ብቻ እንዲበር ባደረገው ነበር፤ ቢሆንም ግን በንቃት ስለሚነዳ ምንም አስተያየት ከመስጠት ተቆጠብኩ።

በቀጣዩ ቀን አመሻሹ ላይ ካራካስ ከተማ መድረስ ቻለን። ካራካስ ትልቅ ከተማ ነች!! የእነዚያን በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች እንቅንስቃሴ በማየቱ ውስጤን የሆነ ደስ የሚል ሰሜት ውስጥ ከተተው።

በህይወቱ ትልቅ ከተማ ስመለከት እንግዲህ ይሄ ለሁለተኛ ጊዜ ነው። የመጀመሪያው በ1931 ዓ.ም የፓሪስ ከተማን ሲሆን አሁን በ1946 ዓ.ም ደግሞ ካራካስን ለማየት ችያለሁ። ካራካስ በአሺላ ተራሮች የተከበበች ስትሆን ከመሬት ጠለል በላይ በአንድ ሺህ ጫማ ከፍታ ላይ የምትገኝ እንዲሁም ባለአንድ ነጠላ ፎቅ የሚበዙባት የምታምር ከተማ ነች፤ እንዲሁም የአየር ሁኔታዋም ለሰው ልጅ ምቹ የሚባል አይነት ነው።

ካራካስ ሁሉም አይነት የቆዳ ቀለም ያለው የሰው ዘር የሚኖርባት ከተማ ነች ጥቁሩ፣ ጠይሙና ነጩ ሁሉም ያለዘር ጭቅጭቅ በእኩልነት ይኖርባታል። የፒኮሊኖን እጅ እንደያዝኩ ወደ ከተማው የሚያስወርደውን መንገድ ይዘን ከእዚህ በፊት ቻርሎቴ በሰጠኝ አድራሻ መሰረት እዚች ውብ ሀገር ላይ ማሳደሪያ ሆቴል ወዳለው በፊት ወደሚያውቀው ወንበዴ ጓደኛው አመራሁ

ሀገሬን ለቅቄ ከወጣሁ አሁን ወደ አስራ አምስት ዓመት ገደማ ሆኖኛል። ከ1939 ዓ.ም እስከ 1945 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የናዚ ጦር በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን አርዷል። ከእነዚህ ሀገራት መሀከል ደግሞ የእኔው ሀገር ፈረንሳይ ትገኝበታለች፤ ያ ጊዜ ከሚታሰበው በላይ በሰው ልጅ ላይ አስቀያሚ እልቂት አስከትሎ ያለፈ አይረሴ ጊዜ ነው። አሁን እግዲህ ሠላሳ ዘጠነኛ እሙቴን ብይዝም ገና ልጅ እና ጠንካራ ነኝ፤ ከእዚህ በኋላ ብዙ ነገሮችን የመስራት አቅሙም፣ ወኔውም አለኝ።

ካራካስን በደንብ እያየኋት ስመጣ ውበት እና ድምቀቷ ከጠበኩት በላይ ሆነብኝ፤ በቀን እንዲህ ያሸበረቀች ሲመሽማ በመብራቶቹ ድምቀት ምን ያህል እደምታምር እያሰብኩ መጓዜን ቀጠልኩ። የቻርሎቴ ጓደኛ የሚገኘው አሁን ካለንበት ቦታ የተወሰነ መንገድ እንደሚያስኬድ ሰዎችን በመጠየቅ ስለተረዳሁ ታክሲ ለመጠቀም ግድ ሆነብኝ።

ፒኮሊኖን አጠገቤ እዳስቀመጥኩ ወደ ተባለው ቦታ ጉዞአችንን ቀጠልን፤ ፒኮሊኖ ልክ እንደ ህፃን ልጅ እየሳቀ ነበር፤ ምን ያክል እደተደሰተ ፊቱን አይቶ መናገር ይቻላል። እኔም ደስታው ደስታዬ መሆኑን በሚገልፅ እይታ እየተመለከትኩት ከዚህ ምስኪን ጓደኛዬ አፍ የሚዝረበረበውን ለሀጭ በመሀረቤ ጠረኩለት፤ እሱም ለምስጋና የሚሆኑ ቃላቶችን ከአንደበቱ ማውጣት ባይችልም አስተያየቱ ግን ለማመስገኑ በቂ ምስክር ነበር።

ለፒኮሊኖ ወደ እዚህ ትልቅ ከተማ መምጣታችን በጣም ጥልቅ የሆነ ደስታ ውስጥ እንደከተተው አውቃለሁ፤ ምክንያቱም አሁን ካለበት ሁኔታ አገግሞ ለመዳን ትልቅ ሆስፒታል እና ብዙ ዶክተሮች አስፈላጊ ስለነበሩ ነው። ከታክሲው ከወረድን በኋላ የፒኮሊኖን እጅ ይዤ ጉዞ ጀመርን። መንገዱ በሰዎች እንደተሞላ ነው፤ በዛ ላይ የመኪኖቹ ጡሩንባ ጩኸት፣ የአንቡላንሶቹ እና የእሳት አደጋ መኪኖቹ ኡኡታ፣ መንገድ ላይ የሚጫወቱት የሕፃናቱ ጩኸት፣ በመንገዱ ላይ ውር ውር የሚሉት የሳይክሎች ደውል እነዚህ ሁሉ ተደምረው ከዚህ በፊት ያሳለፍኳቸውን የዝምታ ጊዜያቶች የፈጠሩብኝን ደስ የማይል ስሜት አስወገዱ። በእርግጥ እዚህ ለሚኖሩት ነዋሪዎች እነዚህ ድምጾች ይረብሹ ይሆናል። ለእንደኛ አይነቱ ከብዙ ነገሮች ተገሎ ለኖረ ሰው ግን የሚሰጡት ደስታ ወደር የለውም!! "እንዴት ሰው በጩኸት ይደሰታል?" ትሉን ይሆናል። አትፍረዱብን እኛ የለመድነው የወህኒ ቤቶችን ዝምታ፣ የባህሩን ዝምታ፣ የጫካውን ዝምታን ስለሆነ አሁን በምናየው ነገር ሁሉ መደነቃችን ሊገርማችሁ አይገባም።

በመንገዳችን ላይ እያለንም ወደ ፒኮሊኖ ዞሬ "እንግዲህ አሁን ልክ እንደ ፓሪስ ሁሉ ትልቅ የሆነችው ካራካስ ከተማ ውስጥ ነው ያለነው። እዚህ

በእርግጠኝነት ታክመህ ትድናለህ፡፡ እኔም የሚሰራ ነገር እፈልጋለሁ፡፡ እኔ እስካለሁ ድረስ ምንም የሚያስጨንቅህ ነገር አይኖርም እሺ" አልኩት… እሱም በምላሹ በእጁ ጥብቅ አድርጎ እንደያዘኝ ከአይኖቹ እንባ መፍሰስ ጀመሩ፡፡ እኔም አንደኛው እጁ እኔን እስከያዘኝ ድረስ እና ሌላኛው እጁን ማንቀሳቀስ እስከማይችል ድረስ የጓደኛዬን እንባ የመጥረግ ሃላፊነቱ የእኔ ነበር፡፡

በመጨረሻም ቻርሎቴ በሰጠኝ አድራሻ መሰረት የጓደኛውን ሆቴል አገኘነው፤ ሆቴሉ "ኢምሊ" በሚባል ከዚህ በፊት ወንበዴ በነበረ ሰው የሚመራ ሲሆን ትንሽዬ ነገር ግን ንፁህ ክፍሎች ያሉት ማሳደሪያ ነው፡፡ እኛ ስንደርስ ኢምሊ በቦታው ስላልነበረ ባለቤቱ ነበረች የተቀበለችን፡፡ ከኢል ሴሎ እንደመጣን ከነገርናት በኋላ ወድያውኑ ሁለት አልጋዎች ወዳሉበት ክፍል ውስጥ አስገብታን ለሁታችንም ቡና ይዛልን መጣች፡፡

ቡናችንን አጣጥመን ከጠጣን በኋላ ፒኮሊኖን ገላውን እንዲታጠብ ረዳሁት፤ ከዛ አልጋ ላይ እንዲወጣ ደግፌው አረፍ እንዲል አደረኩት፡፡ በጉዞው በጣም ተዳክሞ ስለነበር አይኖቹን ለመክደን ጊዜ አልፈጀበትም ነበር፤ እኔም እንቅልፍ የወሰደው ስለመሰለኝ ከተማዋን በደንብ ለማየት ከክፍሉ ለመውጣት ተነስቼ ወደበሩ ሳቀና ድንገት ፒኮሊኖ ከእንቅልፉ እንደመባነን ብሎ ትኩር ብሎ አይን አይኔን መመልከት ጀመረ፡፡ እኔም ምን ለማለት እንደፈለገ ከአይኖቹ ስለተረዳሁት "እንደዛ አታስብ ፒኮ! ሳልነግርህ በፍፁም ጥዬህ አልሄድም፡፡ አሁን ከተማዋን ማየት ስለፈለኩ ነው… ቶሎ እመለሳለሁ አንተ እስከዛ አረፍ በል" ብዬ አረጋግቼው ከክፍሉ ወጣሁ፡፡

መሀል ከተማ ላይ ስደርስ ከምሽቱ አንድ ሰዓት ሆኖ ነበር፡፡ በአድናቆት ቆሜ መሀል አደባባይ ላይ የተሰራውን በፈረስ ላይ ተቀምጦ የሚያሳየውን የ 'ሲሞን ቦሊቫርን' ሃውልት እያየሁ ነበር፡፡ ከሀውልቱ ግዝፈት እና ውበት በመነሳት እንደተረዳሁት ከሆነ ሲሞን ቦሊቫር ምን ያህል የተከበረ ሰው እንደነበረ ነው፡፡ በአደባባዩ ዙሪያ ሀውልቱን አተኩሬ ስመለከተው የሚደንቅ ነው! 'እንደኔ አይነቱ እድሜውን ነፃነት ለማግኘት የፈጀ ሰው በአንተ ለነፃነት ሲዋጋ በኖረ ሰው ሀገር ላይ በመገኘቱ ደስታው የእኔ ነው!!' አልኩ ለራሴ በተለያየ ቀለም የሚበሩት የከተማዋ መብራቶች ለቦታው ድምቀትን አላብሰውታል፡፡ ሀውልቱን እንደልቤ አይቼ ከጨረስኩ በኋላ ከተማዋ ውስጥ በተለያየ የመብራት ቀለም ያሸበረቁትን የማስታወቂያ ሴሌዳዎችን መቃኘት ጀመርኩ፡፡ ብዙ ነገር ማየት ብፈልግም ለፒኮሊኖ ቶሎ እንደምመለስ ቃል ስለገባሁለት ወደ ሆቴሉ መሄድን መረጥኩ፡፡ ወደ ሆቴሉ ስደርስም ኢምሊ ከሄደበት ተመልሶ አገኘሁት፡፡ እንዳገኘኝም ቻርሎቴ ምን አልባት ወደ እርሱ ጋር ሊመጡ የሚችሉ ጓደኞች እንዳሉት አስቀድሞ በደብዳቤ መልዕክት እንደላከለት ከነገረኝ በኋላ ሁለታችን

ብቻ እንድናወራ በማሰብ ከሆቴሉ ጀርባ ወደሚገኘው መናፈሻ ይዞኝ ሄዶ አንዱ ወንበር ላይ ቁጭ እንድል እየጋበዘኝ ወሬ ማውራቱን ቀጠለ፡፡

"ወደ አስር ዓመት ገደማ ሆነኝ እዚህ መኖር ከጀመርኩ" ብሎ ወሬ ጀመረ "በሂደትም አንዲት ልጅ ያላትን ሴት አግብቼ ይኸው ያላሰብኩትን ኑሮ እየኖርኩ ነው" ካለኝ በኋላ ትንሽ ፋታ ወስዶ

"ሆቴሉ በእሷ ስም ስለሆነ ምንም ማድረግ ባልችልም ከመደበኛው የማደሪያ ክፍያ በግማሽ ግን እንዲቀንስላቹ አደርጋለሁ፡፡ ያ አብሮህ የመጣው ምስኪን ሰው ጓደኛህ ነው?" ብሎ ጠየቀኝ

"አዎ... አይተኸዋል እንዴ?" አልኩት ወደ ሆቴሉ በገባንበት ሰዓት በቦታው እንደሌላ እርግጠኛ ስለነበርኩ

"አላየሁትም... ባለቤቴ ነግራኝ ነው... እሷ እንደነገረችኝ ከሆነ ውድቅ ያለ ሰው ነው ብላኛለች፡፡ ምንድነው እርጅና ነው?"

"በጭራሽ! ባለቤትህ ተሳስታለች... የሚገርምህ ነገር አዕምሮው ሙሉ ለሙሉ ጤነኛ ነው፡፡ ግማሽ ጎኑ ፓራላይዝ በመሆኑ ምክንያት ብቻ የቀኝ እጁን፣ ምላሱንና አስከመቀመጫው ያለውን የቀኝ ጎኑን መቆጣጠር ስለማይችል ብቻ ነው የወደቀ የመሰላት" አልኩት

"መቼ ነው የጀመረው?"

"ኢል ዶራዶም እስር ቤት እያለንም እዲሁ ነበር፡፡ ስለእሱ የሚያውቅ ማንም የለም በምን ምክንያት እዲህ እንደሆነ ፍንጭ የሚሰጥም የለም፡፡ ዘራፊ ይሁን ገዳይ የሚታወቅ ነገር የለም"

"እንዴ!! ታድያ ለምንድነው የማታውቀውን ሰው ይዘህ የምትጓዘው? ማን እንደሆነ እንኳን አታውቅም፤ ከሁሉ በላይ ደግሞ ላንተ ሸክም ነው"

"በእርግጥ ከባድ ነው፡፡ ለስምንት ወራቶች ኢል ሴሎ ውስጥ ከተዋወቅናቸው ቤተሰቦች ጋር ቆይተናል፡፡ እንደዛም ቢሆን ግን ቀላል አልነበረም"

"እና ምን ልታደርገው አሰብክ?"

"ከተቻለኝ ያረጃውን ወደጠበቀ ሆስፒታል ወስጄ ማሳከም እፈልጋለሁ፡፡ ነገሮች እስኪስተካከሉ ድረስ ግን ሻወርና ሽንት ቤት ያላት ትንሽ ቤት መከራየት ይኖርብኛል"

"ገንዘብ ይዘሃል?"

"የተወሰነ ይዣለሁ...ገንዘብ አያያዜን ግን ማሳመር አለብኝ ምክንያቱም ስፓኒሽኛ መስማት ብችልም እንኳን ለመናገር በጣም ስለሚያዳግተኝ በቀላሉ ስራ አገኛለሁ ብዬ አላስብም"

"እውነት ነው!እዚህ ሁሉ ነገር ከባድ ነው! ብዙ ሰዎች ስራ ለማግኘት ቢጥሩም የሚያገኘው ግን ጥቂቱ ነው። የህዝቡ ብዛትና ስራው ባለመጣጣኑ ምክንያት ብዙኂኑ ስራ አጥ ነው። ቢሆንም ግን ፓፒ ብዙ አትጨነቅ . . . የራስህን መንገድ እስክታመቻች ድረስ ለተወሰኑ ቀናቶች እኛ ጋር መቆየት ትችላለህ" አለኝ

መልዕክቱ ገብቶኛል! ኢምሊ ደግ ሰው ቢሆንም ባለቤቱ ስለፒኮሊኖ ሁኔታ አጋና ስለነገረችው በሆቴላቸው መቆየታችንን እንዳልወደደው ከፊቱ እና ካነጋገሩ ያስታውቅ ነበር።

ከኢምሊ ጋር እደተለያየን ወደያዝነው ክፍል ሄድኩ፤ ወደ ውስጥ ስገባም ፒኮሊኖ ከእኔ ቀጥሎ የሚገኘው ትንሽዬ የብረት አልጋ ላይ ድብን ያለ እንቅልፍ ወስዶት ተመለከትኩ። "ምስኪን ፒኮሊኖ ለማደሪያህና ለምግብህ ብከፍላቸውም እንኳን እዚህ እንድትቆይ አልፈለጉም። አይ የሰው ልጅ በቃ የታመመ ሰው አይወድም አይደል! ግን አታስብ ኋደኛዬ እኔ እስካለሁ ድረስ ምንም እንኳን እንደነዚያ ኢል ሴሎ እንዳሉት ልጃገረዶች ባልንከባከብህም የቻልኩትን ያክል ልንከባከብህ ለራሴ ቃል ገብቻለሁ!" አልኩ በውስጤ

ኢምሊ ስራ ሊገኝባቸው ይችላሉ ብሎ ያሰበባቸውን የተለያዩ ድርጅቶችን አድራሻ ቢሰጠኝም አንዱም ጋር ለኔ የሚሆን ስራ ላገኝ ግን አልቻልኩም። ፒኮሊኖንም ከሁለት ጊዜ በላይ ሆስፒታል ለማስገባት ብሞክርም ሊሳካልኝ አልቻለም። ዋና ምክንያታቸው በሆስፒታሉ ውስጥ ትርፍ አልጋ አለመኖር ቢሆንም በእኔ እይታ ግን ለማከም ፈቃደኛ ያልሆኑት የፒኮሊኖ ሰነድ ከኢል ዶራዶ እስር ቤት መውጣቱን ስለሚያስረዳ ይመስለኛል። ይባስ ብለው እንዴት እና መቼ በእኔ እርዳታ ስር ሊወድቅ እንደቻለ፤ ዜግነቱ ምን እንደሆነ እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ጀመሩ እኔም "ከኢል ዶራዶ እስር ቤት ስወጣ የፖሊሶቹ አዛዥ አብሬ ይዤው እንድሄድና እስካለሁም ድረስ እንድንከባከበው ቃል ስላስገባኝ ነው" ብዬ ስመልስላቸው እነዚህ ዲቃሎች የሰጡኝ መልስ "ጥሩ!! እንግዲህ ከእስር የተፈታው አንተ እንደምትንከባከበው ቃል ስለገባህ ይሆናል። ካንተ የሚጠበቀው ነገር ቢኖር እዛው የምትኖርበት ቦታ ወስደህ የሚገባውን እንክብካቤ መስጠት ነው። ያንን ማድረግ የማትችል ከሆነ መጀመሪያውኑ እችላለው ብለህ ከኢል ዶራዶ ማውጣት አልነበረብህም

ማለት ነው" የሚል ነበር። ቀጥለውም አድራሻዬን ሲጠይቁኝ ምንም ሁኔታቸው ስላላማረኝ የተሳሳተ አድራሻ ሰጥቻቸው ፒኮሊኖን ይዤ በፍጥነት ከዚያ ሆስፒታል ወጥቼ ወደ ሆቴላችን አቀናሁ።

ለሁለታችንም ደህንነት ሲባል ከዚህ በኋላ የኢምሊ ሆቴል ማደራችንን ስላልወደድኩት ክፍያው ብዙም ውድ ያልሆነ ሌላ አነስተኛ ክፍል ተከራየሁ። አንድ ነገር ግልፅ ነው የፒኮሊኖን ጉዳይ መጨረስ አለብኝ። ግን እንዴት? ምን እንደማደርግ ግራ ገባኝ። በሚቀጥለው ቀን ለሶስተኛ ጊዜ ሆስፒታል ላስገባሁ ሞከርኩ አሁንም አልተሳካልኝም። በዚህ ሰዓት ነበር ትልቅ ውሳኔ መወሰን እንዳለብኝ እራሴን ያሳመንኩ፤ ጊዜው ከጠዋቱ አምስት ሰዓት አካባቢ ስለነበር ፒኮሎኖን ይዤ መሀል ካራካስ ወደ ሚገኘው ካልቫሪዮ ተብሎ ወደሚጠራ በአበቦች እና በዛፎች የተሞላ መናፈሻ ይዤው ሄድኩ።

እዛም ቁጭ ብለን ይሄን ንፁህ አየር እየኮመኮምን አረፍ ተደርጎ የተጠበሰ ስጋ ከቀይ ወይን ጋር ተመገብን፤ ምግባችንን በልተን እንደጨረስንም ሁለት ሲጋራዎች ለኩሼ አንዱን አፌ ላይ ከጣድኩ በኋላ አንደኛውን ደግሞ ለፒኮሊኖ አቀበልኩት። ለፒኮ ከአፉ በሚዝረከረከው ለሀጭ ምክንያት ሲጋራ ማጨስ በእጅጉ ከባድ ነበር፤ ሲጋራ በምናጨስበትም ሰዓት የፒኮሊኖ አይኖች የሆነ ትልቅ ጉዳይ ልነግረው እዳሰብኩ አስቀድሞ መረዳቱን ይናገሩ ነበር። "ተናገር!... ተናገር ፓፒ... የሆነ ትልቅ ውሳኔ እንደወሰንክ ስሜቴ ነግሮኛል... ስለማምንህ አትፍራ ንገረኝ!" የሚሉ ይመስሉ ነበር... በመጨረሻም እንደምንም ሀሳቤን አሰባስቤ መስማት የፈለገውን እውነት ለመንገር ወሰንኩ

"ፒኮ ለተከታታይ ሦስት ቀናት አንተን ሆስፒታል ለማስገባት ያደረኩት ጥረት እንዳልተሳካ ታውቃለህ... ለምን እደሆነ ባላውቅም ዶክተሮቹ አንተን ማከም አልፈለጉም... እየተረዳኸኝ ነው አይደል?"

"አዎ" አለ በአይኖቹ

"እንግዲህ በደንብ አድምጠኝ... ሙሉ ጤናህ እንዲመለስ ከተፈለገ ሆስፒታል ገብተህ በደንብ መታከም ይኖርብሃል። ያ ምንም አጠያያቂ አይደለም! ነገር ግን እኔን እንደምታየኝ አንተን ለመንከባከብ የሚሆን በቂ ገንዘብ የለኝም። ስለዚህ አሁን ምን እናደርጋለን መሰለህ ፀሀይዋ አስክትበርድ እዚሁ እናሳልፍ እና ከሰዓት ሲኒማ ገብተን ፊልም እናያለን። በነጋታው ጠዋት የሲሞን ቦሊቫር ሀውልት የሚገኝበት አደባባይ ላይ ይዤህ እሄዳለሁ። ከዛ ሀውልቱ ስር ሄደህ ትተኛለህ... ማንኛውም ሰው እንድትቀመጥ ወይም እንድትቆም ለማድረግ ቢጥር አሻፈረኝ በል። ከትንሽ ደቂቃ በኋላም ፖሊስ መምጣቱ አይቀርም። ያን ጊዜ አምቡላንስ መጥራታቸው ስለማይቀር ወደሆስፒታል ይዘው ለመሄድ

ይገደዳሉ ማለት ነው። ከኢልዶራዶ አስር ቤት ስትወጣ የተሰጠህን የማንነትህን ማረጋገጫ ሰነድ ምን አልባት ሌላ ጥያቄ ሊያስነሳ ስለሚችል እኔ ጋር አስቀምጠዋለሁ አይዞህ! አመቺ ቦታ ፈልጌ ሁሉንም ነገር ስለምከታተል አምቡላንሷ የትኛው ሆስፒታል ይዛህ እንደምትሄድ አያለሁ። ከዛ ይዘውህ ከሄዱ ከሁለት ቀናት በኋላ መጥቼ እጠይቅሃለው። መጀመሪያ የምጠይቅህ ጊዜ ነገሮችን እስካጣራ ድረስ ላላወራህ እችላለሁ። ቢሆንም ግን በአልጋህ አጠገብ ሳልፍ ጥቂት ገንዘብና ሲጋራ ትቼልህ እሄዳለሁ... ያስማማናል አይደል ፒኮ?"

እጆቹን ትከሻዬ ላይ ለመጫን እየሞከረ ሀዘንና ምስጋና በተቀላቀለበት ስሜት ትኩር ብሎ ከተመለከተኝ በኋላ እንደምንም ጉሮሮውን ጠራርጎ በጎረነነ ድምፅ "እ ..ም...እ..ስ..ግ..ና..ለ..ሁ" አለኝ

በሚቀጥለው ቀን ሁሉም ነገር እዳሰብኩት ነበር የተከናወነው፤ ፒኮሊኖ የቦሊቫርስ ሃውልት ስር ከተኛ ከሀያ ደቂቃዎች በኋላ የሆኑ አራት ሽማግሌ ሰዎች ለሆኑ ፖሊሶች የቦሊቫርን አደባባይ እየጠቆሙ የሆነ ነገር ለማስረዳት ሲሞክሩ አየሁ፤ ወዲያው ወደ ቦታው ፖሊሶቹ እና ሽማግሌዎቹ ሄደው ለተጨማሪ ሀያ ደቂቃ ያክል በፒኮሊኖ ዙሪያ ከበው ሲያወሩ ከቆዩ በኋላ አምቡላንስ አስመጥተው ፒኮሊኖን ሲጭኑት ተመለከትኩ፤ ወዲያው ታክሲ አስቁሜ አምቡላንሱን መከታተል ጀመርኩ።

ከሁለት ቀናት በኋላ ጠያቂ መስዬ ወደ ሆስፒታሉ ለመግባት አልተቸገርኩም ነበር፤ እንደ እድል ሆኖ ፒኮሊኖ የተኛው ሁለት በጣም የታመሙ ህሙማን መሃል በአንድ ክፍል ውስጥ ስለሆነ እደፈለኩ ለማውራት አመቺ ጊዜ አግኝቻለሁ፤ ልክ እንዳየኝ ደስታውን ለመቆጣጠር ተስኖት እንደ ህፃን ልጅ ነበር ያቅበጠበጠው።

"በደንብ እየተንከባከቡ ነው?" ጠየኩት

"አዎ" አለ በአይኖቹ

ከፒኮ አልጋ ስር የተለጠፈውን የታማሚዎችን መረጃ የሚሰጥ ሰነድ አነበብኩት "የወባ በሽታ ከተያያዥ ችግሮች ጋር... በየሁለት ሰዓቱ ይታይ" ይላል

ፒኮ ጋር ትንሽ ከተቀመጥኩ በኋላ ለመሄድ ስነሳ ስድስት ፓኬት ሲጋራ እና ሀያ ቦሊቫር ስጥጬው ደህና ሁን ፒኮ" ብዬው ልወጣ ስል እንባ ያቀረሩ አይኖቹን ስላየሁ "አታስብ ጓደኛዬ... እየመጣሁ እኮ እጠይቅሃለው" ብዬ

ካስናናሁት በኋላ ከሆስፒታሉ ወጣሁ። ለነገሩ የእሱ እንደዚህ መሆን አይደንቅም፤ ምክንያቱም በእዚች ምድር ላይ የቀረው ብቸኛ ዘመዱ ቢኖር እኔ ብቻ ስለሆንኩ ነው።

* * * * * * * * *

ካራካስ ከመጣሁ ሁለት ሳመንት ሆነኝ በእነዚህ አስራ አራት ቀናት ውስጥም መቶ ቦሊቫርስ ለማጥፋት ተገድጃለሁ። ደስ የሚለው ወደ ካራካስ ስመጣ የለበስኩት ልብስ ደረጃውን የጠበቀ ስለሆነ ድህነቴ አያስፎግርም፤ ከፒኮ ጋር የተከራየነውን ማደሪያ በመልቀቅ ለሁለተኛ ጊዜ ሌላ አነስ ያለ ክፍል ተከራየሁ። ስራ እስካገኝም ድረስ የቀረኝን ብር ቆጥቤ ካልተጠቀምኩ እዚህ ትልቅ ከተማ ውስጥ መኖር በእጅጉ ከባድ እንደሚሆንብኝ ግልፅ ነው።

ትልቅ ከተማ ሁሌም ቢሆን ሚስጢር አይጠፋውም፤ ታዲያ እነዚያን ሚስጥሮች ማወቅ ቢያንስ የእለት ጉርስን ለመሸፈን ይረዳሉ። ሚስጥሮቹን ለማወቅ ደግሞ አስተማሪ ያስፈልጋል። እኔም እንግዲህ ከእነዚህ ሚስጥሮች መካከል አንዱን ከዚህ በፊት በማውቀው ሰው አማካኝነት ላውቅ ችያለሁ። አንድ ቀን በከተማዋ ውስጥ እየተዘዋወርኩ በመንብኘት ላይ እያለሁ ሳለ ኤል ዶራዶ ውስጥ የማውቀው አንድ ኮሎምቢያዊ አገኘሁ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ እዚህ ምን እየሰራ እንደሆነ ጠየኩት

"ካዲላክ የተባለችውን መኪና በሎተሪ መልክ እየሸጥኩ ነው" አለኝ

"ህይወትህን ቀይረኃላ! በጣም ደስ ይላል መቼስ በስተመጨረሻም ሎተሪውን አንተው ሳታሸንፍ አትቀርም" አልኩት ፈገግ ለማለት እየሞከርኩ

የለበጣ ሳቅ ከሳቀ በኋላ "እዛ ጋር ያለው ትልቁን ባንክ አየኸው? መኪናዋ የባንኩ ዋና ዳይሬክተር ነች። ሁል ጊዜ እየነዳ ይዟት ከመጣ በኋላ ከባንኩ በመቶ ሜትር ርቀት ላይ ያቆማታል። ይህን ስራ ስንሰራ የነበርነው ከአንድ ጓደኛዬ ጋር ነበር። ምን እንደምናደርግ ታውቃለህ? ዳይሬክተሩ መኪናዋን ጥሏት የሄደበት ቦታ ማንም ሳያየን በቀይ ከለር በጉልህ የተፃፈ እቺን ካዲላክ ለማሸነፍ የሚረዱት የሎተሪ ትኬቶች እዚህ በመሸጥ ላይ ናቸው የሚል ፅሁፍ መኪናው ላይ ሁሉም ሰው ሊያየው የሚችል ቦታ ላይ እንለጥፈዋለን። ይሄንን ስናደርግ ምን አልባት ሰው መጥቶብን ችግር እንዳይፈጥር አስጊ ነገር ከአየን

እንዳችን በሩጫ መልክ ማስጠንቀቂያ ስለምንሰጥ የሚያሰጋ ነገር የለም። ታዲያ እኛም መኪናዋ አቅራቢያ በመሆን የተሸጠልንን ያክል እነዚያን ምንም የማያስገኙ የሎተሪ ቲኬቶችን ከሸጥን በኋላ የባንኩ ዳይሬክተር ወደ ቤቱ የሚሄድበትን ሰዓት ስለምናውቅ መኪናዋ ጋር ከመምጣቱ አስቀድመን መኪናዋ ላይ የለጠፍነውን ዕሁፍ አንስተን ወደቤታችን እንሄዳለን ማለት ነው። እንግዲህ ጓደኛዬ ይሄንን ነበር ለተወሰኑ ቀናቶች ከጓደኛዬ ጋር ስሰራ የነበረው። ይህ ስራ ሲጠናቀቅ ደግሞ ወደ ሌላ የማጭበርበር ስራ እንቀይራለን" አለኝ

"የሚገርም ነው!ያንተ ባልሆነ መኪና እነዚህን የውሸት ቲኬቶች እየቸበቸብክ ገንዘብ ታገኛለህ ማለት ነው። የሚደንቅ ነው! እኔ ምልህ ፖሊሶችስ ተጠራጥረው ጠይቀዋችሁ አያውቁም?"

"ያውቃሉ ልክ ሁኔታውን ለማጣራት ወደኛ ሲመጡ ነፃ ትኬት ስለምንሰጣቸው ወዲያው ሀሳባቸውን ለመቀየር ጊዜ አይፈጅባቸውም። ፖሊሶቹ ከቦታው እንደሄዱ ስናረጋግጥ ቲኬቶቹን መቸብቸብ እንጀምራለን ማለት ነው ። እና ጓደኛዬ በስራው ከተመሰጥክ ከእኛ ጋር መቀላቀል ትችላለህ"

"ደስ ይለኛል... እኔ የምልህ ግን የድሃ ገንዘብ መዝረፍ አይሆንብንም?"

"በጭራሽ!... የአንዱ ቲኬት ዋጋ እኮ አስር ቦሊቫር ነው... ብዙም ኪስ የሚጎዳ ብር አይደለም"... ከሚያገኙት ካዲላክ መኪና አንፃር" ብሎ ተንከትክቶ ሳቀ

እኔም ምንም አማራጭ ስሌለኝ በሀሳቡ ተስማምቼ በሚቀጥለው ቀን አብሮት የሚሰራውን ጓደኛውን አስተዋወቀኝ፤ ከዛም ጊዜ ሳላባክን በቀጥታ ወደስራው ገባሁ። ገንዘቡ የሚገኘው ከድሃው ማህበረሰብ ስለሆነ ስራው እርካታ አይሰጥም፤ ነገር ግን በልቶ ማደር ስላለብኝ በስራው ላይ ለመሳተፍ ተገድጃለሁ።ያ ማለት ግን በዚህ ሰዓት ምንም አይነት ገንዘብ የለኝም እያልኩ አይደለም፤ ከኢልዶራዶ እስር ቤት ስወጣ ፊንጢጣዬ ውስጥ በደበቁት የአልሙኒየም ቱቦ ውስጥ የተወሰኑ አልማዞች እና አምስት መቶ ቦሊቫር ይዣለሁ። ቢሆንም ግን በእሱ ተማምኜ መኖር ስለማልችል በግዴታ ውዴታ መስራቱን አማራጭ አድርጌአለሁ። ምን አልባት ከእስር ከወጣህ በኋላ ለምንድነው የገንዘብ መደበቂያ ቱቦህን አሁንም ይዘህ የምትዞረው የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይህን ያደረኩት በሁለት አበይት ምክንያቶች ነው። አንደኛው እዚህ ካራካስ ውስጥ የያዝኩት ክፍል ለከተማው በጣም ቅርብ ስለሆነ ሊዘርፉኝ ይችላሉ የሚል ግምት ስላለኝ ነው፡ ፡ሁለተኛው ምክንያቴ ደግሞ ገንዘቡን በኪሴ ይዤ የምዞር ከሆነ የመጥፋት እድሉ ከፍተኛ ስለሆነ ነው። ለዛም ነው

እቺን ከአልሙኒየም የተሰራችውን የገንዘብ መደበቂያ ቱቦዬን ለአስራ አራት አመታት አብራኝ ልትቆይ የቻለችው፡፡

ሎተሪ ሽያጩ ለአስራ አምስት ቀናት ያህል ቆየ፤ ለነገሩ ከዛም ቀን በላይ ይቆይ ነበር፤ ነገር ግን በመሀል ቲኬቶቹን የገዛ አንድ ደንበኛ መናደዱን በሚያሳይ እርምጃ እየተክለፈለፈ ወደ እኛ መጥቶ አይኖቹን እኛ ላይ አጻፈጠጠ

"እኔ የምለው እቺ መኪና የባንኩ ዋና ዳይሬክተር የዶክተር ፉላኖ አይደለችም እንዴ?"

"አዎ ነች" አለ ኮሎንቢያዊው ጓደኛዬ ትንሽ እንኳን ደንገጥ ሳይል

"ታዲያ እንዴት እናንተ እጅ ልትገባ ቻለች?"

"የባንኩ ዳይሬክተር እቺን መኪና ቀጥታ ሽያጭ ላይ ከማውጣት ይልቅ በሎተሪ መልክ ቢሸጣጥ ጥሩ ትርፍ እንደምታስገኝለት ስለተረዳ ነው"

"ግራ የሚያጋባ ነው!!"

"ከሁሉ በላይ ግን ለዳይሬክተሩ እዳትነገረው" አለ ኮሎምቢያዊው ፍፁም እርጋታ በሰፈነበት አነጋገር ቀጠለናም "ስለዚህ ጉዳይ ለማንም እንዳናወራ ቃል አስገብቶናል፡፡ አንተም ብትሆን ዳይሬክተሩን በደንብ ሳታውቅ አትቀርምና ጉዳዩን በሚስጥር እንዲከወንለት ከፈለገ እንደፍላጎቱ እንፈፅምለት" አለው

"ሊገባኝ አልቻለም ይህ ከእንደሱ አይነት ሰው የማልጠብቀው ድርጊት ነው!!" ብሎ እየተመናጨቀ ከመቅፅበት ከአካባቢው ተሰወረ፡፡

ኮሎምቢያዊውም የሰውየውን ከአካባቢው መራቅ ካረጋገጠ በኋላ ማንም ሳያየው ቶሎ ወደ መኪናዋ ሄዶ የተለጠፈውን ማስታወቂያ አንስቶ ከአካባቢው እሱም ተሰወረ፡፡

ከሦስት ደቂቃ በኋላ ይመስለኛል ያ ተነጫንጮ የሄደው ሰው የተወሰኑ እንደሱ የተጠራጠሩ ሰዎችን ይዞ እኛ ወዳለንበት አካባቢ ሲመጡ እኔ ተደብቄ እያየሁ ነበር፡፡ በቦታው ላይ ማንንም ባለማግኘታቸው እየተገረሙ የባንኩ ባለቤት አለኪውጣ ድረስ ጠብቀው ስለሁኔታው ሲጠይቁጥ አስተዋልኩ፡፡ እኔም በውስጤ በሁኔታው በጣም እየሳኩ የሚሉትን ለመስማት እነሱ ወዳሉበት ቦታ ተጠጋሁ፤ ለነገሩ አጠገባቸው ብሄድ እንኳን የሚያስታውሰኝ ያለ

አይመስለኝም፡፡ ዳይሬክተሩን እንዳገኙትም እየተከናወነ ስላለው ነገር ካስረዱት በኋላ እነሱም እቺን መዘዘኛ ካዲላክ አገኛለሁ በሚል የተጭበረበረ ትኬት መግዛታቸውን ነገሩት፡፡ እሱም በሁኔታው በጣም ተገርሞ ከሳቀ በኋላ "እነዚህ ሰዎች ሲበዛ ብልጦች ናቸው!! እኔም አላጋጠምኳእውም እንጂ ቲኬቶቹን ለእኔም ይሸጡልኝ ነበር" ብሎ በድጋሚ ከልቡ ተንከትክቶ ሳቀ

በአጠቃላይ የእኛም የሎተሪ ጨዋታችን እዚህ ላይ አቆመ ማለት ነው፡፡ ኮሎምቢያዊውንም ከዚያን ቀን ጀምሮ አይቼው አላውቅም፡፡ በእርግጥ በእነዚህ አስራአምስት ቀናቶች ውስጥ ወደ አንድ ሺህ አምስት መቶ ቦሊቫርስ ማጠራቀም ስለቻልኩን ኮሎምቢያዊውን አመሰግነዋለሁ፡፡ ይህም ለአንድ ወር ለቤት ኪራይ እና ለምበላው ሳልጨነቅ ያለሀሳብ እንድኖር ያደርገኛል ማለት ነው፡፡

ቀናቶቹ ማለፋቸውን ቀጥለዋል፤ እኔግን ራሴን ለማስተዳደር የሚሆነኝን ስራ ማግኘት አልቻልኩም፡፡ ኢል ሴሎ እያለሁ ኑሮ ይህን ያህል ከባድ አልነበረም፤ እዚህ ግን ህይወትን ለመግፋት ካሰብኩት በላይ እጅግ ፈታኝ መሆኑን ተረድቻለሁ፡፡ በመጨረሻም የማደርገው ሳጣ ቢሮ ውስጥ ለሚሰሩ ሰራተኞች እዛው የሚሰሩበት ቦታ ድረስ ፔርሙሴን ይዤ በመሄድ ትኩስ ቡና መሸጥ ጀመርኩ፡፡

ታዲያ እንደዚሁ ቡና ለአንዱ ደንበኛዬ ላደርስ ፔርሙሴን በአንድ እጄ በሌላኛው እጄ ደግሞ ለመጠጫ የሚሆኑ ኩባያዎችን ይዤ እየሄድኩ እያለ ከዚህ በፊት ፈረንሳይ ሞንትማንትሪ ውስጥ የማውቀውን አንድ ፓውሎ የሚባል ቦክሰኛ የነበረ ሰው አገኘሁ፡፡ አገኘዋለሁ ብዬ ያልጠበኩት ሰው ስለሆነብኝ ነው መሰለኝ ሳየው በጣም ተደንቄ ነበር፤ ወደ እሱ ጠጋ ብዬም "በእርግጠኝነት ፓውሎ ቦክሰኛው መሆን አለብህ" አልኩት በአድናቆት

"ያለጥርጥር!! አንተ ደግሞ ፓፒለን" ብሎ የሞቀ ሰላምታ ከሰጠኝ በኋላ እጄን ይዞ ወደ አንዱ ካፌ ይዞኝ ገባ፡፡

"ያንን ፔርሙስ ይዘህ ወዴት እየሄድክ ነበር?"

"ቡና እየሸጥኩ ነው፡፡ ለአንዱ ደንበኛዬ ቡና በመውሰድ ላይ እያለሁ እኮ ነው አንተን ያገኘሁህ... ወደዚህ ከመጣሁ በኋላ የሚሰራ ስራ ስላጣሁ ይህንን አስቀያሚ ስራ እየሰራሁ ነው፡፡ አንተስ ምን እየሰራህ ነው?"

"መጀመሪያ ቡናችንን እንጠጣ፡፡ እሱን ሌላ ቦታ እንግርሃለው" አለኝ የተቀዳልኝ ቡና እየቀዘቀዘ መሆኑን አይቶ፡፡ ጠጥተን እንደጨረስን ፓውሎ ሒሳብ ከፍሎ

ለመውጣት ስለተነሳን እኔም ፔርሙሴን ካስቀመጥኩበት ጠረጴዛ ላይ ላነሳው ጎንበስ አልኩ፤ ፓውሎ ተሽቀዳድሞ "ፔርሙሱን እዛው ባለበት ተወው... ካሁን በኋላ አያስፈልግህም" አለኝ

"እርግጠኛ ነህ?"

"አዎ እርግጠኛ ነኝ!!"

በሃሳቡ ተስማምቼ ፔርሙሱን እዛው ያለበት ቦታ ትተነው ወጣን፤ ከዛም ወዴት መሔድ እንዳለብን ከተነጋገርን በኋላ እኔ ወደያዝኩት ክፍል ለመሄድ ተስማምተን ወደዚያው አመራን፡፡ ክፍሌ ውስጥም ተቀምጠን በፊት ሞንትማረትሬ ውስጥ ስላሳለፍናቸው ጊዜአቶች እያነሳን ለጥቂት ደቂቃዎች ከተጨዋወትን በኋላ ፓውሎ ማውራት ወደሚፈለገው ዋና ርዕስ ጉዳይ በቀጥታ ገባ

"ፓፒ ከቬንዙዌላ ብዙም የማይርቅ ቦታ ላይ ለመስራት ያሰብነው ስራ አለ... አንተም ፍቃድህ ከሆነ በስራው ላይ ትሳተፋለህ በአንተ ላይ ያለኝ እምነት ከበፊት ጀምሮ ጥብቅ ስለሆነ ለእዚህ ስራ ትክክለኛው ምርጫዬ አንተ ነህ፡፡ አንተ ለመስራት ከተስማማህ ዛሬውኑ ከአባላቶቹ አንዱ ትሆናለህ... ስራው በተሳካ ሁኔታ ከተጨረሰ ጠቀም ያለ ገንዘብ ወደ ኪስህ ይገባል" አለኝ

"ታዲያ የስራው ቦታ የት ነው?" ብዬ ጠየኩት

"አሁን አልነግርህም... እዛው ቦታ ላይ ስትደርስ ታወቀዋለህ... እስከዛ ድረስ ስለቦታው አትጠይቀኝ"

"ስንት ሆነን ነው ስራውን የምንሰራው?"

"ከአንተ ጋር አራት ነን፡፡ እንደውም አንደኛው እዛው ነው ያለው... እዚህ አመጣጤ የቀረውን አንዱን ጓደኛችንን ይዤ ለመሄድ ነበር፡፡ ጋትሰንን አውቅኸው አይደል? ያንተም ጓደኛ ነበር"

"አዎ አውቀዋለሁ... ካየሁት ግን ቆይቻለሁ፤ እና ስለ ስራው ምንም አልነግርህም ነው ምትለኝ?"

"አዎ ፓፒ... የማልነግርበት የራሴ የሆነ ምክንያት ስላለኝ ነው"

ስለሁኔታው ማሰብ ጀመርኩ፤ ለምን ስለስራው መንገር እንዳልፈለገ ባይገባኝም ሃሳቡን ከመቀበል ውጪ ሌላ አማራጭ ያለኝ አይመስለኝም፡፡ አለበለዚያማ

እዚሁ ቡና ሻጭ ሆኜ ወይም ሌላ መናኛ ስራ እየሰራሁ ጊዜዬን ማቃጠሌ ነው፤ ስለዚህ ምንም ሳላንገራግር መሄዱን መርጫለሁ። በዛ ላይ ፓውሎ እንዳለኝ ከሆነ ስራው ብዙ ገንዘብ እንደሚያስገኝ ነው። ይህ ደግሞ ላሰብኩት እቅድ መሳካት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል።

እዚጋ እንዲታወቅልን የምፈልገው ነገር ቢኖር ዝም ብዬ ፓውሎ የተናገራቸውን ቃላቶች የማምን ደደብ ሆኜ አይደለም ቶሎ ውሳኔ ላይ የደረስኩት ነገር ግን አሁን ካለሁበት አንፃር እሺ ከማለት ውጪ ሌላ አማራጭ ባለመኖሩ ነው። በተለይ ደግሞ ፓውሎ በፊት ፈረንሳይ ውስጥ ሳውቀው እራሱ አፉ ያመጣለትን ሁሉ የሚቀባጥር ሰው ሳይሆን የሚሰራውን እያንዳንዷን ነገር ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነው። ሌላ ማስተማመኛዬ ደግሞ ስራውን ለአራት ሆነን መስራታችን በራሱ ስራው ትልቅ ለመሆኑ ምስክር ነው።

"የሚያጓጓ ይመስላል! ምን ትላለህ ፓፒ?" የሚለው የፓውሎ ጥያቄ ከሀሳቤ ባያነቃኝ ኖሮ ቶሎ አልመለስም ነበር።

"ተስማምቻለሁ!!" አልኩት በሙሉ ራስ መተማመን። በነጋታው ፓወሎና ጋትሰን እና እኔ ራሳችንን ለጉዞ አዘጋጅተን ነበር።

# ምዕራፍ ስድስት

## ከባንኩ ስር ያለው ዋሻ

ጉዞ ከጀመርን ሦስት ቀናቶች አልፈዋል ፡፡ታዲያ በእነዚህ ቀናቶች ውስጥ ለመኪናዋ ጋዝ ለመሙላት ባቆምን ቁጥር ፓውሎ መኪናዋን በጥንቃቄ ይፈትሽ ነበር። ይሄን ያህል ለምን መጠንቀቅ እንደፈለገ ግን አልገባኝም ነበር። ለሰዓታት ከተጓዝን በኋላ እንደገና የሆነ ነዳጅ ማደያ ጋር ስንደርስ ፓውሎ መኪናውን አቁሙ በዚያ ዝናብ ካስወረደን በኋላ መኪናዋን እየነዳ ወደ ማደያው ገባ፡፡ ለግማሽ ሰዓት ያክል እዛ ምንም መጠለያ የሌለበት ቦታ ላይ ዝናብ ካስደበደበን በኋላ መኪናዋን ይዞ ወደ እኛ ሲመጣ ተመለከትኩት፤ በዚህ ሰዓት ግን ንዴቴን መቆጣጠር ስላልቻልኩ

“እኔ የምልህ ፓውሎ... ጋዝ ለመሞላት በቆምን ቁጥር ይሄን ያህል መኪናዋን መፈተሽ አስፈላጊ አይመስለኝም፡፡ እስኪ እኛን ተመልከተን ዝናቡ እኮ በቁማችን ሊገለን ነው” አልኩት ንዴቴ ሳይበርድ

“ምንድነው የምትቀባጥረው ፓፒ ስስራ እኮ ነው የቆየሁት... ጎማዎቹን በንፋስ መሙላት ነበረብኝ፤ የኋላ ጎማውን መቀየር ነበረብኝ፤ ዘይትና ውሃም እንደዚሁ፡፡ ታድያ ይህን ሁሉ ስራ በአምስት ደቂቃ እንድንከውን ነው እንጴ ፍላጎትህ”

“እንደዛ አልወጣኝም... ነገር ግን ሁሌ ባቆምን ቁጥር መኪናዋን መፈተሽ ትርጉሙ ስላልገባኝ ነው”

“እኔ ግን ገብቶኛል... እና ደግሞ ማወቅ ያለብህ ነገር ቢኖር በዚህ ስራ ላይ አለቃው እኔ ነኝ፡፡ ስለዚህ እኔ ያልኩት ነገር ይሆናል ማለት ነው፡፡ ምንአልባት አንተ አስራ አራት ዓመት በእስር ስለቆየህ ህይወት ብዙ ነገር አስተምራኛለች ብለህ ታስብ ይሆናል፡፡ በእርግጥ ትክክል ነው፤ ነገር ግን እኔም እንዳንተው ለአስር አመታት የገዛ ሀገሬ ላይ በእስር አሳልፌያለሁ፡፡ ያ ማለት እኔንም ህይወት አንተን ያስተማረችህን ያህል አስተምራኛለች ማለት ነው፡፡ ስለዚህ

አስቀድሜ ማድረግ ያሰብኩትን ነገር አንተ አትነግረኝም! ስታስበው አንድ ሰው የያዘች ቼቭሮሌት መኪና እና ሦስት ሰው የያዘች ቼቭሮሌት መኪና እኩል አቅም ያላቸው ይመስልሀል?"

ትክክል ነበር! ለአስር ሰዓታትም እንዲሁ መኪናዋን ስትቆም ስንሄድ በመጨረሻ ስራው ሊሰራባት ወደታሰበችው ሀገር ደረስን፡፡ ፓውሎ በግራም በቀኝም የሚያማምሩ ቪላ ቤቶች በተሰሩበት መንገድ እኔና ጋትሰንን ይዞን ሄዶ አንዱ ጥግ ላይ መኪናዋን ካቆማት በኋላ ከመኪናው እንድንወርድ ምልክት እየሰጠን "በቀኝ በኩል ያለውን የድንጋይ ንጣፍ ተከትላችሁ ሒዱ... ትንሽ እንደተራመዳቹ አንድ'ሚያሞር' የሚል ጽሁፍ ያለበት ትልቅ ቤት ታገኛላቹ... ልክ ቤቱን እንዳያችሁት እንደራሳቹ ቤት ዘና ብላቹ ወደ ውስጥ ግቡ፡፡ ቤቱ ውስጥም ኦገስቴ የሚባል ሌላኛውን ባልደረባችንን ታገኙታላችሁ" አለን

እኛም ፓውሎ ባዘዘን መሰረት በስተቀኝ ታጥፈን ጥቂት እንደተጓዝን የነገረንን ቤት ማግኘት ቻልን፡፡ እኛም ፓውሎ እንደነገረን ማንም እንዳይጠረጥር እንደራሳችን ቤት እየተጀነንን ግቢው ውስጥ ገባን፡፡ ግቢው በተለያዩ እፅዋቶች እና አበቦች የተሞላ ስለሆነ ለእይታ በጣም ይማርካል፡፡ በዚያ ላይ የቤቱ ውበት እና የግቢው ፅዱነት ዘላለም ኑሩብኝ የሚያሰኝ ነው፡፡ ወደ በሩ ተጠግተንም በሩን መቆርቆር ጀመርን፡፡

ከውስጥ የሆነ ከወገቡ በላይ ራቁቱን የሆነና ፊት እና እጆቹ በአቧራ የተሸፈነ ሰው በሩን ከፍቶ "እሺ ሰላም ናችሁ...ኑ ግቡ" አለን ቀጠለናም እንድንቀመጥ ከጋበዘን በኃላ "ፓውሎስ?" ብሎ ጠየቀን

"ይመጣል መኪናዋን አመቺ ቦታ አቁሟት ለመምጣት አስቦ ነው" ብሎ ጋትሰን መለሰለት

"ጥሩ... እና ጉዟችሁ እንዴት ነበር?"

"አሪፍ ነበር አልኩት"

ይህንን ከተነጋገርን በኋላ ሌላ ያወራነው ነገር አልነበረም ነበር፡፡ እዛው ሳሎን ውስጥ እንደተቀመጥን በውስጤ ብዙ ነገሮችን ማውጣት እና ማውረዱን ተያያዝኩት... ስራው ምንድነው? ለምንድነው ፓውሎ እዚህ እስክንደርስ ድረስ ስለስራው ሊነግረን ያልፈለገው?. . .ጋትሰንም እንደኔው ሁሉ ስለስራው የሚያውቀው ነገር እንደሌለ ወደ እዚህ ስንመጣ በመንገዳችን ላይ ፓውሎ ጋዝ ለመሙላት መኪናውን ይዞ ወደ ማደያው በገባበት ወቅት ብቻችንን መሆናችንን አይቶ ስለሁኔታው ምንም እንደማያውቅ ነግሮኛል፡፡ ታዲያ

ፓውሎ ይህን ማድረግ ለምን ፈለገ? በዚህ መሃል ፓውሎ የተናገረውንግግር ውስጤ አቃጨለ "ስራውን የመቀበልም ሆነ ያለመቀበል ያንተ ውሳኔ ነው፡፡ ነገር ግን ማወቅ ያለብህ ነገር ቢኖር ስራውን ከጨረስን በኋላ ወደ ኪሶቻችን ጠቀም ያለ ገንዘብ እንደሚገባ አትጠራጠር" ያለውን አስታውሼ በተወሰነ መልኩ ውስጤን ካረጋጋሁ በኋላ 'አሁን እንግዲህ የተባለው ቦታ ላይ ደርሰናል፤ ስለዚህ ስለስራው ግልጽ የሆነ መረጃ ያስፈልገኛል!' አልኩ ለረሴ

አገስቴ ለሁለታችንም ቡና ከማቅረብ እና ስለጉዞው አንዳንድ ጥያቄዎችን ከመጠየቅ ውጪ ስለስራው ምንም ነገር ትንፍሽ አላለም ነበር፤ ለሁሉም ነገር አሁን ፓውሎ ሲመጣ ሁሉን ነገር አውቀው የለ ለምን አሁን እራሴን በጥያቄ አጨናንቃለሁ ብዬ ሁሉን ነገር ትቼ የፓውሎን መምጣት መጠባበቅ ጀመርኩ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ከግቢው ውጪ የመኪና ድምፅ ስለሰማን ፓውሎ ስለመሆኑ አልተጠራጠርንም ነበር፡፡

ፓውሎ ፊቱ ላይ ደስታ እየተነበበት ወደ ቤቱ ከገባ በኋላ ከላይ የለበሰውን ጃኬቱን አውልቆ መስቀያው ላይ እየሰቀለ "እንዴት ነው ታዲያ ሰዎች... አልደበራችሁም አይደል?" አለ

"ኧረ በፍጹም" አልኩት ቀድሜ

"እንግዲህ ጓደኞቼ ሁሉም ነገር በታቀደለት መንገድ እየሄደ ነው" ካለ በኋላ ወደ አገስቴ ዞሮ ከመደርደሪያው ላይ አንድ ጠርሙስ ሩም ይዞ እንዲመጣ አስደርጎ ለሁላችንም እንዲቀዳ አስደረገ፡፡ ቀጠለናም ሁላችንንም ብርጭቆዋችንን ይዘን እንድንጎነጭ ካስገደደን በኋላ ወሬ ለመጀመር ጉሮሮውን ጠራረገ

"ጓዞች... አሁን እንግዲህ ሁላችንም ተሰባስበናል ስለዚህ ስለስራው የምናወራበት ምርጡ ግዜ አሁን ይመስለኛል... ከእናንተ የምፈልገው በጥሞና እንድታዳምጡኝ ብቻ ነው፡፡ አሁን ካለንበት ከዚህች ቤት ፊትለፊት ካለው መንገድ ተሻግሮ የምታዩት ግንብ የከተማዋ ትልቁ ባንክ ጀርባ ነው፡፡ ይህን ስላችሁ በእርግጠኝነት አገስቴ እንዲህ አቧራ በአቧራ የሆነበት ምክንያት ወዲያው ወደ ህሊናቹ ሳይመጣ አይቀርም፡፡ ስራ ለማቅለል በሚል አገስቴ አስቀድሞ ስለጀመረው እናንተ የሚደርሳቹ ትንሽ ነው" አለ

"እና ምንድነው እንድናደርግ የፈለከው?" አለ ጋትሰን ነገሩ ቢገባውምያልገባው በመምሰል

"ከባድ ነገር አይደለም... መቆፈር ብቻ! ከዚህ ቀጥሎ ባለው ክፍል ውስጥ ቁፋሮውን አስቀድመን ጀምረነዋል... ለዛ ነው አገስቴን አቧራ በአቧራ ሆኖ ያያችሁት... እቅዱ ምን መሰላቹ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ክፍል ውስጥ የጀመርነውን ቁፋሮ ቢያንስ እስከ ሦስት ሜትር ድረስ ወደ ታች ከቆፈርን በኃላ እስከ ባንኩ ገንዘብ ማስቀመጫ ካዝና ድረስየሚያደርስ ዋሻ ደግሞ ውስጥ ለውስጥ ወደ ጎን እንቆፍራለን ማለት ነው። እንግዲህ በቀላሉ ስራው ይሄ ነው። ምን ትላላችሁ ታዲያ?"

"ትንሽ ማሰቢያ ጊዜ ስጠኝ እንጂ... ይሄ እኮ የህፃናት ጨዋታ አይደለም" ካለ በኃላ ወዲያው "ትልቅ ባንክ ነው ግን?" ብሎ ጠየቀው

"ነገ ደንበኛ መስለህ ገብተህ ማየት ትችላለህ... ስምንት ካሽሪዎች ያሉት ሰፊ ባንክ ነው"

"እሬ... እንደዛ ከሆነማ ትልቅ ባንክ ነው ማለት ነው። ስለዚህ ጥሩ ገንዘብ ሳናገኝበት አንቀርም" አለ ጋትሰንመዓዓቱ ፊቱ ላይ እየተነበበ... ፓውሎ የጋትሰንን መጓጓት ካየ በኃላ ወደ እኔ ዞሮ "ፓፒ አንተስ ምንም የምትለው ነገር የለም?" አለኝ

"ምንም ማለት አያስፈልግም... እንዳልከው ስራው ከተሳካ ብዙ ገንዘብ ልናገኝበት እንችላለን ነገር ግን ስራው ከመጀመሩ በፊት ማወቅ የምፈልጋቸው ነገሮች አሉ... መጠየቅ እችላለሁ አይደል?"

ያልገባህን ነገሮች በሙሉ መጠየቅ ትችላለህ... አንተ ብቻ ሳትሆን ሁላችሁም ግልፅ እንዲሆንላችሁ የምትፈልጉት ነገር ካለ መጠየቅ ትችላላችሁ... ለዚህ ስራ ህይወታችንን እስከሰጠን ድረስ እና አላማችን ተልቅ አስከሆነ ድረስ ግራ የሚያጋባ ማንኛውም ነገር መኖር የለበትም

"እሺ የመጀመሪያ ጥያቄዬ አሁን ካለንበት ቤት እስከ መንገዱ ድረስ ያለው እርቀት ምን ያህል ነው?"

"እንደግምቴ ከሆነ ወደ አሰራስድስት ሜትር አካባቢ ይደርሳል"

"ከመንገዱ ጫፍ እስከ ባንኩ ጫፍ ያለው እርቀትስ?"

"ዘጠኝ ሜትር"

"ጥሩ... በባንኩ ውስጥ በየትኛው ክፍል ውስጥ ብሩ እንዳለ አጣርተሀል?"

"እሱንማ ሳላጣራማ እንዴት ስራውን አስበዋለሁ ብለህ ነው፡፡ መጀመሪያ ይሄንን ስራ ለመስራት ሳስብ በባንኩ በመመላለስ ደንበኝነት ከማትረፍም አልፌ የባንኩን የውስጥ ክፍሎች የማየት እድሉን አግኝቼ ነበር፡፡ እና ዋናው የገንዘብ ማስቀመጫ ክፍሉ የሚገኘው ከመደበኛው ደንበኞችን ለማስተናገድ ከሚጠቀሙበት የገንዘብ ማስቀመጫ ክፍል በወፍራም ግንብ ተከፍሎ ነው"

"የግንቡን ስፋት መገመት ትችላለህ?"

"ይሔን ያህል ነው ለማለት ያዳግተኛል…ብቻ በጣም ወፍራም መሆኑንን እርግጠኛ ነኝ"

"ከዋናው የባንኩ ወለል አስከ ዋናው የገንዘብ ማስቀመጫ ክፍል ለመድረስ ምን ያህል ደረጃ ያስወርዳል?"

"አስራሁለት"

"ስለዚህ የገንዘብ ማስቀመጫው ካዝና የሚገኝበት ክፍል ከመሬት ጠለል በታች ወደ ሦስት ሜትር አካባቢ ዝቅ ብሎ ይገኛል ማለት ነው… ታዲያ እቅድህ ምንድነው?" አልኩት

"የእኔ እቅድ ምን መሰለህ… ቁፋሮአችንን በሁለቱ ክፍሎች መሀከል እስካለው ግንብ ድረስ ማድረግ . . .ይሄን ለማድረግ ደግሞ ባንኩ አካባቢ ስንደርስ ከስር በምናገኛቸው የኤሌክትሪክ ሽቦዎስ እየተመራን እስከ ግንቡ ድረስ መሄድ እንችላለን፡፡ ግንቡ ጋር እንደደረስ እርግጠኞች ስንሆን አሳቻ ሰዓት ጠብቀን ግንቡን በማፈራረስ ባንድ ግዜ ሁለቱም ክፍሎች ውስጥ ለመግባት እንችላለን ማለት ነው"

"በትክክል ነገር ግን የኤሌክትሪክ ገመዶቹበግንቡ መሀል ለመሀል ከመሄድ ይልቅ ከግድግዳው ውጪ ከሆኑ ከሁለቱ በአንደኛው ክፍል ውስጥ መውጣታችን የማይቀር ነው"

"እሱን አላሰብኩትም ነበር ባክህ… ቢሆንም ግን ቀላል ነው ግንቡ ጋር ስንደርስ ሰፋ አድርጎ በመቆፈር በሁለቱም ክፍሎች ውስጥ ለመውጣት እንዲያመች ማድረግ ይቻላል"

"ከዛይልቅ ግን በሁለቱም ክፍሎች ውስጥ ራሳቸውን ቀዳዳ ብንቆፍርላቸው የተሸለ ይመስለኛል"

"እኔም እንደዛ አስባለሁ" አለ ጋትሰን በሃሳቤ ሙሉ ለሙሉ ተስማምቶ

"እሺ ፓፒ እሱን እዛው ስንደርስ ብናወራው አይሻልም… ለጊዜው ግን ስለጅማሮው እናውራ"

"እሺ… የምንቆፍረው ዋሻ ከዋናው መንገድ በምን ያህል ይርቃል?"

"በሦስት ሜትር"

"ስፋቱስ ምን ያህል ነው?"

"ሰማኒያ ሳንቲም… ቢያንስ ሁለት ሰዎችን ባንድ ጊዜ ማሳለፍ ይኖርበታል"

"የዋሻው ቁመትስ"

"አንድ ሜትር"

"በዋሻው ስፋትና ቆመት ተስማምቻለሁ… ነገር ግን ከመሬትየሸሸንበት እርዝማኔ ግን አልተዋጠልኝም ሦስት ሜትር በጣም ትንሽ ነው ያ ማለት ከመንገዱ በላይ የሚርመሰመሱት መኪኖች ሊደረምሱት ይችላሉና ነው"

"ለእሱ አታስብ… ወደእዚህ አካባቢ ትልልቅ መኪኖች አይመጡም"

"ጥሩ ባንኩ ባለስንተ ወለል ነው"

"ከመሬት በላይ አንድ ብቻ ነው"

"ስለዚህ መሰረቱ ቅርብ ነው ማለት ነው"

"አዎ ቅርብ ነው"

"ስለ ጥበቃውስ . . . ለምሳሌ የማስጠንቀቂያ ደውል ቢኖርስ"

"ለእኔም ጥያቄ የሆነብኝ ነገር እሱ ነው… ቢሆንም ግን የትኛወንም በር እስካልነካን ድረስ የማስጠንቀቂያ ደውሉ ይጮሃል ብዬ አላስብም"

"ምን አልባት ወደባንኩ እየተጠጋን ስንመጣ ቁፋሮአችን በሚፈጥረው መንቀጥቀጥ ምክንያት ካልጮኸ በስተቀር እኔም ባንተ ሀሳብ እስማማለሁ…

እሱም ቢሆን ወደባንኩ ስንቃረብ በጥንቃቄ የምንቆፍር ከሆነ የሚያሳስብ ጉዳይ ያለ አይመስለኝም" አለ ጋትስን

"ጥሩ ጥያቆችህን ጨረስክ ፓፒ?"

"አዎ… ለቁፋሮ የሚሆኑ ቁሶችን የት ነው ያሉት?"

"ከጎሮ በኩል ባለው ትንሽዬ ጋራዥ ውስጥ ሁሉም የሚያስፈልጉን እቃዎች ተቀምጠዋል"

"ጥሩ… ተቆፍሮ የወጣው አፈርስ የት ነው የምናደርገው?"

"በቅድሚያ ግቢው ውስጥ ለመነተን እንሞክራለን ቀጥለን ደግሞ ለአበቦች መትከያ የሚሆን ቦታ አዘጋጅተን እዛ ውስጥ እንጨምራለን… ይሄም የማይበቃው ከሆነ ግን ግቢው ውስጥ ለመቆለል እንገደዳለን ማለት ነው"

"ከጎን ስላሉት ጎረቤቶችስ የሚሳስብ ጉዳይ የለም?"

"በቀኝ በኩል ያሉት ምስኪን አሮጊትና ሽማግሌ ናቸው፡፡ ይገርምሃል ውሻቸው አንድ ቀን ግቢዬ ውስጥ ስለተፀዳዳ ብቻ ባገኙኝ ቁጥር ይቅርታ የሚጠይቁኝ ሰዎች ናቸው፡፡ በስተግራም በኩል እናትና አባታቸው ስራ ቀኑን ሙሉ ስራ በመዋላቸው ምክንያትበብዛት ግቢው ውስጥ የሚውሉት የስምንት እና የአስር አመት ልጆች ናቸው፡፡ እነሱም ቢሆኑ ኾዋኾዌ ላይ ሲጫወቱ ነው የሚውሉት ስለዚህ ምንም የሚያሳስብ ጉዳይ የለም"

"አንድ የዘነጋሁት ጥያቄ አሁን መጣልኝ ገንዘብ ማጠራቀሚያው ክፍል ከገባን በኃላ የብረት ካዝናውን እንዴት ነው የምንቆርጠው?"

"በእኔ አስተሳሰብ እንግዲህ ብረቱን ለመቁረጥ ሁለት አይነት መንገዶች መጠቀም እንችላለን አንደኛው መንገድ ኦክስጅንን በመጠቀም ሲሆን ሌላኛው አማራጭ ደግሞ የብረት መበየጃ በመጠቀም ብረቶቹን መቁረጥ እንችላለን ማለት ነው፡፡ በእርግጥ ለኛ የሚቀለው በመበየጃ ማሽን መቁረጡ ነው፤ ነገር ግን የመበየጃ ማሽኑን ለማንቀሳቀስ ሁለት መቶ ሃያ ቮልት ሲያስፈልገው ወደእዚህች ቤት የሚገባ ሀይል ግን መቶ ሃያ ቮልት ነው፡፡ ለነገሩ የሚያሳስብ ነገር የለም አሰቀድሜ ስለሁኔታው አስቤበታለሁ ለዚህ መፍትሄ የሚሆን ከአንድ የማውቀው ሰው ጋር አውርቼአለሁ ይህም ማለት አምስተኛ ሰው ከእኛ ጋር ይቀላቀላል ማለት ነው፡፡ አሁን ያልጠራሁትም በቁፋሮው ስራ ላይ

እንዲሳተፍ ስላልፈለኩ ነው፡፡ ቁፋሮውን ከጨረስን ከሁለት ቀናት በኃላ እንዲመጣ ማድረግ ይቻላል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ምን ትላላችሁ ጓደኞቼ?"

"አምስተኛ ሰው መምጣቱ ምንድነው ጥቅሙ… ማለቴ ምን የተለየ ነገር ይፈጥራል?" አልኩት

"እንደሱ አባባል ከሆነ 'ምስጥ' ብሎ የሰየመው ማሽን እንዳለውና ምንም ነገር ሊቆርጥ እንደሚችል ነው የነገረኝ"

"ከአራት ይልቅ ለአምስት ልንካፈል ነዋ?" አለ ጋትሰን እየከፋው

"ለእሱ አታስብ… አራት ሆንን አምስት ያው ነው… መያዝ ከምትችለው በላይ የሆነ ገንዘብ በባንኩ ውስጥ ስላለ ድርሻዬ ያንሳል ብለህ እንዳትሰጋ… ዋናው ስራውን በድል መወጣት መቻል አለብን"

"እንደኔ እንደኔ ያንን አንተ የምታመጣውን ባለማሽኑንን ብንጠብቀው የተሸለ ይሆናል በማይሆን ነገር ጊዜአችንን ከምናጠፋ እሱ ይዞት በሚመጣው ማሽን ስራችንን ማቅለሉ በጣም ተመራጭ ነው" ብዬ በፓወሎ ሃሳብ መስማማቴን ገለፅኩላቸው

"ሌላ ተጨማሪ የምናነሳው ነገር ከሌለ አንግዲህ እቅዳችን ይህን ይመስላል… ሁላችንም ተስማምተናል?"

ሁላችንም መስማማታችንን በአዎንታ ገለፅን… በመጨረሻም ፓውሎ ወደ እኔ ዞሮ እኔም ሆንኩ ጋትሰን በቀን በፍፁም ለውጪ ሰው መታየት እንደሌለብን ነግሮን መውጣት ከፈለግን እንኳ ማታ ማታ ማንነታችንን የማያጋልጥ አለባበስ ለብሰን መውጣት እንደምንችል ማስጠንቀቀቅያ አዘል ምክር ሰጠን፡፡ ከእሱ በተጨማሪ ደግሞ በምንም አይነትመልኩ አራታችንም አንድ ላይ መታየት እንደማይኖርብን አስረዳን፡፡

ውይይታችንን እንደጨረስን አገስቴ የጀመረውን ቁፋሮ ለማየት ወደ ቀጣዩ ክፍል ገባሁ፡፡ አጀማመሩ የሚደንቅ ነው፡፡ አገስቴ በደንብ አድርጎ ነበር የቆፈረው ጎንና ጎኑን በስነስረዓት እንደተገነባ ግንብ ቀጥ አድረጎ ነበር የቆፈረው ያም ዋሻውን ለመብሳት አዳጋች አይደለም፡፡

በዚህ መሃል ዋሻውን እየቆፈርን ወደውስጥ በገባን ቁጥር የአየር እጥረት ሊከሰት እንደሚችል እርግጠኛ ስለነበርኩ አብሮኝ ቆሞ የተቆፈረውን ጉድጓድ በመመልከት ወደ ነበር ፓውሎ ዞሬ

"ጉድጓድ ውስጥ እኮ አየርሊያጥረን ይችላል"

"አዎ ሊያጋጥም ይችላል... ለዛም ነው ካራካስ እያለሁ አንድ በኦክስጅን የተሞላ ሲሊንደር(ኮምፕሬሰር) የገዛሁት እሱም ጋራዡ ውስጥ አለ። እየሰራን ባለንበት ወቅት አንዳችን አየር እጥረት ቢያጋጥመን ከኛ የሚጠበቀው ነገር ቢኖር ከኮምፕሬሰሩን ቱቦ ወደአፋችን በማስጠጋት ከኦክሰጅኑ ትንሽ መሳብ ብቻ ነው"

"በጣም ጥሩ! የአየር ማቀዝቀዣስ?"

"እሱም አለ ግን ትንሽ ከሰራ በኃላ ፊውዙን እያቃጠለ አስቸግሮኛል"

"መኖሩ በቂ ነው...ለማስተካከል እንሞክራለን" ቀጠልኩና "ፓውሎ ያ ባለምስጡ ሰውዬ የሚያገጥመውን አናውቅምና ምናልባት ካልመጣ እኛም የራሳችንን መንገድ መፍጠር ይኖርብናል፤ ስለዚህ ምን እናደርጋለን መሰለህ ብረቶቹን ለመቁረጥ የብረት መበየጃ ማሽኑ የተሻለ ስለሚመስለኝ በዚች ቤት ውስጥ የሚገባውን የኤሌክትሪክ ሀይል ማስጨመር ቀላሉ መንገድ ነው። ይህንንም ለማድረግ ምን እናደርጋለን መሰለህ  ፍሪጅ እና የአየር ማቀዝቀዣ ልታስገባ እንደሆነ ትናገርና በቤትህ ውስጥ ያለው መቶ ሃያ ቮልት ደግሞ ፍሪጁን ም ሆነ የአየር ማቀዝቀዣውን ለማንቀሳቀስ በቂ ስላልሆነ ወደ ሁለት መቶ ሀያ ቮልት እንዲያሳድጉልህ አመልክት። ይህንን ማድረግ ከቻልክ ያለማንም እገዛ እኛው ራሳችን ብረቶቹን መቁረጥ እንችላለን ማለት ነው  ምን ትላለህ?"

"የተቀደሰ ሀሳብ ነው ፓፒ እንደዛ ማድረጉ ሳይሻል አይቀርም። አሁን ግን ስለስራው ማውራታችንን ለጊዜው ገታ እናድርገውና ኦገስቴ የሰራልንን ፓስታ እንብላ" ብሎ ወደ ሳሎኑ ይዞኝ ገባ

የኦገስቴ ፓስታ እጅግ ከመጣፈጡ የተነሳ ወንድ የሰራው ለመሆኑ ያጠራጥር ነበር። በጣም ግሩም እራት ነበር። ተመግበን እንደጨረስን ስላለፈው ጊዜ እያነሳን መጨዋወት ጀመርን። በወሬአችን መሀል ጥሩ ጥሩ ተውስታዎችን ብቻ እያነሳን እንድንጫወት ስለተስማማን ስሜትን የሚረብሽ ጨዋታ አንዴም አልተነሳም ነበር። የምናነሳቸው ጨዋታዎች በሙሉ  ከሴት፣ ከወሲብ፣ እና ወቅታዊ ስለሆኑ ጉዳዬች ብቻእንዲሆን ተስማምተናል። በቃ ምሽቱን ልክ እንደተኮረኮረ ህፃን ልጅ ስናገጥ አሳለፍነው። በጣም የገረመኝ ግን ስለባንኩ ዝርፊያ ያን ያህል ስናውራ እኔም ሆንኩ ሌሎቹ አንዳችንም ልንዘርፈው ያሰብነው ብር የገዛ የማህበረሰባችን ገንዘብ መሆኑን ለማስረዳት የፈለገ አለመኖሩ ነው።

በቀጣዩ ቀናቶች ፓውሎ ጊዜ ሳያጠፉ እንደተባባልነው ፍሪጅና የአየር ማቀዝቀገር ሊያስገባ ስለፈለገ የቤቱን የኤሌክትሪክ ሀይል እንዲጨምሩለት ስለተናገረ ወዲያው ወደ ሁለትመቶ ሃያ ቮልት ቀየሩለት። ለነገሩ እንዲህ በፍጥነት የቀየሩለት ከፓውሎ ግቢ አጠገብዋናው የኤክትሪክ ማከፋፈያ ትራንስፎርመር ስላለ ነው። እኛም ከዚያ ቀን ጀምሮ ጉድጓዱን የመቆፈር ስራውን ተያይዘነው ነበር። መጀመሪያ አካባቢ ቁፋሮአችንን ከላይ ስለነበረ በቁፋሮ በሚወጣው ድምጽ ሰው ይሰማናል የሚል ፍርሀት ውስጣችን ላይ አድሮ ነበር። ከሦስት ሜትር ጥልቀት በኃላ ግን ጥልቀቱም እየጨመረ ስለመጣ ሰው ይሰማናል የሚለው ስጋታችን እንደ ጉም በኖ ጠፋ። ከጥቂት ቀናቶች በኃላም ጉድጓዱን ሙሉ ለሙሉ ቆፍረን ጨረስን። ያም ሆኖ ጊዜ ማባከን ስላፈለግን ቶሎ ብለን ወደ ዋሻው ቁፋሮ ገባን። እንደ ፓወሎ ስሌት ከሆነ ከእዚህ በኃላ ወደ ሀያአምስት ሜትር ኩብ የሚሆን አፈር ማውጣታችን እንደማይቀር ነግሮናል።

"አይዟቹ! ይህ የጥበበኛ ዘራፊዎች ስራ ነው" ይላል ፓሎ ድካም ሲሰማን

እያንዳንዳችን የተለያየ ስራ ስለምንሰራ ስራው በቅልጥፍና እየተካሄደ ነበር። አንድ ሰው ሲቆፍር ሁለተኛው ሰው ደግሞ አፈሩን በእጅ የሚገፋው ጋሪ ላይ እያደረገ ከዋሻው የሚወጣውን አፈር ወደ ጉድጓዶቹ ይዞ ይሄድና ለሶስተኛው ሰው ይዞ ሄዶ ይዘረግፍለታል። ሦስተኛው ሰው ደግሞ በጆንያ አፈሩን እያስገባ ከጉጓዶቹ በማውጣት ከጉድጓዱ ውጪ ለሆነው ለአራተኛው ሰው ያቀብላል። ከውጪ ሆኖ አፈሩን የሚቀበለው ሰውም አፈሩን እንዳመቸው እየወሰደ ለአትክልትመትከያ ወደተዘጋጀው ቦታና ብቢው ውስጥ የመበተንና የመደልደል ስራ ይሰራል ማለት ነው።

በቀን ውስጥ ያለማቋረጥ ለሰዓታት እንሰራለን ዋሻውን ስንቆፍር ከሚያጋጥመን አንዳንድ ጠንካራ ድንጋይ ውጪ አብዛኛውን ጊዜ ለስላሳ አፈር ነበር የሚያጋጥመን። ችግር እየሆነብን የመጣው ነገር ቢኖር የአየሩ ሁኔታ ነው። ወደውስጥ በገባን ቁጥር እንደልብ መተንፈ በራሱ አስቸጋሪ እየሆነ ይመጣል። ጭራሽ ኮምፕሬሰሩ ባይኖርማ መሰራት ሁሉ ባልቻልን ነበር ። የሙቀቱ ነገርማ አይወራ! መፈጠርን ያስጠላ ነበር። ያ በየሰዓቱ ፊውዝ የሚያቃጥለው የአየር ማቀዝቀዣ ቢኖርም ወበቁ ግን የማይቻል ነው። እንደውም በሙቀቱ ነው መሰለኝ ቆዳዬ ላይ ቀያይ ነቁጦች ከወጡብኝ ቀናት ተቆጥረዋል። ሰውነቴ በሙሉ በእነሱ ተሸፍኗል። ጋትሰን እና አገስቴም ልክ የእኔ አይነት ቀያይ ነቁጦች እደወጣባቸው አስተውያለው። ከነዚያ ቀያይ ነቁጦች ነፃ የሆነ ብቸኛው ሰው ቢኖር ፓውሎ ብቻ ነው። እሱም ሊወጣበት ያልቻለው ከጉድጓዱ እና ከዋሻወ የሚወጣለትን አፈር ከውጪ ሆኖ በመቀበል አትክልቶቹ ላይ የመደልደል ስራ ስለሚሰራ ብቻ ነው። ሁሌም ሰርተን ስንጨርስቆዳቸን

ከድርቀትና ከመሰነጣጠቅ ለመከላከል ገላችንን እንታጠብ እና በቫዝሊንና በካካዋ ዘይት ቆዳችንን ለቅልቀን ነበር የምንተኛው፡፡ ያም ሆኖ ግን ነቁጦቹ ሊጠፉልን አልቻሉም ነበር፡፡ ለነገሩ በማንም አስገዳጅንት እዚህ ስራ ውስጥ እስካልገባን ድረስ ምንም ነገር ቢደርስብን መቻል ግዴታችን እንደሆነ ለራሴም ሆነ ሁሌም ለሚነጫነጨው ኦገስቴ ከማስረዳት ቦዝኜ አላውቅም ነበር

በዚህ ስራ የተረዳሁት ነገር ቢኖር እንደዋሻ መቆፈርአስቸጋሪና ጥበብ የሚጠይቅ ስራ እንደሌለ ነው፡፡ አስቡት እስኪ መሮ፣ መዶሻና ዶማ በመጠቀም ብቻ ሁለት ሰው ባንድ ግዜ የሚያሳልፍ ረጅም ዋሻ መቆፈር በጣም ከባድ ነው! በዛ ላይ መፋቁ፣ መጫሩ ከዛ ደግሞ በዛች ጠባብ ዋሻ ውስጥ ግራ ቀኝ ብሎ እቃ መፈለጉ ብቻ ሁሉም ነገር አሰልቺ ነው፡፡ የሙቀቱ ነገር ደግሞ ስራችን ላይ አተኩረን እዳንሰራ ያደረገን ሌላው ችግር ነው፡፡ መታጠቢያ ገንዳ ውስጥ ገብቶ እንደወጣ ሰው ላብ አጥምቆን ነው የምንውለው፡፡ ይህን ሁሉ አልፈን ስራውን ከጨረስነው ግንምንም እንኳን የኛ ባይሆንም በጣም ብዙ የሆነ የሰው ሀብት እንደሚያገጥመን ግን አልጠራጠርም!

ስራችን በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ ነው፡፡ ከጓሮ የምንከምረው አፈር ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ መጠኑ እየጨመረ ነበር እኛም ግቢው ውስጥ መበተን ጀምረናል፡፡ ስራችን በእንዲህ ሁኔታ ባሪፉ እየሄደ ባለበት ሰዓት ነበር ለሁለት ቀናት ያህል ያላሰብነው ዶፍ ዝናብ የዘነበው፡፡ ዝናቡም ያላሰብነውን ትልቅ ችግር ፈጥሮብን ነበር፡፡ ወደ አርባ ሳንቲም የሚጠጋ ጥልቀት ያለው ውሃ የቆፈርነው ጉድጓድ ውስጥ ገብቶብን ነበር፡፡ ይህም የውሃ መምጠጫ ማሽን እንድንገዛ አስገደደን፡፡ ከአንድ ሰዓት በኃላም ማሽኑን ገዝተን አምጥተን ገጥመነው ነበር፡፡ ውሀ የማውጣቱ ስራ ጊዜአችንን ቢሻማብንም ውሃው ሳይወጣ ደግሞ ለመቆፈር ስለማይቻል ውሃውን አውጥተን መጨረስ ነበረብን፡፡

የታህሳስ ወር እያለቀ ነው ጥር ከመግባቱ በፊት ዋሻውን ብንጨርስ መልካም ነው፡፡ በዛ ላይ ማሽኑን ይዞ ይመጣል የተባለው ሰው ከመጣ አሁንም ቢሆን ቅድሚያ ለእሱ እንደምንሰጥ ጥርጥር የለውም፡፡ ካልመጣም ግድ አይሰጠንም አስቀድመን በነገሩ ላይ ተዘጋጅተናል፡፡

ልክ ታህሳስ ሃያ አራት ላይ የባንኩ የስር መሰረት ጋር መድረስ ችለን ነበር፡፡ ወደባንኩ በተቃረብን ቁጥር የእኛም ወኔ በዛው ልክ በጣም ጨምሮ ነበር፡፡ ከዚህ በኃላ የሚቀረን ሦስት ሜትር እንኳን የሚሆን አይመስለኝም እሱም ወደምንፈልገው ክፍል ውስጥ ለመግባት የሚያስችለንን ቀዳዳ ለማዘጋጀት ነው፡፡ ስራችን የተጠናቀቀ ያህል ስለተሰማን ደስታችንን ለማድመቅ ከፈረንሳይ የመጣ ሻምፓኝ በፓውሎ ግብዣ ተከፈተልን፡፡ ሳሎን ውስጥ ቁጭ ብለን በደስታ ሻምፓኛችንን ማጣጣም ጀመርን

"ጣዕሙ አረንጓዴዎቹን... አረንጓዴዎቹን ነው የሚለው" አለ ኦገስቴ ሊቆጣጠረው ያልቻለውን ሳቁን እየለቀቀ

"እውነት ነው! ጥሩ ትንበያ ነው። የዶላሮቹ ከለር መሆን አለበት" አለ ጋትሰን ከኦገስቴ የባሰ እያገጠጠ

በጠረጴዛ ዙሪያ እደተሰባበሰብን ያንን ምርጥ ሻምፓኝ እየጠጣን የፓውሎን ቀጣይ እቅድ መስማት ጀመርን። የሱ ሃሳብ በተቀሩት ስድስት ቀናቶች ውስጥ አፈሩን አውጥተን ከዛ በኃላ ባሉት ሦስት ቀናቶች ውስጥ ደግሞ ወደ ባንኩ ገብተን የምንፈልገውን ገንዘብ ዘርፈን እንድንወጣ ነው ሃሳቡ... እንደሱ ሃሰብ ከሆነ በዘጠኝ ቀናቶች ውስጥ ጣጣችንን ያልቃል ማለት ነው. . .ስለዚህ ዛሬ ታህሳስ ሃያአራት ነው። ዘጠኝ ቀን ሲጨመርበት ጥር አራት ይሆናል። የፓውሎ ሀሳብ ሲጠቃለል አርብ፣ ቅዳሜና እሁድን ተጠቅመን ሰኞ ጠዋት ሁለት ሰዓት አካባቢ ቦታውን ለቀን እንድንወጣ ነው

"ተስማምተናል አይደል" አለ ፓውሎሀሳቡን አውርቶ ከጨረሰ በኃላ

"እኔ አልተስማማሁም" አልኩት

"ለምን ፓፒ?"

ምክንያቱም ሰኞ ጠዋት ለፅዳት ሰራተኞች ሲባል የባንኩ በር ጠዋት አንድ ሰዓት ላይ ነው የሚከፈተው... ይህ ደግሞ እኛን ማጥውስጥ ይከተናል ማለት ነው። ስለዚህ መሆን ያለበት እሁድ እደምንም ስራችንን በሙሉ ለመጨረስ ከሞከርን በኃላ የዛኑኑ ቀን ድርሻችንን ተከፋፍልን መለያየት መቻል አለብን። እንዲህ ካደረግን ነገሩ ታውቆ ከመጣራቱ በፊት ሰፊ ሰዓት ስለሚሰጠን ከአካባቢው በጣም እንድንርቅ ይረዳናል ማለት ነው።

ሁላችንም በእኔ ሀሳብ ተስማምተን ምሽቱን እየተሳሳቅን አሳለፍነው። ደስ የምትል ምሽት ነበረች። ሁላችንም የለፋንበት ስራ ከፍፃሜ ላይ መድረሱ ሳይገባን አልቀረም። በእርግጥ በጣት የመንካት ያክል እንደተቃረብን እውነት ነው።

'ያሰብከው ሊሳካ ጥቂት ቀን ቀረህ ፓፒ' አልኩ ለራሴ 'በቅርቡ ፈረንሳይ እንደምንም ብዬ ከገባሁ በኃላየቋመጥክለትን የብቀላ ውጥንህን ትፈፅማለህ። ከዛም በላይ እድለኛ ከሆንክ ወደ ኢል ሴሎ ተመልሰህ ወደምትናፍቅህ ማሪያ ትሄዳለህ' መጀመሪያ ውዱ አባቴን ማየት አለብኝ በጣም ናፍቆኛል ቀጥሎ ብቀላዬን እፈፅማለሁ!

ዋሻውን ቆፍረን በመጨረሳችን ምክንያት ሻምፓኝ በከፈትን ከሁለት ቀናት በኃላ ነበር በጭራሽ ይፈጠራል ብለን ያላሰብነው ዱብ እዳ የደረሰብን... በእረግጥ ድርጊቱ ሲከሰት እኛበቦታው አልነበርንም ነገሩ እንዲህ ነው

ጊዜው ዋሻውን ቆፍረን መጨረሳችንን አስመልክቶሻምፓኝ በጠጣን ማግስት ወደ ከተማ ሄደን ለሁለት ቀናት ተዝናንተን ለመምጣት ሌላ ሀሳብ ስለቀረበ ሁላችንም በሀሳቡ ተስማምተን ራሳችንን ለማዝናናናት የተነሳንበት ጊዜ ነው፡፡ አራታችን አንድ ላይ መታየት የለብን የሚለው ህግ ስላለ ፓውሎና አገስቴ አስቀድመው ወደከተማ ሄደው የእኛን መምጣት ነበር የሚጠብቁት

እኛም ሽክ ብለን ከለበስን በኃላ እነፓውሎ ወደሚጠብቁን ቦታ አመራን፡፡ እነሱም ማንም የማያያቸው ቦታ ላይ የፓውሎ ቼቭሮሌት መኪና ውስጥ ተቀምጠው አገኘናቸው፡፡ ከቤት ስንወጣ ሁላችንም ተነጣጥለን በተለያየ አቅጣጫ ስለመጣን በፍፁም ጓደኛሞች ናቸው ብሎ የሚጠረጥር አይኖርም፡፡ እኔና አገስቴቶሎ ብለን ማንም ሳያይን ወደ መኪናው ከገባን በኃላ ፓውሎ ሞተሩን አስነስቶ የከተማው አቅጣጫ ይዘን መጓዝ ጀመርን፡፡ በመንገዳችን ላይም ፓውሎ ድምፁን ከፍ አድርጎ የደስታ ቃና ባለው ድምፅ "የዛሬዋ ቀን የኛ ነች ይህ ደስታ ለኛ ይገባናል፡፡ ይህንን የነፃነት አየር እንደልባችሁ ሳቡት" አለ

"ኧረ ባክህ ፍጥነትህን ቀንስ እንጂ... ዛሬ እንኳን እስኪ ከተማዋን በደንብ እንየው" አለ ጋትሰን በፓውሎ የፍጥነት አነዳድ ተናዶ... በመጨረሻም ከተማው ከደረስን በኃላ ለሁለት ተከፍለን መጪዎቹን ሁለት ቀናቶች ዘና ለማለት ከተስማማን እና በሁለተኛውም ቀን ወደቤት ለመሄድም የት እንደምንጠባበቅ ከተነጋገርን በኋላ እኔና ፓውሎ አንድ ላይ አገስቴና ጋትሰን ደግሞ አንድ ላይ ሆንን በተለያየ አቅጣጫ ሄድን፡፡ የመጀመሪያው ቀን ፓውሎ ከተማዋን በደንብ ሲያስጎበኘን አመሸን በሁለተኛው ቀን እንደዚሁ ከተማዋ ውስጥ ካሉት" ከአንዱ መጠጥ ቤት ወደአንዱ እየሄድን ራሳችን ካዝናን በኃላ ከሰዓት ለምን ቲያትር አናይም የሚል ሀሳብ ፓውሎ ስላፈለቀ ወደ ቲያትር ቤት ሄድን... ነገርግን ፓውሎ እጅ ላይ የተረፈውገንዘብ ሁለታችንንም ወደቲያትሩ ለማስገባት ስለማይበቃ የቀረበትን ገንዘብ ቲያትሩን አይተን እንደጨረስን ተመልሶ መጥቶ እንደሚከፍል ተገዝቶ ወደቲያትሩ ገባን... ቲያትሩ ግሩም ነበር!

እኛም ቲያትሩን አይተን እንደጨረስን ወደቤት ለመሄድ ከእነአገስቴ ጋር ወደ ተቀጣጠርንበት መንገድ ፓውሎ መኪናውን እየነዳ ሄድን፡፡ ከዛም ጋትሰንና አገስቴን ከጫንናቸው በኃላ ወደቤታን ጉዞ ጀመርን፡፡ የፓውሎ ሃሳብ እኛን

እቤት ካደረሰን በኃላ ከቤት ብር ይዞ ሄዶ ቲያትር ቤት ያለበትን እዳ ለመክፈልና በዛውም የመበየጃ ማሽኑን ገዝቶ ለመምጣት ነበር፡፡

ፓውሎ ከዚህ በፊት እንደሚያደርገው ሁሉ  የሆነ ሰዋራ ቦታ ፈልጎ እኔና ጋትሰንን ከመኪናው ካወረደን በሃላ አገስቱን ይዞ በሌላ አቅጣጫ ወደ ቤት ገብ ጀመረ፡፡ እኛም ወደ ቤቱ አቅራቢያ ለመድረስ የተወሰኑ እርምጃዎች እንደቀረን ባየሁት ነገር ልቤ ለተወሰኑ ሰከንዶች ቀጥ ብላ እንደነበር አስታውሳለሁ… ከድንጋጤዬ የተነሳ የጋትሰንን እጅ ጨምድጄ ይዤው ነበር

"ምንድነው የተፈጠረው?" አልኩት ድንጋጤዬ እንዳለ

"እኔንጃ" አለኝ ጋትሰን የወጡት ቃላቶች የሱ በማይመስል የለቀሰ ቃና ባለው ንግግር

ከፓውሎ ቤት እስከ ባንኩ የቦረቦርነው ዋሻ ተደርምሶ አካባቢው በሰዎች እና በፖሊሶች ተከቦ እየታየ ነበር፡፡ የእሳት አደጋ ሰራተኞች ደግሞ ምንአልባት የሞተ ሰው ሊኖር ከቻለ በሚል የተደረመሰውን አፈር ከዋሻውውስጥ እያወጡ ነበር … ዋሻችንን አግኝተውታል!

ጋትሰን አጠገቤ ቆሞ ልክ ወባ እንደያዘው ሰው እየተንዘፈዘፈ ወደእኔ ዞሮ "እነዚህ እርጉሞች ዋሻችንን አፈረሱብን "አለ

በዚች ቀውጢ ሰዓት አንድ ፖሊስ አትኩሮቱን ወደእኛ ሲያደርግ ስላየሁት የሆነ ሰበብ ፈጥሬ ነገሩን ማስቀየስ ስነበረብኝ የጋትሰንን እጅ ይዤ ተንከትክቼ ከሳቁ በኃላ በተሰባበረ ስፓኒሽኛ "እነዚህ ሌቦች የሚገርም ዋሻ አይደል እንዴ የሰሩት" አልኩ በማላገጥ አይነት ፖሊሱም ምስጋና ይግባውና ወዲያው ነበር እይታውን ከእኛ ላይ የነቀለው… እኔም ጊዜ ሳላባክን ጋትሰንን ይዤ በዝግታ ወደ አንዱ ሰዋራ ቦታ ይዤው ከሄድኩ በኂላ

"ጋትሰን ኪሶችህ ውስጥ ስንት ብር አለ? እኔ  ስድስት መቶ ዶላር እና አንድ ሺ አምስት መቶ ቦሊቫርስ አለኝ" አልኩት ወሳኝ ቦታ ላይስላለን ሌላ ነገር ለማውራት ጊዜ ሳልሰጥ

"ሁለትሺ ዶላር"

"ጥሩ… የገንዘብ ጉዳይ ሁለታችንም ጋር እንደሌለ እርግጠኞች ከሆንን አሁን ማድረግ የሚኖርብን ነገር ቢኖር የተለያየ አቅጣጫ ይዘንመጓዝ ብቻ ነው"

"ምን ለማድረግ አስበሃል ፓፒ?"

"እንደምንም ብዬ ወደመጣንበት ወደብ ለመመለስ እሞክርናእዛ ከደረስኩ በኃላወደቬንዙዌላ የሚሄድ ማንኛውም ጀልባ ካገኘሁ በሱ ተሳፍሬ መሄድ ነው ያሰብኩት"

መንገዱ ላይ ተቃቅፈን መሰነባበት ብንፈልግም ለሚያየን ሰው ፍንጭ እንደመስጠት ስለሆነ አይኖቻችን በእንባ እንደተሞሉ እጅ ለእጅ ብቻ ከተጨባበጥን በኃላ "ይቅናህ እንግዲህ ጋትሰን" የሚል ቃል ብቻ አወጣሁ

እሱም "ላንተም እንደዛው" ካለኝ በኃላ ሁለታችንም የተለያየ አቅጣጫ ይዘን ጉዞዋችንን ጀመርን፡፡

ፓውሎና አገስቴም ሁኔታውን መኪናቸው ውስጥ ሆነው በሩቁ ስላዩ ወዲያው አቅጣጫቸውን ቀይረው ከሄዱ በኃላ ተሰነባብተው ተለያይተዋል፡፡ ፓውሎ ወደ ፓራጓይ አገስቴ ደግሞ ወደ ቦውኖስ ኤየርስ መሄዳቸውን አውቄአለሁ፡፡ እኔም እድለኛ ሆኜ ወደ ፖርቶሪኮ የሚወስድ ጀልባ ስላገኘሁ በእሱ ተሳፍሬ ሽሽቴን ጀምሬ ነበር፡፡ ከዚያ ደግሞ ኮሎምቢያ ድረስ የሚወስደኝን አውሮፕላን ይዤ ሄድኩ፡፡ ኮሎምቢያም ምንም ያህል ጊዜ ሳልቆይ ወዲያውኑ ቬንዙዌላ የሚወስደኝንመርከብ ተሳፈርኩ፡፡

ታዲያ የዝርፊያ እቅዳችን እንዴት ሊበላሽ እንደቻለ ያወቅሁት ወራቶች ካለፉ በኃላ ነበር፡፡ እኛ ከተማ በወጣኝባቸው በነዚያ በሁለት ቀናቶቹ በዘነበው ሀይለኛ ዝናብ ምክንያት ከባንኩ ፊት ለፊት ያለውን ዋናውን መንገድ ስለዘጋው እኛ የቦረቦርነውን መንገድ እንደአማራጭ መንገድ ወስደውት ነበር፡፡ ታዲያ በዚህ መሀል አንድ ብረት የጫነ ትልቅ መኪና በመንገዱ ለማለፍ ሲሞክር እኛ የቆፈርነው መንገድ የመኪናውን ክብደት መቋቋም ስላልቻለ የኃላው ጎማው ጉድጓዱን ደርምሶት ይገባል፡፡ ነገሩ ሲጣራም የተደረመሰው ጉድጓድ የተፈጥሮ ሳይሆን ሰው ሰራሽ መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡ ከዚያ በኃላ የተፈጠረውን ማስረዳት አይጠበቅብኝም፡፡ ባጭሩ የኔምእቅድ እንደመንገዱ ሁሉ የተደረመሰ ያህል ነበር የተሰማኝ!

# ምዕራፍ ሰባት

## ካሮቴ እና አራጣ አበዳሪው

ካራካስ ስደርስ የገና በዓል እየተከበረ ስለነበረ ከተማዋ የተለያዩ ህብረ ቀለም ባላቸው መብራቶች አሸብርቃ ነበር ያገኙኋት። የገናን በዓል ሁሉም በደማቅ ሁኔታ እያከበረ ይገኛል። በዓሉን አስመልክቶ በቬንዙዌላዊኛ የተከፈቱ ሙዚቃዎች የካራሳስን ጐዳናዎችን ቀውጢ አድርገውታል። በእኔ በኩል ያሰብነው ባለመሳካቱ ባዝንም ያን ያህል ግን አልተማርኩም። በቃ!! ቁማር ተጫወትን፤ ጨዋታውን ተበላን!! ይሄነው በእኛ ሥራ ላይ የተፈፀመው ለእኔ ከሁሉም በላይ የሚያስፈልገኝ ነፃነቴ ነው፤ እሱ ደግሞ አብሮኝ አለ፤ ስለዚህ ነፃ እስከሆንኩ ድረስ የፈለኩትን የማድረግም፣ የመስራትም መብት አለኝ። ምንም እንኳን ከጆጆ ጋር ቁማር ተጫውቼ ሀሳቤ ባይሞላም፤ አሁን ዳግም ከአነፖውሎ ጋር ባንክ የመዝረፍ እቅዳችን ቢከሽፍም፤ ነፃ እስከሆንኩ ድረስ እቅዴ እንደሚሳካ ጥርጥር የለኝም።

የሆነ ስሜቴ የገና በዓልን አስመልክቶ ለማሪያ መልዕክት እንድልክላት ስለገፋፋኝ "ማሪያ ይህ የገና በዓል እናንተ ለእኔ የሰጣችሁኝ ደስታ ያህል እንዲሰጣችሁ ላንቺም ለቤተሰቦችሽም ተመኘሁ" ብዬ ቴሌግራም ላኩላት። ከዛ የገና በዓልን ከፒኬሊኖ ጋር ለማሳለፍ ወደ ሆስፒታሉ ሔድኩ። እንደደረስኩ ፒኪሊኖን ይዤ ከሆስፒታሉ ጀርባ ባለው መናፈሻ ውስጥ በተዘረጋው አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀመጥን። የገና በዓልን አስመልክቼ ሁለት ሃላካል አምጥቼለታለሁ (ሃላካስ ከአሳ እና ከዶሮ ስጋ የሚሰራ ሆኖ በዘቢብ እና በወይራ ዘይት ተለውሶ፣ በሙዝ ልጣጭ ተጠቅልሎ ለበዓላት የሚዘጋጅ የቬንዜላውያን ምግብ ነው) በነገራችን ላይ ውዱና ምርጡ ቬንዙዌላውያን የሚያዘጋጁት ምግብ ጭምርም ነው። ከእሱ በተጨማሪ ዳግም ሁለት በትንሽ ጠርሙስ የተሞሉ የጣሊያን ቀይ ወይን አምጥቼለታለሁ። እውነት ለመናገር ይህ በዓል ለእኔም ሆነ ለፒኮ ደስታን አጐናፅፎን ነበር። ፒኮሊኖ ከበፊት አሁን

በጣም ለውጥ አለው፤ ምላሱን እንደድሮ ከአፉ ውስጥ ማውጣት ትቷል፤ አፉ ላይ የሚዝረከረከው ለሀጭም አሁን ቆሟል፤ ይሄ ተዓምረኛ የገና በዓል ለፒኮሎም ፈውስ ይዞለት ሳይመጣ አይቀርም። ድሮ ለመናገር ቃላት የሚጐትተው ሰውዬ ሃላካሱእንደተመቸው ስጠይቀው ጥርት ባለቃል ነበር "አዎ"ብሎ የመለሰልኝ… በዓሉን ከፒኪሊኖ ጋር ካሳለፍኩ በኃላ ብቻዬን ሆኜ ወደፊት ስለሚገጥመኝ እጣፈንታ ማሰብ ስለፈለኩ ወደ ተከራየኂት ክፍሌ አመራሁ።

አሁን እንግዲህ ተመልሼ ካራሳስ መጥቻለሁ፤ ምን ሰርቼ እንደምኖርእያሰብኩ ነው። አሁን ምንም ነገር የለኝም የቀረኝ ነገር ቢኖር በውስጤ ያለው ምንም ያልተበረዘው በራስ መተማመኔ ነው። በዛ ላይ ደግሞ ፍቅር የሞላበት ሕይወት መምራት እፈልጋለሁ፤ ይህን ለማሳካት ምን ማድረግ እንዳለብኝ ለጊዜው አላውቅም።

በሆነ አጋጣሚ ዶ/ር ቦጋርትን መልሼ ካራካስ ውስጥ አገኘሁት። ሳገኘው ስራ ስላልነበረኝ እሱ በሚሰራበት የውበት መጠበቂያ ቅባቶች መመርመሪያ ላብራቶሪ ውስጥ ስራ ሰጠኝ። የሚከፍለኝ ገንዘብ አነስተኛ ቢሆንም ስራ እስካገኝ ግን ማፋለግያ ሆኖኛል። ከዶ/ር በጋርት ጋር ብዙም ሳልቆይ እሱን ትቼ ለአንዲት የእርጐ ፋብሪካ ላላት ሀንጋራያዊት መስራት ጀመርኩ። ይሄንን ጊዜ ነው እንግዲህ አንድ አውሮፕላን አብራሪ የተወወቅኩት፤ እውነተኛ ስሙን መጥቀስ አልፈልግም!! ምክንያቱም በዚህ ጊዜ ለፈረንሳይ ጦር ኃይል ግዳጅ ላይ የተሰማራ ሰው ስለሆነ ነው። እኔም እሱን ለመገለፅ እንዲያመቸኝ ካሮቴ ብየዋለሁ።

እኔ እና ካሮቴ ለመተዋወቅ የቻልነው እሱ ከጦር ግዳጅ በተጨማሪ ለባለ እርጐ ቤቷ ሀንጋራዊት ይሰራ ስለነበር ነው። ለመቀራረብ ጊዜ ስላልፈጀብን ሁል ጊዜ ከሰዓት በኃላ ወደ አንዱ ቡና ቤት ወይም ማጀስቲክ ወደተባለው ሆቴል ሔደን ዶሚኖ ስንጫወት ነው ጊዜያችንን የምናሳልፈው በአሁኑ ሰዓት በእርግጥ ማጃስቲክ ሆቴል ፈርሷል፤ በጊዜው ግን ትልቅ ስም የነበረው ሆቴል ነበር።

ከእለታት አንዱ ቀን ያልጠበኩት ነገር ተከሰተ፤ ካሮቴ የት እንደሔደ ሳይነግረኝ እንደወጣ ሳይመለስ ቀረ። ለተወሰኑ ቀናቶች ከተሰወረብኝ በኂላ እንደገና ተመልሶ መጣ፤ ሲመለስ ግን እንደ ከዚህ ቀደሙ ብቻውን አልነበረም። ከፊት

እና ከኋላ ሁለት ሰው ብቻ የምታስቀምጥ አውሮፕላን ይዞ ነበር የተመለሰው። አውሮፕላኗ ግሩም ነች!! ከአሜሪካ ነበር ይዟት የመጣው፤ እንዴት ሊያገኛት እንደቻለ አልጠየኩትም ብቸኛው የጠየኩት ነገር ቢኖር ምን ሊሰራባት እንዳሰበበት ብቻ ነው። ከትከት ብሎ ከሳቀ በኋላ በኋላ " እኔንጃ ለጊዜው ምን እንደምሰራባት አላውቅሁም። ምን አልባት አብረን እንሰራ ይሆናል" አለኝ

"ምን?"

"አዎ ምንም ነገር ሊሆን ይቻላል። ዘና እስካልንበት እና ገንዘብ እሳገኘንበት ድረስ የተገኘውን እንሰራበታለን"

"ጥሩ እንደዛ ከሆነ የሚሰራ ነገር እንፈልጋለን"

ምን እንደምንሰራ እና ምን ያህል ጊዜ እንደሚፈጅብን እንኳን ሳታውቅ ሀንጋሪያዊቷ ሴት ያሰብነው ስራ ተሳክቶልን በሰላም እንድንመለስ መልካም ምኞቷን ገለፀችልን።

ለተወሰኑ ወራቶች ያህል ከአውሮችላን አብራሪው ሰውዬ ጋር ጥሩ የሚባል ጊዜን አሳለፍኩ። ካሮቴ ጥበበኛ አብራሪ ነው። በዚያ አስቃቂ ጦርነቶች ወቅት ከለንደን ወደፈረንሳይ መምጣት የሚፈልጉትን እንዲሁም ከፈረንሳይ ወደ ለንደን መሔድ የሚፈልጉ የፈረንሳይ የጦር አዛዦችን በትጋት ያመላልስ ነበር፤ የሚገርመው የጦር አዛዦቹን ሲያመላልሳቸው የማንንም እርዳታ ሳያስፈልገው ብቻውን ሆኖ ነው። ይህ እንግዲህ ካሮቴ በስራው ላይ ምን ያህል ልምድ እንዳለውየሚያሳይ ነው። እኛም ከአሜሪካ ይዟት በመጣው ትንሽዬ አውሮፕላን ብዙ ቦታዎችን ማየት ቻልን፤ እጅግ በጣም የሚያዝናና ጊዜ እያሳለፍን ያለነው። ብቸኛው ችግር የሆነብን ነገር ለአውሮፕላኗ ነዳጅ ፍጆታ የሚወጣው ገንዘብ ነው። ለዚህም መፍትሔ እንዲሆነን በማሰብ እግር መንገዳችንን የንግድ ስራ ሰጀመርን፤ ቶሎ ቶሎ ሊሸጡ የሚችሉ እቃዎችን እያስመጣን መሸጥ ልማዳችን አደረግነው። በዚህ መሀል አንድ ኮሪያት የሚባል የሴት እና የወንድ አልባሳት መሸጫ ሱቅ ያለው ነጋዴ ተዋወቅን የመደብሩ ስም "አልማሴን ሪዪ" ይባላል ኮርያት መካከለኛ ቁመት ያለው አይሁዳዊ ነው እዚህ ካራካስ ውስጥም ከወንድሙ ጋር አንድ ላይ በመሆን ጥሩ ትርፍ የሚያስገኝ ስራ እየሰራ ይገኛል። የልብስ መሸጫ መደብሩ ከሞላ ጐደል የተሟላ ነው ማለት ይቻላል። የወንድም የሴትም ልብስ በአይነት በአይነቱ ተደርድረው

ተቀምጠዋል፤ በተለይ ደግሞ ለሴቶች የሚሆኑ አልባሳት የዘመኑ ፋሽን ጠብቀው በብዛት ተሰቅለዋል። አብዛኞቹን የሚያስመጣው ከፈረንሳይ ነበር፤ ያም በመሆኑ ምክንያት ለእኛ ጥሩ የስራ እድል ሳይፈጥርልን አይቀርም። የእኔ ሀሳብ እኛ ከኮርያት ልብሶች ተረክበን የሚገባንን ትርፍ ማግኘት የሚል ነበር። ኮርያት በሀሳቤ ቢስማማም ልብሶቹን ግን ከከተማ ወጣ ብለን እንድንሸጣቸው ነገረን።

ኮርያት በሰጠን መመርያ መሰረት ከከተማ ወጣ በማለት ልብስ መሸጡን ተያያዝነው፤ ስራው ጥሩ የሚባል ትርፍ ያስገኛል፤ በዛ ላይ እኛ አያይዘን መሸጥ የምንፈልጋቸው እቃዎች ስለምንሸጥ ጥቅማችን ጥሩ የሚባል ነው። ኮርያት ግን የአውሮፕላኗን ነዳጅ የመሙላት ድርሻው የእሱ ስለነበር የሚያገኘው ትርፍ እምብዛም ነበር።

የእኛ ምርጥ ደንበኞቻችን ሴተኛ አዳሪዎች ነበሩ። ከፍሎ ተጠቃሚ ወንድን ለማማለል ሲሉ በየጊዜው አዳዲስ እና ያማሩ አልባሳትን ስለሚፈልጉ ለእኛ ቋሚ ተጠቃሚ ሆነዋል። ምንም እንኳን ትርፋማ ብንሆንም በእኛ ስራ ቆሽታቸው የሚያር ሌሎች ተፎካካሪ ነጋዴዎች በዙርያችን ነበሩ።

በአንድ ወቅት ባርሴሎና አውሮፕላን ማረፍያ አካባቢ ወደሚገኝ ፖርቶ ላክሩዝ ወደሚባል ቡና ቤት ሄድን። በቡና ቤቱ ውስጥ ከስልሳ ያላነሱ ሴተኛ አዳሪዎች ይገኙበታል። አንድ አስቀያሚ ፊት ያለው ግትር ፓናማዊ ወደ እዚህ ወደ እዛ እያለ ሴተኛ አዳሪዎችን እና ሰራተኞችን ይቆጣጠራል። ባለቤቱ ደግሞ መልክ ከፀባይ ጋር ያደላት ቬንዜዌላዊት ነበረች። የሚያናድደው ግን በቡና ቤት ውስጥ ትዕዛዝ የሚያስተላልፈው እሱ ብቻ መሆኑ ነው። የሆነ ቀን ላይ ይህ ፓናማዊ መስመሩን ያለፈ መሰለኝ፤ በቡና ቤት ውስጥ ትሰራ የነበረች አንድ ሴተኛ አዳሪ እኔ አንገት ላይ ያለውን ስከርብ ስለገዛች ከስራዋ አሰናበታት። እዚህ ላይ ነው ስምምነታችን ሁላ ወደ አስቀያሚ መስመር ያመራው፤ አልፎ ተርፎ ነገሩ ወደ ፀብ ደረጃ ሲደርስ በአካባቢው ያለ አንድ ፖሊስ ለመምጣት ተገደደ። ፖሊሱም የተፈጠረውን እንኳ በቅጡ ሳያጣራ ቦታውን ለቀን እንድንሄድ እና ደግመንም እንዳንመጣ አስጠንቅቆ አባረረን

"እሺ አንተ ወፍራም አር!!" አለው ካሮቴ በብስጭት… ነገሩ ሳይገባው ፖሊሱ ማሸርገዱ ስላናደደው። እኛም ወደ እዛ ስፍራ ደግመን አልሄድንም፤ ከኮርያት

ጋር የምንሰራም ንግዱንም ከእነጭ ራሹ አቋረጥነው። እኔ እና ካሮቴ የሚያመሳስለን አንድ ትልቅ ነገር አለ፤ እሱም ሁለታችንም ለተፈጥሮ የገዘፈ ቦታ መስጠታችን ነው። አንዳንዴ ሆን ብለን አውሮፕላናችንን እንይዝ እና ያላየናቸውን ድንቅ የተፈጥሮ መስህቦች እንፈልጋለን። አንድ ቀን እንደዚሁ ቦታ ስንዳስስ ሎስ ሮኮስ የሚባል ትልቅ ደሴት አገኘን። ደሴቱ የእንቁላል ቅርፅ ያለው ሲሆን በውስጡም ሶስት መቶ ስልሳ የሚሆኑ ትንንሽ ደሴቶች የያዘ ነው። በትንንሾቹ ደሴቶች ቁርኝት ምክንያት መሀል ላይ ሀይቅ መፍጠር ችሏል። ሀይቁ ፅዱህ እና ዝም ያለ ነው፤ ያለመታደል ሆኖ ግን በደሴቱ ላይ አውሮፕላናችንን የምናሳርፍበት ቦታ አጣን። በእዚህም ምክንያት ከሎስ ሮኮስ ደሴት በስተምዕራብ በኩልአድርገን ወደ አራት ኪሎ ሜትር ከተጓዝን በኋላ ላስ አቬስ የምትባል ሌላ ደሴት ላይ ለማረፍ ተገደድን።

በእውነት ካሮቴ ድንቅ አብራሪ መሆኑን ያስመሰከረልኝ በእነዛ ኮረብታዎች መሀል አውሮፕላኗን ልክ እንደ አሻንጉሊት ሲጫወትባት ስመለከት ነው። ደሴቷ ላይ ደርሰን ልናርፍ ስንል የአውሮፕላኗ አንደኛው ክንፍ አሸዋውን እየጠረገ፣ ሌላኛው ክንፍ ደግሞ በውሀው ላይ እየቀዘፈ ሲሄድ በአድናቆት ነበር የተመለከትኩት። ይቺ ላስኤቨስ የተባለችው ደሴት በሌላ ስሟ "የወፎች ደሴት" ተብላ ትጠራለች፤ ምክንያቱም በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ ወፎች መኖርያቸው በደሴቷ ውስጥ ስለሆነ ነው። ወፎቹ ህፃናት ሆነው ነጭ ከመሆናቸው በስተቀር ሁሉም ወፎች ግራጫ ላባ ያላቸው ናቸው። እኔ እና ካሮቴም ንፁህ አሸዋ ላይ ራቁታችንን ተኝተን በወፎቹ ዝማሬ፣ በባህሩ ውበት ተመስጠን በራሳችን አለም ውስጥ ከትመናል። የሚገርመው ነገር ወፎቹ ፍራቻ የሚባል ነገር አልፈጠረባቸውም። ሲያሻቸው በአጠገባችን ሽው ብለው ያልፋሉ፤ ሲያሻቸው ደግሞ እላያችን ላይ ያለ ሀሳብ ተንደላቀው ይቀመጣሉ። አንዳንድ ጥጋበኛ ወፎች ደግሞ በመንቁራቸው ፀጉራችንን ይፈትላሉ። በቃ ከወወፎቹ ጋር መጫወት በእራሱ የተለየ ደስታ ይፈጥራል።

ፀሃይዋ ማቃጠል ስጀምር ወደ ባህሩ ሄደን ሰውነታችንን ካቀዘቀዝን በኋላ እንደገና ደግሞ አሸዋው ላይ ሄደን እንሰጣለን። የረሀብ ስሜት በተሰማን ሰዓትም ወደ ባህሩ ዳር በመሄድ ፀሀይ ሊሞቁ የወጡ ቅርፊት አልባ አሳዎች (ክሬይ ፊሽ ) በመያዝ ለማብሰያነት ባመጣነው መጥበሻ ጠብሰን እንበላለን። እዚች ደሴት ላይ አስቸጋሪ ነገር ቢኖር ለእሳት ማቀጣጠያነት የሚውል ማገዶ መፈለግ ነው፤ ምክንያቱም በደሴቱ ላይ ምንም አይነት ዛፍ አልነበረም።

በእዚች ስው አልባ በሆነች ደሴት ላይ ተኝተን እነዚያን ትንንሽ ቅርፊት አልባ አሳዎችን እየተመገብን፣ በዛ ላይ ይዘነው የመጣነውን ነጭ ወይን እያጣጣምን፣ በባህሩ ዝምታ ሰላማችንን አግኝተን፣ የጸሐይዋን ድምቀት፣ የሰማንዩን ጥራት እያደነቅን ሰላም የሰፈነበት ጊዜ ነበር የምናሳልፈው። ከእኔ እና ካሮቱ ውጪ ያሉት እነዛ ባለ ግራጫ ቀለም ወፎች ብቻ ስለሆኑ የሚረብሸን ሌላ አካል አልነበርም።

በእነዚህ ደሴቶች ላይ በተመላለስንበት ወቅት እኔም ሆንኩ ካሮቴ ተፈጥሮን ከማድነቅ ውጪ ስለሌላ ነገር ተጨንቀን አናውቅም። ላስ አቨስ በነበርንበት አንድ ወቅት ትልቅ ዋሻ ማግኘት ችለን ነበር፤ ዋሻው ጥርት ባለ የባህሩ ውሀ የተሞላ ነው፤ ጥልቀቱም ከሁለት ሜትር አይበልጥም፤ የውሀው ጥራት እጅጉን የሚያምር ስለሆነ ገብቼ እንድዋኝበት ውስጤን ገፋፋኝ። ልብሴን አወላልቄ ገባሁበት። ወደ ውስጥ ገብቼ ያስተዋልኩት ነገር ቢኖር የዋሻው ግድግዳ በሺዎች በሚቆጠሩ ክሬይ ፊሽ (Cray fish ) መሞላቱ ነው። የአሳዎቹ እዚህ ቦታ ላይ መገኘት ለአውሮፕላናችን የምናወጣውን የነዳጅ ፍጆታ እንደሚቀርፍልን ወዲያውኑ ነበር ጭንቅላቴ የተረዳሁ። ጉዳዩን ለካሮቴ ነግሬው አሳዎቹን ለመሰብሰብ የሚረዱንን እቃዎች ይዘን ተመለስን። የአንዱ አሳ ክብደት ቢያንስ አንድ ኪሎ ግራም ይመዝን ነበር። አቅማችን የፈቀደውን ያህል አሳዎችን ከሰበሰብን በኋላ መሀል ካራካስ ውስ ወደ ሚገኘው ካርሎታ ተብሎ የሚጠራው አውሮፕላን ጣብያ ይዘን በረርን። እዛም እንደደረስን አሳዎቹን መቸብቸብ ጀመርን፤ ሸጠን ለመጨረስ ጊዜ አልወሰደብንም። አሳ መሸጡ ለአውሮፕላናችን ነዳጅ እና እኛም እንደ ልባችን እንድንቀሳቀስ ጊዜያዊ መፍትሄ ስለሆነልን እየተመላለስን አሳ መሸጡን ስራችን አደረግነው። ምንም እንኳን ለአውሮፕላኗ ከባድ ቢሆንም አንዴ ደርሰን ስንመለስ ግን ከግማሽ ቶን በላይ አሳ ይዘን ነበር የምንመለሰው፤ ለነገሩ ከደሴቱ እስከ ካራካስ ድረስ ያለው ርቀት አስራ ዘጠኝ ኪሎ ሜትር ስለሆነ አውሮፕላኗ ያን ያህል ብዙ ርቀት አትጓዝም። ካርሎታ ላይ አንዱን አሳ በሁለት ከ ሀምሳ ቦሊቮር ነው የምንሸጠው፤ ያ ማለት ነዳጅ ችለን ተጨማሪ ለመንቀሳቀሻ ገቢ ሰቶናል ማለት ይቻላል። አንዳንዴ ወደ ደሴቷ ሄደን ባዶ እጃችንን የምንመለስበት ጊዜ አለ፤ ነገር ግን ምንም አይመስለንም። አውሮፕላኗን ይዘን የፈለግነውን መስራት እስከቻልን ድረስ ባዶ እጃችንን መመለሳችን አሳስቦን አያውቅም።

አንድ ቀን ወደ ፖርቶ ላክሪዝ እየበረርን እያለ ካሮቱ በውስጥ የመገናኛ የድምፅ መስመር "ፓፒ ነዳጅ ሳንጨርስ አንቀርም፤ ስለዚህ በቅርብ ወደምናየው የስንቶሚ ዘይት ማውጫ ኩባንያ ማሳ ላይ ለማሳረፍ እገደዳለሁ" አለኝ. . በመቀጠል አውሮፕላኗ እንድታዘቀዝቅ ካደረገ በኋላ ማረፍ እንደሚፈልግ ምልክት ሰጣቸው። ቦታው ላይ የነበሩት ደደብ ሰዎች ምን እንዳሰቡ ባናውቅም ፍቃደኛ አለመሆናቸውን በተለያዩ ምልክቶች ገለፁልን። በእዚህ ሰዓት ድምፅ ማጉያውን በመጠቀም ካሮቱን "ምላሻቸውን እያየሽው ነው... እና ምን ለማድረግ አሰበህል?" አልኩት

"ቆይ አንዴ ታገስ" ካለኝ በኋላ አውሮፕላኗ ወደ ጎን እንድትዞር አድርጎ በፋብሪካው ውስጥ ባለው ሰፊ መንገድ ላይ ያለምንም ችግር ለማሳረፍ ቻለ። ሆኖም ግን አውሮፕላኗ ያረፈችበት ፍጥነት እና የመንገዱ ርዝመት ስላልተጣጣመ፣ በዛላይ ደግሞ ካሮቱ አውሮፕላኗን መቆጣጥር ስለተሳነው ዘለን ለመውረድ ተገደድን። ካሮቱ ቶሎ ብሎ ከወደቀበት በመነሳት የአውሮፕላኗን ፍጥነት እንዲቆጣጠሩለት የተሰበሰቡትን ሰዎች እርዳት መጠየቅ ጀመረ። እነርሱም በርብርበ ከውጪ ይዘው እንደምንም እንድትቀዘቅዝ አደረጉ። ካሮቱም በፍጥነት ሄዶ የሰዎቹ እርዳታ ታክሎበት ማቆም ቻለ።

ይህ አግባብነት የጎደለው የአውሮፕላን አስተራረፍ ካሮቱ ለሀገሪቱ መንግስት አውሮፕላኗን እንዲሸጣት አስገደደው። የእኔም የአውሮፕላን ላይ ህይወት እዚህ ላይ መቋጫውን አገኘ። ደስ የሚል ጊዜ ነበር ያሳለፍኩት፤ ነገር ግን ካሮቱ አውሮፕላኗን ሲያጣ እኔ ደግሞ እሰራበት የነበረው የሀንጋራዊቷ የእርጎ ፋብሪካ ላይ ያለኝ የስራ ድርሻ በሌላ ሰው ተይዞ ነበር የጠበቀኝ፤ ስለዚህ አሁን ስራ ፈት ነኝ ማለት ነው። ያም ሆኖ ግን ከካሮቱ ጋር ያሳለፍኩትን ጊዜ በፍፁም የማልፀፀትበት አይረሴ ጊዜ ነው።

አውሮፕላኗ ከተሸጠች በኋላ ጊዜያችንን የምናሳልፈው በአንድ ፈረንሳዊ ሽማግሌ በምትመራ ሻይ ቤት ውስጥ ዶሚኖ በመጫወት ሆነ። የሆነ ጊዜ ላይ እዚቺው ቤት ውስጥ እኔ፣ ካሮቱ እና አንድ ከስፓኒሽ የመጣ ሰውዬ በመሆን ዶሚኖ እየተጫወትን እያለ ሁለት መነፅር ያደረጉ ሰዎች ወደ ሻይ ቤት ውስጥ ገቡ። ሶስታችንም አይተናቸው አናውቅም፤ ከሁለቱ መሀል ዘለግ ያለው ሰውዬ "እዚህ ቤት ውስጥ ፈረንሳዊ ፓይለት አለ?" ብሎ ጠየቀ...ካሮቱም ከተቀመጠበት በመነሳት "አቤት እኔ ነኝ" አለ

አትኩሬ ሁለቱንም ከእግር ጥፍራቸው እስከ እራስ ፀጉራቸው ድረስ ተመለከትኳቸው፤ አንደኛውን ከመነፅሩ ውጪ የሆነ ቦታ እማውቀው ስለመሰለኝ አትኩሮቴን የበለጠ ጨምሬ ተመለከትኩት፡፡ በድንገት ሰውነቴን ነዘረኝ!! የት እንደማውቀው ለመናገር አፌን ልከፍት ስል እሱ ቀድሞ "ፓፒ?" አለኝ

"ትልቁ ሊዎን" አልኩ ከተቀመጥኩበት በመነሳት... ሊዎን እስር ቤት በነበርኩበት ወቅት ጥሩ ጓደኛዬ ነበር፡፡ ረጅም እና ቀጭን ፊት ያለው ሊዎን!! ያ ልበ ደንዳናው እና ለጋሹ ሊዎን!! እውነት ለመናገር ስላገኘሁት ሀሴት ተሰምቶኛል፡፡ ሁኔታው ለመጨዋወት አመቺ ስላልነበር አብሮት የመጣውን ሰው ከማስተዋወቅ ውጪ ሌላ ምንም አላለም

"ተዋወቁት... ጓደኛዬ ነው...'ፔድሮ' ይባላል " ካለን በኋላ ሁላችንም ሰብሰብ ብለን ለመቀመጥ እንዲያመቸን ወደ ጥጉ ላይ ሄደን ተቀመጥን፡፡

"እኔ እምልህ... ለምን ጉዳይ ነበር የተፈለኩት ?" አለ ካሮቴ

"ቀለል ያለች አውሮፕላን ከአብራሪዋ ጋር ፈልገን ነበር... እናም ሰዎች ስንጠይቅ... አንድ ፈረንሳዊ እናዳለ ገልፀውልን ወደ እዚህ ጠቁመውን ነው" ሊዎን መለሰ

"አብራሪው ይኸውና እና... ነገር ግን አውሮፕላኗ የለችም፡፡ አሁን የሌላ ሰው ንብረት ሁናለች"

"በጣም ያሳዝናል" አለ ሊዎን በቁጭት

ካሮቴ የተፈለገበትን ምክንያት ከሰማ በኋላ ዶሚኖ ለመጫወት ወደ ስፓኒሹ ዘራፊ ሄደ፡፡ የሊዎን ጓደኛ ፔድሮም ከሻይ ቤቱ ወጣ ስላለ እኔ እና ሊዎን በነፃነት ለማውጋት ጊዜ ሰጠን፡፡

"እሺ ፓፒ"

"አለሁልህ ሊዎን"

"ከተለያየን ቢያንስ አስር አመት ሆነን አይደል?"

"አዎ... እና ኑሮ እንዴት ይዞሀል?"

"አይከፋም... አንተስ ጋር ፓፒ?"

የጠየቀኝ ሊዎን በመሆኑ የውስጤን አውጥቼ ከመናገር አልተቆጠብኩም፡፡

"ሊዎን... እዚህ ኑሮ በጣም ከባድ ነው፡፡ በተለይ ምንም አይነት መተዳደርያ ሳይኖርህ ኑሮን ለማሸነፍ መሞከር ከባድ ነው፡፡ ያላሰብከውን የተራራ ጫፍ እንደመውጣት ነው፡፡ አእምሮዬ ውስጥ ያለውን ነገር እነግርሀለሁ፡፡ ልብ ብለህ አዳምጠኝ... ከእስር ከወጣሁ በኋላ በመጀመርያ የተቀላቀልኳቸው ማህበረሰቦች ከምገልፅልህ በላይ ትሁት እና ለሰው አዛኞች ናቸው፡፡ እኔም ወርቅ ለሰጠኝ አመድ መመለስ ስለሌለብንኝ ማህበረሰቡን የሚጎዳ ድርጊት ላለመፈፀም ቃል ገብቻለሁ፡፡ ነገር ግን እድሜ ልክ ላክመው የማልችለው ቁስል ተሸክሜ የምኖር ሰው ነኝ፡፡ ቁስሌን ለማዳን ደግሞ የግዴታ መፈፀም ያለብኝ እቅድ አለ፡፡ ምን አልባት እኔ ፓሪስ እስክደርስ ድረስ ካልሞቱ በስተቀር በውስጤ ያለውን እውነት መፈፀሜ አይቀሬ ነው፡፡ ታውቃለህ ሊዮን? እዚህ ከተማ መጥቼ ወጣቶችን ስመለከት የእኔ የወጣትነት ዘመን ትውስ ይለኛል፡፡ የእኔ ከእነሱ የሚለየው ግን ቦርቄ፣ ተደስቼ ሳይሆን ያሳለፍኩት ጥቁር ጠባሳ ጥሎብኝ ያለፈውን ታሪክ ተሸክሜ ነው ያለፍኩት፡፡ የሀሰት ፍርድ እንድማቅቅ አድርጎኝ ነው ወጣትነቴን የነጠቀኝ፡፡ ፍርድ ሳይሰጠኝ ያሳለፍኩት ሶስት አመታትም ሆኑ ፍርድ ከተቀበልኩ በኋላ ያሳለፍኩት ጊዜ ለአበደ ውሻ እንኳን የማይነፈገውን ክብር እየተሰጠኝ ነው የኖርኩት፡፡ ሌላው ቀርቶ በዚያች ጨለማ ክፍሌ ውስጥ እግሮቼ እስኪዝሉ ድረስ የቆጠርኳቸው ቁጥሮች... አንድ!!... ሁለት!!... ሶስት!!... ልርሳስ ብል እንዴት አድርጌ ልርሳው? ፍርድ አዛብተው ለእዚህ ስቃይ የዳረጉኝ ሰዎችማ ቅንጣት ይቅርታ አይገባቸውም"

"አዝናለሁ ፓፒ... ለሁሉም ነገር ግን እራስህን ማረጋጋት ይኖርብሀል"

"አሁንማ እራሴን መቆጣጣር ችያለሁ፡፡ እዚህ ሀገር እስከኖርኩ ድረስ ምንም አይነት አደጋ የሚያስከትል ነገር ላለመፈፀም ለእራሴ ቃል ገብቻለሁ፡፡ ቢሆንም ግን ይህ ስሜቴ አንድ ቀን ብዙ ገንዘብ የሚያስገኝልኝ ስራ ካገኘ መቋቋም እንዳያቅተው እሰጋለሁ፡፡ ይህን ያልኩበት ምክንያት በህይወት እስካለው ድረስ የትኛውንም ለብቀላ እቅዴ የሚረዳኝን ገንዘብ የሚያስገኝ ስራ እስካገኘው ድረስ ሀሳቤን ላለመቀየሬ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ እንደማንኛውም መደበኛ ሰው

ስርቼ በማጠራቅመው ገንዘብ የብቀላዬን ፍፃሜ ማየት እንደማልችል አውቀዋለሁ። ለዛ ነው አንድ ቀን ለእዚች ሀገር እና ህዝቦቿ ያለኝ ስሜት እንዳይቀየር የምፈራው"

ትልቁ ሊዎን የማጠራውን በጥሞና ካዳመጠ በኋላ በሚቀጥለው ቀን ከእሱ እና ከጓደኛው ፔድሮ ጋር ምሳ እንደምንበላ ነግሮኝ ተለያየን።

በቀጣዩ ቀን በዛፎች የተከበበ ፀጥ ያለ ሬስቶራንት ውስጥ ሬስቶራንት ውስጥ ተገናኘን፤ ቦታውን ከዛሬ በፊት አይቼው አላውቅም።ውበቱ ግን የተለየ ስሜት ይፈጥራል። ጥሩ ምሳ ከመልካም መስተንግዶ ጋር ከተመገብን በኋላ "ስማኝ ፓፒ" አለኝ ሊዎን

"ምንድ ነው እሱ?"

"ከስዎች እንደተረዳነው ከሆነ ከእዚች ሀገር ወጣ ብሎ አንድ አራጣ አበዳሪ ሱቅ ይገኛል. . .በሱቁ ውስጥ ደግሞ እጅግ ውድ እና የከበሩ ጌጣጌጦች ይገኙበታል. . .የእኛም ሀሳብ እሱን ሰርቀን ወደ ዶላር ከቀየርን በኋላ ወዲያው ሀገር ለቆ መውጣት ነበር. . .ለዛም ነው አውሮፕላን አብራሪውን የፈለግነው... አሁን ግን አውሮፕላኗ ስለሌለች ስለእሱ ማውራቱ ጥቅም የለውም... እና ፓፒ አንተም ፍላጎትህ ከሆነ ከእኛ ጋር ወደ ደቡብ አሜሪካ መሄድ ትችላለህ"

"ፓስፖርት የለኝማ"

"ለፓስፖርቱ አታስብ... አይደል እንዴ ፔድሮ?"

"አዎ እንደወጣልህ ቁጠረው... ዋናው ነገር ገንዘብ ይዘሀል?"

"ምን ያህል?"

"አንድ ሺህ ዶላር"

"አዎ...ይኖረኛል"

"ጥሩ ከእንግዲህ በኋላ ማመንታት የለም" አለ ፔድሮ ፈገግ ብሎ

ከሁለት ሳምንት በኋላ ከደቡብ አሜሪካ ዋና ከተማ የተወሰኑ ኪሎ ሜትሮች ርቄ በመሄድ የተካፈልኩትን ገንዘብ ከአንድ ዛፍ ስር እየደበኩ ነበር። ከተወሰኑ ቀናቶች በፊት የተጠናው ቀላል የዝርፍያ ስልት የተከወነው እንዲህ ነበር።

ከአራጣ አበዳሪው ሱቅ አጠገብ ከረባት መሸጫ ሱቅ አለ። ፔድሮ እና ሲ.ምንም ወደ ከረባት መሸጫው በተደጋጋሚ በመመላለስ የትኛውን የግድግዳ አቅጣጫ ብንበሳ የአራጣ አበዳሪውን ሱቅ ልናገኝ እንደምንችል በሚገባ ጥናት አረጉ። ከዛ በኋላ ቅዳሜ ከሰዓት አስር ሰዓት ላይ ገብተን ከለሊቱ አስራ አንድ ሰዓት ሁሉን ነገር በተሳካ ሁኔታ አጠናቀን ለመውጣት ቻልን።

እንግዲህ ይህ የዝርፍያ ስልት መሳካቱ ነው አሁን ከደቡብ አሜሪካ ዋና ከተማ ራቅ ብዬ የተካፈልኩትን ጌጣ ጌጥ በጣሳ አድርጌ ከዛፉ ስር ለመደበቅ ያስቻለኝ። ተመልሼ ስመጣም ጌጣጌጦቹን ያስቀመጥኩበት ቦታ እንደማይጠፋኝ በጣም እርግጠኛ ነኝ፤ ምክንያቱም ጫካው የሚጀምረው ከድልድዩ ቀጥሎ ሲሆን በጣሳ ውስጥ ያለው የእኔ ሀብት ደግሞ የመጀመርያው ትልቅ ዛፍ ስር ነው የተቀበረው።

በዛን ቀን ምሽት ሶስታችንም አንድ ዝንጥ ያለ ሬስቶራንት ውስጥ ተገናኘን። ሁላችንም በተለያያ አቅጣጫ ስለሆነ የመጣነው ሬስቶራንት ውስጥ ስንገናኝ ልክ እዛው እንደተገናኘ ሰው ነው ያስመሰልነው። ይህን ያደረግነው የሰዎችን ትኩረት ለመቀነስ ያህል ነው። ሶስታችንም የዘረፍነው ሀብት በእጃችን ላይ አይገኝም፤ ሲምን አንዱ ጓደኛው ጋር ሲያስቀምጠው ፔድሮ ደግሞ ልክ እንደ እኔ ጫካ ውስጥ ደብቆት ነበር።

"ሁላችንም በየራሳችን መንገድ ሀብታችንን መደበቃችን ጥቅሙ የጋራ ነው። ምን አልባት አሳማዎቹ ከሶስት አናዳችንን ሊይዙን ቢችሉ ምን ሊያደርጉን እንደሚችሉ የታወቀ ነው። በእዚህ መሀል ከእኛ ውስጥ አንድ ምስኪን የሆነ ሰው የት እንደደበቀ ቢናገር የራሱን መሞቻ ጉድጓድ ነው የሚቆፍረው። የቀረነው ሀብታችን ምኑ ጋር እንዳለ ራሳችን ብቻ ስለሆነ የምናውቀው ወኔያችን ያድነናል" አለ ሲምን አስከትሎም "እና ፓፒ በክፍፍሉ ላይ ምን ትላለህ?" አለኝ

"በአግባቡ ስታከፋፍል ተመልክቻለሁ… ስለዚህ ምንም ቅራኔ የለኝም"

ሶስታችንም በሰራነው ስራ ስለረካን የቀረበልንን መጠጥ በደስታ ማጣጣት ጀመርን፤ በእዚህ መሀል ድንገት "እጅ ወደ ላይ!!" የሚል ድምፅ ሰማን

"እንዴ ምንድነው የተፈጠረው?ምን አጠፋን?" አለ ሲምን ለማልቀስ እየዳዳው

ሁኔታውን እንኳን በአግባቡ ሳያስረዱን ፖሊሶች እጃችንን በካቴና አስረው እያዳፉ ወደ ዋናው ፖሊስ ጣብያ ወሰዱን። የእዚህ ሀገር ፖሊሶች ትዕግስት የሚባል ነገር አልፈጠረባቸውም። ይዘውን ሲሄዱ እየተመገብን የነበረውን

ምግብ ለማስጨረስ እንኳን ጊዜም አልሰጡንም፤ ለሊቱን በሙሉ መጠይቅ ሲያደርጉልን አደሩ፡፡ የመጀመርያው ጥያቄያቸው "እንዴት ነው ከረባት ይመቻችኋል?" የሚል ነው. . . እኛም የምንሰጣቸው መልስ "ገደል ግቡ" አይነት ይዘት ያለው መልስ ነው፡፡

እስከ ጠዋቱ አምስት ሰዓት ድረስ በጥያቄያቸው ቢያደርቁንም ከእኛ አንደበት ግን እዚህ ግባ የሚያስብል ፍንጭ ሊያገኙ አልቻሉም፡፡ በእዚህም የተናደደው አንድ ፖሊስ የምርመራ ስልቱን መቀየር እንዳለበት የገባነው ይመስል "እሺ እንግዲህ አሁን እንዳየሁት ከሆነ ሙቀቱ በጣም ከፍተኛ በመሆኑ ምክንያት ሰውነታችሁን ላብ አጥምቆታል፡፡ ስለዚህ ለእናንተ ቀዝቃዛ ነገር እንሰጣችኋለን" ብሎ የስላቅ ንግግር ተናገረ፡፡ ከዛም ሦስታችንም እንድንቆም ካደረጉ በኋላ እየገፈታተሩን ትንሽዬ ዋገን መኪና ውስጥ እንድንገባ አደረጉን፡፡ ለግማሽ ሰዓት ያህል ከተጓዝን በኋላ አንድ ትልቅ ህንፃ ስር ስትደርስ መኪናዋ ቆመች፡፡ ፖሊሶቹ ከመኪናዋ እንድንወርድ አድርገው ወደ ህንፃው ውስጥ ይዘውን ገቡ፡፡ እኛ ወደ ህንፃው በምንገባበት ሰዓት በህንፃው ውስጥ የነበሩት ሰራተኞች ደግሞ እየወጡ ነበር፡፡ በፖሊሶቹ መሪነት እየተረዳን ወደ አንዱ ክፍል ገባን፡፡ በክፍሉ ውስጥ ደግሞ ትንንሽዬ የብረት በር ያላቸው ሌሎች ንዑስ ክፍሎች ነበሩት፡፡ እያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ሰዓት እና ቴርሞ ሜትር ተገጥሟል፤ ክፍሉን እና ቴርሞ ሜትሩን እንዳየው ማቀዝቀዣ ክፍል መሆኑን ተረዳሁ፡፡ የፖሊሶቹ አለቃ ወደ እኛ ዞሮ " እንግዲህ አሁም አንድ የመጨረሻ እድል እሰጣችኋለሁ... ከመወሰናችሁ በፊት በደንብ አስቡበት... እነዚህ የምታይዋቸው ክፍሎች ስጋ ማከማቻ ናቸው! መቼም ምን እያወራሁ እንደሆነ ሳይገባችሁ አይቀርም፡፡ ስለዚህ ለመጨረሻ ጊዜ እጠይቃችኋለሁ... የዘረፋችሁት ጌጣ ጌጥ የት ነው ያለው?" ብሎ አንቧረቀብን

"አንተ ስላምታወራው ከረባት እና ጌጣ ጌጥ የምናውቀው ነገር የለም" አለ ሊዎን ቆፍጠን ብሎ

"እሺ ጠበቃው መጀመርያ አንተ ትገባለህ...በሩን ክፈተው!" የታዘዘው ፖሊስ ከክፍሎቹ አንዱን ሲከፍተው ጭስ የሚመስል ነገር ወጣ...ሌሎች ሁለት ፖሊሶች የሊዎንን ጫማ እና ካልሲ ካስወለቁት በኋላ እዛ ማቀዝእቀዣ ውስጥ እየገፈታት አስገቡት

"ኧረ ቶሎ በል እንጂ አለቃ... ያለበለዚያማ እኛም በበረዶ ቅዝቃዜ መሞታችን ነው" አለ አንዱ ፖሊስ እያለገጠ

"እሺ አሁን ደግሞ ቺላዊው ታወራለህ?" አለው ፔድሮን

"ምንም የማወራው ነገር የለኝም"

"ሌላኛውን በር ክፈተው!!"

ፔድሮንም እየገፈታተሩ ወሰደው ወደ ተዘጋጀለት ማቀዝቀገዣ ክፍል ከተቱት

"እሺ... አንተስ?" አለኝ የፖሊሶች አዛዥ

"እኔ ምን?"

"ይኸውልህ አንተ ከእነሱ አንፃር በእድሜ ልጅ ትመስላለህ:: እነዚያን ቴርሞ ሜትሮች አየሀቸው? ከዜሮ በታች አርባ ሴንቲ ግሬድ ላይ ናቸው:: አንተም የማታወራ ከሆነ እነዛ ክፍሎች ውስጥ መግባትህ የማይቀር ነው:: እዛ ውስጥ ገባህ ማለት በትንሽ ደቂቃ የደረቀ ቋንጣ ትሆናለህ ማለት ነው:: እድል ቀንቶህ በህይወት ወጥተህ ወደሆስፒታል የመሄድ እድል ቢያጋጥምህ እንኳን በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ በሳንባ በሽታ ምክንያት ሟች ነህ... ስለዚህ አንድ እድል ነው የምሰጥህ... የአራጣ አበዳሪውን ጌጣ ጌጦች በከረባት መሽጫው ሱቅ በኩል ገብታችሁ ሰርቃችኋል?ወይንስ አልሰረቃችሁም?የምፈልገው መልስ አዎ ወይም  አይ የሚል መልስ  ብቻ ነው"

"እኔ ከእነዛ ሰዎች ጋር የሰራሁት ምንም ስራ የለም... ሲጀምር የማውቀው አንደኛውን ብቻ ነው:: እሱም ከረጅም አመታት በፊት ነው:: እንደ አጋጣሚ ሆኖ ሬስቶራንት ውስጥ ስገባ ነው ያገኘኋቸው:: ካላመንከኝ አስተናጋጆቹን መጠየቅ ትችላለህ:: እንደዚህ አይነት ስራ ሊሰሩ ስለማሰባቸውም ሆነ ስለመስራታቸው ምንም አይነት መረጃ የለኝም"

"ጥሩ እንግዲህ... አንተም እውነታውን ማውጣት ስላልፈለክ ሞትን ምርጫህ አድርገሀል... በእዚህ እድሜ መሞትህ ቢያሳዝነኝም የራስህ ፍላጎት ስለሆነ ምንም ማድረግ አልችልም... እሱንም አስገቡት!!"

በሩ ተከፈተ!! እኔም ቢያስመልጠኝ ብዬ ያቀረብኩት ምክንያት ሊያስጥለኝ ስላልቻለ እየተገፈተርኩ ወደ ጨለማው ማቀዝቀዣ ክፍል ተወረወርኩ፤ ሳላስበውም ተንደርድሬ ወለሉ ላይ ተደፋሁ:: ወለሉ ሙሉ በረዶ ነው:: ሰውነቴ ከበረዶ ጋር በተገናኘበት ቅጽበት ነበር አጥንቴ ድረስ የሚጠዘጥዝ ቅዝቃዜ መሰማት የጀመረኝ:: እንደምንም ብዬ ከወደኩበት በመነሳት በእግሬ ለመቆም ሞከርኩ፤ ክፍሉ ከመጠን በላይ ይቀዘቅዛል:: በእጆቼ ከአንገቴ ጀምሮ ፊቴን በመፈተግ ሙቀት ለመፍጠር ሞከርኩ፣ ከላይ የለበስኩትን ቲሸርት ከእጆቼ ጋር በማፋተግ ቅዝቃዜውን ለመቋቋም ጣርኩ፤ ግን ከንቱ ልፋት ከመሆን

በስተቀር ምንም ሊያመጣልኝ አልቻለም፡፡ በዛ ላይ ጫማ እና ካልሲዬ ስለተወሰደብኝ እግሮቼ ወደ በረዶነት ሲቀየሩ ይሰማኛል፤ ቅዝቃዜው ወንድነቴን ቢፈታተነኝም እጅ ላለመስጠት ግን ቆርጬ ተነስቻለሁ፡፡

"ፓፒ እዚህ ክፍል ውስጥ ለአስራ አምስት ደቂቃ ብትቆይ ነው፡፡ ከዛ በኋላ በጥሩ ሁኔታ የደረቀ ስጋ ሆነህ ነው የምትገኘው… ይህ ደግሞ ፈፅሞ አይሆንም!! ያን ያህል በእኛ ላይ ርህራሄ ያጣሉ ብዬ አላስብም! ከእነ ነፋሳችን ያደርቁናል የሚል እምነት የለኝም!! ታገስ ፓፒ… ከደቂቃዎች በኋላ መተው ይከፍቱልሀል" እያልኩ ደጋግሜ ለእራሴ ነገርኩት፡፡ አሁን ደግሞ እጆቼ ሙሉ ለሙሉ መስራት አቁመዋል፤ እግሮቼን ከወለሉ ላይ ለማንቀሳቀስ ብሞክርም ከበረዶ ጋር ተጣብቀው ማንሳት አቃተኝ፤ ብዙም ሳልቆይ እራሴን ወደ መሳቱ ደረጃ ደረስኩ፡፡ በሰመመን ውስጥ የአባቴን ገፅታ ተመለከትኩ፡፡ ወዲያው የአባቴ ገፅታ የመሰለኝ ፊት በሌሎች ሶስት ፖሊሶች ፊት ተቀየረብኝ፡፡ ከእዛ እራሴን ሙሉ ለሙሉ ሳትኩ

አይኖቼን እንደምንም ብዬ ስገልጥ እራሴን ጠረጴዛ ላይ ተኝቼ አገኘሁ፤ አጠገቤ አንድ ሰው ቆሟል "ምንድ ነው የተፈጠረው? የት ነው ያለሁት?" ብዬ እራሴን መጠየቅ ጀመርኩ፡፡ አፌ በበረዶ ምክንያት ስለተያያዘ ማውራት አልቻልኩም፡፡ አእምሮዬ የት እንዳለሁ እና ምን እንደተፈጠረ ማሰቡን ቀጥሏል፡፡ በተኛሁበት ጠረጴዛ መሳይ አልጋ ላይ የሆነ ትልቅ እና ጠንካራ እጅ በቅባት እያሸኝ ነበር፤ ከተወሰነ ቆይታ በኋላ በሰውነቴ ውስጥ ሙቀት ሲፈጠር ተሰማኝ፡፡ ቀስ በቀስ አዕምሮዬ የተፈጠረውን ሁሉ ማስታወስ ጀመረ፡፡

የፖሊሶቹ አዛዥ እኔ ከተኛሁበት በ ሁለት ሜትር ራቅ ብሎ ሁኔታውን ሲከታተል ተመለከትኩት፡፡ በተደጋጋሚ አፌን ለመክፈት እየሞከሩ የሆነ ሞቃት ፈሳሽ ይከታሉ፤ የሆነ ሰዓት አፌን ከፍተው ከመጠን በላይ ስለከተቱብኝ በሀይል አስዬ ተፋሁት፡፡

"ይኸው ተርፏል" አለ የሚያሸኝ ሰውዬ

ለሁለት ሰዓት ያህል ያለማቋረጥ በቅባት ሲያሹኝ ነበር፡፡ አሁን ላይ በርግጥ ለማውራት አቅሙን አግኝቻለሁ፤ ቢሆንም ግን ከማውራት ዝም ማለቱ የተሻለ ስለመሰለኝ ምንም ቃል አለማውጣቱን መረጥኩ፡፡ አስተኛኘቴን ለማስተካከል ወደ ቀኝ በኩል ስዞር ከጎኔ ካለው ሌላ ጠረጴዛ ላይ ተኝቶ ልክ እንደኔው በቅባት ሲታሽ አየሁ፡፡ "ማነው ? ሊዎን? ወይንስ ፔድሮ?" መለየት አልቻልኩም… ሌላ የሚታሽ ካለ ብዬ ዙርያውን ቃኘው፤ ነገር ግን ሁለታችን ብቻ ነበር የተኛነው፡፡ "ታድያ ሶስተኛው የት አለ?" ያልተመለሰለኝ ጥያቄ ነው፡፡

በሚያሸኝ ሰው በመታገዝ እንደምንም ብዬ ጠረጴዛዬ ላይ ለመቀመጥ ቻልኩ፤ ዮኔ አጠገቤ የተኛውን ሰው አይቼ ለመለየት እድሉን አገኘሁ፤ ፔድሮ ነበር። ልብሶቻችንን አለባበሰውን ፔድሮም እንዲቀመጥ ካደረጉት በኋላ ፋታ እንኳን ሳይሰጠን የፖሊስ አዛዡ በጥያቄ ማድረቁን ተያያዘው

"ቺላዊ ማውራት ትችላለህ?"

"አዎ" አለ ፔድሮ

"ጌጣ ጌጦቹ የት አሉ?"

"አላውቅም"

"አንተስ?" አለ ወደ እኔ ዞሮ

"ከእነሱ ጋር አልነበሩኩም" አልኩት የሰጠሁትን ቃል ማጠፍ ስለሌለብኝ

"እሺ"አለ አዛዡ

ድካም ስለተሰማኝ ጠረቤዛው ላይ ጋደም ለማለት ሞከርኩ፤ በእግሮቼ ሙቅ ደም ሲርመሰመስ ይሰማኝ ጀመር። ምንም እንኳን ደስ የሚል ንዝረት እግሬን ቢሰማውም ህመም ግን ነበረው። ከሁልም በላይ ግን የሰውነት ክፍሎቼ መስራታቸውን ማረጋገጤ የበለጠ ደስ ብሎኛል።

የማስቃየቱ ዘመቻ ለአንድ ቀን ብቻ ነበር የመሰለኝ፤ ግን ተሳስቻለሁ። በሚቀጥለው ቀን እኔ እና ፔድሮ ጎን ለጎን እንድንቆም ከተደረገ በኋላ የፖሊስ አዛዡ "ልብሶቻቸውን አውልቁላቸው" ብሎ ትእዛዝ ሰጠ። ከላይ እስከ ታች ድረስ የለበስነውን አስወልቀው እራቁታችንን እዛ ብርድ ላይ ገተሩን።

"ወደ ማቀዝቀዣው ከመግባታችሁ በፊት አንድ ልብ ብላችሁ መመልከት ያለባችሁ ነገር አለ" የፖሊስ አዛዡ በምልክት ለፖሊሶች የሆነ ትእዛዝ ሰጠ፤ ከጠረቤዛው ስር የሆነ ግዑዝ አካል አውጥተው እኛ እንድናየው ፊት ለፊታችን ያለው ጠረቤዛ ላይ አስቀመጡት፤ የሰው ሬሳ ነው!! በከፊል በጨርቅ የተሸፈነውን አስከሬን አስፈሪ ገፅታ ነበረው፤ ትልቁ ሊዎን ነበር!! ከእነስትንፋሱ አስገብተው አድርቀው በድን አድርገውታል!! አይኖቹ እንደፈጠጡ ቀርተዋል።

"በደንብ ተመለከቱት...ጓደኞችሁ አልናገርም በማለቱ እንደ ቋንጣ ለማድረቅ ተገደናል። እናንተም ካልተናገራችሁ እጣ ፈንታችሁ ይኸው ነው። ለመናገር

አፋችሁን የማትከፍቱ ከሆነ እመኑኝ ከመቼውም በላይ እጨክንባችኋለሁ... የዘረፋችሁት የአራጣ ማበደርያው ሱቅ የሚመራው በከተማዋ አስተዳደር ነው:: በመሆኑም አንዳንድ ሰዎች በፖሊሶች ስብጥር ሆን ብለን ያዘረፍነው አርገው ነው የሚያስቡት... ይህ ደግሞ የእኛን ስም እና ስራ የሚያጠላሽ ወሬ ነው. . .ስለዚህ ካደረጋችሁበት ቦታ የሰረቃችሁትን ጌጣ ጌጦች አውጡ አለበለዚያ በግማሽ ሰዓት ውስጥ ከፊታችሁ የምታዩትን ጓደኛችሁን ትቀላቀላላችሁ"

ይህን ስሰማ የደበኩበትን ቦታ ለመናገር ዳድቶኝ ነበር፤ ነገር ግን እኔ የግሌን ባወጣ ሌሎቹ የደበቁበትን ቦታ ስለማላውቅ ማንም ሊያምነኝ አለመቻሉን ሳስብ ምንም ከመናገር ተቆጠብኩ:: በእዚህ ጭንቅ ሰዓት "ምን እያደረጋችሁ ነው?" የሚለውን የፔድሮን ድምፅ ሰማሁ "ልታስፈራሩን እንደሆነ ገብቶናል... ይህን ምንም የማያውቅ ጓደኛችንን ለማድረቅ አስባባችሁ አልነበረም! በስህተት እሱ ስለቀደማችሁ እንጂ አሁን ደግሞ ሁለተኛ ስህተት መስራት እንደማትፈልጉ እርግጠኛ ነን... ምን አልባት የአንድ ሰው ህይወት መጥፋት ላያስቀጣችሁ ይችላል... የሶስት ሰው ህይወት ስትቀጥፉ ግን ነገሩ ወደ ሌላ ይቀየርባችኋል... ለዛ ደግሞ ምንም አይነት መልስ አይኖራችሁም" ፔድሮ ያሳየው ልበ ደንዳናነት ሳላደንቅ አላፍኩም፤ የፖሊስ አዛዡ ፔድሮን ትኩር ብሎ ከተመለከተው በኋላ

"በርግጥ ዘራፊ ስለመሆንህ ጥርጥር የለኝም... ቢሆን ግን ድፍረትህን ሳላደንቅ አላልፍም" ቀጥሎም ወደ አንዱ ተራ ፖሊስ ዞረ እና

"ልብሶቻቸውን ይልበሱ. . .ከዛ ወደ ዋናው ፍርድ ቤት ይዛቸዋቸው ሂዱ... ዳኛው እንዳደረገ ያድርጋቸው:: እዚህ ገዜ ከማጥፋት ውጪ የምንፈጥረው ነገር የለም" ብሎ ክፍሉን ለቆ ወጣ

ከአንድ ወር በኋላ እኔን ነፃ ለቀቁኝ፤ የከረባት መሸጫው ሱቅ ባለቤት ሊዎንን እና ፔድሮን ብቻ ማየቱን ለፍርድ ቤቱ ስላስረዳልኝ፣ እንዲሁም የሬስቶራንቱ አስተናጋጅ እነ ፔድሮን ሳገኛቸው በሬስቶራንት ውስጥ ተቀምጬ በድንገት መተው እንደሆነ የምስክርነት ቃሉን ስለሰጠ በነፃ ለመውጣት ችያለሁ:: የፖሊስ አዛዡ በአምስት ቀናት ውስጥ ከተማዋን ለቅቄ እንድወጣ አስጠነቀቀኝ:: ሲመስለኝ ስለ ሊዎን ሞት ምንም አይነት መረጃ እንዲወጣ አልፈለጉም::

የዘረፍነውን ሀብት የተካፈልን እለት ፔድሮ አንድ ሌላ ሰው ይዞ መቶ ነበር፤ ያ ሰው የአራጣ አበዳሪው ሱቅ ውስ የሚሰራ ተቆጣጣሪ ነው:: ለዝርፍያው መሳካት ሲባል አግባብተው ነው ወደ ስራው ያስገቡት:: እኛም የሰረቅነውን

ተከፋፍለን የምንፈልግበት ቦታ ከደበቅን በኋላ ፖሊሶች ይህን አራጣ አበዳሪ ሱቅ ውስጥ የሚሰራ ተቀጣሪ በገንዘብ እያባበሉ ነገሩን ሁሉ አፍረጥርጦ እንዲነግራቸው አደረጉ፡፡ ከዛም ወደ እኛ ሲመጡ ሊዎንን እና ፔድሮን ለመለየት አላዳገታቸው፡፡

ከእስር በተፈታሁ ማግስት በ አምስት መቶ ዶላር የአውሮፕላን ትኬት ገዝቼ ወደ ካራካስ ተመለስኩ፡፡ የዘረፋው ወሬ እስኪረሳ ድረስ በፍፁም የደበኩት ንብረት አካባቢ መሆን እንደሌለብኝ ቀደም ብዬ ተረድቻለሁ፡፡ ስለ ተፈጠረው ነገር ምን ተብሎ እንደተዘገበ ለማወቅ ስለፈለኩ ወደ አውሮፕላን ጣብያው ከመግባቴ በፊት ጋዜጣ ገዝቼ ነበር፡፡ የአራጣ አበዳሪው ሱቅ ቢያንስ ከሁለት መቶ ሺህ ዶላር በላይ የሚገመት ንብረት እንደጠፋ ተዘግቧል፤ ነገሩ ቢጋነንም ቢያንስ ግን ከ መቶ ሺህ ብር በላይ የሚገመት ንብረት መዝረፋችንን አልጠራጠርም፡፡

ከዘረፍነው ጌጣ ጌጥ የደረሰኝ ድርሻ ቢያንስ እስከ ሰላሳ ሺህ ዶላር ያወጣልኛል፡፡ ምን አልባት በኑሮ ውጣ ውረድ ውስጥ ካልጨረስኩት በስተቀር ይህ ገንዘብ ላስብኩት የብቀላ እቅዴ ከበቂ በላይ ነው፡፡

ከድሮ ጓደኛዬ ፔድሮ ሞት በስተቀር ይህ ስራ ለእኔ እጅግ ጠቃሚ ነበር፤ ስለ ፔድሮ እንደተረዳሁት ከሆነ የሚያምነው አንድ ጓደኛው ንብረቱን እንዲያወጣለት በማድረግ ጠበቃ ማቆም ነው የሚጠበቅበት፡፡ ምንም አይነት ምስክር በቦታው ስለሌለ በነፃ የመለቀቁ ጉዳይ የማይቀየር ነው፡፡ ሆነም ቀረ ንብረቱን ከተካፈልን በኋላ በሶስታችን መሀል የተፈፀመው "የግል ንብረትን በሚስጥር መደበቅ" ውል የአንዳችን መያዝ ለሌሎቻችን ጦስ እናዳይሆን ትልቅ አስተዋፆ እንዳለው ሊዎን ከነገረን ቀን በላይ ዛሬ ግልፅ ሆኖ ታየኝ፤ ስለዚህ ሁሉም እንደታሰበው ተከውኗል፡፡ እኔም ሆንኩ ፔድሮ ልንኮነን አይገባም፡፡ በዚህ ዝርፍያ እድል ለእኔ ስትቀናልኝ፣ ለሊዎን ደግሞ መጥፎያው ሆነችበት፣ ፔድሮንም መሀል ሰፈሪ በማድረግ አስቀረችው፡፡ እንዲህ ናት ፍርቱና!!

ሌላው እውነት ከእዚህ ጉድ ያወጣኝ አምላክ ከሆነ በእርግጥም የሚደነቅ አባት ነው!! ሆኖም ግን ሌት ተቀን በማስበው የብቀላ እቅዴ ውስጥ የፈጣሪ እጅ እንደሌለበት እርግጠኛ ነኝ፡፡ እርሱ የሰራውን ፍጡር እኔ እንድቀጣ እንደማይፈልግ አውቃለሁ!! በአንድ ወቅት ኤልድራዶን ከመልቀቄ በፊት የካቶሊኮች አባት የሆነውን ፈጣሪ ለማመስገን ፀሎት ላይ ሆኜ በውስጤ "ክብርህን ለመመስከር ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ?" ብዬ ጠየኩት... እሱም "የብቀላ እቅድህን ከውስጥህ አውጥተህ ጣል" ያለኝ መሰለኝ... እኔም መልሼ "አይሆንም!! ከፈለክ ሌላ ነገር ጠይቀኝ ብቀላዬን ግን በህይወት እንድኖር እስከፈቀድክልኝ ጊዜ ድረስ አልተወውም!" በማለት ከአምላኬ ጋር

መውጣት ገጠምኩ፡፡ ስለዚህ በአሁን ሰዓት እየተንከባከበኝ ያለው ፈጣሪዬ ሳይሆን እድሌ ነው፡፡ ሰይጣናዊ ዕድል!! እንጂ ፈጣሪ በእንደዚህ አይነት ልክስክስ ስራ ውስጥ እጁን አያስገባም፡፡ ያም ሆነ ይህ የበቀል ጥማቴን ሳልወጣ አልቀርም!! አሁን ከእኔ የሚጠበቀው ካራካስ ስደርስ ያገኘሁትን ስራ እየሰራው ለተወሰኑ ወራቶች ነገሩን ማብረድ፤ ከዛ ሁሉም ነገር ከተረጋጋ በኋላ ተመልሼ ከድልደዩ አጠገብ ባለችው ዛፍ ስር የተቀበረውን ሀብቴን አውጥቶ መሸጥ…አለቀ!!

# ምዕራፍ ስምንት

## ቦምቡ

በካራካስ ጎዳናዎች ላይ እንደገና ለመራመድ በመቻሌ እጅግ ደስ ብሎኛል። ነፃነቴን ካሳወጅኩ ሃያ ያህል ወራቶች አላፈዋል።ሆኖም ግን የዚች ሀገር አባል አላሆንኩም። በዚህ ሰአት ማድረግ ያለብኝ ነገር ቢኖር ስራ መፈለግ ብቻ ነው። ስራ እንዳላገኝ ካደረጉኝ ምክንያቶች ዋነኛው መንስኤ የስፓኒሽኛ ቋንቋ መናገር አለመቻሌ ነው ስለዚህ ይንን ችግር ለመቅረፍ በማሰብ ስፓኒሽኛ ለመናገር የሚረዳኝን መፅሃፍ ገዝቼ ለማንበብ ሞከርኩ... ነገር ግን ለማንበብ በሞክረኩ ቁጥር ከእነጭራሹ የአነባብ ቅላፄው ስለጠፋብኝ የበለጠ ንዴቴን አመጣው። ምን አልባት ስራ ሊያገኝልኝ የሚችል ሰው አገኝ ይሆናል በሚል መንገድ መንገዱን ማየት ጀመርኩ። ነገር ግን አንድም የማውቀው ሰው ለማየት አልቻልኩም ነበር።

ብዙ ፈረንሳዊያን እና ሌሎች የአውሮፓ ከተማ ዜጎች በጦርነቱ ምክንያት ወደ እዚህ መጉረፍ ከጀመሩ ሰንበትበት ብለዋል። አንዳንዶቹ በስሩት ወንጀል ምክንያት ከፍትህ ለማምለጥ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ሰላም እና ጸጥታ ፍለጋ ነው ስደትን መርጠው እዚህ የተገኙት።

ከፈረንሳይ የሚመጡ ዜጎች ላይ እኔ ልጅ እያለው የማውቀውን የአንድ ፈረንሳዊ ባህሪ አላይባቸውም ነበር። ለነገሩ ምን ያድርጉ በጦርነቱ ምክንያት አእምሮዋቸው ውስጥ እንዳይወጣ ሆኖ የተቀረፀ መጥፎ ምስል ቀርቷል። አብዛኞዎቹ ወደእዚህ የሚመጡት ፈረንሳውያን አስተሳሰባቸው በእጅጉ ተበክሏል። ፈረንሳውያን ላይ የማውቀው ወኔ እና ድፍረት አሁን ጭራሹኑ ጠፍቷል። እርግጥ ነው ጦርነት አስከፊ ነው ምን አልባት ያለፈውን መርሳት ላይጠበቅብን ይችላል። ስላለፈው ነገር እያነሱ ማወራት ግን ተገቢ መስሎ አይታየኝም! በእዚህ ሰአት ጦርነቱ ቢያበቃም አሁንም ግን የናዚ ደጋፊዎች

እንደማይጠፉ እርግጠኛ ነኝ ስለ አይሁዶች ባሰብኩ ቁጥር አዕምሮዬ ውስጥ የሚመጣው መልስ በአንደ ሀገር ምክንያታዊ ባልሆነ ጥላቻ ከጫዋታ ውጪ የማድረግ ዘመቻ የተከናወነባቸው ያህል ይሰማኛል፡፡

እዚህ ግን ቬንዜዌላ ነው በሀይማኖትም ሆነ በዘር የሚነሳ ጥል ቀርቶ ክርክር እንኳን የማይታይባት ሀገር ነች፡፡ እናም እዚህ ላይ የእኔ ፍራቻ ከአውሮፓ ተሰደው የሚመጡት ዜጎች እንደልማዳቸው ስለብቀላ፤ ስለ ዘር፤ ስለሀይማኖት፣ ስለጥላቻ የመስበክ አባዜአቸውን ይዘው እዳይመጡ ነው፡፡ እንደዚህ ካደረጉ ከረጅም ዘመናት ከደግነት በስተቀር ምንም የማያውቀውን ማህበረሰብ እንደ መበረዝ ይቆጠራል… በርግጥ ይህ የበቀልና ጥላቻ ቫይረስ በእነዚህ ምንም በማያውቁ ማህበረሰቦች ውስጥ እንዳይዛመት ሁሌም እፈራለሁ፡፡

ጊዜው 1947 ነው… በዚህ አመት አንድ ቀደም ባለ ህይወቱ ዘራፊ የነበረ 'ፔሪ ሬኒ ዲሎይፍሬ' የሚባል ሰው የተዋወቅሁበት ወቅት ነው ዲሎይፍሬ ፊጣን፣ ስሜታዊ እና ግልፅ የሆነ ሰው ሲሆን የቬንዜዌላ የቀድሞ ፕሬዝዳንት የነበረው ጀነራል መዲና አንጋሪታን መውደድ ብቻ ሳይሆን ያመልከዋል ማለት ይቻላል… ሁሌም ስለሱ ባነሳ ቁጥር አውርቶ አይጠግብም ጀነራል መዲና እንደሚታወቀው በ1945 በሃገሪቷ የጦር ሰራዊት አድማ ተነስቶ ከስልጣን የወረደ ፕሬዝዳንት ነው… ለዲሎይፍሬ ግን የእሱ ከስልጣን መነሳት አይዋጥለትም… በእሱ አስተሳሰብ ጀነራል መዲና ከስልጣኑ የወረደው መጥፎ ድርጊት ስለፈፀመ ሳይሆን ይልቁኑ ጀነራሉ ቅን አሳቢ በመሆኑ እና የሀገሪቱ ንብረት ልክ እንደራሱ ንብረት በአግባቡ የሚጠብቅ መሪ በመሆኑ ይህንን አመለካከቱን የማይቀበሉት ሙሰኞች ለራሳቸው ጥቅም ሲባል በሸፍጥ ከስልጣን እንዲለቅ እንዳደረጉት ነው የሚያምነው፡፡

ከቆይታም በኋላ ዲሎይፍሬ አንድ 'አርማልዶ' ተብሎ ከሚጠራ ባለሀብት ጋር አስተዋወቀኝ አርማልዶ ሀብታም ከሚባሉ ቬንዙዌላውያን ቤተሰብ የወጣ ሲሆን ደግ፣ ብልህ እና የተማረ ለመሆኑ ከአነጋገሩ ያስታውቃል፡፡ 'ክሊሜንቴ' የሚባል በፀባይም በምግባርም ከሱ ተቃራኒ የሆነ ወንድምም ነበረው፡፡ ዲሎይፍሬ ከባለሀብቱ ጋር ሲያስተዋውቀኝ ግልፅ የሆነውን ማንነቴን በመግለጽ ነበር ፡፡

"ተዋወቀው ፓፒለን ይባላል ከእስር ያመለጠ ሰው ነው"

አርማንዶም በየዋህነት አስተያየት ከተመለከተኝና ሰላምታ ካቀረበልኝ በኋላ "ገንዘብ ያስፈለግሃል?" ብሎ ጠየቀኝ"

"ገንዘብ አልፈለግም ጌታዬ . . . እኔ የምፈልገው ስራ ነው" አልኩት

"መልካም... እንደዛ ከሆነ ነገ ዘጠኝ ሰአት ላይ እንገናኝ"

በነጋታው ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን ከ ዲሎይፍሬ ጋር ተያይዘን አርማንዶ ወደሚሰራበት ጋራዥ አመራን፡፡ የጋራዡ ስም 'ፍራንክ ቬንዜዌላን' ይባላል፡፡ እዛም ከእርሱ ጋር የሚሰሩ ሰስት ወጣት ወንዶችን አስተዋወቀኝ... ሁለቱ ወንዶች ባለትዳሮች ናቸው፡፡ አንደኛው 'ሲሞኔ' የምትባል የሀያ አምስት ዓመት ፈረንሳዊት ያገባ ሲሆን ሌላኛውም እንዲሁ 'ዴዴ' ከተባለች የሀያ ዐመት ልጅ ጋር ነበር የተጋባው. . .ዴዴ የመጣችው ከምዕራቡ የፈረንሳይ ክፍል ሲሆን አረንጓዴ እና የሚያመሩ አይኖች አሏት አንድ 'ክሪ' የሚባል ልጅም ወልዳለች፡፡

ቤተሰቡ በጣም ደስ የሚል ስብዕና የተላበሰ ቤተሰብ ነው፡፡ለረጅም ጊዜ እንደሚተዋወቅ ሰው ነበር አቀባበል ያደረጉልኝ፡፡ ከጋራዡ በጥግ በኩል ባለችው አንስተኛ ክፍል ውስጥ የራሴን መኝታ አዘጋጁልኝ፡፡ ይህ ቤተሰብ እንግዲህ ከአስራ ሰባት አመት በኋላ የተዋወቅሁት እውነተኛ ቤተሰብ ነው ማለት እችላለው፡፡ ምናልባትም እዚህ ያሉት ሁለት ፈረንሳዊያን እንስቶች ይሄን ስሜት ሳይፈጥሩብኝ አይቀሩም፡፡

ከቆይታም በኋላ ቤተሰቡ ስለመካኒክነት ሙያ ብዙም የሚያውቁት ነገር አለመኖሩን ተረዳሁ የባሰ ብሎ በጋራዥ ውስጥ የብረት እና የእንጨት ቅርፅ ማውቻ አየሁ ግራ የሚያጋባ ነገር ነው! የማሽኑ እዚህ መገኘት ጥቅሙ ሊገባኝ አልቻለም፡፡ ስለሁኔታው ስጠይቃቸውም ለአንዳንድ መኪኖች ውስጣዊ እቃ ለመስራት የሚያገለግል ነው የሚል መልስ ሰጡኝ፡፡ ምላሹ ባይዋጥልኝም በምን አገባኝነት ስሜት ነገሩን ችላ ብዬ ማለፍን መርጫለሁ፡፡ከትንሽ ጊዜ በኋላ ግን ማሽኑ በምብ ውስጥ የሚገኝን የጋዝ ብልቃጥ ለመቀየር የሚያገለግል መሆኑን ተረዳሁ፡፡

'ፍራንክ ቬንዙዌላ' የተሰኘው የአርማንዶ ጋራዥ አንዳንድ መኪኖች ሲበላሹ ከመጠገን ጎን ለጎን በሚስጥር በምብ እንደሚያመርት ከቀናት በኃላ አወቅሁ።

"ምን?" አልኩ ደንግጬ ቀጠልኩና "ለማን ነው በምቡን የምታመርቱት ማንንስ ለማጥቃት ታስቦ ነው?" ይህን ጥያቄ ስጠይቅ ምሽት ስለነበር ከፊት ለፊቴ ከተቀመጡት ሦስቱ የጋራጁ ሰራተኞች ውጪ ሌላ ማንም አልነበረም ነበር።

"እሱ እኛን አይመለከትም የኛ ስራ አርማንዶ የሰጠንን በምብ ውስጣዊ የጋዝ ብልቃጥ አስተካክሎ መመለስ ነው። ስለዚህ ምንም የሚያሰጋ ነገር የለም" አለ አንደኛው

"ለእናንተ ነዋ የማያስጋው... እኔን ግን ያሰጋኛል... ስለዚህ ስለሁኔታው ማወቅ አለብኝ!"

"ለምን? ደህና ገንዘብ እስከተከፈለህ ድረስ ምን አስጨነቀህ?"ሚስት አልባው ወጣት ነበር ይህን የተናገረው

"በእርግጥ ጥሩ ገንዘብ ይከፍለኛል... ነገር ግን አምኖኝ እንደፈለግሁ እንድንቀሳቀስ በፈቀደልኝ ማህበረሰብ ላይ መጥፎ ድርጊት መፈፀም አልፈልግም"

ከዚህ በፊት በጨዋታ መሃል ለሦስቱ አዲስ ጓደኞቼ ሙሉ የህይወት ታሪኬን እስከአቀድኩት በቀል ድረስ ስለነገርኳቸው አሁን በተናገርኩት ንግግር ግር ሳይሰኙ አይቀርም

"ይህ ስራ ካለቀ እቅድህን ሊያሳካልህ የሚችል ብዙ ገንዘብ ያስገኝልሃል። እኛም ብንሆን ይህ ስራ ከተጠናቀቀ በኃላ እዚህ ጋራዥ ውስጥ የመቆየት ሀሳብ የለንም... ወደ ደቡብ አሜሪካ ስንመጣ ያሰብነውን ያህል ገንዘብ ስርተን ማጠራቀም አልቻልንም... ይህ ስራ ደግሞ ጥሩ እድል የከፈተልን ይመስለኛል' አለኝ ሌላኛው

"እሺ እሱስ ይሁን... ሚስትና ልጆቻችሁስ?" አልኩ

"ስለሁሉም ነገር ያውቃሉ" የዶዶ ባል ነበር መልስ የሰጠኝ

ስለሁሉም ነገር ካወቁ ከዚህ በኃላ ለሚፈጠረው ማንኛውም ነገር እራሳቸውን አዘጋጅተዋል ማለት ነው። በዛኑ ምሽት ዲሎፍሪ እና አርማንዶን አግኝቼ ለረዥም ሰዓት በጉዳዩ ዙሪያ አወሩኝ።

"ይኸውል ፓፒ" ብሎ አርማንዶ ወሬ ጀመረ "ጀነራል መዲና ከስልጣን ከወረደ በኃላ እቺን ሀገር እየመሯት ያሉት ሰዎች ለግል ጥቅማቸው ሲሉ አይናቸው የታወረና ለገንዘብ ሲሉ እራሳቸውን የሸጡ ሰዎች ናቸው። መዲናን ደግሞ የቬንዙዌላ ህዝብ የሚያውቀው በለጋስነቱ፣በቅን አሳቢቱና ለሰው ባለው ክብር ነው። የሚገርምህ ለመዲና መውረድ ምክንያት የሆኑት ወታደሮች በምን ሰበብ መፈንቅለ መንግስት እንዳስነሱ እንኳን አያውቁም አድርጉ ስለተባሉ ብቻ ነበር ያደረጉት። በዛ ጊዜ በነበሩት እርኩስ የጦር ጀነራሎች ሃሳብ ተመርዘው ነው በመዲና ላይ መፈንቅለ መንግስት ያካሄዱት። ስለዚህ ፓፒ ወደዚህ ነገር ውስጥ የገባነው ለዚች ሀገር የሚበጃትን ጀነራል መዲናን ወደ ስልጣን ለመመለስ በማሰብ ነው ይሄን ሁሉ ነገር የምናደርገው" አለኝ በስሜት

"ጥሩ አርማንዶ... ነገሩን በጥሞና እንደተረዳሁት ከሆነ ከምንም በላይ ጀነራል መዲናን ወደ ስልጣኑ እንዲመለስ መፈለግህን ነው ዲሎፍሪም እንደዛው ያንተን ሃሳብ ሙሉ በሙሉ እንደሚቀበለው አውቃለሁ...ነገር ግን እናንተም በጥሞና እንድታዳመጡኝ የምፈልገው አንድ ነገር አለ። እንደምታውቁት ለእኔ ነፃነቴን የሰጠኝ ይህ ህዝብ ነው ከኢል ዶራዶ እስር ቤት ከወጣው ጀምሮ በዚች ሀገር ውስጥ ያገኘሁት እንክብካቤ እና ነፃነት በህይወቴ ውስጥ የማይፋቅ ቦታ አለው። እናንተ ደግሞ ይህን ማህበረሰብ እንድከዳ እየገፋፋችሁኝ ነው በፍፁም አላደርገውም! ስለዚህ እኔን ተውኝ እናንተ የፈለጋችሁትን መስራት ትችላላቹ እኔም ስለጉዳዩ ትንፍሽ ባለማለት እተባበራችኋለው" አልኳቸው።

አርማንዶ ትኩር ብሎ ከተመለከተኝ በኋላ "ኢንሪክ በቦንብ ማምረት ስራው ላይ እኮ አንተ አትሳተፍም። በብልቃጥ መቀየሪያ ማሽኑ ላይም የስራ ድርሻ አየኖርህም። አንተን የፈለግሁበት ዋንኛ ምክንያት መኪኖቹን እንድትቆጣጠር ብቻ ነው። እሱንም ቢሆን ለትንሽ ጊዜ... ስለዚህ ፓፒ እሺ በለኝ... በዛ ላይ እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት አስቀድመን እንነግርሀለን" አለኝ

አማራጭ ስላልነበረኝ በሃሳቡ ተስማምቼ ከሶስቱ የአርማንዶ ሰራተኞች ጋር ለመቆየት ወሰንኩ። እነዚህ ሶስት ሰዎች ከአሁን በኋላ ከኔ ጋር ስለሚቆዩ

ስማቸውን ባጭሩ ለአንባቢያን መግለፅ ይኖርብኛል፡፡ የሴሞኔ ባል ፒ.አይ ሲባል የዴዴ ባል ደግሞ ቢ.ኤል ይባላል ሌላኛው የቀረው ወንደላጤው ደግሞ ጂ ጂ ይባላል፡፡ ሶስቱም ጥሩ ወዳጆቼ ሆነዋል፡፡ ከስራ በኃላ ሁሌም የምንንቀሳቀሰው በጋራ ነው፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ ቀናት በቀናት እየተተኩ ለተወሰኑ ወራቶች ከእነሱ ጋር ደስ የሚሉ ጊዜ ባሳልፍም በስራው ግን አንድም ቀን ደስ የሚል ስሜት ተሰምቶኝ አያውቅም ነበር፡፡

ለወራት በእንደዚህ አይነት ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ውስጥ ብሆንም አንድም ቀን ግን ስለደበቅሁት ሀብቴ ሳላስብ ቀርቼ አላውቅም፡፡ የደረቀ ስጋ ከመሆን ተርፌ ያዳንኩት ሀብቴን አሁን የማውጫው ጊዜ የደረሰ ይመስለኛል፡፡ ዛሬ ላይ ሆኜ ብቀላዬ ስለመፈፀሙ ምንም አይነት ጥርጣሬ የለኝም! ለዛ ደግሞ ከዛፍ ስር ያለው ሀብቴ ከበቂ በላይ ነው፡፡

እዚህ ያለኝን ስራ በመጠኑም ቢሆን አገባድጄ በጋራጁ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ስላደረጉልኝ እንክብካቤ እና ስለሰጡኝ ጥሩ የወዳጅነት ስሜት አመስግኜ ወደ ቀበርኩት ሀብቴ ለመሄድ ተዘጋጀው፡፡ ወደ ስፍራው የሚያደርሰኝን አውሮፕላን ከያዝኩ ከተወሰኑ ጊዜ በኋላ ቦታው ላይ ደረስኩ፡፡ ከአውሮፕላኑ እንደወረድኩም ወደ ስፍራው የሚያደርሰኝን ታክሲ ይዤ ንብረቴን በጄ ለመያዝ ጉዞ ጀመርኩ፡፡

በአቅራቢያው ስደርስም ይዞኝ ለመጣው ታክሲ የሚገባውን ከፍዬ ወደ ድልድዩ አመራሁ… ድልድዩን ተሻግሬ ያየሁትን ነገር ግን አይኖቼ ማመን አቃታቸው 'አብጃለው? ወይስ ቦታ ተሳስቼ ነው?' አልኩት ለራሴ ንብረቴን የቀበርኩበት ዛፍ በስፍራው የለም እሱ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ላይ የነበሩት በመቶዎች የሚቆጠሩ ዛፎችም ተቆርጠዋል፡፡ ለመንገዱ መስፋፋት ሲባል ዛፎቹን ቆርጠዋቸዋል… ዛፎቹን መቁረጥ ብቻ ሳይሆን በመንገዱ አጠገብ ያሉትን ማንኛውም ነገር በቁፋሮ አስወግደውታል፡፡ ውስጤ ከመቁሰሉ እና ከመናደዴ የተነሳ ቦታው ሌላ እንዲሆን ተመኘው… ነገር ግን ቦታው እራሱ መሆኑን ልቦናዬ ያውቀዋል፡፡

የሆነ የማላውቀው ቁጭት እና የንዴት ስሜት ሲወረኝ ይሰማኛል ብስጭቴን መቋቋም ስላቃተኝ የሆነ የሚሰበር ነገር ካገኘው በሚል ዙሪያዬን ቃኘሁ… አስፋልቱ ላይ በነጭ ቀለም ከተሳለው ምስል በስተቀር ምንም ነገር አጣው፡፡

በንዴት ሄጄ ምስሉን የሚያጠፋልኝ ይመስል የተሳለውን ስዕል በርግጫ መጠለዜን ተያያዝኩት

'ቆፍረው ያወጡትን አፈር የት አድርገው ይሆን?' እራሴን ጠየኩ ለነገሩ አፈሩን እንኳን ባገኘው ከዛ ውስጥ በጣሳ የተደበቀውን ንብረቴን ፈልጎ ማግኘት በራሱ ትልቅ ፈተና ነው፡፡ ከድልድዩ ፊት ካለው ከፍታ ላይ ቁጭ ብዬ በፅሞና የሚወርደውን ውሃ መመልከት ጀመርኩ በሚገርም ሁኔታ ንዴት እና ቁጭቴ ቀስ በቀስ እየለቀቀኝ ወደ መረጋጋት ስሜት ውስጥ ስገባ ይታወቀኛል፡፡ ቢሆንም ግን አእምሮዬ ሳወጣው ያልቻልኩት ነገር ቢኖር ሁሉም ያሳካኋቸው የሚመስሉኝ ነገሮች ለምን እንደሚሸሹኝ አለማወቁ ነው፡፡ ጥረቴን በሙሉ እርግፍ አድርጌ ልተወው እንዴ? አሁን ምንድነው የማደርገው? የሚሉ ተስፋ አስቆራጭ ሀሳብ ውልብ ይልብኛል... ወዲያው ደግሞ 'ከወህኒ ቤት ለማምለጥ ምንም ያህል ጊዜ ውጥንህ ከሽፎብሀል? ሰባት ወይም ስምንት ጊዜ አይደል? ስለዚህ ይሄም ተመሳሳይ ነው፡፡ አንደኛዋ እድል ስትሸሽህ ሌላኛዋ ፍርቱና አሸናፊ ታደርግሀለች' እራሴን በራሴ ለማፅናናት ሞከርኩ

የቀበርኩት ሀብት ከደበቁት ቦታ እንዳጣሁት እርግጠኛ ስሆን ከዚህ በኃላ እዚህ መቆየቱ አስፈላጊ መስሎ ስላልታየኝ ወዲያውኑ ወደ ካራካስ የሚመልሰኝን አውሮፕላን ተሳፈርኩ፡፡ በጉዞዬ ላይ የሰው ልጅ በህይወት ሲኖር ስለሚያጋጥመው ውጣ ውረድ እያሰብኩ ነበር እንደተረዳሁት ማንኛውም ሰው ተስፋ አስቆራጭ ሁነቶች ሊያጋጥሙት ይችላሉ፡፡ ከዛም አልፎ እስከህይወት ማጥፋት ድረስ ሊያደርሱ የሚችሉ መሰናክሎች ዙሪያውን ሊከቡት ይችላሉ፡፡ መከራ ያልደረሰበት ሰው ቢኖር እንኳን ደስታውን ለጊዜውም ቢሆን የሚነጥቀው ነገር አይጠፋም ዋናው ነገር ችግር እንዲያሸንፈን አለመፍቀድ ነው የትኛውም ውድቀት ሲገጥመን እንደገና ለመነሳት መጣር አለብን፡፡ እኔም ይህንን ነው የማደርገው ከአርማንዶ ቤት ተነስቼ ንብረቴን ወደደበቅኩበት ቦታ ሳመራ ጌጦቼን ወደ ገንዘብ ቀይሬ ከቬንዝዌላ ለመውጣት እንጂ ተመልሼ ወደ ካራካስ የመምጣት እቅድ አልነበረኝም ነበር፡፡

የአርማንዶን ጋራዥ ከፍቼ ስገባ በቦታው የነበሩት ሶስቱ ሰራተኞች ባዩት ነገር ሳይገረሙ አልቀሩም፡፡ ለተወሰኑ ሰኮንዶች ያህል እነሱም ቆመው እኔም ተገትሬ ከመተያየት ውጪ ቃል አልተለዋወጥንም ነበር፡፡ ይመስለኛል ተመልሶ ይመጣል ብሎ ያሰበ አልነበረም፡፡ በመመለሴ ግን ሁሉም ደስተኞች ነበሩ፡፡

መምጣቴን ለማብሰር ግሩም እራትና መጠጥ በአበቦች በተከበበ ጠረጴዛ ላይ ተሰናዳ። ግሩም እና ደስ የሚል ስሜት የሚጭር የእራት ምሽት አሳለፍን። እቅዴ የሚሳካበት ጊዜባላውቅም ህይወት ግን ትቀጥላለች።

አርማንዶ እና ዲሎይፍሬ መመለሴ በጣም ነው ያስደሰታቸው። ዲሎይፍሬ ወደቤቱ ሄደን እንድናሳልፍ ባቀረበው ሃሳብም ሁላችንም ተያይዘን ወደ እሱ ቤት አመራን። መኖሪያ ቤቱ እንደደረስን ዲሎይፍሬ ምግብ ለማብሰል ወደ ኩሽና ሲገባ የእሱ ታማኝ ሹፌር የሆነው ቪክቶር ደግሞ የምግብ ጠረጴዛውን አሰናድቶ ጨረሰ። ከቆይታ በኋላም ዲሎይፍሬ በራሱ እጅ ያዘጋጀውን ግሩም እራት ተመገብን። የሰራልንን ምግብ ተመግበን እንደጨረስንም ነጭ ወይን እየተጎነጨን የተለያዩ ርዕስ ጉዳዮችን እያነሳን ማውራት ጀመርን በወሬያችን መሃል ግን ዲሎይፍሬ የሚወደውን ፕሬዝዳንት ስም ጣል ሳያደርግ አያልፈም ነበር . . .አርማንዶም ቢሆን ስለጀነራሉ ያለው አስተሳሰብ ከዲሎይፍሬ ቢበልጥ እንጂ አያንስም ነበር።

"ይገርምሃል ጀነራል መዲና ነፃ ሰው ነው… በእሱ ጊዜ አንድም የፖለቲካ እስረኛ አልነበረም። እኔ በህይወቴ ከማውቃቸው የቬንዙዌላ መሪዎች ውስጥ እንደ ጀነራል መዲና የዋህና ቅን አሳቢ እስካሁን አላጋጠመኝም" አለኝ ዲሎይፍሬ… አርማንዶም ከሱ ቀበል አድርጎ "አዎ ጀነራል መዲና ህዝቡን በጣም ነው የሚወደው፤ ከፍቅሩ የተነሳ እንደማንኛውም ዜጋ ሲኒማ ገብቶ ፊልም አይቶ ይወጣል። ካሰኘው ደግሞ አንዱ ምግብ ቤት ገብቶ ያማረውን ምግብ ከህዝቡ ጋር በልቶ የሚወጣ መሪ ነው። ይህ ደግሞ ለህዝቡ ምን ያህል ክብር እንዳለሁ ያሳያል፤ እመነኝ ጀነራሉ ወደ ስልጣን እስካልተመለሰ ድረስ አሁን ላይ ያሉት መሪዎች ሀገሪቷን እንደሚበዘብዟት አያጠያይቅም" አለኝ በቁጭት

በአርማንዶ እና በዲሎይፍሬ ስብከት የተነሳ አእምሮዬ ጀነራል መዲና ለሀገሩ ሟች መሆኑንና በሌቦች የተከዳ መሆኑን ለመቀበል ተገደድኩ። አሁን ያለው መንግስት ላይ መጥፎ እይታ እንዳላቸው ለመረዳት የግድ ከእነሱ ጋር ጓደኛ መሆን አይጠበቅብኝም ገና ስሙ ሲጠራ ነው የሚንገሸገሹት። በአሁኑ ሰዓት ጀነራል መዲና የሚኖረው ዲሎይፍሬ ከሚኖርበት ቤት ብዙም ሳይርቅ ሲሆን ከዛን በላይ ጥሩ ጓደኛቸው እንደሆነ ጭምር ነገሩኝ።

በመጨረሻም በእነሱ አሸናፊነት ወሬያችን ተገባደደ፡፡ አብሬያቸው ለመስራት ብወስንም ሀሳቡ ስህተት እንደሆነ ግን ይሰማኝ ነበር፡፡ በስራው ላይ ያለኝ ድርሻ ምን ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ጀመርኩ፡፡ ከዛ በላይ ግን ለምሰራው ስራ ጠቀም ያለ ገንዘብ ስለሚከፈለኝ ለማህበረሰቡ መቆርቆሬን ትቼ ሙሉ በሙሉ የብቀላ እቅዴን ለማሳካት አዲስ መስመር ከፈትኩ፡፡

እንግዲህ ወደ ታሰበው የመፈንቅለ መንግስት እንቅስቃሴም ሳላስበው ገባው ማለት ነው፡፡ በታቀደው መሰረት እኔ ሙሉ የሻንበል ልብስ ለብሼ፣ ዲሎይፍሬ ደግሞ የኮረኔል ልብስ በመልበስ እራሳችንን ከደበቅን በኃላ ወደ ቤተ መንግስቱ አካባቢ ሹፌሩ ቪክተርን አስከትለን ሔድን፡፡ መኪናችን ውስጥ አንድ በጨርቅ ጠቅልለን ከመኪናው የኂላ መቀመጫ ስር ያስቀመጥነው ቦንብ ይዘናል፡፡ ሁለቱ ቦንቦች ደግሞ አርማንዶ ይዟቸው በሌላ አቅጣጫ ሄዷል፡፡ ቤተ መንግስት አካባቢ ስንደርስ መኪናችንን ሰዋራ ቦታ ላይ ካቆምናት በኃላ ሶስቱ የአርማንዶ ሰራተኞች በጥበብ ቤተ መንግስቱ ውስጥ ገብተው በሩን እስኪከፍቱልን መጠበቅ ጀመርን፡፡

ምንም እንኳን በስራው ላይ ለመሰማራት ብስማማም ምንም አይነት ሰው እንዳይጎዳ ቃል ገብተውልኝ ነበር፡፡ እዚህ ቦታ ላይ ሆኜ ቃላቸውን ለማስታወስ ያህል ወደ ዲሎይፍሬ ዞሬ "ወደ እዚህ ስራ ውስጥ ስገባ ለጀነራሉ ያላቹ ክብር እና ፍቅር ስላስገደደኝ ነው ስለዚህ ምንም አይነት ሰው እንደማይጎዳ የገባችሁልኝን ቃል እንዳትዘነጉ... አላማችን ማስደንገጥ ብቻ ነው" አልኩት፡፡ ዲሎይፍሬም እየሳቀ እና የለበሰው የኮረኔል ልብስ እየት ካደረገ በኂላ "ስለሱ አታስብ ፓፒ... እነዚህን ሶስት ቦንቦች የፈለግናቸው በፍንዳታው ድምፅ እንዲርበደበዱ ለማድረግ ነው፡፡ እንደምታውቀው ቦንቦቹ የተሞሉት በባሩድ ዱቄት ብቻ ስለሆነ ከድምፅና ከጩኸት ውጪ ጉዳት አያስከትሉም፡፡ ለዛም ነው ቦምቦቹን እኛ ጋራዥ ውስጥ ፈታተን ዋናውን የጋዝ ብልቃጥ የምናወጣው፡፡ ፍላጎታችን ስርዓታቸውን እንደማንደግፍ እንዲያውቁልን ለማድረግ ብቻ ነው "አለኝ፡፡

"ድምፁስ ቢሆን ጥቅሙ ምንድን ነው?" ብዬ እንደቀልድ ጠየኩት

"የዚህ ቦንብ ጥቅም ቤተ መንግስት ያሉትን ሹማምንት ከማስበርገግ በተጨማሪ ከተማ ባዘጋጀነው መርሃ ግብር ላይ ለሚሳተፉ የዚህ መንግስት

ተቃዋሚዎች እንደ ምልክት መስጫ ያገለግለናል። ያ ነው እንግዲ አላማው ጋር ከእኛ ውስጥ ማንም የደም ጥማት ያለበት ሰው የለም! ማንም ሰው እንዲጎዳም አንፈልግም"

"እሺ" አልኩት... ሆነም ቀረ ስራውን ለመስራት እስከተስማማው ድረስ የአሁኑ መወላወል እርባና ቢስ መሆኑ ግልፅ ነው። ማድረግ ያለብኝ ነገር ቢኖር ከእኔ የሚጠበቀውን የስራ ድርሻ መፈፀም ብቻ ነው።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ቦንቦቹ የት የት ሊጣሉ እንደታሰቡ ተረዳሁ... የመጀመሪያው በፕሬዘዳንቱ መቀመጫ ቤተ መንግስት ውስጥ ሲሆን የተቀሩት ሁለቱ ደግሞ ምዕራብ እና ምስራቅ ካራካስ እንዲፈነዱ ነበር የታቀደው... የተለያየ ቦታ ላይ እንዲፈነዱ የተደረጉት ተቃውሞው የተነሳው ከተለያየ አቅጣጫ ነው የሚለውን እሳቤን ለመፍጠር ነው። በእርግጥ በስነስዓት የታቀደበት ለመሆኑ ጥርጥር የለውም።

እኛ አሁን የቆምንበት ቦታ ከቤተ መንግስቱ የኋላ በር አካባቢ ሲሆን በአመዛኙ የጦር መኪኖች ለመግባትና ለመውጣት የሚጠቀሙበት በር ነው። አንዳንዴም ፕሬዘዳንቱ ከሰዎች እይታ ውጪ ሆኖ ለመውጣት ሲፈልግ ይጠቀምበታል።

የሁላችንም ሰዓት ተመሳሳይ ሆኖ እንዲሞላ ተደርጓል። የእኔ የስራ ድርሻ ከውስጥ ባሉን ሰዎች በሩ እንደተከፈተልኝ አንዱን ቦንብ ይዤ ገብቼ መወርወር ነው። ቦንቡ ከመፈንዳቱ በፊት ትንሽ ጊዜ ስለሚሰጠን እኛ በዛ ሰአት አካባቢውን ለቀን እንወጣለን። በተመሳሳይም ሰዓት ምስራቅ እና ምእራብ ካራካስ ያሉትም ቦንቦች እንዲፈነዱ ይደረጋል ማለት ነው።

ምን አልባት ያሰብነውን ስንፈጽም ፖሊስ አልያም ወታደር ቢመጣ ለዲሎይፍሬ የኮለኔል ልብስ ምስጋና ይግባውና ያለምንም ችግር ከቦታው በሰላም እንደምንወጣ ሁላችንም እርግጠኞች ነን። ለዛም ነው እኔ የሻምበል እሱ ደግሞ የኮለኔል ማዕረግ ያለው የጦር ልብስ ለመልበስ የተገደድነው።

ሰአቴን ስመለከት ሁለት ሰዓት ሊሆን ጥቂት ደቂቃዎች ነበር የቀሩት ውስጥ ካሉን ሰዎች ጋር በሩን እንዲከፍቱ የተነጋገርነው ደግሞ ሁለት ሰዓት ላይ ነው። የተወሰኑ ደቂቃዎች ቆይቼ ሰዓቴን በድጋሚ አየሁት...ሁለት ሰዓት ሆኗል... በሩ ግን አሁንም አልተከፈተም ነበር

"ሁለት ሰዓት ሆነ እኮ አልኩት"ዲሎይፍሬን

"አውቃለው እኔም ሰዓት አለኝ እኮ"

"ይሄ ነገር አላማረኝም"

"እኔም ግራ ገብቶኛል. . . ለማንኛውም ቢያንስ ለአምስት ደቂቃ እንጠብቅ"

"እሺ"

ሁለት ደቂቃዎች እንዳለፉ በሩ ከውስጥ ተከፈተ ያየነው ግን የጠበቅነውን አይደለም... እኛ እንዳሰብነው የላክናቸው ሶስት ሰዎች ሳየሆኑ በሩን ከፍተው የወጡት ይልቁንም በተቃራኒው መሳሪያ የታጠቁ ብዙ ወታደሮች ነበሩ. . .በሆነ ሰው ምክንያት እንደተከዳን ገባን

"ተከድተናል አሁኑኑ አካባቢውን ለቀን እንጥፋ" አልኩት

ዶይልፍሬ ግን በሁኔታው ብዙም ሳይደናገጥ "አፍህን ዝጋ... እነዚህ ከእኛ ወገን ናቸው አለኝ"

ንግግሩ ስላልተዋጠልኝ ወዲያው ትንሹን ሽጉጤን አውጥቼ የቪክቶር አንገት ላይ ከጣድኩት በኃላ "መኪናውን አስነሳው ያለበለዚያ ጭንቅላትህን እበረቅሰዋለሁ አልኩት"

ቪክቶር ግን እኔ ባልኩት ነገር ከመደናገጥ ይልቅ ጭራሽ መኪናዋን ወደ ወታደሮቹ እያንደረደረ ማመን ያቃተኝን ንግግር ተናገረ "እዚህ እኮ ትዕዛዝ የምትሰጠው አንተ አይደለህም... አለቃ አንተ ምን ትላለህ?" ብሎ ፊቱን ከኔ ወደ ዲሎይፍሬ አዞረ

ብዙ ዓይነት ደፋር ነኝ ባዮች አይቻለው... የእዚህ ህንዳዊ ሹፌር ድፍረት ግን የሚገርም ነው እኔ ግን ውስጤ እንደሱ ሊረጋ አልቻለም... እነዚ ወታደሮች እንደሚወስዱት እርምጃ እኔም የምወስደው እርምጃ የከፋ ሊሆን ይችላል

ፊቴን ወደ ዲሎይፍሬ አዙሬ "ትሰማኛለህ ለሹፌርህ ከዚ ቦታ ለቀን እንድንሄድ የማትነግረው ከሆነ ከሱ ይልቅ ያንተን ጭንቅላት ለመበተን እገደዳለሁ"አልኩት

"ምስኪን ፓፒ ስነግርህ አትሰማም እንዴ... እነዚህ ወታደሮች ከኛ ወገን ናቸው አልኩህ እኮ" አለ ፊቱን ወደኔ አዙሮ... የዛኔ ነበር አፍንጫው ላይ ዱቄት መሳይ ነገር የተመለከትኩት... ለካ የኮኬን ዱቄት እየሳበ ነው። ውስጤ ፍርሃት ሲሰማው ይታወቀኛል። መታገስ አልቻልኩም... በቀጥታ ሽጉጤን አንገቱ ላይ አሳርፌ "የመጨረሻ እድልህ ነው መኪናውን እንዲያስነሳ ንገረው!"

"ፓፒ ስድስት ደቂቃዎች እኮ አለፉ... ቢያንስ ለተጨማሪ ሁለት ደቂቃ እንጠብቅና እንሄዳለን" አለኝ

እነዚያ መቶ ሀያ ሰኮንዶች ምን ያህል እንደረዘሙብኝ ማሰብ አያስፈልግም። ወታደሮቹ የሆነ የተፈጠረ ነገር እንዳለ ደርሰውበታል። ነገር ግን የት እና በማን እንደሆነ ያወቁ አይመስሉም ምክንያቱም ቪክቶር መኪናዋን እያሽከረከረ ባጠገባቸው ሲያለፍ እኛን ሲመለከቱን የነበረው ልክ እንደ ማንኛውም ሻንበል እና ኮረኔል ነው። በመንገዱ እያለፉን ስለመሰላቸው የተለየ አትኩሮት አልሰጡንም በመጨረሻም ዲሎይፍሬ ለቪክቶር "ጓደኛዬ ተረጋግተህ እና ፍጥነት ሳተጨምር ቀስ ብለህ አካባቢውን ለቀህ ውጣ" አለው

ፊጣሪ ረድቶን ከዛ መአት ለመውጣት ቻልን። ዲሎይፍሬ ለሹፌሩ ድልድዩን አቋርጦ እንዲሄድ ስለነገረው በድልድዩ ላይ ማዝገም ጀመርን። በመንገዳችን ላይ ሁለት የጭነት መኪኖች ላይ ተጭነው የነበሩ ብዛት ያላቸው ተቃዋሚዎች የእኛን የቦንብ ምልክት ባለመስማታቸው ምን እንደተፈጠረ ጠየቁን። እኛም በሆነ ሰው ምክንያት እንደተከዳን ነገርናቸው። በዛው ቅፅበት ዲሎይፍሬ ወደ እሱ መኖሪያ ቤት መኪናውን እንዲነዳው ለቪክቶር ነገረው። እኛን ቤት ካደረሰን በኋላ ቪክቶር መኪናው ውስጥ የደበቅነውን አንዱን ቦምብ ካወጣ በኃላ መኪናዋን ራቅ ወዳለ ቦታ ይዟት ሄዶ ሰዋራ ቦታ ፈልጎ ካቆማት በኃላ ቁልፉን እዛው መኪናዋ ላይ ጥሎት መጣ። እኛም ልብሶቻችንን በፍጥነት ቀያይረን ዲሎይፍሬ የሚፈልጋቸውን እቃዎች ከያዘ በኋላ ቤቱን ለቀን ወጣን። በመንገድ ላይ እየሄድን ሳለም ዲሎይፍሬ እርምጃችንን ገታ አድርጎ "ፓፒ ምንም ያክል የምትሰራው ስራ አደገኛ ቢሆንም ነገሮችን ግን በብልሃት እና

በትዕግስት ማከናወን እንዳለብህ አትርሳ" ብሎኝ በተለያየ አቅጣጫ ተጓዝን። እኔ ወደ አርማንዶ ጋራዥ ሳቀና እሱ ወደ ሌላ ቦታ ሄደ። ጋራዡ እንደደረስኩም ሰራተኞቹ ሲዋከቡ አገኘኋቸው። የቦንቡን ማሽን እና እዛ ያሉትን አምስት ጅምር ቦንቦች ከ አካባቢው አርቀን ደበቅናቸው። ልክ ከቀኑ ስድስት ሰዓት ላይ የጋራዡ ስልክ ጠራ...ሄጄ አነሳሁት

"ሄሎ"

"ፈረንሳዊው . . .ሁላችሁም ጋራዡን ለቃችሁ በተለያየ አቅጣጫ ውጡ ቢ.ኤል ብቻ ጋራዥ ውስጥ ይሁን አለኝ

"ማን ልበል?"ከማለቴ ስልኩ ጆሮዬ ላይ ተዘግቶ ነበር

ከአሁን በፊት ፈረንሳይ ውስጥ ፖሊስ ሆኖ አውቀው በነበረ ሰው እርዳታ የሴት ልብስ ለብሼ ራሴን ከደብቅሁ በኃላ ያለምንም ችግር አካባቢውን ለቅቄ ከካራካስ በሰባ ሰባት ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ ወደምትገኘው 'ሪዮቴካ' ወደ ተባለች ከተማ ከፖሊሱ ጋር ሄድኩ። እዛም ለ ሁለት ወራት አብሮኝ ከመጣው ፈረንሳዊ ፖሊስ ቤተሰቦች እና ጓደኞች ጋር ቆየው

ቢ.ኤል በፖሊሶች ቁጥጥር ስር ውሏል... ስቃይ በሌለው መንገድ ጥያቄ ብቻ እየተጠየቀ እንደሆነ ለማወቅ ችያለው... በርግጥ ፕሬዝዳንት ጋሊጉስን እነዲሎይፍሬ አናንቀው እንደነገሩኝ አይነት ጅል ሰው አይደለም ዲሎይፍሬ የዛኑ እለት ምሽት 'ኒካራጉዋን' ኤንባሲ ሄዶ ጥገኝነት እንደጠየቀ ሰምቻለው ስለ አርማንዶ ግን ምንም አይነት መረጃ የለኝም።

እኔ እስካሁን ድረስ በራስ መተማመኔ የፀና ነው። ሪዮ ቺኮ ከደረስኩ ከሳምንት በኋላ ከፈረንሳዊው አዲስ ወዳጄ ጋር በመሆን በመንገድ ስራ ላይ የገልባጭ መኪና ሹፌር በመሆን መስራት ጀመርን።በቀን ሃያ አንድ ዶላር ይከፈለናል።የመንገድ ስራው ለሁለት ወራት ያህል ሳይቋረጥ ስለቀጠለ ለእኛም ጥሩ የገቢ ምንጭ ሆኖልን ነበር። በዛ ላይ ካራካስ ውስጥ በእኛ ምክንያት ተፈጥሮ የነበረው ግርግር እንዲበርድ እና ፖሊሶች ፍለጋቸውን ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዲቀይሩ ጊዜ ስለሰጠኝ ለኔ ጥሩ ሆኗል። እኔም ከዚ በኋላ ወህኒ ገብቼ ምንም አይነት ጥያቄ መጠየቅ አልፈልግም። ከእንግዲህ በኃላም ዳግም በእንደዚህ አይነት ስራ ላይ እንደማልሳተፍ ለራሴ ቃል ገብቻለሁ።

አብዛኛውን ጊዜ ከስራ መልስ ከሰዓት በኋላ አሳ ለማጥመድ ወደ ባህሩ ዳርቻ መውረድ ያስደስተኝ ነበር። የሆነ ቀን 'ሮባሎ' ተብሎ የሚጠራ ትልቅ አሳ ያዝኩ. . .እኔም የፀሀይዋን አገባብ እየተመለከትኩ በእጄ ደግሞ የአሳውን ቆዳ እየገፈፍኩ ነበር። የፀሃይዋን አገባብ ከደመናው ጋር ተደምሮ ሰማዩን አስውቦታል። 'ቀይ ሰማይ ማለት ተስፋ ማለት ነው ፓፒ' አልኩት ለራሴ ተስፋ በህይወት ውስጥ አስፈላጊ ነገር ነው። ነገር ግን ተስፋን ተከትሎ የማልመው ስኬት መች እንደሚመጣ ለማወቅ እጓጓለው። እስኪ ባሳለፍኳቸው ሁለት የነፃነት አመታቶች ውስጥ ያገኘዋቸውን እና ያጣኋቸውን ነገሮች እናስታውስ፤ በርግጥ ራሴን ለማስተዳደር የሚሆን ገንዘብ አጥቼ ባላውቅም ያጠራቀምኩትም ሆነ ቅሪት አለኝ ብዬ ያስቀመጥኩት ሀብት ግን የለኝም።

በእነዚህ ሁለት አመታት ውስጥ ምን ተፈጠረ?

አንድ፡-ኢልሴሎ ውስጥ የነበረው የወርቅ ቁልል… በዚህ እንኳን አልፀፀትም ምክንያቱ ደግሞ ለእነዚያ ዘራፊዎች ሰላም ስል ነው። ይህም በገዛ ፈቃዱ ላለመውሰድ የወሰንኩት እራሴው ስለሆንኩ መቼም ልፀፀትበት አይገባም።

ሁለት፡- በአልማዝ ማውጫው የተካሄደው ቁማር… ይህ እንግዲህ ለአስር ሺህ ዶላር ብዬ ከሃያ ጊዜ በላይ እራሴን አደጋ ውስጥ የጣልኩበት ወቅት ነው። በዛ ላይ ለማላገኘው ብር… በእርግጥ ጆጆ ሞቷል እኔ ደግሞ ያለምንም ሳንቲም ተርፌያለው። መትረፌ በራሱ ትልቅ ነገር ነው። ቢሆንም ግን እነዚያን አስፈሪ ምሽቶች በፍጹም አልረሳቸውም። በካርቦን ፈሳሽ የሚሰሩት መብራቶች፣ የቁማርተኞች ፊት፣ የጆጆ የማይንቀሳቀስ ሰውነት… ብቻ ብዙ ነገሩ ዘግናኝ ነበር… ስለዚህ እዛም ባጣሁት ነገር አልፀፀትም!

ሶስት፡-ከባንኩ ስር ያለው ዋሻ… ይሄኛው ደግሞ እድል ከኛ ጋር እንዳልነበረች ያሳያል። ለሶስት ወራት ያህል ቀን ከሌሊት እዛ ዋሻ ውስጥ አፈር ስንዝቅ ቆይተን በመጨረሻው ሰዓት ነገሩ መበላሸቱ ቢያናድደኝም አሁን ግን አልቆጭበትም። በርግጥ እንዳሰብነው ቆፍረን ከጨረስን ወደባንኩ ስንገባ በብዙ ሚሊዬን የሚቆጠር ገንዘብ ይዘን መውጣት እንችል ነበር። ነገር ግን እኛ እዛው ዋሻ ውስጥ እያለን ተደርምሶብን ቢሆንስ ኖሮ? ልክ እንደ አይጥ የቅሌት ሞት ሞተን ነበር። ብንተርፍ እንኳን መውጫ ስንፈልግ በቀላሉ በፖሊሶች ተይዘን ይሄኔ ወህኒ ነበርን… ስለዚህ ይሄኛውም አይፀፅተኝም!

አራት፡- የአራጣ አበዳሪው ሱቅ... በእሱም አልፀፀትም

አምስት፡-በምቡ... የአሁኑ የፖለቲካ ቁማር... ይህንንም ቢሆን ብሩን ብዬ እንጂ ከልቤ አልነበረም ለመስራት የተስማማሁት... የብቀላ እቅዴ በልጦብኝ እንጂ የሰው ነብስ ሊያጠፋ በሚችል በማንኛውም ስራ ላይ መሳተፍ አልፈልግም ነበር። ከእስር በነፃ የለቀቀኝን መንግስት እና በሰላም እንድኖር የፈቀዱልኝን ማህበረሰቦች ማስቀየም አልፈልግምና ነው። ሆነም ቀረ በእነዚያ አራት ወራት ከአርማዶ ጋራዥ ሰራተኞች ጋር ቤተሰባዊ ጊዜን እና በህይወቴ ውስጥ የማልረሳውን ደስታ ሰጥቶኛል። ስለዚህ በነዚህ ሁለት አመታት የሚያናድድ እና የሚፀፅት ህይወት አልመራሁም ማለት ይቻላል።

ለአስራ አራት ዓመታት ያህል ባልሰራሁት ወንጀል በእስር ማቅቄ ወጣትነቴን ሙሉ በሙሉ እንዳላይ ሆኛለሁ። ከሁለት ዓመታት በፊትም ነፃ ሰው ለመሆን በቅቻለሁ። በእነዚህ ሁለት አመታት ጊዜ ውስጥም የሚያኮሩ ብዙ የጀብዱ ስራዎችን ሰርቻለው። ከእነሱ ደግሞ ጥሩ ልምድ እና ደስታ አግኝቻለው። ባንድ ወቅት ደስ በሚል የፍቅር ሕይወት ውስጥ ገብቼም ነበር። ከብዙ ሰዎች ጋርም የጠበቀ ጓደኝነት ለመመስረት በቅቻለው 'ታዲያ ምን ያስጨንቅሃል' አልኩት ራሴን' እሺ‹ገንዘብ የለህምወይ ደግሞ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ምንም ገንዘብ አይኖርህም፤ ምንድንነው ታዲያ ተዓምሩ። ድህነት ለማከም የሚከብድ በሽታ አይደለም!' ብዬ ለራሴ ነገርኩት። ለአምላክ ክብር ይግባውና አሁንም ጥሩ አቋም ላይ የምገኝ ሰው ነኝ...ዋናው ነገር ደግሞ እሱ ነው!

ያም ሆን ይህ አሁን ለሁሉም ነገር እንደ አዲስ መጀመር አለብኝ አንደኛዋ እድል ስትሸሽህ ሌላኛዋ ፍርቱናህ አሸናፊ እንድትሆን ታደርግሃለች።

የፀሀይዋ ብርሃን መደብዘዝ ሲጀምር እኔም የበለትኩትን ዓሳ ይዤ ወደ ቤት ለመሄድ ተነሳው። ቀኑ ደስ ብሎኝ ነበር ያለፈልኝ... እራሴን እንደ አዲስ ሰርቼ የዋልኩበት ቀን ስለነበር ቅልል ብሎኝ ነው ያለፈልኝ። ይህን ደስ የሚል ቀንም ፈጣሪ እንዳይ ስለፈቀደልኝም አመሰግነዋለሁ!!

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ማራካይቦ በህንዶች መሀከል

አንድ ቀን ወደ ካራካስ ደረስ ብዬ ለመመለስ በሄድኩበት ወቅት አንዱ ወዳጄ ከፓሪስ ስለመጣች ስለአንዲት ሞዴሊስት አጫውቶኝ ነበር።ይህችው ሞዴሊስት ማራካይቦ ላይ አዲስ ሆቴል መክፈቷን እና በማንኛውም ነገር የሚረዳት ሰው እንደምትፈልግ አጫወተኝ። ባገኘሁት እድል ለመጠቀም ጊዜ አልፈጀብኝም ነበር። እኔም ምንም ሳላንገራግር መስራት እንደምፈልግ ከነገርኩት በኂላ ወዲያው ሰው እንዳገኘላት የሚገልፅ መልዕክት እንዲልክላት አደረኩ።የሞደሊስቷ ስም 'ላወረንስ' ይባላል። ወዳጄ እንደነገረኝ ከሆነ ወደ ቬንዙዌላ የመጣችው ከተለመደው እቃ ለየት የሚሉ አንዳንድ የቤት እቃዎችን ለህዝቡ ለማሳየት እና ለመሸጥ አስባ ሲሆን በመጨረሻ ግን ሀገሪቷን በጣም ስለወደደቻት ኑሮዋን ማራካይቦ ላይ ለማድረግ በቅታለች። ማራካይቦ ከካራካስ በአንድ ሺህ ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ የምትገኝ ከተማ ስለሆነች ለእኔ ከካራካስ መራቁ በጣም ጥሩ ነው። ፕሬዝዳንቱን ለመስደንገጥ ያደረግነው ዘመቻ ገና ክሱ ስላልተዘጋ ዳግም ቢከፈት ቶሎ በፖሊሶቹ ቁጥጥር ስር እንዳልወድቅ ጊዜ ይሰጠኛል።

ከአስራ አራት ሰዓታት ጉዞ በኃላ የማራካይቦን ሐይቅን ለማየት ቻልኩ። በእርግጥ እነሱ ሐይቅ አሉት እንጂ ከወንዞ ተቆርጦ በወጣ ውሃ የተፈጠረ ቦታ ነው። ወደ ማራካይቦ ከተማ ለመግባት ያንን ሐይቅ በጀልባ ማቋረጥ ነበረብን።

ሐይቁ ለየት ያለ ነው በሺህ የሚቆጠሩ የመኪና ነዳጅ ከባህሩ መሬት ስር በሚያወጡ ቱቦ በሚመስሉ ብረቶች በሞሞላቱ በሐይቁ ላይ እጅብ ብሎ የበቀሉ ዛፎች ይመስሉ ነበር። እነዚህ የብረት ቱቦዎች ታዲያ ሌት ተቀን ከሐይቁ ስር ካለው መሬት ውስጥ ይህን ጥቁር ወርቅ በገፍ ያወጣሉ።

በሀይቁ ላይ ከትንንሽ ጀልባዎች እስከ ትልልቅ መርከቦች ሰውን እና እቃ በማመላለስ የማይናቅ ትርፍ ያገኛሉ. . .እኔም ሀይቁን በአድናቆት እየተመለከትኩ ፈጣሪ ቬንዙዌላን በአልማዝ፣ በወርቅ፣ በብረት፣ በኒኬል፣ በማግኒዥየም፣ በቶራኒየም እና በመሳሰሉት ንጥረ ነገሮች ሲሞላት እቺን ማራካይቦ ደግሞ በዚህ በጥቁር ወርቅ የመኪና ነዳጅ ማደሉን ሳይ እውነትም እቺን ሀገር ፈጣሪ የባረካት ሀገር ለመሆኗ አልተጠራጠርኩም ነበር።

ማራካይቦ እንደደረስኩ በቀጥታ የሄድኩት ወደ ላውረንስ ሆቴል ነበር። የላውረንስ ሆቴል 'ኖርማንዲ' ተብሎ ይጠራል። ሚያምር ቪላ ሆኖ ዙሪያውን በአበቦች የተከበበ ነው። ጣፋጯ ላውረንስም ሞቅ ባለ ፈገግታ ታጅባ "እንግዲህ ይህ የእኔ ግዛት ነው" ሄኒሪ አለችኝ... እኔም ለሰላምታዋ አፀፋውን ከመለስኩ በኋላ ወደ ሆቴሉ ተያይዘን ገባን።

ሆቴሉን ከከፈተችው ገና ሁለት ወሯ ሲሆን በውስጡም አስራ ስድስት ምቹና ቅንጡ የሆኑ ክፍሎች የያዘ ነበር። በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥም የራሱ ሽንት ቤትና መታጠቢያ ክፍል እንዲኖረው ተደርጎ ነበር የተሰራው። ወደ ስራው ለመግባት ጊዜ አላባከንኩም ነበር። ለላውረንስ የቀኝ እጅ ሆኜ መስራቴ ደስታን ፈጥሮልኛል። ላውረንስ በአርባዎቹ መጀመሪያ ላይ የምትገኝ ቆንጆና በጣም ጠንካራ ሴት ነች። በነገራችን ላይ ደከመኝ የማታውቅ ሴት ነች። ሆቴሉን ሙሉ ለሙሉ የምትቆጣጠረው እሷ ነች ማለት ይቻላል። ጠዋት አስራ ሁለት ሰዓት በመነሳት ለደንበኞች ቁርስ ታበስላለች ቀጥላም ከሆቴሉ ጓሮ ጀምሮ እስከ እያንዳንዱን የሆቴሉ ክፍሎች በየአንድ አንድ ሰዓቱ እየዞረች ለደንበኛ ምቹ መሆናችን ታረጋግጥ ነበር። ባጠቃላይ ስራ ብዙ ነች ብትባል ይቀላታል። እኔም ካሉባት ብዙ ችግሮች አንፃር በተቻለኝ አቅም መስራት በምችለው አቅም በማንኛውም ስራ ላይ አግዛታለሁ። ላውረንስን በዚህ ሰዓት የሚያስጨንቃት ነገር ቢኖር ሆቴሏን የበለጠ የሚስብና ምቹ ለማድረግ ስትል  የተበደረችውን ከልክ በላይ የሆነ ገንዘብ ነው።

ታድያ ይህን ስለማውቅ አንድ ቀን እሷን ሳላማክር በጭራሽ ያላሰበችውን ነገር አደረኩላት

"እንዴት አመሸሽ ላውረንስ" አልኳት እንደገባሁ

"እንዴት አመሸህ ሄነሪ... ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሆኗል... ዛሬ ቀኑን ሙሉ እዚህ አልነበርክም... የት ሔደህ ነው?" አለች በጓደኝነት ስሜት

"እየተንሸራሸርኩ ነበር"

"እየቀለድክ ነው?"

"አዎ በህይወት ላይ እየሳቅሁባት ነው፡፡ መሳቅ ለሰው ልጅ እረፍ ነው... አይመስልሽም?"

"ሁልጊዜ ባይሆንም አዎ... በእዚህ ሰዓት ግን ያንተን እርዳታ በጣም እፈልጋለሁ፡፡ መጥፎ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለሁት"

"መጥፎ?"

"አዎ ሄነሪ . . .ሆቴሉ ምንም እንኳን በጥሩ ሁኔታ እየሰራ ቢሆንም የተበደርኩትን ገንዘብ ለመመለስ ግን ብዙ ጊዜ እንደሚወስድብኝ እርግጠኛ ሆኛለሁ ያም ከአበዳሪዎቼ ጋር እንዳያጋጨኝ ሰግቻለሁ"

"አይዞሽ ላውረንስ... አሁን እዳሽን በሙሉ የምትመልሽበት መፍትሄ አዘጋጅቼአለሁ"

"እያሾፍክብኝ ነው?"

"አይደለም...ከጥቂት ቀናቶች በፊት እዚሁ ማራካይቦ ውስጥ በሚገኝ አንድ የነዳጅ ማውጫ ድርጅት ውስጥ በዋና ስራ አስኪያጅነት ከሚሰራ ካናዳዊ ጋር አውርቼ ነበር"

"ስለምን?" አለች አይኖቿ በጉጉት እያቁለጨለጨ

"ምን መሰለሽ... ይህ ካናዳዊ ለሰራተኞቹ ያንቺን ሆቴል ለአንድ አመት ያክል ለመከራየት ይፈልጋል"

"የማይሆን ነገር ነው!" አለች ፊቷ በደስታ ፈክቶ

"ሆኗል!" አልኳት... ወዲያው ዘላ ከተቀመጠችበት እንደፌንጣ ተነስታ በእፎይታ መንፈስ ተጠምጥማብኝ ጉንጮቼን አገላብጣ ከሳመቻቸው በኋላ መልሳ እዛው ወንበር ላይ ዘፍ ብላ ተቀመጠችበት

በነጋታው ከእዚያ ካናዳዊ ጋር ሆቴሉን ለአንድ ዓመት እንዲገለገልበት ተዋዋለች... ይህም ከተዘፈቀችበት እዳ ሙሉ ለሙሉ ወጥታ በእጇ ላይም ትንሽ ገንዘብ እንዲተርፋት አስቻላት፡፡

ከስምምነቱ በኋላ ደስታውን ለማብሰር እኔ ላውረንስ እና ካናዳዊው በመሆን ሻምፓኝ ከፈትን. . . ላውረንስ ስትደሰት በማየቴ እኔም ተደስቻለሁ፡፡ ማታ ትልቁ አልጋዬ እንደተጋደምኩ አሁን ስላለሁበት ሁኔታ ማሰብ ጀመርኩ ፓፒ የስራ አለሙን ለማወቅ ብዙም ጊዜ አልፈጀብህም፡፡ 'እና ስለመለወጥ ምን ታስባለህ ፓፒ?' አልኩ ለራሴ... በሆቴል ኖርማዲ በቆየሁባቸው ጊዜአቶች የሰው ልጅ ጠንክሮ ከሰራ የማይለወጥብ ምክንያት እንደሌለ ተረድቻለሁ፡፡ ፈረንሳይ እያለሁ ግን እንደዚህ አይነት አስተሳሰብ የለኝም ነበር፡፡ አሁን ግን በስራ መቀየር እንደሚቻል ብቻ ሳይሆን የተረዳሁት በዙሪያዬ በተከፈተ ማንኛውም የስራ እድል ራሴን መቀየር እስካስቻለኝ ድረስ ከመጠቀም መቦዘን እንደሌለብኝ ነው፡፡ በፊት ግን ተለፍቶና ተጥሮ ገንዘብ ማግኘት እጅግ ከባድ ነገር አድርጌ ነበር የማየው፡፡ ስለዚህ ፈረንሳይ ልፈፅመው ላሰብኩት የብቀላ ውጥኔ የግድ ገንዘብ ለማግኘት መዝረፍ ብቻ እደማይጠበቅብኝና ጊዜ ይፈጃል እንጂ እስካለሁ ድረስ ስራ ከሰራሁ ገንዘቡን ማግኘት እንደምችል አረጋግጫለሁ፡፡ ዋናው ነገር ስራውን ማግኘት ብቻ ነው፡፡ ገንዘቡ እንደሆነ አንዱ ሲመጣ ሌላኛውን አስከትሎ ነው፡፡ ዋናው የሚያስጋኝ ነገር ሰርቼ የማገኘው ገንዘብ የሚጠራቀመው በሒደት ስለሆነ ያሰብኩት የብቀላ እቅድ ለመፈፀም ብዙ ጊዜ ሊወስድብኝ መቻሉ ነው፡፡ ይህም ለጠላቶቼ ጊዜ እንደመስጠት ይቆጠራል፡፡ መቼም ፈረንሳይ ለመሄድ የሚያስችለኝን ገንዘብ በአንድ ቀን ስራ ማግኘት አልችልምና ነው፡፡

ማራካይቦ ውስጥ ንግድ በፍፁም አይቀዘቅዝም፡፡ ብዙ አይነት ንግድ ይካሄዳል፡፡ ከቢራ ጀምሮ እስከ ሲሚንቶ ድረስ በጥቁር ገበያው ላይ የማይሸጥ ነገር የለም፡፡ እዚች ሀገር ላይ እንደ ካራካስ ስራ አጥ አይበዛባትም፡፡አብዛኛው ሰራተኛ የሚያገኘው ገቢም ጥሩ የሚባል ነው፡፡ በዛ ላይ ማራካይቦ በነዳጅ የታደለች ሀገር ነች. . .አንድ መሬት ላይ ነዳጅ እንዳለበት ከተረጋገጠ የተለያዩ ነዳጅን

የማውጣት አቅም ያላቸው ድርጅቶች ይህንን ጥቁር ወርቅ ለማውጣት ይሻማሉ።

የነዳጅ ማውጣት ስራው ለመስራት በመጀመሪያ ነዳጁ በተገኘበት ቦታ ላይ መሰረታዊ ነገሮች ማሟላት ይገባል።ለምሳሌ መንገድ መስራት፣ ቢሮዎች መገንባት፣ ማረፊያ ቤት መስራት፣ የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ የመሳሰሉትን ነገሮች መሟላት ይገባቸዋል። በዚህ ደረጃ ላይ ነው እንግዲህ ለአካባቢው ሰው የስራ እድል ከመፍጠርም አልፎ ጥሩ ገቢ እንዲያገኙ የሚረዳቸው። የአካባቢው ሰው የገንዘብ ጥቅሙ ሳይገባው አልቀረም። ጥሩ ቤት በመስራት ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት በመላክ ህይወቱን ለመቀየር የሚጥር ህዝብ ሆኗል። እንግዲህ እነዚህ ነገሮች ከተሟሉ በኋላ ቀጣዩ ስራ የሚሆነው ነዳጁን የማውጣት ስራ ነው። በቀን ውስጥ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የሚያስገኙ በነዳጅ የተሞሉ በርሜሎችን ያወጡ ነበር። በሚያሳዝን ሁኔታ ግን ከዘይቱ ሽያጭ የሚገኘው ገንዘብ ለህዝቡ ጥቅም ከማዋል ይልቅ አብዛኛው የሚገባው ለከተማዋ ባንክ ነበር። የተቀረውን ደግሞ ነዳጁን የሚያወጡት ድርጅቶች ይቀራመቱታል!

እኔ እድለኛ ነኝ ወደ ማራካይቦ የመጣሁ ሰሞን ከፔርጃ ተራራሮች ተነስቶ እስከ ሀይቁ ድረስ ያለው መሬት ምናልባት ነዳጅ ሊኖረው ይችላል ተብሎ ስለታሰበ መሬቱን ለመጥናት የተለያዩ ድርጅቶች እየተፎካከሩ የነበረበት ሰዓት ነው። ምን አልባትም ለእኔ ትልቅ እድል ይዞ ይሆናል የመጣው…ማን ያውቃል? እስከዛው ድረስ ግን እጄ መስራት የሚችለውን ስራ ሁሉ ለመስራት ለራሴ ቃል ገብቻለሁ።

ላውረንስ ጋር በነበርኩበት ሰዓት በእሷ እና ሆቴሉ ውስጥ በሚሰሩት ሰራተኞቿ እገዛ ምግብ ማብሰል ተምሬያለሁ። ስለዚህ ምግብ አብሳይ የሚፈልግ ድርጅት ካለ ለምን በምግብ አብሳይነት ተቀጥሬ እድሌን ለምን አልሞክርም የሚል ሀሳብ ስለመጣልኝ ስሜን ሙያዬንና አድራሻዬን በጋዜጣ ላይ እንዲወጣ አስደረኩ። ከአንድ ሳምንት በኃላም ሪችሞንድ የተባለ የአፈር ጥናትና ምርምር ድርጅት ውስጥ በምግብ አብሳይነት ተቀጠርኩ። በእርግጥ ከላውረንስ ጋር መለያየቴ ቢያስከፋኝም አሁን የገባሁበት ድርጅት ውስጥ የሚከፈለኝን ደሞዝ በግማሽ ያህል እንኳን ላውረንስ ስለማትከፍለኝ በመሄዴ ብዙም አልተቆጨሁም።

በዚህ ድርጅት ውስጥ ምግብ ከማብሰል ውጪ ሌላ ስራ ስለሌለኝ ልምድ ለማካበት ጥሩ እድል ፈጥሮልኛል። ደስ የሚለው አጋጣሚ ደግሞ አሁን የምሰራበት ድርጅት ያንን ከፔርጃ ተራሮች አንስቶ እስከ ሀይቁ ጫፍ ድረስ ያለውን መሬት እንዲያጠና የተፈቀደለት ድርጅት መሆኑ ነው። ስለዚህ በእርግጠኝነት በምግብ አብሳይነት የምቀጥለው ለትንሽ ጊዜ እንደሆነ ውስጤ ነግሮኛል።

በዚህ በሪችሞንድ ድርጅት ውስጥ በምግብ አብሳይነት ለትንሽ ጊዜ ከቆየሁ በኋላ የድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ ፀባዬንም የምሰራላቸውንም ምግብ ስለወደደው ለካምፑ አስተዳደሮች ብቻ ምግብ እንዳበስል አደረገ። የካምፑ አስተዳደሮች በቁጥር አስራ ሁለት ብቻ ስለነበሩ ለእኔ ትልቅ ስራ አቃሎልኝ ነበር።

የመጀመሪያ ቀን ስራዬን ከመጀመሬ በፊት ወደ ካምፑ አስተዳደር ሄጄ በኩሽናዬ ውስጥ እንዲኖሩ የምፈልጋቸው አንዳንድ ተጨማሪ እቃዎች እና ምግቦች እንዳሉ ነገርኩት። እሱም ሳያቅማማ ነበር የምፈልገውን ነገር እንድገዛ የፈቀደልኝ።እኔም ሁልጊዜ ማታ ማታ ለነገ የማቀርባቸውን ምግቦች ማታውኑ አዘገጃጀቼ ነበር እዛው ድርጅት ውስጥ ወደ ተሰጠኝ አልጋ ለመተኛት የምሄደው። በነጋታውም የሰራኋቸውን የተለያዩ የምግብ ዝርዝር ስሞችን የያዘ ደብተር ለሁሉም እንዲዳረስ ካደረኩ በኋላ እንደየፍላጎታቸው ማቅረብ ነው። አስተዳደሮቹ ሁል ጊዜ በምሰራላቸው የተለያዩ ምግቦችን እና ለምግቦቹም በምሰጣቸው ስያሜ እንደተደመሙ ነበር። እዚህ ጋር ሳልጠቅሰው ማለፍ የማልፈልገው ነገር ቢኖር አሁን ለአስተዳደሩ የምሰራላቸውን ለየት ያለ ስም እና ጣዕም ያላቸው ምግቦችን ለማወቅ የቻልኩት አንድም በላውረንስ ምክንያት ቢሆንም ባንድ ወቅት ፈረንሳይ ውስጥ እራሷን ከሴተኛ አዳሪነት ካገለለች ሴት እንደስጦታ በተበረከተልኝ እንዴት የፈረንሳይ ምግቦችን ለመስራት እንደሚቻል በሚገልፅ መፅሐፍም ጭምር ነው።

በምሰራላቸው የምግብ አይነቶች የረኩት የካምፑ አስተዳደሮች ከእራሳቸው አልፎ ሌሎች ሴቶች ይዘው መምጣት ጀመሩ። ይህ ለእኔ ጥሩ እውቅና የሚያስገኝልኝ ቢሆንም የተመጋቢዎቹ ቁጥር ግን ከ አስራ ሁለት ወደ ሀያ አድጎ ነበር። ያ ማለት የስራ ጫናውም በዛው ልክ በእኔ ላይ ጨምሯል ማለት ነው። እኔም በምሰራላቸው ምግቦች እንደረኩ እርግጠኛ ከሆንኩ በኋላ ደሞዜን

አሁን ይከፍሉኝ ከነበረው ስምንት መቶ ዶላር ወደ አንድ ሺ አራት መቶ ዶላር እንዲያሳድጉልኝ ጠየኳቸው፡፡ እኔ ባቀረብኩት ሀሳብ ባይስማሙም ደሞዜን ግን ወደ አንድ ሺህ ዶላር ከፍ እንደሚያደርጉልኝ ቃል ገብተውልኛል፡፡ እኔም አንድ ሺህ ዶላር በቂ አይደለም ብዬ ብከራከርም ሰሚ ስላጣሁ ነገሩን ለመተው ተገድጄአለሁ፡፡

ሁለት መቶ ዶላር ተጨምሮልኝ ጥቂት ወራቶችን ካሳለፍኩ በኋላም ምግብ መስራቱ በጣም ስለሰለቸኝ የካምፑን ዋና አስተዳደር ለማናገር ወደ ቢሮው ሄድኩ፡፡ እንዳጋጣሚም ቢሮ ውስጥ ተቀምጦ አገኘሁት

"ጤና ይስጥልኝ አለቃዬ... አንድ ነገር ላማክሮት ነበር አመጣጤ" አልኩት

"እሺ ንገረኝ ምን ነበር?"

"ከጥቂት ቀናት በኃላ የፐርጂ ተራሮች ድረስ ያለውን መሬት ለማጥና እንደምትሄዱ አውቄአለሁ፡፡ እኔም ታዲያ በህይወቴ በማንኛውም አደገኛና እና መሳጭ ጉዞ ላይ መሳተፍ የመንፈስ እርካታን ይሰጠኛል እና እባኮትን ባሁኑ ጉዟችሁ እኔን እንድታካትቱኝ እፈልጋለሁ"

"እሺ አብሳዩ. . . አስብበታለሁ" አለኝ እኔም አመስግኜ ወደ መጣሁበት ተመለስኩ

አሁን የሚደረገው ጉዞ በዋነኛነት የሚያተኩረው በኮሎምቢያ እና ቬንዙዌላ ድንበር የሚለየውን የፐርጂ ተራራ ስራ ያለውን መሬት ለማጥናት ነው፡፡ ታዲያ ይህንን ጉዞ አደገኛ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ በእነዚህ ተራሮች እና ጫካ ውስጥ የሚኖሩ 'ሞቲሊኖ' የሚባሉ የህንድ ጎሳዎች መኖራቸው ነው፡፡ አንዳንዴ እንደውም ይህ የፐርጂ ተራራ 'የሞቲሊኖች ተራራ' ተብሎ ይጠራል እስካሁን ድረስ ይህ ጎሳ ከየት እንደመጣ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ ቋንቋቸው እና የአለባበስ ስልታቸው ከጎረቤት ሀገር ጋር ፈፅሞ አይገናኝም ከእሱ በተጨማሪ እጅግ አደገኛ ጎሳዎች ናቸው፡፡ ገና ስልጣኔ እነሱ ጋር አልደረሰም ነበር፡፡ የሚኖሩትም ሰብሰብ ብለው ከሳር በተሰራ ጎጆ ቤት ውስጥ ሲሆን በአንዳዱ ቤት ውስጥም ከሃምሳ እስከ መቶ የሚደርሱ ሰዎች በአንድ ላይ ይኖራሉ፡፡ለብቻ ኑሮ የሚባል ነገር እነሱ ጋር አይሰራም ወንዱም፣ ሴቱም፣ ሽማግሌውም፣ አሮጊቱም፣ ህፃኑም ሁሉም ተሰባስበው በአንድ ላይ ነው

የሚኖሩት፡፡ በእዚህ ጎሳ ውስጥ ብቸኛው ለማዳ እንስሳ ውሻ ብቻ ነው፡፡ ከአሁን በፊት በሰለጠነው አለም ቅኝ ግዛት ስር ቢወድቁም ለመልመድ እጅግ የሚከብዱ ጎሳዎች ናቸው፡፡ ከሰው ጋር ለመመግባባት እና ለመላመድ ምንም አይነት ፍለጎት የላቸውም፡፡ እንደውም በሆነ ጊዜ ከእነዚህ ጎሳዎች የወጡ ሰዎችን ተይዘው ለማልመድ ጥረት ተደርጎ ነበር፡፡ ነገር ግን ምግብ ባለመብላት እና የገዛ ደምስራቸውን በጥርሳቸው በመበጠስ ህይወታቸውን ለማጥፋ በመሞከር የሰለጠነው ሰው ከእነሱ ጋር ለመግባባት ያደረገውን ጥረት አክሽፈውታል፡፡ በእርግጥ በዚህ ሰዓት የሰለጠነው ዓለም እነዚህን ጎሳዎች በተለያየ ነገር እያባበለ መግባባት ችሏል፡፡ ምግብ፣ ልብስ እና አንዳንድ ቁሳቁሶችን በሄሊኮፕተር ወይም በአውሮፕላን በመውሰድ እነርሱ ወደሚኖሩበት ቦታ በመጣል እንዲሁም በእነሱ የአለባበስ ስልት ፎቶ ተነስቶ በመላክ በጥቂቱም ቢሆን ለመግባባት ችለዋል፡፡ ነገር ግን እኔ ወደ እዚህ ጎሳዎች ጉዞ ሳደርግ ጊዜው 1948 ስለነበር የሰለጠነው ማህበረሰብ ከእነዚህ ጎሳዎች ጋር ለመግባባት ከመሞከሩ በፊት ነበር፡፡

የአፈር ጥናት እና ምርምር ቢሮ ሃላፊው ፍቃድ ታክሎበት የማደርገው ጉዞ ሦስት አበይት ጥቅሞች ነበሩት

የመጀመሪያው ከኩሽና ህይወት መውጣቱ በራሱ ለአዕምሮ ሰላም ነው፡፡ የእኔ ህይወት የምትሻው ጀብዱ የሞላበት አለም ነው፡፡ ያን ደግሞ በዚህ ጉዞ ላይ አገኘዋለሁ ብዬ አስባለሁ፡፡ በዛው ልክም ጉዞው አደገኛ ሊሆን እንደሚችል አልጠራጠርም… ምክንያቱም ከአሁን በፊት ወደእነዚያ ጎሳዎች የሄዱ ተመራማሪዎች ስልጣኔን በማያቁት ሞቲሎች ተገድለው ነበር፡፡ የሞቲሊኖ ነዋሪዎች በቀስት ውርወራ የተካኑ ጎሳዎች ናቸው፡፡ እደሚባለው ከሆነ የሞቲሊኖ ሰው አንዴ ካነጣጠረ ኢላማውን ከመምታት የሚያግደው ነገር የለም ይባላል፡፡ እነዚህ ጎሳዎች ምንም እኳን በራሳቸው አለም ውስጥ ብቻ የሚኖሩ ሰዎች ቢሆኑም ሰውን ይገድላሉ እንጂ አይበሉትም ነበር፡፡ ይህም ለእኔ ትልቅ እፎይታ ነው ምክንያቱም ምናልባት በጎዞው ወቅት ቢገድሉኝ እንኳን ስጋዬ በእነሱ አፍ ከመበላት ይልቅ በአፈር በመበላቱ ነው፡፡

በዚህ ጉዞ ላይ የማገኘው ሁለተኛው ጥቅም ጉዞው የሚደረገው ጥቅጥቅ ባለ እና አደገኛ በሆነ ጫካ ውስጥ ስለሆነ ደሞዜን በፊት ይከፈለኝ ከነበረው በሁለት እጥፍ አሳድጎልኝ ነበር፡፡

ሦስተኛው ጥቅም ደግሞ ከእነዚህ የአፈር ተመራማሪዎች ጋር መሄዴ በራሱ ብዙ የማላውቃቸውን ነገሮች እንዳውቅ ይረዳኛል ያም ቢያንስ ጊዜዬን በከንቱ ያሳለፍኩ ያህል እንዳይሰማኝ ያደርጋል።

አሁን እንግዲህ የምርምሩ አባል እንደሆንኩ እስካረጋገጥኩ ድረስ በራስ መተማመኔም ጨምሯል። በዚህ ጉዞ ላይ የእኔ የስራ ድርሻ የሚሆነው ከያዝናቸው የምግብ ጣሳዎች መሀከል ለተመራማሪዎቹ ከአንድ አንድ ዳቦ ጋር ማደል ነው። በዚህ ሰዓት የምግብ መጥበሻዬ እና የምግብ አሰራሩን የምትገልፀዋ መፅሀፌ ምንም አይነት ጥቅም የላቸውም ።

በእዚህ የጥናትና የምርምር ጉዞ ላይ ጓደኛ የሆነኝ የጥናቱ ዋና ሀላፊ የሆነው ክሬቼት የተባለው ሰው ነው። ይህ ሰው ወደእዚህ የመጣው ከአሜሪካ ካሊፎርኒያ ሲሆን ለሪችሞንድ ድርጅት እንደተውሶ ነበር የመጣው አሁን የጀመረውን ምርምር እንደጨረሰም ይመለሳል። ከነዳኸ ጋር የተያያዘ ስለማንኛውም ነገር እውቀት አለው ብሎ ለማውራት ቢደፈርም ከዛ ውጪ ግን ስለ ታሪክ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም! ናፖሊዮን ከአሌክሳንደር በፊት ያለ መሪ ይሁን አይሁን የሚያውቀው ነገር የለም። ሲመስለኝ ማወቅም አይፈልግም!

ሞቲሊኖ ላይ የሚደረገው የመሬት ጥናት ቢያንስ ከሀያ እስከ ሀያ አምስት ቀናቶች ይፈጃል። የእኛ ቡድን ውስጥ ሦስት የአፈር ተመራማሪዎች እና ወደ አስራ ስምንት የሚደርሱ ሰራተኞች አሉ። የሰራተኞቹ የስራ ድርሻ የምርምር እቃዎችን መሸከም፣ የተለያዩ መጠለያ ለመስራት የሚረዱ ቁሶችን መሸከም፣ እንዲሁም በምግብ የተሞሉ ጣሶችን መሸከም የእነሱ ድርሻ ነው። ሰራተኞቹ የራሳቸውን ምግብ ስለሚሰሩ የእኔ የስራ ድርሻ ለሦስቱ ተመራማሪዎች ምግብ መስጠት ብቻ ነው። ከሦስቱ ተመራማሪዎች ውስጥ የአንደኛው ስም ካርሎስ ይባላል። ይህ ሰው ቬንዙዌላ ላይ ዲሞክራሲን ለማስፈን ከታገሉት ሰዎች መሀከል ስሙ የሚጠራ ግለሰብ ነው።

የመጀመሪያ እርምጃችን የሚሆነው ነዳጁ ይኖርበታል ተብሎ የታሰበውን ቦታ ማግኘት ነው። ቦታውን ለማግኘት ደግሞ የወንዙን መነሻ እስከ ሆነው ተራራ ድረስ መጓዝ ይጠበቅብናል። ጉዞአችንን ስንጀምር ሁላችንም በአንድ በትልቅ መኪና አንድ ላይ ሆነን ነበር። ነገር ግን የተወሰኑ ኪሎሜትሮች

ከሄድን በኋላ መንገዱ ትላልቅ መኪኖችን ለማሳለፍ ስለማይመች በትንንሽ መኪኖች ተከፋፍለን ለመሄድ ተገደናል። በትንንሾቹ መኪኖች የተወሰን ያክል ከሄድን በኃላ ጭራሽ መኪና የማያስገባ ቦታ ስለደረስን በእግር ለመሄድ ወሰንን። በእግራችን የተወሰነ እርቀት ከሄድን በኋላም ወንዝ ስላገኘን በታንኳ ተሳፍረን ወንዙን ማቋረጥ ጀመርን። ወንዙን ለመጨረስ የተወሰኑ እርቀት ሲቀረንም ውሃው መጠን ስላነሰ ከታንኳው ወርደን ወንዙን በእግራችን ማቋረጣችንን ተያያዝነው።እኔ እና ሦስቱ ሳይንቲስቶች ምንም አይነት እቃ ስላልያዝን መሻገሩ እምብዛም አላስቸገረንም፤ ከኋላችን ያሉት ሰራተኞች ግን የውሀው ግፊት ከተሸከሙት እቃ ጋር ተዳምሮ መንገዱ እንደከበዳቸው ያስታውቃል። በጉዟችን መሀል ሳይንቲስቶቹ በተወሰነ የመሬት ርቀት ላይ አፈር እየዘገኑ በብልቃት ናሙና ይወስዳሉ፤ ወድያው አፈሩን የዘገኑበትን መሬት አቅጣጫ በደብተራቸው ላይ ይመዘግባሉ፤ የመሬት አቀማመጡም ምን እንደሚመስል ደብተራቸው ላይ በምስል ለማስፈር ይሞክራሉ።

እንግዲህ እነዚህን እና የመሳሰሉትን መረጃዎች ካግበሰበሱ በኋላ ዘይት ያለበት ቦታ ተጣርቶ አንድ ቀን ይወጣል ማለት ነው። ሳይንቲስቶቹ የሚሰሩት ስራ በእርግጥ የሚደነቅ ስራ ነው፤ ሁል ግዜ ከአጠገባቸው ስለማልጠፋ ምን ጊዜም በሚሰሩት ስራ እንደተደመምኩ ነበር። የሳይንቲስቶቹ ስራ ግን ሙሉ ለሙሉ የተሳካ የሚሆነው ከእኛ ቡድን ውስጥ በእነዚህ የሞቲሊያውያን ጎሳ ካልተጎዳ ወይም ካልተገደለ ነው። ከአሁን በፊት በነበሩ የምርምር ጊዜያቶች በሞቲሎያውያኑ ሰው ስለተገደለ ድርጅቱ ከፍተኛ ገንዘብ ለካሳ ለማውጣት ተገዷል።

በጉዞ ላይ የሚደንቅ ጊዜን ነው እያሳለፍኩ የምገኘው፤ ከሳይንቲስቶቹ ውስጥ እስካሁን ስሙን ያልጠቀስኩት 'ላፕ' የተባለውን ሆላንዳዊ ነው። ታድያ ይህ ሰው ወንዙ ዳር የሚኖሩ የአሊጌተሮችን ( አሊጌተር ከአንዳድ ውስን ልዩነቶች በስተቀር አዞ የሚመስል ተሳቢ እንስሳ ነው) እንቁላላቸውን ከጣሉበት መሬት አውጥቶ ይዞ መምጣት ለምዷል። የአዞዎችን እንቁላል ማግኘት በጣም ቀላል ነበር፤ በመጀመርያ የአንዷን አዞ ዱካ መከተል ነው፤ ሴቷ አዞ እንቁላሎችን የምትጥለው ደረቅ ያለ ቦታ ላይ ሰለሆነ ዱካውን ለማግኘት አስቸጋሪ አይደለም። እንቁላሎቿን ለመጣል ቢያንስ ከአንድ ሰዓት እስከ ሁለት ሰዓት ያህል ከተቀመጠችበት አትነሳም። ስለዚህ እሷ እስክትጨርስ ጠብቆ እንቁላሎቹ በማንሳት በፀሀይ ደርቀው ለምግብነት እንዲውሉ ማድረግ ነው። ላፕም ይህን

ለምዶ ሁል ግዜ ወደ ወንዙ በመውረድ እንቁላል ይዞ ይመጣል፡፡ ታድያ አንድ ቀን እንቁላል ከወንዝ ይዞ እንደመጣ በሰኮንዶች ልዩነቶች ውስጥ አንዲት አዞ እሱ በወጣበት አቅጣጫ ብቅ አለች፡፡ ለካ ላፕ እንቁላሎቿን አውጥቶ ሲመጣ አይታዋለች፤ እርሷም የእሱን ዱካ ተከትላ ነው እኛ ጋር የደረሰችው፡፡ አመጣጧ የሰላም እንዳልነበረ እንቅስቃሴዋ ይናገራል፤ ላፕን እንዳየችው ልክ ውድድር እንዳለበት መኪና ተንደርድራ ወደ እሱ ሮጠች፡፡ በሁኔታው የተደናበረው ላፕ የሚያደርገው ስለጠፋበት በአንድ ዛፍ ስር ኡኡታውን እያቀለጠው አባሮሽ መጫወት ጀመረ፡፡ በአቅራቢያው የነበርኩት እኔ ብቻ ስሆን ከመደናገጥ ይልቅ ቆሜ በትርኢቱ እየሳቅሁ ነበር

"ኡ..ኡ..ኡ...ኧረ የሰው ያለ... እርዱኝ... ኡ..ኡ..ኡ" ምጡን ሳያቋርጥ በአፉ ይለፈልፋል፡፡ እኔ ደግሞ እያየሁት ባለሁት ነገር ዝም ብዬ እስቃለሁ፡፡ ከሁሉም በላይ እያሳቀኝ ያለው ነገር ይህ ግዙፍ ሰውዬ ልክ እንደ ህፃን እየጮኸ እና እያለቀሰ ለእርዳታ ሲለምን መመልከቴ ነው፡፡ ከተወሰኑ ሰኮንዶች በኋላ ክርቼት እና ሰራተኞቹ እየተሯሯጡ መጡ፤ ከመካከላቸው ጥይት የያዘው ሰውዬ አከታትሎ በተኮሰው ሁለት ጥይት አዞዋን ሊገድላት ቻለ፡፡ ሁሉም ሰው ከአዞዋ መምጣት ባልተናነሰ በእኔ ቆሞ መገልፈጥ ተደናግጠዋል፡፡

"በሰላም ነው?" አለኝ ክሪቼት ወደ እኔ ዞሮ

"ምንም አይነት መሳርያ አልያዝኩም፡፡ ስለዚህ ምንም ማድረግ አልቻልኩም... ሁኔታውን ደግሞ ለተከታተለው ሰው በጣም ያስቅ ነበር" አልኩት፡፡ የዛን እለት ምሽት የጣሳ ምግባችንን በመብላት ላይ እንዳለን ክሪቼት በፈረንሳይኛ ቋንቋ " ልጅ አትመስልም!! ቢያንስ ሰላሳ አራት አመት ይሆነህል አይደል? " አለኝ

"ለምን ጠየቅሽኝ?"

"አኗኗርህም... ፀባይህም ልክ ሃያ ቤቶች ውስጥ እንዳለ ወጣት ነው"

"እንግዲህ ንገረኝ ካልክማ ገና ሃያ ሰባት አመቴ ነው"

"ውሸት!!"

"እውነት ነው!! እንዴት እንደሆነ ላስረዳህ... ለአስራ አራት አመት በቁም ሳጥን ውስጥ ታሽጌ ኖርያለሁ::እነዛን አመቶች ደግሞ እንደኖርኩ አልቆጥረውም:: እድሜዬ አርባ አንድ ነው... ከእዛ ላይ አስራ አራቱ ሲቀነሱ ሃያ ሰባት ይሆናል:: ስለዚህ የእኔ እድሜ ሀያ ሰባት ነው:: አዎ!! አንተ አልተሳሳትክም አሁንም ልቤ የሃያዎቹ ነው!! እነዛን ሳልኖራቸው ያሳለፍኳቸውን አስራ አራት አመታትን አሁን ላይ ኖሬ ማምጣት አለብኝ... ስለሆነም ሃያ ሰባት ዓመቴ ነው በማለቴ ማንም ሊፈርድብኝ አይገባም" ይህንን እንደተናገርኩ ንግግሬን ገታሁ...እሱም ስሜቴን ስለተረዳልኝ በመደናገር መንፈስ ከመመልከት ውጪ ምንም ቃል ከአንደበቱ አልወጣም::

አንድ ቀን ሀይለኛ ጨኸት ከተኛንበት አስበርግጎ አስነሳን፤ ቁርስ ለማዘጋጀት በጠዋት ከተነሱት ሰዎች መካከል በአንዱ ላይ ቀስት ተወርውሮበት ነበር፤ ጎኑ እና ግራ ቂጡ ላይ ቀስቶች ተወድረውበታል:: ወደ ካራካስ ሄዶ መታከም ስለነበረበት በቀጥታ አራት ሰዎች ተሸክመውት በቀጥታ ወደ ታንኳው ወሰዱት፤ ከታንኳ ጉዞ በኋላ ደግሞ በትንሸዋ መኪና ሌላ ጉዞ፤ ከዛ እንደገና ከትንሿ መኪና ወርዶ ወደ ትልቁ መኪና በመዘዋወር ማራካቦ እንዲገባ ተደረገ:: ይህን ያህል ረጅም ጉዞ ተጉዞ ማራካይቦ እስኪደርስ ድረስ ህመምን መታገስ በጣም ከባድ ነው፤ ቢሆን ግን ከእዛ የተሻለ ምርጫ የለም!!

ከዛን ቀን በኋላ የሞተሊኖ ጎሳዎች በዙርያችን እንደሚያንዣብቡ ተረድተናል፤ ነገር ግን ያየነውም ሆነ ሲያወራ የሰማነው ሞቲሊናዊ የለም:: ቢሆንም ግን ሁሉም ሰው በእዛ ልጅ በተሰኩት ቀስቶች ስለተረበሸ የታጠቅነውን ሽጉጥ ደግኖ መዋል ግድ ሆኗል፤ ወፍ አልያም ጥንቸል ባንኮሻኮሹ ቁጥር የጥይት እሩምታ መስማት ከተለመደ ውሎ አድሯል:: በእርግጥ የትኛውም ሰው በመተኮሱ አይፈረድበትም፤ ምክንያቱም በሞተሊኖች ክልል ውስጥ እስካለህ ድረስ ሞት በማንኛውም ሰዓት ሊመጣ እንደሚችል ግልፅ ስለሆነ ነው:: ሁሉም ሰው በአደጋው ስለተደናገጠ እንደ በፊቱ መዝፈን እና መቀላለዱን ትተው በንቃት ዙርያቸውን ነበር የሚጠብቁት፤ በመጨረሻም በውስጣቸው ያለው ፍረሀት ሰላም የነሳቸው ሰራተኞች ስራውን አቋርጠን ወደ መጣንበት እንመለስ የሚል ሀሳብ አመጡ:: የጉዞው መሪ የሆነው ክሬቼት ስራውን አቋርጦ ይመለሳል የሚል ግምት የለኝም፤ ካርሎስም ጀግና የሚባል አይነት ሰው ቢመስልም የእነዚህ የህንድ ጎሳዎች ጉዳይ ግን የጣመው አይመስልም:: እንመለስ የሚለው

ሀሳብ የቀረበ ሰዓት እኔ ወዳለሁበት ቦታ መጥቶ "ኢንሪክ አንተስ ምን ትላለህ?" አለኝ

"ስለምን ጉዳይ?"

"ወደ ማራካይቦ እንመለስ በሚለው ሀሳብ ላይ"

"በምን ምክንያት?"

"በሞተሊኖ ጎሳዎች ምክንያት ነዋ"

"ህንዳውያኑ በእዚህ ጫካ ውስጥ እንዳሉ እርግጥ ነው... ነገር ግን እኛን ማጥቃት ከፈለጉ ስንመለስም አይቀርልንም"

"እሱን እንኳን እርግጠኛ መሆን አልችልም፡፡ የሞተሊኖዎች መንደር ግን በአቅራቢያችን ነው ያለው... አየኸው እዛ ጋር ያለውን ድንጋይ?ጥራጥሬ የሚፈጩበት እኮ ነው" አለኝ ፍራቻ በአዘለ ቅላፄ

"በእርግጥ ያስፈራል... ለማንኛውም ክሪቼት ምን እንደሚል እንስማው"

ክሪቼት ነገሩን ከእኔ አስቀድሞ ስላወቀው ወዲያውኑ ነበር ነጋሪም ሳያስፈልገው ሰራተኞቹን የሰበሰበው፤ ይህ ሰው በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጥ አሜሪካዊ አልነበረም፡፡ ስራውን በእጅጉ እንደሚወደው ያወቅሁት ሰራተኞቹ ለመመለስ በማሰባቸው ከመናደዱ የተነሳ ሁላችንም ባለንበት የተናገረውን ንግግር ሳዳምጥ ነው

"ይሔን ያህል ፈሪዎች ከሆናችሁ ተመለሱ!!" ይህቺን ቃል ብቻ ነው ለሰራተኛው ያስተላለፈው

ከእኔ፣ ከካርሎስ እና ከላፕ ውጪ የተቀሩት መሄዱን መርጠው ጉዟቸውን ጀምረዋል፡፡ እኔም ልቀር የቻልኩት ስራችንን ጨርሰን በምንመለስበት ወቅት ምንም አይነት ሸክም እንደማንይዝ እና እቃዎቹን የሆነ ቦታ ላይ ቀብረናቸው ጥለናቸው እንደምንሄድ ስለተስማማን ነው፡፡ ባራንኪላ ወህኒ ቤት በነበርኩበት ጊዜ ሁለቱ ቁርጭምጭሚቶቼ በዝላይ ምክንያት ተሰብረው እንደነበር የማይረሳ ነው፤ በእሱም ምክንያት እግሮቼ አይደለም እቃ ተሸክሜባቸው ቀርቶ እንደዚሁ

በራሱ ረዘም ያለ ጉዞ ሳደርግባቸው ያብጣሉ፤ ለእዚህ ደግሞ በአሁኑ ጉዞ ላይ ብቻ የሚያውቀኝ ካርሎስ በቂ ምስክር ነው።

ክሪቼት፣ ካርሎስ፣ ላፓ እና እኔ በመሆን ለአምስት ቀናቶች በጫካ ውስጥ የአፈር ናሙና እየወሰድን እና እየመዘገብን ቆየ። በእነዚህ አምስት ቀናቶች ውስጥ ምንም የተፈጠረ ችግር አልነበረም፤ ነገር ግን አምስቱንም ቀን ያሳለፍኩት በሚያስፈራ እና በሚጨንቅ ስሜት ውስጥ ሆኜ ነው። እነሱ በሚመለከቱን እኛ ደግሞ ጭራሽ በማናያቸው ሰዎች ተከበን ለአምስት ቀን መቆየት የእውነት ያሳቅቃል። የመጨረሻው ቀን ወንዙ የሚነሳበት ቦታ ላይ ደረስን፤ ክሪቼት ወዲያው ከእኛ ተነጥሎ ወደ ወንዙ ዳርቻ ተጠግቶ አንዳች ነገር በአትኩሮት ከተመለከተ በኋላ ተመልሶ እኛ ወዳለንበት መጣ። ተመልሶ ሲመጣ ባየው ነገር ልቡ እንደተሰበረ ከፊቱ ላይ ቢያስታውቅበትም ምንም እንዳልተፈጠረ ለማስመሰል እየጣረ ወደ እኛ ቀረበ

"እኛም ወደ ማራካይቦ የምንመለስበት ሰዓት ሳይደርስ አይቀርም። ለጊዜው የምንፈልገውን ናሙና በእጃችን ይዘናል... እኛም ከእዚህ በላይ በመቆየት የሞተሲኖች ናሙና መሆን የለብንም" አለ ወደ ላፓ እየተመለከተ

እኛም የአለቃችንን ሀሳብ ተቀብለን ወደ ማራካይቦ ለመመለስ ተነሳን፤ ምንም አይነት ችግር ሳይገጥመን 'ቡራ' የምትባል መንደር ላይ ደረስን፤ ቡራ በጣም ትንሽ መንደር ስትሆን በውስጧ በዛ ከተባለ አስራ አምስት የሚሆን ቤቶችን ብትይዝ ነው። እኛም መኪና መጥቶ እስኪወስደን ድረስ ዘና ለማለት መንደሯ ውስጥ ወዳገኘነው መጠጥ ቤት ገባን። ገብተን ትንሽ እንደተቀመጥን አንድ የሰከረ ቅይጥ ህንዳዊ እኛ ወደተቀመጥንበት ቦታ መጥቶ ከመካከል እኔን ለይቶ ጎትቶ አወጣኝ።

"አንተ ፈረንሳዊ ነህ አይደል? አሁን ከየት እንደመጣችሁ አውቃለሁ። ሀላፊነት የማይሰማችው ሰዎች ከሆናችሁ ግን ብዙ ነገር አጥፍታችሁ ነው የመጣችሁት" አለኝ መጠጥ ባሰረው አንደበቱ እየተኮለታተፈ

ከሳይቲስተቹ ትንሽ ገንጠል ማለት ስለፈለኩ እና ከእዚህ ሰካራም ሰውዬ በሚወጡ ቃላቶች ዘና ማለት ስለፈለኩ ነበር ከመሀል ጎትቶ ሲያወጣኝ ያልተቃወምኩት

"ምን እያወራህ እንደሆነ አልገባኝም" አልኩት

"ልነግርህ አይደል ምን አስቸኮለህ… በሞቲሊኖች መንደር አቋርጣችሁ እንደመጣችሁ አውቃለሁ፤ ግን በእነሱ ጫካ ውስጥ ስታልፉ ምን አደረጋችሁ?ያገኛችሁትን የሚበሩ አእዋፍት እና የሚዋኙ የባህር ላይ እንስሶች እየተመገባችሁ እዚህ ደረሳችሁ አይደል? ይህ ስታስበው ታድያ ጥናት ነው ትለዋለህ? ይሄ አደን ነው!!"

የሰከረ ቢሆንም ከአንደበቱ የሚወጡ ንግግሮች ቁም ነገርን ያዘሉ ነበሩ፤ ስለዚህ ባዋራው ትርፍ እንጂ ኪሳራ እንደማላገኝበት ስለገባኝ ማውጋቱን ቀጠልኩ

"ዋናው ነጥብህ ምንድነው ታድያ?"

"ይውልህ እናንተ የምትጠቀሙበት የአደን ስልት የህንዳውያኑን የምግብ ምንጭ እንደሚያጠፋ መርሳት የለባችሁም.። ሞተሊኖዎች በቀን ለምግብነት የሚያስፈልጋቸው እንስሳ በዛ ከተባለ ሁለት ነው። እነሱም ሲገደሉ ፀጥታ እና ጥበብ በተሞላበት የአደን ስልት ነው። ድምፅ አልባ አደን የሚጠቀሙበት ምክንያት እንስሶች እንዳይበረግጉ እና አካባቢውን ጥለው እንዳይሰደዱ ስለሚረዳቸው ነው። እናንተ ግን እሳት በሚተፉ ሽጉጦቻችሁ አራዊቶቹን እየገደላችሁ እና እያስደነበራችሁ እዚህ ለመድረስ ችላችኋል። ከእዛም ወደመጣችሁበት ትመለሳላችሁ። የእነዚህ ምስኪን ህንዳውያን እህል ውሀ ግን አጥፍታችሁ ነው የምትሄዱት" አለ

ይሄ ሰው የዋዛ እንዳልሆነ ከንግግሩ ያስታውቃል፤ ጨዋታው ስለተመቸኝ "ምንድነው እየጠጣህ ያለኸው? የዛሬው ግብዣ በእኔ ነው" አልኩት

"ሩም ነው!! ስለግብዣው አመሰግናለሁ ፈረንሳዊው" ብሎኝ በአቅራቢያችን የሚገኝ ወንበር ላይ ቁጭ አለ… እኔም ወንበር ስቤ ከአጠገቡ ተቀመጥኩ

"አየህ ሞተሊኖዎች ቀስት የሚወረውሩባችሁ ያለ ምክንያት አይደለም። እነሱ እንደሚሉት አጥኚዎች ነን እያሉ ወደ እዚህ በሚመጡ ሰዎች ምክንያት አድነው መብላት እየተቸገሩ እንደሆነ ነው"

"አዎ ልክ ነው… በገዛ ክልላቸው እየዘረፍናቸው ነው ማለት ነው እኮ"

"ትክክል ነህ ፈረንሳዊው!! ለምሳሌ በጀልባ በወንዙ ላይ ስትመጡ እና ከጀልባዋም ወርዳችሁ በእግራችሁ ስትራመዱ ወንዙ ዳርቻ ላይ በቀርከሀ የተሰሩ ትንንሽዬ ግድብ የሚመስሉ ነገሮች እየረጋገጣችሁ አልፋችኋል አይደል?"

"አዎ… አስታውሳለሁ"

"ተመልከት እንግዲህ… እነዚያ ግድቦች ለአሳ ማጥመጃ ተብሎ በሞተሲኖች የተሰሩ ናቸው። ይህን ለመስራት ብዙ ጊዜ ፈጅቶባቸዋል… እናንተ ግን እየረጋገጣችሁ ታፈርሱታላችሁ። ታድያ በእዚህ ቢናደዱ ምን ይደንቃል?"

"ግድቡ ምንድነው ጥቅሙ?"

"ይውልህ ፈረንሳዊው… ከወንዙ ጀምረው በአስገራሚ ጥበብ የተጥመዘመዙ ቱቦ መሳይ ነገር በቀርከሀ ይሰራሉ… ከዛ ያንን የተጥመዘመዘ ቱቦ መሳይ ቀርከሀ መሬት ላይ ከገነቡት ሳጥን ጋር ያገናኙታል። በእዚህም መልኩ አንድ አሳ በእዛ ቱቦ ውስጥ አልፎ በቀርከሀ ወደተገነባው ትንሽዬ ግድብ ውስጥ አንዴ ከገባ በፍፁም መውጣት አይችልም። የእናንተ ጀልባ እና እግር ግን ለታሰሩት አሳዎች ነፃነትን ሲሰጥ የህንዳውያኑን ጉሮሮ ግን እየዘጋ ይሄዳል። ሌላው ቀርቶ ለፍተው የሰሩትን የጥበብ ስራ ማፍረሱ በራሱ ቂልነት ነው"

"ትክክል ነህ! እኛ መስራት የማንችለውን ጥበብ ያውም በቀርከሀ የተሰራ ግድብ ማፍረስ አለማወቅም፣ ሞኝነትም ነው። ይህ ማለት የራሳችንን እንጀራ እያበሰልን የሰውን እንጎቿ መርገጥ ነው" አልኩት ቅይጡ ህንዳዊም ሀሳቡን ስለተቀበልኩት ካመሰገነኝ በኋላ ለጥቂት ደቂቃዎች ስለሞቲሎች ከተጫወትን በኋላ ተሰናብቶኝ ከመጠጥ ቤቱ ወጣ።

በመልሱ ጉዟችን ላይ ግማሽ ህንዳዊው ስለተናገራቸው ነገሮች እያብሰለሰልኩ ነበር። አእምሮዬ የሆነ ነገር ለመሞከር ስለፈለገ ልክ ማራካይቦ እንደደረስን ለጥናት እና ምርምር ዋና ዳይሬክተሩ ላገኘው እንደምፈልግ የሚገልፅ ደብዳቤ ላኩለት።

በበነጋታው ላገኘው እንደምችል ስለገለፀልኝ ዳይሬክተሩን ለማግኘት ወደ ቢሮው ሄድኩ። ስደርስም የጉዟችን ቡድን መሪ የነበረው ክሪቼት አጠገቡ ተቀምጦ አገኘሁት፤ እኔም ሰላምታ ከሰጠኋቸው በኋላ በቀጥታ ወደ መጣሁበት ጉዳይ ገባሁ።

"አለቃዬ ለተጨማሪ ጥናት ተመልሰን ወደ ሞተሲኖዎች ጎሳ መሄዳችን አይቀርም አይደል?"

"አዎ እንደውም በቅርቡ ትመለሳላችሁ"

"ጥሩ... እንደዛ ከሆነ በጉዞ ላይ ማንም እንዳይጎዳ እኔ ሀላፊነቱን ለመውሰድ የቁጥጥሩ የስራ ድርሻ ለእኔ ይሰጠኝ... ክሪቼት አሁን ባለበት ሀላፊነቱ ይቀጥላል። እኔ መውሰድ የምፈልገው ስነ-ስረዓት ማስያዙን ብቻ ነው"

"በጣም የተቀደሰ ሀሳብ ነው። የእኔንም የስራ ድርሻ አቀለልክልኝ ማለት ነው" ብሎ ክሪቼት ድጋፍ ሰጠኝ... ዳይሬክተሩም ሀሳቤን ለተወሰኑ ሴኮንዶች በጥሞና ከአጠኑት በኋላ መስማማታቸውን ገለፁልኝ

"በቀጣዩ የምርምር ጉዞ ላይ የቁጥጥሩን ስራ አንተ ትሰራለህ... አጣምረህም ለተመራማሪዎቹ ምግብ የማዘጋጀቱንም ስራ ትሰራለህ. . .ስለ ደሞዝ ጭማሪ ከሚቀጥለው ጉዞ በኋላ እናወራለን" አሉ ዳይሬክተሩ  ደስ ያለኝ ተቆጣጣሪ ለመሆን ምን እንዳነሳሳኝ የጠየቀኝ አለመኖሩ ነው። እኔም የጫካው እና የሰራተኞቻችን  ደህንነት እስከተጠበቀ ድረስ ከእዛ ቅይጥ ህናዳዊ ጋር ስላወራሁት ነገር ማንሳት አልፈለኩም ነበር።

ክሪቼት በእዚህ ጉዳይ ላይ አንድ ልፈጥረው ያሰብኩት ነገር እንዳለ ስለገባው በእኔ ተቆጣጣሪ መሆን ደስተኛ ነው። በእዛ ላይ እነዛ ቦቅቧቃ እቃ ተሸካሚዎች ፈርተው ወደ ማራካይቦ ሲፈረጥጡ እኔ በአቋሜ መፅናቴ ድጋፍ ለመስጠቱ አስተዋፆ ሳይኖረው አይቀርም።

ከዛን ጊዜ በኋላ ባደረግናቸው ጉዞዎች ይዘናቸው የምንሄደውን ስራተኞች በወንዙ ዳርቻ የተሰሩትን የአሳ ማጥመጃ ግድቦች ሳይነኩ እንዲያልፉ እና

ምንም አይነት እንስሳ ድምፅ ባለው መሳርያ እንዳይገሉ ትዕዛዝ መስጠት ጀመርኩ። ይህም በመሆኑ በሄድንባቸው የተለያዩ ጉዞዎች ላይ በጫካ ውስጥ አንድም ሰው ሳይጎዳ ነበር የምንመለሰው። እኔ ከሄድኩበት የመጀመርያው ጉዞ ውጪ ባደረግናቸው ጉዞዎች ላይ የራሳችንን ምግብ ከመመገብ በስተቀር ምንም አይነት ጥፋት ላለማጥፋት በጣም ጥረት አድርገናል። ሌላው ደግሞ የሞተሊኖች ችግር ምግብ እንደሆነ ስለገባኝ ጫካ ውስጥ በምንቀሳቀስባቸው ወቅት እና ጥናታችንን ጨርሰን በምንመለስበት ጊዜ በስኳር የተሞሉ ጣሳዎችን ጥዬላቸው እሄዳለሁ። አንዳንዴም ስራችን ሲጠናቀቅ ጨቤ፣ ገጀራ እና ሎሎች ቁሶችን ጥለንላቸው እንመለሳለን፤ እንደገና ተመልሰን ወደ እዛ ቦታ ስንሄድ እቃዎቹ በጠቅላላ ተወስደው ይጠብቁናል፤ ይህም ማለት የእኔ የመግባቢያ ስልት ሰርቷል ማለት ነው። ሆኖም ግን ወደ ማራካይቦ ስንመለስ ምንም አይነት ችግር ሳይገጥመን ምንም መመለሳችን ግራ ያጋባቸው ሰዎች እኔን እንደጠንቋይ አልያም ደግሞ ከሞተሊኖች ጋር ሚስጥራዊ ግንኙነት እንዳለኝ አርገው ነበር የሚያስቡት።

ለምርምር በወጣንበት አንድ ወቅት አሳን ያለ መረብ እና መንጠቆ እንዴት ማጥመድ እንደሚቻል ተምሬያለሁ፤ አስተማሪዬ ደግሞ 'ታፒር' የሚባል እንስሳ ነው። ይህ እንስሳ አሳማ መሳይ ሲሆን ከአሳማ ግን በተወሰነ መልኩ ይገዝፋል። በአብዛኛው ታፒሮች ከአፍንጫቸው እስከ ጭራቸው ድረስ ሲለካ እስከ አንደ ሜትር ከሰማንያ ድረስ ይረዝማሉ። እናም አንድ ቀን ወንዙ አካባቢ ቁጭ ብዬ ተፈጥሮን እያደነቅሁ እንዳለሁ ለመጀመርያ ጊዜ ይሄን እንስሳ አየሁት። ከጎኔ ካለው ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ውስጥ ነበር የወጣው። ቆዳው የአውራሪስ አይነት ሲሆን የፊት እግሮቹ ልክ እንደ ጅብ አጭር ናቸው፤ ፊቱ ላይም እንደዝሆን ረጅም ባይሆንም ኩንቢ መሳይ ነገር አለው።

እንስሳው በእኔ መኖር ተደናግጦ እንዳይሸሽ የተቻለኝን ጥረት እያደረኩ የሚሰራውን መመልከት ጀመርኩ። አጠገቡ ያለውን ሳር የሚመስል እፅዋት አፉ እስከቻለ ድረስ እየቀጠፈ መብላቱን ተያያዘው፤ ሳር በል እንስሳ እንደሆነ እያሰብኩ ባለሁበት ቅፅበት በአፉ የያዘውን ቅጠል እያመነዠገ ወደ ወንዙ አመራ። ከእዛም የወንዙን ፀጥ ያለ ቦታ መርጦ ወደ ውሀው በመጠጋት በአፉ የያዘውን ቅጠል ማመንዠጉን ቀጠለ። ከጥቂት ቆታዎች በኋላ ሲያኘከው የነበረውን ቅጠል በፈሳሽ መልክ በእነዛ ኩምቢ በሚመስሉ ቀዳዳዎች ውሃው ላይ ማፍሰስ ጀመረ። ያንን ያፈሰሰውን አረንጓዴ ፈሳሽ ደግሞ በጭንቅላቱ

በመታገዝ ከውሃው ጋር አደባለቀው፡፡ ይህንን ሁሉ ትርዒት ለምን እንደሚከውን ለማወቅ በጉጉት ነው እየተከታተልኩት የነበረው፡፡ ስለዚህም ሙሉ ትኩረቴን የእሱ ድርጊት ላይ አደረኩ፡፡ ብዙም ሳይቆይ አረንጓዴ ፈሳሽ ከተደባለቀበት ውሃ ውስጥ ትንንሽዬ አሳዎች ሲወጡ ተመለከትኩ፡፡

አሳማ መሳዩ እንስሳ ብቅ ብቅ ያሉትን አሳዎች በተረጋጋ ሁኔታ አንድ በአንድ እየለቀመ ሲበላ ተመለከትኩት፡፡ እንደገባኝ ከሆነ የእጽዋቱ ፈሳሽ አሳዎቹ እንዲደነዝዙ ሳያደርጋቸው አልቀረም፡፡ በህይወቴ ባየሁት ነገር እንደዛች ቀን የተደመምኩበትን ጊዜ አላስታውስም!!

ይሄን ትርዒት ከተመለከትኩ በኋላ ታፒሩ ይበላው የነበረውን ሳር መሳይ እፅዋት ጋር ሄጂ የምፈልገውን ያህል ከቀጠፍኩ በኋላ ውሃ እስኪሆን ድረስ ጨፈጨፍኩት፤ ያንን የተጨፈጨፈውን ቅጠል ይዤው በነበረው የምግብ ማሸግያ እቃ ውስጥ በደንብ አድርጌ ጨመኩት፤ በመጨረሻም ፀጥ ያለውን የውሀ ክፍል መርጬ የተወሰኑ ጠብታዎችን ወደ ወንዙ ጨመርኩ፡፡ ብዙም ሳይቆይ አሳዎቹ ብቅ፣ ብቅ እያሉ መውጣት ጀመሩ፤ በሁኔታው በጣም እየተደነቅሁ ውሃው ላይ የተንሳፈፉትን አሳዎች ለቀምኳቸው፡፡ እነዚህን አሳዎች ለምግብነት ማዋል ከተፈለገ ወድያውኑ የውስጥ አካላቸውን ማውጣት ያስፈልጋል፤ ያለበለዚያ በሁለት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ሊበላሹ ይችላሉ፡፡

በሌላ የምርምር ጊዜያችን ወቅት ደግሞ አንድ አዞ የሚያድን 'ፌንሜሪያዊ' ተዋውቄ ነበር፤ ይህ ፌሪሜናዊ ታድያ ሁለት ልጆቹን አስከትሎ ነበር የሚጓዘው፤ ከእዚህ ሰውዬ ጋር መተዋወቃችን ለእኛም፣ ለእሱም ጥቅም ነበረው፡፡ የእኛ ጥቅም ቦታውን በደንብ ስለማናውቀው የምንፈልገውን ቦታ በእሱ እርዳታ ያለምንም ችግር ማግኘት መቻላችን ሲሆን እሱ ከእኛ የሚያገኘው ጥቅም ደግሞ ሞተሲናውያን እና ፌንሜራዊያን ምንም እንኳን አንድ አይነት የዘር ግንድ ቢኖራቸውም በመሀከላቸው ቅራኔ ስላለ በጫካ ውስጥ ብቻውን ካገኙት ሊገሉት ስለሚችሉ ነው፡፡ ታድያ ይህ ሰው ቀን ቀን እኛን አቅጣጫ በመጠቆም ሲያግዘን ይውል እና ምሽት ላይ ደግሞ ከሁለት ልጆቹ ጋር በመሆን አዞ ያድናል፡፡

ፌንሚሪያውያን በማራካይቦ አቅራቢያ የሚኖሩ የህንድ ዝርያ ያለባቸው ጎሳዎች ሲሆኑ የሚግባቡትም የሙዚቃ ቃና ባለው ቋንቋ ነው፡፡ ለመግባባት

በጣም ቀላል ከመሆናቸው የተነሳ ከእነዚህ ማህበረሰቦች ጋር ጥሩ የሆነ ጓደኝነት እስከመመስረት ደረሻለሁ። የእዛ አካባቢ ሴቶችም ቢሆኑ እንዴት ማፍቀር እና እንዴት መፈቀር እናዳለባቸው ያውቁበታል።

ከሁለት ሜትር እስከ ሶስት ሜትር የሚደርሱ አዞዎችን ማጥመድ እጅግ አደገኛ ስራ ነው። በአንዱ ምሽት ከፌንሚሪዊው እና ከትልቁ ልጅ ጋር በመሆን አዞዎችን ለማደን ወደ ወንዙ ወረድኩ፤ ወንዙ ጋር እንደደረስን ለማጥመጃነት ባዘጋጇት ጀልባ ላይ እኔን ከመሀል አስቀምጠው አደኑን ጀመሩ። አዞዎቹ የሚወራጩት እኛ ካለንበት በተወሰነ ርቀት ላይ ነው፤ ፌንሜሪያዊው ከአዞዎቹ መካከል በቅርብ ርቀት ያለውን ለመለየት ትልቅዬ መብራት አበራ፤ አይቶ እንደጨረሰ መብራቱን በማጥፋት በፀጥታ መጓዝ ጀመርን። ይህ ሽማግሌ ፌንሜሪያዊ አንዴ ቅርብ ላይ ያለውን አዞ ካየ በኋላ መብራት ፈፅሞ አያስፈልገውም።

አዞው ያለበት አካባቢ እንደደረስን ጫፉ ላይ ረጅም ገመድ የታሰረበት የብረት ዘንግ በመያዝ አነጣጥሮ የአዞው ጀርባ ላይ ሰካበት። ከዛ ጀልባችንን በቶሎ ወደ መሬት በመቅዘፍ ገመዱን ከግንድ ጋር አሰርነው፤ ይህም የሆነበት ምክንያት ለአዞው የሚዋኝበት ጊዜ ከሰጠነው ከእነ ጀልባችን ገልብጦን ለሌሎች አዞዎች እራት ሊያደርገን ስለሚችል ነው። ከግንዱ ጋር ከታሰረ በኋላ ግን ለመዋኘት ቢሞክርም ገመዱ እንዳይዋኝ ስለሚያግደው ምን እንደያዘው ለማረጋገጥ የግድ ወደ ዛፉ ይመጣል። የዛኔ ነው እንግዲህ ትንሹ ፌንሜሪያዊ የአዞውን አንገት በያዘው ቆንጨራ ለመቁረጥ ሲታገል የተመለከትኩት። ቶሎ ሊሞትለት ስላልቻለ በገጀራው ደጋግሞ ይመታው ነበር። በእዚህ መሀል ግን ያለ ማቋረጥ የሚያወናጭፈው ጅራቱ ቢያገኘው በእርግጠኝነት እንደኳስ ሊያሽቀነጥረው እንደሚችል አልጠራጠርም። አንዳንድ አዞዎች ደግሞ በገጀራ ተቀጥቅጠውም ለመሞት ፍንክች የማይሉ አሉ።

በዛን ምሽት ብዙ አዞች እያደንን አስደናቂ ጊዜ ነበር ያሳለፍኩት፤ አዞዎቹን ወንዙ ዳር ካደረግናቸው በኋላ እዛው ትተናቸው ሄድን። በበነጋታው ተመልሰን በመግፈፍ ከአዞው ጀርባ ውጪ ሌላውን የሰውነት ክፍሉን ለምግብነት ለይተን አስቀመጥነው። የተቀረውን አካሉን ደግሞ አፈር ውስጥ ሲቀብሩት ተመለከትኩ

"የተቀረውን ለምን ወደ ወንዙ ውስጥ አትጥሉትም?" የሚል ጥያቄ አነሳሁ

"አንድ አዞ ሌላኛውን አዞ ሞቶ ቢሆን እንኳን አይበላም… ስለዚህ ወንዙ ውስጥ ብንጥለውም ውሃውን መበከል ነው የሚሆነው" ብሎ መለሰልኝ ፊንሜሪያዊው

ከእዚህ ጉዞ በኋላም ብዙ ደስ የሚሉ የጥናት ጉዞዎችን አድርጌያለሁ፤ ባካሄድኳቸው ጉዞዎችም ጥሩ የሚባል ገንዘብ እና ልምድ ለማካበትም ችያለሁ፡፡ በምርምር ህይወት እንዲህ ደስ የሚል ወቅት አሳልፌ ነው እንግዲህ በህይወቴ ይከሰታል ብዬ ያላሰብኩት ክስተት የተከሰተው!

# ምዕራፍ አስር

## ሪታ የቬራ ክሩዟ

በቅዱስ ዮሴፍ እስር ቤት በነበርኩበት ወቅት በእስር ቤቱ ፍርግርግ በኩል ሆኜ ምሽት ላይ ሰማዩ ላይ የተነጠፉትን ከዋክብቶች ማየት ያስደስተኝ ነበር። በዛ ሰዓት ላይ ሆኜ እንኳን አንድ ቀን ነፃነቴን ተጎናፅፌ በሆነ ትልቅ ከተማ ውስጥ ትልቅ የሚባል ስራ እየሰራሁ የራሴን ቤተሰብ መስርቼ እንደምኖር እርግጠኛ ነበርኩ። ታድያ በእዚህ ጨለማ በዋጠው ህይወት ውስጥ ሆኜ የብርሀንን ጮራ በምናፍቅበት ሰዓት አንድ ነገር ሳስብ ሁሉንም ነገር እረሳ ነበር። አንድ መፈጠሯን እንኳን የማላውቃት እንስት ሁሌም በአእምሮዬ እየተመላለሰች አንድ ቀን የእኔ ደስታ እንደምትሆን ሁሌም ውስጤ ያስባል። የሚገርመው በምናቤ የምስላት ሴት ውበት እና ቁመና ቁልጭ ብሎ ይታየኝ ነበር። ታድያ ቅዱስ ዮሴፍ በተሰጠኝ ክፍል ውስጥ ሆኜ ምናቤ ስለፈጠራት ሴት ሳስብ ሁሉም ነገር ብሩህ ሆኖ ነበር የሚታየን። መች እንደማገኛት እንጃ አንድ ቀን አብራኝ እንደምትሆን አውቅ ነበር። በዛ ስቃይ በበዛበት የእስር ቤት አለም ውስጥ ሆኜ አእምሮየዬ የፈጠራት ገፀ ባህሪዬ አብራኝ ያለች ያህል ካለሁበት ቁስል እንዳገግም በቻለችው አቅም ሁሉ ትረዳኝ ነበር። ነገር ግን በገሀዱ አለም የሌለች ውስጤ ፅፎ ያስቀመጣት ድርሰቴ ናት።

ታድያ ይቺን ቅዱስ ዮሴፍ ወህኑ ቤት ውስጥ በምናቤ ደርሼ ልቤ ውስጥ ያስቀመጥኳን እንስት ማራካይቦ ላይ ገፅታዋ እንኳን ሳይቀየር አገኘኋት ብል ማን ያምነኛል? ማንም!! አብራኝ ስንት ሌሊቶችን ያሳለፈችውን ህልሜን በአጋጣሚ ይሁን በፈጣሪ እርዳታ እርግጠኛ ባልሆንም ግን አግኝቻታለሁ። እኔ አብዛኛውን ነገሯን አውቀዋለሁ፣ እሷ ግን ከእነመፈጠሬም አታውቀኝም። ማን ያውቃል የወደፊት ሚስቴ ልትሆን ትችላለች... ነገሩ እንዲህ ነው

በሪችሞንድ የአፈር ጥናት እና ምርምር ድርጅት ካደረግነው ገዞ እንደተመለስኩ ራሴን ዘና ማድረግ ስለፈለኩ ቀጣይ ስራ እስኪጀመር ድረስ አንዱ ሆቴል ክፍል ተከራይቼ ራሴን ማዝናናት እንደምፈልግ ለድርጅቱ አሳወኩ:: እነሱም አንድ ትንሽዬ የእጅ ቦርሳ አስይዘውኝ፣ ከተማ የሚያደርሰኝ መኪና መድበውልኝ አሰናበቱኝ:: ከመኪናውዋ እንደወረድኩ በከተማ ውስጥ ጥሩ የሚባሉ ሆቴሎች ወዳሉበት አካባቢ መሄድ ስለፈለኩ 'ሴሌ ቬንዙዌላ' ተብሎ የሚጠራውን መንገድ ይዤ መጓዝ ጀመርኩ:: በመንገዱ ዳር እና ዳር የተሰሩት ቤቶች ከመሬት በላይ አንድ በዛ ከተባለ ደግሞ ሁለት ወለል ብቻ ያላቸው ህንፃዎች ነው ያሉቸው:: ቀኑ በጣም ይሞቅ ስለነበር የፀሀይዋን ንዳድ ለማምለጥ የእነዚህን አጫጭር ህንፃዎች ጥላ ተከልዬ መጓዝ ጀመርኩ::

አንድ ሆቴል ጋር ስደርስ እግሮቼን ከመራመድ ገታኋቸው:: 'ሆቴል ቬራ ክሩዝ' ይላል የሆቴሉ ስያሜ፣ ፅዳት እና ፀጥታው ከውጪ ሲመለከቱት እራሱ ይማርካል:: ወደ ሆቴሉ ዘው ብዬ ገባሁ፣ ከፊት ለፊቴ ተቀምጣ ባየኋት ሴት ግን ክው ብዬ ቀረሁ:: ልቤ ላይ ላልሰርዝ አድምቄ የፃፍኳትን የቅዱስ ዮሴፍ ትዝታዬን በአካል አየኋት:: "እሄ ሰውዬ ይቀልዳል እንዴ?" ሊያስብላችሁ ይችላል... ግን እራሷ ነች:: አምላክ ሳላቃት ለምን አስቀድሞ እንዳሳየን አላውቅም:: እግሮቼ ለመራመድ አቅም ቢያጡም እንደምንም እየሰነዘርኩ እሷ ወደተቀመጠችበት የእንግዳ መቀበያ አመራሁ::

"ጤና ይስጥልኝ የምታከራዩት ክፍል ይኖራል?" አልኳት የያዝኳትን ትንሿን ቦርሳዬን መሬት ላይ እያስቀመጥኩ... እሷም ቀና ብላ እየተመለከተችኝ

"አዎ ጌታዬ ይኖራል" አለች ልዕልቷ በፈረንሳይኛ ቋንቋ

"ፈረንሳዊ መሆኔን እንዴት አወቅሽ"

"ካወራህበት የስፓኒሽኛ ቋንቋ ቅላፄ ስፓኒሻዊ እንዳልሆንክ ስለገባኝ ነው... ተከተለኝ" አለች ከተቀመጠችበት በመነሳት. . .እኔም መሬት ላይ ያስቀመጥኳትን ቦርሳዬን በማንሳት መከተል ጀመርኩ:: እስካሁን ድረስ ከራሴ ጋር አልነበርኩም፣ በእውኔ ሳይሆን በህልሜ እየተከወነ ያለ ድርጊት ነው የመሰለኝ:: እሷ ግን አንድ ፅድት ያለ ክፍል ውስጥ አስገብታኝ ከመጤፍም ሳትቆጥረኝ በመጣችበት ተመለሰች::

እኔም ክፍሌን ከተረከብኩ በኋላ ወደ መታጠብያ ቤት በመሄድ ሰውነቴን ተለቃለኩ። ከዛ አልጋዬ ላይ ቁጭ ብዬ ሲጋራዬን በማቀጣጠል የህልም እውነት ስለሆነችው እንስት ማሰላሰል ጀመርኩ። አሁንም በህልሜ ይሁን በእውኔ ያየኋት አእምሮዬ መልስ መስጠት ተስኖታል፤ ነገር ግን በእውኔ እንዳየኋት ጥርጥር የለውም አዎ እራሷ ነች። በቅዱስ ዮሴፍ ወህኒ ቤት ውስጥ ያለምኳት ሴት ዛሬ በአይኔ ለማየት በቃሁ። አሁን ከእኔ በትንሽ ሜትሮች ርቀት ላይ ትገኛለች፤ ቢሆንም ግን ለነገሮች መጣደፍ የለብኝም፤ ሁሉም ነገር ፍሬ የሚያፈራው በቆይታ ነው፤ ስለዚህ ሰከን ማለት ይጠበቅብኛል። ልቤ በሀይል ስትመታ ይታወቀኛል፤ እንደምንም ብዬ እራሴን ካረጋጋሁ በኋላ በእርግጥ እውነት ግን እቺን ልጅ እስር ቤት እያለሁ ሁሉ ነገሯን ሳላውቃት አውቃታለሁ ብል ማን ያምነኛል... ምክንያቱም ከእሷ ጋር ያሳለፍኩትን የብቻ ታሪኬን ለሰው ብነግር የደራሲ የፈጠራ ውጤት ነው የምትመስላቸው። በእርግጥ ልቤ ሳያገኛት ደርሶ ነው ያነገሳት!  ቢሆንም ግን ይሄ ለሌላ ሰው የማይገባው  የእራሴ እውነት ነው። የሆነው ሆነና ዋናው ነገር እሷን በአካል ማግኘቴ ነው፤ ለዘመናት ከእኔ እርቃ ብትኖርም ልታመልጠኝ ግን አልቻለችም፤ ከእዚህ በኋላም እንድታመልጠኝ አልፈልግም። እሷን ለማግኘት መከፈል የሚጠበቅብኝን መስዋትነት በሙሉ እከፍላለሁ። ብቻ ከእኔ የሚጠበቀው ነገሮችን በእርጋታ መፈፀም ነው። እንቁላል በእግሩ የሚሄደው ቀስ በቀስ አይደል፤ ስለዚህ በጊዜ ሂደት የራሴ ማድረግ እችላለሁ።

ከቀናቶች በኋላ በአንዱ ምሽት በሆቴሉ ውስጥ ወዳለው መናፈሻ ሳመራ የልቤን ንግስት ተቀምጣ አገኘኋት። ለብዙ አመታት ያለምኳትን ቆንጆ ለብቻዋ ተቀምጣ ሳያት እኔ ቀጥሬአት እየጠበቀችኝ እስኪመስለኝ ድረስ ነበር የተደነቅሁት። የዛሬዋ ምሽት የሰጠችኝን እድል ማክሸፍ እንደሌለብኝ ውስጤ ስለነገረኝ እሷ ወደተቀመጠችበት ወንበር በቀጥታ አመራሁ። ሆቴሉን ከያዝኩበት እለት ጀምሮ ዛሬ ለመጀመርያ ጊዜ ቃል ከአንደበቴ ወጣ።

"ሰላም ሪታ"

"ሰላም... ስሜን እንዴት አወቅኸው?"

"ሲጠሩሽ ሰምቼ ነው... መቀመጥ ይቻላል?"

"ትችላለህ... ተቀመጥ"

እንደፈራሁት ለመግባባት ብዙ ጊዜ አልፈጀብንም ነበር፡፡ ሳልማት የኖርኳት ሪታ በሰሜን ሞሮኮ ውስጥ በምትገኝ ታንጋራ በምትባል ከተማ የተወለደች ልጅ መሆኗን አወቅሁ፡፡ሆቴሉም እሷ እንደምታስተዳድረው ተረዳሁ፡፡ አይኖቿ ልክ እንደ ሰማይ ከዋክብት ያበራሉ፤ ዝም ብዬ ብመለከታት ምን ያህል ደስ ባለኝ፤ ነገር ግን አይን አውጣ እንዳያስብለኝ እይታዬን ለጊዜው ገታ አደረኩት፡፡ ይሄን ምሽት ደስ በሚል ሁኔታ ካሳለፍን በኋላ በነጋታው በተመሳሳይ ሰዓት እንደምንገኛኝ ቃል ተገባብተን ተለያየን፡፡

ምሽቱ ደርሶ ያቺን  የፍቅር ፊርጥ የሆነች ልጅ እሳካገኛት ድረስ በጉጉት ነበር ስጠብቅ የነበር፡፡ የማይደርስ የለ ሰዓቱ ደረሰ እና ወደተቀጣጠርንበት መናፋሻ ሄድኩ፡፡ ቀድሜአት ነው የተገኘሁት፤ ቢሆንም ግን ብዙም ሳታስጠብቀኝ ረጅም ፀጉሯን ጀርባዋ ላይ እየነሰነሰች ወደ ተቀመጥኩበት መጥታ አጠገቤ ተቀመጠች፡፡ ከሷ ጋር ዋዛ ፈዛዛ ከማውራት ስሜት ሊሰጡ በሚችሉ ርዕስ ጉዳዎች ለማውራት ተዘጋጅቼ ስለመጣሁ በቀጥታ መሳጭ የሆኑትን የእራሴን ታሪክ ማውራት ጀመርኩ፡፡ በህይወቴ ከሰራኋቸው ወንጀሎች እና ከጆጆ ጋር ካሳለፍኩት የቁማር ጊዜ ውጪም  ምንም ሳላስቀር በጠቅላላው ነገርኳት፡፡ እሷም በአንክሮ ነበር ስታዳምጠኝ የነበረው፡፡ የእራሴን ጉዳይ ብቻ እየዘበዘብኩ ሳይታወቀኝ ምሽቱ ነጎደ፤ ነገር ግን ውስጤ ሊነግራት የሚፈልገውን ነገር አንደበቴ ማውጣት አቃተው፡፡ "አፈቅርሻለሁ… ዛሬ ሳይሆን ለዘመናት ሳፈቅርሽ ኖርያለሁ" ብዬ ብላት እንዴት ነው የምታምነኝ… ለሳምንት ያህል በእደዚህ አይነት ሁኔታ እያወራን ከቆየን በኃላ በመጨረሻ ያበጠው ይፈንዳ ብዬ ልነግራት ወሰንኩ፡፡

ሪታ አንቺ ውብ ሴት ነሽ… አንቺን አይቶ የማይመኝ ሰው ቂል ይመስለኛል… እኔም ከልቤ አፈቅርሻለሁ፡፡ ዛሬ ሳይሆን መፈጠርሽን እንኳን ሳላውቅ ለዘመናት ሳፈቅርሽ ኖርያለሁ፡፡ በርግጥ ይህ ላንቺ እንቆቅልሽ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን እውነቱ ይህ ነው፡፡ ምላሽሽ ምን ሊሆን እንደሚችል አላውቅም፡፡ ነገር ግን ላንቺም ቢሆን የሚያፈቅርሽ እና ልታፈቅሪው የምትችይው ሰው ከጎንሽ ቢኖር አይከፋም፡፡ በርግጥ እኔ ብዙ ብር የለኝም፡፡ አንቺ ደግሞ ከእኔ በተሻለ መልኩ ሀብታም ነሽ ማለት ይቻላል፡፡ ግን እመኚን የእኔ ፍላጎት ገንዘብ አይደለም፡፡ አብሬሽ መኖር ብቻ ነው የምፈልገው፡፡ ሞት እስኪለየን ድረስ ልቦቻችን ተሳስረው መኖርን እሻለሁ፡፡ የኔ ቆንጆ የት እና እንዴት እንደሆነ ባልነግርሽም ለዘመናት ግን ሳፈቅርሽ ኖርያለሁ" ብዬ ንግግሬን ጨረስኩ፡፡

ሬታም ምንም እንኳን ከአንደበቴ የሚወጡት ቃላቶች ውሸት እንዳልሆኑ የተረዳች ቢሆንም ቶሎ ምላሽ ለመስጠት ግን አልደፈረችም ነበር

"ምነው ዝም አልሽ?" አልኳት

"አይ ምንም ጥያቄው የጠበኩት ስላልሆነ ነው"

"አዎ በርግጥ ያስደነግጣል...አንድ ማንነቱን እንኳን በቅጡ የማታውቂው ሰው አፈቀርኩሽ ሲልሽ ተረተ ተረት ሊመስልሽ ይችላል"

"እንደዛ ማለቴ አይደለም"

"ይገባኛል...አሁን መልስ እንድትሰጪኝ አልፈልግም...ጊዜ ወስደሽ አስቢበት። እስከዚያው ግን እንደ ጓደኛ ዝም ብለን እናውራ"

"እሺ" አለችኝ የውስጤን ስሜት አውጥቼ በመናገሬ የሆነ ያህል እፎይታ እየተሰማኝ

ለአንድ ወር ያህል ከእሷ ምላሽ ሳልጠብቅ እየተገናኘን ማውራት ቀጠልን። ሁሌም ማታ ላይ መናፈሻ ውስጥ እየተገናኘን እናወራለን። አንዳንዴም ስራ ሲበዛባት አግዛታለሁ። መቀራረባችን ስር መስደዱ ሲገባኝ አንድ ቀን ጥያቄውን አነሳሁላት

"ሬታ መቼም ጥያቄዬን አልረሳሽውም አይደል?"

"አዎ ግን እኔ የምፈልገው የምተማመንበት አይነት ሰው ነው"

"ለእሱ ስጋት አይግባሽ እድሜ ልኬን ስንከባከብሽ ለመኖር ለዘመናት በናፈቀኝ አባቴ ስም ቃል እገባልሻለሁ"

"የምርህን ነው?"

"ምን አስዋሸኝ...አንቺ ብቻ ፍቃድሽን አትንፈጊኝ... ሌላውን በጊዜ ሂደት አሳይሻለሁ"

"እሺ… ጥያቄህን ተቀብየዋለሁ" አለችኝ ህልሜን በአካል ስላገኘኋት እንጂ ህፃን ልጅ ነበር ውስጤ. የቦረቀው ከአሁን በኋላ ትልቅ ስራዬ እሷን ማስደሰት ብቻ ነው!!

ሪታ ሲበዛ አይን አፋር ነች፤ ወደ እሷ ክፍል በምሄድበት ሰዓት ሰው እንዳያየን ተደብቄ እንድገባ ሁሌም እንዳስጠነቀቀችኝ ነበር፡፡ ከጊዜ በኋላ ግን ፍቅራችን ገሀድ ስለወጣ መደባበቁን ተውነው፡፡ እኔም እንደሰዉ ወግ ደርሶኝ ትዳር መሰርቼ፤ የእራሴ ቤት ኖሮኝ መኖር ጀመርኩ፡፡ በእርግጥ በሄድኩባቸው ቦታዎች ሁሉ ከሴት ጋር ኖሬያለሁ…ግን እሱ ትዳር አይደለም፤ ጊዜያዊ ፍላጎት እንጂ!! ትዳሬማ ሪታ ነች! እኔ ሳልሆን ልቤ ፈልጎ ያገኛት!!

በህይወቴ ለመጀመርያ ጊዜ ሪታን ካገኘሁ በኋላ የህይወት አቅጣጫዬን መቀየር እንዳለብኝ ተረዳሁ፡፡ ያንን ለማድረግ ወሳኝ ጊዜ ላይ እንደደረስኩ ይሰማኛል፡፡ ሪታ ልክ እንደኔው ሁሉ ወደ ቬንዙዌላ የመጣችው አምልጣ ነው፡፡ ያመለጠችው ግን ከወህኒ ቤት አይደለም ወይም ደግሞ ከፍርድ ቤት አይደለም፤ ብቻ አምልጣ ነው!

ሪታ ከእኔ ጋር ከመገናኘቷ ከአመት በፊት ነበር ከባለቤቷ ጋር በመሆን ወደ ቬንዙዌላ የመጣቸው፤ ከዛም አሁን ያለንበትን ሆቴል ከፍተው መኖር ጀመሩ፡፡ ነገር ግን ከትንሽ ጊዜ በኋላ ባለቤቷ ከማራካይቦ ሶስት መቶ ያህል ኪሎሜትሮች ርቃ ወደምትገኝ ቦታ ሄዶ መኖር በመፈለጉና በእዚህም ሀሳቡ ከእሷ ጋር መግባባት ስላልቻሉ መለያየትን መርጠዋል፡፡ እሱ ርቋት ቢሄድም ሪታ ግን አሁን ያለንበትን ሆቴል እያስተዳደረች ማራካይቦ ላይ ደምቃ እኔን ጠበቀችኝ፤ ሌላው እዚሁ ማራካይቦ ውስጥ በንግድ ስራ የሚተዳደር አንድ ወንድም አላት፡፡

የጫጉላ ጊዜያችንን ያሳለፍነው እሷ ስላለፈችበት ህይወት እየነገረችኝ እኔም ከልቤ ያለመሰልቸት እየሰማኋት ነበር፡፡ ሪታዬ የተወለደችው በጣም ዝቅተኛ የገቢ ምንጭ ካላቸው ታንጋራውያን ቤተሰብ ነው፡፡ ቤት ውስጥ ከእናት እና አባቷ ውጪ ስድስት ልጆች ነበሩ፡፡ ሶስቱ ወንዶች ሲሆኑ የተቀሩት ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ ልዕልቷ ሪታ ለቤተሰቧ የመጨረሻ ልጅ ነች፡፡ ህፃን ሆና ቤት ውስጥ ከእህት እና ከወንድሞቿ ጋር ከመዋል ይልቅ መንገድ ላይ መዋልን እንደምትመርጥ አጫውታኛለች፡፡ ለእሷ እውነተኛ ቤቷ ብላ የምታስበው

በከተማ ውስጥ በሰዎች ተሞልተው የሚታዩ መናፈሻዎች አልያም ደግሞ ሰው በገፍ የሚታይበት የንግድ ቦታዎችን ነበር። በእነዚህ ቦታዎች ላይ ሰዎች ሲበሉ፣ ሲገበያዩ፣ ሲዘፍኑ ሲጨፍሩ ወ.ዘ.ተ ማየት የመንፈስ እርካታን ይሰጣት ነበር። እሷ እና መሰል ጓደኞቿ ትምህርት ቤት ከሚውሉበት ጊዜ ይልቅ በየመንገዱ ዳር የሚያውደለድሉበት ጊዜ ይበልጥ ነበር። ቢሆንም ግን እናቷን በጣም ስለምትወዳት የእሷ እርዳታ ባስፈለጋት ቁጥር ከጎኗ ጠፍታ አታውቅም። ሌላው ለመጀመርያ ጊዜ ጫማ ያደረገችው በአስር አመቷ ነው።

ሪታዬ ከልጅነት እስከ አሁን አብሯት ያደገ ነገር ቢኖር ለአዲስ ነገር ሁሌም ትኩረት መስጠቷ ነው። አለም ላይ ስለሚከወኑ ነገሮች እምብዛም አታውቅም፤ ነገር ግን ሁሌም ቢሆን ለማወቅ ጥረት ታደርጋለች። "እነዛ መርከቦች ከየት ነው የመጡት? ምንድነው የያዙት? እዛ ጋር የሚታየው ነገር ምንድነው" አይነት እና መሰል ጥያቄዎችን መሰንዘር ትወዳለች። ስለ አለም እውቀት ባይኖራትም ሰሜን አሜሪካ ከላይ በኩል እንደምትገኝና ዋና ከተማዋም ዋሽንግተን እንደሆነ በውስጧም ሀብታም እና የፊልም ተዋናዬች በብዛት እንደሚኖሩባት ታውቃለች፤ እንዲሁም ደቡብ አሜሪካ ከታች እንደምትገኝ እና በውስጧም የህንድ ዘር በብዛት እንደሚኖሩባት መረጃው አላት።

ሪታ የትውልድ ቀየዋ በነበረችበት ወቅት ከሚያዝናኗት ነገሮች አንዱ የሰርከስ ትዕይንት ነበር። በርግጥ የሰርከስ ትርኢት ላይ መታደም የቻለችው ለሁለት ጊዜያቶች ብቻ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ለመታደም የበቃችው ትርኢቱ በተዘጋጀው ድንኳን ውስጥ አስቀድማ ገብታ በማደር ሲሆን ሁለተኛውን ደግሞ በሰርከስ ቡድን ውስጥ ከሚሰራ ሰው ጋር አብራ በመግባት ነው ልታይ የቻለችው። ከዛ ጊዜ በኋላ ነበር እሷም በሰርከስ ቡድኑ ውስጥ ገብታ የሰዎችን አድናቆት ለማግኘት ተስፋን ያነገበችው።

የሆነ ጊዜ ላይ ታድያ የሰርከስ ቡድኑ ወደ ደቡብ አሜሪካ ሄዶ ትርኢት ሊያቀርብ እንደሆነ ስትሰማ አብራቸው እንድትሄድ ልመነዋን ትያያዝዋለች፤ የእሷ እቅድ ከእነሱ ጋር ወደ ቦታው አቅንታ እዛ ከደረሰች በኋላ ሌላ ስራ በመፈለግ የቤተሰቦቿን ህይወት መቀየር ነበር። ነገር ግን እንዳሰበችው ከቡድኑ ጋር አብራ መጓዝ አልቻለችም ነበር፤ ይልቁንም በዛው አመት ቤተሰቦቿ ታንጋሪን ለቀው የሞሮኮ ዋና ከተማ ወደሆነችው 'ካዛ ብላንካ' ሄደው ኑሮዋቸውን መሰረቱ። ሪታ በዛን ሰዓት የአስራ ስድስት አመት ልጅ ነበረች።

ሬታ ካዛ ብላንካ በሰፈሩበት አካባቢ በሚገኝ ሱቅ ውስጥ በመቀጠር ቤተሰቦቿን መርዳት ግዴታዋ ሆነ። ሱቁ የሚገኘው የሌትኮር አውሮፕላን ማረፍያ አቅራቢያ ስለነበር አለምን እየዞሩ የማየት ጉጉቷ እና ህልሟ እንዳይደበዝዝ አድርጎታል። በጊዜው ስመጥር የነበሩ ፓይለቶች ልክ እንደ እነ ሜርሚዝ፣ ኢክልፔሪ፣ ሚሜል የመሳሰሉ አብራርያንን ከማየትም አልፋ ሰላም ለመባባልም በቅታለች።ከዛም አልፋ ከአንዳንድ ፓይለቶች ጋር ባለፉት ጉዞ ላይ ምን እንደገጠማቸው፣ የማረካቸው ነገር ምን እንደነበር ጠይቃ ማወቅ ያስደስታት ነበር። እነሱም ልክ እንደ ታናሽ እህታቸው ስለሚቆጥሯት ከጉዞ ሲመለሱ ትንሽ ነገር ግን ውድ የሆነ እቃ ይዘውላት ይመጣሉ።

አስራ ዘጠኝ አመት ሲሞላት አንድ ፍራፍሬዎች ወደ አውሮፓ በመላክ ከሚተዳደር ነጋዴ ጋር ጋብቻን ፈፀመች። ከእሱ ጋር በመሆን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትል በትጋት በመስራት ኑሮን ለማሸነፍ መሮጡን ተያያዘችው። ታታሪዋ ሬታ ጋብቻ በፈፀመች በሁለተኛው አመት የመጀመርያዋን ሴት ልጅ ወልዳ ለባለቤቷ አስታቀፈችው። ከዛም ኑሮዋቸው የበለጠ ደስታ የሰፈነበት ሆነ፤ ለመመላለሻ እና እቃ ማጓጓዣ የሚጠቀሙበት ሁለት መኪኖች ነበሯቸው። ሬታም ቤተሰቦቿ ከድህነት አረንቋ አለቃ የተመቻቸ ኑሮ እንዲኖሩ አደረገች። ይህ ለእሷ መፈፀም የነበረባት ትልቁ ግቧ ነበር።

ከእለታት ባንዱ ቀን ግን ያላሳቡት ዱብ እዳ ገጠማቸው... ብርቱካኖቹን ከነጋዴ ላይ በብድር መግዛታቸው ሳያንስ... ወደ አውሮፓ በመሄድ ላይ የነበሩት ሁለቱም በብርቱካን ፍሬ የታጨቁ መርከቦች ሊሰምጡባቸው ቻሉ፤ ይህም ካሰቡት በላይ ለኪሳራ ዳረጋቸው። የነበረባቸውን ብድር ከፍሎ ለመጨረስ ለዘመናት መልፋት እንደሚጠበቅባቸው የተረዳው የሬታ ባለቤት ሀገር ለቀው ወደ ደቡብ አሜሪካ ሄደው እንዲሰሩ ለሬታ አማከራት፤ ሬታም ወደ እዛ አልማዝ፣ ወርቅ እና የመኪና ዘይት በገፍ ወደሚወጣበት ምድር ለመጓዝ አላቅማማችም። በእዚህ ከተስማሙ በኋላ የወለዷትን ሴት ልጅ ለሬታ እናት በአደራ ሰጥተው ከሀገራቸው የምታስድዳቸውን መርከብ መጠበቅ ጀመሩ።

እነርሱን ወደ ደቡብ አሜሪካ የምትወስደው መርከብ የአሳ ማጥመጃ መርከብ ስትሆን ቁመቷ አስራ አንድ ሜትር ሲሆን የጎን ስፋቷ ደግሞ አምስት ሜትር ነበር። የመርከቧ ካፒቴን አስቶናዊ ነው፤ ይህ ሰው ያለመታወቅያ ቬንዜዌላ ድረስ እንደሚያደርሳቸው ከተስማሙ በኋላ ለጉዞ አምስት መቶ ፓወንድ

አስከፍሏቸው መርከቧ ላይ ተሳፈሩ። በእዚች መርከብ ውስጥ ለጉዞ የተሰናዱት እነ ሪታ ብቻ አልነበሩም፤ ከፈረንሳይ አምባገነናዊ የአገዛዝ ስረዓት ያመለጡ አስር ስፓኒሻውያን፣ ከሳላዛር ወህኒ ቤት ያመለጠ አንድ ፖርቹጋላዊ እና ሁለት ሴቶችን በተጨማሪነት ይዛለች። ስለዚህ በአጠቃላይ በእዚች መርከብ ውስጥ እነ ሪታን ጨምሮ አስራ ስድስት ሰው ይዛለች።

ቬንዙዌላ ለመድረስ አንድ መቶ አስራ ሁለት ቀናቶች እንደሚፈጅባቸው አስቀድሞ በካፒቴኑ በኩል ገለፃ ተደርጎላቸዋል።ለሁለት ወራት ያህል እንደተጓዙ መርከባቸው ውሀ ማስገባት ስለጀመረች 'ኬፕ ቬርዴ' ደሴቶች ላይ ለመቆም ተገደደች። በደሴቱ ላይ መርከቧን በመጠገን ላይ እንዳሉ የሪታ ባል በመርከቧ መንቆሻቆሽ ቬንዜዌላ መድረሱ ስላጠራጠረው በድጋሚ ተሳፍሮ ለመሄድ አቅማማ፤ ቢሆንም ግን ሪታ በካፒቴኑ ብቃት እርግጠኛ መሆኗን አሳምናው ጉዟቸውን ቀጠሉ።

ጉዞውን እንደጀመሩ ብዙም ሳይቆይ እነዛ አስር ስፓኒሾች ካፒቴኑ ያሴረባቸው አሻጥር እንዳለ ለእነ ሪታ በንዴት ነገሯቸው። ያም 'ዳካር' ላይ ለእረፍት በሚቆሙበት ጊዜ እነሱን አዘናግቶ እዛው ትቷቸው ከሄደ በኃላ ሌሎች ተሳፋሪዎች አሳፍሮ በላያቸው ላይ ሊነግድ እንዳሰበ እንደደረሱበት ነበር በብግነት ለተሳፋሪዎች ያወሩት። የማንንም ምላሽ ሳይጠብቁ አስሩም ስፓኒሾች ወደ ካፒቴኑ በመሄድ የታጠቁትን ጩቤ አውጥተው ከከበቡት በኋላ ሊያደርግ ያሰበውን ነገር እንደደረሱበትና ያቀደውን እቅድ ጭምር ዘርዝረው ነግረውት መኖር የሚፈልግ ከሆነ ሳይወሰልት ቬንዙዌላ እንዲያደርሳቸው አስጠነቀቁት። ካፒቴኑም ሳይወድ በግዱ ተስማምቶ ጉዞውን ቀጠለ፤ በቀጣዩ ቀንም ኬፔ ቬርዲን ለቀው ወደ አትላንቲክ ውቅያኖስ ገቡ።

ከሃያ አምስት ቀናት ጉዞ በኋላ የሎስ ቴስቲጎስን ደሴቶች ማየት ቻሉ፤ ይህም ቬንዜዌላ መድረሳቸውን የሚያበስር ነበር። በመርከቧ ላይ የተሳፈሩት ሰዎች በሙሉ ከዚህ በፊት ምንም ነገር የደረሰባቸው እስካይመስል ድረስ በደስታ ቦረቁ... ስለማዕበሉ፤ ስለሻርኮቹ፤ ስለ መርከቧ ብልሽት... በቃ ስለሁሉም ነገር እረስተው በደስታ ፈነጠዙ። ሪታ እራሱ ካፒቴኑ ሊፈፅምባቸው ስለነበረው በደል እረስታ አቅፋ ሁለቱንም ጉንጮቹን አገላብጣ ሳመችው፤ ዞር ስትል እነዛ ስፓኒሻውያን በደስታ በራሳቸው ቋንቋ እየዘፈኑ ነበር

A Venezuela nos vamos

A Nonque no hay carretena

A Venezlua nos vamos

En un bar quito de veda

( በእዚች ትንሽ መርከብ ቬንዙዌላ ደርሰናል... ምንም ያህል እንኳን መንገዱ ቢከፋም ቬንዜውላ ከመግባት ግን አላገደንም) እያሉ ነበር ያዜሙት

ሚያዝያ 18/1948 ከሰባት ሺህ ስምንት መቶ ኪሎ ሜትሮች ጉዞ በኃላ የካራካስ ወደብ ወደ ሆነው 'ላጉዌራ' መድረስ ቻሉ፤ ወደ ወደቡ እንደተጠጉም ካፒቴኑ አንድ ነጭ ሻሽ በማንሳት ፖሊሶችን እርዳታ ለመጠየቅ ከፍ አድርጎ ማውለብለብ ጀመረ፡፡ ብዙም ሳይቆይ የቬንዜዌላ ባንዲራ ያለበት ፓትሮል መኪና እየከነፈ ወደ እነሱ ሲመጣ ተመለከቱ፤ ይሄኔ በፀሀይዋ ንዳድ እና በንፋስ ግርፋት የወየበው ፊታቸው በአንዴ ፈካ. . .እርግጥ ነው ቬንዜዌላ ደርሰዋል!! በእዚህም አሸናፊዎች ናቸው፡፡

ሪታ ከክብደቷ ላይ አስር ኪሎ ከመቀነስ በስተቀር ምንም የተለየ ድካምም ሆነ ህመም አይታይባትም፤ በርግጥ ስላልደከማት አይደለም ግቧን ስለመታች ከመነጨ ደስታ ድካሙን ስለረሳችው እንጂ. . .ለእርሷ በዛ ሰዓት ትልቁ ቁም ነገር ቬንዙዌላ መድረስ፡ነው፤ እሱን ደግሞ አሳክታዋለች፡፡ወደቡ ላይ ከደረሱ ከሰዓታት በኂላ ምንም እንኳን አንዳቸውም መታወቂያ ወይም የይለፍ ወረቀት ባይዙም ፖሊሶቹ ግን ወደ ሀገሪቷ እንዲገቡ ከፈቀዱላቸው በኃላ "መታወቂያ ከጊዜ በኂላ ይሰጣቸዋል" አላቸው አንዱ ፖሊስ ከመሀል ከተንጓዦቹ መካከል ሁለቱ በጠና ታመው ስለነበር ወዲያውኑ ወደ ሆስፒታል እንዲወሰዱ ተደረገ፤ የተቀሩት ደግሞ ልብስ፣ ምግብ እና መጠለያ ሰጥተዋቸው እራሳቸውን እንዲያደራጁ ጥሩ እድል ከፈቱላቸው፡፡ ከቀናቶች በኃላም ሁሉም በየፊናው ተበታትኖ የራሱን ህይወት መምራት ጀመሮ ነበር፡፡ ይህ እንግዲህ በአጭሩ የእኔ ልዕልት ሪታ ታሪክ ነው፡፡

ይቺ ሴት ታድያ በቅዱስ ዮሴፍ ወህኒ ቤት ውስጥ ብቻዬን በምቆዝምበት ወቅት በምናቤ እየተመላለሰች፤ ለብቻዬ እያስወራችኝ ሰላም የምትሰጠኝ ሴት

ነች፡፡ ያኔ በአካል ባለውቃትም ዛሬ ግን አግኝቻታለሁ፤ ስትፈጠርም ጀምራ ለእኔ ተብላ የተሰራች ስለሆነች ፈጣሪ አስቀድሞ በሰመመን አሳየኝ እና ጊዜው ሲደርስ የእኔ አረጋት፡፡ እንዴት ግን ብላችሁ እንዳጠይቁኝ፡፡ እሱን የማውቀው እኔ ብቻ ነኝ፡፡ ምክንያቱም እሷ የህልሜ አለም እውነታ ነች! ሪታ የሰቆቃው አለም ነፃነቴ መሆኗን የሚረዳው የእኔ ልብ ብቻ ነው!! ለማንኛውም ከእዚህ በፊት ሪታ ወደ ቬንዜዌላ የመጣቸው አምልጣ ነው ያልኩት ሀገሯ ላይ የደረሰባትን ኪሳራ ሽሽት ተሰዳ ስለመጣች እንደሆነ የተግባባን ይመስለኛል፡፡ ሆኖም ግን የቬንዜዌላ ሰዎች ሲበዛ ቅን ስለሆኑ እኔን ያለ መታወቂያ እንደተቀበሉኝ እነሱንም በእንኳን ደህና መጣችሁ መንፈስ ነው የተቀበሏቸው፡፡

በሆቴል ቬራ ክሩዝ ከሪታዬ ጋር ለሶስት ወራቶች ስቆይ ፍቅሬን እና ሰላሜን የሚያደፈርስ አንዳችም እንከን አላጋጠመኝም ነበር፡፡ አንድ ቀን ግን ማንነቱን ያላወቅሁት ሰው በሪችሞንድ የምርምር እና ጥናት ድርጅት ውስጥ በተቆጣጣሪነት እንደምሰራ ለፖሊሶች ጥቆማ ስለሰጠብኝ በቀጥታ ወደ ቤት መጥተው ይዘውኝ ሄዱ፤ ከዛም ነገሩ እስኪጣራ በሚል ማራካይቦ የእስረኞች ማረፍያ ውስጥ ከተቱኝ፡፡ በዛ ሰውዬ ምክንያት መታሰሬ ሪታ ስለእኔ የማታውቀው ነገር እንዳለ ፍንጭ ሰጣት፡፡ ፖሊሶቹም ስለ እኔ የሚያትት የኢንተርፖል መረጃ ስለነበራቸው የደበቋትን የወንጀል ታሪኬን በእነሱ በኩል ማወቅ ቻለች፡፡ እንደዛም ቢሆን ግን ሪታ ጥላኝ አልጠፋችም፤ ማረፍያ ቤት በነበርኩበት ሰዓት የምትችለውን ሁሉ ከማድረግ አልተቆጠበችም፤ ጠበቃም ቀጥራልኝ ከሁለት ሳምንት እስራት በኃላ ነፃ መሆኔ ስለተረጋገጠ እንድለቀቅ ተደረገ፡፡ ሪታ ምንም እንኳን መለቀቄ ቢያስደስታትም እኔ ደብቄያት ፖሊሶች በነገሯት ድብቅ ታሪኬ ውስጧ እንደተረበሸ ያስታውቃል፡፡

ከማረፍያ ቤቱ ይዛኝ ስትወጣ እንደተረበሸች ከፊቷ ላይ ያስታውቅ ነበር፡፡ በፊት ስለእኔ የነበራት አመለካከት አሁን ላይ እንደተበረዘ ገብቶኛል፤ ውስጧን ፍርሀት እንደወረረው አልጠራጠርም፡፡ከእንደ እኔ አይነት ወንጀለኛ ጋር መቀጠል ይኑርባት አይኑርባት ለራሷ ግራ እንደገባት ያስታውቃል፡፡ ሁሉም ነገር መበላሸቱን እና እንዴት ማረቅ እንዳለብኝ ከውስጤ ጋር እየተሟገትኩ እያለሁ "ለምንድነው የዋሸኸኝ?" የሚለው የሪታ ድምፅ አነቃኝ፡፡ በፍፁም እሷን ማጣት እንደማይኖርብኝ አውቀዋለሁ፤ ስለዚህ የተበታተነ ስሜቴን ሰብስቤ እሷን ለማሳመን ያለኝን እድል ሁሉ መጠቀም እንደሚኖርብኝ ወሰንኩ፡፡

"ሪታ የምነግርሽን ነገር ልታምኚኝ ይገባል፤ አንቺን ሳይሽ የተሰማኝ ስሜት ሲበዛ ጥልቅ ነው። ሳለመንገሬ ምንም ምክንያት የለኝም። ሙሉ ታሪኬን ሳለማውራት የፈለኩት በጣም ስለምወድሽ እና ስለማፈቅርሽ በጭራሽ ላጣሽ ስለማልፈልግ ብቻ ነው"

"ዋሸኸኝ!! ዋሸኸኝ!! እኔ ደግሞ ግብረ ገብ ያለህ ሰው መስለኸኝ" አለች እያለቀሰች

"እሺ ግብረ ገብ የጎደለው ሰው ነበርኩ እንበል... አሁን ግን ግብረ ገብ ያለው ሰው መሆን አትችልም ያለው ማነው? እንደማንኛውም ሰው ደስተኛ ኑሮ ለመምራት እና ጥሩ ለመሆን ሁለተኛ እድል ሊሰጠኝ ይገባል። ሪታ መርሳት የሌለብሽ ለአስራ አራት አመታት በእነዛ አደገኛ እስር ቤቶች ውስጥ ስንገላታ ኖርያለሁ። ይውልሽ እኔ አንቺን የማፈቅርሽ በፊት በነበረኝ ልብ ሳይሆን አሁን ባለኝ ልቤ ነው እንደነገርኩሽ ብቸኛው እንዳልነግርሽ ያደረገኝ ምክንያቴ አጣታለሁ የሚለው ስጋት ወጥሮ ስለያዘኝ ነው። ከእዚህ በፊት የኖርኩት በተጭበረበረ አለም ውስጥ ነው። እመኚኝ ካንቺ ጋር ግን መኖር የምፈልገው ከዛ በተቃራኒው በሆነ አለም ውስጥ ነው። እጅ ለእጅ ተያይዘን የምንሄድበት መንገድ ብሩህ እና ሰላም የሰፈነበት እንደሆነ ይታየኛል። ለስቃይ በተዳረገው በአባቴ ስም አሁንም ደግሜ እምልልሻለሁ የነገርኩሽ ሁሉ የእውነቴን ነው" እንዳልኳት ያላሰብኩት እንባ በአይኔ ላይ ግጥም አለ... አንገቴን እንደደፋው ሊወርድ የተዘጋጀውን እንባ ለቀቅሁት

"የእውነት ከልብህ ነው ግን?"

እጆቿን በእጆቼ እንደያዝኩ ሳግ በተቀላቀለበት ድምፅ "አዎ ከልቤ ነው ያለፈው ታሪኬ ለእኔም ላንቺም አይጠቅምም... ሁለታችንም ስለ ዛሬ እና ስለ ወደፊቱ ማሰብ ነው የሚበጀን"

" ይህን እንዳልኳት የፍረሀት ስሜቷ በአንዴ እንደጉም ተኖ ጠፋ፤ በፍቅር አይን እየተመለከተችኝ እና ከአይኖቹ ወርደው ጉንጮቼን ያራሱትን የእንባ ዘለላዎች እየጠረገችልኝ "ሄነሪ በቃ አታልቅስ... ሲመስለኝ የወደፊት እጣ ፈንታችንን እንደ አዲስ መጀመር ይኖርብናል። ነገር ግን አንድ ቃል እንድትገባልኝ የምፈልገው ነገር አለ። ከእዚህ በኋላ ምንም አይነት መጥፎ ድርጊት ላለመፈፀም እና ምንም ቢፈጠር እንደማትወሽኝ ቃል ግባልኝ። ያ

ከሆነ ስላማችንን የሚያደፈርስ ነገር ከአሁን በኋላ አይኖርም" አለች እኔም የማያዳግም ቃሌን በሙሉ እምነት ሰጠኋት።

ሊዘም የነበረውን ፍቅራችንን አቃንተን እጅ ለእጅ እንደተያያዝን ወደ ቤታችን አመራን፤ በእውነት እቺን ለመሰለች ሴት እኔነቴን ምንም ሳልደብቅ መናገር እንደነበረብኝ ሳስብ መወቀስ እንደሚገባኝ ተረዳሁ። ስለዚህ ያልነገርኳትን ድብቅ የህይወት ታሪኬን እንዳለ ተናዘዝኩላት። ከ1931 ዓ.ም ጀምሮ በአእምሮዬ ስለታነፀው የብቀላ እቅዴ፣ እሱን ለመፈፀም ያለማቋረጥ ያሰብኩባቸውን ዓመታት፣ የበቀል ውጥኔን ለማየት የገባሁበትን ወጥመድ ምንም ሳላስቀር ከ ሀ እስከ ፐ ሁሉንም ከነገርኳት በኋላ ለእሷ የሚገባትን ብስራት አበሰርኳት

"ሪታዬ ምን ያህል እንደማፈቅርሽ ምስክር እንዲሆንሽ ከዛሬ ጀምሮ የብቀላ እቅዴን ትቸዋለሁ። ምንም እንኳን እነዛ በውሸት ወንጅለው ለስቃይ የዳረጉኝ ፖሊሶች፣ ዓቃቤ ህጉ እና ምስክሮቹ ሞት የሚገባቸው ቢሆኑም ከአንቺ ሊበልጡ ስላልቻሉ ምሬያቸዋለሁ። በርግጥ የስቃይን ፅዋ ላስጎነጬኝ ፍጥረቶች ቅጣት መስጠት ነበረብኝ። ነገር ግን ለስቃዬ ማካካሻ አንቺን ስለሰጠኝ ሁሉን ነገር ለመተው እገደዳለሁ። አንቺ በህይወቴ ገብተሽ ከድሮ ማንነቴን ገፈሽ በመጣል አዲስ ማንነት አላብሰሽኛል" አልኳት

ሪታ በተናገርኳቸው ንግግሮች ፊቷ እየፈካ "አባትህስ… ያንተን እርዳታ የሚፈልግ እስከሆነ ድረስ ልትፅፍለት ይገባል"

"ከ1933 ጀምሮ ስለመኖሩ እንኳን መረጃው የለኝም። እሱም የት ልድረስ፣ ምን ልሁን የሚያውቀው ነገር የለም። በርግጥ ላለመገናኘታችን መንስኤው እኔ ነኝ። ምክንያቱም እስር ቤት እያለሁ በምፅፍለት ደብዳቤ የተነሳ አባቴ ላይ ሊፈጥር የሚችለውን መሳቀቅ ሳስበው አለመፃፍን መረጥኩ። በእኔ እድሜ ልክ መታሰር ልቡ መሰበሩ እንዳለ ሆኖ በምፅፍለት ደብዳቤዎች ደግሞ የበለጠ ማድማት አልፈለኩም። ስለዚህ ለእህቴ ሾኒ ከእዚህ በኋላ ከእኔ ምንም አይነት ደብዳቤ እንደማይደርሳቸው እና እነሱም ወደ እኔ መልዕክት እንዳይልኩ የሚገልፅ ፅሁፍ ላኩላት። ከዛ በኋላ ከየትኛውም ቤተሰቤ ጋር ተገናኝቼ አላውቅም" አልኳት

"እሄ እኮ ያለፈ ታሪክህ ነው…አሁን ግን ለአባትህ መፃፍ አለብህ"

"እሺ አንቺ ካልሽ ነገ እፅፍለታለሁ"

"አይቻልም አሁን ነው መፃፍ ያለብህ"

ወደ ፈረንሳይ የሚላክ ረጅም ደብዳቤ ፃፍኩ፤ ደብዳቤውን ስፅፈው የእሱን ስሜት ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን በሙሉ አስወግጄ የገጠሙኝን መልካም ሁነቶች እና አሁን ያለሁበትን ደረጃ አካትቼ ነው። ነገር ግን የላኳቸው ደብዳቤዎች ከጥቂት ቀናት በኋላ ተመልሰው መጡ፤ ምክንያቱ ደግሞ አባቴ አድራሻውን ሳይተው ወደ ሌላ ቦታ በመሄዱ ነው።

"በፈጣሪ!!" አልኩ ደብዳቤዎቹን ተመልሰው እጄ ላይ ሳያቸው። ምን አልባትም እኮ በእኔ የተነሳ የአካባቢው ሰዎች አላስቀምጥ ሲሉት ይሆናል ሀፍረቱን ተከናንቦ ለመሸሽ የመረጠው። የአባቴ መጥፋት እንዳሳሰበኝ እንደገባት ነበር ሪታ ፈጣን ውሳኔ የወሰነችው"

"ነገሮችን ቦታ ቦታ አስይዤ የአንተን አባት ለመፈለግ ወደ ፈረንሳይ መሄዶ አይቀርም... እና ደግሞ ይሄ የአፈር ምርምር እና ጥናት ውስጥ የምትሰራውን ስራ ማቆም ይኖርብሀል። ስራው አደገኛ ነው። ከሄድኩ በኋላም እንግዲህ እኔ እስክመለስ ድረስ ሆቴሉን የመቆጣጠር ሙሉ ሀላፊነቱ ያንተ ነው"

ሪታ ለእኔ ይሄን ያህል መስዋትነት ልትከፍል መነሳቷን ሳይ በእሷ መፈቀሬ ከመቼውም ጊዜ በላይ ካገኘሁት ደስታ እንደሚልቅ ጥርጥር የለውም።ብቻዋን ወደ ፈረንሳይ ለመሄድ ከማሰቧ በላይ ያስገረመኝ ሆቴሉን ለእኔ ጥላ ለመሄድ ማሰቧ ነው። . . .ሪታ ሆቴሉን ተከራየችው እንጂ የግሏ አልነበረም። ስለዚህ ሆቴሉ ከእጃችን እንዳይወጣ ለማድረግ ያለን አማራጭ መግዛት ነው። በዚህ ሰዓት ግን አንድን ንብረት በጥሩ መንገድ ተጠቅሞ ለማፍራት ምን ያህል ፈተና እንዳለሁ ተረድቻለሁ!

ወደ ሪችሞንድ ድርጅት ሄጄ ከስራ እንዲያሰናብቱኝ በጠየኩት መሰረት ስድስት ሺህ ቦሊቫር ሰጥተው ሸኙኝ። ያንን ስድስት ሺህ ቦሊቫር ሪታ አጠራቅማው ከነበረው ብር ጋር አዳምረን የሆቴሉን ግማሽ ዋጋ ከፈልን፤ ቀሪውንም ገንዘብ ለመክፈል ቀን ከለሊት መፍጋቱን ተያያዝነው። እሷም ሆነች እኔ ደከመን ሳንል ቢያንስ ለአስራ ስምንት ሰዓታት ቆመን እንሰራ ነበር፤ አንዳንዴም ገፋ አርገን የምንሰራበት ጊዜ አለ። የሚገዙ እቃዎችን በመግዛት፣

ምግብ በማብሰል እንግዶችን በመቀበል ቀኑን ሙሉ በስራ ነው የምናሳልፈው፤ ምሽቱንም እንዲሁ ደንበኞቻችንን ፈገግታ በተላበሰ አቀራረብ በማስተናገድ እናሳልፈዋለን፡፡

በፍጥነት እዳችንን ከፍሎ ለመጨረስ ተጨማሪ ስራ መስራት እንዳለብን ስለተረዳሁ ጃኬት እና ቲሸርቶች በባለ ሁለት ጎማ ጋሪ ላይ በማድረግ ከተማ ውስጥ በሚገኘው 'ባራት' የገቢያ ማዕከል ውስጥ መሸጥ ጀመርኩ፡፡ ጃኬት እና ቲሸርቶቹን የማወጣቸው ልብስ ከሚያመርቱ ድርጅቶች ሲሆን ተረፈ ምርት ስለሆነ በቅናሽ ነበር የሚሸጡልኝ... ምንም እንኳን እንደሌሎቹ ገበያ ላይ እንደሚሸጡት ልብሶች ጠንካራ ባይሆኑም ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች ግን ጥሩ አማራጭ ስለሆነ ገዢ አይጠፋም ነበር፡፡ አንድ ቀን እንደውም የቲሸርቱን ጥንካሬ ለገዢ ለማሳየት ጎን እና ጎኑን ይዤ ስስበው ተተርትሮ አዋርዶኝ ነበር፤ የዛን ቀን ብዙም ሳልሸጥ ነው የተመለስኩት፡፡ ከጠዋት እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ ልብስ በመሸጥ ካሳለፍኩ በኋላ ሁሌም እንደማደርገው ወደ ሆቴሉ በመመለስ የማስተናገድ ስራዬን እቀጥላለሁ፡፡

ባራት የገቢያ ማዕከል ለማራካይቦ ወሳኝ የንግድ ማሳለጫ ቦታ ነው፡፡ የገቢያ ማዕከሉ ከተማዋ ውስጥ በሚገኘው ቤተክርስትያን አቅራብያ የሚገኝ ሲሆን ለአይን እንዲማርክ ተደርጎ ነው የተሰራው፤ በውስጡም ለሰው ልጅ ያስፈልጋሉ ተብለው የሚገመቱ ነገሮችን በሙሉ አካቶ ይዟል፡፡ የባህር አሳዎች፣ የአሳማ ስጋ፣ ከሚበሩ አእዋፍ እስከ በደረታቸው እስከሚሳቡት እንስሶች ሁሉም በእዚህ ገቢያ ውስጥ ይገኛሉ፤ ሌላው ቀርቶ ገበያተኛውን ዘና የሚያደርጉ የተለያዩ ጨዋታዎች አካቶ ይዟል፡፡ በዛ ላይ እዚህ የገቢያ ማዕከል ውስጥ የማይመጣ የሰው ዘር የለም፡፡ አይናቸውን የጨፈኑ ከሚመስሉ ቻይናውያን እስከ ክብ አይን እስካለው ጥቁር ድረስ እቃ ለመግዛት ፈልጎ ባራት የገብያ ማዕከል ውስጥ ሳይገባ አያድርም

እኔም ሆንኩ ሪታ ማራካይቦን ወደናታል፡፡ ቢሆንም ግን የአየር ንብረቷ ሞቃታማ ከሚባሉት ከተሞች መሀል ያስመድባታል፡፡ ልክ እንደሌሎቹ የቬንዜዌላ ከተሞች ሁሉ ማራካይቦም ህዝቦቿ በፍቅር፣ በደስታ እና በመተሳሰብ የሚኖሩባት ከተማ ነች፡፡ የአወራር ዘያቸው ሙዚቃ የመሰለ ሲሆን ሲበዛ ደጎች ናቸው፡፡ የስፓኒሽ የዘር ግንድ በጥቂቱ ቢኖርባቸውም የህንዶች ደም ግን በአጠቃላይ ሰውነታቸው ውስጥ አለ ማለት ይቻላል፡፡ ወንዶቹ

ቁጡነት ቢነበብባቸውም ሲቀርቧቸው ግን ለጓደኝነት የሚመረጡ አይነት ሰዎች ናቸው፡፡ ሴቶቹም ትንንሽዬ ሆነው ቆንጆዎች ሲሆኑ ለባሎቻቸው ሲበዛ ታማኞች ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ማራካይቦ ሁሌም እንቅስቃሴ የማይጠፋባት የንግድ ከተማ ነች ማለት ይቻላል፡፡ የባራት የገቢያ ማዕከል ከሚያስተናግዳቸው ደንበኞቹ በተጨማሪ በአቅራቢያው ባሉ ጎዳናዎች ላይ የህገ ወጥ ንግድ ሞቅ ባለ መልኩ ያካሄድባቸዋል፡፡ ደብቀው የሚሸጡትን መጠጥ እና ሲጋራ በመንገዱ የሚያልፍ ሰው እንዲገዛቸው ከመጠየቅ አይቦዝኑም፡፡ የሚገርመው ደግሞ ይህንን ህገ ወጥ ንግድ የሚያከናውኑት ፖሊስ በአቅራቢያቸው እያለ ነው፡፡ ለነገሩ ፖሊሶቹ ትንፍሽ እንዳሉ ለማድረግ አንድ ጠርሙስ የፈረንሳይ ኮኛክ ወይም አንድ ፓኮ ሲጋራ በቂ ነበር፡፡

ሆቴል ማስተዳደር በጣም ከባድ ስራ ነው፡፡ ሪታ በመጀመርያ ወደ እዚህ ሀገር መጥታ ሆቴሉን ስትከፍ ከሀገሪቱ ምግብ አበላል ስርዓት ጋር ፍፁም ተቃራኒ የሆነ ስልት ነበር ይዛ የመጣችው፤ የቬንዚዌላ ሰዎች ደግሞ በዛ አድርገው ካልበሉ ደስ አይላቸውም፡፡ የበቆሎ ቂጣ ከተጠበሰ ወይም ከተቀቀለ የአሳማ ስጋ ጋር ከዛ በተጨማሪ እንቁላል፤ ክሬም ለቁርስ ብቻ የሚመገቡ ነው፡፡ ታድያ ሪታ ምግብ ቤት ስትከፍት ከላይ የጠቀስኳቸውን የምግብ ዝርዝሮች ትታ በምትኩ "ለቁርስ. . .ቡና ወይም ወተት ከዳቦ ጋር" የሚል ፅሁፍ ለጠፈች፤ በእዚህም ምክንያት ሪታ ሳትመጣ በፊት በሆቴሉ ይጠቀም ከነበረው ደንበኛ በግማሽ ሊቀንስ ቻለ፡፡

በእዚህ መሀል ነው እንግዲህ እኔ የተከሰትኩት፡፡ ሪታ በርግጥ ሌሎች አማራጮችን ለመጠቀም አስባ ነበረ፤ ነገር ግን የእኔ መምጣት ሀሳቧን ቀይራ ሌላ ውሳኔ እንድትወስን አደረጋት፤ ቁጭ ብለን ለመወያየት ለሆቴሉ የሚበጀንን አዲስ መመርያ አረቀቅን

*መመርያ አንድ፡- የምግብ ዋጋችንን እጥፍ ማድረግ*

*መመርያ ሁለት፡- የፈረንሳይ ምግቦችን ማካተት*

*መመርያ ሶስት፡- የአየር ማቀዝቀዣ በሁሉም የሆቴሉ ክፍሎች ላይ መግጠም*

እነዚህ ለውጦች ለሆቴላችን እድገት ጉልህ አስተዋፅኦ ነበራቸው። በተለይ በሁሉም ክፍሎች ላይ ማቀዝቀዣ በመኖሩ ደንበኞቻችን የበለጠ ወደ እኛ እንዲቀርቡ አድርጓል። ከጊዜ ወደ ጊዜ የደንበኞቻችንም ቁጥር እያደገ መሄድ ጀመረ። በአጭር ጊዜ ውስጥ የንግድ አለም ውስጥ ያሉ ሰዎች ለማረፍ የሚመርጡት ሆቴል ለመሆን በቃ። የሆነ ወቅት ላይ አንድ 'ባስካዊ' እኛ ሆቴል አረፈ። (ባስካውያን በፈረንሳይ እና ስፔን የሚኖሩ የዘር ግንዳቸው ከየት እንደሆነ የማይታወቅ ማህበረሰቦች ናቸው) ይህ ባስካዊ ፔሩ ውስጥ የሚመረቱ ሰዓቶችን የሚሸጥ ነጋዴ ነው፤ ሰዓቶቹን የሚሸጠው በችርቻሮ መግዛት ለሚፈልጉ ሰዎች ብቻ ሲሆን ቤታቸው ድረስ እንዲያደርስላቸው ለሚፈልጉም ደንበኞችም ሂሳብ ጨምሮ ያሉበት ቦታ ድረስ በመሄድ ያደርስላቸዋል። የእሱ ሁነኛ ደንበኞች በመኪና ነዳጅ ማውጫ ውስጥ የሚሰሩት ሰራተኞች ነበሩ። ሆቴላችን ከምቾቱ ውጪ ጥብቅ ክትትል ያልተለየው ቢሆንም ይህ ባስካዊ ግን የተከራየውን ክፍል በር በእራሱ ወጪ ሶስት ተጨማሪ ቁልፎች እንዲኖሩት አድርጓል፤ እንደዛ ቢያደርግም ከክፍሉ ውስጥ ሰዓቶቹን ከመሰረቅ ግን አልዳነም ነበር። ሰውየው እራሱ ሰዓት እየጠፋው እንደሆነ ያወቀው ዘግይቶ ነበር። የሚገርመው ግን የሰዓቶቹ ሌባ ሴት መሆኗ ነው፤ ለዛውም የገዛ ሰራተኛችን ቦቺሊቲ!! ልክ እንደ ፖሊስ ውሻ ድምፅ ሳታሰማ በመግባት ነበር እሱ በተኛበት ሰዓቶቹን ይዛ የምትወጣው፤ የእውነት አደገኛ ሌባ ነች!!

የዝርፍያ ወንጀል የተፈፀመበት ባስካዊ መሰረቁ ሲገባው እሳት ጎርሶ እሳት ለብሶ ነበር ወደ እኔ የመጣው

"በጣም የሚያበሳጭ ድርጊት ነው የተፈፀመብኝ... እንዴት እንደዚህ ታደርጋላችሁ?"

"ይቅርታ የእኔ ጌታ... እኔ ያሰረቁህ አስመሰልከው እኮ" አልኩት በተረጋጋ ስሜት

"ምን ይታወቃል... አንተ ባትሰርቀውም ልጅቷ እንድትዘርፍ ያስለጠንካት አንተ ትሆናለህ" አለኝ

ንግግሩ ከልቤ ነበር እንድስቅ ያረገኝ፤ የእሱን ሰዓቶች ለማስረቅ ቦቺሊቲን ሳሰለጥን እያሰብኩ ሳቄን መቆጣጠር አቃተኝ። እንደምንም እራሴን ከሰበሰብኩ በኋላ "ትሰማኛለህ የእኔ ወንድም... እኔ የአንተን ልቅምቃሚ ሰዓቶች

አይደለም አስጠኝቼ ላስርቅ ይቅርና በአይኔ ማየት እንኳን አልፈልግም ስለዚህ ይህን ተገንዝበህ አርፈህ የምትቀመጥ ከሆነ ተቀመጥ ከዚያ ውጪ ግን ሆቴላችን ለቀህ መውጣት ትችላለህ" ብዬ ስላስደነበርኩት እሱም ነገሩን ወዲያው መተውን ነበር የመረጠው፡፡

እኛ ሆቴል ውስጥ ከሁሉም አቅጣጫ የሚመጡ እንግዶች ያርፉበታል፡፡ ማራካይቦ በእንደዚህ አይነት ነገር ችግር የለባትም፤ ሁሉንም በእኩልነት ታስተናግዳለች፡፡ በእዚህም የተነሳ የመኝታ ክፍል ማግኘት አስቸጋሪ ነው. . .የሆነ ጊዜ የኔፐልስ ዜጎች በሆቴላችን ለማረፍ ወደ እኛ መጡ፡፡ እነዚህ የኔፐልስ ዜጎች አጭበርባሪ ነጋዴዎች ሲሆኑ አሁን በመሸጥ ላይ ያሉት ያልተሰፉ ብትን ጨርቆችን ነው፡፡ ከአጭበርባሪነታቸው የተነሳ ጨርቆቹን የሚሸጡት ሁለት ልብስ የሚወጣውን ብትን ጨርቅ አራት ልብስ ይወጣዋል ብለው በማሳመን ይህንን ምስኪን ህዝብ ይበዘብዙት ነበር፡፡ እንደ ሰዓት ነጋዴው ሁሉ የእነሱም አብዛኛው ደንበኞች በዘይት ማውጫዎቹ ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች ናቸው፡፡ እነዚህ የኔፐልስ ዜጎች ወደ ሆቴላችን ሲመጡ በሆቴላችን ያሉት ሁሉም የማደርያ ክፍሎች ተይዘው ስለነበር የነበራቸው አማራጭ በሆቴላችን መናፈሻ ውስጥ ማደር አለበለዚያ ሌላ ቦታ መሄድ ነበር፡፡ እነሱም ብዙ ቦታ ፈልገው አጥተው ስለነበር እዚሁ እኛው መናፈሻ ውስጥ ለማደር አላቅማሙም ነበር፡፡ ሁሌም ከሰዓት ከሰዓት ወደ ሆቴላችን ይመጡና ገላቸውን ተለቃልቀው ምግብ ከወሰዱ በኋላ ወዲያው ነበር ወደስራቸው የሚሄዱት፡፡ ለፓስታ ያላቸው ፍቅር የተለየ ስለሆነ የኔፐልስን የፓስታ አሰራር እንድማር መንገድ ከፍቶልኛል፡፡ እነዚህ ኔፐልሳውያን ምንም እንኳን አጭበርባሪዎች ቢሆኑም ገንዘብ ለማውጣት ግን ችግር አልነበረባቸውም፡፡

ሁሌም ምሽት ላይ ሪታ ከሁለት ሰራተኞች ጋር በመሆን የብረት አልጋዎቹን ወስዳ መናፈሻ ውስጥ ትዘረጋላቸዋለች፡፡ በክፍያ በኩል በሆቴሉ ውስጥ ከሚያድሩ ደንበኞች እኩል ነው የሚከፍሉት፡፡ በእርግጥ ሆቴሉ ውስጥ ከሚያድሩት ደንበኞች እኩል በመክፈላቸው መነጫነጫቸው አልቀረም... ቢሆንም ግን አማራጭ ስለሌላቸው ሳይወዱ በግዳቸው ይከፍላሉ፡፡ የመጀመርያ ቀን ሂሳብ ልቀበላቸው ስሄድ ከመሀከላቸው አንዱ " የመኝታ ክፍል ከያዙት እኩል ስንከፍል ትንሽ አይከብድም?" አለኝ

"አይከብድም"

"እንዴት... እነሱ እኮ ቢያንስ ምቾታቸው ተጠብቆላቸው ነው የሚያድሩት?"

"አዎ ልክ ናችሁ...ነገር ግን ማታ ማታ አልጋ እዚህ ድረስ ማውጣቱ፤ ከዛ ማስተካከሉ፤ ጠዋት ስትነሱ ደግሞ እንደገና መመለሱ ከባድ ስራ ነው. . .ከዚህ አንፃር ስንመለከተው እንደውም ዋጋችን ተመጣጣኝ ነው" ብዬ ቁርጥ ያለ መልስ ሰጠኋቸው፤ ከዛ በኋላ ለመነጫነጭ ቢሞክሩም ምላሼ ተመሳሳይ ስለሆነ ችላ ማለቱን መርጠዋል። ለነገሩ ከሚያገኙት ገቢ አንፃር ለእኛ የሚከፍሉን ገንዘብ እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም። ቢሆንም ግን ለመኝታ የሚያወጡት ገንዘብ ሁሌም ቢሆን ተውጦላቸው አያውቁም። አንድ ቀን ግን በተኙበት ዝናብ በላያቸው ላይ ሲወርድ ከልክ በላይ ነበር የተበሳጩት። እኔም የስራው ባህሪ ስለሆነ አረጋግቼ ምግብ ቤት ውስጥ ገብተው እንዲያድሩ አደረኩ።

* * * * * * * * *

የሆቴሉ በረንዳ ላይ ቁጭ ብዬ መፅሀፍ እያነበብኩ እንዳለሁ አንዲት ቡና ቤት ያላት ሴት እኔን ፈልጋ ወደ ሆቴላችን መጣች። ከማራካይቦ በአምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኝ 'ላ ካቤዛ ዲ ቶሮ' በምትባል ቦታ ላይ ትልቅ ቡና ቤት እንዳላት ነገረችኝ።

"ኢልኖሬ እባላለሁ" አለች ጣደፍ ጣደፍ እያለች

"እሺ የእኔ እመቤት... ምን ልርዳሽ?"

"ላ ካቤዛ ዲቶር ላይ 'ቴቤሪ-ታቦሪ' የሚባል ቡና ቤት አለኝ። በቡና ቤቱ ውስጥ ከመቶ ሀያ በላይ ሴተኛ አዳሪዎች አሉኝ። እነዚህ ሴተኛ አዳሪዎች ምሽት ላይ ብቻ ነው ስራቸውን የሚሰሩት"

"በጣም ጥሩ... ታድያ እኔ ምን ልተባበርሽ?"

"ምን መሰለህ... ከፈረንሳይ የመጡ አንዳንድ ሰራተኞቼ ከእዛ ቤት መውጣት ይፈልጋሉ" አለችኝ

"ለምን?"

"በቡና ቤት ውስጥ ሃያ አራት ሰዓት ማሳለፍ አይፈልጉም… ከስራ ሰዓት ውጪ የፈለጉትን ምግብ የሚያገኙበት እና የሚያርፉበት ሆቴል እንድፈልግላቸው ስለጠየቁኝ ነው ወደዚህ የመጣሁት"

እንዳጋጣሚ ሆኖ ኤልኖሬ ወደእኛ ስትመጣ በሆቴላችን ከነበሩት ክፍሎች የተወሰኑት ተለቀው ስለነበር ሌላ ደንበኛ ለመቀበል በዝግጅት ላይ እያለን ነበር የመጣችው

ኢሊኖር ወፍራም ሴት ብትሆንም ብልህ እና ቀልጣፋ መሆኗ ከነገረ ስራዋ ያስታውቃል። በኢሊኖር ሀሳብ ተስማምቼ ውል ከፈፀምን በኃላ ከፈረንሳይ እና ከጣልያን የመጡ ሴተኛ አዳሪዎች ወደ እኛ መጡ፤ ከመደበኛው ክፍያ የአስር በሊቮር ጭማሪ አድርገን ነበር ያስገባናቸው፤ እነሱ ግን ጭማሬውን ከቁብም አልቆጠሩትም፤ በቬራ ክሩዝ ከፈረንሳይ ሰዎች ጋር መቆየታቸው ብቻ ሳያስደስታቸው አልቀረም።

ሪታ ለእነዚህ ሴቶች ጠንከር ያለ ህግ አውጥታላቸዋለች። ምንም እንኳን ሁሉም ሴቶች ወጣት እና ቆንጃጅት ቢሆኑም አንዳቸውም ቢሆን ግን ወደ ሆቴላችን ወንድ ይዘው መምጣት አይችሉም ነበር፤ ሌላው ቀርቶ በሆቴሉ አካባቢ እራሱ ወንድ መቅጠር እንደማይፈቀድላቸው አስረድታቸዋለች። በእዚህም የተነሳ ሴቶቹ በቡና ቤታችን ውስጥ ሲንቀሳቀሱ ማንም ሴተኛ አዳሪ እንደሆኑ አይገምትም። ምሽት ላይ ወደ ኤሊኖር ቡና ቤት የሚወስዳቸው ታክሲ ሲመጣ ግን አለባበሳቸው፣ የፊት ገፅታቸው፣ ፀጉራቸው ሁሉም ይቀየራል።

በሚያስገርሙ እና በሚያሳዝኑ ክስተቶች ተሞልተን የተወሰኑ ወራቶችን አሳለፍን፤ ሁሌም ቢሆን በሆቴላችን የሆነ አዲስ ነገር መከሰቱ አይቀርም። ይህም እኛን ዘና ስለሚያደርገን የስራ ጫናው ብዙም አይታወቀንም። እዚህ በሆቴል ቬራ ክሩዝ ያሳለፍናቸው ደስ የሚሉ ጊዜያቶች ናቸው ማለት ቢቻልም ቬንዙዌላ እስከኖርን ድረስ ግን የኢኮኖሚውን እና የፖለቲካውን ቀውስ መጋፈጥ መቻል ግዴታ ነበር።

በ1948 የፖለቲካው ውዝግብ አስቀያሚ ሁኔታ ላይ ደርሷል ማለት ይቻላል። ከ1945 ጀምሮ ፕሬዘዳንት ጋሊጎስ ከባልደረቦቹ ቤታኮርት ጋር በመሆን ሀገሪቷን እየመራ እንደሆነ ይታወቃል። ታድያ ሪታን ከተዋወቅ኷ት ከሶስት ወራት በኋላ ህዳር 13/1948 በጀነራል ሜንደዛ የሚመራ መፈንቅለ መንግስት ለመጀመርያ ጊዜ በፕሬዘዳንት ጋሊኮስ ላይ ተሞክሮ ነበር፤ ነገር ግን ሳይሳካ ሊከሽፍ ችሏል። በእዚህ ሁሉ ውጥንቅጥ መሀል ብንሆንም የእኔ እና የሪታ ፍቅራችንም፣ ስራችንም ሳይቀዘቅዝ የኑሮን ውጣ ውረድ መጋፈጡን ተላምደታል፡

# ምዕራፍ አስራ አንድ

## አባቴ

ሪታ ወደ ፈረንሳይ ለመሄድ ዝግጅቷን አጠናቃለች፡፡አባቴን እንደምታገኘው በሙሉ ልብ ሆና ነው ለመሄድ የተነሳችው፡፡

"በእኔ ተማመን ሄነሪ... አባትህን ይዤው እንደምመለስ እርግጠኛ ሁንብኝ!" ስሸኛት ነበር ይሄን የተናገረችኝ

እኔን ከሆቴሉ ጋር ትታኝ አባቴን ለመፈለግ ወደ ፈረንሰይ አቀናች፡፡ ሆቴሉን የሚቆጣጠር ሌላ አካል ባለመኖሩ ለጊዜው ቲሸርት እና ጃኬቶች መሸጡን ተውኩት፡፡ ሪታ የእኔን አባት ለመፈለግ እስከሄደች ድረስ እኔ ደግሞ አሁን እሰራበት ከነበረው ሀይል ሁለት እጥፍ ጨምሮ በመስራት ላስደስታት እንደሚገባ ከራሴ ጋር ተነጋግሬ ጨርሻለሁ፡፡

ሪታን ከሸኘኋት በኋላ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ለማሰብ ወደ መኝታ ክፍላችን ገብቼ አልጋችን ላይ ጋደም አልኩ፡፡ ሆቴሉን እንዴት አድርጌ እንደማገነው እያሰብኩ በመሀል ሪታ አባቴን ስታገኘው ታወሰኝ፡፡ "እኔ ማለት የልጅህ ሄነሪ ባለቤት ነኝ፡፡ ከዚህ በኋላ እኔም ልጅህ ነኝ፡፡ ወደዚህ ያመጣኝም ምክንያት ልጅህ ሄነሪ በራሱ ጥረት ነፃነቱን አውጆ ቬንዙዌላ ውስጥ ማራካይቦ በምትባል ከተማ ውስጥ ጥሩ ኑሮ እየኖረ ስለሆነ ለዘመናት ሲናፍቅህ የኖረውን አንተን ይዤለት በመሄድ ቁስሉን ለማከም ነው" ስትለው አባቴ የደስታ እንባ እያነባ ተጠምጥሞ ሲያቅፋት በአይነ ህሊናዬ እየሳልኩ በዛው ወደ እንቅልፍ አለም ገባሁ፡፡

ጠዋት ከእንቅልፌ እንደነቃሁ 'ሜት' የተባለውን ፀጉራም ውሻዬን እና ከእስር ቤት ከተለቀቀ ጀምሮ አብሮኝ እንዲሰራ ያደረኩትን 'ካርሊቶስ' የተባለውን

የአስራ ሁለት አመት ልጅ አስከትዬ ወደ ገበያ ሄድኩ። ስጋ፣ አሳ፣ የተላያዩ የአትክልት አይነቶችን እና በሆቴሉ ውስጥ ለእለት የሚያስፈልገኝን ፍጆታ በአንድ ሰዓት ውስጥ ገዝተን ተመለስን። ኩሽና ውስጥ ምግብ የሚያበስሉ ሁለት ሴት ሰራተኞች አሉን። አንደኛዋ የሃያ አራት አመት ልጅ ስትሆን አንደኛዋ ደግሞ የአስራ ስምንት አመት ልጅ ነች። ሁለቱም ቢሆኑ በሙያቸው የሚታሙ አይደሉም። እኔም ከገበያ ተሸክሜው የመጣሁትን እቃ ጠረጴዛው ላይ ሳስቀምጥላቸው በየመልኩ ደርደሮ ለማስቀመጥ ጊዜ አይወስድባቸውም ነበር። ስለዚህ አብረውኝ ያሉትም ሰራተኞች ፈጣን እና ቀልጣፎች ስለሆኑ እንደ እቅዴ ሪታ አባቴን ይዛ ስትመለስ ብዙ ስራ ሰርቼ እጠብቃታለሁ የሚል ግምት አለኝ።

ሪታ ከሄደች በኃላ በሆቴሉ ከማሳልፋቸው ሰዓቶች ውስጥ የሚማርከኝ ጠዋት ከእንቅልፌ እንደተነሳሁ እራሴን አነቃቅቼ ቁርስ እየበላሁ የሚያልፈው ጊዜ ነው። የቁርስ ሰዓቴን እንድወደው ያረገችኝ ደግሞ የምግብ አብሳይዋ ትንሽዬ ልጅ ነች። ሁሌም ለቁርስ የምግብ ጠረጴዛው ላይ ስቀመጥ ህፃኗ ከጎኔ አትጠፋም። ታድያ ይቺ የአራት አመት ልጅ ቁርስ የምትበላው እኔ ካለው ብቻ ነው። እኔም ቁርስ እየበላው ከኮልታፋው አንደበቷ የሚወጡትን ቃላቶች መስማት፣የውሻዬን ቅናት መመልከት፣ የሪታን ተናጋሪ ወፍ በጎጆ ውስጥ እንዳለ ዳቦ ለመብላት ሲሞክር ማየት ሌላም ሌላም ተደምሮ ለቁርስ ሰዓቴ ቦታ እንዲኖረኝ አድርጎኛል።

ሪታ ከሄደች ወር ሲሆናት ነው፤ ፈረንሳይ ለመድረስ ደግሞ ቢበዛ አስራ ስድስት ቀን ቢፈጅባት ነው። ነገር ግን እስካሁን ምንም አይነት ደብዳቤ አላከችልኝም። ፈረንሳይ ገብታ እንዴት ደብዳቤ እንዳላከችልኝ ግልፅ ሊሆንልኝ አልቻለም። "ምን አጋጥሟት ይሆን?" የሚል ሀሳብ ውስጤን አስጨንቆ ይዞኛል። ከእሷ መስማት የምፈልገው አንድ አጭር መልዕክት ነው "አባትህ ደህና ነው... አንተ እስካሁን ሲናፍቅህ እንደኖርከው ሁሉ እሱንም ስትናፍቀው ነው የኖረው... ዛሬ ድረስ የድሮውን  ያህል ይወድሃል" የሚል የምስራች እንድትነግረኝ እመኛለሁ።

ሪታ ፈረንሳይ ትደርሳለች ብዬ ከገመትኩባት እለት አንስቶ ከ አሁን  ፖስታ ይዞ የሚመጣ ሰው አያለሁ በሚል ተስፋ ነበር ቀኖቼን የምገፋው። ቬንዙዌላ ውስጥ ፖስታ የሚያመላልሱ ሰራተኞች የተለየ የደንብ ልብስ የላቸውም፤ ነገር

ግን ሁሉም ፖስታ አመላላሽ ሰራተኞች ወጣቶች ስለሆኑ አንድ ወጣት በሆቴሉ በኩል ባለፈ ቁጥር ልቤ ስለሚመታ ወደ እሱ ተጠግቼ እጁ ላይ ፖስታ መያዝ እና አለመያዙን አረጋግጣለሁ፡፡እንደዛም ሆኖ ግን ፖስታ የያዘ ወጣት የማገኘው ከስንት አንድ ነው፡፡ ፖስታ የያዙትም ቢሆኑም ኩቲያቸው ደረቅ ነው፡፡በበሩ ላይ የሚያልፉት እግረ መንገዳቸውን ወይም በሆቴላችን ክፍል ከያዙት ደንበኞች ለአንዱ የመጣለትን ፖስታ ለማድረስ እንጂ የሪታዬን የምስራች መልዕክት ለእኔ ለመስጠት አልነበረም፡፡

የሪታ ደብዳቤ እስካሁን ወደ እኔ አለመምጣቱ አስጨንቆኛል፡፡ ከሀሳብ ለመራቅ እራሴን በስራ መወጠሩን እንደ አማራጭ ስለወሰድኩት ኩሽና ውስጥ ምግብ በማብሰል ሴቶቹን አግዛቸዋለሁ፤ ከዛ በተጨማሪ በየሰዓቱ የሆቴሉን ክፍሎች እና አካባቢውን እየዞርኩ እቆጣጠራለሁ፤ እንደገና በሆቴሉ ውስጥ የሚስተናገዱ ደንበኞችን ምን እንዳነሰ እና ምን እንደሚፈልጉ እየቀረብኩ እጠይቃለሁ፡፡ የሚሰጡኝንም ሀሳብ በጥሞና በማዳመጥ በጎደለው ለማስተካከል እጥራለሁ፡፡

ነገሮች በእንደዚህ አይነት ሁኔታ እየሄዱ እያሉ አንድ ቀን ትንሹ ካርሊቶስ አደገኛ ስህተት ሰራ፡፡ ለኩሽናው ወለል እና ጠረጴዛ ማፅጃ ፓራፊን (ከነዳጅ የሚገኝ ሳምባ ) እንዲገዛ ልኬው እሱ በስህተት ቤንዚል ገዝቶ መጣ፡፡ ውስጥ ያሉት ሰራተኞችም ፓራፊን ስለመሰላቸው የኩሽናውን ወለል ፈትገው ያፀዱበታል፡፡ ከዛ ምግብ ለማብሰል እሳት ሲያነዱ ኩሽናው በአንዴ ቦግ ብሎ በእሳት ይያያዛል፡፡ ውስጥ ላይ የነበሩት ሁለቱ ሴቶች ከእግር እስከ ሆዳቸው ድረስ በእሳቱ ነበልባል ይቃጠላሉ፡፡ ወደ ኩሽናው ስገባ ቅድሚያ የታየችኝ ትንሽዬዋ ልጅ ስለነበረች እሷን ምንም ሳይነካት ጠረጴዛው ላይ ባገኘሁት ጨርቅ ጠቅልዬ በማውጣት ላተርፋት ችያለሁ፡፡ ሰውነቷ ላይ አይደለም የመቃጠል የጭረት ምልክት እንኳን አይታይባትም ነበር፡፡ የልጅቷ እናት እና ሌላኛዋ ሰራተኛ ግን በእሳቱ ተለብልበው ስለነበር ወደ አንዱ ክፍል አስገብቼ ቃጠሎውን በውሀ ማብረድ ይገባኝ ነበር፡፡ እሳቱ ምን ያህል እንደ ጎዳቸው ለማወቅ የተቃጠውን የሰውነት ክፋላቸውን በአትኩሮት ተመለከትኩት፡፡ የላይኛውን የቆዳቸውን ክፍል በስሱ ስለሆነ ያገኛቸው ቁስለቱ ለክፉ እንደማይሰጥ ተረዳሁ፡፡ ስለዚህ ለእነሱ የማገገሚያ እረፍት ሰጥቼ ምግብ የማብሰሉን የስራ ድርሻ ሙሉ ለሙሉ ወደ እኔ አዞርኩት፡፡ የተወሰኑ ቀናቶችን

የኩሽናው ሀላፊነት እኔ ላይ ቢጣልም ብዙም ሳይቆይ ሴቶቹ አገግመው ሁሉም ወደ ነበረበት ሊመለስ ችሏል።

በሆቴል ቬራ ክሩዝ ህይወት እንደነበረ ቢቀጥልም የሪታ ዝምታ ግን ቀን በቀን ጭንቀት እየወለደ አእምሮዬን መበጥበጡን ተያይዞታል። ከሄደች ሁለት ወር ሊሞላት ሶስት ቀናቶች ብቻ ሲቀሩት አንድ መልእክት ወደ እኔ መጣ። ለቀናት ስጠብቀው የነበረው መልእክት እጄ ላይ እንደደረሰ በፍጥነት ነበር የከፈትኩት

"ማክሰኞ ከምሽቱ 3፡30 ላይ በበረራ ቁጥር 705 አውሮፕላን እመለሳለሁ...ሪታ" ይላል

'ለምን ስለሄደችበት አለማ በጥቂቱም ቢሆን እንኳን አላነሳችም? ማንንም አላገኘችም ማለት ነው?' የሚል ጥያቄ ስለረበሸኝ ባልሰማሁት እና ባላየሁት ጉዳይ ላይ ምን አጨናነቀኝ ብዬ ወዲያው ስለደብዳቤው ማሰቡን እርግፍ አድርጌ ተውኩት።

እመጣለሁ ባለችበት ቀን እና ሰዓት የኔዋን ሪታን ለመቀበል ወደ አየር ማረፍያው ሄድኩ።ከሩቅ እንደተያየን ሁለታችንም እጃችንን በማውለብለብ ጊዜያዊ ሰላምታ ተለዋወጥን። ወደ እኔ በምትመጣበት ወቅት ከፊቷ ላይ አንዳች ነገር ለማንበብ ሞከርኩ፤ ነገር ግን ዘወትር ከማይጠፋው ፈገግታዋ ውጪ ምንም ማየት አልቻልኩም። እየቀረበችኝ ስትመጣ ግን የፈገግታዋ ምንጭ ይዛው የመጣችው ብስራት ሳይሆን የእኔ እዚህ መገኘት እንደሆነ አረጋገጥኩ። አጠገቤ ደርሳ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኃላ ትግዕስቴ እንደተሟጠጠ በሚያሳውቅ ቃና "አባቴን አገኘሽው?" ብዬ ጠየኳት

ይህ ጥያቄዬ እንደ ፀሀይ ሲያበራ የነበረ ፊቷን አደመነው። በርግጥ አባቴን አግኝታው ነበር የተመለሰችው። ፈልጋ ፈልጋ አንድ ቦታ ላይ አገኘችው። አርድቼ ከታማ ውስጥ ከሚገኘው የመቃብር ስፍራ ውስጥ በአንዱ ውስጥ ተኝቶ ነበር! ሪታ አባቴን ይዛልኝ መምጣት ባትችልም የመቃብሩን ፎቶ ግን ይዛልኝ መጥታለች። መቃብሩ በስነ-ስረዓት በሲሚንቶ ተሰርቶ ከበላዩ 'ፒ.ጂ. ቬሪሪ' የሚል ስም ተቀርፆበታል። ያለመታደል ሆኖ አባቴ ያረፈው ሪታ ወደፈረንሳይ ከመሄዷ ከ አራት ወር በፊት ነበር። ለአይነ ስጋ ስመኘው

የነበረውን አባቴን ሳላየው ሞት ነጠቀኝ። ሪታም ፈረንሳይ ድረስ ለፍታ ይዛልኝ የመጣችው የመቃብሩን ፎቶ ብቻ ነው። ክፉ እጣ ፈንታ ማለት ይህ ነው!!

ሪታ ይዛልኝ በመጣችው ዜና ለሰኮንዶች ደንዝዤ ነበር የቀረሁት። በውስጤ የነበረው አባቴን እየዋለሁ የሚለው በራስ መተማመኔ እንደ ሰም ቀልጦ ሲጠፋ ይታወቀኛል። ፈጣሪ የወጣትነት ጊዜዬን ከአባቴ ጋር እንዳላሳልፍ ሲፈርድብኝ ለካ እስከመቼውም አቅፌ እንዳልስመው አድርጎ ነው።

"ትንሹ ሄነሪ ወደ እኔ ና እስቲ" የአባቴ ድምፅ የጠራኝ ይመስለኛል። "ልጄ እጣ ፈንታህ አስቀያሚ ቢሆንም እኔ ግን ዛሬም ድረስ እወድሀለሁ. . .አሁን ያለህበት ደረጃ ላይ ቆመህ በማየቴ እጅጉን እረክቻለሁ" የሚለኝ እየመሰለኝ አእምሮዬ ውስጥ የአባቴ ድምፅ እንደ ገደል ማሚቱ እያስተጋባ ሰላም ነሳኝ። ይሄኔ ነበር ደግሜ ላላነሳው ቃል የገባሁለት የበቀል ሀሳቤ በእልህ እና በሀዘን ታጅቦ ውስጤ ላይ መንተክተክ የጀመረው። በ36 ኳይ ደስ ኦርፌብረስ (በፈረንሳይ ውስጥ የሚገኝ በሀገሪቱ ፖሊስ የሚመራ ፍርድ ቤት ነው) እዛ የሚገኙትን ፖሊሶች አንድ መኪና ሙሉ ፈንጂ ይዤ በመሄድ ከእነህንፃቸው ማፈንዳት ይኖርብኛል!! የሀሰት ምስክሩ ጎልድስቲንም ቢሆን የዘራውን ማጨድ አለበት!! የእሱን ውሸት ተመርኩዞ በወህኒ ቤት እንድማቅቅ ያደረገኝን ዓቃቤ ህግም መቀጣት ይኖርበታል።

ከአውሮፕላን ማረፍያው ተነስተን ሆቴላችን አካባቢ እስክንደርስ ድረስ እያሰብኩ የነበረው አባት እና ልጅን ነጣጥለው የዘላላም ጠባሳ ልብ ውስጥ ስለጣሉብን ሰዎች ነው።

"ሪታ ከመቼውም በላይ አሁን ልትረጂኝ ይገባል... የእድሜዬን ግማሽ ያሳለፍኩት አባቴን አቅፎ ለመሳም በመናፈቅ እና የአባቴን ይቅርታ ለማገኘት በመሻት ነው። ብቀላዬን መፈፀም ይኖርብኛል! ይቅርታ ቃሌን በማጠፌ ነገር ግን ይህን ባላደርግ የአባቴ አጥንት እራሱ ይቅርታ የሚያደርግልኝ አልመስልህ አለኝ፤ ስለዚህ እነዚያ ውሾች መቀጣት ይኖርባቸዋል። አሁን የምጠይቅሽ ነገር ቢኖር ካጠራቀምነው ገንዘብ ላይ አምስት ሺህ ቦሊቫር እንድወስድ እንድትፈቅጂልኝ ብቻ ነው" አልኳት ምንም አይነት ምላሽ አልሰጠችኝም። በመሃላችን ዝምታ እንደሰፈነ ወደ ሆቴል ቬራ ክሩዝ ገባን።

በምን አይነት መንገድ ብቀላዬን ከግብ ላደርስ እንደምችል ማሰብ ጀመርኩ። የመጀመርያው ጥያቄዬ ገንዘብ ከየት አመጣለሁ የሚለው ነው። ለእሱ ደግሞ ሁለት አማራጮች አሉኝ። የመጀመርያው ኤልሴሎ ውስጥ በይሉንታ የተውኩትን ያንን የወርቅ ቁልል መዝረፍ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ካራካስ ውስጥ የማውቀው አንድ ትልቅ ድርጅት ውስጥ የሚሰራ ገንዘብ ተቀባይ ነው። ይህ ገንዘብ ተቀባይ ታድያ የሰበሰበውን ገንዘብ ይዞ ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሰው ያለ አጃቢ ስለሆነ እሱን ተከታትሎ ገንዘቡን የት እንደሚያስቀምጠው ማወቅ በጣም ቀላል ነው። ለመስራት ያሰብኩት ስራ ይህ ሀገር ለእኔ ከዋለልኝ ውለታ አንፃር የማይጣጣም ድርጊት ቢሆንም  የአባቴ የዕረፍት ዜና ግን ምንም እንዳደርግ ያስገድደኛል።

ከሪታ ጋር ምንም ሳላወራ በውስጤ የጉዞ እቅዴን አውጥቼ ጨርሻለሁ። ፈረንሳይ ለመድረስ የመጀመርያ ጉዞዬን የማደርገው በብሪቲሽ ጊዮና በኩል ስለሆነ ጆርጅ ታውን ስደርስ ከ ኢል ሴሎ ከምሰርቀው ወርቅ ላይ የተወሰነውን እሸጣለሁ። በመቀጠል አይን ውስጥ ላለመግባት ቀሪውን ወርቅ በባንክ ወደ ቦውኖ ኤርስ እንዲላክ አደርጋለሁ። ከዛ ከ ትሪንዳድ ወደ ሪዮ ዲጀኒሮ የሚወስደኝ አውሮፕላን ላይ እሳፈራሉ፤ ርዮ ላይ ፓስፖርቴን እቀይርና ከ ርዮ ደግሞ ወደ አርጀንቲና እሄዳለሁ። የፓስፖርቱ ጉዳይ ብዙን አስጨናቂ አይደለም፤ሪዮ ውስጥ አንድ የማውቀው ጓደኛዬ ስላለ ነገሮችን ለመጨረስ የሚከብደኝ አይመስለኝም።

ፈረንሳይ እንደምንም ከገባሁ በኃላ ፓሪስ ውስጥ የሆነ ክፍል ተከራይቼ በተቻለኝ አቅም በሰዎች እይታ ውስጥ ላለመግባት እሞክራለሁ። ሆቴል ከያዝኩ በኃላ ቢያንስ ለሳምንት ያህል ከእይታ እርቄ መቆየት ይኖርብኛል። ምንም አይነት ጥርጣሬን ከእኔ ለማራቅ ፂሜን ማሳደግ ይኖርብኛል፤ የፀጉር አቆራረጤንም በዛው ልክ እቀይረዋለሁ። ከሞላ ጎደል ስፓኒሻዊ መስዬ ነው መታየት ያለብኝ፤ አሁን ላይ ስፓኒሽኛ በደንብ ስለምናገር የትኛውም ፈረንሳዊ እኔን ከስፓኒሾች ለመለየት ይከብደዋል።

ከአንድ ሺህ ጊዜ በላይ ነበር ብቀላዬን ከማን መጀመር እንዳለብኝ ያሰብኩት፤ መጨረሻ ላይ ግን በቅድሚያበ በ36 ኳይ ደስ ኦርፌቭረስ ያሉ ፖሊሶችን በሙሉ ለማፈንዳት ወሰንኩ። ያን ለማድረግ በቅድሚያ ማንንቴን በተለያየ ነገር እየሸፈንኩ ፍርድ ቤቱ ውስጥ በመግባት ማጥናት በቂ ነው። ከዛም ከእኔ

የሚጠበቀው የራሳቸውን የደንብ ልብስ ፊልጌ በመልበስ ከእነሱ አንዱ መስዬ የምፈልገውን ፊንጂ በምፈልግበት ቦታ ላይ አጥምጄ እንዲፈነዳ ማድረግ ብቻ ነው፡፡ ስለፈንጂ ያለኝ እውቀት የሚያሳማኝ ስላልሆነ መች ሊፈነዳ እንደሚችል እና የት ቦታ ላይ ቢፈነዳ ውጤታማ ሊያደርገኝ እንደሚችል አውቃለሁ፡፡ ስለዚህ እቅዶን የሚያሰናክል ነገር ይገጥመኛል ብዬ አላስብም፡፡ ምንም ሳደርግ ግን መጠንቀቅ የሚገባኝ ነገር ቢኖር የምፈፅመው ሁሉም ድርጊት ከፓፒሎን ጋር እንዳይዛመድ ማድረግ ብቻ ነው፡፡

ፖሊሱቹን አጋይቼ ከጨረስኩ በኋላ ሁለተኛ የቤት ስራዬ የሚሆነው ያንን ሀሰተኛ አቃቤ ህግ 'ፕራዶልን' ወደ ዘላለማዊ ቤቱ መላክ ነው፡፡ ትክክለኛ የመኖርያ አድራሻውን ማግኘት የመጀመርያው ስራዬ ነው፡፡ ከዛ የት እንደሚሰራ፣ ምን አይነት ቦታ እንደሚዝናና፣ ለመንቀሳቀስ የሚጠቀመው የግል መኪና ይሁን የህዝብ ትራንስፖርት ካጣራሁ በኋላ አግቶ ማሰቃየቱ በጣም ቀላሉ ስራ ነው፡፡ዋናው ነገር ብቻውን የሚሆንበትን ሰዓት ጠብቆ ማግኘት ነው፡፡ ይህ ሀሰተኛ አቃቤ ህግ በ1931 ፍርድ ቤት በቀረብኩበት ሰዓት በዛ አስቀያሚ ድምፁ የተናገረው አስታውሳለሁ

"አንተ ውሻ የምታመልጠኝ እንዳይመስልህ! የአንተን መጥፎነት የሚገልፁ ነገሮች ሁሉ ፈልፍዬ በማውጣት ወደ ወህኒ አወርድሀለሁ" ነበር ያለኝ በርግጥ ተሳክቶለታል! ስለዚህ እኔም ይዤው ቶሎ እንዲሞት አላደርገውም፤ እኔ በአስራ አራት አመት ውስጥ ያለፍኩትን ስቆቃ ቢያንስ ለ አንድ ሳምንት እንዲያጣጥመው አደርገዋለሁ፤ ከዚያ አባቱ ወደ ገባበት ጉድጓድ እሱንም እልከዋለሁ፡፡

የመጨረሻው ሟች የሚሆነው ጎልድስቲን ነው፡፡ የሀሰት መስካሪው! እሱን መጨረሻ ላይ ለመግደል ያሰብኩት ሊፈጥርብኝ የሚችለውን ተፅኖ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ምክንያቱም ጎልድስቲን ሲሞት ፖሊሶች የእሱን የኋላ ታሪክ ማጥናታቸው አይቀርም፤ ያ ከሆነ ደግሞ የእሱ፣ የአቃቤ ህጉ እንዲሁም የፊረድ ቤቱ ወንጀል ተያይዘው የመጡ እንደሆነ ሊደርሱበት ይችላሉ፡፡ የእዚህ ሁሉ ሴራ ጠንሳሽ ማን ነው ብለው ሲጠይቁ ፓፒሎን የሚለውን መልስ ያገኙታል፡፡ ስለዚህ ወዲያውኑ ፓሪስ ውስጥ ያሉ ሆቴሎች፣ የባቡር ጣብያዎች፤ የአየር ማረፍያዎች በጠቅላላው ሁሉም ቦታዎች ላይ ቁጥጥር

ይደረግበታል፤ ያ ደግሞ እኔን ችግር ውስጥ ይጥለኛል። የጎልድስቲን በመጨረሻ መሞት ግን ለእኔ ፓሪስን ለቅቄ የምወጣበትን ፋታ ይሰጠኛል።

ጎልዲስቲን አባቱ ከቆዳ የተሰሩ አልባሳት መሸጫ ሱቅ ስለነበራቸው አብዛኛውን ጊዜውን የሚያሳልፈው ሱቅ ውስጥ በመስራት ነበር። ስለዚህ ምን አልባት ሱቁን ካልተውት እና ቦታ ካልቀየሩ በስተቀር ጎልድስቲንን ማደን ቀላል ይመስለኛል። እንደያዝኩት እንዲነግረኝ የምፈልገው ማንነቴን ነው፤ ነገር ግን ሊነግረኝ አይችልም። የተወጋሁት እኔ ለዘመናት ባስታውሰውም እሱ ግን ይሄኔ ከእነመፈጠሬ እራሱ ረስቶኛል። ስለዚህ መጀምሪያ የማደርገው ማን እንድሆንኩ እንዲያስታውስ ማድረግ ነው። ከቻልኩ አንገቱን በእጆቼ አንቄ በመያዝ "አንተ የቁም እሬሳ... በደንብ እወቀኝ ፓፒለን ነኝ... ባንተ ወሸካታ ምላስ የተነሳ በሞት ጥላ ስር ሲኖር የነበረው ፓፒለን! የሞተው አፈር ልሶ ተነስቷል! ይሄን አልጠበክም አይደል? እነዚህ እጆቼ ይገሉኛል ብለህ አስበህ ታውቃለህ? በርግጥ አሁንም አሸንፈሀል! ምክንያቱም የእኔን ስቃይ ጥቂቱን እንኳን ሳትቀምሰው ከደቂቃዎች በኋላ ትሞታለህ። እኔን በቁሜ እንደገደልከኝ ግን አትዘንጋ" ማለት እፈልጋለሁ።

ጎልድስቲን  ከሞተ በኋላ ከፈረንሳይ መውጣቴ አጠራጣሪ ነው። ነገር ግን በዚህ ሰዓት ሀሳቤን ከፈፀምኩ በኋላ ብሞትም አይደንቀኝም። ምክንያቱም አባቴ የሞተበት ምክንያት ምንም ይሁን ምን ለመሞቱ ተጠያቂዎች ግን እነሱ ናቸው። እኔ ላይ ስላደረሱት በደል እማ ለሪታ ስል ይቅር ብያቸው ነበር፤ የአባቴ ሞት ግን ቃሌን አሳጠፈኝ። በርግጥ ለአባቴ መሞት በቀጥታ ተጠያቂ ባይሆኑም በእኔ ምክንያት ማህበረሰቡ የሚያደርስበት መገለል እና ጫና የሞቱ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ግን አልጠራጠርም። ለዛ ደግሞ ተጠያቂዎቹ እነሱ ናቸው። ታድያ ለእነዚህ እንዴት ይቅርታ ላድርግላቸው?በፍፁም!ይሄን ማድረግ አልችልም!

ይሄን ሁሉ ሀሳብ ሳስብ በሆቴላችን እንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ ሶፋ ላይ ቁጭ ብዬ ነው። እኔ በሀሳብ በተዋጥኩበት ሰዓት ሪታ ጭንቅላቷን እግሬ ላይ አድርጋ ጋደም በማለት ምንም ሳትናገር ከታች ወደ ላይ በተመስጦ እየተመለከተችኝ ነበር። ሀሳቤን አውርጄ፣አውጥቼ ከጨረስኩ በኋላ "ሪታዬ" አልኳት

"አቤት" አለችኝ ለስለስ ባለ ድምፅ

"ይሄውልሽ. . .ነገ ማራካይቦን ለቅቄ መሄድ ይኖርብኛል"

"በፍፁም አትሄድም!" አለችኝ ከተኛችበት ብድግ ብላ... ቀጥላም እጆቿን ትከሻዬ ላይ ጭና እይን አይኔን እየተመለከተች "መሄድ የለብህም ሄነሪ... በእኔም ህይወት ውስጥ አዲስ ነገር ተከስቷል... አባትህን ፍለጋ ወደ ፈረንሳይ ባቀናሁበት ወቅት እግረ መንገዴን ወደ ካዛ ብላንካ ልጄን እንዲልኩልኝ መልዕክት ልኬ ነበር፤ ከተወሰኑ ቀናቶች በኋላም መምጣቷ አይቀርም። እስከዛሬ ያላመጣኋት እንደምታውቀው የራሴ የሆነ መኖርያ ቦታ ስላልነበረኝ ነው። አሁን ግን ሁሉም ነገር የተስተካከለ ነው፤ በዛ ላይ አንተን የመሰለ አባት ይኖራታል። በሁለታችን መሀል በፅናት የተገነባውን የፍቅር ድልድይ ለመደርመስ ሀሳብ አለህ እንዴ? እስኪ አስበው እነዛን እድሜያቸውን የፈጁ ሰዎች መግደሉ አሁን ካለንበት የደስታ ህይወት የበለጠ እርካታን ይሰጥሀል? ሄነሪ ለእኔ እና ለምትመጣዋ ልጄ ስትል ይሄን የብቀላ እቅድህን እንድትተው እለምንሀለሁ"

"ሪታ... ይሄን ካላደረኩ የአባቴ አጥንት እሾህ ሆኖ የሚወጋኝ ነው የሚመስለኝ"

"በጭራሽ! አባትህ በህይወት ኖሮ ይሄን የብቀላ ሀሳብህን ቢሰማ የበደሉህን ሰዎች እረስተህ አሁን ያለህበትን የነፃነት ህይወት ዝም ብለህ አጣጥም ኑር የሚልህ ይመስለኛል። በጣም የምትወድህ እና የምትወዳት ሚስት አለችህ። ልጄም ጥሩ አባት በማግኘቷ እንደምትደሰት አልጠራጠርም። ስለዚህ ይህንን ሰላማዊ ህይወት አትበጥብጥ"

"አልገባሽም ሪታ"

"በደንብ ገብቶኛል! አንተ ነህ ያልገባህ! የተጣመመውን ማቅናት ሲገባህ የተቃናውን ለማጉበጥ መንገድ ትፈልጋለህ፤ ምን እንደምመኝ ታውቃለህ? የእኛ ቤተሰብ ደስተኛ ሆኖ ለሌሎች አርዐያ መሆን ሲችል ባይ ደስ ይለኛል. . .የህይወት መስመራችን በመልካም መንገድ እንድሄድ የማድረግ ድርሻው የራሳችን ነው። የገጠመህ ክፉ እድል የሚያሳዝን እንደሆነ ይገባኛል። ነገር ግን ሁሉንም አሸንፈህ እዚህ እስከተገኘህ ድረስ በድጋሚ የጨለማውን አለም

ለምን እንደምትፈልገው ሊገባኝ አልቻለም፡፡ ለእኔ አንተ ተበቃይ የምትሆነው እራስህን ተቆጣጥረህ ያጣኸውን ደስታ አግኝተህ መኖር ስትችል ነው፡፡ ወደ ፈረንሳይ መሄድ አይደል ፍላጎትህ... ሂድ!... አልከለክልህም! ነገር ግን አንድ ያላስተዋልከውን እውነት ልንገርህ ምን አልባት እድል ቀንቶህ ፓሪስ ስትገባ ፍርቱና ካንተ ጋር ከሌለች እነዛን የምትፈልጋቸውን ሰዎች ልክ እንዳ አባትህ ከመሬት ስር ልታገኛቸው ትችላለህ" ብላኝ ፀጥ አለች

ከደቂቃዎች በፊት እቅድ የነደፍኩለት ብቀላ በሪታ ውስጠ ወይራዊ ንግግር እንደ ጉም ተኖ ጠፋ፡፡ ሪታ አሸነፈችኝ፤ ባላሰብኩት መንገድ መጥታ ጭንቅላቴን ወጥሮ የያዘውን ሀሳብ ብትንትኑን አወጣችልኝ፡፡ ሁሉንም ነገር እረስቼ ከሪታ ጋር ሌሊቱን ሙሉ ስናወራ አደርን፡፡ በጉዞዋ ወቅት ስላጋጠሟት ነገሮች ማወቅ ስለፈለኩ እዛው ሶፋ ላይ ተቆላልፈን እንደተኛን በጥያቄ ማጣደፍ ጀመርኩ፡፡ እሷም ያጋጠማትን ስትነግረኝ ሌሊቱ ሳይታሰብ ነጎደ፡፡

ሪታ ወደ ፈረንሳይ ለመሄድ ስትነሳ በቅድሚያ ከማራካይቦ ወደ ካራካስ ወደብ ነው ያቀናችው፡፡ ከዛም ወድያውኑ 'ኮሎምቢያ' በምትባል መርከብ ላይ ለመሳፈር ትኬት ቆርጣ መጠባበቅ ጀመረች፡፡

"ትኬት ቆርጬ መርከቧ ላይ ከተሳፈርኩ በኋላ የረሳሁት ወሳኝ ቪዛ እንዳለ አላስታውስ መሰለህ" አለችኝ

"እና እንዴት አደረግሽ?"

"መርከቧ እንዳታመልጠኝ ከጊዜ ጋር ተሽቀዳድሜ ቪዛውን ለማምጣት ወደ ካራካስ ሄድኩ. . .ቪዛውን እንዳወጣሁ ወዲያው ነበር ወደ ወደቡ የሚመልሰኝን መኪና ያገኘሁት ነገር ግን ወደቡ ጋር ልንደርስ ትንሽ ሲቀረን መንገዱ አጠገብ ያለው የአፈር ክምር ተደርምሶ መንገዱን አልዘጋው መስለህ. . .እኛ እራሱ ለጥቂት ነው የተረፍነው፡፡ ሹፌሩ ደግሞ በሁኔታው ተደናግጦ እኔን እዛው መንገዱ ላይ ጥሎኝ ወደኋላ ተመለሰ፡፡ ከዛ አማራጭ ስላልነበረኝ በእግሬ መጓዝ ጀመርኩ፡፡ የሆነ ያህል እንደሄድኩ እድል ቀንቶኝ አንድ ታክሲ አግኝቼ ጉዞዬን ቀጠልኩ፡፡ ልክ ወደቡ አቅራቢያ ስደርስ የመርከብ ጡሩምባ ድምፅ ሰማሁ፡፡ ያኔ በቃ ይዛኝ የምትሄደው መርከብ ተሳፋዎቿን ይዛ እየሄደች ነው በሚል በጣም ፈርቼ ነበር፡፡ ወደቡ ጋር ስደርስ ግን የአምላክ ፍቃድ ሆኖ እኔ የምሄድባት መርከብ ተበላሽታ ስትጠገን አየኋት፤ ያኔ በቃ ልቤ በደስታ ፈካ"

አለችኝ። ለእኔ ስትል ምን አይነት ፈተና ውስጥ እንደነበረች ሳስብ ስለብቀላ አንስቼ እሷን ማስከፋቴ አሳፈረኝ

መርከቧ ጥገናዋን እንደጨረሰች የውቅያኖስ ላይ ጉዞ ጀመረች። ቀናቶችን ያለማቋረጥ በውቅያኖስ ላይ ከተጓዙ በኋላ በመጨረሻ 'ሊ ሃቬሪ' ( የሰሜን ፈረንሳይ ወደብ ) ለመድረስ ቻሉ። በመቀጠል ማርሴል ውስጥ የምታውቃት አንድ ልጅ ስለነበረች ለማረፍ ወደ እሷ አቀናች። ያቺ ሴት ሪታን አንድ የመንግስት አማካሪ ከሆነ ሰው ጋር ስላስተዋወቀቻት ለፍለጋዋ ጥሩ መንገድ ከፈተላት። ሰውዬው አርዴቼ ውስጥ የሚኖር 'ሄነሪ ቻፓል' የሚባል ጓደኛ ስለነበረው ለእሱ ደብዳቤ ፃፈላት። ሪታም ጊዜ ሳታባክን በሚቀጥለው ቀን ባቡር ተሳፍራ ወደ አርዴቼ ሄደች። እዛም እንደደረሰች የመጀመርያ ስራዋ የሆነው ሰውየው በሰጣት አድራሻ መሰረት ቻፓልን ማግኘት ነው። ብዙም ሳትለፋ ቻፓልን አገኘችው። ጊዜ መፍጀት ስላልፈለገች ወዲያው የመጣችበትን ምክንያት ነግራው ትብብር እንዲያደርግላት ጠየቀችው። እሱም አርድቼ ውስጥ ወዳለ 'አቡና' ተብሎ የሚጠራ መንደር ውስጥ ይዟት በመሄድ 'ሜትሪ ቴሱድ' የሚባል የጥብቅና ተቋም ያለው 'ቴሱድ' የተባለ ሰው ያስተዋውቃታል። ይህ ጨቃኝ ሰውዬም አባቴን ፈልጋ እንደመጣች ገና ከማወቁ ነበር መሞቱን ያረዳት። ከየት ትምጣ እንኳን ለማወቅ አልፈለገም ነበር። ይባስ ብሎ ማንነቷን እንኳን ሳያውቅ እና ማንንም ሳያማክር የአባቴን እህት እና ባሏን እንድትጠይቅ ይዟት ሄደ። ደስ የሚለው ነገር እነሱ ደስ በሚል መስተንግዶ ነበር የተቀበሏት።

ቴሱድ የተባለውን ጠበቃ እኔም አውቀዋለሁ፤ የዛሬን አያርገውና ከቤተሰቦቼ ጋር በነበርኩበት ሰዓት የእኛም ጠበቃ ነበር። በታሰርኩበት ወቅት ታድያ እኔን ከቤተሰቤ ጋር የማገናኘት የስራ ድርሻው የሱ ነበር፤ ነገር ግን በእሱ ቸልተኝነት የተነሳ ለብዙ አመታት ከቤተሰቦቼ እንድርቅ ተገድጃለሁ። በፊት ያለው መሰሪነቱ አሁን ድረስ አብሮት አድጓል። እህቶቼ ያሉበትን አድራሻ እንደሚያውቅ አልጠራጠርም፤ ሆኖም ግን ለሪታ ሊነግራት ፍቃደኛ አልነበረም። በሪታ ጥረት ባይሆን ኖሮ የአባቴ መቃብር የት እንዳለም ለመናገር ፍቃደኛ አልነበረም። በመጨረሻም ተለምኖም ቢሆንም የአባቴ መቃብር "ቅዱስ ፕሬይ" እንደሚገኝ ነገራት።

ሪታም ቻፓልን አስከትላ የአባቴን መቃብር ለማየት ወደ ቅዱስ ፕሬይ ሄደች፡፡ እዛም ደርሰው የአባቴን መቃብር ከማየት በተጨማሪ ስለሱ የሚገልፅ መረጃ ለማግኘት ቻሉ፡

"ምን አይነት መረጃ ነው ያገኛችሁት?" አልኳት ለመስማት እየጓጓሁ

"አባትህ ለ ሃያ ዓመታት ያህል ያለሚስት ነበር የኖረው... ከእዛ በኋላ ግን ከአንዲት መምህር ጋር ገብቻ ፈፅሞ አዲስ ህይወት መምራት ጀምሮ ነበር"

"ይህ የሆነው እኔ እስር ቤት በነበርኩበት ወቅት ነው ማለት ነው... እሺ ከዛስ?"

"ከዛማ ሴትየዋን ፈልጌ አገኘኋት 'ታንቴ ጁ' ትባላለች፡፡ በቅፅል ስሟ 'ቴቴ ጁ' እያሉ ይጠሯታል፡፡ ብታያት እንዴት ያለች ደስ የምትል ሴትዬ መሰለችህ፡፡ በሚገርም ሁኔታ የእናትህ ማስታወሻ በሙሉ በቤት ውስጥ እንዳለ ነው፡፡ በመመገቢያ ክፍል ውስጥ የእናትህ ፎቶ በትልቁ ግድግዳው ላይ ተሰቅሏል፡፡ ከዛ አልፎ እናትህ በፊት ትገለገልባቸው የነበሩ ቁሶችን እያነሳች ስታሳየኝ ነበር" አለችኝ

ይህን ስትነግረኝ ታንቴ ጁ የህይወቴ አንድ አካል የሆነች መሰለኝ፤ እቺን ሴትዮ ባላውቃትም ውስጤ ግን የማውቃት አይነት ስሜት ነበር የተሰማው፡፡ እንደማስበው ከሆነ ቴቴ ጁ የእናቴን እቃዎች ለ ሪታ ለማሳየት የፈለገችው የተቀመጡት በምክንያት እንደሆነ እንድታውቅላት ስለፈለገች ይመስለኛል"

"ሌላስ ምን ነገረችሽ?" አልኳት ወሬውን ለመስማት እየጓጓው

"ሌላ የተወለድከው ህዳር አስራስድስት እንደሆነ እና የልደትህ ቀን በመጣ ቁጥር አባትህ ያለቅስ እንደነበር ነግራኛለች፡፡ ከእሱ ውጪ ደግሞ ከእስር ማምለጥህን ሰዎች ሲነግሯቸው አባትም ታንቴም ምን ያህል ይደሰቱ እንደነበር አጫውታኛለች፡፡ አንተ ከእስር ማምለጥህ የተሰማ እለት እዛ ቤት ሲፈነጠዝ ነው የዋለው"

ታንቱ እኔን ሳታውቀኝ በእኔ ማምለጥ መደሰቷ፡ ድንቅ እና የምትወደድ ሴት ለመሆኗ ምስክር ነው፡፡ ምንም እንኳን ባታውቀኝም አባቱ ለእኔ ያለውን ፍቅር ስለምታውቅ የእሱን ፍቅር መካፈሏ የጥሩነቷ መለከያ ነው፡፡ ታንቴ ሪታን ያስተናገደቻት በጥሩ አቀባበል ነበር፡፡ ነገር ግን ቴቴ ጁ አንድ ችግር ብቻ ነበረባት፤ እሱም የእህቶቼን አድራሻ ለሪታ መስጠት አልፈለገችም፡፡

"እንዴ አድራሻውን ብትሰጥሽ ምንድነው ችግሩ?"

"እኔም ብዙም ግልፅ አልሆነልኝም… ከእሷ አባባል እንደተረዳሁት ግን ከእዚህ ሁሉ ዓመታት በኂላ ያንተ መገኘት ቢሰሙ ለማመን ሊከብዳቸው ይችላል የሚል እሳቤ ስላላት ይመስለኛል"

ለነገሩ እውነት አላት፡፡ እህቴ ቮኔም ሆነች ሄለን የእኔን መገኘት ቢሰሙ ያለጥርጥር ይደነግጣሉ፡፡ ታንቴ ጁም አድራሻቸውን መስጠት ያልፈለገችው እነዚህን እህቶቼን ከአማቾቻቸው ጋር እየኖሩ ያለውን የሰላም ህይወት መበጥበጥ እንዳይሆንባት ስለሰጋች ይመስለኛል፡፡

ሁለቱም አግብተው እና ልጅ ወልደው እየኖሩ ነው፡፡ የወለዷቸው ልጆች ደግሞ እኔን እስከመፈጠሬ እንኳን አያውቁኝም፡፡ እንደማስበው ከሆነ ለአስራ አራት ዓመት እኔ በወህኒ ቤት ስቆይ እህቶቼ በህይወታቸው ውስጥ እኔን ለመርሳት እንጂ ለማስታወስ እንደማይጥሩ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ምክንያቱም በእነሱ ጭንቅላት ውስጥ ሊኖር የሚችለው ሀሳብ "ሄነሪ ሞቷል" አልያም ደግሞ "መቼም ላናገኘው ርቆ የራሱን ህይወት እየመራ ነው" የሚል ነው፡፡ ስለዚህ አያስታውሱኝም፡፡ በርግጥ ትክክል ናቸው!! ሆነም ቀረ ሚስቴ ፈረንሳይ ድረስ ተጉዛ ልታመጣልኝ የቻለችው ነገር ቢኖር በአባቴ መቃብር ዙርያ ከተሰገሰገው አፈር አንድ እፍኝ እና የአባቴን መቃብር የሚያሳይ ፎቶ ብቻ ነው፡፡

በሪታ እይታ ጥሩ የማስታወስ ችሎታ እንዳለኝ ተመስክሮልኛል፡፡ ምክንያቱም ስለተማርኩበት ትምህርት ቤት፣ በውስጡ ስላሉት ክፍሎች፣ ስለ መናፈሻው፣ ስለ ቤታችን አቀማመጥ በአጠቃላይ ስለሰፈራችን እኔ ከእዚህ በፊት ከነገርኳት ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ስላገኘችው ነው፡፡

"ሰፈርህ አንተ ከምታውቀው እምብዛም ልዩነት የለውም፡፡ ከነገርከኝ የልጅነት ትውስታ ጋር ሲነፃፀሩ በሚገርም ሁኔታ አንድ አይነት ነው፡፡

የማውቀው ቦታ የሄድኩ እስኪመስለኝ ድረስ ነው የነገርከኝ እና ሰፈርህ የተመሳሰሉብኝ" ብላኛለች መደነቋ ከፊቷ ላይ እየተነበበ

የባጥ የቆጡን እያነሳን በማውራት ጭጋጋማውን ሌሊት እየገፋነው ነው። ያልጠየኳትን ጥያቄ እያስታወስኩ ስጠይቃት እሷ ያለመሰልቸት ስትመልስ ደስ የሚል ትዝታ አመጣችልኝ። ሆቴላችን ስራውን እንደ ቀድሞው ሲሰራ ነው የዋለው። ነገር ግን የአባቴን ሞት እንደ አርባ አመት ጎልማሳ መቀበል ተሳነኝ። ስናፍቀው ኖሬ በሞት መነጠቄ እጅጉን ልቤን ሰብሮት ነበር። ቢሆንም ግን አምላክ ያመጣውን ነገር እኔ ልመልሰው እንደማልችል ሳውቅ እራሴን ማፅናናቱን መረጥኩ።

የሪታ ልጅ ክሎታይዶ በተባለው ቀን ሆቴል ቬራ ክሩዝ ደረሰች። ክሎታይድ አሁን አስራ አምስት አመት የሞላት ብትሆንም ሲያዩዋት ግን ገና የአስራ ሁለት አመት ልጅ ነበር የምትመስለው። ረጅም እና ጥቁር ፀጉሯን ትከሻዋ ላይ በትናዋለች፤ አይኖቿ ብልጥ መሆኗን ይናገራሉ። የፊቷ ትንሽ መሆን የእድሜዋን መብሰል ሳይሆን የሚናገረው ገና ቦርቃ ያልጨረሰች ህፃን እንደሆነች ነው የሚገልፀው። ገና እንዳየኋት በቶሎ ልንግባባ እንደምንችል ተረድቻለሁ።

አሁን እንግዲህ ሪታዬ ተመልሳ ስለመጣችልኝ እንደ በፊቱ ገበያ በጠዋት መሄድ አይጠበቅብኝም። ጠዋቱን ረጋ ብዬ ካሳለፍኩ በኋላ ክሎታይድን፣ ካርሊቶስን እና ውሻዬን አስከትዬ ወደ ገበያ እወጣለሁ። ለክሎታይዳ ሁሉም ነገር አዲስ ስለነበር በምታየው ነገር ሁሉ እየተገረመች ምን እንደሆነ በመጠየቅ ናላዬን ታዞረዋለች። አንድ የተለየ አዲስ ነገር ባየች ቁጥር እየጮኸች ትሄድና ምን እንደሆነ ትጠይቃለች። ከሁሉም በላይ ያስገረማት ግን በአደባባይ ላይ የምታያቸው ህንዳዊ ሴቶች አለባበስ ነበር። ፊታቸውን የሚቀቡት ነገር፣ ጫማቸውን ለማሳዋብ የሚጠቀሙት የተለያዩ ቀለማት ተደምሮ በህንዶቹ በጣም ነበር የተደመመችው።

ከጊዜ ወደጊዜ ለክሎታይድ ያለኝ ፍቅር እና የአባትነት ስሜት እየጨመረ መሄዱን ውስጤ ይነግረኛል።በምንም አይነት ሁኔታ አባቷ እንዳለሆንኩ እንዲሰማት ማድረግ አልፈልግም።

'ክሎታይድ የወደፊት ህይወትሽ ቀላል እና ነፃ እንዲሆን እፈልጋለሁ። በመንገድሽ ላይ የሚያጋጥሙሽን የትኛውንም ፈተና በቻልኩት አቅም ለመጥረግ እሞክራለሁ' አልኩ በውስጤ

ክሎታይድ ከመጣች በኋላ ሁልጊዜ ከገበያ ስንመለስ በውሏችን ወቅት ያጋጠመንን ነገር ለሪታ ለመንገር መሽቀዳደም የእለት ከእለት ልምዳችን ሆነ። በዛ ላይ እሷ አብራን መኖር ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ ቤታችን ከመቼውም በላይ ደስታ የሰፈነበት ሆኗል።

# ምዕራፍ አስራ ሁለት

## ቬንዙዌላዊ መሆን

በእርግጠኝነት በእዚህ ምዕራፍ አንባብያን ስለ እኔ ምን ለማወቅ እንደምትፈልጉ አውቃለሁ። የእኔን ጀብዱ የተሞላበት የህይወት ታሪክ እንጂ የቬንዙዌላን ታሪክ ለማንበብ እንደማትፈልጉ እገምታለሁ። ነገር ግን በህይወቴ ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የቬንዙዌላ የፖለቲካ ሽኩቻ ያደረሰብኝ ተፅዕኖ ስላለ በመጠኑም ቢሆን ስለ ቬንዜውላ ፖለቲካ ለማውራት እገደዳለሁ።

ብዙ ሰዎች ቬንዜውላ ደቡብ አሜሪካ ውስጥ እንደምተገኝ ቢያቁም አንዳንዶች ግን የት እንደምትገኝ ከእነ ጭራሹ የማያውቁም አሉ። የእነዚህ ሰዎች አስተሳሰብ ቬንዜውላ ነጋዥ ለማውጣት በአሜሪካኖች የተገኘች ሀገር አርገው ነው የሚቆጠሯት። ይህ አመለካከት ግን ከእውነት የራቀ ነው። አሜሪካኖች በርግጥ ትንሽ የማይባል ዘይት አውጥተዋል፤ ነገር ግን የቬንዙዌላ መንግስት ቀስ በቀስ ሃገሪቷ ከአሜሪካ ጫና ሙሉ ለሙሉ እንድትላቀቅ አድርጓታል።

ቬንዙዌላ በእዚህ ሰዓት በተባበሩት መንግስታት ሙሉ ለሙሉ ነፃነቷን ያረጋገጠች ሉአላዊት ሀገር ነች። እንደሚታወቀው የቬንዜዊላ ኢኮኖሚ መሰረት ያደረገው ተፈጥሮ ባደላት የነዳዥ ምርት ሲሆን ከእሱም ቀላል የማይባል ትርፍ ታጋብሳለች። ሲጀምር ነዳዡን የምትሸጠው በከፍተኛ ዋጋ ሲሆን ከዛ በተጨማሪ ደግሞ በሀገሪቷ ላይ ነዳዥ ከሚያወጡ ድርጅቶችም ሦስት አራተኛውን ትርፍ የምትወስደው ሀገሪቷ ነች። ይህም ከነዳዥ የምታገኘው ትርፍ ከፍተኛ ስለመሆኑ ጥሩ ማሳያ ነው።

ሌላው የቬንዜውላ የገቢ ምንጭ የብረት ምርቷ ነው። ከእሱ በተጨማሪም ቬንዙዌላን ወደላቀ ደረጃ ለማድረስ ቀን ከሌሊት በሚለፉ እና ተስፋን ባነገቡ ሰዎች የተሞላች ሀገር ነች። በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ያሉ ተማሪዎች

ለሀገራቸው ለውጥ መድከም እንዳለባቸው ከገባቸው ውሎ አድሯል፡፡ ሀገሪቷ በአንባገነኖች እጅ እንዳትወድቅ እና የህዝቦቹ ነፃነት እንዳይነፈግ የቻሉትን ሁሉ ከማድረግ አይቦዝንም፡፡ እኔም በእነዚህ ወጣት ሀይሎች ሙሉ እምነት አለኝ፡፡ ቬንዙዌላ ለሌሎች ሀገራት ተምሳሌት እንድትሆን የማድረጉ ድርሻ የወጣቶቹ ትኩስ ሀይል እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ በኢኮኖሚውም ሆነ በፖለቲካው ለሚመጣው በጎም ሆነ ክፉ ለውጥ ወጣት ሀይሉ ተጠያቂ ነው፡፡

ሌላው ቬንዜዌላውያን በመጪው አመታት ውስጥ ሀገሪቷን ለቱሪዝም ምቹ ማድረግ እንደ አንድ መሰረታዊ እቅድ የታሰበ ነገር ነው፡፡ ለተፈጥሮ ምስጋና ይግባውና ሀገሪቱ ለቱሪዝም መስህብነት በሚሆኑ ነገሮች የታደለች ነች፡፡ እነዛ በኮከናት ዛፍ የተከበቡ የውሀ ዳርቻዎች ጋር ተቀምጦ ፀሀይዋ ከባህሩ አድማስ ስትወጣ እና ስትገባ የምትፈጥረውን ትርኢት መመልከት፤ የአሳዎቹን ብዛት እና አይነት ማየት ብቻውን ሰላም ይሰጣል፡፡ በዛ ላይ ደግሞ አንተ ነጭ ነህ አንተ ጥቁር ነህ ከሚል የዘር ሽኩቻ ነፃ ሆኖ መኖር ለሚፈልግ ሰው ምቹ እና የምትመረጥ ሀገር ነች፡፡ ሌላ መስህብ  የሚፈልግ ካለ ደግሞ ከካራካስ ጥቂት እንደተጓዙ እነዛን በራሳቸው የአኗኗር ዘይቤ የሚኖሩ ህንዶችን፣ የማራካይቦን የሀይቅ ከተማን፣ እንዲሁም የአንዲስን ተራራ እና መልከዓ ምድራዊ አቀማመጥ መመልከት በራሱ መንፈስ ያድሳል፡፡

በአጭሩ ቬንዜውላ በተፈጥሮ ሀብት እጅግ የታደለች ስለሆነች ሀገሪቷ ትርኪሚሪኪ የሚያወራ የፖለቲካ ሰው ሳይሆን የሚያስፈልጋት ከተፈጥሮ ሀብት የሚገኘውን ገንዘብ እንዴት ተጠቅመን ሀገራችንን እና ህዝቦቻችንን እናሳድግ የሚል ሂሳብ አዋቂ ነው የሚያስፈልጋት፡፡

በ1950 'ኮለኔል ቻልባድ' ከተገደለ በኂላ ኮለኔል ፔሬዝ ስልጣኑን ተቆጣጥሮት ነበር፡፡ ፔሬዝ ስልጣን ላይ ከወጣ በኂላ ከእዚህ በፊት ከስልጣን የተወገዱ የመንግስት አካላትን ደብቆ ያኖራቸዋል ተብሎ ይታማ ነበር፡፡ ይህ ሰው ስልጣን ላይ እንደወጣ አምባገነንነት የተሞላበት አገዛዙን ወዲያው ነበር ያንፀባረቀው፡፡ መጀመርያ ላይ ያደረገው የሀገሪቱን የጋዜጣ ድርጅቶች እና የሬድዮ ጣብያዎችን መቆጣጠር ነበር፡፡ በመቀጠል የኮሚኒስት እና የአዲኮስ አባል የነበሩ ሰዎችን እያደነ ማሰር ጀመረ፡፡

ብዙ ጊዜ የኮሚኒስት አባል የነበሩ ሰዎች ለመደበቂያ የእኛን ሆቴል ቤራ ክሩዝ ይመርጣሉ፡፡ ሁሌም ቢሆን በሆቴላችን ለመጠለል ለሚመጡ ሰዎች በራችን ክፍት ነው፡፡ "ማነህ? ከየት ነው የመጣኸው?" የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳት አንፈልግም፡፡ በዛ ላይ ደግሞ እኔን ከፍርድ እስረኝነት ነፃ ያወጣኝ መንግስት አባላትን መደበቅ እንደ ትልቅ እድል ነው የምቆጥረው፡፡ ውለታቸውን ለመመለስ ይሄን ማድረጌ በቂ ባይሆንም የተወሰነ እፎይታ ግን ሰጥቶኛል፡፡ በርግጥ እነዚህን የኮሚኒስት አባላት መደበቅ በጣም አደገኛ የሆነ ድርጊት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ቢሆንም ግን ከመሸሸግ ወደኋላ አንልም ነበር፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሆቴላችን ከተለያዩ ቦታዎች ምንም ገንዘብ ሳይዙ ወደ ቬንዙዌላ ለሚመጡ ፈረንሳውያን ጥሩ መጠለያ ሆኗል፡፡ ለሰዎች ደግ ማድረግን ከቬንዜላውያን የተማርኩት ስለሆነ እነዚህን ሰዎች ስራ እስኪያገኙ ድረስ ምግብም ሆነ ማደርያ ያለምንም ክፍያ በሆቴላችን እንዲያገኙ እናደርጋለኝ፡፡ ይህ ድርጊቴ በማራካይቦ በጣም ከመታወቁ የተነሳ "የፈረንሳውያን ጠበቃ" የሚል ቅፅል ስምም አሰጥቶኝ ነበር፡፡

* * * * * * * * *

በዚህ ዓመት በህይወቴ ሪታን በማግኘቴ የተደሰትኩትን ያህል የሚያስደስተኝ ነገር ገጠመኝ፡፡ሪታ አባቴን ፍለጋ ፈረንሳይ ደርሳ እንደተመለሰች ታንቴ ጁ ለካ ለእህቶቼ ደብዳቤ ፅፋላቸው ነበር፡፡ ይህንን ለማወቅ የቻልኩት ባላሰብኩት ሰዓት የታንቴ ጁ እና የሁለቱ እህቶቼ ደብዳቤ እጄ ላይ ሲገባ ነው፡፡ ከሃያ አመታት በኋላ ዝምታው ተሰብሮ የእህቶቼን ንግግር የያዘ መልዕክት እጄ ላይ ደረሰ፡፡ ደብዳቤውን ለመክፈት ከመፍራቴ የተናነሳ እጆቼ ሲንቀጠቀጡ ይታወቀኛል፡፡ "በህይወታችን ገብተህ እናዳትበጠብጠን... አንፈልግህም" ይል ይሆን ወይስ "በመኖርህ በጣም ደስተኞች ነን" ነው የሚለው... ደብዳቤውን ሳልከፍተው በውስጡ ስላለው ሀሳብ ብዙ ተጨነኩ፤ በመጨረሻም ያበጠው ይፈነዳ ብዬ ደብዳቤውን ከፈትኩት፡፡

አሸንፈሀል ፓፒ!! ደብዳቤዎቹ እህቶቼ በእኔ መኖር እጅግ ደስተኛ መሆናቸውን በሚገልፅ ማራኪ ቃላቶች የተሞሉ ናቸው፡፡ የሁለቱንም እህቶቼን ደብዳቤ አንብቤ እንደጨረስኩ በአካል የማላውቃትን የታንቴ ጁን ደብዳቤ

ከፈትኩት፡፡ እሷም ነፃነቴን ተጎናፅፌ እየኖርኩ ባለሁት ህይወት የእናት ያህል ደስተኛ እንደሆነች ነው የገለፀችልኝ፡፡ በእዚህ ደብዳቤ ውስጥ በርግጥ እህቶቼን ብቻ አልነበረም ያገኘሁት፤ ከእነሱ በተጨማሪ ወደፊት የእኔም ቤተሰብ የሚሆኑትን የእነሱን ቤተሰብም እንጂ፡፡ ትልቋ እህቴ እዛው አርድቼ ውስጥ ከባለቤቷ ጋር እንደምትኖር እና የአራት ልጆች እናት እንደሆነች ደብዳቤው ያትታል፡፡ ሶስቱ ሴቶች ሲሆኑ አንድ ወንድ ልጅ ነበራት፡፡ ከዛ በተጨማሪ እህቴ ከእንደዛ አይነት የተጨማለቀ ህይወት ወጥቼ በራሴ ጥረት ነፃነቴን ማግኘቴ እንዳስደሰታት በደብዳቤው ላይ በስፋት ገልፃለች፡፡ ባለቤቷም ቢሆን በደብዳቤው ላይ ለረጅም አመታት ያጣሁትን ነፃነቴን በመቀናጀቴ የተሰማውን ደስታ ገልፆልኛል፡፡

ሌላኛዋ እህቴ ፓሪስ ውስጥ አንድ ኮርሲካዊ ጠበቃ አግብታ እንደምትኖር ከላከችልኝ ደብዳቤ ተረዳሁ፡፡ እሷም ሁለት ወንዶች እና አንድ ሴት ልጅ ነበራት፡፡ ባለቤቷ ጥሩ የሚባል ስራ እንደሚሰራ እና የተሻለ ኑሮ እንደሚኖሩ ከደረሰኝ ደብዳቤ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ከእነሱ የመጣው ደብዳቤ ሲጀምር "ፓፒ… ነፃ ሰው ሆነህ፣ የራስህ ቤት እና ንብረት አፍርተህ እንደማንኛውም ሰው የሰላም ኑሮ እየኖርክ መሆኑን አውቀናል፡፡ ትንሹ ወንድሜ ባጋጠመህ መልካም እድል በጣም ተደስተናል፡፡ እኔ፣ ልጆቼ እና ባለቤቴ ከእነዚያ አሰቃቂ እስር ቤቶች አሸንፈህ በመውጣትህ ፈጣሪን በጣም ነው ያመሰገነው" ይላል

ለመጀመርያ ደብዳቤያቸው ምላሽ እኔም በተራዬ ለሁሉም በየአድራሻቸው ላኩኝ፡፡ ከዛ በኋላ በቃ ክብር ለአምላክ ይግባውና ደብዳቤዎች ከፈረንሳይ ወደ እኔ ይመጣሉ እኔም ወደ እነሱ እልካለሁ፡፡ በተለይ ትልቋ እህቴ ስላሳለፉት ህይወት፣ ስለ ጦርነቱ የሚገልፁ ሁነቶችን ከፎቶ ጋር አብራ ትልክልኛለች፤ እኔም በተመስጦ ስለነበር የማነበው ስላሳለፉት ህይወት ከሞላ ጎደል ለማወቅ ችያለሁ፡፡ እኔም ደብዳቤ ስልክላት ፎቶዬንም አንድ ላይ ልኬላት ስለነበር ሁለተኛ ላይ በላከችልኝ ደብዳቤ ላይ እንዲህ ብላኝ ነበር " የላክልኝን ፎቶ ሳየው በጣም ደንግጫለሁ… ቁርጥ አባታችንን አይደል እንዴ የምትመስለው፡፡ እሱ እራሱ በህይወት ኖሮ ቢመለከተው ይደነግጥ ነበር፡፡ በአቋም እና በመልክ እንደምትመስለው ሁሉ በፀባይም እንደምትመስለው አልጠራጠርም" አዎ እውነቷን ነበር በተግባር ባለውቅም በመልክ ግን አባቴን እንደምመስል በደንብ አውቀዋለሁ፡፡ ከዛ በተጨማሪ ታላቅ እህቴ ክሎታይድ ፈረንሳይ መጥታ በተሻለ

ሁኔታ ትምህርቷን መማር እንደምትችል እና ይሄንንም በሙሉ ደስታ ለማድረግ ዝግጁ መሆኗን ጭምር በሁለተኛ ደብዳቤዋ ላይ አስፍራለች፡፡

ይህን ዓመት ደስታ በደስታ ላይ ደስታ እየተደረበልኝ ነው እያሳለፍኩ ያለሁት፡፡ ከእህቶቼ በተጨማሪ ሮያሌ እስር ቤት በነበርኩበት ወቅት ልክ እንደ ቤተሰቡ ቆጥሮ ስታመም ያክመኝ የነበረውን 'ዶክተር ጊበርት ጀርሜን' የሚኖርበትን አድራሻ ለማወቅ ችያለሁ፡፡ ጊበርት ከብዙ ችግሮች እንድተርፍ ጉልህ ሚና ተጫውቶልኛል፡፡በእሱ የተነሳ ነው ከቅዱስ ዮሴፍ እስር ቤት ወደ ሰይጣን ደሴት ልዘዋወር የቻልኩት፡፡ ስለዚህ በእኔ ማምለጥ ውስጥ ይህ ሰው ከፍተኛ አስተዋፆ አለው፡፡ ጊዜ ሳላጠፋ ነበር ለዶክተር ጊበርት በአድራሻው ደብዳቤ የፃፍኩለት፡፡ ከተወሰኑ ሳምንታት በኋም ከ ዶክተር ጊበርት ለእኔ የተፃፈ ደብዳቤ ደረሰኝ

"ሊዮን የካቲት 21/ 1952" ይላል ከላይ

"ለውድ ፓፒለን"

"በመጨረሻ ስለአንተ በሰማሁት ዜና በጣም ተደስቼያለሁ፡፡ ለረጅም ጊዜ ከእኔ ጋር ለመገናኘት እንደምትጥር ይሰማኝ ነበር፡፡ የላከው ደብዳቤ በመጀመርያ የደረሳት እናቴ ነበረች፤ እሷ ናት መልሳ ወደ እኔ የላከችልኝ፡፡ ፓፒ ከስንት እስር እና እንግልት በኋላ ያሰብከውን ነፃነት አግኝተህ ለእኔ ለመፃፍ በመብቃት በእኔ እና በቤተሰቦቼ ስም የተሰማኝን ደስታ ስገልፅልህ ከውስጥ ከመነጨ ልባዊ ፍቅር ጋር ነው፡፡ ሮያሌን ከለቀቅኩ አንስቶ ብዙ ጥሩ ነገሮች በህይወቴ ውስጥ ተከስቷል፡፡

ይውልህ ፓፒ በጥቅምት 1951 ጉዞዬን ወደ ኢንዶ ቻይና ለማድረግ መሄዴ የማይቀር ነው፡፡ እዛም ለሁለት አመታት ያህል ለመቆየት እገደዳለሁ፡፡ በዚህም የተነሳ በአሁኑ ሰዓት ባለቤቴ አብራኝ የምትሄድበትን መንገድ እያመቻቸሁ ነው፡፡ ፓፒ ከአንተ ጋር ከተለያየን በኋላ ብዙ ቦታዎች ላይ ኖርያለሁ፡፡ ያም ይመስለኛል በመሀከላችን ያለውን ርቀት ሊያሰፋው የቻለው፡፡ ሆነም ቀረ አሁን ተገናኝተናል፤ በማግኘቴም በጣም ተደስቻለሁ፡፡ በመልካም ጤንነት ላይ መገኘትህ እና ደስታን የሞላበት ኑሮ እየኖርክ መሆኑን በማወቄ በጣም ተደስቻለሁ፡፡ ህይወት ከባድ ብትሆንም አንተ ግን ሁሌም ተስፋ

እንደማትቆርጥ አውቃለሁ። ተስፋ ያለመቁረጥህንም ፍሬ ዛሬ ላይ አሳይተኸኛል።

የላክልኝ ፎቶዎች እንደሚያሳዩት አንተ እና ባለቤትህ በተሳካ የኑሮ አርክን ውስጥ እንዳላችሁ ነው። ማን ያውቃል አንድ ቀን መጥተን እናያችሁ ይሆናል። በፎቶ ላይ እንዳየኋት ባለቤትህም በጣም ቆንጆ ነች፤ ሆቴላችሁም በዛው ልክ የሚማርክ ነው። ሳስበው ምን ማድረግ እንዳለብህ ሳይገባህ አይቀርም። እንግዲህ ጓደኛዬ ይህን ደብዳቤና እኔ እና ባለቤቴ ከሁለት ወር በፊት 'ማርሲትል' ውስጥ ከተነሳነው ፎቶ ጋር ልኬልሀለሁ... ከእዚህ በኋላም ሁሌም ጥሩ ነገር እንዲገጥምህ እየተመኘው በቅርቡ ተገናኝተን ያሳለፍነውን ጊዜ ቁጭ ብለን እንደምናወጋው ባለ ሙሉ ተስፋ ነኝ"

"ጊበርት-ጀርሜን"ይላል

ጊበርት አይደለም እኔን ባለቤቱን ሳያገኛት ነበር በዛው አመት በኢንዶ ቻይና ጦርነት ውስጥ ሲገደል የቻለው።ያሳዝናል በአካል ቀርቶ በደብዳቤ ድጋሚ ሳላገኘው ነው ህይወቱ የተቀጨው። ይህ ሰው በእኔ ህይወት ላይ ትልቅ ቦታ አለው። ሮያሌ እስር ቤት በነበርኩበት ወቅት ምንም እንኳን ወንጀለኛ እንደሆንኩ ቢያውቅም ከሌሎች በተሻለ መልኩ ያቀርበኝ እና ይንከባከበኝ ነበር። ባለቤቱም ከእሱ ባልተናነሰ መልኩ ነበር የምታቀርበኝ። በእውነት በጊበርት ሞት ከልቤ ነበር ያዘንኩት!

ታንቴ ጁ የምትልክልኝ ደብዳቤዎች የእንጀራ እናት ስሜትን ከውስጥ አውጥቶ የእናትነት ፍቅርን ልብ ውስጥ ያሰርፃል። የአባቴን ታሪክ እስኪሞት ድረስ ያለውን ታሪክ በእሷ ደብዳቤዎች ነው ያወቅሁት ማለት ይቻላል። እኔ ለእስር በተፈረደብኝ ሰዓት ፍርድ ቤት በመመላለስ “ልጁ ንፁህ ነው” እያለ ይከራከር እንደነበር ጭምር ፅፋልኛለች።

ደብዳቤዎች ሲላኩልኝ ልክ እንደተራብ ሰው ተስገብግቤ ነበር የማነበው። እነዚህን ከቤተሰቤ ጋር ያቆራኙኝን ደብዳቤዎች በመደጋገም ለሪታ በተመስጦ ማንበብ ያስደስተኛል። ቤተሰቦቼ የአካባቢው ሰዎች ስለ እኔ ያላቸውን መጥፎ አመለካከት ወደ ጎን ችላ ብለው ባጋጠመኝ እድል የተሰማቸውን ሀሴት አሳይተውኛል። ይሄም ለእኔ ትልቅ ሰላም እና እረፍት እንዲሰማኝ አድርጎኛል።

በ1953 ሆቴል ቬራ ክሩዝን ሸጥነው፡፡ የማራካይቦም ሙቀት አጅግ የጨመረበት ወር ነበር፡፡ በእዚሁ ወቅትም ደግሞ ቬንዙዌላ ጊኒ ውስጥ የብረት ክምችት በብዛት እንደሚገኝ ወሬ የሰማንበት ወቅትም ነው፡፡ ሁኔታው በጣም አትጊ ስለነበር ለማጣራት ወደ ካራካስ መሄድ እንዳለብን ወሰንን፡፡

ሆቴላችንን እንደሸጥነው ጊዜ ሳናባክን በቅርቡ በገዛሁት ትልቅ አረንጓዴ ዋገን መኪናዬ ውስጥ የምንፈልገው እቃዎችን ጭነን ለአምስት አመት ጥሩ ወዳጆችን ያፈራንበትን እና የማይረሳ ደስታን ያጎናፀፈችንን ውዷን ማራካይቦን ላንመለስ ለቀን ወጣን፡፡

* * * * * * * * *

ካራካስ በድጋሚ!... ምንአልባት መምጣት የሌለብኝ ቦታ ይሆናል የመጣሁት፣ ቢሆንም ግን ብዙም የሚያስጋኝ ነገር ያለ አይመስለኝም፡፡ እኛ ካራካስ በገባንበት ወቅት አምባገነኑ ፔሬዝ ቤፋ የሀገሪቱ ፕሬዘዳንት መሆኑን አሳውጆ ነበር፡፡ ያ ማለት ግን ሙሉ ህዝባዊ ድጋፍ አለው ማለት አይደለም፡፡ የአምባገነኑ ፔሬዝ አመራር ሰላም የማይሰጣቸው ብዙ ዜጎች እንዳሉ መዘንጋት የለበትም፡፡ ታድያ እነዚህ ሰዎች ቅሬታቸውን በተለያየ መንገድ ሲገልፁ ቆይተዋለል፡፡ በእርግጥ ፔሬዝም የሚቃወመው ስለበዛ ምንም አልሰራም ማለት አይደለም፡፡ ካራካስን በአጠቃላይ ቀይሯታል ማለት ይቻላል፡፡ ከካራከስ እስከ ሜይኩታ አየር ማረፍያ ድረስ ያለው ያረጀ መንገድ እንዳለ ቢሆንም ከከተማውዋ እስከ ባህር ዳርቻው ያለውን መንገድ ግን በጣም በሚያምር መልኩ አስርቶታል፤ በፊት ከሁለት ሰዓት በላይ ይወስድ የነበረው ይህ መንገድ አሁን ከግማሽ ሰዓት ባነሰ ጊዜ ውስጥ መድረስ በሚያስችል ደረጃ ነው ያሰራው፤ በሳይለንሺዎ አውራጃም ኒዎርክ ላይ ከተሰሩ ፎቆች የማያንሱ ህንፃዎችን ማሰራት ችሏል፤ ከእሱ በተጨማሪ በከተማዋ ውስጥ ከዳር እስከ ዳር ሊያገናኝ የሚችል ባለ ስድስት መስመር መንገድ አሰርቷል፡፡ እነዚህ እንግዲህ ከሰራቸው ስራዎች ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ይህን ሁሉ ስራ ሲሰራ ብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ለስራው ማዋሉ የማይካድ ሀቅ ነው፡፡ ያ ማለት ደግሞ ፔሬዝ ምንም እንኳን አምባገነንነት ቢያጠቃውም ለሀገሪቱ እድገት ግን ጥሩ ሚና ተጫውቷል ማለት

ነው፡፡ በካራካስ ያደረግነው እረፍት ከተማዋ ውስጥ ያሉኝን ጓደኞቼን እና ፒኮሊኖን ለመፈለግ ጥሩ እድል ከፍቶልኛል፡፡ ፒኮሊኖ በአሁን ሰዓት ምን አጋጥሞት እንደሆነ አላውቅም፡፡ ባለፉት ዓመታት አልፎ አልፎ በሰዎች ጥቂት ገንዘብ እልክለት ነበር፡፡ ማራኳይቦም በነበርኩበት ሰዓት እኛ ጋር መጥቶ እንዲኖር መልዕክት ልኬበታለሁ፤ ነገር ግን ብዙ ዶክተሮች ያሉት ካራካስ ውስጥ ስለሆነ እና ያለእነሱ እርዳታ ደግሞ በጤናው ላይ ለውጥ ማምጣት ስለማይችል እዛው መቆየቱን እንደሚመርጥ እሱም በጓደኛው መልዕክት ልኮልኛል፡፡ ሙሉ ለሙሉ ማውራት መቻሉን እና ቀኝ እጁም ቢሆን የተሻለ ለውጥ እንዳለሁ በጓደኛው በኩል ለማወቅ ችያለሁ፡፡ አሁን ግን የት እንዳለ የሚያውቅ ሰው የለም፡፡ላ ጉዌራ ወደብ አካባቢ ታይቶ ነበር፤ ከዛ በኋላ ግን ደብዛው ጠፍቷል፡፡ "የት ሄዶ ይሆን... ወደ ፈረንሳይ ወይስ ወደ ሌላ ቦታ" ያለበትን አለማወቁ ውስጤን ረበሸኝ... ወደ ማራኳይቦ እንዲመጣ ማስገደድ ነበረብኝ!! "በሄድክበት ሁሉ ቀና መንገድ ይግጠምህ ፒኮ" አልኩ ከወህኒ ቤት ያስናበተኝን ፖሊስ አዛዥ ንግግር አስታውሼ

በዛች በእቃ በታጨቀች ዋገን መኪናችን የካራካስ ዋና እይታ ወደ ሆነችው ሲዮዳድ ቦሊቫር ሄድን፡፡ ከስምንት አመት በኋላ ነው እንግዲህ እቺን በፍቅር የተሞሉ ህዝቦች መኖርያ የሆነች ከተማ በድጋሚ ማየት የቻልኩት፡፡ ደክሞን ስለነበር ምሽቱን በተከራየነው ሆቴል ውስጥ አሳለፍነው፡፡ በነጋታው ንፋስ እየወሰድን ቡና መጠጣት ስለፈለግን እዛው ሆቴላችን ውስጥ ወዳለው መናፈሻ ሄደን ቡና አዘን አንዱ መቀመጫ ላይ ቁጭ አልን፡፡ እዛ ቁጭ ብለን ቡና በመጠጣት ላይ እንዳለን አንድ እድሜው በሀምሳዎቹ ውስጥ ያለ ቀጭን እና ረዥም ሰውዬ ወደ እኔ ሲመለከት ያየሁት፣ ፊቱ በፀሀይዋ ንዳድ ወይቧል፣ በመገረም አተኩሮ ከተመለከተኝ በኋላ ትንንሽ አይኖቹን በለጠጣቸው፡፡ ቀጥሎም እየተጣደፈ በቀጥታ ወደ እኛ መጥቶ

"ካላበድኩ በስተቀር አንተ ፈረንሳዊው ፓፒለን ነህ?!"

እኔም ማንነቱን ባውቀውም ለሪታ የሚገባትን ሰላምታ ሳያቀርብ ዘሎ ወደወሬ መግባቱ ስላናደደኝ

"ምን አይነት ወራዳ ነህ ባክህ አጠገቤ ያለችውን ሴት አይተሃታል?"

"በጣም ይቅርታ ከመደነቁ የተነሳ ነው የዘነጋኋት"

"ተወው በቃ... በል ና ተቀላቀለን... አብረህን ቁጭ በል"

የድሮ ጓደኛዬ ነው 'ማርሴል በ.' ይባላል፣ እኔን በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ በማግኘቱ ተገርሟል:: ለእኔ እዚህ መድረስ ዕድል ከፍተኛውን ሚና እንደተጫወተች ነገርኩት፤ በተቃራኒው ለእሱ እድል ጀርባዋን እንደሰጠችው የለበሰው ልብስ ይናገር ነበር::ምሳ አብረን እንድንበላ ሀሳብ አቀረብኩለት፤ እሱም ሳያቅማማ ግብዣዬን ተቀበለው:: ሶስታችንም ለምሳ እንደተቀመጥን ማርሴል ወደ ሪታ ዞሮ "እውነት ነው እሜቴ... አሁን እንዲህ ሆኜ አይተሽኝ ስለእኔ ያለሽ አመለካከት ጥሩ ባይሆን አይገርመኝ:: ወጣት እያለሁ ህይወቴ የተስተካከለ እና የተሳካ ነበር:: በጊዜው ምንም አይነት ነገር አልፈራም ነበር:: በመጀመሪያ ከእስር ካመለጥኩ በኋላ የሄድኩት ወደ ካናዳ ነው:: እዛም የካናዳ የፖሊስ አባል የመሆን እድሉን አግኝቼው ነበር:: በፖሊስነትም ብዙ አመት ሰርቻለሁ:: ነገር ግን አንድ ክፉ ቀን ከሆነ ሰው ጋር ፀብ ገጥሜ ሳለ ሳይታሰብ ሰውዬው ከጎኔ በያዝኩት ጩቤ ላይ ሊወድቅ ቻለ:: በዚህም ምክንያት ህይወቱ አለፈች:: ይህ ካናዳዊ ሰው ሊሞት የቻለው በተሰካበት ጩቤ ቢሆንም እኔ አስቤው ያደረኩት ሳይሆን በምንጣለበት ወቅት እላዬ ላይ ሲወጣ በአጋጣሚ ከጎኔ በያዝኩት ጩቤ ላይ ሊያርፍ በመቻሉ ነው:: በርግጥ አላመንሽኝ ይሆናል ለነገሩ የካናዳ ፖሊሶችም አላመኑኝም፤ ስለዚህ በፍጥነት ያደረኩት መጀመርያ ወደ አሜሪካ ከተጓዝኩ በኋላ መዳረሻዬን ፓሪስ አደረግሁ:: ነገር ግን ፓሪስ ስደርስ ማን እንዳቃጠረ ባላውቅም በፖሊሶች ተይዤ ወደ ዘብጥያ ወረድኩ:: የዛኔ ነው እንግዲህ ባለቤትሽን የማውቀው፤ የዛሬን አይበለው እና ምርጥ ጓደኛማማቾች ነበርን" ብሏት ንግግሩን ቋጨ:: እኔም ምንም እንኳን የማውቀውን ታሪኩን ቢሆንም ለሪታ የደገመላት ሳዳምጠው ግን እንደ አዲስ የሆነ ስሜት ፈጥሮብኝ ነበር

"እና አሁን ምን እያደረክ ነው ማርሴል?" አልኩት ከገባበት ትዝታ ለማንቃት

"ሞስ ሞሪቸልስ ውስጥ ቲማቲም አሳድጋለሁ"

"በጥሩ ሁኔታ ያድግልሀል?"

"በከፊል ያድጋል... አንዳንዴ ግን ደመናው ፀሀይ ብርሀኗን ለቲማቲሞቹ እንዳይደርስ ይጋርደዋል:: በዚህ ሰዓትም የፀሀይዋን ጨረሮቹ በአይን

ወደማይታዩ መርዛማ ጨረሮች ይቀየራሉ:: በዚህም ምክንያት ቲማቲሞቹ ይደርቁብኛል::

"በፈጣሪ! ምን አይነት ነገር ነው ባክህ?"

"የተፈጥሮ አንዱ የሚገርም ክስተት መሆኑ ነው እንግዲህ"

"እዚህ ሌሎች በወንጀል ተጠርጥረው ታስረው የነበሩ ሰዎች አሉ እንዴ?"

"አዎ. . .ከ ሃያ ያላነሱ ሰዎች አሉ"

"ደስተኞች ናቸው?"

"ማለት ይቻላል "

"እና ከእኔ የምትፈልገው ነገር አለ?"

"እ... የእውነት ፓፒ እንደዚህ ብለህ ባትጠይቀኝ ኖሮ ምንም ባላልኩህ ነበር... ነገር ግን አንተ ካነሳኸው አይቀር አንድ የማስቸግርህ ነገር ይኖራል"

"ምንድነው የምትፈልገው ማርሴል... ተናገር" አልኩት በልቤ ከባድ ነገር እንዳይጠይቀኝ ፈጣሪዬን እየለመንኩ

"ካላስቸገርኩህ ሁለት ሱሪ፣ ሁለት ጫማ፣ ቲሸርት እና ከረባት እንድትገዛልኝ እፈልጋለሁ"

"ይሄማ በጣም ቀላል ነው... ና ወደ መኪናዬ እንሂድ" ተያይዘን መኪናዬን ወዳቆምኩበት ቦታ ሄድን

"ያንተ መኪና ነች... እውነትም እድል ከአንተ ጋር ነበረች"

"እውነት ነው"

"እኔ ምልው ፓፒ እዚህ ትቆያላቹ እንዴ?"

"አንቆይም"

"መቼ ልትሄዱ ነው?"

"ዛሬ ማታ"

"እ... ያሳዝናል... ዛሬ ባትሄዱ ኖሮ የጋብቻ ስነ-ስረዓቱ ላይ ትታደሙ ነበር"

"የምን ጋብቻ?"

"ለካ አልነገርኩህም... ልብስ እና ጫማውን የፈለኩት እኮ አንዱ ጓደኛዬ ስለሚያገባ ነው"

"እኔ አውቀዋለሁ?"

"እኔንጃ... ምን አልባት ካወቅሽው 'ማቹሬቴ' ይባላል"

"አዎ! በደንብ አውቀዋለሁ እንጂ... ከቅዱስ ላውረንት-ዱማሮኒ ሆስፒታል እንድናመልጥ የረዳን ሰው ነው። ከዛ በተጨማሪ ባህር ላይ በምናመልጥበት ወቅት አብሮን ረጅም ጉዞ ተጉዟል። እስኪ ከቻልኩ ሰርጉ ላይ ለመገኘት እሞክራለሁ" ዛሬ ማታ ልናድገው የነበረው ጉዞ በማቹሬቴ ሰርግ ምክንያት እንድንሰርዘው አደረገን። በአንድ ወቅት ውለታ የዋለልኝ ሰው ሰርግ ላይ በአጋጣሚ መታደም መቻል እድለኝነት ነው። በነጋታው ማርሴል በሰጠን አድራሻ መሰረት ወደሰርጉ ቦታ አመራን። እኛ ስንደርስ እድምተኛው ገብቶ እየተስተናገደ ነበር። ማቹሬቴ ከአንዲት ትንሽ ጥቁር ሴት ጋር ለሙሽሮቹ በተዘጋጀው ትንሽዬ መድረክ ላይ ተቀምጧል። ምንም እንኳን ሰፈራቸው ደሀ ተብሎ የሚጠራበት ማህበረሰብ የሚኖርበት ቢሆንም ግን የእሱ መኖርያ ቤት ግን የተሟላ ነው፤ በውስጡ ኩሽና፣ መታጠብያ ክፍል እንዲሁም መመገቢያ ክፍልን አካቶ የያዘ ነው። እድምተኛው ከቀነሰ በኋላ ማቹሬቴን በቅርበት በማግኘት ለተወሰኑ ደቂቃዎች አወራን፣ ነገር ግን ለሁለተኛ ጊዜ እንዴት ልናመልጥ እንደቻልን ለማውራት ሁኔታው አመቺ አልነበረም፤ ዋናው ነገር ሁለታችንም ለማምለጥ ችለናል። በመጨረሻም ከሁለቱም ጋር እንደምንገናኝ ቃል ተገባብተን ተለያን። እኔም ሪታዬን ይዤ ወደዛች የብረት ክምችት ወደ.ተገኘባት ወደተባለው ሲዮዳድ ቦሊቫር ተመለስኩ። በጉዟችን ወቅት ማቹሬቴን በእዚህ ሁኔታ ላይ ማግኘቴ አስደንቆኝ ነበር።

"አይገርምም" አልኳት መኪናችን ውስጥ ቁጭ ብልን በመጓዝ ላይ እያለን

"ምኑ"

"ይህ ሰው ልክ እንደኔው የመከራን ገፈት ቀምሷል። ሁለታችንም ከእስር ካመለጥን በኋላ እንደገና ተይዘን ታስረናል። ከዛ በተጨማሪ ለሁለት አመት ያክል እኔም እሱም የብቸኝነት እስርን ቀምሰናል። አስቢው እስኪ እኔ እና አንቺ እዚህ የመጣነው ተገኘ የተባለውን የብረት ማዕድን ለመፈለግ ነው፤ የአጋጣሚ ነገር ሆነና ግን የእሱ የሰርጉ ዋዜማ ላይ ደረስን "

"እውነትም ድንቅ አጋጣሚ ነው... ያልታሰበ ቀን የማይረሳ ገጠመኝ ጥሎ አለፈ" አለችኝ ሪታ ልክ እንደ እኔው በሁኔታው ተገርማ

የማቹሬቴ ሰርግ አንድ ትልቅ ነገር አስተምሮኝ አለፈ፤ እርሱም ማንም ሰው ያሳለፈው ከባድ ህይወት ካመነበት ጥሩ ህይወት ከመምራት እንደማያግደው ነው። ለእዚህ ደግሞ እኔ፣ ማቹሬቴ እና ቻርሎቴ በቂ ማሳያዎች ነን።

በሲዮዳድም ለተወሰኑ ቀናቶች ብንቆይም ምንም ልንፈጥር የቻልነው አዲስ ነገር ስለሌለ ሁሉንም ነገር ትተን ወደ ካራካስ ለመመለስ ተገደድን። ካራካስ ደርሰን ብዙም ሳንንገላታ ለእኛ ተስማሚ የሆነ ስራ አገኘን። ስራው እንደተለመደው የምግብ ቤት ስራ ነበር፤ ምግብ ቤቱን በፊት ይሰራበት የነበረው ሰው 'አራጎን' ብሎ ሰይሞታል። ከ ካራቦቦ መናፈሻ ብዙም ሳይርቅ የሚገኘው ይህ ሆቴል በጣም የሚመስጥ ነበር። በመጀመርያ ሆቴሉን ይዞት የነበረው ሰውዬ ሆቴሉን ለመልቀቅ የተገደደው ኪሳራ ስለደረሰበት ነበር። ዜግነቱ 'ካናራዊ' (በሰሜን ምዕራብ አፍሪካ የምትገኝ በተራሮች የተከበበች ሀገር ነች) ስለነበር የምግብ ዝርዝሮቹ ከእርሱ የአኗኗር ዘይቤ ጋር ተላምደው የመጡ ናቸው። ያም ይመስለኛል ለኪሳራ የዳረገው። ስለዚህ ሆቴሉን ስንከራየው በቅድሚያ ያያደረግነው የምግብ ዝርዝራችንን የፈረንሳይ እና የቬንዙዌላን ምግቦች ያካተተ እንዲሆን ማድረግ ነው። በእዚህ አካሄዳችንም ተሳክቶልን በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ደንበኞችን መሳብ ቻልን። ከደንበኞቻችን መካከል በሙያቸው የተከበሩ ዶክተሮች፣ የጥርስ ሀኪሞች፣ ኬሚስቶች፣ ጠበቃዎች የፋብሪካ ባለቤቶች ይገኙበታል። ይህም ስራችን ጥራት ያለው እና በሰዎች ተመራጭ ስለመሆኑ ማሳያ ነው። እኛም ሆቴሉን ከተከራየንበት አንስቶ ያለፈውን አንድ ወር ደስ በሚል ሁኔታ ለማሳለፍ ችለናል።

ቀኑ ሰኔ 6/1956 እለቱ ደግሞ ሰኞ ነበር። ረፋዱ አካባቢ ላይ የሚያስደስት የምስራች ሰማሁ፤ የሀገሪቱ የውጪ ጉዳይ ቆንፅላ ከእዚህ በፊት አቅርቤው የነበረውን ቬንዜዌላዊ የመሆን ጥያቄዬን እንደተቀበሉት የሚገልፅ ዜና ነበር የደረሰኝ።

በእዚች ሀገር ለአለፉት አስር አመታት በመኖሬ ሰኔ 16/1956 የሀገሪቷ ብሄራዊ ክብረ በዓል በሚከበርበት እለት ለአዲሷ ሀገሬ መሃላ ለመፈፀም ዝግጁ ሆኜ ተገኝቻለሁ። ከእኔ ጋር ለሎች ሶስት መቶ የሚሆኑ ሰዎች የቬንዙዌላን ዜግነት ለማግኘት እየተጠባበቁ ነበር።ሪታ እና ክሎታይዳ በስነ ስረዓቱ ላይ ለመታደም ከተገኙት ሰዎች መሀል ተቀምጠዋል። ምን እየተሰማኝ እንደሆነ ለማወቅ በጣም ከብዶኛል። የቬንዙዌላ መንግስት ለእኔ ባለውለታዬ ነው። አሁን ላለሁበት ጠንካራ አቋም በመንፈስም ሆነ በቁስ ከፍተኛ ድጋፍ አድርጎልኛል። ለእዚህም ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን ማቅረብ እፈልጋለሁ።

የሀገሪቷ ብሄራዊ መዝሙር ሲከፈት ሁሉም ሰው ከተቀመጠበት ተነሳ።እኔም ከግራ ወደ ቀኝ የምትውለበለበውን የቬንዙዌላን ሰንደቅ አላማ ትኩር ብዬ ስመለከት ሳላስበው እንባ ከአይኔ እየተንከባለለ መውረድ ጀመረ። በውስጤም ከቬንዜዌላ ህዝብ መዝሙር ውጪ የሌላ ሀገር ህዝብ መዝሙር ላለመዘመር ቃል ገባሁ። ምክንያቱም የወለደችኝ እናት ሀገሬ ስገፋኝ ቬንዙዌላ ግን አቅፋ ሰው እንድሆን እረድታኛለች። ስለዚህ ሀገሬ እቺ ነች!! ለአዲሷ ሀገሬ ክብርም ድምፄን ከህዝቡ እኩል ከፍ አድርጌ ብሄራዊ መዝሙሯን መዘመር ጀመርኩ

" Abajo cadenas..."

ይቺ ቀን ለረጅም ጊዜ በውስጤ ተጋርዶ የነበርው ጭጋግ ግልጥልጡ የወጣባት ቀን ናት ማለት ይቻላል።

"ከአሁኗ ሰዓት ጀምሮ የእናንተም ሀገር ለሆነችው ቬንዜዌላ ቃለ መሃላችሁን አሰሙ" አለ የፕሮግራሙ አስተባባሪ ሶስት መቶዎችንም በአንድ ድምፅ ለአዲሷ ሀገራችን ቃለ መሀላችንን ሰጠን። የገዛ ሀገሬ ባልሰራሁት ወንጀል ዘብጥያ ብታወርደኝም ይቺ ሀገር ግን ሰው ነህ ብላ አንስታ አከበረቺኝ፤ ስለዚህ ለቬንዙዌላ ያለኝ ክብር እስሞት ድረስ የፀና ነው!!

# ምዕራፍ አስራ ሶስት

## ወደ ስፔን ጉዞ

ቬንዙዌላዊነቴን የሀገሪቱ መንግስት ማፅደቁን በይፋ ካወጀልኝ በኋላ ከተወላጁ እኩል መብት እንዳለኝ እንዲሰማኝ አድርጎኛል፡፡ አልፎ ተርፎ ዜግነቱን ማግኘቴ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ እድል እንዲመቻችልኝ መንገዱን ከፍቶልኛል፡፡ ከእዚህ በኋላ እኔ የፈረንሳዩ ወንጀለኛው ሄነሪ ሳልሆን ህይወት አስከናኝ በተረጋጋ የህይወት ምህዳር ውስጥ የምገኝ ቬንዜዌላዊው ፓፒለን ነኝ፡፡ ካራካስ ውስጥ የጀመርነው የሆቴል ስራ ልክ እንደ ሆቴል ቬራ ክሩዝ ሁሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ ስም እና ዝናን የተጎናፀፈ ሆኗል፡፡ ደንበኞቻችንም ከቀን ወደ ቀን ቁጥራቸው በመጨመሩ የእኛም ገቢ በዛው ልክ እያደገ ነበር፡፡ ነገሮች በእንደዚህ አይነት መንገድ እየሄዱ ባሉበት ወቅት ታንቴ ጁን እና እህቶቼን ማግኘት የምችልበትን ሀሳብ ሪታ አቀረበችልኝ፡፡

"እኔ እምልህ ፓፒ"

"ወዬ የእኔ ፍቅር"

"አንድ ሀሳብ መጥቶልኝ ነበር... እንደምትወደውም እርግጠኛ ነኝ" አለች አንዳች ነገር ልትነግረኝ እንዳሰበች ከአኳኋኗ መረዳት ቀላል ነበር

"ምንድነው እሱ?" አልኳት እኔም በመጓጓት ስሜት

"ወደ ስፔን እንሄዳለን"

"ለምን?"

"ምናልባት እህቶችህንና ታንቴ ጁን ለማግኘት ፈረንሳይ መግባት ላይጠበቅብህ ይችላል... እዛ መግባ አለመቻልህ ግን እህቶችህን እንዳታገኝ አያግድህም፡፡ እኛ

በእዚህ ወቅት ኑሮዋችንን ከመምራት በዘለለ የምንፈልገውን ለማድረግ የሚያስችለን በቂ ገንዘብ አለን:: ስለዚህ ካራካስ ያለንን ህይወት ለጊዜው ተወት አርገነው የሚያስፈልጉንን እቃዎች መኪናችን ላይ ጭነን በመርከብ ጉዟችንን ወደ እስፔን እናደርጋለን:: ከዛ አንተ ስፔን ትቆያለህ እኔ ደግሞ ወደ ፈረንሳይ ሄጄ እህቶችህን እና ታንቴ ጁን ወደ ስፔን ይዣቸው እመጣለሁ ማለት ነው:: እንዴት ነው ጥሩ ሀሳብ አይመስልህም?" አለችኝ ምን ማለት እንዳለብኝ እንኳን ቃል አጣሁ፤ ብቻ የሪታ አፍቃሪነት ከአእምሮዬ በላይ መሆኑን ስለእኔ ጉዳይ ከእኔ በላይ መጨነቋ በቂ ምስክር ነው:: ከእኔ የምጠብቀው መልስ ምን እንደሆነ ባላውቅም ከአንደበቴ የወጣው ግን አንድ ቃል ነው

"እስከሞት አፈቅርሻለሁ ሪታ" አልኳት ከዛ ደረቴ ላይ ልጥፍ አድርጌ አቀፍኳት

ካራካስ የጀመርነውን የሆቴል ስራ አቁመን ወደ እስፔን ለመጓዝ በአጭር ጊዜ ውስጥ ዝግጅታችንን አጠናቀን ጨረስን:: በእርግጥ አብዛኛዎቹ ደንበኞቻችን ስራችንን በማቆማችን ደስተኞች አልነበሩም፤ መልቀቃችንን ሲሰሙ ሁሉም ደንበኞቻችን በምስጋና እና በሀዘኔታ ነው የሸኙን፤ ግማሹ ስለምናዘጋጀው ምግብ ጥራት አድናቆቱን ሰጥቶ ይሰናበተናል፤ ሌላው ስለ መልካም መስተንግዷችን እና አቀባበላችን አመስግኖን ይሄዳል:: በአጠቃላይ ሆቴሉን ስንለቅ ሰዉ ያሳየን ፍቅር እና ክብር ሆቴሉ መከራየት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እንደኛ የሰራበት ሰው እንደሌለ በቂ ማሳያ ነው::

የምንፈልገውን እቃ ከእነመኪናችን መርከቧ ላይ ጭነን ልጃችንን ደግሞ ከሰራተኛዋ ጋር ካራካስ በሚገኘው ቤታችንን ውስጥ ትተን እኛ ጉዞዋችንን ወደ ስፔን አደረግን:: ለክሎታይድ እስክንመለስ የሚያስፈልጋትን ነገሮች ሁሉ ስላሟላንላት ከእሷ መራቃችን ብዙም አላስጨነቃትም:: ለእህቶቼ እና ለታንቴ ጁ አስቀድመን ደብዳቤ ልከንላቸው ስለነበር መቼ እንደምንደርስ እንጂ መቼ እንደምንነሳ ያወቁ ነበር:: ምንም እንኳን የምናደርገው ጉዞ ረጅም ቢሆንም ለእኔ ግን ከሁለት እና ከሶስት እጥፍ በላይ ነበር የረዘመብኝ:: ለነገሩ "እውር አይንህ ነገ ይበራልሀል ሲሉት ዛሬን እንዴት አድሬ" አለ አይደል የሚባለው. . . የእኔም እንደዛው ነው!! ለዘመናት ፊልጌ ማግኘት የተሳነኝን ስጋዎቼን ላገኛቸው መሆኔን ሳስብ ጊዜው የክፍለ ዘመን ያህል የራቀብኝ ቢመስለኝ

አያስደንቅም፡፡ እራሴን ሰብስቤ መቀመጥ ስላቃተኝ በመርከቧ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ በማለት ጊዜው እንዲሄድልኝ ጣርኩ፡፡

አሁንም በመርከቧ የፊተኛዋ ክፍል ላይ እንደተቀመጥኩ የስፔንን ምድር ለማየት እንደቋመጥኩ ነው ያለሁት፡፡ በእዚህ መሀል "እንዴ እዚህ ምን ትሰራለህ ፍቅሬ? ለደቂቃዎች እየፈለኩህ ነበር እኮ" የሚል የሪታን ድምፅ ከኋላዬ ሰማሁ፡፡ ምንም ሳልል ብድግ ብዬ አቀፍኳት፤ የዛኔ የተጨነቀው ውስጤ ሲረጋጋ ይታወቀኛል፤ ውስጤን ጨምድዶ ይዞት የነበረውን የፍርሀት ስሜቱን በሪታ እቅፍ ውስጥ መሆኔ ሲያበርደው ታወቀኝ፡፡ ለዘመናት ያጣኋቸውን ቤተሰቦቼን ለማየት መቸኮሌ ሰላም ሲነሳኝ የእኔ የብቻዬ ቤተሰብ የሆነችው ግራ ጎኔ መጥታ ሰላሜን መለሰችልኝ፡፡ ለእዚህም ደረጃ እንድበቃ ያደረገችኝ እሷ ነች፡፡ ሪታ እፎይታዬ ነች!! ይህ የማልክደው ሀቅ ነው!!

"ውዴ ለዘመናት በአይነ ስጋ የተለየኋቸውን እና ሞት እናዳላያቸው ያስገደደኝ ቤተሰቦቼ ወዳሉበት ምድር መቃረቤ ሳስብ ፍርሀት ውስጤን ወሯት ነበር፡፡ አንቺ ስትመጪልኝ ግን ነፃ ሰው አደረገሽኝ " አልኳት አይን አይኗን እየተመለከትኩ

የማይደረስ የለ እያማጥኩም ቢሆን በስተመጨረሻ የናፈቋትን የስፔንን ምድር ለማየት ቻልኩ፡፡ ከጥቂት ሰዓታት ጉዞ በኋላ ወደ የብስ ቀርበን ከመርከቧ መውረድ ቻልን፡፡ በማስከተልም እቃዎቻችንን የጫንባትን መኪናዬን ለማውረድ ወደ መርከቧ የእቃ ማውረጃ አመራን፡፡ ከዛ በመኪናችን የእስፔን ጎዳናዎች ላይ መሽከርከር ጀመርን፡፡ እየዞርን ከተማዋን በምንመለከትበት ወቅት "የስፔንን ድንበር አቋርጠህ ወደ ሀገርህ ግባ!!" የሚል ስሜት ተጠናውቶኝ ነበር፡፡ ይህንን ስሜቴን እንደምንም አደብ ለማስያዝ ሞከርኩና መኪናዬን ወደ ሌላ አቅጣጫ አዙሬ ትኩረቴን ከተማዋን መቃኘት ላይ አደረኩት፡፡

የሆነ ገላጣ ቦታ ላይ ስደርስ መኪናዬን ለማቆም አመቺ ቦታ ስላገኘው ከመኪናው ወርደን ከፊት ለፊታችን ያለውን የተፈጥሮ መልክዓ ምድር መመልከት ጀመርን፡፡ ካለንበት ቦታ አሻግረን በርቀት ስንመለከት ግርማ ሞገስ ያለው አረንጓዴ መልክዓ ምድር ይታያል፡፡ የእርሻውን ዙርያ ከበው የሚታዩት ዛፎች አካባቢውን አረንጓዴ ባህር አስመስለውታል፡፡ በተለያዩ ሰብሎች ተከፋፍሎ የታረሰው የመሬት እይታ እና ከማሳው ቀጥሎ ያለው የግጦሽ መሬት ላይ የተሰማሩት ላሞች ደግሞ ሌላው የቦታው ድምቀቶች ናቸው፡፡ አብዛኞቹ ጥጆች አንገታቸው ላይ ደውል ታስሮላቸዋል፤ እሱን እያወዛወዙ በሚፈጥረው ድምፅ ሲቦርቁ መመልከት መንፈስ ያድሳል፡፡ በአጠቃላይ አሁን

እያየሁት ያለውት መልክዓ ምድር ፈረንሳይ ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ እንዳለ ሳስብ የትውልድ ሀገሬ የገባሁ ያህል ተሰማኝ። ፈረንሳይ ላይ ያሉ ነገሮች ሁሉ እዚህም አሉ። ሌላው ቀርቶ ወደ እርሻው ማንም እንዳይገባ በማሰብ የሚያጥሩት አጥር ፈረንሳዮች ከሚያጥሩበት ስልት ጋር ፈፅሞ አይለያይም። በርቀት የማየው እርሻ አጠገብ ውሃ ለማስተላለፍ ተብለው የተቆፈሩት ቦዮች ውስጥ እንቁራሪቶች እንዳሉ ለማወቅ ሄዶ ማረጋገጥ አይጠበቅብኝም። ምክንያቱም ልጅ እያለሁ ከእህቶቼ ጋር እንቁራሪት ለማደን የምሄድበት ስፍራ አሁን እያየሁት ካለሁት ቦታ ጋር ልዩነት ስለሌለው ነው።

ያንን የተዋበ መልክዓ ምድር አድንቀን ከጠገብን በኋላ መኪናችንን አስነስተን እያሽከረከርን መጎብኘታችንን ቀጠልን። አንዳንዴ በመንገድ ሳልፍ የምመለከታቸው ሰፈሮች ፈረንሳይ ውስጥ የማቃትን አርዲቼን ስለሚመስሉኝ ከእነጭራሹ ስፔን ውስጥ መሆኔን እንኳ እዘነጋ ነበር። ጉብኝታችንን በተወሰነ መልኩ ካገባደድን በኋላ ስፔንን ሳንለቅ ከፈረንሳይ ድንበርም ሳንርቅ አዋሳኝ ቦታ ላይ 'ሮዛስ' የሚባል የተዋበ ሆቴል ስላገኘን መኪናችንን ዳር በማስያዝ ካቆምኳት በኋላ ወደ ሆቴሉ ገብተን ማረፊያ ክፍል ተከራየን።

በሚቀጥለው ቀን ሪታ ወደ ፈረንሳይ ሄዳ ታንቴ ጁን ከቅዱስ ፕሬይ ለማምጣት በባቡር ተሳፈረች። እንደ ህጉ ቢሆን ኖሮ ይዣት መሄድ የነበረብኝ እኔ ነበርኩ፤ ነገር ግን አሁንም ቢሆን የፈረንሳይ መንግስት ስለእኔ የሚያውቀው ከጊዬና ያመለጥኩ እስረኛ መሆኔን ስለሆነ የእኔ ፈረንሳይ መግባት አደገኛ ሊሆን ይችላል። ሪታን ሸኝቼ ወደ ክፍሌ ከተመልስኩ በኋላ አልጋዬ ላይ ጋደም ብዬ በሀሳቤ ደጋግሜ አንድ ነገር ለአእምሮዬ እየነገርኩት ነበር

"ፓፒ ከጥቂት ሰዓታቶች በኋላ በአንድ ወቅት የአባትህ ፍቅረኛ የነበረች፣ ለአንተ ደግሞ ሳታውቅህ እጅግ በሚማርኩ ቃላቶች የተዋቀረውን ፍቅሯን እንደእናት በደብዳቤዎቿ ስትለግስ የነበረችውን ሁለተኛ እናትህን ታገኛታለህ" እያልኩ ነበር ለአእምሮዬ የምነግረው

ሪታ ወደፈረንሳይ በሄደች ማግስት እንደገና እሷን እና ይዛት የምትመጣውን ታንቴ ጁን ለመቀበል ባቡር ጣብያው ከደረስኩ ሰዓታት አልፈዋል። ጊዜው ቢርቅብኝም ከባቡር ወርደው እስካያቸው ድረስ በጉጉት ነበር የምጠብቀው። በመጨረሻም ሪታዬን እና ታንቴ ጁን ያሳፈረችው ባቡር ጣብያው ላይ ደርሳ ቆመች። በመጀመርያ የወረደችው ሪታ ነበረች፤ ከኋላዋ ደግሞ ተከትላት ታንቴ ወረደች። ወደ እኔ እየተጠጉ በመጡ ቁጥር ልቤ ምቷ ሲጨምር ይታወቀኛል። አጠገቤ እንደደረሱም ሪታን ሰላም የምልበት ፋታ እንኳን ሳላገኝ ታንቴ በጠንካራ እጆቿ ጎትታ ጭምድድ አድርጋ እቅፍ ተንሰቅስቃ ማልቀስ

ጀመረች፡፡ እኔም የእንጀራ እናቴ አቅፋኝ ስታለቅስ ሳይ እናቴን ያገኘኒት ያህል ስለተሰማኝ ለቅሶዋን በለቅሶ አጀብኩላት፤ ለደቂቃ ያህል እንደተቃቀፍን ከተላቀስን በኋላ ታንቴ ልባዊ በሆነ ስሜት እያገላበጠች ጉንጮቼን ሳመቻቸው፡፡ በመቀጠልም ወደ ሪታ እየዞርኩ ይሄን አይነት ክብር እና እድል እንዳገኝ የረዳችኝን የልቤን ንግስት አቅፌ ሰላም አልኳት፡፡ ከባቡር ጣብያው ስንወጣ ሪታን ከቀኜ ታንቴን ደግሞ በግራዬ በኩል አድርጌ የሁለቱንም እጅ እንደያዝኩ ነበር፡፡

ሪታ እና ታንቴ ስፔን የደረሱት ጠዋት ሁለት ሰዓት አካበቢ ነበር፡፡ ታንቴ ወደ ስፔን የመጣችበት አላማ እኔን ለማግኘት ስለሆነ የትም ቦታ መሄድ ሳይጠበቅብን በቀጥታ ክፍል ወደ ተከራየንበት ሆቴል ነው ያመራነው፡፡ እዛ እንደደረስንም እኛ የያዘዝነውን ክፍል ትተን ለታንቴ ወደ ያዝነው ክፍል ገባን፡፡ እዛው ቁጭ ብለን ስለኖርኩት ኑሮ፣ አባቴ በእኔ ላይ ስላለው እምነት እና ፍቅር፣ ስለተፃፃፍናቸው ደብዳቤዎች ፣ ስለ እህቶቼ ስናወራ አንድ ቀን እና ሌሊት ያለ እንቅልፍ እዛው አሳለፍን፡፡ ቀጣዩ ቀንም እስከ አመሻሽ ድረስ ስንስቅ ስንጫወት ካሳለፍን በኋላ እኔ ሁለቱን ሴቶች አንድ ላይ ትቼ ለመተኛት ወደክፍሌ ሄድኩ፡፡ እንቅልፍ በአይናችን ሳይዞር እያወራን ስላደርን፣ በዛ ላይ ደግሞ ይህ ሳይታሰብ ያገኘሁት ጥልቅ ደስታ ሰውነቴን ስላዛለው ለመተኛት ብዙ ጊዜ አልፈጀብኝም ነበር፡፡

ጠዋት በተኛሁበት ሚስቴ እና ሁለተኛዋ እናቴ ክፍሌ ድረስ መጥተው ነበር የቀሰቀሱኝ፤ ሰላምና የአእምሮ እረፍት ከመቼውም ጊዜ በላይ አግኝቼ ስለሆነ የተኛሁት የወደቅሁበትን ሳላውቅ ነው ሌሊቱ የነጋው፡፡

"ፓፒ... ፓፒ... ፍቅር... አንተ" የሚለው የሚስቴ ድምፅ ነው መንጋቱን ያበሰረኝ

"ምነው የእኔ ፍቅር በጠዋት ተነሳችሁ? ትንሽ አይረፍድም ነበር" አልኳት ከእንቅልፌ መነሳቴ ስለተጫጫነኝ

"ነግቷል እኮ...በዛ ላይ ታንቴ የምታሳይ ነገር አለ...በል አሁን ተነስ" አለችኝ

ከአልጋዬ እንደወረድኩ ቁርስ ተሰናድቶ እጠበቀን ስለነበር በቀጥታ ወደ እዛው አምርተን ቁርሳችንን እንደነገሩ ከቀማመስን በኋላ አንድ ትልቅ የምስራች ነገሩኝ

"አሁን ወደባቡር ጣብያው መሄድ ይኖርብናል" አለች ሪታ

"ለምን?"

"እህትህን እና ቤተሰቦቿን ለመቀበል ነዋ" የ ታንቴ ምላሽ ነበር

አንዳች የማለውቀው ደስታ ውስጤን ሲወራት ይታወቀኛል፤ ከልካይ ሳያስፈልጋቸው የእንባ ዘለላዎች ከአይኖቼ ክብልል እያሉ ዝም ብለው ይወርዳሉ፤ ታድያ የሰቆቃ እንባ አይደለም ብርታትን አድሶ መኖርን የሚያስመኝ የደስታ እንባ እንጂ!! "ተመስግን አምላኬ" አልኩ ወደ ላይ አንጋጥጬ... ሁሉንም በጊዜው አሳምሮ ለሚሰጥ ፈጣሪ ይህ ስለሚገባው!!

ታንቴ እንደነገረችኝ እህቴ እኔን ለማየት ከመጓጓቷ የተነሳ የቀድሞ ባለቤቱን ወንድም አስከትላ ከሁለት ሰዓት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ባቡር ጣብያው እንደሚደርሱ ነው፡፡ ስለዚህ ጊዜ ማጥፋት አልፈለኩም፤ በቀጥታ መኪናዬን ወዳቆምንባት ቦታ አምርተን ጉዞዋችንን ወደ ባቡር ጣብያው አደረግን፡፡ አነዳዴን ለተመለከተው ለመድረስ አምስት ደቂቃ ቀርቷቸዋል የተባልኩ ነው የሚመስለው፤ ብቻ የእኔ ፍላጎት ባቡር ጣብያው ጋር በቶሎ መድረስ ነው፡፡

ባቡር ጣብያው እንደደረስን መኪናዬን ፊት ለፊት አቁሜ ተያይዘን ወደ ውስጥ ገባን፡፡ እንደ አጋጣሚ ሆኖ እኛ ወደ ውስጥ በገባንበት ቅፅበት እህቴ እና ቤተሰቦቿ ከባቡር ወርደው በእግራቸው እየተራመዱ ነበር፡፡

"አጋጣሚው ደስ ሲል... እነዛውና አየኻቸው" አለችኝ ታንቴ በእጆቿ ወደ እነሱ እየጠቆመች

እህቴ ገና እንዳየችን በሩጫ ወደ እኔ መምጣት ስትጀምር እኔም እየሮጥኩ ወደ እሷ ስሄድ መሀል መንገድ ላይ ተገናኘን፤ በመካከላችን ሶስት ሜትር ክፍተት ሲቀር ሁለታችንም ቀጥ ብለን ቆመን ቃል ሳናወጣ መጠናናት ጀመርን፡፡ እኔም የልጅነት ወዟን ነው የማውቀው እሷም ልክ እንደ እኔው፤ ዛሬ ስንገናኝ ግን ሁለታችንም እንቡጥ አበባነታችን ጠፍቶ፣ የወጣትነት ወዘናችን በጊዜ ርዝማኔ ረግፎ፤ ስለሆነ ከሰላምታ በፊት መተያቱን መርጠነዋል፡፡ ሁለታችንም በቆምንበት ቃል ከአንደበታችን ማውጣት ሳይጠበቅብን አይኖቻችን በእንባ ተሞልተው እርስ በርሳቸው ያወሩ ነበር፡፡ ዝም ብዬ አይኖቿን ስመለከታቸው "አዎ በእርግጥ እርሱ ነው!! የእኔ ትንሹ ወንድም ሄነሪ" እንደሚሉ አያጠራጥርም... የእኔም አይኖች የሚናገሩት የእሷን እሳቤ ነው 'አዎ በእርግጥ እራሷ ነች!! የእኔ እህት ኔኒ'

በመተያየት እኔም የእሷ ወንድም፣ እሷ ደግሞ የእኔ እህት መሆኗን ልቦናችን ካረጋገጠልን በኋላ እንደተነጋገረ ሰው ዘለን ተጠማጠምን፡፡ እንደተቃቀፍን

እየተንከቀስቅን ተላቀስን፤ ግን የደስታ እንባ ነው!! ፊቷን በሁለት እጆቼ ይዤ ይቺ ሀምሳዎቹ የእድሜ ክልል ላይ ያለችውን እህቴን በአድናቆት መመልከት ጀመርኩ፡፡ በእርግጥ ከእድሜዋ መጨመር እና ከሰውነቷ መግዘፍ በስተቀር ብዙም የተለየ ለውጥ አላየሁባትም፡፡ እነዛ ብልጥ እና ንቁ አይኖቿ በፊት እንደማውቃቸው ቀልጭ እንዳሉ ናቸው፡፡ እሷም እንደኔው አይነት ስሜት እየተሰማት እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ፡፡

ለደቂቃዎች እኔ እና እህቴ ተቃቅፈን ናፍቆታችንን ስንወጣ አብሮን ሰው እንዳለ እንኳን እረስተነው ነበር፡፡ ከእህቴ ልጆች አንዱ ሪታን "አክስቴ እንዴት ነው የምታምሪው" ሲላት እኔ እና እህቴ ከገባንበት የራሳችን አለም ወጣን፡፡

"ቆንጆ ነች አይደል? በደንብ ውደዷት እሺ... እኛ ለዛሬዋ ቀን እንድንበቃ ያደረገችው እሷ ነች፡፡ እኔ ደግሞ አጎታችሁ ነኝ" ከማለቴ የእህቴ የመጀመርያው ልጅ ከአፌ ነጥቆ "አዎ እናውቅሀለን እኮ... ሄነሪ አይደል ስምህ? እናታችን ስለአንተ ብዙ ቀን ትናገራለች " አለኝ ከልጁ የሰማሁት ቃል በቀደመው ህይወቴ ምንም እንኳን ራሴን ብቸኛ አድርጌ የማስብ ቢሆንም ሁሌም የሚናፍቁኝ ቤተሰብ እንዳለኝ ማረጋገጫ ሆኖኛል፡፡ አብረዋት እኔን ለማግኘት የመጡትን ሁሉንም ሰዎች ተዋውቄ በሚገባ ሰላምታ ከሰጠኋቸው በኋላ መኪናችንን ውስጥ ገብተን ወደ ሮዛስ ሆቴል ተመለስን፡፡ እህቴም፣ ልጆቿም ሁሉም በጥሩ ሁኔታ ላያ እንደሚገኙ ያስታውቃሉ፡፡ ሮዛስ ደርሰን አንድ ላይ ተሰብስበን የበላነውን ምግብ እስከ ህይወቴ ፍፃሜ ድረስ አልረሳውም፡፡ ምግቡ ሳይሆን ቦታው ላይ የነበረውን ቤተሰባዊ ድባብ ከአየሁት ዘመናት ስላለፉ ነው፡፡

ከ1930 ዓ.ም አሁን እስከምንገኝበት 1956 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በእኔም ሆነ በእነሱ ህይወት ላይ ብዙ ነገሮች ተከስተዋል፡፡ ቢሆን ግን ለማዕድ በተቀመጥንበት ቦታ ላይ እስር ቤት ስላሳለፍኩት አስቸጋሪ ጊዜ ማንሳት አልፈለኩም፡፡ ምክንያቱም አሁን በመሰባሰባችን ውስጣችን ላይ የተፈጠረውን ደስታ ማጠልሸት አስፈላጊነቱ ስላልታየኝ ነው፡፡ ከእህቴ ጋር አብሮ የመጣውን የቀድሞዋ ባለቤቴን ወንድም ግን እኔ በወንጀል ተጠርጥሬ ወደ ወህኒ መውረዴ የፈጠረባቸው ችግር ካለ እንዲነግረኝ ጠይቄው ነበር፡፡ እሱም ትህትና በተላበሰው ንግግሩ ምንም አይነት እንከን እንዳላጋጠማቸው ቢነግረኝም እውነቱ ግን እሱ ካለው በተቃራኒው ሊሆን እንደሚችል ልቦናዬ ያውቀዋል፡፡ ነገር ግን ከዛ በላይ ጥያቄ ማንሳቴ ያለፈ ህይወቴ ውስጥ አዙሮ ሊከተን ስለሚችል ምንም አለመጠየቄን መረጥኩ፡፡ ለነገሩ ምስጋና ለሪታ ይግባት እና የድሮ ማንነቴን ፍቄ እንደ አዲስ እንድወለድ አድርጋኛለች፡፡ ስለዚህ ከአሁን በኋላ መወራት ያለበት ስለስቃይ ሳይሆን ስለድሎት ነው፡፡

የነሀሴን ወር በሮዛስ የባህር ዳርቻ ላይ ሳቅ ከእኛ ሳይለየን በሚማርክ ሁኔታ አሳለፍነው። ጊዜው እንዴት እንደነጎደ እንኳን አላወቅነውም ነበር። አንድ ወርን በእስር ማሳለፍ የአመት ያህል ከባድ ነው፣ ከሚወዱት ሰው ጋር ሲሆን ግን ጊዜው በጣም ያጥራል። ይህ አንድ ወር እለት ከእለት በደስታ የሰከርኩበት ጊዜ ነው ማለት ይቻላል። እህቴን እና የድሮ አማቼን ብቻ ሳይሆን ያገኘሁት ሳላውቃቸው የተፈጠሩትን የእህቴን ልጆች ጭምር ነው ያገኘሁት።የእህቴ ልጆች!! ከልጆቹ ጋር ለመተዋወቅ እና ለመግባባት የፈጀብን አንድ ቀን ብቻ ነው፤ አሁን እነሱም የሚያቀርቡኝ ልክ እንደ አባት ነው፤ እኔም ፍቅር የምሰጣቸው እንደወለድኳቸው ልጆች ነው።

ሪታ እኔ ተደስቼ በማየቷ ከልብ የመነጨ ሀሴት እንደተሰማት ሁኔታዋ ይናገራል። እኔ አይደለም ፈረንሳይ ሄጄ ቤተሰቦቼን ላገኝ ይቅር እና የፈረንሳይን ምድር መርገጥ እንኳን በማልችልበት ወቅት ሪታ ለእኔ መሰዋትነትን ከፍላ ቤተሰቦቼን ልታገናኘኝ ችላለች። ይህ ማለት እሷ ለእኔ ያበረከተችልኝ ትልቅ ስጦታ ነው። ታድያ ይህንን ሁሉ መስዋትነት የከፈለችልኝን ሴት እድሜ ልኬን ስታዘዝላት ብኖር ውለታዋን መክፈል እንደማልችል ልቦናዬ ያውቀዋል። ምክንያቱም እሷ ከእኔ አእምሮ በላይ ነች!!

ከእህቴ እና ቤተሰቦቿ ጋር ልንለያይ አንድ ቀን ሲቀረን ምሽት ላይ በባህሩ ዳርቻ አሸዋው ላይ ሪታን እግሮቼ ላይ አስተኝቼ እያወራን ነበር።

“የኔ ፍቅር ጊዜው እንዴት ነው የሚሮጠው? ነገ እኮ ሁሉም ተመልሰው ይሄዳሉ፤ ቢሆንም ግን ያሳለፍነው ጊዜ በጣም ግሩም ነው። አሁን በመገናኘታችን የተሰማኝ ሀሴት ጥልቅ ቢሆንም ለመገናኘት የፈጀብን ጊዜ ረጅም ነውና ዳግም መቼ እንደማገኛቸው ሳስብ ይጨንቀኛል ” አልኳት ፀጉሯን እየደባበስኩ

“ስለወደፊቱማ አትጨነቅ... አሁን ስታገኛቸው እኮ ፈጣሪ እንድታገኛቸው ስለፈቀደልህ ነው. . .ስለዚህ በእርግጠኝነት አንድ ቀን ደግሞ በድጋሚ ታገኛቸዋለህ... ያን ጊዜ ግን እንደአሁኑ ሩቅ እንደማይሆን እርግጠኛ ነኝ” አለችኝ አይን አይኔን እያየች

በሚቀጥለው ቀን ታንቴን እና እህቴን ከእነ ቤተሰቧ ባቡር ጣብያው ድረስ በመሄድ ሸኘናቸው። ባቡር ውስጥ ገብተው ከአይናችን እስኪሰወሩ ድረስ አይናችንም አብሮ ተጉዞ ሸኛቸው። በእርግጥ ስንለያይ ምንም አይነት የመረበሽ ስሜት ሁላችንም ላይ አይነበብም ነበር። ምክንያቱም በሚቀጥሉት ሁለት

አመታት ውስጥ በእርግጠኝነት ሰፋ ላለ ጊዜ እንደማገኛቸው ቃሌን ስለሰጠኋቸው ነው ፡፡

እነሱን ከሸኘን ከሳምንት በኋላ ሁለተኛዋ እህቴ እኔን ለማግኘት የባርሴሎና አየር ማረፊያ ደረሰች፡፡ እቺኛዋ ስትመጣ ማንንም ሳታስከትል ለብቻዋ ነበር፡፡ ልክ ከአውሮፕላኑ ወርዳ እንዳየችኝ ያለማንም ጥቆማ ነበር ያወቀችኝ፤ እኔም እንዳየኋት ነው ሁሉ ነገሯ በአእምሮዬ ላይ የመጣው፡፡ ሁለተኛዋ እህቴ ከእኛ ጋር የምትቆየው ለሶስት ቀናት ብቻ ስለሆነ ሽርፍራፊ ሰከንዶች እንኳን እንድታለፍን አላደረግንም ነበር፤ በቆየችባት ሶስት ቀናቶች ከእኔ በላይ ከሪታ ጋር እጅ እና ጓንት ሆነው ነው ያሳለፉት፡፡ ምንም እንኳን ሶስት ሌሊት እና ሶስት ቀን ለረጅም አመት ለተለያዩ ወንድም እና እህት ሲበዛ አጭር ጊዜ ቢሆንም ስለ እሷ ታሪክ ለመስማት እኔም ስላሳለፍኩት ህይወት ለመንገር ግን በቂ ጊዜ ነበር፡፡ እነዚያን ሰባ ሁለት ሰዓታት በስስት ካሳለፍን በኋላ በሰፊው እንደምንገናኝ ቃል ተገባብተን እሷንም ሸኘናት፡፡

እህቴን በሸኘናት በሁለት ቀናት ልዩነት ውስጥ ደግሞ የሪታ እናት ከታንገርስ መጣች፡፡ ስፔን ከተለያዩ ዘመናት ያስቆጠሩ ቤተሰቦችን በማገናኘት ተጠምዳለች፡፡ ደስ የሚል ወቅት ነው ጥላቻን አንዕቶ ፍቅርን የሚያላብስ ጊዜ፤ የሪታ እናት እንዳየችኝ በሚያማምሩ እጆቿ ጉንጮቼን ይዛ አገላብጣ ከሳመችኝ በኋላ "ልጄ... ሪታ አንተን የመሰለ ሰው ስላገኘች በጣም ደስተኛ ነኝ፤ አንተም እቺን ውብ እንስት በማቀፍህ እድለኛ ነህ" ነበር ያለችኝ እየሳቀች... እውነትም ነው! የእሷ እኔን ማግኘት እድለኝነቱ ባይገባኝም ለእኔ ግን የሪታ ከጎኔ መሆን ከእድለኝነትም በላይ ነው፡፡ የሪታ እናት ነጭ ፀጉሯ ላይ የፊቷ ግርማ ሞገስ ተጨምሮበት ውበትን ተላብሳለች፡፡ እሷም የመጣችው ልጇን እና የማታውቀውን አማቿን ለማየት ከመጓጓቷ የተነሳ ነው፡፡ ስለዚህ እሷም ከስፔን ተመላሽ ነች፡፡ ለዘመናት ከጎኔ ሰው የለም ብዬ የማስበው ሰው አሁን ላይ በሚፈልጉኝ ሰዎች ተንበሽብሼ እና ተከብቤ ለመኖሬ ትርጉም ከሰጠሁበት መንገድ በተለየ መልኩ ህይወቴን እንድመራ አድርጎኛል፡፡ የሰው ልጅ ሆኖ ማንም ባሰበው መንገድ አይኖርም፡፡ ለዘመናት ሳልመው የኖርኩት ብቀላ ሳላስበው ባገኘሁት ክብር እና ፍቅር እንደ ጉም ተኖ ከእኔ ጠፍቷል፡፡ ከሪታ እናት ጋርም ያሳለፍነው ጊዜ በህይወቴ ሳላገኘው ባልፍ ቆጭቶኝ የሚያልፍ ጊዜ ይመስለኛል፡፡ ስፔን በነበርኩበት ወቅት ቤተሰቦቼን ከማግኘት እና ሀሴትን ከመጎናፀፍ ባሻገር አንድ ትልቅ ነገር ሰጥቶኛል፡፡ እሱም በህይወቴ

ስኖር ሶስት እናቶች አግኝቻለሁ፤ አንዷ የእኔነቴ መሰረት ወደ እዚች ምድር የመምጣቴ ምክንያት የሆነችው ወላጅ እናቴ ስትሆን ሌላኛዋ አባቴን ከብቸኝነት እስራት ነፃ ያወጣቻውና እኔን ለማየት የፈረንሳይን ድንበር አቋርጣ ስፔን ድረስ የተጓዘቸው የወላጅ እናቴ ምትክ ታንቴ ስትሆን ሶስተኛዋ ደግሞ የሚስቴ እናት ነች። ተፈጥሬ እስከዛሬ በኖርኩበት እድሜዬ ከሦስቱም ያገኘሁት ፍፁም ተመሳሳይ የሆነ የእናትነት ፍቅር ነው።

ስፔን ውስጥ ከወር በላይ ስለቆየን በዛ ላይ እዚህ ያመጣንን ጉዳይ ስለጨረስን የመመለሻ ጊዜያችን እንደደረሰ ተረድተናል። በመርከብ የምንመለስ ከሆነ ተጨማሪ አስራ ስድስት ቀናት በመንገድ ላይ ማባከናችን ስለማይቀር ጊዜ ላለማጥፋት በ አውሮፕላን መመለሱን መረጥን። መኪናችንን ደግሞ እንዳመጣጧ በመርከብ ጭነናት ካራካስ በደረሰች ቀን ለመውሰድ ተስማማን።

ስፔን በነበርኩበት ሰዓት ከተመለከትኳቸው ቦታዎች መሀል በግራንዳ መናፈሻ ውስጥ ያነበብኩትን ጥቅስ ለዘለአለም ከአዕምሮዬ የማወጣው አይመስለኝም!

“Dale lironosana, mujer, que nohay enla vida comola Pena de ser ciego en granda”

“በግራንዳ ውስጥ አይነስውር እንደመሆን የሚያስፈራ ነገር የለም፤ ገንዘብ ስጡት፤ ሴትም ስጡት የዛኔ አስፈሪው ገፅታ ከእሱ ይወገድለታል“ ይል ነበር

በእርግጥ ተሳስቷል! ግራንዳ ውስጥ አይነስውር ከመሆን በላይ የሚያስጨንቅ ነገር አለ። አንድ በሙሉ ጤንነት ላይ የሚገኝ የሃያ አራት አመት ወጣት በሰላም በሚኖርበት ወቅት ሌላ ሰው በሰራው ወንጀል እድሜ ልክ እንዲፈረድበት ሲደረግ፤ ከዚያን ደግሞ በዚያ አተላ ህይወት ውስጥ እንዲኖር ሲፈረድበት፤ የነበረው ተስፋ ተንኮታኩቶ ሲወድቅ፤ ታድያ እውነት ለመናገር ያ አይነ ስውሩ ምን ሆነ... ስንቶች አሉ ኢ-ፍትሀዊ በሆነ ፍርድ የነፃነትን አየር ተነፍገው ወደ አላሰቡት አዘቅት ውስጥ ተወርውረው እራሳቸውን እስከማጥፋት የሚደርሱ። ታድያ ከእዚህ ሁሉ ስቃይ አይነ ስውር መሆን አይቀልም? እሱኮ የተሳነው ማየት ነው፤ ያ በእርግጥ ህመም ነው፤ ነገር ግን ሰውን የማይወቅስበት ተፈጥሮ የሰጠችው ህመም ነው!

# ምዕራፍ አስራ አራት

## ነውጡ

ከማድሪድ የተሳፈርንበት አውሮፕላን ካራካስ ማይኪታ አየር ማረፍያ ሲደርስ ልጃችን እኛን ለመቀበል ከጓደኞቿ ጋር በመሆን እየጠበቀችን ነበር፡፡ ለወር ያህል በጉጉት ስትጠብቀን ስለነበር እንዳየችን ሮጣ ነው የተጠመጠመችብን፡፡ ከአየር ማረፍያው ወጥተን ቤታችን ለመድረስ ሃያ ደቂቃ ብቻ ነበር የፈጀብን፡፡ ወደ ውስጥ ስንገባ ውሻችን እየጮኸ እና ጭራውን እየቆላ እንኳን ደህና መጣችሁ በሚል መንፈስ ነው አቀባበል ያደረገልን፡፡ በዚህ ሰዓት እንደ ቤተሰባችን አንድ አካል የምንቆጥራት ህንዳዊቷ ሰራተኛችንም በመደጋገም "የሄነሪ ቤተሰቦች እንዴት ናቸው? ሄነሪ አንተስ ስለ ሪታ እናት ምን ታስባለህ? እኔ እኮ እንደውም ብዙ የሚወዷችሁን ሰዎች ስላገኛችሁ ትመለሳላችሁ የሚል እቅድ አልነበረኝም ነበር፡፡ ስለመጣችሁ ፈጣሪዬን አመሰግነዋለሁ" በማለት እዛ ስላጋጠመን ህይወት እና ስላሳለፍነው ጊዜ ለማወቅ ያለማቋረጥ በየዋህ አንደበቷ ትጠይቃለች፡፡

የኑሮ ውጣ ውረዱ ከስፔን መልስ እንደ አዲስ ተጀመረ፡፡ ወደ ስፔን ባቀናንበት ወቅት ተከራይተነው የነበረውን ሆቴል ለቀን ስለነበር የሄድነው አሁን ላይ እንደ አዲስ ምሽቱን ሙሉ የሚሰራ ቡና ቤት መግዛት ቻልን፡፡ ካራካስ ውስጥ የሚሰሩ መሸታ ቤቶች ውስጥ የሚገቡት ወንዶች ብቻ ናቸው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ቡና ቤቶቹ የራሳቸውን ሴቶች ስለሚያዘጋጁ ነው፡፡ ደንበኛ ለመሰብሰብ ሲባል የተዘጋጁት ሴቶች ወደ ቡና ቤቱ የሚገባውን ወንድ እንዲያዋሩት እና እነሱን እየጎመጀ የቤቱ ቀንደኛ ደንበኛ እንዲሆን ከማድረግ በተጨማሪ የገቢ ምንጭ እንዲሆኑ ታሳቢ በማድረግ ነው ካራካስ ውስጥ ያሉ መሸታ ቤቶች ሴት የማያጣቸው፡፡ ስራው ሰላም የማይሰጥ ቢሆንም ልክ ምግብ ቤት ስንሰራ እንደሚያጋጥመን ሁሉ ሁሌም ቢሆን አዲስ ነገር መከሰቱ አይቀርም፡፡ ወደ እኛ ቡና ቤት የማይመጣ ሰው የለም፡፡ የህግ ሰዎች፣ የባንክ

ባለቤቶች፣ ጠበቃዎች፣ ፖሊሶች ወ.ዘ.ተ የእኛ ቋሚ ደንበኞች ናቸው። በአልኮል ኢጋዥነት ከነበሩበት ድብርት ቀስ በቀስ ይላቀቁ እና ሁሉም የራሱን ሀሳብ እየሰነዘረ መጫወት ይጀምራል። እርስ በርስ የሚያደርጉት ጨዋታ ስልቹት ሲላቸው ደግሞ ቡና ቤታችን ውስጥ ተመርጠው ከገቡት ቆነጃጅት ጋር ማውጋት ይጀምራሉ። የእኛ ቡና ቤት ካራካስ ውስጥ ካሉት ጋር የሚለየው ማንኛውም ወንድ በቡና ቤታችን ውስጥ ካሉ ሴቶች ጋር ከማውራት በዘለለ ምንም ነገር እዲያደርግ አለመፈቀዱ ነው። በእዚህ ጉዳይ ላይ ሪታ ለሴቶቹ ጥብቅ ማሳሰብያ ስለሰጠች መመርያውን ለመተላለፍ የሚደፍር ሴት አልነበረም። ወንዶቹም ቢሆኑ ከሴቶቹ ጋር ማውራቱን ብቻ የመረጡት ይመስላሉ፤ አብዛኞቹ ወንዶች አንድ ሴት ከአጠገባቸው አስቀምጠው በመጋበዝ በመጠጥ ሀይል የውስጣቸውን መናዘዝ የሚወዱ ናቸው።

የቡና ቤታችን ቋሚ ደንበኞች ከሆኑት መካከል ሁሌ ምሽት ሶስት ሰዓት ላይ የሚመጣ አንድ ደንበኛ ነበረን። በእርግጥ እሱንም እንደማንኛውም ተጠቃሚ እዚሁ ቡና ቤት ውስጥ ነው የማውቀው፤ ቢሆንም ከማውቃቸው ደንበኞቻችን የተረጋጋ ስብዕና ያለው ሰው ነው። ያም ነገሩ ስላቀራረበን ሁሌም ወደ ቤቱ ለመሄድ ሲነሳ መኪናው ድረስ እሸኘው ነበር። ታድያ አንድ ቀን እንደተለመደው መኪናው ድረስ ሸኘቼው ልሰናበተው ስል እጁን ትከሻዬ ላይ ጭኖ በሌላኛው እጁ ደግሞ የካራካስን ተራሮች እያሳየኝ "ተመልከት ኢንሪክ... ምሽቱ እየተገባደደ ነው። ፀሀይ ቦታዋን ለማስጠበቅ በጉጉት ላይ ነች። ጨለማው ተገፎ ብርሀን ሲወጣ የትም የመሄድ ተስፋ የለህም፤ በቀጥታ ወደ ስራ መሰማራታችን ግዴታችን ነው። ሁሉም በየፊናው ህይወቱን ለመቀየር ይንከራተታል። ስለዚህ ቀናችን የሚያልፈው በድካም ነው። ታድያ እንደናንተ አይነት መሸታ ቤቶች ባይኖሩ ኖሮ ምን ይውጠን ነበር" አለኝ እኔም አባባሉ ስለገባኝ በሀሳቡ መስማማቴን ገለፅኩለት።

በጥቂት ጊዜያቶች ውስጥ ሌሎች ተጨማሪ ሁለት መሸታ ቤቶች ገዝተን ቀኑን በስራ ለሚያሳልፉ ሰዎች ምሽቱን እየተዝናኑ እራሳቸውን እንዲያፍታቱ ጥሩ እድል ከፈትንላቸው። አንደኛው 'ማድሪጋል' ሲባል ሌላኛው ደግሞ 'ኖርማንዲን' ይሰኝ ነበር። ከእነሱ በተጨማሪ 'ጎንዛሎ ዱራንድ' ከሚባል የአሁኑን መንግስት ከማይደግፍ ሶሻሊስት ጋር በመሆን የቡና ቤት ባለቤቶች፣ የምሽት ክለቦችን እና የምግብ ቤት ባለቤቶችን ፍላጎትን ለማሟላት የሚሰራ ተቋም አቋቋምን፤ የተቋሙ ፕሬዘዳንትም እኔ እንድሆን ተደረገ። ተቋማችን

አባላቶቹን በምንም ነገር ከመደገፍ እና ከመጠበቅ በዘለለ የአንዳንድ ጥቅም ፈላጊ ፖሊሶችን ጥቃት ከመከላከል አንፃር የቻለውን ሁሉ ያደርግ ነበር፡፡

1958 ዓ.ም ለአንባገነኑ ፔሬዝ ጥሩ አመት አልነበረም፡፡ በተመቻቸ ኑሮ ላይ እየኖሩ ያሉ ዜጎች እንኳን ጀርባቸውን ከሰጡት ውለው አድረዋል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ብቸኞቹ እሱን የሚደግፉት ሰዎች የጦር ሰራዊቱ እና ዘወትር ሰውን ከማሰር የማይቦዝኑት ፖሊሶች ናቸው፡፡ በፔሬዝ ላይ የተነሳውን ነውጥ ተንተርሰው ኒዎርክ ውስጥ የራሳቸውን ኑሮ መስርተው ይኖሩ የነበሩ የቀድሞ የቬንዙዌላ የፖለቲካ ሰዎች ሸኩቻውን ተገን አድርገው ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ስልጣኑን ለመያዝ ቀን ከለሊት እየተጉ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ በሀገሪቷ ፖለቲካ ምክንያት ተሰደው የነበሩት የፖለቲካ ሰዎች ራፋኤል ካልድራ፣ ጆቪቶ ቪላልባ፣ እና ረሙሉ ቤታንኮርት በመባል ይታወቃሉ፡፡

በጥር አንድ የአየር ሀይል ዋና ጀነራል የነበረ 'ካስትሮ ሊዎን' የተባለ ሰው ካራካስ ውስጥ በሚገኘው የፕሬዘዳንት ፔሬዝ ማረፍያ የሆነው ቤተ መንግስት ላይ ጥቂት ቦንቦችን ለማፈንዳት ሞክሮ ነበር፤ ነገር ግን እቅዱ ስለከሸፈበት ወደ ኮሎምቢያ ለመሰደድ ተገዷል፡፡ ብዙም ሳይቆይ በዛው አመት በጥር ሀያ ሶስት አምባገነኑ ፔሬዝ ጂሚኔዝን ከእነቤተሰቡ እና አንዳንድ ጓደኞቹን የያዘች አውሮፕላን በካራካስ ሰማይ ላይ ስታልፍ ታየች፡፡ ጀነራል ፕሬዝ ጨዋታውን መሸነፉን ያመነ ይመስላል፤ ከአስር ዓመታት የአምባገነንነት አመራር በኋላ የጦር ሰራዊቱ ሳይታሰብ ሊከዳው ችሏል፡፡ አውሮፕላኗ በቀጥታ የምትሄደው እዛው ደቡብ አሜሪካ ውስጥ ወደምትገኝ 'ሳንቶ ዶሚኖ' ወደተባለች ሀገር ሲሆን የሀገሪቱ መሪ ጀነራል 'ትሩጂሎ' ልክ እንደ ፔሬዝ ሁሉ አምባገነን ስለሆነ ጓደኝነታቸውን እንደ መሸሸጊያ ተጠቅሞ ነው ወደ እዛ መጓዝን የመረጠው፡፡

በእዚህ የነውጥ ሰዓት ለሶስት ሳምንታት ምንም አይነት ፖሊስ በጎዳናው ላይ አይታይም ነበር፡፡ በእርግጥ ከስንት አንድ ቀን ረብሻ ይነሳ ነበር፡፡ ይህም የሚሆነው ጥቂት የፔሬዝ ደጋፊዎችን ፀጥ ለማስባል ሲባል ብቻ ነበር፡፡ በአስር አመታት ውስጥ በፔሬዝ ስልጣን ስር ላይ የነበሩ ሶዎች በእዚህ የነውጥ ወቅት ሊገደሉ ችለዋል፡፡ ታድያ ይህ የነውጥ ወቅትም እኛንም ለአስራ ሁለት ዓመት ያጠራቀምነውን ጥሪታችንን አሳጥቶን ነበር፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው... የፔሬዝን አመራር አጥብቀው የሚጠሉ የሆኑ ብዛት ያላቸው ሰዎች ከዚህ በኃላ ፔሬዝ

ዳግም ወደ እዚች ሀገር እንደማይመጣ እርግጠኞች ስለሆኑ ፔሬዝ ስልጣን ላይ በነበረ ሰዓት ያስገነባቸውን ማንኛውንም ህንፃም ሆነ ቤት ማፈራረስ ይጀምራሉ፤ ይሄኔ እዛው ከማውቃቸው ጓደኞቼ አንዱ ደውሎ የፔሬዝ አመራር አጥብቀው የሚጠሉ ሰዎች የንግድ ስፍራዎችን በማውደም ላይ እንዳሉ ነገረኝ፤ ጥቃት የሚያደርሱት ደግሞ ምግብ ቤቶች እና መዝናኛ ክበቦች ላይ በመግባት ያገኙትን እቃዎችን በመሰባበር ነበር፡፡ እንግዲህ እኛ ደግሞ ያለነው የከተማዋ እምብርት ቦታ ላይ ባለው 'ካቲ ባር' ብለን በሰየምነው ሆቴል ውስጥ ነው፡፡ ከምድር በላይ ያለውን የህንፃውን ክፍል ለመኖርያ እና ወሳኝ የሆኑ ንብረቶችን ማስቀመጫነት ነው የምንጠቀመው፡፡ ያለንበት ቦታ ደግሞ ለምንም ነገር ቅርብ ስለሆነ በማንኛውም ሰዓት የሚከሰት አደጋ ቀድሞ ያገኘናል፡፡ ስለዚህ ቤተሰቤንም የአካባቢው ማህበረሰብንም መጠበቅ ስላለብኝ ሀያ በተቀጣጣይ ነዳጅ የተሞሉ ጠርሙሶችን አዘጋጀው፤ ከዛ የሆቴላችን ጣርያ ላይ በመውጣት ደምሳሾቻችንን መጠባበቅ ጀመርኩ፡፡ በእርግጥ ብቻዬን አልነበርኩም፤ ሪታ በነዳጅ የተሞሉ ጠርሙሶችን የማቀጣጥልበትን መለኮሻ ይዛ በንቃት ከጎኔ ሆና እተጠባበቀች ነበር፡፡

ጣርያችን ላይ ተቀምጠን ጥቃት አድራሾቹን በመጠበቅ ላይ እንዳለን ጨኸት የተሞላበት የሰዎች ጋጋታ ወደ እኛ ሆቴል ሲጎርፍ ተመለከትኩ፡፡ ከመቶ ያላነሱ የፔሬዝ ስርዓት የማይደግፉ ሰዎች በእጆቻቸው የተለያዩ ለማፈራረስ የሚጠቅሙ ቁሶች ይዘው ወደእኛ እየመጡ ነበር፡፡ ልክ የሆቴሉ በር ላይ ሲደርሱ ከመካከላቸው አንዱ ጮክ ብሎ "የእዚህ ሆቴል ባለቤት ቀንደኛ የፔሬዝ ደጋፊ ናቸው" ብሎ የያዘውን ዶማ እያወራጨ ሲሮጥ ከኋላው ያለውም ህዝብ "ሆ..ሆ..ሆ " እያለ ተከተለው፡፡ እኔም አንዱን የጠርሙስ ፈንጂ ለማቀጣጠል ስዘጋጅ ከየት መጡ ሳንል አራት ሰዎች ሮጠው ለማውደም ወደተሰማሩት ሰዎች በመሄድ ለማረጋጋት ሲሞክሩ ተመለከትኩ፡፡

"ይኸውላችሁ እኛ ሰራተኞች ነን፡፡ ማለቴ የማህበረሰቡ አንድ አካል ስለሆንን ለውጡን ከሚደግፉ ሰዎች መካከል ነን ቢሆንም ግን እኛም ሆንን የእዚህ ሆቴል ባለቤት ከፔሬዝ ጋር የሚያገናኘን ነገር የለም፡፡ እንደውም የፔሬዝን አምባገነናዊ አመራር አንደግፌውም፡፡ ሆቴሉን ባለቤት በደንብ እናውቀዋለን፡፡ ለህዝቡ ታማኝ እና አገልጋይ መሆኑን በተለያ ሁነቶች አስመስክሯል፡፡ ስለዚህ ይህን ጥቃት መፈፀም ለእናንተ ፋይዳ አይኖረውም፡፡ ከጠቀመችሁ ግን ይኸው የፈለጋችሁትን ማድረግ ትችላላችሁ" አለ ከአራቱ አንዱ

ጥቂት ቢያጉተመትሙም አንድም ሰው ግን እቃ ለመስበር እጁን ያነሳ ሰው አልነበረም፡፡ እኔ እና ሪታም ለሃያ ደቂቃ ያህል ጣሪያው ላይ እንደተቀመጥን በአራቱ ሰዎች እና በአውዳሚዎቹ መካከል የሚደረገውን ምልልስ በአትኩሮ መከታተላችንን ቀጠልናል፡፡ በመጨረሻም የአራቱ ሰዎች ሀሳብ ሚዛን ደፍቶ ምንም ጥቃት እንዳይፈፅሙ አሳምነዋቸው ሆቴላችን ምንም ሳይሆን ለቀው እንዲወጡ አስደረጓቸው፡፡ የፈጣሪ ያለህ! ይቺ ቀን በጣም አስፈሪ ነበረች፤ በርግጥ ጥቃቱን ቢፈፅሙት ብዙ ነገር ማወደም እንደሚችሉ ግልፅ ቢሆንም ከእነሱም መካከል ግን  በህይወት የሚወጣ ሰው አይኖርም ነበር፡፡ እድሜ ለእነዛ አራት ሰዎች፤ ምንም አይነት አደጋ እንዳይደርስ የበኩላቸውን ድርሻ ተወጥተዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ከእኛ ሆቴል ጀርባ በሚገኘው የካራካስ ውሃ እና ፍሳሽ ድርጅት ውስጥ የሚሰሩ ናቸው፡፡ እዛ ድርጅት ውስጥ የሚሰሩ ሰዎች ምግብ የሚመገቡትም ሆነ የእረፍት ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በእኛ ሆቴል ውስጥ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜም መክፈል ለማይችሉ የድርጅቱ ሰራተኞች የነፃ መስተንግዶ እናቀርብላቸው ነበር፡፡ ታድያ በዛ በፔሬዝ የአማንገነንነት አመራር ዘመን  እንኳን አብዛኞቹ የእዛ ድርጅት ሰራተኞች ስለፖለቲካ ለማውራት ብዙም አይደፍሩም ነበር፤ ምክንያቱም አልፎ አልፎ በመጠጥ ሀይል የሚነሱ ትንንሽ ሀሳቦች እንኳን እንዴት እንደሆነ ሳይታወቅ ፖሊሶች ዘንድ ይደርሱ ስለነበር ነው፡፡ እነሱም ምንም ሳይሉ በቀጥታ ያወራውን  ሰው በመውሰድ ወህኒ ይወረውሩታል፡፡ አብዛኛውን እኛ ጋር የሚስተናገዱ ሰዎች ይህንን ጉዳይ ስለሚያውቁት አፋቸውን ከወለምታ ይጠብቁታል፡፡ ታድያ እኛ አካባቢ እንደዚህ አይነት ነገር ሲከሰት የምንቀርባቸውን የህግ  ሰዎች በማነጋገር ለማስፈታት ጥረት እናደርጋለን፣ በእርግጥ አንዳንዶቹ እንዲህ አይነት ትብብር ለማድረግ ፍቃደኛ የማይሆኑ አሉ፤ ቢሆንም ግን እኛ የተቻለንን ሁሉ ከማድረግ ወደ ኋላ ብለን አናውቅም፡፡

የፔሬዝ ደጋፊዎች ጥቃት ለመሰንዘር ወደ እኛ ሆቴል በመጡበት እለት በሚገርም ሁኔታ የተቀሩት ሁለት ቡና ቤቶቻችንም ምንም ጥቃት ሳይደርስባቸው መትረፍ ችለዋል፡፡ አንደኛው ቡና ቤት አንዲት ብርጭቆ እንኳን አልተሰበረም ነበር፡፡ ኖርማንዲን ቡና ቤትም ቢሆን ከጥቂት መስታወት መሰበር በስተቀር የተዘረፈ ንብረት እንደሌለ ለማወቅ ችለናል፡፡ በፈጣሪ እገዛ የከፋ ችግር ሳያጋጥመን የታቀደውን መሰናክል ለማለፍ ችለናል፡፡

በአምባገነኑ ፔሬዝ የአገዛዝ ዘመን ያለስምምነት ነገሮችን መከወን ቬንዙዌላ ውስጥ ተለምዷል፤ ሁሉም ነገር በግዴታ የታጠረ ነበር። ታድያ ከእሱ ውድቀት በኋላ ለጊዜያዊ መሪነት ህዝቡ በአንድነት እና በደስታ የተቀበለውን መሪ ስልጣን ላይ አስቀምጧል። ያም ሰው የቀድሞ የቬንዝዌላ የባህር አዛዥ የነበረው 'አድሚራል ላራዛባልን' ነበር። አድሚራሉ ስልጣን ላይ እንደወጣ ነፃ እና ዲሞክራሳዊ ምርጫ እንደሚያካሄድ ቃል ገብቶ ነበር፤ በአጭር ጊዜ ውስጥም ቃሉን ተግባራዊ አድርጎ ህዝቡን ደስ አሰኝቶታል። እንደ እድል ሆኖ ምርጫውን የቀድሞ የቤታን ኮርት ፓርቲ ስላሸነፈ አድሚራል ላራዛባልም በሰላማዊ መንገድ ስልጣኑን ለማስረከብ ተገዷል። እኛም በሰዓቱ ሀገሪቷ ያለችበትን ሰላም ምክንያት በማድረግ ቶሎ ብለን መሀል ካራካስ ውስጥ ወደ አራት መቶ መቀመጫ ያለው 'ግራንድ ካፌ' የተሰኘ ትልቅ ምግብ ቤት ገዛን።

ሀገሪቷን እያመሳት የነበረው የፖለቲካ ውጥንቅጥ ግን ለቤታን ኮርት ፓርቲ ስልጣኑን አልጋ በአልጋ አላደረገለትም። በሳንቶ ዶሚኖ መሪ ትሩ ጂሎ በተቀነባበረው ሴራ ፕሬዘዳንቱ እና አብረውት የነበሩት የቅርብ ሰዎቹ የበዓል ቀን ሽርሽር እያደረጉ እያለ መኪና ውስጥ በተጠመደ ፈንጂ በመፈንዳቱ ጉዳት ሊደርስባቸው ችሏል። በፍንዳታውም መኪና ውስጥ ከፕሬዘዳንቱ ጋር የነበረው የሀገሪቱ የጦር አዛዥ ወድያው ህይወቱ ሲጠፋ ሾፌሩ ደግሞ ከባድ የአካል ጉዳት ሊደርስበት ችሏል። ከእነሱ በተጨማሪ መኪና ውስጥ የነበሩት ጀነራል ሎፔዝ እና ባለቤታቸው በከፍተኛ ሁኔታ በእሳት የተለበለቡ ሲሆን ፕሬዘዳንቱም በእሳቱ ነበልባል ቀኝ እጁ ሊቆስል ችሏል።

በእዚህ በተጨማለቀ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ ፖሊሶች የእለት ከእለት ግዴታቸውን በትጋት መወጣት የሌት ተቀን ተግባራቸው ሆኗል። የካራካስ ጎዳናዎች ፖሊስ ተርበው አያውቁም። ታድያ በእዚህ መሀል ግዴታቸውን በአግባቡ የሚወጡ ፖሊሶች እንዳሉ ሁሉ ስልጣናቸውን ለሰይጣናዊ ተግባር ለማዋል የሚጠቀሙ ፖሊሶችም ጥቂት አልነበሩም። እነዚህ ጥቅማጥቅም ፈላጊ ፖሊሶች ወደ እኔ እየተመላለሱ በጥያቄ ማደንቆር ከጀመሩ ውለው አድረዋል። ይሄን ነገራቸውን ደግሞ እኔ በፍፁም አልወደድኩትም። ይባስ ብለው ስላለፈው ታሪኬ አጥርተው እንደሚያውቁና ባሳለፍኩት የህይወት ታሪኬ ውስጥ ደግሞ ብዙ ወንጀል ነክ ነገሮችን መሳተፌን እየገለፁ ሊያስፈራሩኝ ሞከሩ። ከእኔ ጋር ሊገናኝ የማይችሉ ጥቄዎችን እያነሱ ሰላሜን መረበሽ ምርጫቸው አድርገውታል። ለምሳሌ "ከሁለት አመት በፊት አንድ

የተገደለ ፈረንሳዊ ነበር፡፡ ማን እንደገደለው እስካሁን የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ እንዴት መረጃ ልናጣለት እንደቻልን ግልፅ አይደልም፤ አንተ ስታስበው ግን ምን ይመስለሀል?" ብሎ ይጠይቁኛል ይህ ማለት እኮ አንተ ወንጀለኛ ስለነበርክ ማን ይህን ድርጊት ሊፈፅም እንደሚችል ከእኛ በተሸለ መልኩ አንተ ጋር ፍንጭ ሊኖር ይችላል ማለታቸው ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ እኔ ከእነሱ ጋር ሰጣ ገባ ውስጥ መግባት አልፈልግም፤ ምን እንዳሰቡ ባይገባኝም የፖሊሶቹ መደጋገም እና የማይመለከታቸውን ጥያቄ እያነሱ መዘባረቃቸው ለጤና እንዳልሆነ ተረድቼዋለሁ፡፡ ምንአልባት ነገሩ በእዚሁ ከቀጠለም ምን ደረጃ ላይ ሊደርስ እንደሚችል ስለማውቅ በዛ ላይ በስንት መከራ ያገኘሁትን ነፃነቴን ማጣት ስለማልፈልግ ካራካስ ያሉኝን ሆቴሎች ሁሉ ሸጠን በድጋሚ ወደ ስፔን ተጉዘን ኑሮን እንደ አዲስ ለመምራት ከሪታዬ ጋር ተስማማን፤ እዛ ደርሰን የሚሰራ ስራ እንደማናጣ ልቤ እርግጠኛ ነው፡፡

# ምዕራፍ አስራ አምስት

## ካማሩንስ

የስፔን ጉዟችንን አስርዞ በድጋሚ ካራካስ ውስጥ የሚያስቆይ አጋጣሚ በህይወታችን ውስጥ ተከሰተ። ጊዜው 1962 ዓ.ም ነው፤ ከኤልድራዶ ከወጣው አስራ ስድስት አመታት ተቆጥረዋል። ከአሁን በኋላ እንደ ግራንድ ካፌ ንፁህ እና የተዋበ ምግብ ቤት ለማግኘት በጣም ከባድ ነው። በዛ ላይ በእዚሁ ወቅት ማህበረሰቡ ላይ ችግር እየፈጠሩ ያሉት የመሸታ ቤቶች እና መጠጥ የሚሸጡ ሱቆች እንደሆኑ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት እምነት ስላደረበት ፖሊሶች በእነዚህ አካባቢዎች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር እንዲያደርጉ ትዕዛዝ ሰጥቷል። ስለዚህ አሁን ላይ ምግብ ቤት እና መጠጥ መሸጫ ላይ መስራት ችግር ይዞ የመምጣቱ ነገር አጠያያቂ አይደለም። ስለዚህ ለጊዜውም ቢሆን ስለ ሆቴል ስራ ማሰቡን እርግፍ አርገን ትተነዋል።

ምን እንስራ ብለን በምናስብበት ወቅት ከካራካስ ሳንወጣ ሌላ የተሸለ ስራ መስራት የምችልበት ሀሳብ አእምሮአችን አፈለቀ። ይህ ስራ አልማዝ ማውጣት አልነበረም፣ እሱ የድሮ እቅዴ ነው።ያሁኑ ሃሳባችን ማራካይቦ ውስጥ ካማሩንስ' እየተባሉ የሚጠሩ ትልልቅ የሽሪምፕ የዓሣ ዝርያዎች ማጥመድ ነው። በጣም ትልልቆቹ ሽሪምፖች ደግሞ ላንጎስቲኖስ ተብለው ይጠራሉ። እነዚህን የአሳ ዝርያዎች ያገኘኋቸው ስፔን ከመሄዳችን በፊት ማራካይቦ ላይ አዲስ ነገር ካለ በሚል በተጓዝኩበት ጊዜ ነው። እዛም ስላረፍኩም እነዚህን ዓሦች ለማግኘት ችለናል።

በጊዜያዊነት ለማረፍያነት የሚሆን አንድ ምቹ ሆቴል ከተከራየን በኋላ ነገሮችን ቦታ ቦታ አስይዘን እነዚያን ዓሦች ያገኘንበት ባህር አቅራቢያ ላይ የራሳችንን ቦታ ገዛን። በመቀጠል በገዛነው ቦታ ለይ 'ካፒታል ቺክ' የተሰኘ ድርጅት በገዛነው ቦታ ላይ አቋቋምን። የድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ እና

ዳሬክተር ሄነሪ ሽሬሪ በመሆን ቦታው ላይ ተሰየምኩ፤ የእኔ ምክትል ደግሞ ውዷ ባለቤቴ ሪታ በመሆን ስልጣኗን ተረከበች።

አሁን እንግዲህ በአዲሱ ስራችን እራሳችንን ልንፈትሽ ዝግጅታችንን አጠናቀን ጨርሰናል። አስራ ስምንት የሚሆኑ የአሳ ማጥመጃ ጀልባዎችን ገዛን። እያንዳንዱ ጀልባ የሀምሳ ፈረስ ጉልበት ያላቸው ሲሆን በእያንዳንዱ ጀልባ ላይ ለዓሣ ማጥመድ የሚያገለግሉ እቃዎች በሙሉ እካተው እንዲይዙ ተደርጓል። በአጠቃላይ ለአንዷ ጀልባ ከእነ ተሟላ እቃዋ ከ አስራ ሁለት ሺህ ቦሊቫር በላይ ወጪ አድርገንበታል። ይህ ማለት አስራ ስምንቱ ጀልባ ለመግዛት ብዙ ወጪ አስወጥቶናል ማለት ነው።

በባህሩ አቅራቢያ የምትገኘውም ያቺ ትንሽዬ መንደር በእኛ ድርጅት መከፈት ምክንያት ሞቅ እንድትል እድል ፈጥሮለታል። በዛ ላይ ለብዙ ሰዎች የስራ እድልን ፈጥረንላቸዋል። ስለዚህ የእኛ ስራ ጥቅሙ የግላችን ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡም እንደሆነ የተረዳው ህዝብ በእኛ መምጣት ተደስቷል። በአካባቢው ላይ የሚኖሩ አብዛኛውን ሰዎች በድህነት አረንቋ ውስጥ የወደቁ ናቸው። እኔም ወደ ስራ ስገባ ስራ ፈላጊዎችን አምስት ለአንድ እየመደብኩ ያለተያዥ አንዳንድ ጀልባ በመስጠት ወደ ስራ በማስገባት የድርሻዬን ለመወጣት እየሞከርኩ ነው። በድርጅቴ ውስጥ ስራ ለመቀጠር የሚመጡ ሰዎችን የምቀጥረው ያለተያዥ ነበር። ምክንያቱም አንደኛ ስራ ፈላጊ ሰውን በተያዥ ምክንያት ማጉላላት ስለማልፈልግ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሰው ልጅ ካመንከው እምነት ከማጉደል እንደሚቆጠብ ስለማምን ነው።

በእኛ እና በሰራተኞቻችን መሀል ያለው ስምምነት እነሱ የተሰጣቸውን ጀልባ ይዘው በፈለጉት አቅጣጫ ይሰማራሉ ከዛ ይዘው የሚመጡትን ካማሩንስ እና ላንጎስቲኖስ ገቢያ ላይ ከሚሸጥበት ዋጋ በግመሽ ቀንሶ የእኛ ድርጅት ይረከባቸዋል ማለት ነው። እነሱ የመስራት አቅሙ ቢኖራቸውም አሳዎቹን ለማጥመድ የሚውል መሳርያ እና ጀልባ የሚሰጣቸው ድርጅቱ መሆኑ ጥቅማችንን እኩል ስለሚያደርገው በሰሪ እና ሰራተኛ መሀል አለመግባባት ፈፅሞ አይፈጠርም።

ስራችንም ካሰብኩት በላይ በጥሩ ሁኔታ እየሄደ ነው። ሰራተኞቻችንም በብዛት አሳ በያዙ ቁጥር የሚያገኙትም ገንዘብ በዛው ልክ እንደሚጨምር ስለገባቸው

ቀን በቀን ያለመሰልቸት ነው ስራቸውን የሚያከናውኑት። አሳዎቹን ወደ ከተማ ለመውሰድ እንዲያገለግሉን የተከራየናቸው ሶስት ማቀዝቀዣ የተገጠመላቸው መኪኖች ስራቸውን በተገቢው መልኩ ነው የሚከውኑት።ከባህሩ አጠገብ ትልቅ እና ረዥም ከእንጨት የተሰራ ጠረጴዛ አዘጋጅተናል። የጠረጴዛው ዋነኛ ጠቀሜታም ከአጥማጆቹ የተረከብነውን ካማሩንስ እና ላንጎስቲያኖስ አሳዎች ጭንቅላታቸውን እና የሆድ እቃቸውን ለማውጣት ነው። ይህንንም ስራ ለመከወን ከመቶ ሃያ እስከ መቶ አርባ የሚጠጉ ሴት ሰራተኞች በሪታ ስር ይተዳደራሉ። እነዚህ ሰራተኞች የአሳዎችን ጭንቅላት እና የሆድ እቃ ካወጡ በኋላ በቀዝቃዛ ውሀ አጥርተው እንዲያጥቧቸው ይደረጋል፤ ከዛ በአይነት በአይነታቸው መድበው ያስቀምጧቸዋል። ሪታ ከአጠገባቸው ስለማጠፋ ስራው በጥራት እና በቅልጥፍና ነው እየሄደ ያለው። እንደ አሳው ጥልቀት የሽያጭ ዋጋውንም የምታወጣው እራሷ ሪታ ነች። በየሳምንቱ ማክሰኞ እለት አሜሪካ ውስጥ የአሳዎች የገበያ ዋጋ ምን እንደሚመስል ከአንዱ ድርጅት አስቀድሜ በአረንጓዴ ወረቀት ይላክልኛል። ስለዚህ ለአሳዎቹ ዋጋ ለመተመን ብዙም ከባድ አልነበረም። በየቀኑ ቢያንስ ወደ አስራ አንድ ሺህ ኪሎ ግራም የሚመዝን አሳ ወደ አሜሪካ ሚያሚ እንልካለን።

ወደ አሜሪካ አሳዎቹን መላክ ከመጀመራችን በፊት የምናገኘው ገቢ ጥሩ የሚባል ነበር። በተጨማሪም ይህን ስራ አድማሱን ለማስፋት አንድ የተዋወቅሁት አሜሪካዊ ሁነኛ አስተዋፅዎ አድርጎልናል። ይህ አሜሪካዊ እንደ ወረቀት የነጣ ፊት ያለው ሲሆን በሀብትም ረገድ የሚታማ አይደለም። ነገር ግን የጅል አስተሳሰብ ያለው ሰው እንደሆነ ነገረ ስራው ይገልፃል። ስፓኒሽኛም ሆነ ፈረንሳኝኛ ፊፅሞ አይችልም። እኔ ደግሞ በተቃራኒው እንግሊዘኛ መናገር ይሳነኛል። እኛም ከእዚህ ሰውዬ ጋር ልንግባባ የቻልነው በምንሰራው ስራ ላይ የገንዘብ እገዛ አድርጎልን ሳይሆን አሳዎቻችን ጭንቅላታቸው ተቆርጦ ከፀዱ በኋላ የምናስቀምጥበት ማቀዝቀዣ ያለው ቤት ሊያከራየን በመቻሉ ነው። በእንደዚህ አይነት መልኩ ተቀራርበን ንግዳችንን ሚያሚ እንድናደርሰው በሚያቃቸው ሰዎች በኩል መንገድ ከፍቶልናል።

የእኔ ስራ የሚሆነው ከተረካቢዎቻችን ጋር ያለኝን ጉዳዮች መከወን ሲሆን ከእሱ በዘለለም ጀልባዎቹ ብልሽት አጋጥሟቸው እንደሆነ እና እናዳልሆነ በየጊዜው እቆጣጠራለሁ፣ እንዲሁም የአሳዎቹን ቁጥር የመቆጣጠሩን ሀላፊነት

ከሬታ ጋር በጋራ በመሆን እንሰራለን፤ በተጨማሪም ሰራተኞቻችንን የመንከባከብ እና ደሞዝ በአግባቡ የመክፈል ግዴታም የእኔ ነው። አንዳንዴ ለሰራተኞች ደሞዝ ለመክፈል ይገባ ከምሄደው ገንዘብ ድንቡሎ ሳንቲም ሳይተርፈኝ የምመለስበት ጊዜ አለ። ምክንያቱም በስራቸው ጠንክረው ያለመሰልቸት እንዲሰሩ ስለምፈልግ በደሞዛቸው ላይ የሆነ ያህል ጭማሪ እያደረኩ ስለምሰጣቸው ነው።

ስራችን በተገቢው መንገድ እየሄደ ነው ማለት ይቻላል፤ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ የባህር ላይ ወንበዴዎች ለስራችን እንቅፋት በመሆን ያስቸግሩናል። ቀደም ብዬ እንደተናገርኩት አሳዎቹን ለማጥመድ የሚገለገሉበትን እቃዎች የሚያቀርበው ድርጅታችን ስለሆነ አሳዎቹን የምንረከባቸው ገበያ ላይ ከሚሸጥበት በግማሽ ባነሰ ዋጋ ነው። ነገር ግን እነዚህ የባህር ላይ ወንበዴዎች የእኛን ሰራተኞች አሳቻ ቦታ ላይ እየጠበቁ ገበያ ላይ በሚሸጥበት ዋጋ መግዛትን ስላስለመዷቸው የሰራተኞቼን ታማኝነት ከቀን ወደ ቀን እየሸረሸሩት መጥተዋል። ይህም በመሆኑ በቀን የምናገኘው የአሳ ብዛት መቀነስ ከጀመረ ውሎ አድሯል። አንዱ ጀልባ በቀን ቢያንስ ስምንት መቶ ኪሎ ግራም አሳ ማስገባት ሲጠበቅበት እነዚህ የባህር ላይ ወንበዴዎች ከመጡ በኋላ ግን በእጥፍ ቀንሶ እስከ አራት መቶ ኪሎ ግራም ይዘው መመለስ ሰራተኞቹ ልምድ አድርገውታል። በእርግጥ እንደሰውኛ ሲታሰብ በሰራተኞቼ መፍረድ ከባድ ነው፤ ምንም እንኳን ይህን የስራ እድል የፈጠርኩላቸው እኔ ብሆንም እንዲሁም በእኔ ጀልባ እና መሳሪያ ቢሆንም አሳዎቹን የሚያጠምዱት በገቢያው ዋጋ የሚገዛቸው ሰው ሲያገኙ ግን በገንዘብ ቢደለሉ አይገርምም፤ ምክንያቱም ሰው ናቸዋ!! አብዛኛውን ሰው ደግሞ ጥቅም እምነቱን ያስበላዋል። እነዚህ የባህር ወንበዴዎች ደግሞ ይህ የሌብነት ንግድ ስለተመቻቸው በአካባቢው እየተመሸጉ የእኔን ሰራተኞች ማጥመዱን ቋሚ ስራቸው አድርገው ይዘውታል። ስለዚህ እኔ ስራውን ማቆም እስካልፈለኩ ድረስ የሆነ ዘዴ ፈልጌ እነሱን ከአካባቢው ማራቅ እናዳለበኝ ገብቶኛል። እንዴት ልቆጣጠራቸው እንደምችል ግን መላው ጠፍቶብኛል።

እነዚህን ካማሩንስ እና ላንጎስቲኖስ የተባሉ የአሳ ዝርያዎችን ወደ ተለያዩ ሀገሮች ከላክን በኋላ የሸጥንበት ገንዘብ ለእኛ የሚደርሰው በደብዳቤ አልያም በደረሰኝ መልኩ ነው። ታድያ እነዛን ደረሰኞች ወደ አንዱ ባንክ ወስጄ ስሰጣቸው እነሱም አሳዎቹ በደንብ መታሸጋቸውን እና መድረቃቸውን

የሚገልፅ ደብዳቤ አሳዎቹ ከተላኩበት ሀገር እንደደረሳቸው አረጋግጠው የትርፋችንን ሦስት አራተኛውን ገንዘብ ወዲያው ይሰጡናል፤ ቀሪውን ገንዘብ ደግሞ በተላኩት አሳ ምርታችን እንደረኩ የሚገልፅ ደብዳቤ ከተረካቢዎቻችን ሲደርሳቸው ይሰጡናል ማለት ነው፡፡ ይህ እንግዲህ የአሰራሩ ሂደት ነው፡፡

እንዲህ እንዲህ እያልን የሚያጋጥሙንን መሰናክሎችም በማለፍ ስራችንን በጥሩ ሁኔታ በመስራት ላይ እያለን ነው እንግዲህ ያ ያመንኩት አሜሪካዊ ያላሰብኩትን ዱብ እዳ ጥሎብኝ ያለፈው፡፡

ቀኑ ቅዳሜ ነበር፤ በእዚህ ቀን ደግሞ ባንኮች የእረፍት ቀናቸው ስለሆነ ስራ አይሰሩም፡፡ በዛ ላይ ያ ጅል ብዬ የገለፅኩት ሰው ጉድ የሰራኝ በባህር ወንበዴዎቹ ምክንያት የአሳ ምርቴ በቀነሰበት ወቅት ነበር፡፡ ስለዚህ የማጣውን አሳ ለማካካስ በሚል አንድ ትልቅ መርከብ ተከራይቼ ወደ 'ሎስ ሮክስ' ደሴት ሄደው እነዛን ክሬይ ፊሽ የሚባሉትን አሳዎች እንዲያመጡ አስደረኩ፡፡ የሎስ ሮክስ ደሴት እስከዛሬ ሰራተኞቼ ከሚሄዱበት አቅጣጫ በተቃራኒ ስለሆነ ከባህር ወንበዴዎቹ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን እሸሻለሁ በሚል ነው ይሄን ያደረኩት፡፡ የላኳቸውም ሰራተኞች ሲመለሱ የጠበኩትን ያህል አሳ ይዘውልኝ ተመለሱ፡፡ ከዛ እንደተለመደው የአሳዎቹ ጭንቅላት እና ሆድ እቃቸው ወጥቶ ከፀዱ በኋላ መርከብ ላይ ተጭነው ለጉዞ ዝግጁ ሆኑ፡፡ ከላይ እንደገለፅኩት ቀኑ ቅዳሜ በመሆኑ ገንዘቤን በባንክ በኩል መቀበል ስለማልችል ሁለተኛው አማራጬ ያ ያመንኩት ጅል አሜርካዊ ነበር፡፡ ስለዚህ ይህንን አሜሪካዊ ከመርከቧ ጋር ሚያሚ አብሮ ተጓዞ አሳዎቹን ሸጦ እንዲመለስ በእምነት ላኩት፡፡

ቀን አልፎ ቀን ቢተካም ምንም አይነት ምላሽ ግን ከአሜሪካዊው መስማት አልቻልንም፡፡ ሰኞን እና ማክሰኞን ስጠብቀው ብውልም እሱ ግን የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ፤ አለመምጣቱን ሳረጋግጥ ምንአልባት ከሚያሚ የተላከ መልዕክት ካለ ላረጋግጥ ብዬ ወደ ባንኩ አቀናሁ፤ "ምንም የለም" ነበር መልሳቸው፡፡ በዛ ጅል መጭበርበሬን አምኖ መቀበል በጣም ከብዶኝ ነበር፤ ግን ምን ያደርጋል ተከድቻለሁ፡፡ እኔ የጅል ሀብታም ነው ብዬ ሳስብ እሱ እኔን አጃጅሎ ገንዘቤን ይዞ ተሸበለለ፡፡ ቅዳሜ ባንኮች ስለማይሰሩ አሳዎቹን የሸጠበትን ደረሰኝ የሚቀበለው በእጁ ነው፡፡ ስለዚህ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ሚያሚ እንደደረሰ አሳዎቹን በፊት ከማስረክብበት ቦታ ውጪ ወደ ሌላ ቦታ ይዞ በመሄድ ሸጦ በእዛው መኮብለሉን መርጦ ነው፡፡

ይሄ ህሊናውን የሸጠ አሜሪካዊ ስንት ያቀድኩበትን ገንዘቤን ወስዶ የራሱን ህይወት ማደላደሉን ባሰብኩት ቁጥር ያበግነኛል። መሽነፌ ሰላም ስለነሳኝ ጊዜ ሳላባክን ወደ ሚያሚ በማምራት የአሜሪካዊውን ዱካ ማጣራት ጀመርኩ። በመጨረሻም የባለቤቱን አድራሻ ለማግኘት ችዬ ነበር፤ ነገር ግን እሷንም ጥሏት ከጠፋ ብዙ አመት እንደሆነው ስለነገረችኝ ከእሷ ጋር መጨቃጨቁ ትርጉም እንደሌለው ስለገባኝ ሁሉንም ነገር ትቼ ወደ ማራካይቦ ተመለስኩ። በተሰጡኝ መረጃዎች በመጠቀም ይገኝበታል ተብሎ የታሰበበት ቦታ ድረስ አሰስኩ፤ ግን ላገኘው አልቻልኩም። የጎረቤት ሀገራት ጭምር ሳይቀር ለማጣራት ሞክሬአለሁ፤ ጥረቴ ግን ፍሬ ሊያፈራልኝ አልቻለም።

ይኸው በእሱ ምክንያት በደረሰብኝ ኪሳራ ድህነት በሬ ድረስ መቶ ማንኳኳት ጀመሯል። ከሌላው ጊዜ በዘለለ ብዛት ያለውን ምርት ስለነበር እሱን አምኜ የላኩት ለማንሰራራት እራሱ አቅም አሳጥቶን ነበር። በትንሹ ከአንድ መቶ ሀምሳ ሺህ ዶላር በላይ የሚገመት ንብረት ወስዶብናል። የእሱ እና የባህር ወንበዴዎች ሴራ ተደማምሮ የመስራት አቅማችንን አዳከሙት። በእርግጥ ጀልባዎቹ ነበሩ፤ ነገር ግን የጀልባዎቹን የቀን ወጪ ለመሸፈን እና ለእዛ ሁሉ ሰራተኛ ደሞዝ ለመክፈል በእጃችን ላይ ያለው ገንዘብ በቂ አልነበረም። በእዚህም የተነሳ በሁለት እግራችን መቆም አስቸጋሪ ሆነብን፤ በዚህም ምክንያት እጃችን ላይ የቀሩንን ንብረቶች በሙሉ ለመሸጥ ተገደድን። ለዛ አሜሪካዊ ያለ ተያዥ ያን ሁሉ ንብረት አምኜ መስጠቴ ስህተት ቢሆንም ሪታ ግን በሚገርም ሁኔታ አንዳችም ክፉ ነገር አልተናገረችም ነበር። ለ አስራ አራት ዓመታት ለፍተን ካጠራቀምነው ሀብታችን አብዛኛውን በእኔ ስህተት በአንድ ቀን ለማጣት ብንገደድም እሷ ግን ተናግራ እኔን ማስከፋቱን አልመረጠችም። ምን አይነት ፍጥረት ነች? አምላክ ከሰጠኝ ነገሮች መካከል ለእኔ የማትገባ እሷ ብቻ ነች፤ ለእዛ ደግሞ ሁሌም አመሰግነዋለሁ።

አይኖቻችን በእንባ እንደተሞሉ፣ ሀዘን ውስጣችንን እንዳቆሰለው እነዛን በአሳ ማጥመድ ህይወታቸውን እንዲገፉ ጥሩ የስራ እድል የፈጠርንላቸውን ሰዎች ተሰናበተን መሄዳችን የግድ ሆነ። ለእነሱም ቢሆን የእኛ ከዛ መሄድ እጅጉን አስከፍቷቸዋል። ሁሉም በእኛ ምክንያት ህይወታቸውን መቀየር እንደቻሉ ምስክረነታቸውን ሰጥተውናል፤ ታድያ ምን ያደርጋል ማናችንም ባሰብንበት መዋል አንችልም። እኛ በእዚህ የባህር ዳርቻ የጀመርነው ስራ ሰላም ሰቶን መኖር ብንጀምርም ክፉ ቀን ግን በአሜሪካዊው ተመስሎ የሥራ ህሞታችንን

አፈረሰው፡፡ ከእዛ ይዘነው የወጣነው ትልቁ ሀብታችን ስናሰራቸው የነበሩት ሰዎች የሰጡንን በለቅሶ የታጀበ ፍቅር እና የሚያፅናና ተስፋ ብቻ ነው፡፡

# ምዕራፍ አስራ ስድስት

## ጎሬላዎቹ

የቤታችን በር እየተንኳኳ ስለነበር በሩን ለመክፈት ከተቀመጥኩበት ተነሳሁ፡፡ ጓደኛዬ ነበር፡፡ 'ኮለኔል ቦላኖ' ይባላል፡፡ እሱና ቤተሰቡ በሙሉ ፓፒለን ብለው ነው የሚጠሩኝ፡፡ ሌሎች ሰዎች እኔን ለመጥራት የሚቀናቸው ኢንሪክ በሚለው አልያም ሄነሪ በሚለው ነው፡፡ ይመጣል ብዬ ያላሰብኩት ጓደኛዬ ስለሆነ በሩ ላይ ቆሞ በማየቴ እየተደነቅሁ ተጠምጥሜ ሰላም አልኩት፡፡

"እንዴት ነህ ፓፒለን... ከተለያን ሶስት አመታት ተቆጠሩ አይደል" አለኝ

"በትክክል! የዛሬ ሶስት አመት ነው ለመጨረሻ ጊዜ የተያየነው... አምሮብሀል ወዳጄ"

"አንተም ተስማምቶሀል. . .ለምንድ ነው ግን መጥተህ አዲሱን ቤቴን የማታየው?"

"አንተ መች ጠራኸኝ"

"ጓደኛዬ እስከሆንክ ድረስ የግድ ቤቴን እንድታይ እኮ መጋበዝ አይጠበቅብኝም፡፡ የኔ ቤት ማለት የጓደኛዬም ቤት ነው፤ ስለዚህ መምጣት በፈልግህ ሰዓት መጥተህ ማረፍ ትችላለህ፡፡ በእኔ እሳቤ አንድ የልብ ወዳጅ የሆነን ሰው ወደቤቴ እንዲመጣ መጋበዝ እንደስድብ ነው የምቆጥረው፤ ምን አልባት የህይወት ሩጫ ፋታ ስላልሰጠህ ይሆናል መጥቶ መጠየኩን ችላ ያልከው" ብሎኝ ፈገግ አለ ሀሳቡ ላይ ስህተት ስላላገኘሁበት ምንም ማለት አልቻልኩም፤ ሄጄ ባለመጠየቄ ይቅርታ ጠይቄው ወደ ቤት እንዲገባ ጋበዝኩት፡፡ እኛ ወደ ውስጥ ስንገባ ሪታ ከመኝታ ቤት ስትወጣ ስለተገጣጠመ

በቆመበት አቅፎ በናፍቆት ሰላም ካላት በኋላ አጠገቡ የነበረውን ወንበር ስቦ ተቀመጠ፡፡ ከመቀመጡ ጭንቅላቱ ላይ ያለውን ኮፍያ በመሰልቸት ስሜት አውልቆ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠው፡፡ ውስጡ እንደተረበሸ ገፅታው በደንብ ይናገራል፤ ሪታ የቀዳችለትን ቡና ፉት እያለ ከራሱ ጋር በውስጡ ይነጋገራል፡፡

"እንዴት አደራሻዬን አገኘሽው?" አልኩት ዝምታውን ለመስበር

"እሱ የእኔ ጉዳይ ነው አይመለከትህም... አንተ ለምንድነው አድራሻህን ያላክልኝ?"

"ያው ህይወት አስቸጋሪ ነው፤ አንዱ ሲሞላ ሌላው ደግሞ ይጎላል፡፡ እሱን ለማስተካከል ደፋ ቀና ስትል ብዙ ነገሮችን ትዘነጋለህ፡፡ በዛ ላይ የማታስበው ችግር ያጋጥምህ እና አእምሮ ይወጠራል. . .ከዛ መርሳት የሌለብህን ነገሮች ትዘነጋለህ... ለዛ ነው ጓደኛዬ"

"አንተም ተቸግረሀል እንዴ?"

"አዎ እንዴት አልቸገርም ሰው አይደለሁ... እነሳለሁ በዛው ልክ በእንቅፋቶች እወድቃለሁ"

"ታድያ አጉል ሰዓት ነው የመጣሽው በለኛ? "

"ማለት?"

"አምስት ሺህ ቦሊቫር እንድታበደረኝ ነበር አመጣጤ"

"አይ ጓደኛዬ በማይሆን ሰዓት ነው የመጣሽው"

"እኛም ኪሳራ ውስጥ ነው ያለነው" አለች ሪታም አያይዛ

"የእውነትህን ነው ፓፒለን? ከስራችኋል? ታድያ በእዚህ ምክንያት ነው መምጣትህ እኔን መጠየቅ ያልቻልከው"

"አዎ... እሱንም ይጨምራል"

"እንግዲያውስ አንድ ነገር ልንገርህ ፓፒለን... እጅግ አሳዛኝ ሰው ነህ... ምን አስበት እንደዚህ አይነት ችግር ውስጥ ስትገባ ማንን ላማክር ብለህ ብታስብ? እኔ ጓደኛህ አይደለሁም እንዴ? እና ቀድሞ ምናለ ችግሩን ነግረኸኝ በጋራ መፍትሄ ብንችል:: የደረሰባችውን ኪሳራ ከእናንተ ባልሰማም ከማወቅ ግን አላገዳችሁኝም:: አሁን የመጣሁት ገንዘብ ስላስፈለገኝ ሳይሆን ላጋጠማችሁ ችግር የኀኝነቴን አስተዋፅዎ ለማድረግ ነው" አለ እንደተናደደብን በሚገልፅ ንግግር

እኔም ሆንኩ ሬታ በሰማነው ነገር ልባችን ተነክቷል፤ አንዳችም ቃል ከአንደበታች አልወጣም:: ምንም እንኳን እኛ የማንንም እርዳታ ባንጠይቅም እኛ ከረዳናቸው ሰዎች ግን የደረሰብንን ኪሳራ ሰምቶ በራስ ፍቃድ ሊረዳን የመጣ ማንም የለም ነበር:: አንዳንዶቹማ በእኛ ስር ተቀጥረው ሰርተው፣ ተለውጠው የራሳቸውን ህይወት ያደላደሉ ናቸው:: ሁሉም እራሳቸውን ሲችሉ ግን በእነሱ ላይ ካለኝ ሀላፊነት በላይ አስተዋፆ አድረጌላቸዋለሁ፤ ነገር ግን እኔ ስወድቅ ሁሉም "ጆሮ ዳባ ልበስ" ብለው ነው የሸሹት:: ይህ ሰው ግን ሀቀኛ ሰው ነው፤ እኔ ምን እንዳደረኩለት ብረሳም እሱ ግን አስታውሶኝ መጣ::

"ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ ፓፒለን?" አለኝ ከጥቂት ዝምታ በኋላ

"እንደገና ለማንሰራራት ብዙ ገንዘብ ያስፈልገናል" አልኩት በቀጥታ ላለመጠየቅ

"ሬታ ግቢና ልብስሽን ቀይሪ... ሶስታችንም ወጣ ብለን እራታችንን እየበላን ማውራት አለብን" አለ የእኔን ምላሽ ችላ ብሎ

አንድ ግርማ ሞገሱን ወደጠበቀ ሆቴል ይዞን ሄዶ ካለንበት ውጥረት ረገብ እንድንል የተቻለውን ሁሉ ከማድረግ ሳይቆጠብ አዝናናን::

"ፓፒ መስራት የምትፈገውን ስራ ለይተህ እወቀው:: ከዛ ምን ያህል ገንዘብ እንደሚያስፈልግህ አስላ እና እኔን ጠይቀኝ:: ያንን ወጪ እኔ እሸፍናለሁ:: ያ በቂ ሆኖ ካልተገኘ ደግሞ ከወንድሜም ቢሆን ተበድሬ እሰጥሀለሁ:: ዋናው ነገር አንተ መስራት የምትፈልገውን አጥርተህ እወቅ:: ገንዘቡ አሳሳቢ አይደለም" አለኝ እኔም ጊዜ ወስጄ አስቤበት እንደማሳውቀው ነገርኩት

ከቦሎኛ ጋር ከተለያየን በኋላ እኔ እና ሪታ በራችንን አንኳኩቶ ስለመጣልን እድል እየተወያየን ወደ ቤታችን ተመለስን፡፡ እውነት ለመናገር ወጥሮን ከነበረው ጭንቀት በተወሰነ መልኩ ነፃ እንድንሆን ቦሎኛ ትልቅ ድርሻ ተወጥቷል፡፡ ኮለኔል ቦሎኛን የማውቀው ኢል ዶራዶ ውስጥ አስር አለቃ ሆኖ በሚሰራበት ወቅት ነው፡፡ የዛኔ ነው እንግዲህ ጓደኝነታችን መሰረቱን የጣለው፤ ይኸው ያኔ የተጀመረው ወዳጅነታችን ዛሬ ላይ ለችግሬ መፍቻ ቁልፍ ሆኖ ዛሬ ላይ ብቅ አለ፡፡

ምን መስራት እንዳለብኝ ሳስብ ከምግብ ቤት የተሻለ ሌላ አማራጭ ሊመጣልኝ አልቻለም፡፡ ስለዚህ በእዚሁ ሀሳብ ከሪታ ጋር ከተስማማን በኋላ ነገሩን ለቦሎኛ አሳወቅነው፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥም 'ጋፕ' ተብሎ የሚጠራ ምግብ ቤት ስላገኘን ኪራዩን ከፍለን ዳግም ወደ ስራ ለመሰማራት በቃን፡፡ እንደ አጋጣሚ ሆኖ በሰዓቱ የፈረንሳዩ ፕሬዝዳንት ጀነራል ቻርልስ ዲጋሊ በቬንዙዌላው ፕሬዝዳንት ጥሪ ተደርጎላቸው ሀገሪቱን ለመጎብኘት የመጡበት ወቅት ነበር፡፡

ካራካስም ሆነች ህዝቦቿ ጀነራሉን ለመቀበል ሽር ጉድ እያሉ ነው፡፡ እኔም በአዲሱ ሆቴላችን በረንዳ ላይ ከአንዱ ደንበኛችን ጋር ቁጭ ብዬ የህዝቡን ትርምስ በትዝብት እየተመለከትኩ ቡና እየጠጣሁ ነበር፡፡ አጠገቤ የተቀመጠው ሰውዬ ስለሰማው የተለያዩ ነገሮች እያነሳ የባጥ የቆጡን እያነሳ ማውራቱን ቀጥሏል፡፡ በመጀመርያ አሳ እንዴት እንደሚገፈፍ ሳልጠይቀው ከነገረኝ በኋላ እንደገና ደግሞ ድምፁን ዝቅ አድርጎ እዚህ ሀገር ላይ አንድ ሊሰራ ያሰበው ስራ እንዳለ እና በስራው በሚሊየን የሚቀጠር ገንዘብ ሊያገኝበት እንደሚችል መደስኮር ጀመረ፤ በስራው ላይ ሊያግዘው የሚችል ሰው እየፈለገ እንደሆነ ከነገረኝ በኋላ ማንም እንዳልሰማው ለማረጋገጥ ዙርያውን ቃኘ፡፡ በዚህ መሀል ነበር በምግብ ቤታችን ከሚሰሩት አስተናጋጆች መሀከል አንዱ መጥቶ ለሁለት የታጠፈች ወረቀት የሰጠኝ፡፡ ወረቀቷን ከፍቼ ሳየው የሪታ የእጅ ፅሁፍ ነው፡፡

"ከዚህ ሰውዬው ጋር ምን እያወራችሁ እንደሆነ አላውቅም፤ ነገር ግን አጠገብህ ያለው ሰውዬ አንተ ለመናገር አፍህን በከፈትክ ቁጥር በተመስጦ ነው የሚያዳምጥህ፡፡ ሲታይ ደግሞ ፖሊስ ይመስላል፡፡ ስለዚህ ተጠንቀቅ" ይላል

እኔም ከተቀመጥኩበት ፊት ለፊት አይኔን ስጥል አንድ ሰውነቱ ግዙፍ የሆነ ሰውዬ ላይ አረፈ፡፡ ዝንጥ ያለ አለባበስ ነው የለበሰው፤ በደንብ ካስተዋልኩት በኋላ ከመቀመጫዬ ተነስቼ ወደእሱ ሄጄ "ይቅርታ ወንድሜ… እያጨስከው ያለው ሲጋራ የፈረንሳይ ምርት ነው አይደል?" ብዬ በስፓኒሽኛ ጠየኩት ዜግነቱ ምን እንደሆነ እንኳን ሳላረጋግጥ

"አዎ… የፈረንሳይ ምርት ነው… እኔም ፈረንሳዊ ነኝ" አለኝ

"እውነት? ታድያ ከፈረንሳዩ ፕሬዝዳንት ጎሬላዎች መሀከል ነሃ" አልኩት እሱም ከተቀመጠበት ተነስቶ እራሱን ማስተዋወቅ ጀመረ "ኮሚሽነር ቢሎን እባላለሁ፤ የጀነራሉን ደህንነት የመጠበቅ ሀላፊነቱ የኔ ነው" ካለኝ በኋላ ተመልሶ ቁጭ አለ

"ስላወቅሁ ደስ ብሎኛል"

"አንተም እኮ ቬንዙዌላዊ አትመስልም…የየት ሀገር ሰው ነህ?"

"ተው እንጂ ኮሚሽነር… ማንነቴንማ በደንብ ታውቀዋለህ… በአጋጣሚማ እዚህ አልተገኘህም" አልኩት

"በአጋጣሚ እንኳን አይደለም… ግን… "

"ለመዋሸት አትሞክር ኮሚሽነር…መናገር ያለብህን እውነት ብቻ ንገረኝ… መጠጥ ይጨመርልህ?"

"እሺ"

"እና ወደ እኔ ጋር ያመጣህ ምክንያት ምንድነው?"

ኮሚሽነሩ በመጨረሻ መደባበቁ እንደማያዋጣው ስለተረዳ "ምን መሰለህ… እንደምታውቀው የፈረንሳዩ ፕሬዝዳንት ለጉብኝት ወደ እዚህ ይመጣሉ፡፡ እሳቸው ከመምጣታቸው በፊት ካራካስን ለቀው መውጣት የሚገባቸው ሰዎች አሉ፡፡ የእነዛን ሰዎች ስም ዝርዝር የያዘው ወረቀት ደግሞ ለሀገሪቱ የውጪ ጉዳይ ሚንስቴር ገቢ የማደርገው እኔ ነኝ፡፡ ከዛን የቬንዙዌላ የውጪ ጉዳይ ሚንስትር ደግሞ የራሱን እርምጃ እንዲወስድ ይደረጋል ማለት ነው" አለኝ

"የስም ዝርዝሩ ውስጥ እኔ አለሁ?"

"እሱን ገና አልወሰንኩም"

"ስለ እኔ ምን ታውቃለህ?"

"ቤተሰብ መስርተህ ኑሮህን እዚህ ማድረግህን"

"ሌላስ?"

"ሁለት እህቶች እንዳሉህም አውቃለሁ።አንደኛዋ ፓሪስ ሁለተኛዋ ደግሞ ግሪኖብል ውስጥ እንደሚኖሩም መረጃው አለኝ"

"አንተ ብዙ ነገሮች አጣርህ ነው የመጣኸው ማለት ነው። ሌላስ ምን የምትነግረኝ ነገር አለ?"

"ሌላ የምነግርህ የምስራች ነው። ከሚቀጥለው አመት በኋላ ወደ ፈረንሳይ መግባት ትችላለህ። ምንም እንኳን በወንጀል ብትፈለግም ከቆይታ ብዛት የክስ ፋይሎችህ ስለጠፉ ነፃ ሰው ሆነሃል"

"ማነው ይሄን ሁሉ ነገር የነገረህ?"

"ፓሪስን ከመልቀቄ በፊት ስለ ሁሉም ነገር መረጃ ነበረኝ፣ በርግጥ እዚህ ሀገር ላለው የፈረንሳይ ቆንፅላም የክሱን መነሳት የፈረንሳይ መንግስት አስቀድሞ አሳውቋል"

"ታድያ ለምንድነው እነሱ እስከዛሬ ያልነገሩኝ?"

"አድራሻህን ስላላወቁት ነው"

"ስለነገርከኝ መልካም ዜና አመሰግናለሁ። ታድያ እዚህ ሀገር ላለው ቆንፅላ ሄጄ ስለሁኔታው ማስረዳት እችላለሁ ማለት ነው?"

በተመቸህ ሰዓት"

"ነገር ግን ኮሚሽነር በእርግጠኝነት አንተ በእኔ ሆቴል የተገኘኸው የእኔ ክስ መነሳቱን ለመንገር አልያም እህቶቼ የት እንዳሉ ለመንገር ብቻ አይመስለኝም"

"ትክክል! አንተን ለማየት ነው ወደ እዚህ የመጣሁት"

"አንተ ፈረንሳይ ውስጥ የምታውቀው ፓፒለን ባልሰራው ወንጀል ተከሶ ለፍርድ የቀረበውን ነው። ያኔ የሰጡኝ ማንነት ግን በዛን ጊዜ ላይ ሆኜ እንኳን የሌለኝን ስብዕና ነው"

"አምንሀለሁ... አሁን ያለህበት ደረጃ ላይ ቆመህ መመልከቴ አስደስቶኛል"

"ስለእኔ አሁን በሚገባ ተረድተሃል... እና አሁን ስሜን በዝርዝርህ ውስጥ ታካትተዋለህ?"

"አይ"

"እንደዛ ከሆነ ወደ እኔ ምን እንዳመጣህ አሁን እኔ ልንገርህ?"

"ደስ ያለኛል"

"እንግዲያውስ አንተ ወደ እዚህ የመጣኸው እኔ እና እኔን መሰል በወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎች ለገንዘብ ሟቾች ናቸው የሚል እምነት ስላላችሁ ነው። ምን አልባትም ጥቅም የሚያስገኝላቸው ከሆነ በጀነራሉ ላይ ጥቃት ያደርሳሉ ብላችሁ ስላሰባችሁ ነው ወደ እዚህ የመጣኸው... ነገር ግን ሀሳቡ ስህተት ነው ኮሚሽነር! በመጀመርያ ደረጃ ምንም ያህል ገንዘብ ባገኝበት እንኳን የፖለቲካ ውጥንቅጥ ውስጥ መግባት አልፈልግም። ሲቀጥል ደግሞ በጀነራሉ ላይ በሚደርሰው ማንኛውም ጥቃት ቬንዙዌላ ውስጥ ያለ ሰው የሚጠቀመው ጥቅም ያለ አይመስለኝም ስለዚህ ሀሳባችሁ ስህተት ነው" አልኩት

"ጥቅሙማ ለእናንተ ሳይሆን የኦ.ኤ.ኤስ (organization of America sate) ነው ተጠቃሚው" አለኝ

"እሱም ቢሆን ምን አልባት ነው እንጂ የተረጋገጠ መረጃ የላችሁም። አንተ እንዳልከው የእዚህ እቅድ ባለቤት ኦ.ኤ.ኤስ ቢሆን እንኳን ፈረንሳዊ በሆነ ሰው

ተጠቅመው ይህን ድርጊት ይፈፅማሉ ብዬ አላስብም። ጀነራሉን ለማስወገድ እንዲህ ያለ የጅል መንገድ ይጠቀማሉ የሚል እምነት የለኝም" አልኩት

ኮሚሽነሩ በሀሳቤ የተስማማ ይመስል ወዲያው ሌላ ርዕሰ ጉዳይ በማንሳት ጨዋታ ለመቀየር ሞከረ። ትንሽ ካወራን በኋላ ፈረንሳይ በምሄድ ጊዜ እንደምጠይቀው ቃል አስገብቶኝ ምግብ ቤቱን ለቆ ወጣ። እኔም በነገረኝ የምስራች እየተገረምኩ ተነስቼ ወደውስጥ ገባው። ስላወራነው ነገር ሪታ ለመስማት በጉጉት እየጠበቀችኝ እንደሆነ ስለማውቅ ሳትጠይቀኝ ሁሉንም ዘክዝኬ ነገርኳት። ከሁሉም በላይ ፈረንሳይ መግባት እንደምችል እና የክስ መዝገቤ ከጊዜ ቆይታ መጥፋቱን ስትሰማ ደስታዋ ገደብ አጥቶ ነበር።

ጀነራል ቻርልስ ሲመጣ የፈረንሳይ ዜግነት ያላቸው ብዙ ሰዎች ካራካስን ለቀው እንዲወጡ ተደርጎ ነበር፤ እኔን ግን የተናገረኝ ሰው አልነበረም፤ ስለዚህ ኮሚሽነር ቢሎን ቃሉን አክብሯል ማለት ነው። ቬንዙዌላ ላይ የነበረው የጀነራሉ ጉብኝት ያለ ችግር በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል። እኔን የገረመኝ ግን በጀነራሉ እዚህ መገኘት የቬንዙዌላ ህዝብ ደስታው ከምን የመነጨ እንደሆነ አለማወቄ ነው። የሀገሬ ሰዎች እኮ በእድሜዬ ማየት የሌለብኝ ሰቆቃ እንዳይ የፈረዱብኝ ናቸው። ስለዚህ የእነሱ ወደ እዚህ መምጣት ምኑ ያስደስታል? ይሄ ጅልነት ነው!!

የፈረንሳዩ ጀነራል ወደ ሀገሩ ከተመለሰ ከጥቂት ቀናቶች በኋላ በቀጥታ ካራካስ ውስጥ ወደሚገኘው የፈረንሳይ ቆንፅላ አመራሁ። ከዛም ክሴ መጥፋቱን የሚገልፀውን ሰነድ እንዲያሳዩኝ ጠየኩ። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ አንዲት ልጅ እግር ፈረንሳዊት ሰነዱን አምጥታ አሳየችኝ። ከአንድ አመት በኋላ ፈረንሳይ መግባት እንደምችል ወረቀቱ ላይ ተገልጿል። ባልታሰበ ሰዓት የተገኘ የምስራች ነው፤ ቢያንስ ተወልጄ ወጣትቴን እስካየሁባት ጊዜ ድረስ የነበረኩባትን ምድር በነፃነት አይቶ መውጣት እራሱ ትልቅ ነገር ነው።

የምግብ ቤት ስራችን በፍጥነት ከገባንበት ኪሳራ እንድናንሰራራ አድርጎናል፤ አልፎ ተርፎ ከእሱ በተጨማሪ መሀል ካራካስ ውስጥ "ቻካይቶ" የሚባል የምሽት ጭፈራ ቤት እንድንገዛ አረድቶናል። ይህን መሸታ ቤት ስንከፍት የተውነውን ህይወት በድጋሚ መላመድ ግድ ሆነብን። ካራካስ ውስጥ መሸታ ቤት ውስጥ የሚያመሸው ሰው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሄዷል። አብዛኛውን ጊዜዬን በምግብ ቤታችን ውስጥ አሳልፍ እና ሲደብረኝ ደግሞ በካራካስ ጎዳናዎች ላይ መንሸራሸርን እመርጥ ነበር። በዛን ጊዜ ነው እንዲህ መንገድ ላይ ገንዘብ ለማግኘት ውር ውር የሚሉ ህፃናቶችን የተዋወኩት። እነዚህ

ህፃናት ገና በጨቅላነታቸው የድህነትን ቀንበር ተሸክመው የወጡ ስለሆኑ ያለ እድሜያቸው ስራ ይሰራሉ። ቤተሰቦቻቸውም ድህነታቸው ስለሚበልጥባቸው ልጆቹ ከሚውሉበት ቦታ ይልቅ ይዘውት የሚመጡት ገንዘብ ላይ ያተኩራሉ። አብዛኞቹ ህፃናት ከአምስት እስከ አስራ ሁለት አመት ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ናቸው። እነዚህ ልጆች ጫማ በመጥረግ፣ የምሽት ክለቦችን በር በመጠበቅ፣ ሲጋራ በመሸጥ እና በመሳሰሉ ስራዎች ላይ ተሰማርተው ያሉ ናቸው።

እኔም እንግዲህ በመንገድ ላይ ራሰሴን ለማዝናናትና ንፁህ አየር መውሰድ በምፈልግት ወቅት ነበር 'ፓቢሊቶ' የሚባል ትንሽዬ እና ሲበዛ ቀጫጫ የሆነ ልጅ የተዋወቅሁ። የሚገርመው ግን ድፍረቱ እንደቅጥነቱ አልነበርም፤ ማንንም አይፈራም። ፀብ ለመፍጠር ካሰበ ትልቅ ትንሽ አይልም፤ ሲጣላ ያ ቀጫጫ ሰውነቱ እንደ አንበሳ ይቆጣል። ፓብሊቶ እና ጓደኞቹ ወደ መሸታ ቤት መኪናውን አቁሞ የሚገባ ሰው ካዩ መኪናዋን ለመጠበቅ ተሽቀዳድመው ወዳቆማት ሰውዬ ጋር ይሄዳሉ። ፓብሊቶ ደግሞ በእንደዚህ አይነት ነገር ችግር የለበትም፤ ቀድሞ የሚደርሰው እሱ ነበር። እኔም ሳቀርበው የቻልኩት ይህ ፍጥነቱ ስለሳበኝ ነው። ፓብሊቶ የሚኖረው ከሴት አያቱ ጋር ሲሆን አያቱ በጣም ከማርጀታቸው የተነሳ እንደልባቸው ተንቀሳቅሰው መስራት እንደማይችሉ ነግሮኛል፤ ከዛ በተጨማሪ ደግሞ ሁለቱም አይኖቻቸው የማየት አቅማቸው እንደቀነሰ ነግሮኛል። እናቱ ደግሞ የገዛ ጎረቤታቸው ቤታቸው ገብቶ ሬዲዮ ሊሰርቅ ሲል እጅ ከፍንጅ ስለያዘችው አጠገቧ ባገኘችው ጠርሙስ ጥርሱን በማውለቋ እስር ቤት ገብታለች። እናቱ ስትታሰር የዘጠኝ ዓመት ጨቅላ ነበር። ቢሆንም ግን በእዚች ትንሽ እድሜው አያቱን እና ከስሩ ያሉትን ወንድም እና እህቱን የማስተዳደር ጫናው እሱ ላይ ወደቀ። እኔም የተዋወቅሁት በእዚሁ የጭንቅ ሰዓት ነበር፤ አያቱን ሆስፒታል ይዞ ሄዶ እንዲያሳክም ገንዘብ ሰጥቼዋለሁ። ከዛም አልፎ ለመድሀኒት መግዣ እና ለአንዳንድ ወጪዎች የተቻለኝን ያህል ድጋፍ አደርግላቸው ነበር።

የሆነ ጊዜ ላይ የማይረሳኝ ልክ እንዳየኝ እየሮጠ ወደ እኔ መቶ አያቱ ካለባቸው በሽታዎች በተጨማሪ የአስም በሽታ እንዳለባቸው ዶክተሩ እንዳስረዳው እያለከለከ ነገረኝ። ከዛ ጊዜ በኋላ አያቱን በአግባቡ እንዲከታተላቸው በአንክሮ ነገርኩት፤ እሱም ሁሌ ማታ ማታ ወደ እኔ እየመጣ አያቱ ያሉበትን ሁኔታ ይነግረኝ ነበር። ታድያ አንድ ቀን አርባ ቦሊቮር እንድሰጠው ጠንከር አድርጎ ጠየቀኝ፤ ለምን እንደፈለገው ስጠይቀው አያቱ ተንጠልጣይ አልጋ ላይ እንደሚተኙ እና ያ ደግሞ የአስም በሽታቸውን ሊያባብስባቸው ስለሚችል ፍራሽ ሊገዛላቸው አስቦ እንደሆነ ነገረኝ፤ እኔም ምንም ሳላቅማማ ያለኝን ብር ከኪሴ አውጥቼ ሰጠሁት።

ይህ ህፃን ታድያ አንድ ቀን የመኪና ግጭት ይደርስበት እና ሆስፒታል ይገባል፡፡ በቀጣዩ ቀን ስለጤናው ለማወቅ ወደ ሆስፒታሉ ሄድኩ፡፡ ዶክተሮቹ የቀኝ እግሩ በተወሰነ መልኩ ከመጎዳቱ በስተቀር ለጤናው የሚያሰጋው ነገር አለመኖሩን ነግረውኝ ወደ ክፍሉ አመራሁ፡፡

"ፓብሊቶ እንዴት ነህ?"

"ደህና" አለኝ ቅልስልስ ባለ ድምፀት

"ቤተሰቦችህ እንዳይጨነቁ ያለህበትን ቦታ እንዳሳውቅ ቤታቸው የት አካባቢ እንደሆነ ንገረኝ"

"እኔ እራሴ ካላሳየሁ በስተቀር እንደዚህ በምልክት ለመንገር በጣም አስቸጋሪ ነው" አለኝ በጥድፊያ እኔም ብዙም ላስጨንቀው ስላልፈለግሁ ትንሽ አጫውቼው በነገታው ተመልሼ እንደምመጣ ነግሬው ከሆስፒታሉ ወጣሁ፡፡

ምሽት ላይ ጓደኞቹን ሳገኛቸው የቤተሰቡን ቤት እንዲያሳዩኝ ጠየኳቸው፤ በሚገርም ሁኔታ ግን አንድ ሰው እንኳን አውቀዋለሁ ያለኝ አልነበረም፡፡ ምንም እንኳን እነሱ ለእኔ መናገር ባይፈልጉም እንደሚያውቁት ግን እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ ምክንያቱም ሁል ጊዜ ወደቤት ለመግባት ሲፈልጉ ተያይዘው ነበር የሚሄዱት፡፡ ነገሩ ግራ ቢያጋባኝም ተስፋ ላለመቁረጥ ለፓቢሎቲ ነርስ ምን አልባት እሱን ለመጠየቅ የሚመጣ ሰው ካለ ስልክ እንድትደውልልኝ አድራሻዬን ሰጠኋት፤ ከሁለት ቀናት በኋላም ስልክ ደውላ ፓቢሊቶን ሊጠይቅ የመጣ ሰው መኖሩን ነገረችኝ፤ እኔም ጠያቂው እንዳያመልጠኝ ስላልፈለኩ በፍጥነት ወደ ሆስፒታል ሄድኩ፡፡

ፓቢሊቶ ወደተኛበት ክፍል ስገባ ጠያቂዋ ከፊት ለፊቱ ተቀምጣ አየኋት፡፡ ፓቢሊቶ እኔን በማየቱ ውስጡ የተረበሸ ይመስላል፤ ለሁለቱም ሰላምታ ከሰጠሁ በኋላ አቅራቢያዬ ባለው ወንበር ላይ ቁጭ አልኩ፡፡

"እሺ ፓቢሊቶ አሁን እንዴት ነህ? እየተሻለህ ነው?" አልኩት እሱም በአዎንታ እራሱን ነቀነቀልኝ "ታድያ ምነው ፊትህ የተጨነቀ ይመስላል?"

"እረ አልተጨነቅሁም ኢንሪክ ትንሽ እግሬን ስላመመኝ ነው"

"እረ አሁን አንተ ከመምጣትህ በፊት እኮ እየሳቀ ነበር፡፡ ንፋስ ነገር ገብቶት ይሆናል" አለች ጠያቂዋ ሲትዮ

"አንቺ ከቤተሰቡ መካከል ነሽ እሜቴ?" አልኩ ወደ ሴትየዋ ዞሬ

"አይ እኔ ጎረቤት ነኝ"

"አያቱ እንዴት ናቸው... ታናናሾቹስ?"

"የማን አያት?"

"የእሱ ነዋ"

"ኧረ ፓቢሊቶ አያት የለውም!" አለች ግራ እየተጋባች... ወዲያው ነገሩ አቅጣጫውን እንዳይቀይር ስለፈለኩ እጇን ይዤ ከክፍሉ ይዣት ወጣሁ

"ይቅርታ ይዤሽ የወጣሁት ብቻችንን እንድናወራ ስለፈለኩ ነው... ስለ ቤተሰቡ ምን ታውቂያለሽ?"

"በርግጥ ታናናሾች አሉት... አያት የሚባል ግን በጭራሽ የለውም"

"እናቱስ እስር ቤት ነች?"

"ኧረ እናቱ እኮ መስራት የማትችል የአእምሮ ህመምተኛ ነች" አለችኝ

ይህ ካራካስ ያበቀለችው ገራሚ ህፃን እናቱ የአእምሮ ታማሚ መሆኗን ለእኔ ለመንገር አልፈለገም፡፡ ስለዚህ በእውኑ አለም የሌለችውን የአስም ታማሚ አያቱን ፈጥሮ እኔን እርዳታ በመጠየቅ ማስተዋል የተሳናትን እናቱን ለማስደሰት መጣሩ ነው፡፡ ሁሉንም ነገር ልጠይቀው ከመጣችው ሴትዬ ካጣራው በኋላ ተመልሼ ወደ ትንሹ ጓደኛዬ ክፍል አመራሁ፡፡ የደበቀኝን ውሸት እንዳወቅሁ ቀድሞ ስለተረዳ አይኔን ለማየት አፍሮ ሲጨነቅ አየሁት፡፡ እኔም በቀጥታ ወደእሱ ሄጄ እንዲያየኝ ከአገጩ ቀና ካደረኩት በኋላ "pablito , eres un tronco do hombre. . .(ጀግና ነህ!!) " አልኩት፤ ቀጥዬም ለቤተሰቡ የሚሆን የመቶ ቦሊቫር ዋጋ የተፃፈበት ደረሰኝ ሰጥቼው ጓደኝነታችን እንደሚጠነክር እና ሁሌም ከጎኑ እንደሆንኩ ነግሬው ወጣሁ፡፡ ወደ ቤቴ ስመለስም እንደ እዚህ አይነት የልጅ አዋቂ ጓደኛ ስለሰጠኝ ፈጣሪዬን አመሰገንኩ፡፡

# ምዕራፍ አስራ ሰባት

## ሞንትማርትሪ

ጊዜው 1967 ነበር... የክስ ፋይሌ መጥፋቱን ተያይዞ ወደ ፈረንሳይ ብቻዬን ለመሄድ የወሰንኩበት ወቅት ነው፡፡ ብቻዬን ለመሄድ የወሰንኩት በዚህ ሰዓት እዚህ ያለውን ስራ ከመቼውም የበለጠ ትኩረት እንደሚፈልግ ስላማውቅና ሪታ ደግሞ ለዚህ ብቁ መሆኗን በማሰቤ ነው፡፡ እሷም "ሂድና ዘመዶችህን በገዛ ቤታቸው አግኛቸው፡፡ የአባትህ መቃብር ላይም ሄደህ ፀልይ" ከማለት አትቦዝንም ነበር፡፡ ካራካስ ውስጥ ከሚገኘው የፈረንሳይ ቆንስላ ሄጄ የተከሰስኩበት ሰነድ መጥፋቱን የሚያረጋግጠውን መረጃ ከተቀበልኩ በኋላ ተወልጄ ወዳደኩባት ፈረንሳይ ለመሄድ ዝግጅት ጀመርኩ፡፡

እንግዲህ ሀገሬን ለቅቄ ከወጣሁ ከሠላሳ ሰባት አመት በኋላ ተመልሼ ልገባ ነው፡፡ በእርግጥ 1956 ዓ.ም ላይ ስፔን ውስጥ ከቤተሰቦቼ ጋር ተገናኝቼ ደስ የሚል ጊዜ አሳልፌ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላም ባሉት አስራ አንድ አመታትም ደብዳቤ ስለምንላላክ ብዙም የራቁ መስሎ አልተሰማኝም ነበር፡፡

አሁን 1967 ዓ.ም ደግሞ ቤታቸው ድረስልሄድ ችያለሁ፡፡ መሄድ ብቻ ሳይሆን ከእነሱ ጋር አብሬ እራት በልቻለሁ፤ እህቶቼንና የእህቶቼን ልጆች አቅፌ እንደፈለግሁ ለመሳም በስተመጨረሻ አምላክ እድሉን ሊሰጠኝ ችሏል፡፡ ታንቴ ጁ በአባቴ ቤት ውስጥ ሳገኛት አሁንም ለአባቴ ታማኝ እንደሆነች ታስታውቅ ነበር፡፡ ሁሌም ከቤቷ ሳልወጣ ሳጫውታት ብውል ደስ ይላታል፤ እኔም ያጣሁትን የእናትነት ፍቅር በስተርጅና ከእሷ በማግኘቴ ደስታዬ ወደር የለውም፡፡

"ታውቃለህ... አባትህ እኮ ያለ ጊዜው ነው የሞተው" አለችኝ ታንቴ ግድግዳው ላይ የተሰቀለውን የአባቴን ፎቶ እየተመለከተች

"እንዴት?"

"በዚያ እድሜው ጊዜውን ከልጆቹ እና ከልጅ ልጆቹ ጋር እየተጫወተ ማሳለፍ ሲገባው እሱ ግን ራሱን በስራ መወጠርን ነበር የመረጠው፤ አስበው ሁል ጊዜ እነዚያን የምታያቸው ትልልቅ ጣሳዎች ይዞ በመዞር የጓሮ አትክልቶቹን ሲያጠጣ፤ በእርግጥ አባትህ ጠንካራ ነበር፡፡ ቢሆንም ግን እረፍት አያውቅም፡፡ ታዲያ ከእለታት ባንዱ ቀን እነዚያን ከባድ የአትክልት ማጠጫ ጣሳዎች እንደያዘ ነበር የልብ በሽታው ተነስቶበት ሊሞት የቻለው" ብላኝ ማለቀስ ጀመረች፡፡ አባቴ እነዚያን የቲማትም እና የባቄላ ተክል ለማጠጣት ቀን በቀን ከባድ የብረት ጣሳዎች በመያዝ ደፋ ቀና ሲል በህሊናዬ እየሳልኩት እኔም ያለማቋረጥ አብሬያት አነባሁ፡፡

የአባቴን የመቃብር ቦታ ከማየቴ በፊት  ከዚህ በፊት አባቴ አዘውትሮ ከሚሄድባቸው መንገዶች መሀከል አንዱ ጋር ይዛኝ እንድትሄድ ታንቴን ስለጠየቋት እኔና እሷ ብቻ ተያይዘን ከቤት ወጣን፡፡ ከደቂቃዎች በኋላም አባቴ ብቻውን መሆን ሲፈልግና ራሱን ዘና ለማድረግ ሲፈልግ አዘውትሮ ከሚሄድባቸው መንገዶች በአንዱ ላይ በቀስታ በመራመድ ታንቴ ስለአለፈው ጊዜ እያወራችልኝ ነበር፤ መንገዱ ታንቴ ጁ ላይ ብዙ ትዝታዎችን ሳይፈጥርባት አልቀረም፤ ምክንያቱም በእያንዳንዱ ወሬአችን መሀል በመንገዱ ዳር እና ዳር የሚሰሩትን የተለያዩ የንግድ ቤቶች ባየች ቁጥር ወሬአችንን አቋርጣ "ይሄ እኮ አባትህ አዘውትሮ ቡና የሚጠጣበት ቤት ነው፡፡ ይሄ ደግሞ ትንሽ ምግብ መቀማመስ ሲፈልግ የሚገባበት ቤት ነው" ትለኝ ነበር፡፡ አዎ በእርግጥ አልፈርድባትም ሰውን ወዶ እንደመለየት ከባድ ነገር የለም!!

በቀጣዩ ቀንም ወደ አርዲቼ ሄጄ በአባቴ መቃብር ላይ ተደፍቼ አነባው፤ ለዘመናት በአይኖቼ ለማየት የናፈቅሁትን አባቴን ከመሬት በታች ተኝቶ በማግኘቴ የምሬት እንባ በመቃብሮቹ ላይ አፈሰስኩ. . .እኔን ናፍቆ የቆዘመባቸውን ቀናቶች እያሰብኩ ተንሰቀሰኩ፡፡

* * * * * * * * *

ለትንሽ ቀን ከእነታንቴ ጋር ከቆየሁ በኃላ ወደ ሞንትማርትሪ መሄድ ስለፈኩ ሁሉንም ተሰናብቼ ጉዞዬን ወደ እዛው አደረኩ፡፡ ከጥቂት ሰዓታት ጉዞ በኋላም የሞንትማርትሪ ምድርን በእግሬ ለመርገጥ ቻልኩ፡፡

ሞንትማርትሪ!! ወደ ወህኒ የተላኩባት ምድር! እኔ ከማውቃት ሞንትማርትሪ በብዙ መልኩ ብትቀየርም እንደ 'ፒጋሌ' አይነት መናፈሻ ቦታ፣ ዝነኛው 'ፓይሮት' ካፌ፣ በግራና በቀኝ የተሰሩትን የሚያማምሩ አጫጭር ፎቆችን

እያሳየ የሚያሳልፈው የ 'ኢ.ሲ. ዴስ ቤክስ' መተላለፊያ መንገድ፣ እነዚያ በየመንገዱ ዳርና ዳር ፊታቸውን ነጭ ቀለም ተቀብተው ሰውን በማሳቅ ገንዘብ ለማግኘት የሚሞክሩትን ተዋናዮች፣ ጨለም ባለው በየህንፃው ጥግጥግ ስር ቆመው አንዱ መጥቶ እስኪወስዳቸው የሚጠብቁትን ሴተኛ አዳሪዎችን ለሚያውቅ የቱንም ያህል ቆይቶ ቢመጣ በእርግጥ ሞንትማርትሪን በፍፁም ሊረሳት አይቻለውም!! አንዱ ሆቴል ገብቼ ማደሪያ ከተከራየሁ በኋላ እቃዎቼን እዛው አስቀምጬ የትውልድ ሀገሬን በደንብ ለመቃኘት ከክፍሌ ወጣሁ።

ሞንትማርትሪ ተመልሼ የመጣሁት ከሠላሳ ሰባት ዓመት በኋላ ስለሆነ ማንም እኔን ለማወቅ የሚጥር ሰው እንደሌለ እርግጠኛ ነበርኩ፤ ለነገሩ ማነው የስልሳ ዓመት አዛውትን ዞር ብሎ የሚያይ? ሌላው በጣም የገረመኝ ነገር ቢኖር የድሮውን ትዝታዬን ለማስታወስ ከረዱኝ ከጥቂት ከኮርሲካ እና ከማርሴል ከመጡ የፈረንሳይ ሰዎች በስተቀር በዚህ ሰዓት ከተማዋ የተሞላችው በፖሊሶች፣ በጥቁሮች፣ በአረቦች እና ከተለያየዩ ሀገር በመጡ ሰዎች መሆኑ ነው። ጭራሽ የማላውቀው አለም ሆኖብኛል!

እኔ እስከማውቀው ድረስ ሞንትማንትሪ ላይ ደራሲ፣ ተዋናይ ወይም ደግሞ ሰዓሊ ካልሆነ በስተቀር ማንም ቢሆን ፀጉሩን አያሳድግም ነበር፤ አሁን ግን የማየው ኩታራ ወጣት ሁሉ ፀጉሩን አንዠርግጎ በማየቴ በጣም ተደንቄያለሁ። ለነገሩ ጊዜ ሲቀየር ትውልድም አብሮ ይቀየራል፤ ቢሆንም ግን ለእኔ እዚች ከተማ ላይ የማላውቀው ባህል ስለሆነብኝ ግርምትን ፈጥሮብኛል።

ሌሊቱን በሙሉ ከአንዱ መጠጥ ቤት ወደአንዱ እየሄድኩ እራሴን በማዝናናት አሳለፍኩት። በመሃል አንዱ መጠጥ ቤት ያገኘሁት ሰውዬ ጋር ጨዋታ ቢጤ ስለጀመርን ስለ ሞንትማንትሪ ትንሽ እንዲያወጋኝ ጥያቄ ሰነዘርኩ ።

"እኔ የምልህ ከ 1930 ጀምሮ ሞንትማርትሪ የድሮ ገጿ ላይ ነች ብለህ ታስባለህ "ብዬ ጠየኩት

"ጌታዬ እኔ እንግዲህ እዚህ የመጣሁት የአስር አመት ልጅ እያለሁ ነው፤ ከዛን ለአርባ ዓመታት እዚሁ ኖሬያለሁ፤ ታዲያ እስካሁን ድረስ የሞንትማርትሪ ገፅታ የሆኑት የፒጋሊ የመናፈሻ ቦታ፣ የብላንቺ ቦታ፣ የክሊንቺ ቦታዎች እና በውስጣቸው የሚያልፉት መንገዶች በሙሉ ድሮ እንደማውቃቸው ምንም የተቀየረ ነገር የላቸውም። ሳስበው ከእዚህ በኋላ እራሱ የሚቀየሩ አይመስለኝም" አለኝ

በእርግጥ ሞንትማርትሪን ውስጥ ለብዙ ዓመት ለኖረ ሰው ምንም የተቀየረ ነገር ያለ ላይመስለው ይችላል፤ ለእንደኔ ከሰላሣ ሰባት ዓመት በኃላ ዳግም ለመጣ ሰው ግን ብዙ ለውጦች ሊያይ እደሚችል ግልፅ ነው።

በዛው ምሽት ከመሸታ ቤት ወጥቼ በመጋቢት ሀያ አምስት 1930 ዓ.ም ሮላንድ ሌፒቲት የተባለውን ሰው ገለሃል ተብዬ ባልፈፀምኩት ወንጀል ለአስራአራት ዓመታት ለመታሰሬ ምክንያት ወደሆነው የግድያ ወንጀል ወደተፈፀመበት ቦታ ቀስ ብዬ እየተራመድኩ ማዝገም ጀመርኩ። ይህ ቦታ ህይወቴን ምስቅልቅሉን ያወጣው ቦታ ነው!! ብርሀን እየናፈቅሁ ጨለማን እንዲወርሰኝ ያደረገኝ ቦታ !! ዛሬ ግን በነፃነት ነው ወደ ቦታው የምንዘው፤ ምክንያቱም ያ ወጣቱ ፓፒ ዛሬ የለም፤ አሁን ወደ እዛ ቦታ የምሄደው ለመማቀቅ ሳይሆን ለጉብኝት ነው። ያ ሁሉ እንግልት እና ስቃይ ሊደርስብኝ የቻለው 'ሮላንድ ሌፒቴት' የተባለውን ሰው ገድለሀል ተብዬ ነው፤ ግን አልገደልኩትም!!

ሮላንድ ላይ የተተኮሰበት እዛው ሞንትማርትሪ ውስጥ በሚገኘው ታዋቂው የ 'ቦሊቫርድ ዲ ክሊቺ' መሸታ ቤት ነው። ዛሬ ላይም ከሰላሳ ሰባት አመት በኂላ ቦታው ላይ ስደርስ ሮናልድ ላይ እኔ ጥይት ላለመተኮሴ አንደኛ ምስክር የሆነው በመንገዱ ዳር ላይ ለህዝብ ማረፊያ ተብሎ የተሰራውን አግዳሚ ወንበር ከቀለሙ መቀየር ውጪ እዛው እንዳለ ነበር ያገኘሁት፤ እሱ ብቻ ሳይሆን ከአግዳሚው ወንበር አጠገብ ያለው የመንገድ መብራቱ እና በአካባቢው ያሉት ሌሎች ቡና ቤቶች እኔ ሮላንድን እንዳልገደልኩት ምስክር ናቸው። ታዲያ ለምንድነው ዝም ያሉት? ለነገሩ ግዑዝ አካል መች ተናግሮ ያውቃል፤ ቢሆንም ግን የእኔ ሁነኛ ምስክሮች እነሱ ነበሩ!

እዛው አግዳሚ ወንበር ላይ ቁጭ እንዳልኩ ስለተከሰስኩበት ወንጀል ማሰብ ጀመርኩ፤ ነገሩ እንዲህ ነው። በቀን መጋቢት ሀያ አምስት ወይም ሀያ ስድስት ላይ አሁን ከተቀመጥኩበት አግዳሚ ወንበር በተወሰነ ሜትር ያክል እርቆ ከሚገኘው መጠጥ ቤት አንድ ማንነቱን በውል ያላወቁት ሰው ወደ መጠጥ ቤቱ ገብቶ

"ኒኒ ተብላ የምትጠራዋ ሴት ማነች ?" ብሎ አንዱን አስተናጋጅ ይጠይቀዋል

"አቤት እኔ ነኝ" አለች አንድ ሴተኛ አዳሪ የምትመስል ሴት ወዲያው ስሟ ሲጠራ ስለሰማች

"አባወራሽ ሆዱ ላይ በጥይት ተመቷል ለመሞት እያጣረ ነው። ውጪ ታክሲ ውስጥ ታገኝዋለሽ" አላት

ወዲያው ኒኒ ከሴት ጓደኛዋ ጋር ሆነው በመሯሯጥ ወደ ውጪ ወጥተው ታክሲውን ሄደው ሲመለከቱ ሮላንድ የኋላ መቀመጫ ላይ ተቀምጦ ያገኙታል። ወዲያው ኒኒ ዜናውን መጀመሪያ ወደነገራት ሰውዬ ዞራ "ማነው መጀመሪያ ለእኔ እንዲነገረኝ ያደረገው?" ብላ ትጠይቀዋለች

"እሱን መናገር አልችልም" ብሏት ከአካባቢው በፍጥነት ይሰወራል

ወዲያውም ወደ ታክሲው ሹፌር ዞራ "ቶሎ ወደ ላሪቦይሳሪ ሆስፒታል ውሰደን" ብላ ትጮሀለች

ታዲያ ይህ ራሺያዊ ታክሲ ነጂ ጭኖት የመጣው ሰው ጉዳት የደረሰበት መሆኑን ያወቀው የዛን ሰዓት ነበር፤ እስከዛ ድረስ ግን ምንም የተፈጠረ ነገር ያለ አልመሰለውም ነበር።ወደተባለው ሆስፒታል ሮላንድንና ሴቶቹን ይዞ ከሄደ በኋላም ወዲያው ነበር ለፖሊስ ቃሉን የሰጠው። ለፖሊስ በሰጠው ቃል መሰረትም እነኒኒ ከሚገኙበት በተወሰኑ ርቀቶች ላይ ከሚገኘው ቦሊቫርድ ዲ ክሊቺ ከተባለው መሸታ ቤት አንዱ ሮላንድን እንደመደገፍ አድርጎ ይዞት ወደ ታክሲው በመምጣት እንዲገባ ካደረገው በኃላ እነ ኒኒ ወዳሉበት መጠጥ ቤት እንዲነዳ ነግሮት እሱ በፍጥነት እየተራመደ ከመኪናው ኋላ እንደተከተለውና። ከዛም እነ ኒኒ ወዳሉበት ቤት ገብቶ ኒኒን እና ጓደኛዋን ይዟቸው ከወጣ በኃላ ከአካባቢው እንደተሰወረ ለፖሊሶቹ ያስረዳል።

ፖሊሶቹም የዚህ ራሺያዊ ታክሲ ነጂ አንዲትም ቃል ሳትቀር ደብተራቸው ላይ አስፍረውት ነበር፤ እሱ ብቻ ሳይሆን ኒኒም ሮላንድ እሷ በምትሰራበት የመሸታ ቤት ውስጥ ከአንድ ከማታውቀው ሰው ጋር ካርታ ከተጫወተ በኋላ ከሌላ ከማታውቀው ሰው ጋር ደግሞ ዳይስ ሲጫወትና ሲጠጣ ማምሸቱን ተናግራለች፤ ጨዋታውን ካቆመ በኋላም ለትንሽ ጊዜ በቤቱ ውስጥ ሲዝናና እንደነበር እና ከዛ አብሮት ካርታ ሲጫወት የነበር ሰውዬ ቤቱን ለቆ ከወጣ ከትንሽ ደቂቃዎች በኋላ እሱም እንደወጣ ቃሉዋን ሰጥታለች። እንግዲህ ከሷ ቃል እንደምንረዳው ሮናልድ ከቤቱ ሲወጣ ማንም እንዳልተከተለውና እደውም እነዚያ የማታውቀቻው ሰዎች ከወጡ በኋላ ከመሸታ ቤቱ እንደወጣ ነው።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላም የግድያ ወንጀልን የሚያጣሩ ጂራርዲን እና ግሪማልዲ የተባሉ ሁለት ልዩ የፖሊስ ሀይሎች ወደ ላሪቦይሳሪ ሆስፒታል መጥተው ለመሞት በማጣጣር ላይ ያለውን ሮላንድን እናቱ ባለችበት ጥያቄ እየጠየቁት ነበር። እዛ ያሉት ነርሶች የሮላንድን ሁኔታ አይተው እደማይተርፍ እርግጠኞች ነበሩ።

ከፖሊሶቹ አንዱ ሮናልድ ወደተኛበት አልጋ እየተጠጋ "እዚህ እንግዲህ ከእናትህ ውጪ እኛ ሁለት ፖሊሶች አለን... ስለዚህ ማን እንደተኮሰብህ ንገረን" ይለዋል

እሱም በጣር ድምፅ "ፓፒሎን ሮጀር ነው!" ብሎ ይመልሳል

"የተናገርከው ነገር እውነት ለመሆኑ ትምላለህ?" ብሎ መልሶ ይጠይቀዋል

"አዎ የተናገርኩት እውነቱን ነው" ይላል ሌፒቴት

እንግዲህ በመጋቢት ሃያ አምስት 1930 የተፈጠረው ይህ ነው። ሮናልድ ሌፒቲትን የገደለው 'ፓፒሎን ሮጀር' ነው! ይህ ሰው ታድያ እኔ አይደለሁም! ሮናልድ የሚተዳደረው የአሳማ ስጋ በመሸጥ ሲሆን ከእሱ በተጨማሪ ደግሞ ባለቤቱ ኒኒ በዝሙት ስራ የምታመጣው ገንዘብ ደግሞ እንደሌላ የገንዘብ ማግኛ ምንጩ ይጠቀምባት ነበር። የሚኖሩትም በኢሲሲ ዴስ ቤክስ ጎዳና ላይ ካሉት ቤቶች በአንዱ ውስጥ ነው። ታዲያ በመጨረሻው የጣር ሰዓት ላይ ሆኖ የገዳዩን ሙሉ ስም የጠራበት ምክንያት ሞንትማርትሪ ውስጥ ብዙ ፓፒሎኖችን ስለሚያውቅ ምናልባት ሌላ ፓፒልንን እንዳያስሩ በሚል ስጋት ነበር የተኮሰብኝ ፓፒሎን ሮጀር ነው ያለው

እኔም እያንዳንዱ ጠበቃዬ የነገረኝን ነገር በአዕምሮዬ አትሜ ለፍርድ እስከቀርብ ድረስ ሸንጤን ገትሬ ነበር የተከራከርኩት፤ የ ሮናልድም ሆነ የባለቤቱ ኒኒ ቃል እንደሚያስረዳው ከሆን ከሁለቱም አንደበት የእኔን ስም የጠራ እንደሌለ ነው

በዚህ መሀል ሮናልድ በተተኮሰበት በዛው ምሽት ላይ አራት ሰዎች ሁኔታውን ለማጣራት ወደ ላሪቦይሳሪ ሆስፒታል ይመጣሉ፤ ይህም ሁኔታ የፖሊሶች ጆሮ ስለደረሰ ወዲያው ወደ ሆስፒታሉ ገብተው እነዚያን ሮናልድን ለመጠየቅ የመጡትን ሰዎች አንዳንድ ጥያቄ መጠየቅ ስለፈለጉ አራቱንም ወደ ፖሊስ ጣቢያ ይዘዋቸው ይሄዳሉ. . .ስማቸውም አንደኛ ጆርጅ ጎልድስቲን፣ ሁለተኛው ሮጀር ዶርም፣ ሦስተኛው ሮጀር ጆርማር፣ አራተኛው ደግሞ ኢምሊ ኬፐ ይባሉ ነበር። ወንጀሉ የተከሰተ እለት በመጀመሪያ ለፖሊሶቹ የሰጡት ቃል እኔ ለፍርድ በቀረብኩበት ሰዓት አልተነገረም ነበር። ጎልድስቲን እንዳለው ከሆኑ ሰዎች ሌፒቴት የተባለ ሰው ባልታወቀ ሰው በጥይት መመታቱን ሲያውሩ ስለሰማ ምናልባት የራሱ ጓደኛ ሮናልድ ሌፒቴት ሊሆን ይችላል በሚል ወደላሪቦይሳሪ ሆስፒታል ሁሉንም ነገር ለማረጋገጥ በመምጣት ላይ እንዳለ ሌላኛውን ጓደኛውን ሮጀር ዶርምን ስላገኘው አብሮት ወደ ሆስፒታሉ እንዲሄድ ከጠየቀው በኋላ ወደ ሆስፒታሉ ገቡ እንደጀመሩ እና ቀሪዎቹን

ሁለቱን ጓደኞቻቸው ደግሞ እነ ጎልድስቲን እየተጣደፉ ሲሄዱ ስላዩ ብቻ ምናልባት የተፈጠረ ችግር ይኖራል በሚል ሀሳብ ተከተሏቸው እንጂ ስለሁኔታው አንድም የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ነበር፡፡ ይሄንንም ጎልድስቲን እንዴት ወደሆስፒታሉ አራት ሆነው ሊመጡ እንደቻሉ ለፖሊሶቹ አስረዳ፤ ፖሊሶቹ ለጎልድስቲን የሚያቀርቡትን ጥያቄ አቅጣጫውን ቀየሩት

"ፓፒለንን ታውቀዋለህ?"

"በደንብ አውቀዋለሁ ለማለት ባልደፍርም ከሮናልድ ጋር እንደሚተዋወቁ ግን አውቃለሁ፡፡ እኔ ልነግራቹ የምችለው ነገር ቢኖር ይህን ብቻ ነው፡፡ ከዛ በዘለለ የማውቀው ነገር የለም"

ሁለተኛውንም ሰው ፖሊሶቹ በጥያቄ ማጣደፉን ተያይዘውታል "ሌፒቴቲን ታውቀዋለህ?"

"በእርግጥ ለፒቴቲን በስምም ሆነ በአካል አላውቀውም... ጎልዲስተን እንሂድ ሲለኝ ነው የመጣሁት"

"ሞንትማርትሪ ውስጥ አምስት ወይም ስድስት የሚሆኑ ሰዎች ፓፒለን ተብለው እንደሚጠሩ ይታወቃል፡፡ ከእነሱ ውስጥስ ፓፒለን ሮጀር የሚባለውን ሰው ታውቀዋለህ?" የጥያቄ መዓት ነበር የሚያወርዱበት

"አንተ እንዳልከው አምስት ወይም ስድስት ፓፒለኖች እዚህ ከተማ ወስጥ እንዳሉ አላውቅም. . .እኔ የማውቀው ሁሌ በሞንትማርትሪ ጎዳናዎች ላይ የሚያንዣብብ ፓፒለን የሚባል ሰው መኖሩን ብቻ ነው፡፡ በሰዎች ዘንድ በጣም የታወቀ ሲሆን እነሱ እንደሚሉት ከሆን አደገኛ ሰው መሆኑን ነው፡፡ እኔም ከእይታ ውጪ ሌላ ስለሱ የማውቀው ነገር አለመኖሩን ስነግራችሁ እያዘንኩ ነው" አለ ሁለተኛው ሰው

ቀጥሎ ሦስተኛው ሰው ጀርማር መጠየቅ ጀመረ፤ አስቀድሞ ጎልድስቲን እንደገለፀው ጀርማር ወደሆስፒታሉ ሊመጣ የቻለው ጎልድስቲን እና ዶርም እየተጣደፉ ሲሄዱ ስላያቸው እና ጓደኞቹ ስለሆኑ ችግሩን አብሮ ለመጋፈጥ በማሰብ ብቻ እንደተከተላቸው አስረዳ

ከፖሊሶቹ አንዱ "ሌፒሌቲን ታውቀዋለህ? ፓፒለን ሮጀርንስ?" ብሎ አከታትሎ ጠየቀው

"በፒ.ጋሊ. መናፈሻዎች አካባቢ የማይጠፋ አንድ ፓፒለን የሚባል ሰው አውቃለሁ። ለመጨረሻ ጊዜም ያየሁት ከሦስት ወራቶች በፊት ነው። ከዛ ውጪ ሮናልድ ስለምትሉት ሰው ምንም የማውቀው ነገር የለም... ጭራሽ አይቼው እንኳን አላውቅም" አለ

አራተኛውም ሰውም ተመሳሳይ መልስ ነበር የመለሰው . . . ሴፒቴቲን አያውቀውም ፓፒለን የሚባል ሰው ግን ያውቃል።ነገሩ ሳይበለሻሽ በፊትም እናትየዋም ብትሆን የልጇ ገዳይ 'ፓፒለን ሮጆር' ነው ብላ ቃሏን መስጠቷ አውቃለሁ።

ባጭሩ ሮናልድ ከእነዚያ ካልታወቁ ሰዎች ጋር ምሽቱን ካርታ እና ዳይስ ሲጫወት ካመሸ በኃላ ከመሸታ ቤቱ መውጣቱ ሁሉም የተስማማበት ጉዳይ ነው። ግራ የሚያጋባው ነገር አብረውት የተጫወቱትን ሰዎች ሮናልድም ሆነ በቤቱ የነበሩት ሌሎች ሰው እንደማያውቋቸው እና እስካሁንም ድረስ ማንነታቸው አለመታወቁ ነው።

ሌላው ደግሞ ከመሸታ ቤቱ ለመውጣት እሱ የመጨረሻው እንደሆነና ማንም የተከተለው ሰው እንዳልነበር የገዛ ባለቤቱ ተናገራለች። ከቤቱ ከወጣ ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላም በጥይት ተመትቶ ወደ ሆስፒታል ሊገባ ችሏል፤ ለመሞት በጣር ላይ እንዳለ ደግሞ የተኮሰበት 'ፓፒለን ሮጆር' መሆኑን ተናግሯል፤ ሌላው ወሳኝ እማኝ ሊሆን ይችል የነበረው ለኒኒ ባለቤቷ በጥይት መመታቱን የነገራት ሰው ነበር። ይህ ሰው ሮላንድ በጥይት ከተመታ በኋላ ደግፎ ወዲያው ታክሲ ውስጥ እንዲገባ ያደረገ ግለሰብ ነው። ታዲያ እስካሁን ድረስ ስለዚህ ምስክር የተሰማም የታየም ነገር አለመኖሩ ሌላው ትንግርት የሚፈጥር ነገር ነው። ይምስለኛል እሱም በዝርፊያ ስራ የሚሰራ ስለሆነ ፖሊሶች እንዲያዩት አልፈለገም ማለት ነው። ስለዚህ እሱ ያሰበው ሁሉ እንዳቀደው ተሳክቶለት ከእዚህ የግድያ ወንጀል እራሱን አንፅቷል።

እንግዲህ ከእነዚህ መረጃዎች በመነሳት ስለ ፓፒለን የሚታወቀው ነገር ቢኖር ሙሉ ስሙ ፓፒለን ሮጆር መሆኑና አደገኛ መሆኑ ብቻ ነው። ታዲያ እኔ ገና በሃያ አራት አመቴ አደገኛ ነበርኩ? ወይም ሰዉ እንደሚያወራው አሸባሪ ነበርኩ? አይደለሁም ነገር ግን ወደዚያ እያመራሁ ነበር። በእርግጥ ወጣት እያለሁ ምድር ላይ ምንም ነገር የሚያስፈራ ነገር ያለ አይመስለኝም ነበር፤ ገና በዛ እድሜዬ በተለያዩ ትልልቅ የዝርፊያ ስራዎች ላይ ዋና ተሳታፊ እኔ ነበርኩ። ፖሊሶችም ምንም እንኳን እኔን እስር ቤት ለመወርወር የሚያስችል መረጃ ባያገኙም ብዙ ጊዜ ግን በ 'ሦላሳ ስድስት ኩዊ ደስ ኦርፌብረስ' የእስረኞች ማቆያ ውስጥ አስገብተው አሽተውኛል! በእርግጥ ትንሽ ጊዜ ባገኝ ኖሮ የአንዱ ትልቅ ወንበዴ ቡድን መሪ መሆኔ አይቀርም ነበር፤ ነገር ግን

በዚያው አልቀጠልኩም ሁሉንም ነገር ትቼ የሀገሪቷን የጦር ሰራዊት ተቀላቅዬ ለሁለት አመት ያክል አገልግያለሁ፡፡ ያም ቢሆን በፖሊሶቹ ዘንድ አሁንም አንዳንድ ትልልቅ የዝርፊያ ስራዎች የሚከናወኑት በእኔ አማካኝነት ስለሚመስላቸው ሁል ጊዜ እዛ 'ሰላሳ ስድስት' የእስረኞች ማረፊያ ውስጥ በማስገባት ያሰቃዩኝ ነበር፤ እኔም በፖሊሶቹ በጣም ተማርሬ ስለነበር በዛ ላይ ወጣትነቴ ስለሚፈታተነኝ ሁልጊዜ ይዘውኝ ሲሄዱ ከመስደብና ከመዝለፍ አልቆጠብም ነበር፡፡ እንደውም አንድ ቀን የእነሱን ቦታ እንደምተካና እነሱንም በእኔ ቁጥጥር ስር እንደማደርጋቸው እዝትባቸው ነበር፡፡ ታዲያ ዛቻዬ በፖሊሶቹ ዘንድ ይህን ያህል ፍርሃት ይፈጥራል ብዬ ኣሰብኩም ነበር፤ አልፎ ተርፎ "ይሄ ፓፒለን ክንፎቹን ለመብረር ከመጠቀሙ በፊት ማሰወገድ መቻል አለብን፡፡ አለበለዚያ መብረር ከጀመረ ማንም አይዘውም" እንደሚሉ ሁላ ከሰዎች አንደበት ሰምቻለሁ፡፡

ነገር ግን ይህን ሲዶልቱብኝ ገና የሃያ አራት አመት ወጣት ነበርኩ፡፡ አዎ በእርግጥ ምናልባት ስጋት ፈጥሬ ሊሆን ይችላል፤ ቢሆንም ገና ለገና ፖሊሶቹን ተሳደብኩና ምናልባት ይሄ ልጅ አንድ ቀን በጣም አደገኛ ሰው ሊሆን ይችላል በሚል ሰበብ ከዚህች ምድር እንድጠፋ ማድረጉ ተገቢ አይመስለኝም!

ሁሉ ነገር እንዲበላሽ ያደረገው ይሄ የግድያ ወንጀል ጉዳይ በእነዚያ አስቀያሚ ፖሊሶች እጅ ውስጥ መግባቱ ነው፡፡ መጀመሪያ ያደረጉት ነገር በከተማዋ የሚገኙትን ፓፒለን በሚል ስም የሚጠሩ ሰዎችን ማጣራት ነው፡፡ ትንሹ ፓፒለን፣ ፓፒለን ፑሲኒ፣ ፓፒለን ትሮምፔ ላ ሞርት፣ ፓፒለን ሮጀር የመሳሰሉትን ሰዎች ማጣራት ጀምሩ፡፡ እኔን በተመለከተ አንዳንዴ ውዝግብን ለማስቀረት 'አውራው ፓፒለን' ተብዬ ከመጠራት ውጪ ሁሌም ቢሆን የምጠራው 'ፓፒለን' በሚለው መጠሪያ ስሜ ነው፤ ታዲያ ይሄን ነገር እንደሰማሁ ወዲያው ነበር አካባቢውን ጥዬ የሄድኩት፡፡ ምናልባት ወንጀሉን እስካልፈፀምክ ድረስ ለምን ትሸሻለህ ልትሉኝ ትችላችሁ፡፡ ነገር ግን ነገሩ አስኪጣራ ድረስ በሚል በ'ሰላሳ ስድስት' የእስረኞች ማቆያ ወስጥ ምን ሊያደርሱብኝ እንደሚችሉ የማውቀው እኔ ስለሆንኩ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ለእኔ! ማሰቃየት የፈለጉትን ሰው ፀጉሩን ጨምድደው ትንፋሽ እስኪያጥረው ድረስ ውሃ ውስጥ ጭንቅላቱን መንከር ልማዳቸው ነው በዚህ መሀል እንኳን ትሙት ትዳን የምታውቀው ነገር የለም፤ ብልትህን ደም ማስተላለፍ አቅቶት እስኪጠቁር ድረስ በገመድ አስረውት ልክ እደተገረዘ ሰው እንድትራመድ ማድረጋቸውስ፤ ጥፍር በፒንሳ መንቀሉስ፤ ድርቅ ባለ ጎማ ሆድህን ከመገረፍህ የተነሳ ከሳምባህ ደም የተፋህበት ጊዜስ… ያንንማ መርሳት የለብኝም!! ምንም እንኳን የፈፀምኩት ወንጀል ባይኖርም ፖሊሶቹ ከእኔ ጋር ባላቸው ቅራኔ የተነሳ የሚያደርጉትን ላያውቁ ይችላሉና ከፓሪስ ብዙም ሳልርቅ የሆነ ቦታ

ከተሸሸግሁ በኋላ ተጠርጣሪውን 'ፓፒለን ሮጀርን' ሲይዙት የዛኔ ረጋ ብዬ ወደ ስፈራ እመለሳለሁ የሚል ሀሳብ ላይ ደርሼ ከአካባቢው መራቅን መረጥኩት። ችግሩ ይህን 'ፓፒለን ሮጀር' የሚባለውን ሰው ሊይዙት አለመቻላቸው ነው።

ፓፒለን ሮጀር አለመያዙ ለእነዚያ ከይሲ ፖሊሶች አንድ አሪፍ ሀሳብ ይዞላቸው መጣ። ለምን 'ሮጀር' የሚለውን ስም አንስተን ፓፒለን የሚለውን ስም ብቻ አንወስድም የሚል ሰይጣናዊ አስተሳሰብ በአእምሮዋቸው ተቀረፀ፤ ይህን ካደረጉ የእኔ ስም ስለሚሆንላቸው እኔን በቁጥጥራቸው ስር ለማዋል ይቀላቸዋል ማለት ነው። ለዛም ነው በሚያዝያ አስር እዛው የተሸሸኩበት ቦታ ቁርሴን በመብላት ላይ እንዳለሁ ሁለት ፖሊሶች ከተፍ ያሉብኝ፤ ከዚያም የጀመርኩትን ቁርስ እንኳን እንድጨርስ ፋታ ሳይሰጡኝ አንጠልጥለው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ይዘውኝ ይሄዳሉ።

በእርግጥ እኔን ለማሰር ወሳኝ መረጃ እስካላመጡ ድረስ እንዲህ በቀላሉ እኔን ወህኒ ማውረድ እንደማይችሉ ባውቅም በዛው ልክም ይህንን እኔን ለማሰር ያገኙትን እድል ፖሊሶቹም ቢሆን ማለፍ እንደማይፈልጉ ግልፅ ነው። በዛ ላይ የእኔ ጠበቃና የአቃቤ ህጉ በፈጠሩት ጠብ ምክንያት ነገሩ ሊካረር ችሏል። ታዲያ ይህ እርጉም አቃቤህግ ባደረበት እልህ ምክንያት እኔን እስር ቤት አስገብቶ በጠበቃዬ ላይ ሃይሉን ማሳየት ስለፈለገ አንደኛ ምስክር የነበረውን ጎልድስቲንን እንዴት እንዳሳመነው ማወቅ ቢሳነኝም መጀመሪያ የሰጠውን ቃል እንዲቀይር አድርጎት ወንጀሉን እኔ ላይ ጠምጥመውታል።

በመጋቢት ሀያ አምስት ሮናልድ ከመገደሉ በፊት እኔን ከሁለት ከማያውቃቸው ግለሰቦች ጋር በመሆን እንዳገኘኝና፤ ሌፒቴት የት እንደሚገኝ እንደጠየኩት፣ እሱም መጠጥ ቤቱ ውስጥ መሆኑን ለእኔ ከነገረኝ በኋላ ወዲያው ወደ ሌፒቴት ወደነበረበት መጠጥ ቤት ሄዶ የሚፈልገው ሰው እንዳለ ገልፆ ለሁሉም ነገር እንዲጠነቀቅ በመንገር ላይ እያለ ከእኔ ጋር ከነበሩት ሰዎች መካከል አንዱ ወደ መጠጥ ቤቱ ገብቶ ሌፒቴትን ለብቻው ፓፒለን ማናገር እንደሚፈልግ ስለነገረው ጎልድስቲንን እዛው ትቶ እኔን ለማናገር ወደ ውጪ መውጣቱን፣ ከዛ በኋላ የተፈጠረውን እደማያውቅና በፒጋሊ መናፈሻ እራሱን በማዝናናት ላይ እያለ እኔ ወደ እሱ ሄጄ ሌፒቴቴ ላይ መተኮሴን እና ወደ ሆስፒታል ሄዶ አሁን ሌፒቴቴ ያለበትን ደረጃ እንዳጣራለትና ሌላ ነገር ከለፈለፈ እንደምጨርሰው ማስጠንቀቂያ ጭምር እንድሰጥለት እንዳዘዘኩት አድርጎ፣ በመጀመሪያ የሰጠውን ቃል በዚህ መልክ ቀይሮት እኔን ወደ ማልወጣው አዘቅት ውስጥ ከተተኝ፤ ያኔ ችግሩ በሙሉ እኔ ላይ መጫን ተጀመረ።

እንግዲህ ከዚህ በፊት አስቸጋሪ ፀባይ እንዳለኝና ብዙ ጊዜም ለጥያቄ ወደ ፖሊስ ጣቢያ እስከሄድኩ ድረስ ፍርድ ቤቱም ቢሆን ስለጉዳዩ ከማጣራት

ይልቅ እርግጠኛ ሆነው "እንዴት ነው ወንጀሉን የፈፀምከው" ለማለት ቃጥቷቸዋል፡፡ ጎልዲስቲን ይህንን ውሸት የሞላበትን የክህደት ቃሉን ከሰጠ በኋላ እሱ ላይ ሌላ ችግር እንዳይፈጠር በመስጋት ወድያው ነበር ወደ ለንደን የተጓዘው፡፡ ምናልባትም እኮ ከዚህ ጎልዲስቲን ከሚባለው ሰው ጋር ልክ እንደማንኛውም ሞንትማርትሪ ውስጥ እንደማውቀው ሰው ሁሉ ሰላም ተባብለን ሊሆን ይችላል፤ ምናልባትም ቃላቶች ተለዋውጠንም ይሆናል ነገር ግን እንዲህ ተቀራርቦ በጓደኝነት ስሜት ለማውራት የሚያደርስ ቀረቤታ እንደሌለን ማንም የሚመሰክረው ነው፡፡ ታዲያ ምን ቢሰጡት ይሆን እንዲህ ባንድ ጊዜ ሀሳቡን ቀይሮ እኔ ላይ ሊዶልት የቻለው? ባውቀው ደስ ይለኝ ነበር!

የሚገርመው ነገር ጎልድስቲን የሀሰት ምስክርነቱን ባይሰጥ ኖሮ ሌላ እኔን ለማጥመድ የሚያስችል አንዲትም መረጃ እንደማያገኙ አውቅ ነበር፤ ነገር ግን ይሄ ዲቃላና ፖሊሶቹ ባደረጉት ስብጥር ጎልድስቲን የውሸት ቃል እንዲሰጥ ተደርጎ እኔን ለማጥመድ በር ከፈተላቸው፡፡ እንደዛም ቢሆን ግን ከጎልድስተን ቃል ውጪ ሌላ ተጨባጭ መረጃ ስሌላቸው በዛ ላይ ጎልድስቲን የተናገረውንም ቢሆን ፍርድ ቤቱ ሙሉ ለሙሉ ስላላመነው እኔን በቀላሉ ለማሸነፍ እንደማይቻላቸው ግልፅ ነው፡፡ ከዛም በላይ ደግሞ ከሟቹ ጋር ለጠብ የሚያደርስ ምንም አይነት ጓደኝነት እስከሌለን እና እኔም ዝም ብዬ ሰውን የመግደል ጥማት ያለብኝ እብድ እስካልሆንኩ ድረስ አንድ ምንም የማያውቅ ደደብ እንኳን ቢሆንም የእኔ በግድያው ላይ መገኘት ልክ ሾርባ ውስጥ እንደተገኘ ፀጉር እንደሚቆጠር መረዳት አያቅተውም!

ይህን የተረዱት ፖሊሶችም እኔን ለማጥመድ ሌላ ዘዴ መጠቀም እንዳለባቸው ስለገባቸው ሞንትማርትሪ ውስጥ ለአስር አመታት በወንጀል ማጣራት ስራ ውስጥ የቆየ 'ሚዝለር' የሚባል የግድያ ወንጀሎች ማጣራት ላይ ልዩ ብቃት ያለውን ሰው ጉዳዩ ላይ እንዲገባ አደረጉ፡፡

ታዲያ ከጠበቃዎቼ መሀከል 'ሜትሪ ኢፊ' የተባለው ጠበቃዬ ከስራው ውጪ ትርፍ ጊዜውን የሚያሳልፈው የሞንትማርትሪን የተለያዩ ገፅታዎችን በማድነቅ ነው፡፡ ታዲያ በዚህ መሀል ከእነዚያ ፖሊሶች የተላከውን ይህን መከረኛ ሚዝለር የተባለውን ፖሊስ ያገኘዋል፡፡ ጠበቃዬም ሆነ እኔ ስለፖሊሱ የምናወቀው ነገር ባለመኖሩ ጠበቃዬ ፖሊሱን ያዋራው በጓደኝነት መንፈስ ነበር፡፡ ፖሊሱም በመጋቢት ሃያ አምስት የተፈጠረውን ነገር እንደሚያውቅና እኔንም ወግኖ የምስክርነት ቃሉን መስጠት እንደሚፈልግ ለጠበቃዬ ይነግረዋል፡፡ እኛም የመሰለን ምናልባት ይሄ ፖሊስ ለቃሉ የታመነ ወይም ደግሞ ከአቃቤ ህጉ ጋር ጠብ ውስጥ የገባ መሆን አለበት ብለን እኛም ከምስክሮቻችን መሀከል አካተትነው፡፡ በእርግጥ ትልቅ ስህተት ነበር!

እኛም ምስክር በምናቀርብበት ሰዓት ይህን ፖሊስ እንደአንዱ ምስክር አድርገን አቅርበነው ነበር። ነገር ግን በፍርድ ቤቱ ውስጥ ይህ ፖሊስ ይሰጣል ብለን ያላሰብነውን የምስክርነት ቃል ሲሰጥ ስለሰማሁት የትኛው ሰው ሊታመን እንደሚችል ራሴን እየጠየኩ ነበር። እንግዲህ ፖሊሱ የተናገረው ይህንን ነበር

"ለፓፒለን ምስጋና ይግባውና ለእኛ ለፖሊሶች በሚያቀብለን ድብቅ መረጃ መሰረት ብዙ ወንጀሎችን ለመቆጣጠር ችለናል። እኔ እንኳን ብዙ ከግድያ እና ከዘረፋ ጋር የተገናኙ ወንጀሎችን እንዳጣራና በሂደትም ድርጊቱን የፈፀሙትን ወንጀለኞች ከገቡበት ገብቼ መያዝ እንድችል ስላደረገኝ በእኔና በመላው ፖሊስ ስም ላመሰግነው እፈልጋለሁ"አለ

ይህ ወሸታም ፖሊስ የተናገረው ቃል በጭራሽ ያላሰብነውን መዘዝ ይዞብን መጣ። ሌፒቴቲን የገደልከው በድብቅ ለፖሊሶች መረጃ የምታቀብል ጆሮ ጠቢ መሆንህን ለሰው ሁሉ ስለተናገረብህ ነው ወደሚለው ሀሳብ እንዲሄዱ ረዳቸው።ቢሆንም ግን ፍርድ ቤቱ በእኔ ላይ የተነሳው ክስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተወሳሰበና መረጃውም በዛው ልክ እየተቀያየረ ስለመጣ በእኔ ላይ ቶሎ ለመወሰን አልፈለገም ነበር።

እዚህ ጋር ማመን የሚኖርብን ነገር ቢኖር ምንም እንኳን ፖሊሶቹ፣ አቃቤ ህጉ፣ እማኞቹ፣ የፖሊስ ጣብያው አስተዳደር ሁሉም እኔ የተከሰስኩበት ጉዳይ ውሸት እንደሆነ እያወቁ ሆን ብለው የሚያደርጉት ነገር መሆኑን ባውቅም ከእነሱ ውስጥ ልክ እኔ የነበርኩበት ፍርድ ቤት ውስጥ እንዳለው ዳኛ ለእውነት የሚኖሩ ሰዎች እንዳሉ ግን መካድ አንችልም። በዚህም ምክንያት ዳኛው በእነዚህ መረጃ በማይመስሉ ማስረጃዎች ስላልረኩ ተጨማሪ መረጃ እንደሚቀርብ ትዕዛዝ አስተላልፈው ለሌላ ጊዜ ቀጠሮ ሰጡ።

* * * * * * * * *

ሰዓቱ ወደ እኩለ ሌሊት እየተጠጋ ቢሆንም እኔ ግን አሁንም እዛው አግዳሚ ወንበር ላይ እንደተቀመጥኩ የኋሊት ተጉዤ በእስር ላሳለፍኳቸው አስራ አራት አመታት ምክንያት የሆነውን ክስ እያስታወስኩ ነበር. . በብርዱ ምክንያት የተኮማተረውን ሰውነቴን ለማፍታታት ያህል ከተቀመጥኩበት ወንበር ላይ ከተነሳሁ በኋላ ለመንጠራራት ሞከርኩ፤ ቀጥዬም አጥንት ድረስ የሚገባውን ብርድ ለመቀነስ በማሰብ የለበስኩትን ጃኬት ኮሌታ አንገቴን እንዲሸፍን ካደረኩ በኋላ እንዲሁም ጭንቅላቴ ላይ ያደረኩትን ኮፍያዬን ወደ ፊቴ ዝቅ አድርጌ

አስተካክዬ በምናቤ የጀመርኩትን የራሴን የህይወት ድራማ ለመጨረስ ተመልሼ እዛው ወንበር ላይ ቁጭ አልኩ፡፡ ሌላው ደስ የሚለው እንደ እድል ሆኖ አሁን ያለሁበት አካባቢ ላይ ማንም ሰው ካለመኖሩ በላይ ፀጥ ያለና ከእራስ ጋር ለማውራት የሚመችበት ጊዜ መሆኑ ነው፡፡

ፍርድ ቤቱ በቀጠረኝ ቀን መሰረት ሁላችንም በቦታችን ተገኝተናል፡፡ ዳኞቹ፣ አቃቤ ህጉ፣ ጠበቃው፣ ታዛቢዎቹ ሁሉም ቦታ ቦታውን ይዞ ፍጥጫው እስኪጀመር እየተጠባበቁ ነው፡፡ ፖሊሶቹም ሀይላቸውን አጠናክረው እኔን ወህኒ ለመወርወር እንደማያንቀላፉ እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ በዚያን ቀንም ከከሳቾቹ ወገን ምስክር የሚቀርብበት ቀን ነበር፤ በአንደኛ ምስክርነት በእነዚህ ደደብ ፖሊሶች የተመረጠችው የሮናልድ እናት ነበረች ፡፡ ወደ ፍረድ ሸንጎው ገብታም መሀላ ከፈፀመች በኋላ ወደ ተዘጋጀላት መቀመጫ ሄዳ ቁጭ አለች፤ ከፊቷ እደተረዳሁት በሁኔታው ምንም ደስተኛ እንዳልሆነች ሲሆን የምትጠየቀውን ጥያቄም የምትመልሰው በግማሽ ልቦናዋ ነበር፡፡ እናትየዋም የልጅዋ ገዳይ 'ፓፒለን ሮጀር' መሆኑን አጥርታ ብታውቅም አሁን በሰጠችው የእምነት ቃሏ ላይ ግን 'ሮጀር' የሚለውን ቃል አለመጠቀሟን እና ገዳዩ 'ፓፒለን' እደሚባልና ጎልድስቲንም እንደሚያውቀው አክላበት ነበር፡፡ በእርግጥ አልፈርድባትም ይህ ሁሉ ተውኔት በፖሊሶቹ ደራሲነት በሴትየዋ ደግሞ ከዋኝነት እየተካሄደ እንደሆነ ስለገባኝ በውሸቱ ብዙም አልተደነቅሁም፡፡ ቃሏን ከሰጠች በኃላም አቃቤ ህጉ ወደ እኔ በኩራት እየተራመደ በመምጣት እኔ ላይ ተፅዕኖ ለመፍጠር እናትየውን ይቅርታ እንድጠይቃት ነገረኝ... እኔም ወደ እናትየው ዞሬ "ልጅሽን አልገደልኩትምና ይቅርታሽን አልሻም፤ ነገር ግን ከአንቺ ንግግር እንደተረዳሁት ከሆነ የምታደርጊው ነገር ያላመንሽበትን ነገር በመሆኑ ላንቺ በጣም አዝናለሁ! ይሄን ብቻ ነው ማለት የምፈልገው!" አልኳት

የሚገርመው ነገር መጀመሪያ ሮናልድ የተኛበት ሆስፒታል መጥተው የጠየቁት ፖሊሶች እንኳን 'ሮጀር' የሚለውን ስም መስማታቸውን መካዳቸው ነው

ቀጣዩ ምስክር ጎልድስቲን ነበር 'በሰላሳ ስድስት' ጊዜያዊ ማረፊያ ውስጥ እያለ የሰጠውን ቃል የያዘውን የቴፕ ቅጂ ወደ ፍረድ ቤቱ ወጥቶ እንዲሰማ ተደረገ፡፡ ከተናገራቸው ነገሮች ውስጥም ፍረድ ቤቱ እኔን ለመክሰስ ይሆናሉ ብሎ የሚያስባቸውን ነጥቦች ከመመዝገብ አልቦዘነም፡፡

ጠበቃዬ የቴፕ ቅጂው እንደጨረሰ ወደ ጎልድሲቲን በመምጣት "እንግዲህ ደንበኛዬን እንደምታውቀው ብዙ ጊዜ ስትናገር ሰምተናል ነገር ግን መጀመሪያ የሰጠኸው ቃል ስለጉዳዩ ምንም እንደማታውቅ ነበር፡፡ አሁን ግን የተናገርከው ፓፒለንን እንደምታውቀው ከዛም በላይ ወንጀሉ ከመፈፀሙ በፊት

እንዳገኘኸው እና ወንጀሉም ከተፈፀመ በኋላም አግኝተኸው ወደ ሆስፒታል ሄደህ ሮናልድ ያለበትን ሁኔታ እንድታጣራ እንደነገረህ ነው፡፡ ታዲያቱ ሁለቱ ሃሳቦች አይፃረሩም ብለህ ታስባለህ?" ብሎ ድርቅ ያለ ጥያቄ ጠየቀው

ጎልድስቲንም የመጣበትን ላብ እየጠረገ... "አዎ መጀመሪያ ለመናገር ያልፈለኩት ፓፒለን ምን ያህል አደገኛ እንደሆነ ስለማውቅ ምናልባት እኔ ላይ ችግር እንዳይፈጠርብኝ በማሰብ ነው"

ይህን ጊዜ እጄን አውጥቼ ፍርድ ቤቱ ምስክሩን መጠየቅ የምፈልገው ጥያቄ እንዳለ እንዲያውቁልኝ አደረኩ፤ ዳኛውም "ተከሳሽ ምስክርን መጠየቅ የምትፈልገው ጥያቄ አለ" አለኝ

"አዎ" የተከበሩ ዳኛ ካልኩ በኋላ ወደ ጎልድስቲን ዞሬ "ጎልድስቲን ፊትህ አዙርና እኔን እያየህ ንገረኝ... ምንድነው በእኔ ላይ ይሄን ያህል ውሸት እንድታዘንብ ያደረገህ? ምን የሰራኸው ወንጀል ቢኖር ነው እሱን ለማካካስ እኔ ላይ እንዲህ ያለ ውሸት የዘላበድከው? ወይ ደግሞ ምን እንስጥህ ቢሉህ ነው እኔን ወደ እስር ቤት ለመወርወር ቆርጠህ የተነሳኸው?" አልኩት እልህ ባዘለ ቃና

ጎልድስቲንም እኔን ለማይት ቢችልም ሌላ ነገር ለማውራት ግን ድፍረቱን ስላጣ "የተናገርኩት እውነቱን እና የማውቀውን ብቻ ነው" አለ

እኔም እራሴን ወደ ዋና ዳኛው አዙሬ "የተከበሩ ዳኛ በእኔ ላይ የተነሳው ክስ ትርጉም አልባና ያለምክንያት ለመሆኑ በጥሞና እንዲከታተሉልኝ እፈልጋለሁ" ካልኩ በኃላ መልሼ ወደ ጎልድስቲን ዞሬ "ጥሩ እንግዲህ ጎልድስቲን እኔና አንተ ጥሩ ጓደኛሞች መሆናችንን ተናግረሃል፡፡ ፓሪስ ውስጥ ካሉትም ይሁን በመላው ፈረንሳይ ካሉት ሰዎች መሀል እኔና አንተ አንድ ላይ ቆምን ስናወራ ካዩን ሰዎች መሀከል የአንዱን ስም እንኳን ጥራልኝ እስኪ?" አልኩት

"እሺ ብሎ ለመጠየቅ እዚህ ድረስ የሚመጣ ሰው ያለ አይመስለኝም"

"እሺ... እዚህ ፈረንሳይ ውስጥ እኔ እና አንተ ለአንድ ጊዜ እንኳን አብረን ገብተንባቸው ከምናውቅባቸው ቡና ቤቶች ወይም ምግብ ቤት አልያም ደግሞ ሞንትማርትሪ ውስጥ ካሉ መዝናኛ ቦታዎች ውስጥ እስኪ አንዱን ጥቀስ"

"ካንተ ጋር ጠጥቼም በልቼም አላውቅም"

"እሺ. . .ወንጀሉ የተፈፀመበት ምሽት ከሁለት ሰዎች ጋር እንዳየኸኝ ተናግረህ ነበር... እነማን ናቸው?"

"አላውቃቸውም"

"እኔም አላውቃቸውም! አሁን ደግሞ ያለማንገራገር ቶሎ እንድትመልስልኝ የምፈልገው ጥያቄ አለ፡፡ ሮናልድን ከተኮስኩበት በኋላ ሁኔታውን እንዳጣራ ወደ ሆስፒታሉ እንደላክሁ ተናግረሃል ታዲያ መልሱን ለመንገር የት እንደተገናኘን እኮ አልተናገርክም፡፡ ለምን የተገናኘንበትን ቦታ አትነግራቸውም" ምንም አይነት መልስ ሊሰጠኝ አልቻለም

"ኀልድስቲን ተናገር እንጂ ዝም አትበል"

"የት ማግኘት እንዳለብኝ ስላላወቅሁ አልመጣሁም"

ጠበቃዬም አክሎ "ስታስበው እራሱ የሴፒቴቲን ሁኔታ አጣራልኝ ብሎህ የምትገናኙበትን ቦታ ሳይነግርህ የሚሄድ ይምስልሃል... ይህ ጭራሽ ማመን የሚከብድ ነገር ነው" አለ ዳኛውን እየተመለከተ

ዳኛውም ወደ እኔ ዞረው "ሄነሪ ፖሊሶች እንደሚሉት ከሆነ ግን አንተ ሴፒቴቲን ልትገለው የቻልከው የፖሊስ ጆሮ ጠቢ መሆንህ ስላሳበቀብህ ነው ስለሚሉት ነገርስ ምን ትላለህ?"

"የተከበሩ ዳኛ ይህ በፍፁም ሊሆን የማይችል ነገር ነው፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ እኔን ወንጀለኛ ለማስባል የተሴረ ሴራ ለመሆኑ የሚያስረዳ ነው፡፡ እኔ እንኳን በፖሊሶች እጅ ተይዤ ስንት ጊዜ ለጥያቄ እንፈልግሃለን በሚል ወደፖሊስ ጣቢያ ሄጃለሁ፡፡ እንኳን ሌላ ሰው ለማሳሰር ላስብና " አልኩ በዚያ በከዳተኛው መስካሪዬ እየበሸቁ

"ታዲያ እኮ መርማሪ ሚዚለር አንተ ለፖሊሶች እደምትሰልል ተናግሯል፡፡ እስኪ መርማሪ ሚዚለርን ጥሩት" ብለው ለአንዱ ፖሊስ ትዕዛዝ ሰጡ

ወዲያው ሚዚለር ወደ ፍርድ ቤቱ ገብቶ ቃሉን መስጠት ጀመረ "አስቀድሜ እንደተናገርኩት ክቡር ዳኛ ይህ ሰው ብዙ ወንጀለኞችን እንድንይዝ ረድቶኛል. . ሰላይ መሆኑ ደግሞ ሞንትማርትሪ ውስጥ የማያውቅ ያለ አይመስለኝም፡፡ ከዛ ውጪ ግን ከሴፒቴቲ ጋር ያለውን ግንኙነት አላውቅም"

"እሺ ሄነሪ ስለዚህስ ሰው ምን ትላለህ?" አሉ ዳኛው

"መርማሪ ሚዚለርን ለእኔ ምስክር እንዲሆን ለማቅረብ ሃሳቡን ያቀረበው ጠበቃዬ ሲሆን ጠበቃዬ እንደነገረኝ ይህ መርማሪ ወንጀሉ ሲፈፀም በቦታው እንደነበረና እኔንም ወግኖ የምስክርነት ቃሉን እንደሚሰጥ ስለነገረው ነበር፡፡ አሁን ግን እንደተረዳሁት እኔን ለማጥመድ ሆን ብለው ያወጡት እቅድ መሆኑን ነው፡፡ ስለ ግድያው እንደሚያውቅ ጠበቃዬን ካሳመነው በኋላ እኔም ከምስክሮቼ አንዱ እንዲሆን ባቀረበው ሀሳብ ተስማምቼ ነበር፡፡ እኔም ጠበቃዬም የመሰለን ይህ መርማሪ ለእኔ ወግኖ ለመመስከር ያሰበው ለህሊናው የሚኖር ሰው ስለሆነ አልያም ከአቃቤ ህጉ ጋር ፀብ ውስጥ ያለ ሰው መሆን አለበት ብለን ገምተን ነበር፡፡ ነገር ግን የተከበሩ ዳኛ ስለወንጀሉ ምንም የሚያውቀው ነገር እንደሌለ አሁን ተረድቻለው" ካልኩ በኋላ ወደ ዳኛው እየተመለከትኩ "ከተፈቀደልኝ መርማሪ ሚዚለርን መጠየቅ የምፈልገው ጥያቄ ነበር ይፈቀድልኛል?" ብዬ ጠየኩ

ጠበቃዬም ዳኛውን መርማሪ ሚዚለርን ለጊዜው እንዳያወራ የሚያግደውን ስልጣኑን ትቶ ለጥያቄ እንዲተባበረን ጠየቀው

ዳኛውም "ለእውነት እና ለትክክለኛ ፍትህ ሲባል መርማሪ ሚዚለር ለዛሬ ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ እንዲሰጥ ፍረድ ቤቱ ፈቅዷል" አሉ እኔም ፍርድ ቤቱን አመስግኜ የመጀመሪያ ጥያቄዬን ለመርማሪ ሚዚለር አቀረብኩ

"መርማሪ ሚዚለር እስኪ በእኔ ምክንያት ከያዝካቸው ወንጀለኞች መሀከል የአንዳንዶቹን ስም ለፍርድ ቤቱ ግለፅልን"

"እሱን መናገር አልችልም"

"ውሸታም ነህ! መነገር የማትችለው ማንም መጥራት ስለማትችል ነው" አልኩት ትዕግስቴን መቆጣተር አቅቶኝ

"ሄነሪ አነጋገርህን አስተካክል" አሉ ዳኛው

"ክቡር ዳኛ አሁን እየተፋለምኩ ያለሁት ለነፍሴ ብቻ ሳይሆን ለክብሬም ስለሆነ ነው" አልኩ እልሄ ሳይበርድ

ወዲያው ዳኛው የመርማሪው መቆየት አስፈላጊ መስሎ ስላልተሰማቸው ከፍርድ ቤቱ እንዲወጣ ፈቀዱለት፡፡ በጣም የሚገርመው ልክ ከአንድ ጨርቅ ላይ ተቆርጦ የወጣ ብጣሽ ጨርቅ መጠኑ ይቀንሳል እንጂ አይነቱ እንደማይቀየረው ሁሉ እኔ ላይ ለመመስከር የመጡት ምስክሮች በሙሉ የተናገሩት፤ ፖሊሶቹ እንዲናገሩ የነገሯቸውን ነገር ብቻ ነበር፡፡ ያም የእኔ

እውነት ተዳፍና ቀርታ የእነሱ ውሸት እንዲገዝፍ እድሉን አመቻችቶላቸዋል፡፡ ምንም እንኳን ወሽመጤን በጥሰው እንዳልነሳ ለማድረግ ቢጥሩም እኔ ግን የቻልኩትን ያህል ለፍርድ ቤቱ መናገሬን አላቆምኩም ነበር፡፡

"የተከበሩ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ እዚህ ጋር እንዲታወቅልኝ የምፈልገው ነገር ቢኖር ሌፒቴት የሞተው እንደተጋነነው በተተኮሰበት ሦስት ጥይቶች ሳይሆን በአንድ ጥይት ነው፡፡ እንበልና ሌፒቴቲን የተኮስኩበት እኔ ነኝ ይባል... ሌፒቴት ከተተኮሰበት በኋላ ታክሲ ውስጥ ገብቶ ወደ ባለቤቱ እንዲሄድ ተደርጓል ተብሏል... ያ ማለት ተኳሹ ሌፒቴቲን መግደል አልፈለገም ማለት ነው፡፡ መግደል ቢፈልግማ ሦስት ወይም አራት ጥይት ያዘንብበት ነበር፡፡ ይሄ እንዲታሰብልኝ እፈልጋለሁ፤ ከዚህ በፊት ጠበቃዎቼ ከመቶ ጊዜ በላይ ይሆናል ምናልባት ሌፒቴቲን የገደልኩት እኔ ከሆንኩ እንዳምንና ይህም በዛ ከተባለ አምስት ዓመት ብቻ ሊያስቀጣኝ እንደሚችል ያስረዱኝ፡፡ ይህም አሁን ካለሁበት እድሜ አንፃር ሲታይ በጣም ትንሽ እንደሆነ ሁሉ ነግረውኛል፤ ነገር ግን ክቡር ፍርድ ቤት ባልሰራሁት ወንጀል አይደለም ለአምስት አመት ለደቂቃም መታሰር አልፈልግም ምክንያቱም እኔ ከወንጀሉ ነጻ የሆንኩ ሰው ነኝ" አልኩ በስሜት

ይህም ንግግሬ ፍርድ ቤቱ ላይ የሆነ ያክል ተፅዕኖ መፍጠሩን እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ ታዲያ ይህን ጊዜ ዓቃቤ ህጉ ለአስራ አምስት ወራት የለፋበት ጉዳይ ወደ መሽነፉ እያዘነበለ መምጣቱ ስለታወቀው ነው መሰለኝ ፍርድ ቤቱ ለእረፍት በተቋረጠበት ጊዜ ምንም እንኳን የመግባት መብት ባይኖረውም እኔ ለእረፍት ወደተቀመጥኩበት ክፍል ለመግባት ግን ምንም አላገደውም ነበር፡፡ በቀጥታ ወደ እኔ መጥቶም "ለምን ገዳዩ ኮርሲካዊው ሮጀር ነው አትልም?" አለኝ

እኔም ለመመለስ ጊዜ አልፈጀብኝም ነበር "ኮርሲካዊ ሮጀር የሚባል ሰው አላውቅማ" አልኩት ቆፍጠን ብዬ... ይሄ እርጉም አቃቤ ህግ ግን ከእኔ ወዲያው እንደተለየ ለዳኞቹ እና ለገምጋሚዎቹ የሌፒቴቲ ገዳይ ፓፒለን ሮጀር ቢሆንም ዜግነቱ ግን ኮርሲካዊ መሆኑን እንደነገርኩት አድርጎ ነገራቸው፡፡

በሚገርም ሁኔታ በዚህ ምክንያት ክሱ ለጊዜው ከተቋረጠ በኋላ እንደ አዲስ ገዳዩ ፓፒለን ሮጀር የተባለ ኮርሲካዊ ሊሆን ይችላል በሚል ተከፈተ...እኔም በነገሩ በጣም በሽቄ ስለነበር ሁኔታውን ለማስረዳት ማንንም ሳላስፈቅድ መናገር ጀመርኩ፡፡ "ክቡር ፍርድ ቤት... ለአስራ አምስት ወራት ይህ አቃቤ ህግ የሊፒቴት ገዳይ አንድ ፓፒለን ብቻ መኖሩ ሲያስረዳ ቆይቷል፡፡ እሱም እኔ እንደሆንኩ በተደጋጋሚ ሲናገር ሰምተነዋል፡፡ ለዚህም ማስረጃ እንዲሆነው የተለያዩ ምስክሮች እያመጣ ቃላቸውን ሲያሰማን ቆይቷል፡፡ ታዲያ ፖሊስ እኔ

ወንጀለኛ ለመሆኔ አስፈላጊውን መረጃ እስካገኝ ድረስ አሁን ሀሳብ መቀየሩ ለምን አስፈለገ? ይህ ታዲያ በአቃቤ ህግ ሚይዛውድ እና በመስሉቹ የተቀነባበረ ሴራ ለመሆኑ ግልጽ ማስረጃ አይደለም እና ይህ አቃቤ ህግ በፈጠረው ኮርሲካዊ ፓፒለን ሮጀር በድጋሚ ክሱን መጀመር አስፈላጊ ነው ትላላችሁ? ስለዚህ ክቡር ፍርድ ቤት ይህ ውሸት የሞላበትን ክስ መሆኑን ተረድቶ ሚዛናዊ የሆነ ፍርድ እንዲሰጠኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ" አልኩ

በእርግጥ ችሎቱን ለማሸነፍ በጣም ተቃርቤ ነበር. . ቢሆንም ግን አቃቤ ህጉ በፍፁም በቀላሉ እጅ እንደማይሰጥ አውቃለሁ፤ ችሎቱም ቢሆን ፍርድ ለመስጠት የሚያስችል ፍንጭ ስላላገኘ አሁንም በድጋሚ በቂ መረጃ ይሰባሰብ በሚል ጊዜ ቀጠሮ ሰጠ። ጋዜጦችም በመጀመሪያ ገፃቸው ላይ ስለ እኔ ክስ አንስተው 'እንዲህ አይነት መረጃ ያልተገኘለት ክስ ሲያጋጥም ብዙ ጊዜ አይስተዋልም' በሚል ርዕስ የእኔን ጉዳይ አትተዋል።

ችሎቱ በድጋሚ ሲሰየም ከበፊቱ የተለየ ምንም መረጃ በእኔ ላይ ሊያቀርቡ አልቻሉም ነበር፤ ይህ በምናባቸው የሳሉትም ኮርሲካዊው ፓፒለን ሊገኝ አለመቻሉ ነገሩን ውስብስብ አድርጎባቸዋል። ያም ቢሆን ግን ከእኔ በተሻለ መልኩ ከሳሾቼ ታማኝነት ስላላቸው፣ የፈለጉትን መረጃ እና የመሰላቸውን ነገር እያቀነባበሩ ፍርድ ቤቱ በእኔ ላይ ያላውን እምነት እንዲያጠፋ ማድረጋቸውን ግን መቋቋም አልቻልኩም ነበር፤ በቀጣዮቹ ሁለት የፍርድ ቤት ቀጠሮዬ ወቅት ከተወሰኑ ጊዜአቶች ውጪ እንዳወራ እድሉን አልሰጡኝም ነበር።

ፍርድ ቤት በቀረቡኩበት በአንዱ ወቅት  ሌፒቴቲን ወደ ሆስፒታል ይዞት የሄደው የታክሲ ሹፌር ተይዞ ቀርቦ ነበር! ይህ ሰው በእርግጥ ለእኔ ወሳኝ ምስክር ነበር። ወደእዚያ መጠጥ ቤት ከመሄዱ በፊትም የተኩስ ድምፅ መስማቱን ቃሉን ሰጥቷል፤ ታዲያ እነዚህ ምንም እፍረት የሚባል ነገር ያለፈጠረባቸው ፖሊሶቹም በሀሰት መስክረሃል በሚል እሱንም ከሰውታል።

አሁንም እዛው አግዳሚ ወንበር ላይ እንደተቀመጥኩ ብርዱ ሳይበግረኝ ስለክሴ ማሰቤን ተያይዠዋለሁ። ጠበቃዎቼ እኔን ለመታደግ የሚችሉትን በሙሉ አድርጋዋል በዛው ልክም አቃቤ ህጉና ፖሊሶቹም በፍፁም አልተኙልኝም ነበር።

ብዙ ቀናት ከፈጀ ዱላ ቀረሽ ክርክር በኋላም በመጨረሻም ጦርነቱ በእነሱ አሸናፊነት እንደሚጠናቀቅ ወደ ማመኑ እየተቃረብኩ ነበር። በመጨረሻው

ቀንም ዳኛው ፍርድ ቤቱ ለመጨረሻ ጊዜ መናገር የምፈልገው ነገር ካለ እንድናገር ፈቀደልኝ። እኔ ግን ምን ማለት እንዳለብኝ አላወቅሁም ነበር። ንዴቱም፣ እልሁም፣ ሀዘኑም ስለተደራረበብኝ "እኔ ከያመ ንፁህ ነኝ... በፖሊሶች በተቀነባበረ ሴራ ግን ወንጀለኛ ተብያለሁ " ከማለት ውጪ ሌላ ምንም ነገር አላልኩም ነበር፤ በፊት የነበረኝ ጥንካሬ አሁን ከእኔ እርቋል፤ ከእዚህ በኋላ እነሱን ላሳምን የምችልበት አቅሜ እንዳለ ተሟጦ አልቋል፤ ስለዚህ እየጠበኩ ያለሁት ዳኞቹ የሚወስኑትን ፍርድ ብቻ ነው!!

ዳኞቹም ለአንድ ሰዓት ያክል በሌላ ክፍል ውስጥ ተማክረው ከመጡ በኋላ ቦታ ቦታቸውን ያዙ... በመቀጠል የመሃል ዳኛው ከመቀመጫዬ እንድነሳ ጠየቁኝ... ይህን ቅፅበት ሳስታውስ ሳይታወቀኝ አሁን ከተቀመጥኩበት አግዳሚ ወንበር ላይ ተነስቼ ነበር። ዳኛው የሆነ ወረቀት ቢጫ ከሰነድ መያዣቸው ነጥለው ማንበብ ጀመሩ "ፍርድ ቤቱ በጥቅምት 1931 በዋለው ችሎት ተከሳሽ ፓፒለንን ወንጀለኛ ሆኖ መገኘቱ በሰነድ እና በሰዎች የምስክርነት ቃል ስለተረጋገጠ የእድሜ ልክ እስራት ፈርዶበታል! . . . ጥበቃ እባካችሁ ይዛችሁት ሂዱ" አሉ ዳኛው የሆነ ዱብ እዳ ከሰማይ የወረደብረኝ ያህል ነበር የተሰማኝ፤ ግን ምን ማድረግ እችላለሁ... ተሸንፌያለሁ!! በመጨረሻም እውነት ሳስታ ውሸት ድል አድርጋ እንዳሰቡት ዘብጥያ ሊወረውሩኝ ቻሉ!!

እኔም ይህን ጊዜ ነበር ከተቀመጥኩባት አግዳሚ ወንበር ላይ ሆኜ ከገባሁበት ሀሳብ የነቃሁት!! ከወንበሩ በመነሳት ቀስ ብዬ እየተራመድኩ ወደ መንገዱ ከወጣሁ በኋላ እዚህ ቦታ ላይ ብዙ መቆየቱ የውስጥ ህመሜን ስለሚያባብሰው በመንገዱ ያልፍ የነበረውን ታክሲ አስቁሜ ወደ ጌሪ ዱ ሊዮን እንዲወስደኝ አደረኩ። እዛ እንደደረስኩም ጊዜ ሳላጠፋ ወደ እህቶቼ ጋር የሚወስደኝን ባቡር ይዤ ጉዞ ጀመርኩ። ቤት እንደገባሁም እኔ በታሰርኩበት ጊዜ የወጡ ጋዜጦች በቤት ውስጥ ስላገኘሁ ምን እንደሚሉ ለማየት አንዱን አንስቼ ማገላበጥ ጀመርኩ። በአንዱ ጋዜጣ ላይ ስለእኔ ክስ አንስቶ እስከዛሬ ከተከናወኑ የፍረድ ቤት ክሶች ውስጥ የእኔን አጠራታሪ ክስ ብሎ ጋልጾታል። በአንደኛው ጋዜጣ ላይ ደግሞ 'ሄነሪ ሽሬሪ ወይም በቅፅል ስሙ ፓፒለን ተብሎ የሚጠራው ግለሰብ የእድሜ ልክ እስራት ተፈረደበት' ይላል።

ይህ ጎልድስቲን የሚባለው ሰው ለእነዚያ ፖሊሶች የዋለላቸው ውለታ እንዲህ በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም ያለእሱ እርዳታ ይህን ያህልም መግፋት ባልቻሉ ነበር። ከፍርዱ በኋላም የሰጠውን ቃል ሳይቀይር ለሚጠይቀው ሁሉ ተመሳሳይ ምላሽ እየሰጠ ለእነዚያ ዲቃላ ፖሊሶች ታማኝነቱን አሳይቷል።

ለአመታት ራሴን ስጠይቀው የነበረው ጥያቄ ቢኖር ለመስማት እንኳን የሚቀፉ ስንት ወንጀለኛ በሞላበት ሀገር ለምን እኔ ላይ እንዲህ እንደበረቱብኝ ነው። ከእሱ በተጨማሪም ምንም እንኳን ውሸት ቢሆንም ከራሳቸው አንደበት እንደተናገሩት ከሆነ ወንጀለኞችን እየሰለልኩ እንዲያዙ በማድረግ እንደምተባበራቸው ነው። ታዲያ ለምን እኔን ወህኒ ለመክተት እንዲህ እንደተጣደፉ እራሴን ስጠይቅ መልሱ... ለሌላ እንደዚሁ በስለላ ለሚረዳቸው ሰው እንደመሸፈኛ የተጠቀሙብኝ ያህል ይሰማኛል!

በቀጣዩ ቀን ወደ ሞንትማርትሪ ተመልሼ ወጣት እያለሁ የማውቃቸውን ቦታዎች ለመጎብኘት ዞር ዞር ማለት ጀመርኩ። በልጅነቴ የማስታውሳቸውን የሩ ቶሎዚ ሆቴል፣ የሩ ዱራንቲን ሆቴል እና የሩ ሌፒክ ሱቆችን ከመታደስ ውጪ እንደዛው በፊት እንደማውቃቸው ነበር ያገኘኋቸው፤ ውስጡን ለማየት ወደ ሩ ቶሎዚ ሆቴል ገባሁ። በፊት ወጣት እያለሁ በቦታው ትሰራ የነበረችው አጠር ብላ ወፈር የምትለዋ አስተናጋጅ አሁን ቀጠን ብላ ረዘም በምትል ሴት ተቀይሯል። ከዛ ውጪ ሁሉም ነገር ያው ነው ማለት ይቻላል።

በእርግጥ ደስ ያለኝ ነገር ቢኖር ድሮ የማውቃቸው ሞንትማርትሪ ውስጥ የሚገኙት አብዛኛው የንግድ ቤቶች ምንም ሳይቀየሩ በፊት እንደማውቃቸው ነበሩ፤ ይህም የበፊቱ የወጣትነት ጊዜዬን ያሳለፍኩባቸውን ቦታዎች እንዳስታውስ ስለረዳኝ ተደስቻለሁ!! ቤቶቹ ባይቀየሩም የሚሰጡት ግልጋሎታቸው ግን ተቀይሮ ነው የጠበቀኝ ለምሳሌ በፊት ወተት ማከፋፈያ የነበረው ሱቅ አሁን ልብስ ማጠቢያ ሆኗል፤ በፊት መጠጥ ቤት የነበረው ቤት አሁን መድሀኒት መሸጫ መደብር ሆኗል፤ በፊት የፍራፍሬ መሸጫ ሱቅ የነበረው አሁን የመኪና ማጠቢያ ሆኗል፤ ባጠቃላይ ከብዙ አመታት በኋላ የማውቃትን ሞንትማርተሪን ነው ያየሁት ማለት እችላለሁ"

ከሩ ቶሎዚ ሆቴል እስከ ሞሊን ዲ ላ ጋሌቴ መናፈሻ ድረስ የሚያስወርደውን ደረጃ አካባቢዬን እየቃኘው መውረድ ጀመርኩ። አስታውሳለሁ እዚህ ደረጃ ላይ አንድ አይኖቹ የደከሙ ሽማግሌ ሰው የደረጃውን እጀታ እይዛለሁ ብሎ ስለሳተው በአፍንጫው ሲደፋ ሮጬ ሄጄ ያነሳሁበትን ቀን ያስታውሰኛል። ሰውየውም "አንተ ጎልማሳ በእውነት አመሰግናለሁ። ምን አለ ሁሉም ወጣት እንዳንተ ቢሆን" ያሉኝ እስካሁን ድረስ አዕምሮዬ ውስጥ እንደተቀረፀ ነው።

አዎ!! ሞንትማርትሪን ሙሉ ለሙሉ ከእኔ አልወሰዱብኝም የወሰዱብኝ ሰዎቹን ብቻ ነው!! ያን ምሽት አቅራቢያዬ ወደነበረ ወደአንዱ መጠጥ ቤት ገብቼ በአይጫወ በጣም ገፍቷል ብዬ ወደ አሰብኩት አንዱ ሽማግሌ ጋር ሄጄ ቁጭ አልኩ፤ ይህንንም ያደረኩት ሆን ብዬ ነው። ምናልባት በፊት

የማውቃቸውን ሰዎች ካስታወሰኝ ብዬ ነው፡፡ መጠጥ አዝዤ ከሰውየው አጠገብ ቁጭ ካልኩ በኋላ በቀጥታ ወደ ሰውየው ዞሬ ወሬ ለመጀመር ያህል

"ሰላም ነው ጌታዬ" አልኩ

"ሰላም ነው" አለኝ በመደነቅ ስሜት እያየኝ እንደማያውቀኝ እርግጠኛ ስለሆነ

"ከሞንትማንትሪ ከወጣው በጣም ቆይቻለሁ… ምን አልባት ሰው ካስታወሱኝ ብዬ ልጠይቅህ ነበር"

"ጠይቀኝ ካወቅሁት ለመንገር ምን ገዶኝ"

"እከሌን ታውቀዋለህ?"

"አዎ"

"የት ላገኘው እችላለሁ?"

"እዚህ ሀገር የለም"

"እከሌንስ?"

"አውቀዋለሁ"

"እሱንስ የት አገኘዋለሁ?"

"ሞቷል"

"እሺ እከሌስ?"

"አላውቀውም ግን ብዙ ጥያቄ መጠየቅ ትወዳለህ… ቆይ አንተ ማነህ" አለኝ ያ በእድሜ የገፋው ሰውዬ መጠጥ ቤቱ ውስጥ ያለው ሰው ሁሉ እንዲሰማው ድምፁን ከፍ አድርጎ

"ስሜ ሄነሪ ይባላል… ከአቢግኖን ነው የመጣሁት እንደነገርኩህ ለረዥም ጊዜም እዚህ ሀገር ስላልነበርኩ ነው ያላስታዋሳችሁኝ" ብዬ ሁሉንም ተሰናብቼ ቶሎ ብዬ ከመጠጥ ቤቱ ወጣሁ

በቀጣዩ ቀን ፓሪስን እያየኋት ዋልኩ. . .እቺን ውብ ከተማ ላያት በእርግጥ ታስደምማለች!! እኔም እዛው ፓሪስ ውስጥ ወደሚገኘው 'ላ ኮፖል' ምግብ ቤት ገብቼ የምፈልገውን አዝዤ ከተመገብኩ በኋላ አስተናጋጁን ጠራሁት

"አሁንም ከላይ ባሉት ክፍሎች ውስጥ የቦውሊንግ ጨዋታ ታጫውታላችሁ እንዴ?" ብዬ ጠየኩት

"እሲቃዬ በቦታው ለሃያ አምስት አመት የሰራው ሰው ነኝ... ቢሆንም ግን እዚህ ከመጣሁበት ጊዜ አንስቶ እስከዛሬ ድረስ ቦውሊንግ ጨዋታ እዚህ ቤት ውስጥ ተካሂዶ አያውቅም"

"እሺ... ይቅርታ እኔ ቤቱን አንተ ካልከው አመት በፊት ስለማውቀው ነው የጠየኩት" አልኩት

እኔም እዛው ምግብ ቤት ውስጥ ቁጭ ብዬ የፓሪስን ምርጥ ወይን እየጠጣሁ በፓሪስ አውራ ጎዳናዎች ላይ ውር ወር የሚሉትን መኪኖች እየተመለከትኩ ደስ የሚል ጊዜ አሳለፍኩ። እይታው ሲሰለቸኝም ቦታ ለመቀየር ስላሰብኩ ከምግብ ቤቱ ለመውጣት ከወንበሬ ተነስቼ የተወሰኑ እርምጃዎችን እንደተራመድኩ ነበር አስተናጋጁ እየተክለፈለፈ ወደእኔ መጥቶ "ሂሳብ አልከፈልክም. . .ሳትከፍል ለመሄድ አስበህ ከሆነ አሁኑኑ ፖሊስ ነው ይዤ የምመጣው"ብሎ የደነፋብኝ። በእርግጥ ሂሳቡን ላለመክፈል አስቤ አልነበረም ለመውጣት ያሰብኩት ነገር ግን ውስጤ በተለያዩ ሃሰቦች ተወጥሮ ስለነበር ስለ ሂሳቡ አላሰብኩም ነበር። እኔም ሂሳቡን ከከፈልኩ በኋላ ከእሱ በተጨማሪ ደግሞ የተወሰኑ ዝርዝር ሳንቲሞች እየሰጠሁት "ይሄን ደግሞ ለሚስትህ እናት ስጥልኝ... ከእኔ የበለጠ ለእሳቸው ሳያስፈግ አይቀርም!" ብዬ ስላናደድኩት የሰጠሁትን ሳንቲም እላዬ ላይ በትኖት ሄደ።


ፓሪስ ውስጥ በጣም ደስ የሚል ጊዜ ነበር ያሳለፍኩት በፊት ወደ ማውቃቸው ቦታዎች እየሄድኩ የድሮ ትውስታዎቼን ለማደስ ሞከርኩ። ፓሪስ ውስጥ ለስምንት ቀናቶች ስቆይ ስምንት ጊዜም ለእኔ መታሰር ምክንያት ወደሆነው ወያዚያ የግድያ ወንጀል ተፈጽሞበታል ወደተባለው ቦታ ሄጃለሁ!! ስምንት ጊዜም እዛች አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀምጨ ስለክሴ አስቤአለሁ!! ለስምንት ጊዜያቶች እዛችው ወንበሬ ላይ ቁጭ ብዬ እነዚያን እኔን ዘብጥያ ለማረድ የሚፈጉትን ፖሊሶች በምናቤ አይቻለሁ!! ስምንት ጊዜ ይህ ቦታ ለአስራ አራት ዓመት እንድታሰር ምክንያት ለሆነው ወንጀል ጅማሮ ነው ብዬ ለራሴ አውርቼበታለሁ!! ስምንት ጊዜ ለብዙ ዓመታት የወጠንኩትን በቀሌን እንደተውኩት ነገር ግን በደሌን በፍፁም መርሳት እንደማልችል ለራሴ ቃል ገብቼበታለሁ!! ስምንት ጊዜም ፈጣሪዬን በእኔ ላይ የደረሰውን ዱብ እዳ እና

እንግልት ማንም ላይ እንዳይደርስ ፀልያለሁ። ምክንያቱም ሰው ሆኖ ተፈጥሮ ማንነትን አጥቶ መኖር ከባድ ነው፤ ማንም ሰው መኖር በሚጀምርበት ሰዓት ላይ እሱነቱን ሲነጠቅ ቁስሉ ለዘላለም ከአዕምሮ አይወጣም! እኔ ቤተሰብ አለኝ፣ ነገር ግን ሀሰተኛ ፍርድ ከቤተሰቤ አግልሎ አኑሮኛል! ለመኖር መሮጥ በምፈልግበት ሰዓት በጨለማ አስረው አሰቃይተውኛል። ይህ የእኔ ብቻ የህይወት ውጣ ውረድ አይደለም፤ ብዙዎች በእኔ መንገድ አልፈዋል፤ በሀሰተኛ አስመሳዎች እውነታቸው ተቀብሯል። ግን በህይወት እስከኖርክ ድረስ አንድ ትልቅ ተስፋ አለህ... ወድቆ መነሳት!!

ዛሬ ላይ እኔ እዚህ ቦታ ላይ ተገኝቻለሁ፤ ስለዚህ በስተመጨረሻ አሸናፊ መሆኔን አውቄያለሁ!!ጠላቶቼ ሞቴን ቢመኙም እኔ ግን እስካሁኗ ሰዓት ድረስ ኖርያለሁ!! ከእዚህ በኋላም ፈጣሪዬ እስከፈቀደልኝ ጊዜ ድረስ እኖራለሁ!! በዚህ ሰዓት ህይወቴን ያመሰቃቀሉትን አነዚያን ሰዎች የት እንዳሉ ማወቅ አልፈልግም!! ምክንያቱም ያ ያለፈ የህይወት ታሪኬ ውስጥ የነበሩ ሰዎች ናቸው። ዋናው ነገር እኔ ቃሌን ጠብቄ እዚህ ቦታ ላይ ተገኝቻለሁ፤ ያልፈፀምኩት ነገር ቢኖር ብቀላዬን ነው። ለእሱ ደግሞ ፈጣሪ እራሱ ፍርዱን ይሰጣል!! እኔ ዛሬ ድረስ አለሁ፤ ምን አልባትም የእኔ በዳዬዎች በስብሰው ወደ አፈርነት ተቀይረው ይሆናል፤ ስለዚህ በየትኛውም ውጣ ውረድ ውስጥ እንኳን ብታልፍ መኖርህ በራሱ ፈጣሪህን ለማመስገን በቂ ነው!!

# `` ተፈፀመ ``

# ማጠቃለያ



ሄነሪ ሽሪያ ተወልዶ ያደገው ፈረንሳይ 'አርዲቼ' ተብሎ በሚጠራ ቦታ ሲሆን ለቤተሰቦቹ ብቸኛ ወንድ ልጅ ነው፡፡ከእሱ በተጨማሪ ቤተሰቦቹ ሁለት ሴት ልጆች ያላቸው ሲሆን ሁለቱም የእሱ ታላላቆች ናቸው፡፡ እናቱን በሞት የተነጠቀው ገና የአስር አመት ህፃን ልጅ እያለ ስለነበር የእናትን ፍቅር ያን ያህል ሳያጣጥም ነው ያደገው፡፡ በ1923 ዓ.ም የአስራ ሰባት አመት ልጅ እያለ የሀገሪቷን የጦር ሰራዊት ተቀላቅሏል፤ ለሁለት ዓመታት ካገለገለ በኋላ ከጦር ሰራዊት ለቆ ከወጣ በኃላ ነበር የተለያዩ የወንጀል ስራዎች ላይ መሳተፍ የጀመረው፡፡ብዙም ሳይቆይ ደግሞ ሚስት አግብቶ ሴት ልጅ ወልዶ ለመሳምም በቅቷል ፡፡

" ፓፒሎን " በሚለው የመጀመርያ መፀሀፉ ምንም እንኳን ሄነሪ ወንጀሉን አዳልፈፀመ የእምነት ክህደት ቃሉን ቢሰጥም ፍርድ ቤቱ ግን " ሮላንድ ሌፒቴት የተባለውን ግለሰብ ገድለሀል " በሚል የእድሜ ልክ እስራት ከአስር አመት የከባድ ጉልበት ስራ ጋር እንዲታሰር ፈርዶበታል፡፡ ከዛ በፊት ግን በታህሳስ 22/1931 በፈረንሳይ ውስጥ ካሉ ክልሎች የአንዱን ክልል ከንቲባ ልጅ የሆነችውን ጆርጂቴ ፎረል የተባለች ሴት አግብቶ ነበር፡፡ ከእዚች ሴት ጋርም ፍቺውን የፈፀመውም ብዙ እንግልት እና ስቃይን አልፎ ዳግም

ወደፈረንሳይ ሲገባ ነው፡፡ በ1931 ዓ.ም የተጋቡት እነዚህ ጥንዶች ከሰላሳ ዘጠኝ ዓመት በኋላ በሀምሌ 8 1970 ፓሪስ ውስጥ በሚገኘው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊፋቱ ችለዋል፡፡

ሄነሪ ወንጀለኛ ተብሎ ከተፈረደበት በኋላ በ1933 ወደ 'ቅዱስ ላውረን ዱ ማሮኒ' እስር ቤት እንዲሄድ ተደርጓል፡፡ 'ፓፒለን ' በተሰኘው መፅሀፉ ላይ እንደገለፀው የመጀመሪያ የማምለጥ ሙከራውን ያደረገው በህዳር 28 1933 ከጓደኞቹ ከማቹሬቴ እና ከክላውሲዎት ጋር በመሆን ሲሆን ከሰላሳ ስባት ቀን በኋላ ግን ያሰቡት ሳይሳካ በኮሎምቢያ ፖሊሶች ተይዘው በድጋሚ ለእስር በቅተዋል፡፡ መታሰሩ አልዋጥልህ ያለው ሄነሪ በድጋሚ ያደረገው የማምለጥ ሙከራ ተሳክቶለት ከጉጂራ ጎሳዎች ጋር ለተወሰኑ ወራቶች አሳልፏል፡፡ ምንም እንኳን ከእነዚህ ጎሳዎች ጋር ያሳለፈው የወዳጅነት መንፈስ ረዘም ላለ ጊዜ እንዲቆይ ቢያስገድደውም አእምሮው በሚያስባቸው ሀሳቦች ሊረጋለት ስላልቻለ እነዚያን ጎሳዎች ተሰናብቶ መሄድን መርጧል ፡፡

የጉጅራን ማህበረሰብን ለቆ እንደወጣም በፖሊሶች በድጋሚ ተይዞ ወደ ፈረንሳይ ጊዬና እንዲመለስ ተደርጎ ሁለት አመት የብቸኝነት እስርን ቀምሷል፡፡ ከእነዚያ አስቀያሚ የሁለት አመት የብቸኝነት እስር ከተላቀቀ በኃላም ለተጨማሪ ሰባት አመት በእስር አሳልፏል፤ ነፃነቱን ለማግኘት እንቅልፍ የማይተኛው ሄነሪ በእነዚህ የእስር አመታትም ለብዙ ጊዜ ለማምለጥ ሞክሮ ሊሳካለት ግን እንዳልቻለ ገልጿል፡፡ ቀጥሎም ወደ ሰይጣን ደሴት እደተዛወረ ና እዛም እንደዚሁ የማምለጥ ሙከራ እንዳደረገ ፅፏል፡፡

በመጨረሻም በ1941 ዓ.ም የኮኮናት ፍሬዎችን በመጠቀም ከአንዱ ጓደኛው ጋር በተሳካ ሁኔታ ለማምለጥ ቢችሉም የፈረንሳይ ጊዬና ዳርቻ አካባቢ ሊደርሱ ሲሉ ግን ጓደኛው የአሸዋ ማጥ ውስጥ ተዘፍቆ ሊሞት ችሏል፡፡ጓደኛውን በአሸዋ ማጥ የተነጠቀው ፓፒለን የፈረንሳይ ጊዮናን በአሸዋ የተሞላ ደለል በተሳካ ሁኔታ አልፎ ማምለጥ ከሚፈልግ አንድ ቻይናዊ ጋር ስለተገናኘ ከእሱ ጋር በመሆን አንድ ጀልባ በመግዛት ወደ ብሪቴን ጊዮና ለመሄድ ሞክረው ነበር፡፡ እንደዚሁ ለአንድ አመት ያህል ከአንዱ ቦታ ወደ አንዱ ቦታ ሲዘዋወሩ ከቆዩ በኋላ ቻይናዊውን ትቶ ከሌሎች ማምለጥ ከሚፈልጉ ወንጀለኞች ጋር በመሆን በሌላ ጀልባ ወደ ብሪቲሽ ሆንዱራስ ለመሄድ ይሞክራሉ፤ ሆኖም ግን እንዳሰቡት ሳይሆን ቀርቶ ለመድረስ የቻሉት

ቬንዙዌላ ነበር። ቬንዙዌላ እንደደረሱም በፖሊሶች ተይዘው ኢልዶራዶ ውስጥ ወደሚገኝ እስር ቤት ተልከዋል። ከአንድ አመት እስራት በኋላም በጥቅምት 3/ 1944 ዓ.ም ማንነቱን ከሚገልፅ ሰነድ ጋር ከእስር ሊለቁት ችለዋል፤ ከዛም በኋላ የሄንሪ ኑሮ ከቬንዙዌላ ውጪ ስላልነበር ከአምስት አመታት ቆይታ በኋላም የቬንዙዌላውያን ዜግነት ሊሰጠው ችሏል። ቬንዙዌላ ውስጥ ኑሮን ለማሸነፍ ከእዛ . . . ወደ እዚህ በሚኳትንበት ወቅት ማራካይቦ ውስጥ ሪታ ቤንሲሞን የተባለችውን ሴት አግኝቶ፤ ከእሷ ጋር ትዳር መስርቶ መኖር ጀምሯል። ሪታን ካገባ በኋላም ህይወቱ ተቀይሮ ካራካስ እና ማራካይቦ ውስጥም ዝነኛ የሚባሉ ምግብ ቤቶችን ለመክፈት ችሎ ነበር። በመጨረሻም ወደ ፈረንሳይ መግባት የሚችልበት እድል ስለተመቻቸለት ወደ ትውልድ ቀየው ተመልሶ ከቤተሰቦቹ ጋር ለመገናኘትም ችሏል።

ፓፒለን የተሰኘው መፅሐፉም ለመጀምሪያ ጊዜ የታተመው እ.አ.ኤ በ1970 ዓ.ም በለንደን ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ እንግሊዝኛ የተረጎመውም 'ፓትሪክ ኦ ብሬን' ተብሎ በሚጠራ የረዥም ልቦለዶች ደራሲ ነው። 'ባንኮ' በተሰኘው ሁለተኛ መፅሀፉ ደግሞ ከእስር ከተለቀቀ በኃላ በኑሮ ውስጥ ያሳለፈውን ውጣ ውረድ መሳጭ በሆነ መልኩ እንዲህ ተርኮታል።

የብዙ መከራና ስቃይ ገፈት ቀማሽ የሆነው ፓፒለን!!. . .አስቸጋሪ እና ለማመን የሚከብዱ ጀብዱዎችን የፈፀመው ፓፒለን!!. . . ለአመታት በወህኒ ቤቶች የተንገላታው ፓፒለን!!. . . በአጠቃላይ ለውድቀት እጅ የማይሰጠው ይህ ሰው ሀምሌ 29 1973 በተወለደ በስልሳ ስድስት አመቱ በጉሮሮ ካንሰር ምክንያት ከዚህ አለም በሞት ሊለይ ችሏል።


"ተነስ ቶሎ!... ሸጉጥህን... እና መብራትህን ያዝ ወደ መጠጥ ቤቱ መሄድ አለብን ችግር ተፈጥሯል! አልኩት በሩጫው ምክንያት ትንፋሼ እየተቆራረጠ... ወዲያው ቡም!... ቡም! ሁለት ጊዜ የተተኮሰ የሽጉጥ ተኩስ ሰማን... ወዲያው የሚግዌልን መልስ ሳልጠብቅ ነበር ወደ መጠጥ ቤቱ መሮጥ የጀመርኩ... ወደ መጠጥ ቤቱ ስገባም ቤቱ ጨልሞ በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ብቻ የእጅ መብራት ይዘው ውር ውር ሲሉ ተመለከትኩ ። እኛ ወደተቀመጥንበት ቦታ ስሄድ ግን ማንነቱን ከጊዜው ያላወቅሁት አንድ ሰው መሬት ላይ በጀርባው መንጋለሉን አስተዋልኩ


* * * * # # # * * * *


ዛሬ ላይ እኔ እዚህ ቦታ ላይ ተገኝቻለሁ ፤ ስለዚህ በስተመጨረሻ አሸናፊ መሆኔን አውቄያለሁ!! ጠላቶቼ ሞቴን ቢመኙም እኔ ግን እስካሁኗ ሰዓት ድረስ ኖርያለሁ!! ከእዚህ በኋላም ፈጣሪዬ እስከፈቀደልኝ ጊዜ ድረስ እኖራለሁ!! በዚህ ሰዓት ህይወቴን ያመሰቃቀሉትን እነዚያን ሰዎች የት እንዳሉ ማወቅ አልፈልግም!! ምንያቱም ያ ያለፈ የህይወት ታሪኬ ውስጥ የነበሩ ሰዎች ናቸው ። ዋናው ነገር እኔ ቃሌን ጠብቄ እዚህ ቦታ ላይ ተገኝቻለሁ ፤ ያልፈፀምኩት ነገር ቢኖር ብቀላዬን ነው ። ለእሱ ደግሞ ፈጣሪ እራሱ ፍርዱን ይሰጣል!! እኔ ዛሬ ድረስ አለሁ ፤ ምን አልባትም የእኔ በዳዬዎች በስብሰው ወደ አፈርነት ተቀይረው ይሆናል ፤ ስለዚህ በየትኛውም ውጣ ውረድ ውስጥ እንኳን ብታልፍ መኖርህ በራሱ ፈጣሪህን ለማመስገን በቂ ነው!!

*ከመፅሀፉ የተወሰዱ*

"ዋናው ቁም ነገር በህይወት መቆየታችን ነው"
ሄንሪ ሽሪየ




JAFAR BOOKS
+251911125324
Tank Publishers

ዋጋ፡- 200.00 ብር
ሁለት መቶ ብር ብቻ፡፡